# መነሾ

በ1840 የታሪክ ጸሓፊው ቶማስ ካርላይል ይኸን ጻፈ፡-

> *በእነዚህ አስራ ሁለት ክፍለ ዘመናት እስልምና የሐይማኖት ብሎም የሰው ዘር ህይወት ሁለንተና መመሪያ ከመኾኑ ባላይ ከልብ የሚታመኑት ይማኖት ሆኗል። ሙስሊም አረቦች ሐይማኖታቸውን በጽኑ የሚታመኑና የሚኖሩ ናቸው። ከጥንት ጀምሮ የእንግሊዝ አጥባቂ ክርስቲያኖኑ ሳይቀር የሙስሊማኑን ያክል በእምነት፣ በመጋፈጥ እና በጽናት የጠነከረ የለም።*[1]

ዛሬም የእስልምና ተከታዮች በቁጥር ኾነ በእምነት ድካም አይታይባቸውም።

የሙስሊም እምነት የማይወርስ እስኪ መስል ክርስቲያኑ ሙስሊማኑን ወደ ክርስቶስ የመቀየሩ ኃላፊነት ተስፋ ሲቆርጡበት ይስተዋላል።

እግዚአብሔር ሙስሊማኑን እንዳገለግል ሲጠራኝ ተስፋዎቹ ታላቅ ማስጠንቀቂያዎቹ ደግሞ ግልጽ ነበሩ። «እኔ አድንህ ዘንድ ከአንተ ጋር ነኝና ከፊታቸው አትፍራ÷ በፊታቸው እንዳላስፈራህ አትፍራቸው» (ትንቢተ ኤርሚያስ 1÷8፣17) ። አያሌ ጊዜ «ጌታ ሆይ የእስልምናን ግንብ የምታፈርስው መቼ ነው» ብዬ ጠይቄአለሁ፤ ለደቀመዛሙርቱ የሰጠው ምላሽ ነበር መልሱ፡- «አብ በገዛ ሥልጣኑ ያደረገውን ወራትንና ዘመናትን ታውቁ ዘንድ ለእናንተ አልተሰጣችሁም፤ ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ÷ በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ» (ሐዋርያት ሥራ 1÷7፣8)።

የእስልምና ግንብ መሰነጣጠቁን አሁን እያየሁ ነው። እንደ ኤልያስ ወደ ጠራው ሰማይ አሻቅቤ «የሰው እጅ የምታህል ደመና » (መጽሐፈ ነገስት18÷44) እመለከታለሁ። ምኞቴም ሆነ ጸሎቴ መላው ክርስቲያኑ እንደ ኢያሱና ካሌብ የተስፋይቱን ምድር ራዕይ እንዲካፈል ነው። « በኃይል ከእኛ ይበረታሉና በዚህ ህዝብ ላይ መውጣት አንችልም» ሳይኾን «ማሸነፍ እንችላለንና እንውጣ ÷እንውረሰው » የሚል የካሌብና ኢያሱ አእምሮ ሊኖርን ግድ ይላል (ኦሪት ዘኍልቁ 13÷ 30) ።

---

[1]በግንቦት 8/ 1840 «የጀግኖች እና ጀግና አምልኮ » ትምህርት የተወሰደ ። የቶማስ ካርሊልን ታዋቂ ስራዎች ይመልከቱ፣ ( ኒዮርክ ዘ ቡክ ኦፍ አሜርካ ሊግ፣ የብሉ ሪኖን መጽሐፍ ፣ 1942)፣ገጽ 205።

እግዚአብሔር ቤተክርስቲያንን እየሞገተ ያለውም ይኼንኑን ነው። ይህ መጽሐፍ የተሰናዳው ክርስቲያኑ ስለ እስልምና የሚያነሱአቸውን አብይ ጥያቄዎች ለመመለስ ነው፡- የእስልምና እምነት ያገዘፈው ምንድነው? ሙስሊማኑ ክርስትናን የሚቃወሙት ለምንድ ነው? እውነተኛ ክርስቲያን የክርስቶስን ቤዛነትና አዳኝነት ማቅረብ የሚችለው እንዴት ነው?

***አብዱል ሀዲ!***

# 1

# ሙስሊማኑን በወንጌል መድረስ
# (የሥራው ባሕርይ)

በወርኀ ጥር 1፣ 1985 የሊብያው መሪ ኮሎኔል ሙአመር አል- ጋዳፊ የአዲሱን አመት መባቻ ምክንያት በማድረግ ለክርስቲያኑ አገራት መሪዎች ደብዳቤ ላኩ። ጽሑፉ አያሌ ሙስሊማኑ ክርስትናን ስለ ሚረዱበት መንገድ ብዙ የሚለው አለ፡-

*የ1984 ክርስቶስ ልደት አመት አልፎ እንኳን ለአዲሱ አመት አደረሳችሁ ፣ የፈጣሪ ሰላም ስለ እርሱ ምንም በማናውቀው ለመሐመድም በተገለጠው ላይ ይሁን። የኢየሱስና የእናቱ መርየም ሙሉ ታሪክ የነገረን መሐመድ ነው። እኛ ሙስሊማን ለመሐመድ በተገለጠው ቁርኣን፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ተአምራዊ ውልደትና ትንቢት እናምናለን። ይህ ታሪክ በቶራህ ወይም በመጽሐፍ ቅዱስ እንኳ ሳይቀር በግልጥ አልደረሰንም፣ ምክንያቱም አሁን የሚገኙት የብሉይና ሀዲስ ኪዳን መጻሕፍት በሐሰት ተመሳስለውና ተጣመው የተቀዱ በመሆናቸው ነው። የነብዩ መሐመድና መሰል ታሪኮች ኸን ተብለው እንዲጎድሉ ተደርጓል።*

*በእውነተኛው መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ ይቃወሙትና ይገድሉት ለፈለጉ እስራኤላውያን "የእስራኤል ልጆች ሆይ እኔ ከተውራት በፊቴ ያለውን የማረጋግጥና ከኔ በኋላ በሚመጣው መልዕክተኛ ስሙ አሕመድ በሆነው የማበስር ስሆን ወደ እናንተ (የተላክሁ) የአላህ መልዕክተኛ ነኝ "ሲል ተናግሯል (ሱረቱ 61፡6)።*

*በዚህ ቅዱስ ወቅት አዲሱ ትውልድ የክርስቲያኑን ዓለም ቁርአን በማንበብ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ /"ሰላም በእርሱ ላይ ይሁን"/ ፣ ስለ እናቱ መርየም እና ስለ ወንድሙ አሮን እውነተኛውን ያውቅ ዘንድ ጥሪ አደርጋለሁ። የኢየሱስን የምስራች ጅብሪል ወደ ድንግሊቱ መርየም መጥቶ ማብሰሩ እና በተለየ ቦታ መወለዱ ፣ አላህ ከሰማይ የምግብና ዘምባባ ዛፍ ማዘጋጀቱ፣ ሕዝቦችዋም እርሷን ማጥቃታቸው ከቁርኣን መማር ያስፈልጋል ። ኢየሱስ በሀጻንነቱ ሰዎችን በንግግር የሚያሳምን ታላቅ ነብይ እንደነበር፤ መሐመድ የተባለ ነብይ ከእርሱም በኋላ እንደሚመጣ፣ ሊገድሉት በሚፈልጉት እስራኤላውያን በመገለል ለመስቀል መሰጠቱ፤ በአላህ ወደ ገነት መወሰዱ፤ በአላህ አማካኝነት ለሙታን ህይወትን መስጠቱ፣ ብሎም ለምጻሞችንና ዲዳዎችን መፈወሱ ሁሉመረዳት ይቻላል።*

*እነዚህ ሁሉ ማብራሪያዎች በኢየሱስ ተአምራዊ ውልደት፣ ትንቢቶች፣ በዘመነ ጅማሬና ፍጻሜው፣ በእስራኤላውያን ጠላትነት፣ በደቀመዛሙርቱ መደገፉ  እንድናምን ያደርጉናል። ይህን የተማርነው ከቁርኣን ነው፤ ቁርኣንን የማታነቡበትም የማታምኑበትም ምክንያት በአረብ ህዝብ ላይ ጭፍን የብሔራዊ ስሜት ተቃውሞ ፣ የእስራኤላውያን ሐሰት ወሬ ማታለል ፣ እውነትን ከቁርኣን እንደዚሁም ስለ ኢየሱስ እና ሌሎች ነብያት ትርክት ከነገርን ከነብዩ መሐመድ  መረዳት  ስላ ልቻልን ነው።*

*ስለሆነም በክርስቲያኑ አለም የሚገኘው አዲስ ትውልድ የባህል አብዮት በማድረግ እየተዳካመ፣ እርስ በእርሱም እየተነጣጠለ ያለውን የክርስትና እምነት ለመለወጥ እንደ ሳቮናሮላ፣ ማርቲን ሉተር እና ካልቪን ይነሳ ዘንድ ጥሪዩ ነው። ሰላም በጻድቃኑ ሁሉ ላይ ይሁን!* [2]

በዚህ መረጃ መሰረት ሙስሊማኑ ስለ ክርስቲያኑ ያላቸው ግንዛቤ ፣ ክርስቲያኑ ሙስሊማኑን እንደሚረዱት አይነት ጥቂት እውቀት ነው። ሁለቱም ሀይማኖቶች ሌሎችን የሚደርሱ ናቸው፤ ክርስትና የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል በማወጅ ወንጌልን ያደርሳል፤ እስልምና ደግሞ በዳኹ (ጥሪ) ሁሉም የእስልምናን እምነት እንዲቀበሉ ያደረጋሉ። የዚህ መጽሐፍ ማጠቃለያ መልዕክት እንደሚከተለው ማስቀመጥ ይቻላል ፦ እግዚአብሔር የሙስሊሞኑን አለም በወንጌል ለመድረስ ሲጠራን፣ ስኬታማ በሆነ መንገድ የምንፈጽምበትን ኹሉ ይሰጠናል፤ እግዚአብሔር የማይቻለውን  እንድንሰራ አያዘንምና!

ሙሰሊማኑን የመድረስ ስራ ተግዳሮቶች ምንድናቸው ፤ አብዛኛው ክርስቲያኑ ተግዳሮቶችን በመጋፈጥ ስኬታማ መሆን ለምን ተሳነው ። ሁለት ተግባራዊ መንስኤዎችን ማስመር እወዳለሁ፦ የቤተክርስቲያን ድካም እና የእስልምና  እምቢተኝነት ።

## I. የቤተክርስቲያን ድካም

### 1.ታላቁ ተልዕኮን የመታዘዝ ክፍተት

ሙስሊማኑ በወንጌል የመድረስ እንቅፋት ከቤተክርስቲያን ጋር እጅጉን ይገናኛል። ደካማ እና ለብ ያለች ቤተክርስቲያን ሚሲዮናዊነትን የጣለች ናት። የሚከፋፈሉ አማኞች በአብዛኛው ለግጭት እንጂ ለምስክርነት ጊዜ የላቸውም፤ በዚህም አያሌ ጉባኤዎች ራስ -ተኮር ሆነዋል።

[2] ታይመስ ኦፍ ኢንድያ የተወሰደ፣ ጥር 2/1985።

የጠፉትን በወንጌል ለመድረስ ከመጋፈጥ ይልቅ በውስጣዊ  የህብረት ሙቀት ላይ ብቻ በማተኮራቸው ከዓለም እንዲነጠሉ እና ኃጢያተኞችን እንዲያገሉ አድርጓቸዋል። በመንፈስ የሚሞሉ እና መንፈስን የሚታዘዙ አማኞች  ግን የእግዚአብሔርን ማዳን ኃይል በመመስከር ሰዎች ክርስቶስን በማወቅ የግል አዳኛቸው አድርገው እንዲቀበሉ የሚተጉ ናቸው።

## 2. የክርስትናን እምነት የመታመን እጦት

ክርስቲያኖኑ በቁጥር አናሳ በሆኑባቸው አገራት በራሳቸው ኾነ በእምነታቸው የመታመን ክፍተት ይታያል። ብዙዎች ከከነዓን ወደ ሙሴ መጥተው፣ የተስፋይቱን ምድር መውረስ እንደማይቻል እንደተነናገሩት አስር ሰላዮች አእምሮ ነው የሚመላለሱት (ኦሪት ዘኁልቁ 13፥28-33)። ይህ ሁኔታ በሙስሊም አገራት በሰባተኛው ክፍለ ዘመን ከኦማር ኪዳን ጋር በቀጥታ ይገናኛል። የኪዳኑ ዐብይ ዓላማ ሙስሊም ያልሆኑ ክርስቲያኖኑ እና አይሁዳውያኑ ህይወታቸው ኾነ ንብረታቸውን መከላከል ነው። ይህ ተፈጻሚ የሚሆነው በተወሰኑ ቅድመ -ሁኔታዎች ነው። የመጀመሪያው ክርስቲያኑ ሙስሊም መሆን በሚፈልግ ክርስቲያን ፊት ምንም አይነት እንቅፋት ማኖር እንደማይችሉ ይናገራል ። ክርስቲያኖኑ በምንም መልኩ ሙስሊማኑን ወደ ክርስትና መቀየር አይፈቀድላቸውም የሚለው ደግሞ ሁለተኛው ነው።

ከሊፋ ኦማር ኢብኑ አል-ካጣብ ድል የነሳቸውን ለማባበል ይህን ኪዳን  በሚኖሩበት ግዛት በማቅረብ ስምምነቱን እንዲፈርሙ ያደርግ ነበር። ከስምምነቱ አንቀጽ መካካል አንዱ የሚከተለው ነበር ፦

*በአላህ ስም ርኅሩኅ፣ አዛኝ በሆነው።*

*በእኛ አገር ስትደርሱ ህይወታችንን፣ ቤተሰቦቻችንን በእምነት ወንድሞቻችንን ሁሉ እንድትጠብቁ እንጠይቃለን። ንብረቶቻችንን እንድትጠብቁ፣ ቤተክርስቲያንም ኾነ ገዳማት እንዳትሰሩ፣ ሙስሊማኑ በሚኖሩበት ሁሉ እንዳታድሱ ጭምር  እናስጠነቅቃለን። እኛም ክርስቲያኑ በቤተክርስቲያናንም ኾነ በገዳማት ማንኛውም ሰላይ ወይም የውጭ መልዕክተኛ አንሰውርም፤ የሙስሊማኑ ሁለንተናዊ ደኅንነት የሚጎዳ መረጃ አንደብቅም። ሀይማኖታዊ አገልግሎትና ሰበከት ከደጃችን ውጪ እንደማናደርግ ቃል እንገባለን። በሀይማኖታዊ ህብረታችን  መካከል እስልምናን በፍቃዱ ሊከተል የሚፈልግን ሰው አንከለክልም። ሙስሊማኑን በመልካም ሁኔታ ማስተናገድ፣ ሲቀመጡም ቆም ብሎ ማክበር ኃላፊነታችን ይሆናል። የአልኮል መጠጦችን  አንገበያይም፤ እስልምና ባለበት ሥፍራ ሁሉ መጻሕፍቶቻችንም ኾነ የመስቀል  ምልክቶችን እንደማናሳይ ቃል  እንገባለን።*

የስምምነቱ ቃል ከዘመናት በኃላ እንኳ ሳይቀር በእስልምና አገራት በሚኖሩ የክርስቲያንና ሙስሊም ማህበረሰብ መካከል ተገልጦ ይታያል ። አል-አላም የተባለው ዕለታዊ ጋዜጣ የሞሮኮ ዳግማዊ ንጉስና ኢማም ሀሰን በግንቦት 15፣ 1990 ላይ በሰብዐዊ መብቶች ኮሚሽን ፊት የሚከተለውን ተናግረው እንደነበር ዘግቧል፡- " አንድ ሙስሊም ' እኔ ከእስልምና ሐይማኖት ውጪ መከተል እፈልጋለው ቢል' ንስሐ እንዲገባ ከመደረጉ በፊት በህክምና ባለሙያዎች አእምሮው ጤነኛ መሆኑ መረጋገጥ አለበት። ጤነኛ ሆኖ የንስሐውን ዕድል ባይጠቀም፣ በዚህም ከአላህ ውጪ የሆነውን ሀይማኖት መከተል ቢወስን፤ ይህ እስልምና ባለመሆኑ ይፈረድበታል።" በሙስሊም አገራት የሚኖሩ ጥቂት ክርስቲያኖች የሚጠበቅባቸውን ማስተዋል ይኖርባቸዋል ። የምድር ጨው፣ የዓለም ብርሃንና እርሾ ኾነው በበጎ ተጽዕኖ ፈጣሪነት መገለጥ ይኖርባቸዋል (ማቴዎስ ወንጌል 5፥ 13፣ 14፣ 13፥ 33)።

## 3. ሙስሊማኑን የመውደድ ችግር

ከአያሌ የጦርነትና ስደት ዓመታት በኃላ ክርስቲያኑ እግዚአብሔር ሙስሊማኑን እንደሚወድ፣ ክርስቶስም እንደሞተላቸው ማስተዋል ችለዋል። ክርስቲያኑ የሚቃወማቸውን ለመውድድ የመንፈስ ቅዱስ አዲስ ሙላት ያስፈልጋቸዋል (ማቴዎስ 5፥ 43-48)። የፍቅር ታላቁ መገለጫ የኾነው የኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝነት ምስራች ለሌሎች ማካፈል ነው።

## 4. የአስተምህሮ ዕውቀት ዝንፈት

በአብዛኛው ክርስቲያኖኑ ለማያምኑ ሰዎች እምነታቸውን መግለጽ ያዳግታቸዋል። የክርስቶሰን አዳኝነት ተቀብለዋል፣ ነገር ግን መሰረታዊ የእምነት አስተምህሮችን መከላከል አይችሉም። ሐዋሪያው ጴጥሮስ በእኛ ዘንድ ስላለ ተስፋ ምክንያት ለሚጠይቁን ሁሉ መልስ ለመስጠት ዘወትር የተዘጋጀን መሆን እንዳለብን ይናገራል (የመጀመሪያው ጴጥሮስ መልዕክት 3፥15)። ሆኖም አያሌ ክርስቲያኖኑ የሙስሊማኑን ጥያቄም ኾነ ሙስሊማኑ በክርስትና አስተምህሮ ላይ የሚያነሱትን ሙግት መመከት ይሳናቸዋል፤ የሙስሊማኑን ቃላት እንኳ ሳይቀር በቅጡ የሚረዱ አይደሉም። ለአብነት፡- መንፈስ ቅዱስን ሙስሊማኑ ጅብሪል (ገብሬኤል) ብለው እንደሚጠሩት የሚያውቁት ምን ያህሉ ይኾኑ?

## 5. እግዚአብሔርን የመታመን ክፍተት

በርካታ ክርስቲያኑ እግዚአብሔር ሙስሊማኑን እንደሚያድን አያምኑም። በሙስሊም አገራት የሚገኙ ክርስቲያን አገልጋዮች አንድ ሙስሊም ወደ ክርስቶስ ሲመጣ ላይ መለከቱ፣ በአንጻሩ

በመቶዎች የሚቆጠሩ ክርስቲያኖች ወደ እስልምና ሲቀየሩ ሊያዩ ይችላሉ፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ በሰማይና በምድር ሙሉ ስልጣን አለው ፤ ይህ እውነት ወንጌልን ከሚያደርስ ክርስቲያን እይታ ላፍታ መደበዝዝ የለበትም (ማቴዎስ ወንጌል 28፡18)፡፡

## 6. በሙስሊም አገራት የደኅንነት ስጋት

ክርስቲያኖኑ ስደትን ከመፍራት የተነሳ ለሙስሊማኑ መመስከርን ያቆማሉ፡፡ ክርስትናን እንዲነግሩአቸው የሚጠይቋቸው ሙስሊማኑ ቢኖሩ እንኳ አብዛኛዎቹ የፖሊስ ወይም አክራሪ ሙስሊም ቡድኖች ሰላዮች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ አዳዲስ ሰዎችን ለመቀበል ፍቃደኛ አለመሆን፣ የቤተሰብና ጓደኛ ተጽዕኖ ብዙዎችን ወደ ነበሩበት እስልምና እንዲመለሱ ያደርጋል፡፡ በዚህ ጊዜ ተመላሾቹ ለባለስልጣናት ሳይቀር የክርስትናን እንቅስቃሴ ማሳበቃቸው አይቀሬ ይሆናል፡፡

# II. የእስልምና ዕምቢተኝነት

## 1. ሙስሊማኑ በአመዛኙ በእምነታቸው የረኩ ናቸው፡፡

ለሙሴ የኾነው የአምላክ መገለጥ አይሁዳውያኑ እንዳላቸው፣ ክርስቲያኖኑ ለሙሴና ለኢየሱስ የኾነው መገለጥ እንደሆነላቸው ሁሉ አንድ ሙስሊም ለሙሴ፣ ለኢየሱስና ለሙሐመድ የተገለጠው የእርሱ እንደኾነ ያምናል፡፡

በሌላ አገላለጽ አንድ ሙስሊም የመጨረሻና እውነተኛ መገለጥ እንዳለው ነው የሚያምነው፡፡ ለእርሱ ሙሐመድ "የትንቢቶች ወይም የነብያት መደምደሚያ" ነው (ሱረቱ 33፥40)፡፡ በዚህ የተነሳ አንድ ሙስሊም፡- "ኢየሱስ ከታላላቅ ነብያቶቻችን አንዱ እንደሆነ እናማናለን፤ እናንተ ግን መሐመድን ከነብያቶቻችሁ መካከል የማትቀበሉት ለምንድ ነው?" የሚለውን ምክንያታዊ ጥያቄ ሊያነሳ ይችላል፡፡ ኢየሱስና መሐመድ አንድ ሊሆኑ አይችሉም! ሙስሊማኑ ስለ ራሳቸው ያላቸው ሙግት እርስ በእርሱ ይጣረሳል፡፡ ክርስቲያኖኑ መሐመድ እውነተኛ ነብይ አድርገው እንዲቀበሉ ብቻ ሳይኾን፣ እርሱ የመጨረሻ ነብይ ነው የሚለውን አሳብ ጭምር እንዲደግፉ ይገደዳሉ፡፡ ሙስሊማኑ "በየጊዜው የሚነሳ የሀይማኖት መሪ ሁሉ በምን መመዘኛ ነው እውነተኛና ታላቅ ተደርጎ የሚወሰደው?" የሚለውን ጥያቄ ማንሳት ያስፈልጋል፡፡ በቅርብ የተነሳ ታላቅ ፈላስፋ (ብዙዎች በየጊዜው መነሳታቸው ጥርጥር የለውም) የግድ የእውቀት ወይም የአእምሮ ሰው መሆን አይጠበቅበትም፡፡ በዘመናችን የትኛው አርቲስት ነው ከተሐድሶ ሰዎች አእምሮ እኩል

የሚወዳደረው? የትኛው የሃያኛው ክፍለ ዘመን ሙዚቃ አቀናባሪ ነው ከቤትሆቨን ወይም ሞዛርት ጋር የሚተካከለው? ኢየሱስ ክርስቶስ ታላቅ ነብይ ብቻ አልነበረም፤ እርሱ መጀመሪያና መጨረሻ ነው (ዮሐንስ ራዕይ 1፥8)።

የመጽሐፍ ቅዱስን ክፍል በማጣቀስ ሙስሊማኑ በወንጌል መድረስ ጥቅሙ እምብዛም ውስን ሊሆን ይችላል። አብዛኛው ሙስሊማኑ የሚያምኑት አሁን የምንጠቀምበት መጽሐፍ ቅዱስ ከዋናው ቅጂ የተጣረስ መሆኑን ነው። አይሁዳውያኑና ክርስቲያኑ መጽሐፍ ቅዱስን በመለወጣቸው ፣ ሙስሊማኑ የሻሩት መኾኑን ይገልጻሉ። ኢየሱስ ክርስቶስ ከስቅለት በፊት ወደ ሰማይ ሲወሰድ የወንጌላትን ዋና ቅጂ አብሮ ወስዶታል ብለውም ያምናሉ።

## 2. ሙስሊማኑ ያልተወሳሰበ እምነት አላቸው።

እስልምና የሀይማኖት ቅርጽ ቢኖረውም ኃይሉን ግን የካደ ነው። ሙስሊማኑ ዲን አል- ፋትራ "ተፈጥሮአዊ ሀይማኖት" ብለው ይጠሩታል፤ እርሱም፦ ጸሎት ፣ ጾም እና ምጽዋት መስጠትን ይጠይቃል። እስልምና በአለም ሀይማኖት እሳቤ ላይ የጨመረው አዲስ ነገር የለም፤ ቁርኣን በውስጡ ያሉ እውነቶች በጥንት ቅዱሳት መጻሕፍት ቀድመው የተገለጡ መኾናቸውን በግልጽ ይናገራል (ሱረቱ 41፥43፣87፥18፣19) ። አብዛኛው የእስልምና እምነት መግለጫ ቀለል ባለ መንገድ የተቀመጠ ነው።

ሙስሊም ለመሆን አንድ ሰው የሚከተለውን የቃል ምስክርነት በአረብኛ መግለጽ ይኖርበታል፦ "ላ ኢላሃ ኢላላ አላህ፣ መሐመድ ራሱል አላህ" ("አምላክ የለም ከአላህ በስተቀር፣ መሐመድ የአላህ መልዕክተኛ ነው")። በእስልምና አላህ "አንድ" ነው፣ "ሶስት በአንድ" አይደለም ። በፍትህ ረገድ እስልምና "አይንን በአይን" የሚለውን መርህ ሳያወላዳ ይተገብራል (ሱረቱ 5፥45)። ሙስሊማኑ ይህን ህግ ሌላውን ጉንጭህን አዙርለት ከሚለው የኢየሱስ ክርስቶስ የተራራ ስበከት ትምህርት በላይ ያጠበቁታል (ማቴዎስ ወንጌል 5፥39)።

እስልምና በገሃድ ከሴቶች ይልቅ ለወንዶች ያደላል። የሴቶችን ንብረት በማስተዳደር የኢኮኖሚውን ኃይል የሚይዙት ወንዶች ናቸው (ሱረቱ 4፥34) ። በእስልምና ህግ ወንዶች አራት ሴቶችን ማግባት፣ ሌሎችን ዕቁባቶች መያዝ እንደሚችሉ ይደነግጋል (ሱረቱ 4፥3)። ሰው ሚስቱን በማንኛውም ጊዜ መፍታት ይችላል። "ቢፈታትም ከዚህ በኃላ ሌላን ባል እስክታገባ ድረስ ለርሱ አልተፈቀደለትም። ቢፈታትም የአላህን ሕግጋት መጠበቃቸውን ቢያውቁ በመማለሳቸው በሁለቱም ኃጢአት የለባቸውም። ይህችም የአላህ ሕግጋት ናት ለሚያውቁ

ሕዝቦች ያብራራታል” (ሱረቱ 2፥227-230)። ሱረቱ 2፥223 ወንዶች ሚስቶቻቸውን በወደዱት መንገድ እንዲገናኙአቸው መብት ይሰጣል “ሴቶቻችሁ ለእናንተ እርሻ ናቸው። እርሻችሁንም በፈለጋችሁት ኩኔታ ድረሱ።”

የክርስትና ሚስጥር ለሙስሊማኑ እንቆቅልሽ ነው። መለኮት ሰው የኾነበት አስተምህሮተ- ኢየሱስ ለመረዳት እጅግ ያዳግታቸዋል። ሥላሴ ግራ የሚጋቡበት ሌላው አስተምህሮ ነው። ክርስቲያኖኑ እንዴት ሶሶት አማልክት ያመልካሉ፤ ብዙ አማልክት ከሚያመልኩትስ በምን ይለያሉ? የሚለውን ጥያቄ ያነሳሉ። ሙስሊማኑ ከእግዚአብሔር ፍቅር ይልቅ በእግዚአብሔር ትልቅነት ላይ ያተኩራሉ፤ በዚህም እግዚአብሔር ለሰው ዘር በሙሉ ያለውን ታላቅ ፍቅር የገለጠው በመስቀል ላይ ነው የሚለውን እጅጉን ይቃወማሉ።

## 3. ሙስሊማኑ ስለ ክርስቶስ ከፊሉን እውነት ያምናሉ።

እስልምና እና ክርስትና ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚያመሳስላቸው በብዙ ነገር አለ። ሙስሊማኑ ድንግል መርየም በጅብሪል (መንፈስ ቅዱስ) ኃይል መወለዱን፣ ተዓምራት ማድረጉን ያምናሉ። ሆኖም ክርስቶስ እራሱን በማዋረድ የባሪያን መልክ መያዙን አይቀበሉም (ፊልጵስዩስ 2፥7)። ሰዎችን ሁሉ ለማዳን የሆነውን የክርስቶስን ስቅለት ፈጽመው አይቀበሉም። እዚህ ላይ ልብ ልንለው የሚገባ ነገር “የሙስሊም ክርስቶስ” ከወንጌላት ኢየሱስ ፍጹም የሚለይ መሆኑን ነው፤ ይህ አንኳር ነጥብ በምዕራፍ ስምንትና ዘጠኝ የምንመለስበት ይሆናል።

## 4.ሙስሊማኑ ክርስትናን ከምዕራባውያኑ ጋር ያተካክሉታል።

እስልምና ሀይማኖትንና መንግስትን በመጠኑም ቢሆን ለያይቶ የሚመለከት በመሆኑ፣ ክርስትና የምዕራባውያን ማህበረሰብ ፖለቲካና እምነት ቀጥተኛ መገለጫ ተደርጎ ይወስዳል። በእነርሱ አረዳድ የምዕራባውያን ምግባር ሁሉ እንደ ክርስትና ተደርጎ ይቆጠራል፤ ከዚህ የተነሳ ለክርስትና ያላቸው አመለካከት ዝቅተኛ ቢኾን እምብዛም አያስደንቅም። በሆሊ ሁድ ፊልም የሚንጸባረቁ ምግባረ ብልሹነቶች ሁሉ የክርስትና ባህሪይ መገለጫ ተድረገው የሚወስዱትም ለዚህ ነው።

## 5.ሙስሊማኑ ክርስትናን ጥለኛ የፖለቲካ ኃይል አድርገው ያዩታል።

በአብዛኛው ሙስሊማኑ ክርስትናን ቁጥር አንድ ጠላት አድርገው ይቆጥራሉ። የእስራኤል እንደ መንግስት መመስረት፣ የፍልስጤማውያን መበታተን፣ ስምንተኛው የመስቀል ጦርነት (1096-1291 ዓ.ም) እንዲያስታውሱ ያደርጋቸዋል። አሜሪካ ከእስራኤል ጋር ያላት የውጪ

ፖሊሲ አጋርነት፣ ክርስቲያናዊ የፖለቲካ ሚዛንዋ፣ ክርስቲያን ሚሲዮናዊያንን መርዳቷ፣ የመሳሰሉት ጉዳዮች ለሙስሊማኑ የሚፈጥረው ስሜት እስልምናን እንደማጥፋት ነው፡፡

## 6.ሙስሊማኑ ሀይማኖትን በሚክዱ ላይ ጽኑ ህግ አላቸው፡፡

በእስልምና ከሌላ ሐይማኖት ተከታዮች ጋር ሳይቀር ህብረት ማድረግ በጽኑ ይከለከላል፡፡ "**እናንተ** ያመናችሁ ሆይ! አይሁዶችን ረዳቶች አድርጋችሁ አትያዙ፤ ከፊላቸው ለከፊሉ ረዳቶች ናቸው፤ ከእናንተም ውስጥ ረዳቶች የሚያደርጋቸው ሰው እርሱ ከነርሱ ነው፤ አላህ አመጸኞችን ሕዝቦች አያቀናም (ሱረቱ 5፥51) ፡፡

እምነታቸውንና ማህበረሰባቸውን የሚክዱ ሰዎች ጽኑ ቅጣት ይጠብቃቸዋል፡፡ ለሚክዱ ሰዎች ተፈጻሚ የሚሆነው የቅጣት ህግ ሙሴ ለአይሁድ ከዳተኞች ካወጣው ህግ ጋር ይመሳሰላል (ኦሪት ዘዳግም 13፥ 6-11) ፡፡ አቡዱልራህማን አል- ጃዚሪ የእስልምና ከዳተኞችን ቅጣት በተመለከተ በጻፈው መጽሐፍ "አራቱም ኢማሞች (አራቱ የእስልምና ህግ ትምህርት ቤት መስራቾች) እስልምናን የሚክድ ሰው ያለ ጥርጥር እንዲገደል ደሙም ያለ ምንም ዝክር እንዲበተን ተስማምተዋል፡፡ ግብዝ የሆነው ሙስሊምም ሙስሊም ነኝ እያለ በድብቅ ከድቶ ቢገኝ ይገደል"[3] ይላል፡፡

ምንም እንኳ የሕግ ቅጣቱ ሙሉ ለሙሉ ባይተገበርም ፣ ወደ ክርስትና እምነት የሚቀየሩ ሙስሊም ዛሬም ቢሆን ከቤተሰቡ መገለል፣ ከቦታው መፈናቀል ፣ሥራ ማጣት የመሳሰሉ ችግሮችን ይጋፈጣል፡፡

## 7.ሙስሊማኑ ሀይማኖታዊ ቁጡነትን ይቀበላሉ፡፡

በቁርአን "ጸሎት" የሚለው ቃል ዘጠና ዘጠኝ ጊዜ በግሥ፣ በስምና በቅጽል መልክ የተቀመጠ ሲሆን "መግደል" ለአንድ መቶ ሰባ ጊዜ ተጠቅሷል፡፡ በእስልምና ጽኑ ቅጣት የሚፈጸምባቸው ከዳተኞች ብቻ አይደሉም፡፡

ቁርአን ቅጣት በቤት ውስጥ አንዱ የህይወት ክፍል እንደሆነ ይናገራል፤ ሚስትን መቅጣት ህጉ ይደግፋል፡፡ "ወንዶች በሴቶች ላይ ቋሚዎች (አሳዳሪዎች) ናቸው፤ አላህ ከፊላቸውን በከፊሉ ላይ በማብለጡና (ወንዶች) ከገንዘቦቻቸው (ለሴቶች) በመስጠታቸው ነው፡፡ መልካሞቹም ሴቶች (ለባሎቻቸው) ታዛዦች አላህ ባስጠበቀው ነገር ሩቃን ጠባቂዎች

[3] አብዱልራህማን አል-ጃዚሪ፣ በእስልምና የከዳተኞች ቅጣት (ቪ.ሲ.ች፣ አስትሪያ፣ የህይወት ብርሃን፣1997) ፣ የመጀመሪያ ምዕራፍ፡፡

ናቸው። እነዚያንም ማምጣታቸውን የምትፈሩትን ገሥጹዋቸው፤ በመኝታዎችም ተለዩዋቸው (ሳካ ሳታደርሱ) ምቱዋቸውም። ቢታዘዙዋችሁም (ለመጨቆን) በነርሱ ላይ መንገድን አትፈልጉ። አላህ የበላይ ታላቅ ነውና" (ሱረቱ 4፥34)።

በእስልምና ሴት ያላት ቦታ የሚያሳየው የቅጣቱን ሁኔታ ነው። ሱረቱ 4፥3 ከአንድ ሚስት በላይ ማግባትን ያዛል "በየቲሞችም (ማግባት) አለማስተካከላችሁን ብትፈሩ፣ (ዝሙትንና ከተወሰነላችሁ በላይ ማግባትንም ፍሩ)፤ ከሴቶች ለእናንተ ተዋበላችሁን ሁለት ሁለት፣ ሦስት ሦስትም ፣አራት አራትም አግቡ። አለማስተካከልንም ብትፈሩ፣ አንዲት ብቻ፣ ወይም እጆቻችሁ ንብረት ያደረጉትን ያዙ፤ ይህ ወደ አለ መበደል በጣም የቀረበ ነው።"

መሐመድ እራሱ አራት ሚስቶችን እንዲያገባ ተፈቅዶለታል። ሱረቱ 33፥ 50 "አላህ መሐመድን "አንተ ነብዩ! እኛ እነዚያን መህሮቻቸውን የሰጠሃቸውን ሚስቶችህን፣ አላህ ባንተ ላይ ከመለሰልህም እነዚያን እጅህ የጨበጠቻቸውን ምርኮኞች፣ እነዚያንም ከአንተ ጋር፣ የተሰደዱትን የአጎትህንም ሴቶች ልጆች፣ የአክስቶችህንም ልጆች ፣ የየሹማህንም ሴቶች ልጆች (ማግባትን) ለአንተ ፈቅደንልሃል፤ የአመነችም ሴት ነፍሷን (ራሷን) ለነብዩ ብትሰጥ ነብዩ ሊያገባት የፈለገ እንድሆነ ፣ ከምእምናን ሌላ ላንተ ብቻ የጠራች ስትሆን፣ (ፈቀድንልህ)" ፤ ወንድ ከሴት እንደሚልቅ በሚናገርበት አግባብ የሴቶችን ውርስ አስመልክቶ ሱረቱ 4፥11 "ለወንዱ የሁለት ሴቶች ድርሻ ቢጤ " እንዳለው ይናገራል። የሴቶችን ምስክርነት በተመለከተ ሱረቱ 2፥282 "ከወንዶቻችሁም ሁለቱን ምስክሮች አስመስክሩ። ሁለትም ወንዶች ባይኾኑ ከምስክሮች ሲኾኑ ከምትወዱዋቸው የኾኑ የአንድ ወንድና አንደኛዋ ስትረሳ አንደኛይቱ ሌላውን ታስታውሳት ዘንድ ሁለት ሴቶች ይመስክሩ" ይላል።

ከፍቺ በኋላ ስላለ ጋብቻ ሱረቱ 2፥230 "(ሦስተኛ) ቢፈታትም ከዚህ በኋላ ሌላን ባል እስከምታገባ ድረስ ለርሱ አትፈቅድለትም ። (ሁለተኛው ባል) ቢፈታትም የአላህን ሕግጋት መጠበቃቸውን ቢያውቁ በመማለሳቸው በሁለቱም ላይ ሐጢአት የለባቸው። ይህችም የአላህ ሕግጋት ናት ለሚያውቁ ሕዝቦች ያብራራታል" ይላል (ከኦሪት ዘዳግም 24፥ 1-4 ጋርያነጻጽሩ)።

ሱረቱ 24፥31 የሴቶች በአዳባባይ መታየትን አስመልክቶ "ዓይኖቻቸውን ይከልክሉ፤ ብልቶቻቸውንም ፤ ጌጣቸውንም ከርሷ ግልጽ ከሆነው በስተቀር አይግለጡ፤ ጉፍታዎቻቸውንም በአንገት ጌዎቻቸው ላይ ያጣፉ (የውስጥ) ጌጦቻቸውንም....ሕጻኖች ካልሆኑ በስተቀር አይግልጹ" ይላል።

ዝሙት ኃይለኛ ፍዳ እንደሚያስከትል ሱረቱ 24፥2 ይናገራል "ዝሙተኛይቱና ዝሙተኛው ከሁለቱ እያንዳንዳቸውን (ያላገቡ እንደሆኑ) መቶ ግርፋትን ግረፉዋቸው በነርሱም በአላህ ፍርድ ርኅራኄ አትያዛቸው በአላህና በመጨረሻው ቀን የምታምኑ እንደ ሆናችሁ (አትራሩ)፤ ቅጣታቸውንም ከምእመናን ጭፍሮች ይገኙበት ።" የጣኦት አምልኮን በተመለከተ "የተከበሩትም ወሮች ባለቁ ጊዜ አጋሪዎቹን በአገኛችሁባቸው ስፍራ ግደሉዋቸው፤ ያዙዋቸውም፣ ክበቡዋቸውም፤ ለነሱም (መጠባበቅ) በየመንገዱ ተቀመጡ፤ ቢጸጸቱም፤ ሶላትንም በደንቡ ቢሰግዱ ፣ ግዴታ ምጽዋትንም ቢሰጡ ፣ መንገዳቸውን ልቀቁላቸው አላህ መሐሪ አዛኝ ነውና" (ሱረቱ 9፥5) ይላል።

ሰለ አይሁዳውያኑ እና ክርስቲያኖኑ ሱረቱ 9፥29 "ከነዚያ መጽሐፍን ከተሰጡት ሰዎች፣ እነዚያንም በአላህ በመጨረሻው ቀን የማያምኑትን፣ አላህ መልዕክተኛው እርም ያደረጉትንም እርም የማያደርጉትንና እውነተኛውንም ሃይማኖት የማይቀበሉትን እነርሱ የተዋረዱ ሆነው ግብርን በእጆቻቸው እስኪመጡ ድረስ ተዋጉዋቸው።"

ጅሃድ ("ቅዱስጦርነት") ከአላህ ብድራት የሚቸረው ምግባር ነው። ሱረቱ 9፥111"አላህ ከምእምናን ፣ ነፍሶቻቸውን፣ ገነት ለነሱ ብቻ ያላቸው በመሆን ገዛቸው፤ በአላህ መንገድ ላይ ይጋደላሉ፤ ይገድላሉም ፣ ይገደላሉም፤ በተውራት በኢንጅልና በቁርአንም፣ (የተነገረውን) ተስፋ በርሱ ላይ አረጋገጠ፤ ከአላህም በኪዳኑ የሚሞላ ማነው? በዚያም በእርሱ በተሻሻጣችሁባቸው ሽያጫችሁ ተደሰቱ ፤ ይህ እርሱ ታላቅ ዕድል ነው።" ሱረቱ 4፥74 ደግሞ " እነዚያም ቅርቧን ሕይወት በመጨረሻይቱ ሕይወት የሚለውጡ፣ በአላህ መንገድ ይጋደሉ፤ በአላህም መንገድ የሚጋደል፣ የሚገድልም፣ ወይም የሚያሸንፍ፣ታላቅ ምንዳን በእርግጥ እንሰጠዋለን" ይላል።

በእስልምና ላይ ክንዳቸውን የሚያኖሩትን "የነዚያ አላህና መልዕክተኛውን የሚዋጉ ፣ በምድርም ላይ ለማጥፋት የሚተጉ ሰዎች ቅጣት፣ መግደል ወይም መስቀል፣ ወይም እጆቻቸውንና እግሮቻቸውን በማፈራረቅ መቆረጥ ወይም ከአገር ማባረር ነው። ይህ ለርሱ በቅርቢቱ ዓለም ውርደት ነው፤ በመጨረሽይቱ ለነርሱ ከባድ ቅጣት አላቸው" ብሎ ይናገራል (ሱረቱ 5፥33) ።

መሐመድ ከጦር ሰራዊቶቹ ጋር በመሆን የኩሪሽን ህዝብ ባድር ስፍራ ድል ነስቷል። ቁርኣን ሰለ ጦርነቱ የሚከተለውን ይናገራል፦ "እነዚያም ካዱት ከአላህ ቅጣት ያመለጡ መሆናቸውን እያሰቡ፤ አነሱ አያቅቱትምና። ለነሱም ከማንኛውም ሀይልና ከታጀቡ ፈረሶችም የቻሉትን ሁሉ በርሱ የአላህን ጠላትና ጠላታችሁን ሌሎችንም ከነርሱ በቀር ያሉትን

የማታውቋቸውን አላህ የሚያውቃቸውን (መናፍቃን) የምታሸብሩበት ስትሆኑ አዘጋጁላቸው፡፡ ከማንኛውም ነገር በአላህ መንገድ የምትለግሱትንም ምንዳው ወደ እናተ በሙሉ ይሰጣል፤ እናንተም አትበድሉም፡፡ አንተ ነብዩ ሆይ! ምዕመናንን በመዋጋት አደፋፍራቸው፤ ከእናንተ ውስጥ ሃያ ታጋሾች ቢኖሩ ሁለቱ መቶን ያሸንፋሉ፤ ከእናንተም መቶ ቢኖሩ ከነዚያ ከካዱት እነሱ የማያውቁ ሕዝቦች ስለሆኑ ሺህን ያሸንፋሉ" (ሱረቱ 8፥59፣60፣65) ፡፡

አይሁዳውያኑ ክርስቲያኖኑን ሱረቱ 5፥51 "እናንተ ያላመናችሁ ሆይ! አይሁዳውያኑን ረዳቶች አድርጋችሁ አትያዙ፤ ከፊላቸው ለከፊሉ ረዳቶች ናቸው፤ እናንተም ውስጥ ረዳቶች የሚያደርጋቸው ሰው እርሱ ከነርሱ ነው፤ አላህ አመጠኞችን ሕዝቦች አያቀናም፡፡ እንደ መሐመድ ተወዳጅ ሚስት፣ አይሻ መሰረት" በአረብ ባህረ-ገብ ወይም መሬት ሁለት ሀይማኖቶች በአንድ ላይ መኖር የለባቸው" [4] ይላል፡፡

እስልምና ስለ መጤዎች ያለው እሳቤ በመሐመድ የአክስት ልጅና አማች አሊ ኢቡን ታሊብ አባባል ሊጠቃለል ይችላል፡-

*አበቦቻችን ሰይፍ እና ጩቤ ናቸው፣*
*የናርሲስ ዘር እጽዋአት እና ለምልም ዛፍ አይደሉም*
*መጠጦቻችን የጠላቶቻችን ደም ነው፤*
*ዋንጫችንም ራስ ቅሎቻቸው ናቸው፡፡* [5]

ይህ አመለካከት በሳልማን ረሽድ ላይ የነበረውን አመጽ ክፉኛ የሚያነሳሳ ፣ በዓለምም የሚያሰራጭ መኾኑን መገመት አያዳግትም ፡፡ እንደ ፍላደልፊያው ዳሬክተር ዳንኤል ፓይፐስ ፣ የመካከለኛው ምስራቅ ሸንጎ ገለጻ እንደሚከተለው ማስተዋል ይቻላል ፡-

*በዋናነት ችግሩ የተጀመረው በጥር 1989 ነው፤ በብራድፎርድ ፣ ኢንግሊዝ የሚኖሩ ሙስሊማኑ መሐመድን የሚያሳብቁ ጽሑፎች ያካተተው የሳላማን ረሽድ "ሰይጣናዊ ጥቅሶች" ጽሑፍ ላይ ቁጣቸውን ለመግለጽ ወስኑ፡ ብዙኃን ሙስሊማኑ የፓኪሳታን ስደተኞች ሲሆኑ፣ የድርሰቱን ቅጂ በመግዛት በአደባባይ አውጥተው አቃጣሉ፡፡*

*በፓኪስታን ሳይቀር አስር ሺህ የሚያክሉ የረሽድ ተቃዋሚዎች በዋና ከተማዋ ኢስላማባድ በአሜራካዉያን ባህል ማዕከል ጥቃትና ቃጠሎ አደረሱ፡፡ በዚህም ስድስት ሰዎች ሲሞቱ፣*

---

[4] ኢቢን ሒሻም፣ የሙሐመድ ህይወት፣ በኤቢዲ አል ማሺ (ቪሊች፣ አስትሪያ፡- የህይወት ብርሃን፣ 1999) ቅጽ 2፣ ገጽ 305፡፡

[5] ---------፣ ገጽ.306፡፡

*በርካቶች ቆስለዋል። ክስተቱ የኢራን አብዮታዊ መሪ አያቶላ ኮሆሜኒን ትኩረት ወስደ፡ በዚህም ምክንያት በየካቲት 14፣ 1989 "ቀናተኛ ሙስሊም የሆናችሁ በሙሉ "የሰይጣናዊ ጥቅሶች" ደራሲ ሰልማን ረሽድን ብቻ ሳይሆን፣ ህትመቱን ያሰራጩና የተከተሉትን በሙሉ አስወግዱ" የሚለውን ጥሪ አደረገ።*

*አዋጁ ረሽድ  በእንግሊዝ የግል ጥበቃ እንዲኖረው ከማድረጉ ባሻገር ፤ በነጻነትና በትችት ዙሪያ ለወራት ያክል በፖለቲካ ሰዎችና አዋቂዎች መካከል ሙግቶችን አስተናግዷል። አያቶላ ኮሆሜኒ ረሽድን ለማስወገድ የተወጠነው ውጥን አልተሳካም። ይሁን እንጂ አብዛኛው ሙስሊማኑ ነፍስ በመቀስቀስ በእምነታቸው ጠንካራ መተማመንን ፈጥሮአል፤ በእምነታቸው በሚሳለቅና በሚተቹ ሰዎች ሁሉ ላይ እንዲቆጡ አድርጓል።*

*ምንም እንኳ ኮሆሜኒ አዋጁን ባስነገረበት ሳምንት ህይወቱ ቢያልፍም፣ መንፈሱ ግን አሁን ድረስ ዘልቆ እየሰራ ነው። ከ1989 ጀምሮ የእስላማዊው አክራሪ እንቅስቃሴ ቡድን ትችቶችን በኃይል ጸጥ ለማሰኘት ተግቶ እየሰራ ይገኛልም። ይሁን እንጂ የኃይል እንቅስቃሴው ስልታዊና ምክንያታዊ ባለመሆኑ የሚፈለገውን ለውጥ ማምጣት አልተቻለም።*

*ቀድሞ የነበሩ አካላዊ ዛቻዎች በረሽድ ጉዳይ ሳይቀር የተቃጡ ነበሩ። በኖርዌይ፣ጣሊያንና ጃፓን "የሰይጣን ጥቅሶች" ጽሑፍ ተርጓሚዎች ከፉኛ ግድያና ጥቃት ደርሶባቸዋል። በቱርክ አንድ ተርጓሚ በአረፈበት ሆቴል ከተቃጣበት የእሳት አደጋ አምልጧል፣ ሰላሳ ሰባት ያሚያክሉቱ በእሳት ቃጠሎው ህይወታቸው አልፏል። ሙስሊም የሆኑና ያልሆኑ ሰዎች በተመሳሳይ መልኩ ቅጣቱ ተጠንስሶባቸው ነበር።* [6]

## ***ሙስሊሞችን በወንጌል መድረስ  ጠሪውን ጌታ ማክበር ነው።***

በየትኛውም ሁኔታ የእስልምናን ዓለም በወንጌል መድረስ ተግዳሮት አለው። ሆኖም የመጀመሪያዎቹ ደቀመዛሙርት የሮማን ዓለም እንደ ደረሱት የማይቻል አይደለም። ሐዋሪያው ጴጥሮስ የቤተክርስቲያን አይነተኛ መሰረት ወንጌል ማዳረስ እንደሆነ ይናገራል (የመጀመሪያው የጴጥሮስ መልዕክት 2፥9-10) ። የሐዋሪያት ሥራ መጽሐፍ የጥንት አማኞች ያለ ፍርሃት ወንጌል የማድረሳቸውን ሃቅ ያስረግጥልናል (የሐዋሪያት ሥራ 2፥8፣ 4፥20፣ 29፣ 8፥4፣ እና 13፥1-4) ። ክርስቲያን ሁሉ የጌታን እራት በሚካፈልበት ወቅት "ይህን እንጀራ በበላችሁ ጊዜ ሁሉ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ሞቱን ትናገራላችሁና" (የመጀመሪያው መልዕክት ቆሮንቶስ 1፡ 11፡26) የሚለውን ቃል ምንግዜም ልብ ሊለው ይገባል።

---

[6] ዳንኤል ፓይፐስ ፣ እስልምናን ለመጋፈጥ ምንያህል ድፍረቱ አለህ፣ዋሽግተን፣ ዲሲ፡- ሐይማኖታዊ ነጻነት ቤት፣ ህዳር1999)።

እግዚአብሔር የማይቻለውን አያዝም፤ እስከ ምድር ዳርቻ ወንጌልን ታደረስ ዘንድ ቤተክርስቲያንን ሲያዝ አማኞችን በማስታጠቅ ነው። ያላንዳች ምክንያት እንድንታዘዘው ይፈልጋል። "እምቢ" እያልነው "ጌታ" ብለን ልንጠራው አንችልምና! ጌታ ከተከታዮቹ "እምቢ" ን አይቀበልም፤ እግዚአብሔርን "ጌታ" ብሎ መጥራት እና "እምቢተኝነት" ሁለቱም የሚቃረኑ ናቸው። ጌታ ህዝቦቹን ሲያዝ በማስታጠቅም ጭምር ነው። ጳውሎስ "ከቶ በገዛ ገንዘቡ በወታደርነት የሚያገለግል ማን ነው? ብሎ ይጠይቃል (የመጀመሪያው መልዕክት ቆሮንቶስ 9፥7)።

እርሱን የመታዘዛችን ብልጫ በእርሱ ውጤታማዎች የመሆናችን ዋስትና ነው። እርሱ ሁልጊዜ በዙፋኑ ላይ ነው፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀመዛሙርቱን ከማዘዙ በፊት የነገራቸው "ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ" ነበር (ማቴዎስ 28፡20) ። ሰዎችን የመቀይሩ ስራ በእናንተ የሚሰራ አንዳይደለ መገንዘብ ይኖርባችኃል። እናንተ የእግዚአብሔርን ዘር የምትዘሩ ናችሁ ። ኢየሱስ በማቴዎስ ወንጌል 13፥1-9 እንደገለጸው የመሬትን መልካምነት፣ እሾህማነት ወይም ጭንጫነት ማረጋገጥ የዘሪው ዋና ስራ አይደለም ። የዘሪው ሥራ ዘርን መዝራት ነው፤ የሰዎችን ልብ መቀየሩ ግን የመንፈስ ቅድስ ብቻ ይሆናል።

በዚህ ጳውሎስ አንዳች ብዥታ የሌለው መኾኑን ማስተዋል ይቻላል። የቆሮንቶስ ሰዎችን የሚጠይቀውም ይህንኑን ነበር "አጵሎስ እንግዲህ ምንድር ነው ? ጳውሎስ ምንድር ነው ? በእነርሱ እጅ ያመናችሁ አገልጋዮች ናቸው። ለእያንዳንዳቸውም ጌታ እንደ ሰጣቸው ያገለግላሉ። እኔ ተከልሁ፤ አጵሎስም አጠጣ፣ ነገር ግን እግዚአብሔር ያሳድግ ነበር፤ እንግዲያስ የሚያሳድግ እግዚአብሔር እንጂ የሚተክል ቢሆን ወይም የሚያጠጣ ቢሆን አንዳች አይደለም። የሚተክልና የሚያጠጣ አንድ ናቸው፣ ነገር ግን እያንዳንዱ እንደ ራሱ ድካም መጠን የራሱን ደመወዝ ይቀበላል። የእግዚአብሔር እርሻ ናችሁ፤ የእግዚአብሔር ሕንጻ ናችሁ፤ ከእርሱ ጋር አብረን የምንሠራ ነንና" (የመጀመሪያው መልዕክት ቆሮንቶስ 3፥5-9)።

አንድ ሰው ሰዎችን ወደ ክርሰቶስ የማምጣቱ ተግባር በርሱ ብቻ እንደሆነ ቢመስለው ፣ እውነቱ ሙሉ አይኾንም ። መንፈስ ቅዱስ የተጠቀመው እርሱን ብቻ አይደለም፤ የሰው ልብ ለክርስቶስ ክፍት እንዲሆን እግዚአብሔር ብዙ ሰዎችን ይጠቀማል። ስለዚህ ከሰዎች መዳን /መቀየር/ በኃላ የቡድን ስራ አስፈላጊነት ከቶ መዘንጋት የለበትም፤ የተቀየሩ ሙስሊማኑ ይህንኑን የቡድን ድጋፍና ትኩረት ይሻሉ።

ወደ ክርስቶስ የሚመጣ ሙስሊም በማያቋርጥ ጫና ውስጥ ይኖራል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን በቤት ውስጥ ማንበብ ሆነ በግል ከእግዚአብሔር ጋር ጊዜ መውሰድ አይችልም፡፡ ለክርስትና እምነት እንግዳ እንደመሆኑ መጠን ክርስቲያናዊ ስብከቶች ሳይቀር  መረዳት ያዳግተዋል፡፡ እስልምናን በመተው ምክንያት የቤተሰቡ ልብ መሰበሩ፣ በማያቋርጥ ሀዘን ውስጥ እንዲያልፍ ያደርገዋል፡፡ እነዚህ ሁሉ በፍጥነት እንደሚያድግ አረም በውስጡ የተተከለውን  የእግዚአብሔር ቃል ያንቃሉ (ማቴዎስ ወንጌል 3፥21)፡፡ ከቤተሰብ፣ ከጎረቤት እና ከበላይ ባለ ስልጣናት ስደት ሊደርስበት ይችላል፡፡ ብዙ ጊዜ ሚስቶች ባላቸው ወደ ክርስትና በሚለወጥበት ወቅት ልጆችን በመንጠቅ የማሳደግ ኃለፊነቱን ይወስዳሉ፡፡ ስራውንና ርስቱንም እንዲያጣ ይደረጋል፤ ያላገባ እንደሆነ ስፍራውን እንዲለቅ ይገደዳል፡፡

ስለሆነም ሁሉን ስናደርግ በጥንቃቄ ሐሰተኞችን / ላዮችን) የምንለይበትን መንፈስ እንዲሰጠን በመጸለይ መሆን ይኖርበታል (ሁለተኛው መልዕክት ተሰሎንቄ 2፥5፡21)፡፡ በሙስሊማኑ ህዝቦች መካከል የሚኖሩ ክርስቲያኑ ድነትን ለተቀበሉ ሰዎች መልካም ምሳሌ መሆን ይገባቸዋል ፡፡ አንድ ወደ ድነት የመጣ ሙስሊም ከመጠመቁ በፊት አስቀድሞ ሁለቱን የክርስትና እውነቶች እንዲረዳ ማድረግ ያስፈልጋል፡- በክርስቶስ ሰላም እና እረፍት፤  ስለ ክርስቶስ  መከራን መቀበል! የክርስትና እምነት ሚዛናዊ ስዕል በዚህ መልኩ መቅረብ ይኖርበታል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ሰለ አማኞች ሲናገር "ይህ ስለ ክርስቶስ ተሰጥቶአችኃልና፤ ስለ እርሱ መከራ ደግሞ ልትቀበሉ እንጂ በእርሱ ልታምኑ ብቻ አይደለም" ይላል (ፊልጵስዮስ 1 ፥29)፡፡ ቤተክርሰቲያን ነቃታ አዲሱን አማኝ የሚቀበል፣ በእምነቱ የሚያሳድግ ክርሰቲያናዊ ማህበረሰብ ማሰልጠን ይኖርባታል፡፡

ሙስሊማኑን በወንጌል ለመድረስ አስቸጋሪ ከሆኑት አንዱ ወደ ሆነው ኣሳብ እንሸጋገር፡- ክርስቲያን በእስልምና እምነት ለሚኖር ሰው ወንጌልን ውጤታማ በሆነ መንገድ ማድረስ የሚችለው እንዴት ነው?

የግል ማስታወሻ

2

# ከሙስሊማኑ ጋር

# መግባባት የሚቻለው እንዴት ነው

ከሙስሊማኑ ጋር በእምነት ጉዳዮች ፍሬያማና ዘላቂ ውይይትን ማሳደግ ይቻል ዘንድ ትዕግስትና ምክንያታዊ ተግባቦት ያሻል፡፡ በውስብስብ ጉዳዮች ላይ ረጅም ጊዜ መውሰድ ትርፉ ሁለቱንም አካላት ማክሰር ነው፤ በዚህ ረገድ ይህ ምዕራፍ ጠቃሚ መመሪያዎችን ይቸራል፡

## I. ጥያቄዎችን መመለስ እና ማውሳት

ሙስሊም እምነትህን በተመለከተ እንዲጠይቅህ መጸለይ አለብህ፡፡ ሙስሊም ለሚጠይቅህ ጥያቄ ትክክለኛውን ምላሽ መስጠት ዝግጁነት ይጠይቃል፡፡ ተቃርኖአዊ አሳቦችና ውስብስብ ጥያቄዎችን ለራስ ፍላጎት ሲባል ማቀንቀን ሙስሊማኑ ለሚያነሱአቸው ሙግቶች አዎንታዊ ምላሽ አያስገኝም፡፡ የክርስቲያናዊ ሙግት ናሙና ጳውሎስ በአርዮስፋጎስ የማይታወቅ አምላክ አንስቶ ባደረገው ሙግት ላይ ይገኛል፡፡

ስለ እስልምና ግልጥ የሆኑ ጥያቄዎችን ማንሳት ያስፈልጋል፡፡ ከጸሎት በፊት መታጠብ ለምን አስፈለገ? ዘካት ለምን? ሙስሊማኑ ፈጣሪ ይቅር እንዳላቸው በምን ያውቃሉ? ክርስቲያኖኑ በክርስቶስ ቤዛነት ላይ የሚያተኩሩት ለምንድ ነው? ሙስሊማኑ ትልቅ የሆነውን የአል-አደሃ በዐል (የአብርሐም ልጅ ድነት በዐል) ለምን ያከብራሉ? የእስልምናን ባልህል እና ሀይማኖት በይበልጥ ማወቅ የሙስሊማኑን ምላሽ ቀድሞ በመረዳት የክርስትናን እምነት ለማስተላለፍ እጅጉን ይረዳል፡፡

ዶክተር ሪቻርድ ቶማስ "እስልምና ፣ ዝንባሌ እና እይታ" በሚለው ድርሳኑ ሙስሊማኑን በወንጌል ከመድረስ አኳያ የሚከተለውን ምክር ለግሷል፡- [7]

> *አንድ ሙስሊም ጓደኛ የሚለውን በጥንቃቄ እንስማ ፡- ከክርክር ይልቅ ለጥያቄዎች ዝግጁ እንሁን፡፡ በሊባኖስ በሚገኘው ሆስፒታል በአመዛኙ ከባህር ሰላጤ የሚመጡትን ሙስሊማኑ*

[7] ሪቻርድ ቶማስ ፣ እስልምና፣ ዝምበላ እና እይታ ( ቪላክ፣ አውስትሊያ፡- የህይወት ብርሃን)፣ ገጽ 187-190፡፡

*አገኛለሁ፡፡ በአንዱ እሁድ በእድሜ ጠና ያለ ሳውዲ አስቁሞኝ « ኢንጅልን ልታነበልኝ ትችላላህን? ከቁርአን ብጠቅስልህ ትኩረት ትሰጠኛለህን?" ብሎ ጠየቀኝ ፤ ለጥቆም ስልሳ ጥቅሶችን ይነግረኝ ጀመር፡፡ በዚህ መልኩ ውይይት ማድረግ ጊዜ ቢሻማም፣ ዋጋ ለማግኘት ግን ጊዜ መስጠት ምንኛ ወሳኝ መኾኑን መገንዘብ አያዳግትም፡፡*

ማናቸውም የሚነሱ ርዕስ ጉዳዮች አስመልክቶ በፍጥነት ወደ ስምምነት መምጣት ትመኙ ይሆናል፤ ኾኖም ሁሉን ለመዳሰስ መሞከር በራሱ ግርታ አለው፡፡ በሁሉም ውይይቶች ላይ ጊዚያዊ መደምደሚያ ማስቀመጥ መልካም ነው፡፡ ወንድ ሙስሊማኑ ወንዶችን፣ ሴት ሙስሊማኑ ደግሞ ሴቶችን መድረስ መመሪያው ይደነግጋል፡፡ በሁሉም የውይይት መድረኮች ፖለቲካ ነክ ጉዳዮችን ማስወገድ ያስፈልጋል፡፡ ሙስሊም አርቦች በአይሁዳውያኑ እና ክርስቲያኖኑ ላይ ከፍተኛ እንጉርጎሮ አላቸው፡፡ ሪቻርድ ቶማስ ለሙስሊማኑ ግድ የሚሰኝ የወንጌል ሰራተኛን በተመለከተ " የፖለቲካ ክርክር በቤቴ እንዲኾን ከቶ አልፈቅድም" ሲል ፖለቲካ ነክ ጉዳዮችን ማስወገድ እንደሚገባ ያስገነዝባል፡፡

## II. ሙስሊማኑን ማሳወቅ

**ሙ**ስሊማኑ ክርስቲያናዊ የሬዲዮ ስርጭቶችን፣ ቴሌቪዥን ፕሮግራሞችን እና ድኅረ- ገጾችን የሚያገኙበት ሁኔታ መጠቆም ያስፈልጋል፡፡ የኢየሱስን ፊልም እንዲመለከቱ አሳብ ማቅረብ መልካም ነው፡፡ በራሪ ወረቀቶች፣ ትናንሽ ጽሑፎችና የአዲስ ኪዳን ጥቅሶች በማቅረብ ፣ ለሚያነሱአቸው ጥያቄዎች ምላሽ የሚኾኑ ስራዎች መቀረጽ ይኖርበታል፡፡ እነርሱን ለመድረስ ተመራጭ የኾኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች፡- የተራራው ስብከት፣ መዝሙረ ዳዊት እና የሉቃስ ወንጌል ናቸው፡፡ የኢየሱስን ትምህርቶች፣ ምሳሌዎች እና ተአምራቶች የማወቅ እድሉ ጠባብ ቢሆንም፣ ስለ እርሱ ያላቸው አድናቆት ከፍተኛ ነው፡፡ ሙስሊማኑ ቁርኣን እና በራሪ ወረቀቶችን በሚሰጡን ጊዜ በትህትና ተቀብለን ልናነባቸው፣ ለተጨማሪ ውይይትም ልንዘጋጅባቸው ይገባል፡፡

## III. ቁርአንን ለመንፈሳዊ ውይይት መጠቀም

ሙስሊማኑ በክርስትና ላይ የሚያነሱአቸውን ዝርዝር ሙግቶች ከማየት በፊት ሱረቱ ቁርኣንን መነሻ ማድረግ ጥሩ ነው፡፡ ሱረቱ 29፥46 ከመጽሐፉ ሰዎች በመጥፎ ካልኾነ በቀር በመልካም ሁኔታ መወያየት እንደሚቻል ፤ ለእነርሱም የተገለጠው ፈጣሪ የሌሎቹም ፈጣሪ እንደኾነ ፣ እንደሚገዙለትም ይናገራል፡፡

ይህ የቁርኣን  ጥቅስ ሙስሊማኑን የሚያስተምረው፡-

- መልካም የኾኑ አይሁዳውያኑ እና ክርስቲያኑ በበጎ ሁኔታ መመልከት እንዳለባቸው፡፡
- ብሉይ ኪዳን ለአይሁዳውያኑ፣ አዲስ ኪዳን ደግሞ ለክርስቲያኑ የተገለጠ መኾኑን እንዲያምኑ፡፡
- የአይሁዳውያኑ እና ክርስቲያኑ ፈጣሪ የእነርሱም ፈጣሪ በመኾኑ እራሳቸውን ሊሰጡ እንደሚገባ  እና
- ክርስቲያኖኑ ኪዳንን የሚያፈርሱ፣ ብዙ አማልዕክትንም የሚያመልኩ አለመኾናቸውን እንዲገነዘቡ  ነው፡፡

## IV. አብይ እውነታዎችን ማካፈል

የሰው ዘር ከፈጣሪው ጋር  ስላለው ግንኙነት ሦስቱ ዐበይት እውነታዎች ከእስልምና መረዳት በላይ በክርስቲያን ወንጌል በጽኑ ተገልጦ ይገኛል፡-

### 1. የእግዚአብሔር ፍቅር

እስልምና የፈጣሪን ልዕልና ፣ አላሀ አክበር (“አላሀ ታላቅ ነው”) ያተልቃል፡፡ ክርስትና ደግሞ “እግዚአብሔር ፍቅር” ነው የሚለውን ያስተምራል (1ኛ ዮሐንስ 4፥8፣16) ፡፡ ሰዎች እንዲፈሩ በሚያደርግ ሕግና በሚያቀርብ ጸጋ መካከል ምንኛ ልዩነት አለ (ዕብራውያን 12፥18-21፣ ማቴዎስ 5፥1)፡፡

እስልምና ፈጠሪ መንፈሳዊ የኾኑትን ሰዎች ብቻ እንደሚወድ ይናገራል፡፡ ክርስትና እግዚአብሔር መላውን አለም መውደዱን ያበስራል፡፡ እርሱ ኃጢአተኞችን፣

ተቃዋሚዎችን እና መንፈሳዊ ያልኾኑትን ይወዳል፤ የሚፈሩት (የሚያከብሩት) መንፈሳዊያንም እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡

የእስልምና ሀዲስ (ልማድ) ፈጣሪ በቀኝ እጁ አዋራ ወስዶ አንዳንድ ሰዎችን ከፈጠረ በኃላ "እነሆ ገነት ፣ እኔ አልጠነቀቅም" ፤ አንዳንዶችን በግራ እጁ ሌላ አዋራ ወስዶ በመፍጠር እነሆ ሲኦል፣ እኔ አልጠነቀቅም" ብሎ መናገሩን ይገልጣል፡፡[8]

እስልምና አላህ መሐሪ መኾኑን በጽኑ ያምናል፡፡ መሐሪ የሚለው ስም በቁርኣን ለፈጣሪ ከተሰጡት ስያሜዎች ሁሉ ይልቅ ጎልቶ ይታያል፡፡ አላህ ከምህረቱ የተነሳ ታላቅና ከሁሉ የላቀ ቢኾንም፣ ሩቅ ስለ ሆነ ከእርሱ ጋር ህብረት ማድረግ እንደማይቻል ያመላክታል፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ ባንጻሩ እግዚአብሔር ከፍቅሩ የተነሳ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ወደ እኛ እንደመጣ ይናገራል፡፡ የባሪያንም መልክ በመያዝ ፣ ራሱን ባዶ በማድረግ ኃጢአታችንን እንደተሸከመ ፣ በእኛም ፈንታ ለፍርድ አልፎ  መሰጠቱን ያስረዳል፡፡ እራሱን ለእኛ አሳልፎ በመስጠቱ በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ ስፍራ እንዲኖረን ሆነ፡፡ በሁሉ ስፍራ የሚኖሩ ሰዎች ሦስቱን መሰረታዊ ፍላጎቶች ፡- ማፍቀር፣ መፈቀር እና ደኅንነት በእጅጉ ይሻሉ፡፡ እነዚህን ማግኘት የሚቻለው ግን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አባት ብቻ ነው፡፡

## 2. ከእግዚአብሔር ጋር የግል ህብረት ማድረግ

እስልምና ሰዎች የፈጣሪ ባሪያ እንዲሆኑ ያስተምራል፡፡ ክርስቶስ እውነተኛ ክርስቲያኖኑ እግዚአብሔር "አባታችን በሰማይ የምትኖር" ብለው እንዲጠሩት ያበክራል፡፡ ሐዋሪያው ዮሐንስ ይህን በግልጥ ሲያስቀምጥ "የእግዚአብሔር ልጆች ተብለን ልንጠራ አብ እንዴት ያለውን ፍቅር እንደ ሰጠን እዩ፣ እንዲሁም ነን.....ወዳጆች ሆይ አሁን የእግዚአብሔር ልጆች ነን" (የመጀመሪያው መልዕክት ዮሐንስ 3፥1፣2)፡፡

## 3. የድነት ዋስትና

የዘላለም ድነት አስመልክቶ ቁርኣን ለአማኞች እርግጠኝነትን ወይም ዋስትናን አይሰጥም፡፡ የፈርኦንን አስማተኞች በመጥቀስ እንዲህ ይላል « (እነሱም) አሉ «በዓለማት ጌታ አመንን ፤ እኛ የምእምናን መጀመሪያ በመኾናችን ጌታችን ኀጢአቶቻችንን ለእኛ ሊምር እንከጅላለን»

[8] አይቢን ሐኒባል፣ ሙስናድ 26216፣ 31062፡፡

(ሱረቱ 26፥ 47፣51)። አብርሃምንም በመጥቀስ «ያም በፍርዱ ቀን ኀጢአቴን ለእኔ ሊምር የምከጅለው ነው» ይላል ( ሱረቱ 26፥ 82)።

ቁርአን አንባቢዎችን « ትበለጥጉም ዘንድ አላህን ፍሩ » (ሱረቱ 2፥189) እንዲሁም «ይታዘንላችሁም ዘንድ፥ አላህንና መልክተኛውን ታዘዙ» (ሱረቱ 3፥132) ብሎ ያዛል። ስለ ራሱ ሲመሰክር «ይህም ያወረድነው የኾነ የተባረከ መጽሐፍ ነው። ተከተሉትም። ይታዘንላችሁም ዘንድ (ከክህደት) ተጠንቀቁ » ይላል (ሱረቱ 6፥155)።

በሱረቱ 19፥71፣72 መሰረት ማንኛውም ሙስሊም (ሀይማኖት ያለውም ሆነ የሌለው) ወደ ገሃነም እንደሚሄድ ይናገራል ፡- « ከእናንተም ወደ እርሷ ወራጅ እንጂ አንድም የለም፤ (መውረዱም) ጌታህ የፈረደው ግዴታ ነዉ። ከዚያም እነዚያን የተጠነቀቁትን እናድናለን፤ አመጠኞቹንም የተንበረከኩ ኾነዉ በውስጧ እንተዋቸዋለን።»

ፈጣሪን የሚፈራ ሙስሊም በሙሉ መቼ እንደሚድን አያውቅም። ሀዲስ አንደሚናገረው አንድ ሙስሊም ለገነት የበቁ ሰዎችን በሕይወት ዘመኑ ካገለገለ በኃላ ገሃነም ይገባል።[9] ሀዲስ « አላህ አዳምን በጀርባው በስተቀኝ በኩል እየዳበሰ ይህ ገነት ነው ፣ መልካም የሚያደረጉ ይኖሩባታል፤ ግራውን በመዳሰስም ገሃነም ክፉ ለሚያደርጉ እንደኾነ » ይናገራል ። [10]

ክርስትና ግን ኢየሱስ በሰራው ስራ እምነቱን የሚያደርግ አማኝ የዘላላም ህይወት ዋስትና እንዳለው ያውጃል። ድነት የሚገኘው በጸጋ ብቻ ነው። ከፈጣሪ ቅድስና የተነሳ የኃጢአተኞችን ሞት እንዲሁም ከፍቅሩ የተነሳ የኃጢአተኞችን ድነት ከቶውን አይናገርም። አላህ ኃጢአተኞችን አይወድም (ይህ 24 ጊዜ በቁርኣን ተገልጿል፡- ሱረቱ 2፥190-192) ፤ እርሱ የሚወደው የሚፈሩትን ብቻ ነው ( ሱረቱ 3፥76) ። በዚህ ምክንያት ማንኛውም ሙስሊም አላህ ገነትም ሆነ ገሃነም እንደሚያስገባው እርግጠኛ አይደለም።

ክርስቲያን ሰባኪያን ማንኛውንም አጋጣሚ በመጠቀም ሦስቱን ታላላቅ እውነታዎች፡- የእግዚአሔር ፍቅር፣ ከእግዚአብሔር ጋር የግል ህብረት ማድረግ  እና የድነት ዋስትና መስጠትን ማወጅ ይኖርበታል። ይህ የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ሙስሊሙ የሚናፍቀው በመኾኑ በተገቢው ሁኔታ ሊቀርብለት ይገባል። በሉቃስ ምዕራፍ አስራ አምስት እንደ ሰፈረው

[9] ሙስሊም፣ ሳሂ፣ 4791።
[10] ሚስካት አል -ማሳቢሕ፣ ቅጽ 3 ፣ ገጽ 107።

የጠፋው ልጅ ታሪክ ፣ እግዚአብሔር በንስሐ ወደ እርሱ የሚመለሱትን ኃጢአተኞች እጁን ዘርግቶ ይጠባበቃል።

## V. ለግንኙነት ድልድል የሚኾኑ የቁርአን ጥቅሶችን መጠቀም

በቁርአን የሚገኙ በርካታ ምንባባት ለክርስቲያኑ ከበሬታን የሚሰጡ ናቸው። በሙስሊማኑ ዘንድ ያለው ይህ ዝንባሌ ትኩረታቸውን ለመሳብ ትልቅ ሚና ይኖረዋል። ሱረቱ 29፥ 46ን ቀደም ብዩ ጠቅሻለሁ፤ ተጨማሪ ምንባባትን እንመልከት፡-

***ሱረቱ3፥55***

*«አላህም ባለ ጊዜ (አስታውስ)፤ ዒሳ ሆይ! እኔ ወሳጂህ፣ ወደ እኔም አንሺህ ነኝ፤ ከነዚያም ከካዱት ሰዎች አጥሪህ ነኝ፤ እነዚያንም የተከተሉህን እስከ ትንሣኤ ቀን ድረስ ፣ ከነዚያ ከካዱት በላይ አድራጊ ነኝ፤ ከዚያም መመለሻችሁ ወደኔ ነዉ፤ በርሱ ትለያዩበትም በነበራችሁት ነገር በመካከላችሁ እፈርዳለሁ።»*

***ሱረቱ 3፥113-115***

*«የመጽሐፉ ሰዎች ሁሉ እኩል አይደሉም፤ ከመጽሐፉ ሰዎች ቀጥ ያሉ በሌሊት ሰዓቶች እነርሱ የሚሰግዱ ሆነዉ የአላህን አንቀጾች የሚያነቡ፣ ሕዝቦች አሉ። በአላህና በመጨረሻዉ ቀን ያምናሉ፤ በጽድቅ ነገርም ያዛሉ፣ ከመጥፎ ነገርም ይከለክላሉ፤ በበጎ ሥራዎችም፥ ይጣደፋሉ። እነዚያም ከመልካሞች ናቸዉ ከበጎ ሥራ ማንኛውንም ቢሠሩ፣ አይካዱትም አላህም ጥንቁቆቹን ዐዋቂ ነዉ። »*

***ሱረቱ 5፥69***

*«እነዚያ ያመኑና እነዚያም ይሁዳውያን የኾኑ፣ ሳቢያኖችም ክርስቲያኖችም፣ (ከነርሱ) በአላህና በመጨረሻው ቀን ያመነና መልካምን ሥራ የሠራ ሰው፣ በነርሱ ላይ ፍርሃት የለባቸውም፤ እነርሱም አያዝኑም።*

***ሱረቱ 5፥82***

*"ይሁዶችንና እነዚያን ያጋሩትን፣ ለነዚያ ለአመኑት በጠላትነት ከሰዎች ሁሉ ይበልጥ የበረቱ ሆነው በእርግጥ ታገኛለህ፤ እነዚያንም እኛ ክርስቲያኖች ነን ያሉትን ለነዚያ ለአመኑት በወዳጅነት በእርግጥ*

*ይበልጥ የቀረቧቸው ሆነው ታገኛለህ፤ ይህ ከነሱ ውስጥ ቀሳውስትና መነኮሳት በመኖራቸውና እነሱም የማይኮሩ በመሆናቸው ነው።»*

## VI. የቁርአን ውድቀት ታሪክ ማወቅና ማካፈል

የአዳምና ሔዋን ውድቀት ታሪክ በቁርኣን ሁለት ጊዜ በሱረቱ 2 እና 7 ተጠቅሷል። ሙሉው የውድቀት ታሪክ እነሆ፡-

***ሱረቱ 2፥30-38***

*(መሐመድ ሆይ) ጌታህ ለመላእክት፡- «እኔ በምድር ላይ ምትክን አድራጊ ነኝ፤» ባለ ጊዜ (የኾነውን አስታውስ፤ እነርሱም) «እኛ ከማመስገን ጋር የምናጠራህ ላንተም የምንቀድስ ስንኾን በርሷ ውስጥ የሚያጠፋንና ደሞችንም የሚያፈስን ታደርጋለህን?» አሉ። (አላህ) «እኔ የማታውቁትን ነገር አውቃለሁ» አላቸው። አደምንም ስሞችን ሁሏንም አስተማረው። ከዚያም በመላእክት ላይ (ተጠሪዎቹን) አቀረባቸው። «እውነተኞችም እንደኾናችሁ የነዚህን (ተጠሪዎች) ስሞች ንገሩኝ» አላቸው። «ጥራት ይገባህ፤ ከአስተማርከን ነገር በስተቀር ለኛ ዕውቀት የለንም። አንተ ዐዋቂው ጥበበኛው አንተ ብቻ ነህና» (አሉ)። «አደም ሆይ ስሞቻቸውን ንገራቸው» አለው። ስሞቻቸውን በነገራቸውም ጊዜ «እኔ የሰማያትንና የምድርን ሩቅ ምስጢር ዐውቃለሁ፤ የምትገልጹትንና ያንንም ትደብቁት የነበራችሁትን ዐውቃለሁ አላልኳችሁምን?» አላቸው። ለመላእክትም «ለአደም ስገዱ» ባልን ጊዜ (አስታውስ) ። ሁሉም ወዲያውኑ ሰገዱ፤ ኢብሊስ (ዲያብሎስ) ብቻ ሲቀር እምቢ አለ፤ኮራም ከከሓዲዎቹም ኾነ። «አደም ሆይ! አንተ ከነሚስትህ በገነት ተቀመጥ፤ ከርሷም በፈለጋችሁት ስፍራ በሰፊው ተመገቡ፤ ግን ይህችን ዛፍ አትቅረቡ፤ ከበደለኞች ትኾናላችሁና» አልንም። «አደም ሆይ! አንተ ከነ ሚስትህ በገነት ተቀመጥ፤ ከርሷም በፈለጋችሁት ስፍራ በሰፊው ተመገቡ፤ ግን ይህችን ዛፍ አትቅረቡ፤ ከበደለኞች ትኾናላችሁና» አልንም። ከርሷም ሰይጣን አዳለጣቸው በውስጡም ከነበሩበት (ድሎት) አወጣቸው። «ከፊላችሁም ለከፊሉ ጠላት ሲኾን ውረዱ፤ ለናንተም በምድር ላይ እስከ ጊዜ (ሞታችሁ) ድረስ መርጊያና መጣቀሚያ አላችሁ» አልናቸው። አደምም ከጌታው <u>ቃላትን ተቀበለ</u>። በርሱ ላይም (ጌታው ጸጸትን በመቀበል) ተመለሰለት፤ እነሆ እርሱ ጸጸትን ተቀባይ አዛኝ ነውና። «ሁላችሁም ኾናችሁ ከርሷ ውረዱ። ከኔም የኾነ መመሪያ ቢመጣላችሁ ወዲያውኑ መመሪያዬን የተከተለ ሰው በነሱ ላይ ፍርሃት የለባቸውም፤ እነሱም አያዝኑም»*

*ሱረቱ 7፥11-26*

*በእርግጥ ፈጠርናችሁ፤ ከዚያም ቀረጽናችሁ፤ ከዚያም ለመላእክቶች ለአደም ስገዱ አልን ወዲያውም ሰገዱ፤ ኢብሊስ (ዲያቢሎስ) ሲቀር ከሰጋጆቹ አልሆነም። (አላህ) ባዘዝኩህ ጊዜ ከመስገድ ምን ከለከለህ? አለው፤ እኔ ከርሱ የበለጥኩ ነኝ፤ ከእሳት ፈጠርከኝ፤ እሱን ግን ከጭቃ ፈጠርከው አለ። ከርሷ ውረድ፤ በርሷ ውስጥ ልትኮራ አይገባህምና ውጣም አንተ ከወራዶቹ ነህና አለው፤ እስከ ሚቀሰቀሱበት ቀን ድረስ አቆየኝ አለ። አንተ ከሚቆዩት ነህ አለው፤ ስለ አጠመምከኝም ለነርሱ በቀጥተኛው መንገድ ላይ በእርግጥ እቀመጥባቸዋለሁ አለ። ከዚያም ከበስተፊቶቻቸው ከኋላቸውም ከቀኞቻቸውም ከግራዎቻቸውም በእርግጥ እመጣባቸዋለሁ፤ አብዛኞቻቸውንም አመስጋኞች ሆነው አታገኛቸውም (አለ)። የተጠላህ ብራሪ ስትሆን ከርሷ ውጣ ከርሱ የተከተለህ ከናንተ ከመላችሁም ገሃነምን በእርግጥ እሞላታለሁ አለው። (እነሱ) ደንቆሮዎች፣ ዲዳዎች፣ ዕውሮች ናቸው፤ ስለዚህ እነርሱ አይመለሱም። አዳምም ሆይ! አንተም ሚስትህም ከገነት ተቀመጡ፤ ከሻችሁትም ስፍራ ብሉ፤ግን ይህችን ዛፍ አትቅረቡ፤ (ራሳቸውን) ከሚበድሉት ትሆናላችሁና (አላቸው)። ሰይጣንም ከእፍረተ ገላቸው የተሸሸገውን ለነርሱ ሊገልጽባቸው በድብቅ ንግግር ጎተጎታቸው፤ ጌታችሁም መልአኮች እንዳትሆኑ ወይም ከዘላለም ነዋሪዎች እንዳትሆኑ እንጂ ከዚች ዛፍ አልከለከላችሁም አላቸው። እኔ ለእናንተ በእርግጥ ከሚመክሩዋችሁ ነኝ ሲልም ማለላቸው። በማታለልም አዋረዳቸው፤ ከዛፊቱም በቀመሱ ጊዜ እፍረተ ገላቸው ለሁለቱም ተገለጠችላቸው፤ ከገነት ቅጠልም በላያቸው ላይ ይደርቱ ጀመር፤ ጌታቸውም ከዚቻችሁ ዛፍ አልከለከልኋችሁምን? ሰይጣንም ለናንተ ግልጽ ጠላት ነው አላልኩዋችሁምን? ሲል ጠራቸው። ጌታችን ሆይ! ነፍሶቻችንን በደልን፤ ለኛ ባትምር ባታዝንልም በእርግጥ ከከሳሪዎቹ እንሆናለን አሉ። (አላህ)፦ ከፊላችሁ ለከፍሉ ጠላት ሲሆን ውረዱ፤ ለእናንተም በምድር ላይ እስከ ተወሰነ ጊዜ ድረስ መርጊያና መጠቀሚያ አላችሁ አላቸው። በርሷ ላይ ትኖራላችሁ፤ በርሷም ላይ ትሞታላችሁ፤ ከርሷም ውስጥ ትወጣላችሁ አላቸው። የአዳም ልጆች ሆይ! ኀፍረተ ገላችሁን የሚሸሸግን ልብስ ጌጥንም በእርግጥ በናንተ ላይ አወረድን፤ አላህን <u>የመፍራትም ልብስ</u>፣ ይህ የተሻለ ነው፤ ይህ ከአላህ ታምራቶች ነው፤ ይገሠጹ ዘንድ (አወረደላቸው)።*

ከእነዚህ ሁለት ጥቅሶች የአዳም ውድቀት የመጀመሪያ መፍትሄ ሆኖ የቀረበው አዳም ከጌታው “ቃሎችን መቀበሉ” ነው፤ ሁለተኛው “የመፍራት ልብስ መቀበሉ” መኾኑን እንረዳለን። ቁርኣን እነዚህን አሳቦች አያብራራም። ዘፍጥረት 3፥15 የእግዚአብሔር ቃሎች የሴቲቱ ዘር የእባብን ራስ እንደሚቀጠቅጥ ፣እባብም ሰኮናውን እንደሚቀጠቅጥ የሚናገረውን እንደሚያመለክት ማስተዋል ይቻላል። ይህ እውነት ከውድቀት ዘመናት በኃላ ተፈጽሟል። ኢየሱስ “የሴቲቱ ዘር” የእባቡን /ሰይጣን/ ራስ ቀጥቅጧል። ሰይጣንም በመስቀል ላይ የርሱን ኮቴ በመስቀል ላይ ቀጥቅጧል።

ሙስሊማኑ በክርስቶስ ውልደት (የሴቲቱ ዘር) ያምናሉ። በኢየሱስ ፍጹምነትም ያምናሉ (ሱረቱ 19፥19 ይመልከቱ)። የሚቃወሙት ነገር ቢኖር መሰቀሉን ነው። የክርስቶስ መስቀል በዘፍጥረት የፍርሃት ልብስ ጥላ ነበር። እግዚአብሔር የእንስሳን ቆዳ ማዘጋጀቱ ፦ የእንስሳው መስዋዕትነት  የኢየሱስ መጻኢ "የእግዚአብሔር በግ" ቤዛነት አመላካች ነበር።

## VII. ሙግትን በፍጹም ትህትና መተግበር

ከሙስሊም ጋር የሚደረግ ሙግት ፍጹም ክሂሎትና ትዕግስት ይጠይቃል። የሙግት አቀራረባችንም ሆነ መንገዳችን መለየት ይኖርበታል። ከሁሉ በፊት የምናገኘውን ሙስሊም ማንነት ማወቅ አለብን። ስለ ራሱም ሆነ ስለ እኛ ሀይማኖት መሠረታዊያን ምን ያህል ያውቃል? በሀይማኖት ጉዳዮች ላይ ያለው ዕውቀት ቅንጹል ነውን ? በእስልምና እና ክርስትና መካከል ያሉትን ልዩነቶች የመረዳት አቅም አለው? ከሙስሊማኑ ጋር የምንስማማባቸው መዳረሻዎች ቢኖርም፤ በኃጢአት ምክንያት ከእግዚአብሔር መለየት እንዲሁም የእግዚአብሔር ጽድቅ እርቅን የማስገኙቱ አስፈላጊነት እምብዛም ከቁብ አይቆጥሩትም።

በዉይይታችን ሁሉ ውጤታማዎች እንዲያደርገን ጌታን ዘወትር  መጠየቅ አለብን። ክርስቶስ አማኞች ምን መናገርና ማሰብ እንዳለባቸው በሚቸገሩበት ወቅት መንፈስ ቅዱስ እንደሚረዳቸው ተስፋን ገብቷል።  በእምነት ጉዳይ የሚወያዩት ሁሉም ሙስሊማኑ አይደሉም፤ ስለሆነም ሪቻርድ ቶማስ " እግዚአብሔር ስለ ልጁ እንደሚገባ ስንናገር መስማት ይወዳል" እንዳለው  ስለ ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ መናገር ይኖርብናል።

ከሙስሊማኑ ጋር በተገቢው ሁኔታ ለመወያየት እንደ ሬቨረንድ ደብሊው ሴይንት /Rev.W.St/ ክሌር ቲስዳል የተሻለ መመሪያ አላገኘሁም። ከአስር አመታት በፊት በጽሑፉ የሚከተሉትን ዘመን ዘለል ጠቃሚ ምክሮች ለግሷል፡[11]

(1) ***ለመርታት ሲባል አለመከራከር***

*የውይይታችሁ ዋና ግብ ተቃዋሚዎቻችሁን ጸት ማሰኘትና አመክንአዊ ድል መጎናጸፍ ሳይኾን ነፍሳትን ወደ ክርስቶስ መምራት ነው። በሙግት ጊዜ መሰናክል የሚኾኑ ነገሮችን ማስወደግ ይኖርብናል።*

---

[11] ይህ ክፍል የተወሰደው ክሌር ቲስዳል ፣ በክርስትና ላይ የሚነሱ የሙሐመዳውያን ጥያቄዎች መምሪያ (ለንደን፣1904)፣ ገጽ 13-23።

*ነፍሳትን መቀየር አይጠበቅንም፤ ይህ የመንፈስ ቅዱስ ስራ ነውና የጸሎትና እምነት ድርሻችን ላይ እናተኩር። የሚመራመሩ ሰዎችን በተመለከተ ስህተትን ከመፈለግና ችግሮችን ከማሰስ ይልቅ እንዲጸልዩ፣ መጽሐፍ ቅዱስን በተለይም አዲስ ኪዳንን እንዲያነቡ መምራት ይኖርብናል።*

*(2) ትኩረት መስጠት*

*ውይይቱን በመገደብ ቀደም ብሎ ውሳኔ በሚያሻቸው አንድ ወይም ሁለት ነጥቦች ላይ ማተኮር ያስፈልጋል። የሚጠይቁ ሰዎችን ምላሽ ሳንታገስ ከአንደኛው ነጥብ ወደ ሌላው ማቻኮል ለጊዜ ብክነት ይዳርጋል። ሙግቱን ማጠቃለል (መወሰን) አስፈላጊ ስለሆነ ይህን ለማሳካት አስቀድሞ የውይይቱን ሂደትና ግብ ማቀድ ግድ ይላል።*

*(3) በውይይት ወቅት ምሳሌነትን ማስፈን*

*በሙግታችሁ ጊዜ ሙሉ ትኩረት መስጠት ብሎም ትሁታን መሆን ይጠበቅባችኋል። ሙግት በሌላ ጊዜ እንደሚደረገው አይነት ንግግር የማይኾንበት ወቅት አለ። ሙግት ታላቅ ውጤት እንዳለው አምናለው። በምትናገሩትና በምታሳዩት ባህሪይ ትሁታንና ቅኖች ከሆናችሁ፣ ሙስሊሙ በራሱ አሳብ የሚረታ፣ በመልካም ሁኔታም እንዲመለከታችሁ ለሚያደረገው ህግ የሚገዛ ይኾናል። ሙስሊሙ ክርስቶስ የሞተለት ብሎም የማስታረቅ መልዕክት እንድታደርሱለት የተጠራችሁለት ወንድም መኾኑን ማሰብ አለባችሁ። ሙግቱን በምንም ሳታሳዝኑ በትህትና ፣ በግልጽና በመልካም ባህሪይ ላትቀበሉ ወይም ላትስማሙ ትችላላችሁ። ክርክሩም ወደ አላስፈላጊ ግጭት እንዳያመራ መጠንቀቅ ይኖርባችኋል።*

*(4) ቁጣን መግታት*

*ሙስሊሙ በሙግት ወቅት ሊያስቆጣን እንደሚችል ማስታወስ አለብን። ቁጣችንን በማሳበቅ በሙግቱ ሂደት የሰዎችን አትኩሮት ወደ ራሱ በመሳብ በብዙዎች ፊት የተረታን እንደሆንን አድርጎ ሊጠቀምበት ይችላል። ትህትና በሚመስል አካሄድ እኛን በማስቆጣቱ የይስሙላ ይቅርታ በማሳየት በዙሪያ ያለውን ሁኔታ የመቆጣጠርና የማሳመን አቅምን ያገኛል፤ ቁጣ መሸነፍን ያሳያልና!*

*(5) የእምነትና ኃጢአት ትክክለኛ ግንዛቤ*

*ሙስሊሙ በመሰረታዊና ጠቃሚ ጉዳዮች ላይ ማተኮር እንዲችል መጣር አለብን ። የህይወት ወይም ሞት ጉዳይ መኾኑን በጥልቅት ማሳየት ይኖርብናል። ምንም እንኳ ለመጀመሪያ ጊዜ የሚያሸፍ ቢመስልም በኃላ ግን መካቱ አይቀርም ። እንደ እውነተኛ የክርስቶስ ምስክር በኃጢአት የሚወቀስበትን፦ አዳኝ የሚያስፈልግው መኾኑን ልንመራው ይገባል። ሙስሊማኑ ስለ ኃጢአት ያላቸው ግንዛቤ አናሳ ስለሆነ አእምሮቸውን ብቻ ሳይሆን ልባቸውን ጭምር ለመድረስ ጥረት መደረግ አለበት። ወንጌልን ለማድረስ እንደተላከ ሰው ክርስቶስ እንደ ሞተላቸው ድነትም እንደሚያስፈልጋቸው ልንነግራቸው ይገባል።*

### (6) ለመጉዳት ከሚገፋፋ ነገር መቆጠብ

በሙግት ጊዜ «ስለ መሐመድ ምን ታስባለህ?» የሚመሳሰሉ ጥያቄዎችን በምንመልስበት ወቅት ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርብናል፤ በእርሱ ላይም ክፉ ቃላት መሰንዘር የለብንም፡፡ ስለ መሐመድ ያለንን አመለካከት ብዙውን ጊዜ እንድናካፍላቸው ስለ ማይፈልጉ ፈጥኖ መንገሩ ተገቢ አይደለም ፡፡ በጊዜው መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ የራሳቸውን ግንዛቤ የሚደርሱ ስለኾነ፣ «ስለ መሐመድ ያለኝን አመላካከት ባካፍልህ ምን ይመስልሃል? ስለ ክርስቶስ? » የሚለውን በትህትና ማንሳቱ መልካም ይኾናል፡፡ ይህ ለሚሰሙን ግልጽ እና ትህትና የተሞላበት በመኾኑ አቀራረባችን በራሳቸው ስለ ኢየሱስ እንድንነግራቸው ጥያቄ የሚያነሱበት ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡

### (7) ስለ መሐመድ በአክብሮት መናገር

ክርስቲያኖች ስለ መሐመድ በሚናገሩበት ጊዜ ( በሺአ ሙስሊሞች አለለ ፣ ፋጤማ ወይም ክብር የሚሰጣቸው ሰዎች ጭምር ያካትታል) ተገቢው የስም ማዕረግ መጠቀም ይኖርባቸዋል፡፡ በአንዳንድ አገራት የማዕረግን ስም አለ መጠቀም አለ ማክበር ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ በህንድ «መሐመድ ሳሒብ» በኢራን ደግሞ «ሐዝራቲ መሐመድ » ተብሎ ይጠራል፤ ክርስቲያኖኑ ግን የማዕረጉን ስም አይጠቀሙም፡፡ በግብጽና መካከለኛ ምስራቅ « መሐመድ» የሚለው ስም ብቻውን ስለ ማይጠራ ነብዩ መሐመድ የሚለውን መጠቀም ያሻል፡፡ ለ «ኢየሱስ» «አዳኝ» ወይም «ጌታ» የሚለውን የማዕረግ ስም እንደምንጠቀመው ሁሉ፣ ሙስሊማኑ ኢየሱስን ጨምሮ ለማዕረግ ስም ትልቅ አክብሮት አላቸው፤ አለ በለዚያ እነርሱን እንደማቅለል ይቆጠራል፡፡

### (8) የነገረ መለኮት ብልሃትን ማስወገድ

ነገረ - መለኮትን በምንጠቀምበት ጊዜ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርብናል፡፡ በራሳችን የአፍ መፍቻ ቃል ተገቢውን ግንዛቤ መያዝ አለብን፡፡ «ቅድስና፣ ቤዛነት፣ ኃጢአት ፣ መንግስተ ሰማይ እና ሰላም» የመሳሰሉ ቃላት መጽሐፍ ቅዱስ ሁል ጊዜ በሚነገርበት ቋንቋ ነው የተሰናዱት፤ በመጀመሪያዎቹ ጊዜያት ክርስቲያናዊ የነገረ-መለኮት ትርጓሜዎችን ለሙስሊማኑ መስጠት ግራ መጋባት ያስከትላል ፡፡ በራሳቸው ቋንቋ ሊረዱት የሚችሉትን ፣ አስቀድመን የተገነዘብነውን መጠቀም ይኖርብናል፡፡

### (9) መጽሐፍ ቅዱሳዊ ውይይት ማድረግ

ሙስሊማኑ መጽሐፍ ቅዱስን በመጠቀስ ለሚያነሱአቸው ጥያቄዎች የመጽሐፍ ቅዱስን ምንባብ ክፍል አውዳዊ ትርጉም በትክክል መረዳት ያሻል፡፡ በራሳችን ማስተዋል መደገፍ የለብንም፡፡ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ ክፍልን በጥሞና ማንበብ አውዱ ለተነሳው ጥያቄ ትክክለኛውን ምላሽ እንዲሰጥ ያግዛል፤ ለቁርኣንም ይኸው አውዳዊ ትርጋሜ ይሰራል፡፡

### (10) የምናስበውን በቅጡ መረዳት

ከሙግት በፊት መጽሐፍ ቅዱስን ብቻ ሳይኾን በምንከራከረው ርዕስ ጉዳይ ዙሪያ ጥልቅ የሆነ ዕውቀት ሊኖረን ይገባል። በመሰረታዊ የክርስትና አስተምህሮዎች ላይ ምክንያታዊ ልንሆን ፣ መጽሐፍ ቅዱስ በውድቀት፣ ዘላለማዊ ተስፋ፣ ቤዛነት እና ሌሎችም ዙሪያ የሚያስተምረውን እና የማያስተምረውን ልናውቅ ያስፈልጋል።

### (11) በጋራ ጉዳዮች ላይ አጽኖኦት መስጠት

በክርስትና ብሎም እስልምና ዘንድ ለሚገኙ የጋራ እውነታዎች ክፍትና ግልጽ የሆነ የልብ ዝግጅት ያስፈልጋል። ይህን መነሻ በማድረግ መጽሐፍ ቅዱስ ሁሉንም እውነት የያዘ መኾኑን በማሳየት የእምነት መግለጫዎቻቸውን ሆነ የነገረ-መለኮት አስተምህሮቶቻቸውንም መመነት ይቻላል። ስለ ቁርአን በምንነጋገርበት ጊዜ ጥንቃቄና አክብሮት በተሞላበት ስሜት ሊኾን እንደሚገባው ላፍታም መዘንጋት የለብንም። በሁለቱም ሀይማኖቶች የሚገኙ የጋራ እውነታዎች እንደተጠበቁ ፣ የክርስትና አስተምህሮ በሚለይባቸው ጉዳዮች ላይ በነጻነት አድማጮችን በማክበር መናገር ያስፈልጋል።

### (12) ከማስተማር ይልቅ ማስረጽ ዘዴን መጠቀም

ሙስሊማኑን ለመረዳት በእነርሱ ቦታ ኾኖ ማሰብ ያሻል፤ ሊረዱት በሚችሉት ሁኔታም ምላሽ ማዘጋጀት ግድ ይላል። በሶክራጥስ ዘዴ መሰረት ጥያቄዎችን በመጠየቅ፣ መልሱን በራሳቸው እንዲያገኙ በመምራት ልናስተላልፍ የፈለግነውን እውነት ማስረጽ እንችላለን። «ከጸሎት በፊት ለምን መታጠብ አስፈለገ? » «አካላዊ ንጽህና ብቻ ነው የሚያመለክተው? ፈጣሪ ሁሉን ማድረግ የሚችል ከሆነ፣ በሰው መልክ ወደ እኛ መምጣት ያዳግተዋል? የሚሉት ጥያቄዎች ማንሳት እንችላልን።

### (13) ሙስሊማኑ ከሚቀበሉት ነገር መጀመር

እውነተኛ ሙስሊም የሚቀበለው እና የማይቀበለውን መለየት ይኖርብናል። ያንጊዜ የሙግታችን ይዘት ምን ላይ መመስረት እንዳለበት በመለየት ዘራችንን የት ቦታ ላይ መዝራት እንዳለብን ማወቅ ይኖርብናል።

(ሀ)ሙስሊማኑ የሙግት ጭብጥና አስፈላጊት በቁርኣን የፈጣሪ መጽሐፍ፡- በውስጡ ያለው ቃል መለኮታዊ ስልጣን መኾኑና በምንም ማመቻመች እንደ ማይቻል ባለው እሳቤ ላይ እንዲመሰረቱ ያደርገዋል።

(ለ) ሙስሊማኑ ታላላቅ አስተምህሮችን ይቀበላሉ፡- (1) የፈጣሪ አንድነት፣ ልዕልና፣ ጥበብ፣ ዘላለማዊነት፣ ህያውነት እና የመልካም ባህሪያት ሁሉ መገኛ

*(2) የአጥናፈ-ዓለም ፈጣሪ ፣ መለኮታዊ ገዢና መጋቢ (3) የአዳም፣ የኖህ፣ አብራሃም፣ ሙሴ እና ኢየሱስ መለኮታዊ ተልዕኮነት (4) በፈጣሪና በፍጥረት መካካል ያለ መለኮታዊ ልዩነት (5) የአለም ህላዌነት፣ የሰው ኃላፊነት፣ የሰው መንፈስ፣ ከሞት በኃላ ህይወት መኖሩ፣ የዘላለም ሽልማትና ቅጣት፣ ትንሳኤ፣ የእምነት አስፈላጊነት፣ መልካምና ክፉ መናፍስት (6) የክርስቶስ መለኮታዊ ተልዕኮ፣ ከድግል መወለዱ፣ ያለ ኃጢአት መኾኑ (ሁሉም ነብያት በሙስሊማኑ ኃጢአት የሌለባቸው እንደሆኑ ይታመናል)፣ ዕርገቱ፣ አሁን በገነት የሚኖር መኾኑ፣ ዳግም ምጽአቱ ፣ ክርስቶስ "የፈጣሪ ቃል" (ካሊሙት አላህ) እና "ከእርሱ የወጣ መንፈስ" መኾኑ (ሱረቱ 4፥171)፤ (7) የመጽሐፍ ቅዱስ ዋናው ቅጂ መለኮታዊ መገለጥነት (8) ጣኦታትን ማምለክ ይቅር የማይባል ኃጢአት መኾኑ (ሱረቱ 4፥48፣116)።*

*በአንጻሩ አንድ ሙስሊም በኃጢአት ወቀሳና በዘላለማዊ የሞራል ህግ ማመን ያዳግተዋል። ስለ ፈጣሪ ቅድስና፣ ፍትህ እና ፍቅር እውነተኛ መረዳት የለውም ። በእስልምና የፈጣሪ ሁሉ አዋቂነት ሌሎች ባህሪያትን አጠቃልሎ መያዙ በተለምዶ ይታመናል። ቤዛነት፣ ሥላሴ፣ የክርስቶስ ልጅነት እንዲሁም የመስቀል ሞት ለሙስሊሙ አንዳች ፋይዳ እንዳለው ተደርጎ አይወሰድም ። በእስልምና መጽሐፍ ቅዱስ ለመሐመድ በተሰጠው ቁርአን መተካቱ በጽኑ ይታመናል።*

*ዘጠና ከመቶ የሙስሊማኑ ተቃውሞና ትርጓሜ የተመሰረተው በራሳቸው ስጋዊ አስተሳሰብ ላይ ነው። የእኔ ትልቁ ጥረት መንፈሳዊ የሆነውን አስተምህሮ በማደላደል በሀይማኖት ውስጥ ያለውን እውነታ ማትረፍ ነው። ለምሳሌ ፦ ከጸሎት በፊት የሚደረገው የመታጠብ ስርዐት ሌላ መንፈሳዊ እውነታ እንዳለው ሙስሊሙ አይረዳም፤ ስለሆነም ይህን በመጠቀም የጸሎት ባህሪይ ምን እንደሆነ ፣ ወደ ፈጣሪም እንዴት መቅረብ እንደሚቻል፣ መንፈሳዊውን እውነታ በመንተራስ ሙስሊሙን መሞገት እችላለሁ።*

*በተመሳሳይ ሁኔታ ስለ ጺም መቆረጥ፣ ስለ አለባበስ፣ የራስ ላይ መሸፈኛ ልብስ ማድረግ ወይም ማውለቅ የመሳሰሉ ጉዳዮችን በመጠቀም በሀይማኖት ውስጥ ተሰውረው ያሉትን እውነታዎች ለመወያየት በር ይከፈታል። ከጸሎት በፊት በሚያደርጉት የመታጠብ ስርዐት ከውጫዊው እንድምታ ባሻገር ምን ማለትና ምን ማሰብ እንዳለባቸው መንፈሳዊውን እውነት እንዲረዱት ማገዝ ይቻላል።*

***(14) ጸሎት***

*ወንጌል የሚያደርስ ሰው የቤንጌልን ምክር ማስታወስና መተግበር ይኖርበታል፦ « እውነት፣ ፍቅር ፣ አላማ ሳይኖርህ ወደ ክርክር አትግባ » ያለ ጸሎት የሚለው ሳይዘነጋ!*

**የግል ማስታወሻ**

*3*

# መሐመድ

## I. ቅድመ - እስላማዊ ዓርብ

መሐመድ በስድስተኛው ክፍለ ዘመን የአረብ ባሕረ-ገብ ስሙ-ጥር ወንጌላዊ ይሆን እንደ ነበር ማሰብ ተገቢ ነው። መሐመድ በእርግጥ የክርስትና ፣ የይሁዲ፣ ሳቢያንና ሐኒፋይትስ ሀይማኖት ክፍሎች አስተምህሮ ተጽዕኖ እንደነበረው ይታወቃል።

### 1.ይሁዲነት

ይሁዲነት በአረብ ባሕረ-ገብ ሊታወቅ የቻለው ቲቶ በ70 ዓ.ም ኢየሩሳሌምን ማፍረሱን ተከትሎ በተሰደዱ አይሁዳውያኑ ነው። አንዳንድ ባለጠጋ አይሁዳውያኑ በያትሪብ፣ የመን እና ሌሎች ስፍራዎች ይኖሩ ነበር። ብልጽግናቸው የተመሰረተው በእርሻ፣ ገንዘብ በማበደር፣ የጦር መሳሪያዎችን በመነገድ፣ ጌጣ ጌጦችን በመሸጥ ላይ ነው። አይሁዳውያኑ "ቅዱስ መጽሐፍ" ስላላቸው አረቦች ያከቡሯአቸው ነበር ።

መሐመድ ከይሁዲ ቅዱሳት መጻሕፍት ጋር ቁርኝት እንደነበረው በቁርኣን ውስጥ የሚገኙ ክፍሎች አስረጂ ናቸው። ሱረቱ 3 አል-ኢምራን (የኢምራን ቤተሰቦች፣ የሙሴ አባት)፣ ሱረቱ 10 ዩኒስ (ዮናስ) ፣ ሱረቱ 12 የሱፍ ( ዮሴፍ)፣ ሱረቱ 14 ኢብራሒም (አብርሐም)፣ ሱረቱ 71 ኑህ (ኖህ) ተብለው ተሰይመዋል። ቁርኣን ስለ ዘጸአት በሱረቱ 2፥49፣50 ላይ ይናገራል። መሐመድ ለአይሁዳውያኑ በሙሴ በኩል ስለ ተሰጠው የፈጣሪ መገለጥ ያወሳ ነበር። ቁርኣን "ለእስራኤል ልጆችም መጽሐፍንና ሕግን፣ ነቢይነትንም በእርግጥ ሰጠናቸው፤ ከመልካም ሲሳዮችም ለገስንላቸው በአለማት ላይም አበለጥናቸው" ይላል ( ሱረቱ 45፥16)።

አረቦች አይሁዳውያኑ ስለ ድንግል መውለድ፣ ሥላሴ፣ መለኮት፣ የክርስቶስ ሞትና ቤዛነት አስተምህሮ ያዛቡ እንደሆነ ይገነዘባሉ። ቁርኣን የእስራኤልን ውድቀት ይወቅሳል፦ "ቃል ኪዳናቸውንም በማፍረሳቸው፣ በአላህም አንቀጾች በመካዳቸው፣ ነቢያትንም ያለ አግባብ በመግደላቸውና ልቦቻችን ሽፍኖች ናቸው በማለታቸው ምክንያት፣ (ረገምናቸው) ፤ በውነቱ በክሕደታቸው ምክንያት አላህ በርሷ ላይ አተመ፤ ስለዚህ ጥቂትን እንጂ አያምኑም።

በመካዳቸውም፣ በመርየም ላይ ከባድ ቅጥፈትን በመናገራቸውም ምክንያት፣ (ረገምናቸው)" (ሱረቱ 4፥155፣156)።

በሁለተኛው ክፈለ ዘመን በአረብ ባሕረ-ገብ የማይዘነጋ የይሁዲ ክፍሎች ኢቦዮናይትስ ናቸው። እነርሱም ኢየሱስ መሲህ፣ የዳዊት ልጅ እና ታላቅ የሕግ መምህር በመኾኑ ላይ ይታመናሉ። ሆኖም እንደ ሙሴ መሲህነትን የተቀበለ ሰው ይኸውም በጥምቀት ጊዜ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የተዋሃደ አድረገው ነው የሚቀበሉት። የአሌክሳንደሪያው ኦሪገን ኢቦዮናይተስ "የዳዊት ልጅ ማረኝ" ብሎ እንደጮኸው ሰው ናቸው፤ ኢየሱስ ማን እንደ ነበር ያላቸው መረዳት አናሳ ነው ብሏል።

## 1. ክርስትና

መሐመድ በተልዕኮው ጅማሬ ለክርስትና መልካም ዝንባሌ እንደ ነበረው መገንዘብ ይቻላል።

> *ሱረቱ 5፥69፣82*
>
> *ያመኑና እነዚያም ይሁዳውያን የኾኑ፣ ሳቢያኖችም ክርስቲያኖችም፣ (ከነርሱ) በአላህና በመጨረሻው ቀን ያመነና መልካምን ሥራ የሠራ ሰው፣ በነርሱ ላይ ፍርሃት የለባቸውም፤ እነርሱም አያዝኑም። ይሁዶችንና እነዚያን ያጋሩትን፣ ለነዚያ ለአመኑት በጠላትነት ከሰዎች ሁሉ ይበልጥ የበረቱ ሆነው በእርግጥ ታገኛለህ፤ እነዚያንም እኛ ክርስቲያኖች ነን ያሉትን ለነዚያ ለአመኑት በወዳጅነት በእርግጥ ይበልጥ የቀረቧቸው ሆነው ታገኛለህ፤ ይህ ከነሱ ውስጥ ቀሳውስትና መነኮሳት በመኖራቸውና እነሱም የማይኮሩ በመሆናቸው ነው።"*

በአብዛኛው የአረብ ባሕረ-ገብ ለመድረስ የነበረው የክርስትና አስተምህሮ ሱሑትነት ነበረው። የዚህ አይነተኛ ምክንያትም የአረብ ባሕረ-ገብ በሮማ ግዛት ስር አለመሆኑና የስህተት አስተምህሮቶቹ ከአውዱ የራቁ መሆናቸው ነው። በዚህም ክርስቲያናዊው መሐመድ ከእውነተኛው የክርስትና አስተምህሮ እንዲርቅ ሆኗል።

## (ሀ) ሞኖፊሳይትስ

በሮማ ግዛት የተፈጠረው ሀይማኖታዊ ቀውስ ሞኖፊሳይትስን ወደ አል -ሂራአ እንዲሰደዱ አድርጓል። የክርስቶስ ማንነት መለኮታዊ ነገር ግን የሰው ባህሪይ የተላበሰ መኾኑ ላይ ይታመናሉ። ክርስትናን ለማስፋፋት ከሶሪያና ኢራቅ የመጡ ሲሆን፣ የ(ገ)ሐሰን ነገድ ወደ

ሞኖፌሳይትስ እምነት ተለውጧል፡፡ እነርሱም በ518 ዓ.ም ገዳማት ፤ በ 424 ዓ.ም ኦማን እና በ575 ዓ.ም ባህሪን ቀሳውስት የነበሩአቸው መሆኑን መዛግበት ያስረዳሉ፡፡

## (ለ) ኔስቶሪያንስ

ኔስቶሪያንስ ክርስትና ወደ አል -ሃይራ ቀደም ብሎ የገባው በ410 ዓ.ም የገዳማት መገንባት ተከትሎ ነው፡፡ ኔስቶሪያንስ በክርስቶስ ሁለት የተለያዩ ስብዕናዎች፡- አንዱ ሰዋዊ ሌላው መለኮታዊ በመሆኑ ላይ ይታመናሉ ፡፡ ይህ ትምህርት ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ሰው ፍጹም መለኮት (ሁለቱ የማይከፋፈሉ ናቸው) ከሚለው እውነተኛ ትምህርት ይለያል፡፡

ኔስቶሪያንስ ከኢትዮጵያ ወደ የመን የተሰደዱት በ525 ዓ.ም ነበር፤ ወንጌልን ከማድረስ ይልቅ ንግድን በማስፋፋት ላይ ትኩረት በማድረግ ፤ በአረብ ባሕረ-ገብ ደቡባዊ ክፍል መስፈራቸውን ታሪክ ይዘግባል፡፡ በመሐመድ ዘመን የኔስቶሪያንስ ታዋቂና ተጽዕኖ ፈጣሪ የነበረው ዋራቃ ኢቡኑ ኖፋል የመካ መጋቢ እና የመሐመድ መጀመሪያ ሚስት (ከደጃ) የአጎት ልጅ ነበር፡፡ ዋራቃ የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 1-25ን ወደ አረብኛ ተርጉሟል፡፡ የተቀሩትን ሶስት ምዕራፎች ያስወገደበት ምክንያት በስቅለትና በትንሳኤ የማያምን ስለነበር ነው፡፡

## (ሐ) ማርያማትስ

የማርያማትስ ተከታዮች ቬኑስን የሚያመልኩ ነበሩ፤ ወደ ክርስትና በሚለወጡበት ጊዜ ድንግል ማርያምን ማምለክ ጀመሩ፣ የሥላሴ አካል በሆነው መንፈስ ቅዱስ ፈንታ እርሷን ከፍ ያደርጉ ነበር፡፡ መሐመድ ይህን ኑፋቄ አውጉዟል፡-

***ሱረቱ 5፥116፡-***

*"አላህም፡- የመርየም ልጅ ዒሳ ሆይ አንተ ለሰዎቹ፡- እኔንና እናቴን ከአላህ ሌላ ሁለት አምላኮች አድርጋችሁ ያዙብለሃልን? በሚለው ጊዜ (አስታውስ)፤ ጥራት ይገባህ፤ ለኔ ተገቢዬ ያልሆነን ነገር ማለት ለኔ አይገባኝም፤ ብዬው እንደሆነም በእርግጥ አውቀኸዋል፤ በነፍሴ ውስጥ ያለውን ሁሉ ታውቃለህ፤ ግን ዘንድ ያለውን አላውቅም፤ አንተ ሩቆችን ሁሉ በጣም ዐዋቂ አንተ ብቻ ነህና ይላል፡፡"*

### (መ) ዶሴቲዝም

ይህ ኑፋቄ የክርስቶስን ፍጹም ሰውነት የሚክድ ነው፡፡ የስሙ መገኛ የግሪኩ “dokein” ሲሆን፣ ትርጓሜው የሚመስል ማለት ነው፡፡ ዶሴትዝም ቁስ ከመንፈስ ያንሳል ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛ ሰው ሳይሆን፣ ሰውን መስሎ ነው የመጣው የሚለውን እሳቤ ያራምዳል፡፡ እሳቤው የኢየሱስ ሰውነት በውልደት የተገኘ ፣ በመስቀል የተወገደ ፣ ሰዋዊው ባህሪይ ከሰማይ /ዘላለማዊ / ዘንድ መሆኑን ያመላክታል፡፡ ዶሴቲዝም የኢየሱስን ስጋ መልበስ /ሰው መሆን/፣ ቤዛነትና ትንሳኤ አስተምህሮን ይክዳል፡፡ ከዚህም በመነሳት ኢየሱስ በአይሁዳውያኑ አመለካከት በመስቀል ላይ እንደተሰቀለ ተመስሏል በማለት መሐመድ ያስተባብላል (ሱረቱ 4፥ 157ን ይመልከቱ)፡፡

### (ሰ) አርያኒዝም

አርያኒዝም በፈጣሪ አንድነትና ምጡቅነት የሚያጠነጥን ኑፋቄ ነው፡፡ ይህ አስተምህሮ ክርስቶስን የተፈጠረ ሰው ፣ የአባቱም ጥገኛ አድርጎ ይወስዳል፡፡ በወርኀ ግንቦት 325 ዓ.ም የተካሄደው የኒቂያ ጉባኤ ክርስቶስ “የተወለደ እንጂ ያልተፈጠረ፤ ከአብ ጋር እኩል የሆነ” የሚለውን እውነተኛ አምነት በማረጋገጥ አርያኒዝምን አውግዟል፡፡

## 2. ሳቢያንስ

ቁርአን ሳቢያንስን ከሙስሊማኑ፣ አይሁዳውያኑ እና ክርስቲያኑ ጋር በማያያዝ ሦስት ጊዜ ይጠቅሳል፡፡ “እነዚያ ያመኑና እነዚያም ይሁዳውያን የኾኑ፣ሳቢያኖችም ክርስቲያኖችም፣ (ከነርሱ) በአላህና በመጨረሻው ቀን ያመነና መልካምን ሥራ የሠራ ሰው፣ በነርሱ ላይ ፍርሃት የለባቸውም፤ እነርሱም አያዝኑም” (ሱረቱ 2፥62፣ 5፥69፣ 22፥17)፡፡ ስያሜው ከዕብራይስጡ ሳባ ቃል የተገኘ ሆኖ ማጥመቅ የሚለውን ትርጓሜ ይይዛል፤ በሩቅ ምስራቅ የይሁዲ ክርስትና የጥምቀት ልምምድን ለማሳየት ጥቅም ላይ ውሏል፡፡

ቃሉ የአረማውያንን እምነት ያመለክታል፡፡ እነዚሁ ቡድኖች ለአይሁዳውያኑ እና ክርስቲያኑ ሊኖር የሚገባውን መቻቻል ለማስጠበቅ ስያሜውን ተጠቅመውበታል፡፡ ኮከቦችን የሚያመልኩ በመሆኑ የጸሐይ ጭፍሮችን ወይም ፕላኔቶችን “አባት” ፤ የጸሐይ ጭፍሮች አካላትን “እናት”

ብለው ይጠራሉ። ካእባአ ፊት ለፊት በቀን ሰባት ግዜ ይጸልዩ ነበር።[12] የቀብር ጸሎት ሳይንበረከኩ ወይም ግንባራቸውን ሳይደፉ ይጸልያሉ፣ በዓመት አንድ ጊዜ ለአንድ ወር ያህል ይጾማሉ፣ ግርዛትን ይፈጽማሉ ፣ የመካ ጉዞ ያደርጋሉ። ከሕግ ውጪ ሁለት ማግባት፣ ያሳማ ሥጋ መብላት፣ የሞተ ሥጋና ደም ይከለክላሉ፤ በፍርድ ውሳኔ ያገኘውን ፍቺ ይፈቅዳሉ። እስልምና አያሌ አስተምህሮችን ይጠብቃል።

### 4.ሃኒፋይትስ

ሃኒፋይትስ የሚለው ስያሜ "እራሳቸውን ከሀሳዊ ሀይማኖት በመጠበቅ እውነተኛ የሆነውን ሀይማኖት ማለትም ሰማይና ምድርን የፈጠረ አምላክ የሚያመልከውን የአብርሃም ልጅ አስማኤልን ለሚከተሉ"[13] የተሰጠ ነው።

ሃኒፋይትስ አመንዝራነት፣ ይሁዲነትን እና ክርስትናን አይቀበሉም። መንጻት፣ ግርዛት ፣ በዋሻዎች መጸለይ እና ጥሞና ስርአቶችን በመደበኛነት ይፈጽማሉ። አመንዝራነት፣ የብድር ወለድ፣ የአልኮል መጠጥ፣ የአሳማ ሥጋ፣ አዲስ የተወለዱ ሴት ህጻናትን መሰዋትና የመሳሰሉ ተግባራት የተወገዙ ናቸው። ሌቦች እጆቻቸው እንዲቆረጥ ፣ አመንዝራዎች በድንጋይ እንዲወገሩ፣ አልኮል የሚጠጡ በጅራፍ እንዲገረፉ የማድረግ ቅጣቶችም ይከናወናሉ። ሃኒፋይትስ የመሐመድን መልዕክት በመቀበል የመጀመሪያዎቹ በመሆናቸው ስርአቶቻቸው በአብዛኛው ለእስልምና እሳቤዎች እና ሰበካዎች መሰረት ሆኗል።

## II. የመሐመድ ህይወት

መሐመድ ( የስሙ ትርጉም የተመሰገነ ) ከኩሪሽ ነገድ በመካ 570 ዓ.ም አካባቢ ተወለደ።

የምንጊዜም ታላቁ ተጽዕኖ ፈጣሪ፣ የእስልምና ነብይ ፣ "ለፈጣሪ ፍቃድ ፈጽሞ የተሰጠ" ተብሎ ይጠራል። የመሐመድ አባት የአብዱል ሙጠሊብ ልጅ የሆነው አብደላህ፣ እናቱም አሚና ነበረች።

መካ ከጅዳ ወደብ ሰማንያ አምስት ኪሎ ሜትር ርቃ የምትገኝ፣ በመሐመድ ዘመን የአረብ ባሕረ-ገብ ጠቃሚ የንግድና መንፈሳዊ ማዕከል ናት። የመካ ሰዎች ከየመን ወደ ሶሪያ የሚጓጓዙ ነጋዴዎችን በገንዘብ የሚደግፉ ፣ በስተምዕራብ ደግሞ ምግብ፣ ሃር ጨርቅና

---

[12] በታለቁ መካ መስጊድ ግቢ ትንሹ ግንብ ፣ ታዋቂው ጥቁር ድንጋይ። ካእባአ የተጓዦች፣ አምልኮ እና ጸሎት ማዕከል።

[13] ጊብ ኤች ኤ አር እና ክራመርስ ፣ ጄ ኤች (ኤዲተርስ)፣ የኢስላም ዐውደ ጥበብ፣ ሌይደን፡- ኢ ጄ ብሪል 1974፣ የሐኒፋይትስ ርዕስ።

የቅንጦት እቃዎችን የሚያቀርቡ ነበሩ፡፡ እነዚህን ሸቀጣሸቀጦች ከህንድ መርከቦች ኤደን ከተሸመተ በኃላ፣ ነጋዴዎች ወደ ሰሜናዊ መካ በማጓጓዝ ወደ ሶሪያና ግብጽ ያሰራጩት ነበር፡፡ መካ ወሳኝ የምስራቅ ንግድ መዳረሻ ስፍራ ናት፡፡
መንፈሳዊ ጉዞ የሚያደርጉ ሰዎች ከተለያዩ አጎራባች ቦታዎች ለአምልኮ ወደ መካ ይጓዛሉ፡፡ በመካ ካእባአ ተብሎ የሚጠራው ታዋቂ ጥቁር ድንጋይ ለመቶ ዓመታት የጣኦት አምልኮ ዋና ማዕከል ሆኖ አገልግሏል፡፡ አዳምና ሔዋን ከገነት ሲባረሩ አራፋት በሚባለው ቦታ እንደተገናኙ፣ ከዚያም መካ ወደሚገኝበት ምዕራባዊ ሸለቆ ቦታ በመድረስ፣ አዳም በአራት ማዕዘን ቅርጽ የሚመሰል ጥቁር ድንጋይ መገንባቱ በእስልምና ይነገራል፡፡

ከኖህ ጥፋት በኃላ ግንባታው ከአሸዋ በታች ወድሟል፤ ሆኖም በፈጣሪ ትዕዛዝ አብራሐምና ልጁ እስማኤል ፍርስራሹን በመቆፈር በድጋሚ መገንባታቸው ይታመናል፡፡ ቁርኣን “ኢብራሂምና ኢስማኤልም «ጌታችን ሆይ! ከእኛ ተቀበል፡፡ አንተ ሰሚውና ዐዋቂው አንተነህና» የሚሉ ሲኾኑ ከቤቱ መሠረቶቹን ከፍ ባደረጉ ጊዜ (አስታውስ)” ብሎ ይናገራል (ሱረቱ 2፥127)፡፡ ሙስሊሞች ካእባአ የፈጣሪ የመጀመሪያ፣ በታሪክም የምንጊዜ ቤት እንደሆነ ያምናሉ፡፡

በአረብ ባሕረ-ገብ ሃያ ካባዎች በተለያየ ጊዜና ቦታ እንዳሉ ይታወቃል፡፡ በአያሌዎች ዘንድ እጅግ ክብር የሚሰጠው ግንብ በመካ የሚገኘው ነው፡፡ በመሐመድ ዘመን ሶስት መቶ ስልሳ የተለያዩ ጣኦቶች በካእባአ ዙሪያ ይመለኩ ጸሎትም ይደረግባቸው ነበር፡፡

## 1.የመሐመድ ልጅነት ጊዜ

ከውልደቱ በኃላ መካን ወዲያው ነበር የለቀቀው፡፡ በመካዎች ልማድ መሰረት ወደ በረሃ በመሄድ በዘላን አሳዳጊ ሴት እንዲያድግ ተደረገ፡፡ ሐሊማ በምትባለው ሴት አሳዳጊና ቤን ሳድ ነገድ ስር የመጀመሪያ አምስት ዓመት ጊዜውን አሳልፏል፡፡ በዚህም መንገድ ጤናማ ዕድገት፣ በአረቦች ቅዱስ ተደርጎ የሚቆጠረውን የበረሃ-ንግድ ዘዬን እና አንደበተ ርዕቱነትን አትርፏል፡፡

መሐመድ ከሦስት ዓመት ዕድሜው በፊት “ሁለት ነጫጭ ልብስ የለበሱ ወንዶች ” ወደ እርሱ በመቅረብ የሆዱን መቀነት ከፍተው አካሉን እንደነኩት መዛግብት ይናገራሉ፡፡ ሃሊማ ወደ እናቱ በመውሰድ የሚጥል በሽታ መሰል ነገር እንደገጠመው፣ የክፉ መንፈስ ተጽዕኖም እንዳለበት ትነግራታለች፡፡ አሚናም አምስት አመት ሲሞላው መልሳ እንድታመጣው

ታሳምናታለች። ሙስሊማኑ የመሐመድን ልጅነት ልምምድ ሁለት መላዕክት እየቀደሱትና ለመልዕክቱም እያዘጋጁት እንደበር ይገልጻሉ።

*ሱረቱ 94፥1-3*

*ልብህን ለአንተ አላሰፋንልህምን? (አስፍተንልሃል)። ሸክምህንም ካንተ አውርደንልሃል። ያንን ጀርባህን ያከበደውን (ሸክም)።*


የሙሐመድ አባት አብዱላህ ሙሐመድ ከመወለዱ በፊት ሞተ። እርሱም ስድስት ዓመት ሲሞላው እናቱ የአስራ አንድ ቀን ጉዞ ወደሚፈጀው የትውልድ ሃገሯ ሰሜናዊ ያትሪብ ወሰደችው። ከጉዞው መልስ ታማ ስለነበርም፣ ህይወቷ በማለፉ አቡድል ሙታሊብ የተባሉ የሰማንያ አመት አዛውንት አያት እንዲያሳድጉት ሆነ። ከሁለት ዓመት በኃላ እኚህ አያት በመሞታቸው ለአጎቱ አቡ ታሊብ ተሰጠ።

## 2.የሶሪያ ጉዞ በአስራ ሁለት ዕድሜ

የመሐመድ የልጅነት ታሪክ ዝርዝር በአመዣኙ ልማዳዊ በመሆኑ በግልጽ ማስቀመጥ ያዳግታል። በአስራ ሁለት አመቱ ከአጎቱ አብዱ ጣሊብ ጋር ወደ ሶሪያ ወራትን የፈጀ ጉዞ አድርጓል። በዚያም ለመጀመሪያ ጊዜ ከሶሪያ ክርስቲያኖች ጋር መገናኘት ቻለ።

ቁርኣን ስለ ክርስትና ያለው አተያይ የተቀረጸው በዚሁ የጉዞ ወቅት ነበር። የመሐመድ እውነትን የማወቅ ፍላጎት አስቀድሞ የተመሰረተው በኢየሱስ ትምህርቶች ላይ እንደ ነበር መገመት አያዳግትም ። ከዚህ የተነሳ ከክርስቲያን መኖክሴ ጋር ጓደኝነት መስርቶ ነበር። ዊልያም ሙር የተባለው ተመራማሪ ግን እንደሚከተለው ያስቀምጣል፡-

*እግዚአብሔር በልጁ በኩል ሰዎችን ሁሉ ለማዳን ከገለጠው የወንጌል መልእክት ይልቅ፣ የሥላሴ አስተምህሮ ቀናኢ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ አምልኮተ ማርያም አስምልክቶ የሥላሴ አካል ሳትሆን እንደ አምላክ ተደርጋ መወሰዷ ፣ የመሐመድን አግርሞት ስቧል፡፡*[14]




[14] ዊሊያም ሙር፣ ሙሐመድ እና እስልምና (ለንደን ፣ የሀይማኖት ጽሑፍ ማህበረሰብ፣ ኤን ዲ) ገጽ 9፡፡

## 3. ስውሩ ዓመታት

ከአስራ ሁለት ዓመት ጀምሮ እስከ ሃያ አምስት ያለው ወቅት "ስውር ዓመታት "ተብሎ ይጠራል። መሐመድ በመካ አቅራቢያ ከፍታዎች በግና ፍየሎችን እየጠበቀ፣ አልፎ አልፎም የዘላን ጉዞ እያደረገ መቆየቱ ይታመናል። መሐመድ በጎረቤቶቹና ጓደኞቹ ጭምትና ቁጡ አይነት ሰው ተደርጎ ነበር የሚታየው። ዊሊያም ሙር በሚከተለው መልኩ ይገልጸዋል፡-

*ስለ መሐመድ ወጣትነት ዕድገት የተነገረን ጥቂት ነው። ከመካ የሦስት ቀን ጎዞ በሚፈጀው፣ የአረብን ማንነት በመቅረጽ ኩራት በሆነው ዓመታዊ የግጥምና ንግግር ችሎታ ውድድር ላይ ይካፈል ነበር። በዚህ ውድድር ላይ አይዳውያኑ እና ክርስቲያኑ በማግኘት ከአመለካከቶቻቸው ጋር ትውውቅ ያደርግ ነበር። የኃላ ኃላ የናጅራን ኤጰስ ቆጶስ "የአብርሐም እምነት ስብከት" ብሂልን ይጠቅሰው ነበር።*

*አርቆ አሳቢነቱና ብሩህ አእምሮን በመጎናጸፉ ከእራሱ ጋር አያሌ ምቹ ጊዜያቶች እንዲኖሩት ሆኗል። መልካም ባህሪው እና ተወዳጅ ስብዕናው በተከታዮቹ ዘንድ አል -አሚን ማለትም ታማኝ የሚል ስም እንዲኖረው አድርጎታል።*[15]

## 4.ከድጃ ቀዳማዊት ሚስት

መሐመድ ሃያ አምስት ዕድሜ ሲሞላው ከድጃ የምትባል ሐብታም መበለትን ማገልገል ጀመረ። በስራውም ታማኝ ሰለ ነበር የእርስዋ ተጓዥ ነጋዴዎች አንዱ ሆነ፤ በዚህም እንደገና ሰሜናዊውን ክፍል የመጎብኘት፣ ከደማስቆ እስከ አሌፖ ድረስ የመሄድ እድልን አገኘ። ከድጃ በርሱ ስለ ተማረከች በእህቷ አማካኝነት የጋብቻ ጥያቄ እንዲቀርብ አደረገች።

መሐመድ ፍላጎት ሳይኖረው ጥያቄውን ተቀበለ። ሆኖም የከድጃ አባት ስምምነቱን ተቃውመው ነበር፤ ከድጃ ግን ትልቅ ድግስ በመደገስ ፣ አባትዋ በመጠጥ ስካር ውስጥ ሳለ የላምን እርድ በመፈጸም የጋብቻ ስርአቱን በአጎቷ ልጅ የመካ መጋቢ ዋራቃ ኢቡን ኖፈል አማካኝነት አከናወነች። ከድጃ መሐመድን በአምሳ ዕድሜ ትበልጠው ነበር፤ ከቀድሞ ጋብቻዋ አንድ ሴት እና ሁለት ወንድ ልጆች ነበሩዋአት። ከመሐመድም ጋር ደስተኛ ሕይወት ነበራቸው፣ ሁለት ወንድ እና አራት ሴት ልጆችም አፍርተዋል። ሴት ልጆቹ በህይወት ሲቆዩ ወንድ ልጆቹ ግን በጨቅላነታቸው ነበር ህይወታቸው ያለፈው።

---

[15] ዊሊያም ሙር፣ ኦፐ ሲት ገጽ6፣7።

## 5. የመጀመሪያው መገለጥ

ሙሐመድ ትዳሩ በፈጠረለት ሐብትና አንቱታ  በመካ ሕዝባዊ ምክር ቤት ድርሻ ብሎም ነገሮችን በጥሞና የሚያይበት አመቺ ጊዜ እንዲኖረው ሆኗል፡፡ በጥልቀትም የሚያሰላስልበት ልምምድ በምድረ በዳ ከፍታ ቦታዎች እና ዋሻዎች ላይ ያደርግ ነበር ፡፡ ከመካ  ጥቂት ኪሎ ሜትር ርቆ በሚገኘው ሀራራ ተራራ ሰሜናዊ ዋሻ በአንደኛው ቀን ራዕይን ተመለከተ፡፡

ኢብኑ ኢሻቅ የተባለው የመሐመድ ግለ-ታሪክ ጸሐፊ እንዳ ሰፈረው መጻኢው ነብይ ጅብሪል እስኪ ገለጥለት ድረስ በከባድ እንቅልፍ ነበር፡፡ መልአኩም "አንብብ!" ሲል አዘዘው፡፡ በፍርሃትና መንቀጥቀጥም "ምን ላንብብ?" መሐመድ መለሰ ፡፡ መልአኩም አንገቱን በነካው ጊዜ ጉሮሮው ተያዘ፡፡ "አንብብ!" መልአኩ በድጋሚ አዘዘ፤ መሐመድ አሁንም ባለበት ሁኔታ፣ ለሦስተኛ ጊዜ "አንብብ!" መልአኩ አዘዘ ፡- "አንብብ በዚያ (ሁሉን) በፈጠረው ጌታህ ስም፡፡ ሰውም ከረጋ ደም በፈጠረው (ጌታህ ስም)፡፡ አንብብ ፤ጌታህ በጣም ቸር ሲኾን፤ ያ በብርዕ ያስተማረ ፡፡ ሰውን ያለወቀውን ሁሉ ያሳወቀ ሲኾን" (ሱረቱ 96፥ 1-5)፡፡

የመሐመድ ልምምድ የእውነተኛው ፈጣሪ (አላህ) ነብይ የመኾኑ ማረጋገጫ ተደርጎ ተወስዷል፡፡ አላህ የሚለው ስም በብሉይ ኪዳን ለእግዚአብሔር መጠሪያነት ከዋለው የዕብራይስጡ ኤሎሂም ስም ጋር አቻ እንደሆነ ይታመናል፡፡ መሐመድ ወደ ባለቤቱ በመመለስ "እንደ ብርቱ እሳት የመሰለ ነገር በእኔ ላይ እየነደደ ነው" .. እያለቀሰም "ያጠፋልኝ እንደሆነ ውሃ አምጭልኝ" ብሎ ነገራት ፡፡ ከጉድጓድም ውሃ በማምጣት ከድጃና ባለሚልዎቿ በባለቤትዋ ራስ ላይ አፈሰሱ፡፡ በሰውነቱ ላይ የሚነድደውን ሙቀት ለማስወገድም ብዙ ባልዲ ውሐ አስፈልጓቸው ነበር፡፡ የሚያንቀጠቅጠው ነገር ሻል ሲል ከድጃ ወፍራም ጨርቅ በመሸፈን አልጋ ላይ እንዲያርፍ አደረገች፡፡

## 6. የመሐመድ መገለጥ ሁናቴ

ከመሐመድ ጋር በአንድ ዘመን የኖሩ መገለጡን በሚቀበልበት ጊዜ የነበረውን ሁናቴ ተናግረዋል፡-

**ኢቢኑ ሳይድ**

*በመነቃቃቱ (መገለጡ) ቅጽበት ታላቅ ድንጋጤ በነብዩ ላይ ሆኗል፤ ፊቱም ያስፈራ ነበር፡፡ እንደሰከረ (በእንቅልፍ እንደተሸነፈ) ሰው መሬት ላይ ወደቀ፣ ቀዝቃዛውም አየር የፊቱን ገጽታ በጤዛ አረስርሶት ነበር፡፡ ግመልዋ ሳትቀር በርሰዋ ላይ ተቀምጦ ሳለ መገለጡ መጥቶ ቢሆን ኖሮ ፣ በበረሃው አግራሞት ትሞላ ፣ ትቀመጥ፣ ትዘልም ነበር፡፡*

*መገለጡ ባልተጠበቀ ሁናቴ፣ በገሃድ፣ ያለ ምንም ቅድመ ማስጠንቀቂያ በነብዩ ላይ መጣ። በዚህ ረገድ ተጠይቆ " ከሁለቱ በአንዱ መንገድ ነው የመጣው፡- አንዳንድ ጊዜ ጂብሪል መገለጡን ይሰጠኝ ነበር፤ በሌላ ጊዜ ደግሞ በታላቅ የደውል ንዝረት በልቤ ጥልቀት እነካለሁ፤ ይኸውም በጣም ያስደስተኝ ነበር።" ሲል ምላሽ ሰጥቷል። አብረቅራቂ ጸጉሩ በእርሱ ላይ የወረደው አስፈሪው ሱረቱ ውጤት እንደሆነም ይናገራል።* [16]

***ታባሪ***

*መገለጡ ወደ እርሱ ሲመጣ በኃይለኛ የመንፈስ መረበሽ ውስጥ ወድቆ ነበር። የፊቱ ገጽታ ወደ ነበረበት ተመልሶ በጨርቅ እንዲሸፈን አድርጓል፤ ከፍተኛ ላብም በራሱ ላይ ይታይ ነበር።*[17]

***ኢብኑ ሀኒባል***

*ይህ ሂደት በወቅቱ በማንኮራፋት እና በፊት ቅላት እጀባ ያለምንም ቅድመ ዝግጅት ነበር የተከሰተው። ነብዩ መለኮታዊ መገለጡን የተቀበለው በሚመገብበት ወቅት የመጣለትን ጥያቄ ተከትሎ ነበር። በዚህ መልኩ መገለጡ ምናልባት ተረብሾ ሳለ በእጁ ያለውን ጨርቅ በጣለ ጊዜ አሊያም በምስባኩ ፊት ቆሞ ሳለ ጥያቄው በሚመለስበት ወቅት ተከናውኗል። መገለጡ አስቀድሞ ስለ ደረሰው መሐመድ "በመሸፈኛ የተከለለ ሰው " ወይም "የተዋጠ ሰው" ተብሏል።* [18]

***ኦቦዳ ኢብኑ አስማህ***

*መገለጡ ወደ ነብዩ በሚመጣበት ወቅት ጫና ውስጥ ገብቷል፤ የፊቱም ገጽታ ጽልመት ይታይበት ነበር።*[19]

መሐመድ መገለጡን በሚቀበልበት ጊዜ ራሱን ወደ ታች አጎንብሶ እንደነበር ፣ አብረውት በነበሩትም ሰዎች እገዛ መገለጡ ሲያበቃ እንደነቃ ሌላ ምንጭ ያትታል። የመሐመድ ተወዳጅ ሚስት የነበረችው አል-ሪዝ ኢብኑ ሄሻም በአንድ ወቅት "የፈጣሪ መልዕክተኛ መገለጡ ወደ አንተ የመጣው እንዴት ነው ? የሚል ጥያቄ ቀርቦለት ፣ "መገለጡ ወደ እኔ በሚመጣበት ጊዜ እንደ ደውል ድምጽ አይነት ንዝረት ሆኖ እጅግ ያመኝ ነበር። ሲለቀኝም መልአኩ የተናገረኝን አስታወስኩ፤ በሰው መልክ የተመሰለ መልዐክም ተገለጠልኝ፣ እኔም የተናገረኝን ሁሉ አስተዋልኩ።" ብሎ መመለሱን ተነግራለች። መገለጡ በእርሱ ላይ በሚመጣበት ወቅት ቀዝቃዛማ አየር ፣ በፊቱም ገጽታ ላይ ከፍተኛ ላብ ያየች መሆኗን አክላ ገልጻለች።[20]

---

[16] ኢብኑ ሳድ ተባካት ፣ ገጽ 131።
[17] ታባሪ ፣ ሐተታ xii-9 ፣xx viii- 4።
[18] ኢብኑ ሀኒባል ፣ ሙስናድ ፣ iv -222 ፣ vi- 56 ፣ iii-21።
[19] ኢብኑ ሐኒባል ፣ ኦፕ ሲት፣ vi -163።
[20] ሚሽካት አል -ማሳቢእ ፣ ገጽ 1254።

## 7. የመገለጥ ሂደቱ መቋረጥ

መሐመድ ከተቀበለው የመጀመሪያ መገለጥ ሂደት በኃላ ሌላ ተጨማሪ መልዕክት አልተቀበልም፡፡ አል-ቡካሪ አይሻን መሰረት በማድረግ የሚከተለውን አስፍሯል፡- “ የአላህ መልዕክተኛ መለኮታዊ መገለጡን ከተቀበለ በኃላ ፣ ከድጃ የአጎትዋ ልጅ ከሆነው ዋራቃ ኢብኑ ኖፈል ጋር ታገናኘዋለች ፡፡ ይህ ሰው በቅድመ -እስልምና ወቅት ክርስቲያን ነበር፤ አላህ ባዘዘው መሰረት ወንጌላትን በአረብኛ ቋንቋ ጽፏል፡፡ ከድጃ ስትናገር “ የአጎቴ ልጅ ሆይ የመሐመድን ታሪክ በጽሞና ስማ....... ነብዩ የተነጋረው ሁሉ በእርግጥ ያየውን ነው፡፡’ ዋራቃም ‘ይህ መገለጥ አላህ ሙሴን ሲልክው እንደ ነበር አይነት ነው፡፡ ወጣት ብሆን፣ በሕይወትም ብቆይ ኖሮ፣ ሕዝቡ በአንተ ላይ ሲነሳ አብሬህ እሆን ነበር፡፡’ የአላህ መልዕክተኛ ‘ህዝቡ ይነሳብኛልን’ ሲልም ጠየቀ፡፡ ዋራቃም ‘ከዚህ ቀደም በአንተ ሁኔታ መገለጥን የተቀበለና መልዕክትን ያመጣ የለም፤ ሆኖም ህዝቡ ብዙዎችን በጠላትነት ነው የተቀበለው፡፡ በሕይወት ካለሁ ከአንተ ጋር ነኝ ’ ብሎት ነበር፡፡ ነገር ግን ከጥቂት ቀናት በኃላ ዋራቃ በሞት ተለየ፤ የመለኮታዊ መገለጥ ሂደቱም ለጊዜው ተቋረጠ፡፡ ከዚህ የተነሳ ነብዩ በጣም ያዘን፣ ራሱንም ከከፍታ ስፍራ ወርውሮ ለማጥፋት ብዙ ሙከራዎችን ያደርግ ነበር፡፡ ሁልጊዜም ይህን ለማድረግ ወደ ተራራ ጫፍ ሲወጣ ሳለ ጅብሪል ከፊቱ በመቆም ‘መሐመድ ሆይ አንተ የአላህ እውነተኛ መልእክተኛ ነህ’ ይለው ነበር፤ በዚህም ልቡ መለስ ይል፣ በሰላምም ይሞላ ነበር፡፡ መገለጡ በሚመጣበት ጊዜ ሁሉ ግን ልምምዱ የከዚህ ቀደሙን አይነት ነበር፡፡[21]

መሐመድ ሱባይህ መሐመድ በሚለው መጽሐፉ እንደሚከተለው ያስቀምጣል ፡-

> *የመገለጡ ሂደት መቋረጥ የተመሰረተው በጥበብ ላይ ነው፡፡ የመገለጡ ሂደት ግፊት የነብዩን ስነ-ልቦና ተጭኖታል፤ በዚህም ፈጣን ሂደት ቀጣይነት አካሉ ፈጽሞ ሊቃቋመው አይችልም ነበር፡፡ ከአካላዊ ጤናው አንጻር የመገለጡ ሂደት መቋረጡ አስፈላጊ ነበር፡፡* [22]

ጸሓፍት ሂደቱ ከስድስት ወር እስከ ሶስት ዓመት የወሰደ እንደሆነ ግምታቸውን ያስቀምጣሉ፡፡ የሁለተኛው መገለጥ አስመልክቶ ቁርኣን በሱረቱ 74 ላይ ተንትኖታል፡፡ በዚህ ረገድ አል-ሱይቲ ፣ አስባብ አል- ኑዑዙል በሚለው መጽሐፉ የመሐመድን ምስክርነት ያሰፍራል፡-

> *በመንገድ ላይ እየሄድኩ ሳለ ከሰማይ ድምጽ ሰማሁ ፡፡ አይኖቼን አቅንቼ ስመለከት በሰማይና በምድር መካካል በዙፋኑ ላይ የተቀመጠውን ጅብሪል ተመለከትሁ፡፡ በፍርሃትና ድንጋጤም ወደ*

---

[21] ቡካሪ ሳቢእ ፣ኪታብ አል -ታአቢር ፣ ቅጽ 9፣ ሐዲስ ቁጥር 111፡፡

[22] ሙሐመድ ሱቢእ ፣ሙሐመድ ( ካይሮ፡- ዳር አል ታቀፋአ አል -አማ ፣ 1957) ገጽ 35፡፡

*መሬት ወደቅሁ፤ መልአኩም አለኝ ‘ መሐመድ! የልብስህን መሸፈኛ አንሳ፣ ተነሰና አስጠንቅቅ፣ ጌታንም አክብር፣ ልብስህንም አንጻ አቧራንም ከእርሱ አስወግድ!*

መሐመድ ወደ ቤተሰቦቹ በመሄድ “ ሸፍኑኝ ሸፍኑኝ” ብሎ መጣራቱን ሌሎች ምንጮች ያስረግጣሉ፡፡ በዚህም ከድጃ ጥሪውን ለመጀመሪያ ጊዜ በመስማት ፣ በርሱ ያመነች ቀዳሚ ሰው ሆነች፤ በዚህም ታበረታታውም ነበር፡፡

መሐመድ የመገለጡ ምንጭ ምን እንደሆነ በእግጠኝነት የማያውቅበት ጊዜ ነበር፡፡ በዘልማድ እንደሚነገረውም የመንፈሱን ባህሪይ የለየችለት ከድጃ ነበረች፡፡ መሐመድን አስቀድማ በቀኝ ጉልበትዋ ከዚያም በግራዋ በኩል አኖረችው፡፡ በሁለቱም ጎን በምታስቀምጥበት ጊዜ የጻረ-ሞት መንፈስ ይገለጥ ነበር፡፡ ርሱንም ወደ ጭኗ ወሰደች፣ አይነርግቧንም አስወገደች፤ ያን ጊዜ መንፈሱ ወዲያው ጠፋ፡፡ እርሷም “ደስ ይበልህ ፣ ከጌታ ዘንድ የኾነ መልአክ ነው፣ ክፉው መንፈስ የለም” እንዳለችው ይታመናል፡፡

## 8. የተከታዮች መብዛት እና ስደት ጅማሮ

የመሐመድ ቀደምት ተከታዮች የቤቱ ሰዎች ናቸው፡፡ እነርሱም ፡- ከድጃ ባለቤቱ፣ ዛይድ ኢብኑ ሀሪዝ (ከክርስትያን ቤተሰብ የመጣ የከድጃ ባሪያ፣ ኃላም ከድጃ ለመሐመድ የሰጠችው፣ ነጻ ወጥቶ የጉዲፈቻ ልጁ የተደረገ) ፣ ኡም አይመን (የመሐመድ እናት ባሪያ የነበረ) እና አሊ (የመሐመድ የአጎት ልጅ) ናቸው፡፡ አቡ በከር፣ ኡማር እና ዑስማን የተባሉ የእንቅስቃሴው መጻኢ መሪዎችም ነበሩ፡፡

የመሐመድ ነገዶች የጣዖት አምልኮአቸውን በመቃወሙ አዲስ እንቅስቃሴውን ማሰደድ ጀመሩ፡፡ አስራ አምስት የሚያክሉ የመሐመድ ተከታዮች ቀይ ባህርን ተሻግረው ወደ ኢትዮጵያ ተሰደዱ፤ ከእነዚህም መካካል ሪኬይ፣ የመሐመድ ልጅ እና ባልዋ ዑስማን ይገኙበታል፡፡ የኢትዮጵያ ንጉስም በመልካም ተቀብሎአቸው ለሶስት ወር ያክል ቆዩ ፤ ወዲያው መካ ወደ እስልምና ተለወጠች የሚል አዲስ ዜና ተበሰረ፡፡

መሐመድ በምሬት ቃል የመካ ሰዎችን ይሞግት ጀመር ፤ በሱረቱ 53 ፥19፣20 ሦስቱ ጣዖታትን አስመልክቶ “ አል-ላትንና አል-ዑዛን አያችሁን? ሦስተኛይቱንም አነስተናዋን መናትን (አያችሁን? የምትግገዟቸው ኃይል አላቸውን?) የሚለውን ክፍል ያነብ ነበር፡፡ አክሎም “ እነዚህ ታላቅ ክሬኖች በእርግጥ ምልጃቸው ያሻናል” በማለት ተንበረከከ ፣

የመካ ሰዎችም ተንበረከኩ ፣ አመለኩ፣ "ይህ ሰው ስለ አማልክቶቻችን ከዚህ ቀደም እንዲህ መልካምን ተናግሮ አያውቅም " ሲሉ ምስክርነታቸውን ሰጡ፡፡

አላህ መሐመድን ወዲያው ገሰጸው ፡- "ከመልክተኛና ከነቢይም ከአንተ በፊት አንድንም አላክንም ባነበበ (እና ዘም ባለ) ጊዜ ሰይጣን በንባቡ ላይ (ማጥመሚያን ቃል) የሚጥል ቢሆን እንጅ፡፡ ወዲያውም አላህ ሰይጣን የሚጥለውን ያስወግዳል፡፡ ከዚያም አላህ አንቀጾቹን ያጠነክራል፡፡ አላህም ዐዋቂ ጥበበኛ ነው"(ሱረቱ 22፥52)፡፡[23]

መሐመድ በዚህ መልኩ መታለሉን በተመለከተ በጽሑፍ የሰፈረ አስረጅ የለም፡፡ የአማልክቶቹን ማማለድ ስራ መቃወም በጀመረ ጊዜ መካ ሰዎች እጅጉን ተበሳጩ ፣ ሰደትንም አስነሱ ፣ ከማንኛውም ሙስሊም ጋር ጋብቻን እና የንግድን ስምምነት ማድረግ እንዳመይቻል ደነገጉ፡፡ በመሐመድ ምክር ብዙ የሚሆኑቱ በመቶ የሚቆጠሩ ተከታዮቹ ወደ ኢትዮጵያ እንዲሸሹ ተደረገ፤ ለተከታታይ ሁለት እና ሦስት ዓመታት የመካ ሰዎች ነብዩን ይቃወሙት እና ይሳለቁበት ነበር፡፡

መሐመድን የተሳለቁበት ትርክት በቁርኣን ተዘግቧል ፡- " ከእነሱም (ከመናፍቃን) እነዚያ ነቢዩን የሚያሰቃዩ "እርሱም ጆሮ ነው" (ወሬ ሰሚ ነው) የሚሉ አልሉ" (ሱረቱ 9፥61)፣ "አንተ በእርግጥ ዕብድ ነህ አሉም" (ሱረቱ 15፥6) ፣ "አንተ ቀጣፊ እንጂ ሌላ አይደለህም" (ሱረቱ 16፥101)፣ ዕብድ (ሱረቱ 37፥36) እና የተደገመበት ሰው (17፥47)፡፡ ትንቢቱን "የሕልሞች ቅዠቶች" በማለት "ይልቁንም ቀጠፈው እንዲያውም እርሱ ቅኔን ገጣሚ ነው" ይናገራሉ (ሱረቱ 21፥5)፡፡ ሌሎች ሕዝቦች "ያገዙት የኾነ ውሸት እንጂ ሌላ አይደለም" እንዳሉት ሱረቱ 25፥4 ይናገራል፡፡

## 9. የመሐመድ መበርታት

የመካ እገዳ በአስረኛው የመሐመድ ሚሲዮን ሥራ ተነሳ ፤ ከድጃ ብዙም ሳይቀር አቡ ጣሊብን ተከትላ ህይወትዋ አለፈ፡፡ መሐመድ የጉዲፈቻ ልጅ የሆነውን ዛይድ ከታይፍ ጋር በማድረግ መቶ ኪሎ ሜትር ወደ ሚገኘው ምስራቃዊ መካ መልዕክቱን እንዲሰብክ ቢልከውም፣ የታይፍ ሰዎች በታይፍ ላይ ድንደጋይ በመወርወር እና በማቁስል ተቃወሙት፡፡ መሐመድ ወደ መካ ተመልሶ ጎዞ በሚያደርግበት ወቅት ጂኒዎች (መንፈሳዊ አካላት)

---

[23] አል ሱይቲ፣አስባብ አል ኑዙዑል ሱረቱ 22፡52

እንደከበቡት፣ የተቀበለውን መገለጥ ከእርሱ በመስማት የእስልምና እምነት ሲቀበሉ ራዕይን ይመለከታል (ሱረቱ 46፥29፣72፥1፣2)፡፡

በዚህ አስቸጋሪ ወቅት መሐመድ አስደናቂ መገለጦችን ተቀብሏል፡፡ ወደ ኢየሩሳሌም ቤተመቅደስ በቡራቅ ላይ ሆኖ (አል-ታባሪ መብረቅ ብሎ ይጠራዋል) የምሽት ጉዞ (ኢስራ) ማድረጉን ይናገራል፡፡ ቡራቅ ከበቅሎ የሚያንስ ከአህያም የሚገዝፍ ፣ የሴት ገጽታና የፒኮክ ጭራ ያለው ክንፋም እንስሳ ነው፡፡[24] በኢየሩሳሌምም መሐመድ አብራሐምን፣ ሙሴን እና ኢየሱስን በጸሎት በመምራት በእነርሱ ላይ ያለውን ቀዳሚነት ካሰፈነ በኃላ ወደ ሰማይ እንዳረገ (ሚራጅ) ያመለክታል፡፡[25]

አያሌ የሙስሊም ሥነ-መለኮት ሙህራን ኢስራ (የምሽት ጉዞ) እና ሚራጅ (ወደ ሰማይ ማረግ) አካላዊ ክስተት እንደሆነ ያስረግጣሉ፤ ቡራቅ አካላዊ ማንነት እንጂ መንፈስን አያመለክትም፡፡ ሙሐመድ ወደ ሰማይ በጂብሪል አማካኝነት መወሰዱን በዚያም ቀደምት መልዕክተኞችን ማለትም አዳምን በመጀመሪያው ሰማይ፣ ኢየሱስ እና መጥምቁ ዮሐንስ በሁለተኛው፣ ዮሴፍ በሶስተኛው፣ እድሪስ (ሔኖክ) በአራተኛው፣ አሮን በአምስተኛው፣ ሙሴ በስድስተኛው እና አብርሐም በሰባተኛው ሰማይ ላይ እንዳገኛቸው ያመለክታል፡፡

በመጨረሻም መሐመድ ወደ ከፍተኛው ሰማይ በመወሰድ በፈጣሪ ፊት ሆኗል፡፡ ሀዲስ ፈጣሪን ፊት ለፊት እንዳየ እና ሰባ ሺህ ንግግሮች እንዳደረገ ይናገራል፡፡ ቁርኣንም ሲናገር፡-

*ሱረቱ 17፡1*

*ያ ባሪያውን ከተከበረው መስጊድ ወደዚያ ዙሪያውን ወደ ባረክነው ወደ ሩቅ መስጊድ በሌሊት ውስጥ ያስኼደው (ጌታ) ጥራት ይግባው፡፡ ከተዓምራቶቻችን ልናሳየው (አስኼድነው)፡፡ እነሆ እርሱ (አላህ) ሰሚው ተመልካቹ ነው፡፡*

## 10. ሂጅራ

በ62 ዓ.ም በመካ የአስራ ሦስት አመት ያልተሳካ ስብከት በኃላ መሐመድ አያሌ ተከታዮቹ ወደ ሚኖሩበት ያትሪብ ለመሄድ ወሰነ፡፡ አራት ኪሎ ሜትር የሚፈጀው ይህ ጉዞ ከአስር እስከ አስራ ሁለት ቀናት ወስዷል፤ ጉዞውም ሂጅራ (ሽሽት ወይም በረራ) ተብሎ ይጠራል፡፡ የሙስሊም

[24] ጣባሪ ፣ I -165፡፡
[25] ቡካሪ II-147፡፡

ዘመን አብሳሪ ምልክት ከመሆን ባሻገር ከሂጅራ በኃላ (A.H or Afteer Hijra) የሙስሊም ዘመን አቆጣጠር እንዲመሰረት ምክንያት ሆነ።

በያትሪብ በኃላ መሐመድ መዲና (የነብዩ ከተማ) ብሎ በሰየማት ከተማ አዲሱ እምነት እጅጉን መስፋፋት ጀመረ። መዲና ከመድረሱ በፊት መሐመድ የአላህን አንድነት እና ፍርድ ቀን የሚሰብክ ሀይማኖት መሪ ነበር። ከመንፈሳዊ መሪነቱ በዘለል ሕግ አውጪ እና የጦር መሪ ጭምር መሆን ችሏል ፤ ይህ ለውጥ በቁርኣን ሱረቱ ላይ ተገልጾ ይገኛል።

የመጀመሪያው ጸሎትና ስብሰባ በመሐመድ የግል ቤት ተከፈተ። በቅጥር ግቢው ከጸሐይ ብርሃን በጠነከሩ ሚስቶቹ ቁጥር ቤቶች ታነጹ፣ በዙሪያውም ለተካተዮቹ ቤቶች ተሰሩ።

## 11. የመሐመድ ሚስቶች

መሐመድ ከከድጃ ሞት በኃላ በዓመቱ ሁለት ሚስቶችን አግብቷል፣ በርካታ ሰዎችም የቤተሰብ አባላት ሆነው ተጨምረዋል። ከብዙዎቹም መካካል ዘይነብ ፣የሙሐመድ ጉድፈቻ ልጅ ዛይድ ሚስት፣ ሶፊያ (ይሁዲ የነበረች) እና የማርያ ኮፕቲክ ክርስቲያን ይገኙበታል። መሐመድ ለመጽሐፍ ቅዱስና ለይሁዲ-ክርስትና ሀይማኖት የነበረው ትውውቅ ከክርስትና ወደ እስልምና ለመጡት ምክንያት ነበር።

ፈጣሪ የመሐመድን ብዙ ሚስቶች ማግባት መፍቀዱን የሚከተለው ቃል ይናገራል፡-

*ሱረቱ 33 ፥50*

*አንተ ነብዩ ሆይ! እኛ እነዚያን መህሮቻቸውን ሚስቶችህን፣ አላህ ባንተ ላይ ከመለሰልህም እነዚያን እጅህ የጨበጠቻቸውን ምርኮኖች ፣ እነዚያንም ከአንተ ጋር የተሰደዱትን የአጎትህን ሴቶች ልጆች ፣ የአክስቶችህንም ሴቶች ልጆች ፣ የየሹማህንም ሴቶች ልጆች፣ የየሹሜዎችህንም ሴቶች ልጆች(ማግባትን) ለአንተ ፈቅደንልሃል። የአመነችንም ሴት ነፍሷን (ራሷን) ለነቢዩ ብትሰጥ ነቢዩ ሊያገባ የፈለገ እንደ **ኾነ ምእምናን ሌላ ላንተ ብቻ የጠራች ስትኾን (ፈቀድንልህ)።** በእነርሱ (በምእምናን) ላይ በሚስቶቻቸውና እጆቻቸው በጨበጧቸው (ባሮች ነገር) ግዴታ ያደረግንባቸውን በእርግጥ ዐውቀናል። ባንተ ላይ ችግር እንዳይኖር (ያለለፉትን ፈቀድንልህ)። አላህም መሓሪ አዛኝ ነው።*

ያቀለሙኩት ሐረግ ትኩረት እንዲሰጥበት እፈልጋለው። መሐመድ ይህን ፈቃድ ሞኞችን ለማሞኘት ተጠቅሞበታል። ሙሉው የመሐመድ ሚስቶች ዝርዝር የሚከተለው ነው፡-

- ***ከዲጃ ቤኔት ኩዋይላድ*** ፡- የመሐመድ ብቸኛዋ ቀዳሚ የሃያ አምስት ዓመት ሚስት ናት።

- ***ሳውዳ ቤኔት ዛማዕ*** :- ወደ እስልምና የተቀየረች ሚስት ናት፡፡ መሐመድ ያገባት ከከዲጃ ሞት ወራት በኃላ በ620ዓ.ም ነው፡፡ በዕድሜ ጠና ያለችና ወፍራም ነበረች፤ መሐመድም ፈቷታል፡፡ በመንገድ ሳይቀር አግኝታ ትለምነው ፣ በተለይም በፍርድ ቀን የእርሱ ሚስት ሆና መገኘት እንደምትፈልግ ትጠይቀው ነበር፤ እርሱ ግን አልፈቀደላትም! ይህ ክስተት በሱረቱ 4፥128 "ሴትም ከባልዋ ጥላቻን ወይም ፊቱን ማዞርን ብታውቅ በመካካለቻው መስማማትን ቢስማሙ በሁለቱ ላይ ኀጢአት የለም፡፡ መታረቅም መልካም ነው፡፡ መሐመድ ሳውዳን ከሚስቶቹ መካካል እጅግ ለጋስ ስለ ነበረች " በለ ረጅም እጅ" የሚል ስያሜ አውጥቶላታል፡፡
- ***አይሻ ቤነት አቡ ቤከር*** :- የመሐመድ ተወዳጅ ሚስት ነች፤ በምታገባበት ጊዜ የዘጠኝ ዓመት ልጅ ነበረች፡፡ አሻንጉሊቶቿን ይዛ ነበር ወደ ሽማግሌው ባልዋ የገባቸው፡፡ መሐመድ ሲሞት አስራ ስምንት ነበረች፡፡ በሀዲስ ትርክት ውስጥ ትልቁን ስፍራ በመያዝ፣ ከመሐመድ አፍ በቀጥታ አንድ ሺህ ሁለት መቶ አስር ሪፖርቶችን አስፍራለች፡፡ እርሱ ከሞተ በኃላ በሥነ-መለኮት እና ህጋዊ ጉዳዮች ታማክር ነበር፡፡
- ***ሀፍሳ ቤነት ኦማር*** :- መሐመድ በ625 ዓ.ም ነች፤ በጸሎት እና ጾም ልምምዶችዋ ታዋቂ ነበረች፡፡ በቤተሰብ አባላት መካከል ግጭት በሚፈጠርበት ወቅት ከአይሻ ጋር በመሆን ሌሎቹን ሚስቶች ትቃወም ነበር፡፡
- ***ዘይናብ ቤነት ኩዛይም*** :- ለሁለት ያህል ጊዜ መበለት ነበረች፤ ሐፊሳን ባገባበት ዓመት የሙሐመድ ሚስት ሆነች፡፡ በአጭር ጊዜ ውስጥ ህይወትዋ አልፏል፡፡ ለድሆችም ለጋስ ስለነበረች አል-ማሳኪን ( የድሆች እናት) የሚል ስም እንዲሰጣት ሆናል፡፡
- ***ኡም ሳላማ*** :- መሐመድ በባልዋ ሞት ምክንያት ያጽናናት በኃላም በ628 ዓ.ም ያገባት ናት፡፡
- ***ዘይናብ ቤነት ጃህሽ*** :- ራስዋን ለመሐመድ ሚስት አድርጋ የሰጠች ነበረች፡፡ መሐመድም ነጻ ያወጣው የጉዲፈቻ ልጁ ዛይድ ኢብኑ ሀሪታ እንዲያገባት አድርጓል፡፡ ዛይድን ለመጎብኘት በሚሄድበት ወቅት ብቻዋን ሲያገኛት በፍቅር ወደቀላት፡፡ በ625 ዓ.ም ዛይድ ስለ ፈታትም የመሐመድ ሚስት ሆነች፡፡ በዚህም መለኮታዊ ንጽህናን ለማግኘት ሱረቱ 33፥ 36-39ን ተቀብሏል፡፡ ዘይናብ መሐመድን በምታገባባት ወቅት ሰላሳ አመቷ ነበር፤ በአምሳ ዕድሜዋም ህይወትዋ አልፏል፡፡

- ***ጁዋሪ ቤነት አል -ሀሪስ*** ፡- ከኢብኑ ሙስታላክ ይሁዲ ነገድ ነበረች፡፡ ሳፍዋንዋን ኢብኑ ማማሊክ የተባለው ባልዋ ከሙስሊማኑ ጋር በተደረገው ጦርነት ህይወቱ በማለፉም መሐመድ ማርኮ አገባት፡፡
- ***ሶፊያ ቤነት ሁያይ*** ፡- ከይሁዲ ሐቢር ነገድ ስትሆን፣ አባትዋና ባለቤትዋን በጦርነት አጥታለች፡፡ ሙስሊሞች ማርከው ስላመጧት በሙሐመድ ነጻ ወጣች፤ ሚስቱም ሆነች፡፡
- ***ኡም ሀቢባህ*** ፡- የኢትዮጵያ ንጉስ ለመሐመድ ሚስት አድርጎ እንደሰጣት ይነገራል፡፡
- ***የኮፕቲኳ ማርያ፡-*** የግብጽ ንጉስ ሴሪን የተባለቸውን አህቷን ጨምሮ ለመሐመድ ስጦታ በማድረግ ወደ መዲና የላካቸው ናቸው፡፡ አብርሐም የተባለ ልጅ በወለደችለት ጊዜም ነጻ በማውጣት ህጋዊ ሚስቱ ሆነች፡፡
- ***ሬሂና ቤነት ዛይድ*** ፡- ቤኒ ቁራዛ ከሚባለው ነገድ የሆነቸ፣ እንደ ሶፍያ ሁሉ ባልዋ በጦርነት በመሞቱ ምርኮ ተደርጋ የተወሰደች ናት፡፡
- ***ማይሙና ቤነት አል-ሀሪስ*** ፡- ከሃዋዚን ነገድ የሆነችው ይህች ሴት የመጀመሪያ ባለቤቷን የፈታች ፣ ሁለተኛ ባልዋን በሞት ያጣች፣ ኃላም የመሐመድ መጨረሻ ሚስት የነበረች ናት፡፡

## 12. ቅድመ- እስላማዊ ጦርነት

### ሀ. የባዳር ጦርነት

በመዲና ሁለት አረብና ሦስት ይሁዲ የሆኑ አምስት ነገዶች ነበሩ፡፡ በከተማይቱ ዙሪያ ያለው ውሀ ገብ ስፍራ ለሁሉም የምግብ አቅርቦት እንዲኖር አስችሏል፡፡ አዳዲስ አማኞች ወደ ከተማ በመፍለሳቸው ምክንያት ለእርሻ ቦታ በቂ የመስኖ ውሃ እንዳይኖር አድርጓል፡፡ መሐመድ ወደ ከተማይቱ አቅራቢያ የሚገኙትን ዘላኖች ወረረ፤ ከሶሪያም ወደ መካ ባደረገው ጉዞ በሺዎች የሚቆጠሩ ግምሎችን ወርሰ፡፡ ይህ ጦርነት የባዳር ጦርነት ተብሎ ተሰይሟል፤ የመሐመድ ሰልፈኞችም በመካ የሚገኘውን ግዙፍ ኃይል በማሳደድ በርካታ ምርኮኞችን ማርከዋል፡፡ ሁኔታውን አስመልከቶ መሐመድ ሲናገር፡-

*ሱረቱ8፥41*

*ከማንኛውም ነገር በጦር (ከከሀዲዎች) የዘረፋችሁትም አንድ አምስተኛው ለአላህና ለመልክተኛው፡፡*

ሙርከኞቹ በብዙ ስቃይና ጭቆና ያልፉ ነበር፤ በዚህም ምክንያት በአንድ ወቅት መሐመድ ተጠይቆ ሲመልስ “ የአላህና የነብዩ ጠላቶች በመሆናችሁ ሞታችሁን እንዳይ ስላ ጽናናኝ ፈጣሪን አመሰግናለው ” ብሏል፡፡

### ለ. የኡሁድ ጦርነት

የመካ ኃይሎች በሙስሊማኑ ላይ በ625 ዓ.ም ከፍተኛ ጥቃት እና ግድያ ፈጽመዋል፡፡ መሐመድ በከንፈሩ ላይ የመሰጠንቅ፣ በጥርሱም ላይም በሙስሊማኑንየመሰበር አደጋ ደርሶበታል፡፡ የመሐመድ ግለ-ታሪክ ጸሐፊ ኢብኑን ሂሻም የመሐመድ ፊት በደም መታጠቡን ይኸውም "ወደ ጌታ የሚጠራቸውን ነብይ ይህን ለምን ይፈጽማሉ! የፈጣሪ ቁጣ በመልዕክተኛው ፊት ላይ ደም እንዲረጭ ባደረጉ ሁሉ ላይ ይንደድ !" ብሎ መጮኹን ዘግቧል፡፡

ድሉ ጊዚያዊ ከመሆኑ ጋር የመካው ኃይል የጦርነቱን ስኬት ማስቀጠል አልቻለም፡፡ የአዲሱ እምነት ኃይል እየጠነከረ መምጣት ለአጎራባች ነገዶች ድል መነሳት ምክንያት ሆኗል፡፡ ጠላት አንድነቱ በማጠናከር እስልምናን ከማጥፋቱ በፊት ኃይሉን መበታተን ለመሐመድ አማራጭ የሌለው ውሳኔ ነበር፡፡

> *መሐመድ ተከታዮቹንና ሀይማኖቱን ለመከላከል የነበረው ምርጫ ወደ ሰልፍ መመለስ ነበር፡፡ ይህን ባያደረግ ደቀመዛሙርቱ ሳይቀር ይሞቱ ፣ ሀይማኖቱም ይከስም ፣ እርሱና ዘሮቹ ይጠፉ ነበር፡፡*[26]

በርካታ የቁርአን ጥቅሶች ጠብ አጫሪነትን ያስተጋባሉ፡-

> ***ሱረቱ 2 ፥190፣ 191***
>
> *እነዚያንም የሚጋደሉዋችሁን (ከሓዲዎች) በአላህ መንገድ ተጋደሉ፡፡ ወሰንንም አትለፉ፤ አላህ ወሰን አላፊዎን አይወድምና፡፡ ባገኛችኋቸውም ስፍራ ሁሉ ግደሉዋቸው፡፡ ከአወጧችሁም ስፍራ አውጧቸው፡፡ መከራም ከመግደል ይበልጥ የበረታች ናት፡፡ በተከበረው መስጊድም ዘንድ በርሱ ውስጥ እስከ ሚጋደሉዋችሁ ድረስ አትጋደሉዋቸው፡፡ ቢጋደሉዋችሁም ግደሉዋቸው፤ የከሓዲዎች ቅጣት እንደዚህ ነው (ሱረቱ 190፣191)፡፡*
>
> ***ሱረቱ 9፥36***
>
> *አጋሪዎችንም በአንድ ላይ ሆነው እንደሚዋጉዋችሁ በአንድ ላይ ሆናችሁ ተጋደሉዋቸው፤ አላህም ከሚፈሩት ጋር መሆኑን ዕወቁ፡፡*

መሐመድ ሱቢህ የነብዩን የጦርነት ዘመቻ አስመልከቶ የሚከተለውን አስፍሯል፡-

> *የመሐመድ ግለ -ታሪክ ጸሐፊ ግን በጦርነቱ ቁጥር ብዛት ላይ አይስማማም፡፡ ብዙዎች ከሃያ እስከ ሃያ አምስት እንደሚደርስ ያመለክታሉ፡፡ በኡሁዱ ጦርነት ላይ መሐመድ*

[26] ኪዳዊ ፣ ሙሐመድ ፣ ገጽ 180፡፡

*ሉባይ ቤነን ኸላፍ በእጁ ገድሏል፡፡ እርሱ ላካቸው ሳሪያስ አርባ ሰባት ነበሩ፤ ሳሪ ከአምሳ እስከ አራት መቶ የሚያክሉ ተዋጊዎችን ይይዛል፡፡*

## ሐ. የደች ጦርነት

በ627 ዓ.ም ታላቁ የመካ ኃይል መዲናን ከበበ፡፡ በሰልማን የፋርስ ወዳጅ ምክር መሐመድ በከተማዋ ፊት ለፊት ጠንካራ ምሽጎችን ገነባ፤ ታላቁም ገድል "የደች ጦርነት" የሚል ስም ተሰጠው፡፡ አረቦች ለታሪኩ ከሚሰጡት ቦታ ይልቅ ስያሜው የፋርሶችን ዋጋ ያልቃል፡፡

## መ. ድኅረ- ተልዕኮ

ይህ ተልዕኮ የቁራይዛአይሁዳውያኑ ውጊያ ያካትታል፡፡ በዚህ ጦርነት ሰባት መቶ ይሁዲዎች ተማርከዋል፣ ተገድለዋልም ፡፡ ሚስቶቻቸውና ልጆቻቸውም ለባርነት አልፈው ተሰጥተዋል፡፡ ይሁዲዎች የመሪያቸውን ካእባአ አንገት መሰላት አስመልክቶ ተቃውማአቸውን ቢያቀርቡም "ካኣብ በክፉ ንግግሩና ግጥሙ አስቆጥቶኛል፡፡ ከእናንተ መካካል ማንም ተመሳሳይ ነገር ቢፈጽም ሰይፍ ይሆንበታል፡፡"[27]

## ሠ. የመካ ድል

ከሂጅራ ሰባተኛው አመት ድረስ በተለያዩ ቦታዎች ጦርነቱ ቀጥሎ ነበር፡፡ በዚህም ወቅት መሐመድ ወደ ካእባአ መዲና ጉዞ ማድረግ አልቻለም፡፡ መሐመድ የተመኘውን ሙሉ ድል እሲጎናጸፍ ድረሰ ተጨማሪ አመት ብሎም የሁዳቢቢህ ድርድር አስፈልጎት ነበር፡፡ ምንም እንኳ አያሌ የመካ ሰዎች ቢቃወሙ ፣ መሐመድ ጥንታዊቱን ከተማ ለመማረክ ወሰነ፡፡ በመጨረሻም አስር ሺህ ገደማ የሚያክሉ ወታደሮቹ ከተማይቱን ወረሱ፣ በካእባአ ያሉትንም ጣዖታት አወደሙ፡፡ መሐመድ ታዋቂውን ጥቁር ድንጋይ በመካ በማስቀረቱ እስከ ዛሬ ከመላው አለም ሙስሊማኑ የሚጎዝበት ማዕከል ለመሆን በቅቷል፡፡

መካን ከወሰደ በኃላ ኢብራሒም የተባለውን ታናሽ ልጁን በማጣቱ በኃዘን ክፉኛ ተጎዳ፡፡ የልጁ እናት ኮፒቲካዊቷ ማርያ ነበረች፤ ልጁም የአረብና ይሁዲ ዘር አባት ወይም የታመኑ ሰዎች አባት ( የሦሶቱ ዐበይት እምነቶች ፡- ይሁዲ፣ ክርስትና ፣ እስልምና አባት) በሆነው አብርሐም ስም ተሰይሞ ነበር፡፡

---

[27]ኢቢን ካቲር ፣ አል ቢዳያ ዋል ኒአያ ፣ቅጽ 4፣ የካአብ ሞት ምዕራፍ፡፡

## 13. አዲሱ ቂብላ

የመካ መወረስ ታሪካዊ ለውጥን አስከትሏል። በእስልምና ቅድመ -ታሪክ ሙስሊማኑ ፊታቸውን ወደ ኢየሩሳሌም በማድረግ የዕለት ጸሎታቸውን ያደርጉ ነበር፤ ከመካ መወረስ ወዲህ ግን ወደ ካእባአ  አቅጣጫ መሆን ጀመረ።

ቁርአን ቂብላ ( የጸሎት አቅጣጫን) በተመለከተ በሦስት ቦታዎች ላይ ይናገራል፦

*ሱረቱ 2፥125*

*ቤቱንም ለሰዎች መመለሻና ጸጥተኛ ባደረግን ጊዜ (አስታውስ)። ከኢብራሂምም መቆሚያ መስገጃን አድርጉ። ወደ ኢብራሂምና ወደ ኢስማዒልም ቤቴን ለዘዋሪዎቹና ለተቀማጮቹም ለአጎንባሾች ሰጋጆቹም አጥሩ ስንል ቃልኪዳን ያዝን።*

*ሱረቱ 2፥142*

*ይህቺ በእርግጥ ያለፈች ሕዝብ ናት፤ ለእርሷ የሠራችው አላት፤ ለናንተም የሠራችሁት አላችሁ፤ ይሠሩትም ከነበሩት አትጠየቁም።*

*ሱረቱ 2፥144*

*የፊትህን ወደ ሰማይ መገላበጥ በእርግጥ እናያለን። ወደ ምትወዳትም ቂብላ እናዞርሃለን። ስለዚህ ፊትህን ወደ ተከበረው መስጊድ (ወደካዕባ) አግጣጫ አዙር። የትም ስፍራ ብትኾኑም (ስትሰግዱ) ፊቶቻችሁን ወደ ርሱ አግጣጫ አዙሩ። እነዚያም መጽሐፉን የተሰጡት እርሱ ከጌታቸው ሲኾን እውነት መሆኑን ያውቃሉ። አላህም ከምትሠሩት ሥራ ዘንጊ አይደለም።*

የእስልምና ሥነ-መለኮት ሙህራን ሦስተኛው ጥቅስ ሁለቱን የሚሽር ነው ይላሉ። ይኸውም መሐመድ የአይሁዳውያኑ እና  ክርስቲያኑ ሀይማኖቶች እንደሚቀበሉ ተስፋ አድርጎ እንደነበር ያወሳሉ። ሁለቱንም ሀይማኖቶች አህል አሉ ኪታብ (የመጽሐፉ ሰዎች) ብሎ ይጠራቸዋል፤ ተልዕኮውንም ይቀበሉት እንደሆነ ተስፋ ያደርግ ነበር። በመጨረሻም ሙሀመድ ከእነርሱ መለየቱን ቁርኣን ያስተምራል፦

*ሱረቱ 10፡95*

*ከእነዚያም የአላህን አንቀጾች ከአስተባበሉት አትሁን ። ከከሳሪዎቹ ትሆናለህና።*

መሐመድ ተልዕኮው የይሁዲ- ክርስትና ሀይማኖት ተሐድሶ እንቅስቃሴ አድርጎ ነበር የሚረዳው፡፡ ነገር ግን የነበሩት ኩነቶች አስተሳሰቡን እንዲቀይሩት ሆነ፡፡ አይሁዳውያኑ እና ክርስቲያኑ አዲሱን እምነት ባለ መቀበላቸው ቢያዝንም ፣ ወደ ኃይል እንዲመጣ አድርጎታል፡፡ ቁርኣን እስልምናን ለማይቀበሉ አይሁዳውያኑ እና ክርስቲያኑ መርህ አስቀምጧል፡፡

## 14. የመሐመድ ሞት

መካ ከተወረሰች በኃላ ወደ ተለያዩ ነገዶች እስልምናን እንዲያስፋፉ ሚሲዮናዊያን ተልከዋል፡፡ በዚህም አያሌ ነገዶች እስልምናን ሀይማኖታቸው ፣ መሐመድንም የፖለቲካ መሪያቸው አድርገው ተቀብለዋል፡፡ የቁርኣን ሱረቱ መገለጥ ሂደት የቀጠለ ሲሆን፣ መሐመድ ከሀይማኖቱ ተጓዦች ጋር በአዲሲቱ መካ ታላቅ በዐል አድርጓል፡፡

በዚህ ወቅት መሐመድ ስልሳ አመት ነበር፡፡ በጉዞው ወቅት ይሰማው የነበረ ህመም ወደ መዲና ከተመለሰ በኃላ ባሰ፡፡ ህመሙ ጸንቶበት ሳለ ፣ የሀሽማይት ዮርዳኖስ መንግስት በተባለው ስፍራ መስጊድ በማኖር፣ ለተከታዮቹ የመጨረሻውን ንግግር አደረገ፡፡ ራሱንም በተወዳጅዋ ሚስቱ አይሻ ጭን ላይ አኖረ “ ዘላለም በገነት፤ ምሕረት!” ብሎ ተናግሮ በጸጥታ ህይወቱ አለፈች፡፡ ሞቱም በሰኔ 8 ፣ 632 ዓ.ም እንደሆነ ይገመታል፡፡

የመሐመድ ተከታዮች በመጀመሪያ ታላቅ ሐዘን ውስጥ ነበሩ፡፡ ኦማር አል-ኪታብ ለህዝቡ መሪያቸው እንዳልሞተ ፣ ነገር ግን እንዳቀላፋ በመንገር ጸት ማሰኙቱን መዛግብት ይናገራሉ፡፡ አቡ በኽር ይህን በሰማ ጊዜ በታላቅ ድምጽ “ መሐመድን የሚያመልክ መሐመድ እንደሞተ ይወቅ! አላህን የሚያመልክ አላህ ህያውና የማይሞት መሆኑን ይወቅ !” ብሎ አስታወቀ፡፡

ምንም እንኳ የተለያዩ ሂሶች ቢሰነዘሩም በአለም ላይ ከተነሱት ጥቂት መሪዎች መካካል አንዱ መሐመድ መሆኑን መረዳት አያዳግትም፡፡ በጽናት ህይወቱ ተጽዕኖ ፈጣሪ በመሆን በሚሊዮን የሚቆጠሩ ጽኑ ተካታዮችን ማፍራቱ፣ ከኢየሱስ ክርስቶስ ቀጥሎ ሁለተኛውን ቦታ እንዲይዝ አድረጎታል፡፡በአረብ ምድርም እንደ እርሱ ያለ ታላቅና ታሪካዊ ሰው ፈጽሞ አለመኖሩ ይተማናል፡፡

## III. መሐሙድ በመጽሐፍ ቅዱስ ተነግሯልን

ቁርኣን ቀደምት ቅዱሳን መጻሕፍት ስለ መሐመድ እርግጡን እንዳስቀመጡ ያመለክታል።

*ሱረቱ 7፥157*

*ለነዚያ ያንን እነሱ ዘንድ በተውራትና በኢንጅል ተጽፎ የሚያገኙትን የማይጽፍና የማያነብ ነብይ የሆነውን መልእክተኛ የሚከተሉ ለሆኑት (በእርግጥ እጽፋታለሁ)።*

የኢየሱስንም ማረጋገጫ እንደሚከተለው ያስቀምጣል፡-

*ሱረቱ 61፥6*

*የመርየም ልጅ ዒሳም የእስራኤል ልጆች ሆይ እኔ ከተውራት በፊቴ ያለውን የማረጋግጥና ከኔ በኋላ በሚመጣው መልክተኛ ስሙ አሕመድ በሆነው የማበስር ስሆን ወደናንተ (የተላክሁ) የአላህ መልክተኛ ነኝ ባለጊዜ (አስታውስ)፤በግልጽ ታምራቶች በመጣቸውም ጊዜ ይህ ግልፅ ድግምት ነው አሉ።*

አረብ ኢብኑ ሳሪያ የነብዩን ንግግር ያሰፍራል፡-

*የፈጣሪ መልዕክተኛ የሚከተለውን ሲናገር አድምጫለው፡- " በፈጣሪ መጽሐፍ ላይ የመጨረሻው ነብይ ለመሆኔ ተገልጿል፤ የአባቴ አብርሐም ጥሪ፣ ስለ እኔ የኢየሱስ ትንቢትና እናቴ የተመለከተችው ትንቢት መጀመሪያም እነግራችሁ ዘንድ ወደድሁ። የሁሉም ነብያት እናቶች እናቴ እኔን እንደምትወልድ ይኸውም ብርሃን ከርስዋ ወጥቶ ሶሪያን ሲያበራ ተመልክተው ነበር።[28]*

ሙስሊም ሙህራን መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መሐመድ የሚተነበየውን ለማሰስ ሙከራ አድረገዋል። ሁለቱ ዐበይት ክፍሎች፡- ዘዳግም 18፥18 እና ስለ ጴራቅሊጦስ የሚነጋርው ዮሐንስ 14፥16፣17፣26 ፣15፥26፣ 16፡7 እና ሐዋሪያት ሥራ 1፥4፣5።

[28] አል ቡካሪ ፣ቅጽ 6 ፣ኪታብ አል -ማናኪብ። ኢብን ሐኒባል ፣ ሙሳድ ፣ ቅጽ 4፣ ሐዲስ ኢቱባ።

## 1. የብሉይ ኪዳን ማስረጃ

ክፍሉ እንደሚከተለው ይነበባል፡-

*ዘዳግም 18፥18*

*ከወንድሞቻቸው መካካል እንዳንተ ያለ ነብይ አስነሣላቸዋለሁ ቃሌንም በአፉ አድረጋለሁ ፣ ያዘዝሁትንም ቃል ሁሉ ይነግራቸዋል።*

ሙስሊማኑ ይህ ቃል ለነብዩ መሐመድ ካልሆነ በቀር ሌላ ለማንም አለመነገሩን በሦስት መንገዶች ይሞግታሉ፡-

- ቁርአን በመሐመድ አፍ የተቀመጠ የፈጣሪ ቃል ነው።
- መሐመድ የእስማኤል ዘር በመሆኑ የአይሁዳውያኑ ወንድሞች ነው።
- መሐመድ እንደ ሙሴ ነው።

የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ እግዚአብሔር በአያሌ የብሉይ ኪዳን ነብያት አፍ ላይ ነበር ቃሉን ያኖረው ። ለምሳሌ ፡- እግዚአብሔር ለኤርሚያስ “ቃሌን በአፍህ ውስጥ አኑሬአለው ብሏል (ኤርሚያስ 1፥9)። ኢየሱስም ሲናገር “ የሰጠኸኝን ቃል ሰጥቼአቸዋለሁ” ይላል ( ዮሐንስ 17፥8) ። ዘዳግም 18፥18 አንድ ብቻ ሳይኾን አያሌ እውነተኛ ነብያቶች እንዳሉ ያስረግጣል።

ሁለተኛው ነጥብ መሐመድ የአይሁዳውያን ወንድም እንደሆነ ይናገራል። መሐመድ የእስማኤል ዘር ከሆነ ፣ የአይሁዳውያኑ አጎት ልጅ እንጂ ወንድም ሊሆን አይችልም። ሙሴ ለእስራኤላውያን “አምላክህ እግዚአብሔር የመረጠውን በላይህ ታነግሳለህ፣ ከወንድሞችህ መካካል የሆነውን በአንተ ላይ ንጉስ ታነግሳለህ፣ ወንድምህ ያልሆነውን ከሌላ ወገን ሰው በላይህ ንጉሥ ታደረግ ዘንደ አይገባም” ብሎ ያስጠነቅቃል (ዘዳግም 17፥ 15)። ኢየሱስ ከአይሁድ ነገድ የመጣ ንጉስ ነው፤ በዘዳግም 18፥18 አስቀድሞ የተነገረ ነብይ መሆኑን በግልጥ መገንዘብ ይቻላል።

ሦስተኛው ነጥብ በመሐመድ እና ሙሴ መካካል ያለውን ንጽጽር ያሳያል። ሙስሊማኑ ሙሴና መሐመድ ከሰብአዊ ቤተሰብ የተወለዱ ፣ በምድርም የተቀበሩ በመሆናቸው እንደሚመሳሰሉ ያስረግጣሉ። ኢየሱስ ግን በተዓምራዊ አሰራር ከድንግል የተወለደ፣ ወደ ሰማይም ያረገ ስለሆነ ይለያል ። በተጨማሪ ሙሴና መሐመድ ህግ ሰጪዎች፣ የጦር መሪዎች እና መንፈሳዊ

መሪዎች እንደሆኑ ያስረዳሉ፡፡ ሁለቱም ተቃውሞ የደረሰባቸው ናቸው፤ ከሰደት በኃላ ሀይማኖታዊና ዓለማዊ መሪ ሆነው መነሳታቸውን ይጠቀሳል፡፡ ሁለቱም ዓላማቸውን እውን ያደረጉ፣ የፍልስጥኤም ባህረ-ገብ በኢያሱ እና ኦማር ተከታዮቻቸው ያስወረሱ ናቸው፡፡

ሙስሊማኑ ከላይ የተገለጹትን ንጽጽሮች ፈጽሞ በኢየሱስ ክርስቶስ የሌሉ መኾኑን ይሞግታሉ፡፡ ነገር ግን ይህ እውነት አይደለም! መጽሐፍ ቅዱስ በአመዣኙ ኢየሱስ ነብይ መሆኑን ይነቅሳል (ማቴዎስ 13፥57) ፡፡ ርሱ በገዛ ወገኖቹ ተቃውሞ ደርሶበታል፤ ሙሴም በህይወት ዘመኑ በምድር እስራኤላውያንን እንደመራ ፣ ኢየሱስ ቤተክርስቲያንን ከሰማይ ሆኖ ይመራል፡፡ በዚህም ኢየሱስና ሙሴ ምን ያህል እንደሚመሳሰሉ መረዳት አያዳግትም፡፡

ሙሴ ፣ ኢየሱስ እና መሐመድ የማይካፈሉአቸው ነገሮች አላቸው፡፡ ሙሴ እና ኢየሱስ አይሁዳውያን ሲሆኑ፣ ሙሐመድ ግን እስማኤላዊ ነው፡፡ ሙሴ እና ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ስራ ለመግለጥ ከግብጽ ሲወጡ፣ መሐመድ ግን አንዳች በግብጽ ሆኖ አያውቅም፡፡ ተከታዩን የዘዳግም መጽሐፍ በጥንቃቄ ብናጠና ሙሴ እና ኢየሱስ የሚገናኙባቸው ሦስት ዐበይት መንገዶችን መገንዘብ እንችላለን፡-

*ዘዳግም 34፥ 10-12*

*እግዚአብሔርን ፊት ለፊት እንዳወቀው እንደ ሙሴ ያለ ነብይ ከዚያ ወዲህ በእስራኤል ዘንድ አልተነሳም፤ በግብጽ ምድር በፈርኦንና በባሪያዎቹ ሁሉ ላይ በምድሪቱም ሁሉ ላይ ምልክትንና ድንቅን ያደረግ ዘንድ እግዚአብሔር እንደላከው ያለ በእስራኤል ሁሉ ፊት በጸናች እጅ ሁሉና በታላቅ ማስደንገጥ ሁሉ እንዳደረገው እንደ ሙሴ ያለ አልተነሣም፡፡*

ይህ ክፍል ሙሴ ከኢየሱስ ጋር ብቻ የሚመሳሰልበትን ሦስት እውነታዎች ያስረግጣል፡-

## ሀ. እግዚአብሔር ሙሴን በቀጥታ ተናግሮታል

ሙሴ በእግዚአብሔር እና በእስራኤል ህዝብ ቀጥተኛው መካከለኛ ነበር፡፡ እግዚአብሔር “ሰው ከባልንጀራው ጋር እንደሚነጋገር ፊት ለፊት ከሙሴ ጋር ይነጋገር ነበር” (ዘጸአት 33፥11)፡፡ ቁርኣን ሳይቀር ፈጣሪ እንደ ሙሴ በቀጥታ ያነጋገረው ነበይ እንደሌለ ይመሰክራል(ሱረቱ 4፥164)፡፡

እግዚአብሔር የመካከለኛነት ስራ የሚያስቀጥልበት እንደ ሙሴ ያለ ነብይ እንደሚያስነሳ ተስፋ ቃል ገብቷል። "ሙሴም ደሙን ወስዶ በሕዝቡ ላይ ረጨው ፦ በዚህ ቃል ሁሉ እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ያደረገው የቃል ኪዳኑ ደም እነሆ አለ" (ዘጸአት 24፥8)።

ኢየሱስ ክርስቶሰ የአዲስ ኪዳን መካካለኛ ነው። ሙሴ የመጀመሪያውን ኪዳን በደም እንዳጸደቀ፣ ኢየሱስም እንዲሁ የኃለኛውን ኪዳን አጽድቋል፤ ኢየሱስ "ይህ ጽዋ በደሜ የሚሆን አዲስ ኪዳን ነው" ሲል ተናግራል። በዘዳግም 18፥18 አስቀድሞ የተነገረለት ነብይ በእግዚአብሔር እና በሰው መካከል ለሆነው አዲስ ኪዳን መካከለኛ ነው ። ስለሆነም ኢየሱስ የአዲስ ኪዳን መካከለኛ ነው (ዕብራውያን 9:15)። እርሱ ሲናገር "እኔ ግን ከእርሱ ዘንድ ነኝ፣ እርሱም ልኮኛልና አውቀዋለሁ" ይላል( ዮሐንስ 7፥29)። " ከአብ በቀር ወልድን የሚያውቅ የለም ፤ ከወልድም በቀር ወልድ ሊገልጥለት ከሚፈቅድ በቀር አብን የሚያውቅ የለም" ሲል ያስታውቃል (ዮሐንስ 6፥46)።

ኢየሱስ በእግዚአብሔር እና በሰው መካከል ቀጥተኛው መካከለኛ ነው። እርሱ ራሱ ሲናገር "እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፣ በእኔ በቀር ወደ እኔ የሚመጣ የለም.. አኔን ያየ አብን አይቷል።" (ዮሐንስ 14፥6፣9)። በአንጻሩ የመሐመድን መገለጥ ያየን እንደሆነ፣ የቁርኣን መገለጥ በመላዕኩ ጅብሪል (ገብርኤል) በኩል እንጂ ከእግዚአብሔር ጋር ፊት ለፊት በመገናኘት አልነበረም። መሐመድም በእግዚአብሔር እና በእስራኤል ህዝብ መካካል ባለው ልዩ ኪዳን መካካለኛ ሆኖ አያውቅም።

## ለ. እግዚአብሔር በሙሴ ተአምራትን አድርጓል

ኢየሱስ እና ሙሴ የመካካለኛነት ስራቸውን የሚያረጋግጥ ምልክቶች እና ተአምራቶች አድርገዋል። "ሙሴም በባህሩ ላይ እጁን ዘረጋ እግዚአብሔርም ሌሊቱን ሁሉ ጽኑ የምስራቅ ነፋስ አምጥቶ ባሕሩን አስወገደው" (ዘጸአት 14፥21)። ኢየሱስም የባህርን ነፋስና ሞገድ ጸጥ አሰኝቷል ። በዚህም ደቀመዛሙርቱ በፍርሃት "ነፋስም ባሕርም የሚታዘዙለት ይህ ማነው?" ተባብለዋል። "ነፋሱን ገሰጸው፣ ባሕሩንም ዝም በል ፣ ጸጥ በል አለው። ነፋሱም ተወ ታላቅ ጸጥታም ሆነ" (ማቴዎስ 8፥27፣ ማርቆስ 4፥39)።

መሐመድ ምንም አይነት ተዐምራት እንዳለደረገ ቁርኣን ሳይቀር ያረጋግጣል። የመሐመድ ተቃዋሚዎች " ከጌታውም በእርሱ ላይ ለምን ተዓምር አልተወረደም" እንዳሉ ሱረቱ 6፥37 ይናገራል። መሐመድ ራሱ ፈጣሪ ተዓምራትን እንዲያደርግበት ቢጠይቅም

“ ..ከአላህ ሌላ የምትጠሩዋቸውን ከመግዛት ተከልክያለሁ” ሲል አረጋግጧል፡፡ ይህ የሙሴን ተዓምራቶች በእርሱ ሁናቴ እንዳልተፈጸመ ማሳያ ነው፤ በመካ የመሐመድ ባላንጣዎች “ለሙሳ የተሰጠው ብጤ አይሰጠውም ኖሯልን” ማለታቸውን ሱረቱ 28፥ 48 ይገልጻል፡፡ ቁርአን ተዓምራትን አሳንሶ የሚመለከተው በሙሴ የተደረገው ተዓምራት ሰዎች ስላል ተቀበሉ ከመሐመድ ዘንድ ተዓምራት መጠበቅ እምብዛም አስፈለጊ ስልነበር በሚል ነው፡፡

### ሐ. መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ ክርስቶስ ተስፋ የተገባ ነብይ መሆኑን ያጸናል

ኢየሱስ በግልጽ “ሙሴንስ ብታምኑት እኔን ባመናችሁ ነበር፡፡ እርሱ ስለ እኔ ጽፏልና ” በማለት እውነታውን ያስረግጣል፡፡ በሐዋሪያት ሥራ 3፥22 ሐዋሪያው ጴጥሮስ በዘዳግም 18፥18 አስቀድሞ ተስፋ የተገባ ነብይ ኢየሱስ መሆኑን ማረጋገጫ ይስጣል “ ይህ ሰው ለእስራኤል ልጆች ፡- እግዚአብሔር ከወንድሞቻችሁ እንደ እኔ ያለ ነብይ ያስናሳችኃል ፣ ርሱን ስሙት ያላቸው ሙሴ ነው” ( ሐዋሪያት ሥራ 7፥37)፡፡

ቁርአን ነብይነት ከእስራኤል ልጆች ዘንድ መሆኑን ብቻ ነው የሚቀበለው ፡፡ እግዚአብሔር ለአብርሐም የተናገረውን በአስረጂነት ይጠቅሳል፡-

***ሱረቱ 6፥85***

*ዘካሪያንም፣ የሕያንም፣ ዒሳንም፣ኢልያስንም (መራን)፡፡ ሁሉም ከመልካሞቹ ናቸው፡፡*

ይህ ጥቅስ እስማኤልንም ሆነ ዘሮቹን አያመላክተም፡-

***ሱረቱ 19፥49***

እነሱንም ከአላህ ሌላ የሚግገዙትንም በራቀ ጊዜ ለርሱ ኢስሐቅንና ያዕቆብን ሰጠነው፤ ሁሉንም ነቢይ አደረግንም፡፡

በሱረቱ 29፥27 እና 21፥ 72 ተመሳሳይ አሳብ ተገልጾአል፡፡ እስማኤል አልተመረጠም፣ ስሙም የተጠቀሰው ከያዕቆብ በኃላ ነው! ቁርኣን ለአይሁዳውያኑ የተለየ ከበሬታን ይሰጣል፡፡

***ሱረቱ 2፥47***

*የእስራኤል ልጆች ሆይ! ያችን በናንተ ላይ የለገስኳትን ጸጋዬንና እኔም በዓለማት ላይ ያበለጥኳችሁ (አባቶቻችሁን በጊዜያቸው ከነበሩት ዓለማት ያበለጥኩዋቸው) መኾኔን አስታውሱ፡፡ እስማኤላውያንን ከተመረጡት ወይም ከበላጮች መካከል አልተጠቀሱም፡፡*

*ሱረቱ 38 ፥45-48*

*ባሮቻችንንም ኢብራሂምን፣ ኢስሐቅንና ያዕቆብንም፣ የኀይልና የማስተዋል ባለቤቶች የኾኑን አውሳቸው፡፡ እኛ ጥሩ በኾነች ጠባይ መረጥናቸው፡፡ (እርሷም) የመጨረሻይቱን አገር ማስታወስ ናት፡፡እነርሱም እኛ ዘንድ ከመልካሞቹ ምርጦች ናቸው፡፡ ኢስማዒልንም፣ አልየሰዕንም፣ ዙልኪፍልንም አውሳ፡፡ ሁሉም ከበላጮቹ ናቸው፡፡*

ከእስልምና ወደ ክርስትና የተቀየረው የሀምራን አምበሪን ቁልፍ ማጠቃለያ አሳብ ጠቃሚነቱ የጎላ ነው፤ ቀደም ሲል ዘዳግም 18፥18 ለመሐመድ የተነገረ ትንቢት አድርጎ ነበር የሚረዳው፡-

*በዘዳግም 18፥18ን ለመረዳት በዝግታ እና በጥልቀት አነበው ነበር፡፡ መንፈስ ቅዱስ የመሐመድና የሙሴ ከሰው መወለድ ከተቀረው ሰው ዘር ጋር ከማገኛኘቱ በስተቀር ትንቢቱን ለመረዳት መነሻ አሳብ ሆኖ ሊያገለግል አይችልም፡፡*

*መሐመድ እንደሙሴ ሁሉ አግብቷል የሚለው አሳብም እንዲሁ በአለም ካሉ ሰዎች ጋር እንዲመሳሰሉ ከማድረጉ በዘለል የመሐመድን ነብይነት አያረጋግጥም፡፡*

*መሐመድ እንደሙሴ ዘሮች ጭምር ነበሩት የሚለውም አሳብ ብዙዎች በምድር ልጆች ሊኖራቸው ስለ ሚችል የመሐመደን ትንቢት አያመለክትም፡፡*

*መሐመድ እንደሙሴ እድሜ ጠግቦ ነበር የሞተው፣ የተቀበረውም፡፡ ይህ ምሳሌ ትንቢቱን ለመተርጎም በቂ አይደለም ፤ ምክንያቱም በዚህ አለም ማንኛውም ሰው ይሞታል፣ ይቀበራልም!*

*በዘዳግም 18፥18 ሙሴ የተናገረው ትንቢት ኢየሱስ ክርስቶስን የሚመለከት እንደሆነ ይበልጥኑ ተረድቻለው፡፡ ሌሎች እስከማይጋሩትም ድረስ በሁለቱም ያለው መመሳሰል አስረጂነቱ የላቀ ነው፡፡ በሙሴ መወለድ ፈርዖን በመደንገጡ ብዙ ልጆች እንዲገደሉ እንዳዘዘ ሁሉ፣ ኢየሱስም በሔሮዶስ ግድያ ተሞክሮበታል፡፡ ሁሉም ሰዎች በሚወለዱበት ወቅት ተመሳሳይ የግድያ ሙከራ አልተደረገባቸውም፡፡*

*ሙሴ በሚወለድበት ወቅት ፈርዖን በታላቅ ቁጣ አያሌ ልጆች እንዲገደሉ አዟል፤ በኢየሱስ ውልደት ሄሮድስ ብዙ ልጆች እንዲገደሉ አውጇል፡፡ በመላው አለም እንደ ሁለቱ በእጅጉ የተጠላና የተሰደደ የለም፡፡*

*ሙሴ በልጅነቱ በፈርኦን ልጅ እንደተጠበቀ፣ ኢየሱስም በዮሴፍ ተጠብቋል፡፡ በማንኛውም የሰው ዘር ታሪክ በልጅነቱ ከሞትም ከስደትም አዋጅ በተመሳሳይ ሁኔታ የተጠበቀ የለም፡፡ ሙሴ በልጅነቱ ከቤት*

*ርቆ በግብጽ ኖሯል፤ ኢየሱስም በልጅነቱ ወደ ግብጽ ተሰዷል፡፡ በታሪክ ማንኛውም ልጅ በተመሳሳይ ሁኔታ በልጅነቱ ከቤት ርቆ ግብጽ አልሄደም፡፡*

*ሙሴ እንደ እግዚአብሔር መለኮታዊ መልዕክተኝነቱ በጌታ ኃይል ተአምራቶችን አድረጎአል፡፡ ኢየሱስም እንደ ህያው ቃልነቱ፣ በገዛ ስልጣኑ እና በእግዚአብሔር ኃይል ህሙማንን በመፈወስ፣ ሙታንንም በማስነሳት ተአምራቶችን አድርጓል፡፡*

*ሙሴ የእስራኤልን ህዝብ ከግብጽ ባርነት ነጻ እንዳወጣ ኢየሱስ ሰዎችን ከኃጢአት እና ከሞት እስራት ነጻ አውጥቷል፡፡ ዘዳግም 18 ስለ መሐመድ ሳይሆን፣ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ (ስጋ የለበሰ የእግዚአብሔር ቃል) ነብይነት ነው የሚናገረው፡፡*[29]

## 2.የአዲስ ኪዳን ማስረጃ

ሙስሊማኑ የዮሐንስ እና ሐዋሪያት ሥራ ክፍሎች ስለ መሐመድ የተነገሩ ትንቢቶች ማረጋገጫ አድረገው ይቆጥራሉ ፡-

***ዮሐንስ 14፥16፣17***

*እኔም አብን እለምናለሁ፣ለዘላለም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኃል፡፡ እርሱም ዓለም የሚያየውና የሚያውቀው ስለ ሆነ ሊቀበለው የማይቻለው የእውነት መንፈስ ነው፡፡ ነገር ግን ከእናተ ዘንድ ስለ ሚኖር በውስጣችሁም ስለሚሆን እናንተ ታውቃላችሁ፡፡*

***ዮሐንስ 14፥26***

*አብ በስሜ የሚልከው ግን መንፈስ ቅዱስ የሆነው አጽነኝ እርሱ ሁሉን ያስተምራችኃል፡፡ እኔም የነገርኳችሁን ሁሉ ያሳስባችኃል፡፡*

***ዮሐንስ 15 ፥26***

*ዳሩ ግን እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ አጽናኝ እርሱም ከአብ የሚወጣ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ እርሱ ስለእኔ ይመሰክራል፡፡*

---

29 ሐምራን አምብሪ ፣ እግዚአብሔር የዘላለምን ሕይወት መርጦልኛል (ሪኮን፣ኦስትሪያ፡- መልካሙ መንገድ ኤንዲ) ፣ገጽ 11-15፡፡

*ዮሐንስ 16፥7*

*እኔ ግን እውነት እነግራችኋለሁ እኔ እንድሄድ ይሻላችኃል። እኔ ባልሄድ አጽናኙ ወደ እናንተ አይመጣምና ፤ እኔ ብሄድ ግነ እርሱን እልክላችኃለው ።*

*ሐዋሪያት ሥራ 1፥4፤5*

*ከእነርሱም ጋር አብሮ ሳለ ኢየሩሳሌም እንዳይወጡ አዘዛቸው፣ ነገር ግን ከእኔ የሰማችሁትን አብ የሰጠውን የተስፋ ቃል ጠብቁ፣ ዮሐንስም በውኃ አጥምቆ ነበርና ፤ እናንተ ግን ከጥቂት ቀን በኃላ በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ አለ።*

ሙስሊማኑ ጴራቅልጦስ (Paracletos) (አጽናኝ፣ መካር እና ጠበቃ) የሚለውን የግሪክ መጀመሪያ ቃል ኢየሱስ እንዳልተጠቀመ ይሞግታሉ። ከዚህ ይልቅ ጴሪቅሉቶስ (Periklutos) የቃሉ ትርጉም አሕመድ (የተመሰገነ) (praised one) የሚለውን ተጠቅመዋል ይላሉ።

አያሌ የአዲስ ኪዳን ክፍሎች ግን ጴራቅልጦስ (Paracletos) እንጂ ጴሪቅሉቶስ (Periklutos) እንዳልሆነ መገንዘብ ይቻላል።

የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባባትን በጥንቃቄ ስንፈትሽ ጴራቅልጦስ (Paracletos) በፍጹም ለመሐመድ የተነገረ ትንቢት እንዳልሆነ ማረጋገጥ ይቻላል፦

- ምንባብ ክፍሉ ኢየሱስ ጴራቅልጦስ (Paracletos) እልክላችኃለው ይላል። ጴራቅልጦስ መሐመድ ከሆነ፣ ኢየሱስ መሐመድን ልኮታል ማለት ነው፤ ይህ ደግሞ በሙስሊማኑ ተቀባይነት የለውም!
- ጴራቅልጦስ (Paracletos) መንፈስ ነው ፤ አለም እርሱን አያየውም አያውቀውም። መሐመድ ግን አካል ስለ ነበረው ይታይ፣ ይታወቅም ነበር።
- የጴራቅልጦስ (Paracletos) መምጣት ሲናገር፣ ለደቀመዛሙርቱ "ከእናተ ጋር ይሆናል" ጭምር ብላቸኃል። መሐመድ ግን የኖረው ከደቀመዛሙርት አምስት ክፍለ ዘመናት በኃላ ነበር።
- ክርስቶስ ደቀመዛሙርት ኢየሩሳሌምን እንዳይለቁ አጽናኝ የሆነውን መንፈስ ቅዱስ እንዲጠብቁ ነበር። የጌታን ትዕዛዝ በመጠበቅ አስር ቀናት ያህል በኢየሩሳሌም ቆዩ፣ " ሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው " (ሐዋሪያት ሥራ 2፥4)። በጴንጤቆስጤ ቀን መሐመድ አለመገለጡ ለማንም ግልጥ መሆኑ ልብ ይሏል።

- ኢየሱስ ጴራቅልጦስ (Paracletos) ከደቀመዛሙርቱ ጋር ለዘላለም እንደሚኖር ተነግሯል፡፡ ይህ ለመሐመድ ሊሰራ አይችልም፡፡

በኢየሱስ ተስፋ መሰረት በጴንጤቆስጤ ቀን በደቀመዛሙርቱ ላይ የመጣው አጽናኝ የእግዚአብሔር መንፈስ ነው፡፡ የክርስቶስን ማዕረግ ምክንያት በማድረግ ስለ መንፈስ ቅዱስ መምጣት በተመለከተ "ይህን ኢየሱስን እግዚአብሔር አስነሳው ፤ ለዚህም ነገር እኛ ሁላችን ምስክሮች ነን ፤ ስለዚህ በእግዚአብሔር ቀኝ ከፍ ከፍ ብሎና የመንፈስ ቅዱስን የተስፋ ቃል ከአብ ተቀብሎ ይህን እናንተ አሁን የምታዩትንና የምትሰሙትን አፈሰሰው" ሲል ያውጃል" **(የሐዋሪያት ሥራ 2፥32-33)፡፡**

**የግል ማስታወሻ**

4

# የእስልምና መስፋፋት

## I. እስልምና እጅግ በፍጥነት የተስፋፋው ለምንድን ነው?

እስልምና በፍጥነት እንዲስፋፋ ያደረጉ ልዩ ልዩ መንስዔዎች መንገዱን ከፍተውለታል፡፡ እጅግ ጉልህ ከሆኑቱ ምክንያቶች መካከል የሚከተሉት ይጠቀሳሉ፡-

- በመሐመድ ዘመን የአይሁድ ሀይማኖት እምነቱን የማዳረስ ተልእኮ ያለው አልነበረም፡፡ ከዚህ በተቃራኒው አንዳንድ አይሁዳውያን ምናባዊ የሆነ አይሁዳዊ አስተሳሰብን ከብሉይ ኪዳን ታሪክ ጋር የቀየጡበትን አስተምህሮ ወደ መሐመድ አስተላለፉ፡፡
- በክርስቲያኖች አማካይነት የሚደረገው የወንጌል ማዳረስ ዕንቅስቃሴ ሥፍራውን እንዲወስደው ለእስልምና በተወበት ሁኔታ የዓረቡን ዓለም ቸል ብለውት ነበር፡፡
- የአይሁድ እምነት እና ክርስትና በአንድነት ሆነው ባህላዊ የሆኑ የዓረብ ምድር ሀይማኖቶችን አዳክመውት ነበር፡፡ ይህም የአይሁድ እና ክርስቲያናዊ እምነት ድብልቅ የሆኑ ነገሮችን በማጣመር የሆነ ነው፡፡ እነዚህን ነገሮች መሐመድ በስተኂላ ላይ በአስተምህሮው ውስጥ አካትቷቸዋል፡፡ እጅግ ብዙ ተፎካካሪ የሆኑ የሐሰት ትምህርቶች እና አንጻራዊ እምነቶች በመኖራቸው ምክንያት በተለይ የክርስትና እምነት ውጤታማ በሆነ መልኩ እስላማዊ እምነትን በመቃወሙ ረገድ አልተሳካለትም ነበር፡፡
- የምንኩስና ዕንቅስቃሴ ውጤታማነት ያላቸው ክርስቲያኖች በአካባቢው ላይ እንዳይገኙ ወደ ማድረጉ በመምራት ታማኝ የሆኑትን ሰዎች ከማኅበረሰቡ እንዲርቁ አድርጓቸዋል፡፡
- በሙስሊማኑ አገዛዝ ሥር የነበረው ክርስትና ወገን-ለዩ በሆነ የግብር አከፋፈል፣ ዝቅተኛ የሆነ ማኅበረሰባዊ ደረጃን የሚያሰጥ እንዲሆን በመደረጉ እና ስደትን የሚያስከትል መሆኑ እስልምና በፍጥነት ለመስፋፋቱ አንዱ ምክንያት ነበር፡፡ ይህ ጫና ክርስቲያኖች ዘወትር እምነታቸውን እንዲተዉና እስልምናን እንዲቀበሉ ያደርጋቸው ነበር፡፡

- "በዓረቢያን ደሴቶች ሁለት ሀይማኖቶች እንዲኖሩ ሊፈቀድላቸው አይገባም" ብሎ መሐመድ መናገሩ ተዘግቦለታል፡፡ ይህም ደግሞ በርካታ አይሁዳውያኑ እና ክርስቲያኒ ዓረቢያን ለቅቀው እንዲሄዱ አድርጓቸዋል፡፡[30]
- እስልምና በመሐመድ የእርሱ ተተኪ በሆኑቱ ሰዎች የጦር ኃይል የበላይነት ምክንያት ተሰራጭቷል፡፡ በድሎት እና በውስጣዊ መከፋፈል በመዳከም የፋርስ እና የሮማ የንጉሠ-ነገሥት ግዛቶች ከመሐመድ ዘመን በፊት ማሽቆልቆል ጀምረው ነበር፡፡ አንድነት የነበራቸው፣ በእምነታቸውም ይኮሩ የነበሩቱ፣ እንዲሁም መከራን መቋቋም ከሚችሉቱ ዓረቦች ጋር የሚስተካከሉ መሆናቸውን አሳይተዋል፡፡ የእስልምናን ወታደራዊ ድል በመመልከት ብዙዎቹ ክርስቲያኖኑ የእግዚአብሔር ዕርዳታ ከሙስሊማኑ ጋር ነው ያለው ወደሚል መደምደሚያ ደርሰው ነበር፡፡
- በኋለኛው ዘመን እስልምና በወታደራዊ ኃይል ነው እየተስፋፋ ሲሄድ የታየው፡፡ በዓረብ ነጋዴዎች፣ ሙስሊም በሆኑ ነጋዴዎች የንግድ መስመር እየተስፋፋ የሄደበት ሁኔታ ነው የታየው፡፡ የዓረብ ነጋዴዎች ወደ ህንድ እና ቻይና ይጓዙ ነበር፡፡ እነርሱም ሀይማኖታቸውን ከራሳቸው ጋር አብረው ይዘው ይጓዙ ነበር፡፡

## II. አራቱ ከሊፋዎች

### 1. አቡ-በከር ፡- የመጀመሪያው ከሊፋ

መሐመድ በሞተበት ጊዜ ተግባራዊነት ባለው መልኩ መላው ዓረቢያ በእስልምና ቁጥጥር ሥር ውላ ነበር፡፡ የመጀመሪያው ከሊፋ ወይም "የነቢዩ ተተኪ" ለሁለት ዓመታት የገዥነት ተግባሩን አከናወነ (632-634 ዓ.ም)፡፡ በዓረብ ደሴቶች ውስጥ ያሉ ጎሳዎች በመዲና ባለው ማዕከላዊነት ባለው ፖለቲካዊ አስተዳደር ላይ በዐመፅ ተነሡ፡፡ በባሕሬን፣ በኦማን እና በየመን ያሉ ዐመፆችን ለማክሸፍ አቡበከር ጦር ሠራዊትን ላከ፡፡ በሰኔ ወር 634 ዓ.ም በአል-ሂጅራ፣ እንዲሁም ከአንድ ዓመት በኋላ በፍልስጥኤም የጦር ሠራዊቱን ሽንፈት ተመለከተ፡፡

[30] ኢብኑ ሂሻም ፣ የመሐመድ ህይወት፣ በአብዲ አል-ማሺ የሰፋ ጽሑፍ፣ ቢሊች፣ የህይወት ብርሃን ፣1999፣ቅጽ2፣ገጽ 305፡፡

## 2. ኦማር ፡- ሁለተኛው ከሊፋ

በ634 ዓ.ም ኦማር ከሊፋ ሆኖ ተመረጠ፤ ለአሥር ዓመታትም የገዥነት ሚናውን ተወጣ፡፡ የሙስሊማኑን ግዛት ከህንድ ዳርቻዎች እስከ ሰሜን አፍሪካ ድረስ አስፋፋው፡፡ የኦማር መልካምነት እንዲሁም ግዴታዎቹን በመወጣት ረገድ ያሳየው ታማኝነት በጦርነት የተማረኩትን የብዙዎችን ሰዎች አድናቆትም ተቀባይነትም አስገኘለት፡፡

ከሊፋ በሆነበት በመጀመሪያው ዓመት በሶሪያ እና በፍልስጥኤም ላይ በያርሙክ በተደረገው ጦርነት ድልን እንዲቀዳጅ አደረገው፡፡ ይህ ድል ሁለቱንም በእርሱ አገዛዝ ሥር እንዲገቡ አደረጋቸው፡፡ በቀጣዩ ዓመት ደማስቆ እና ሌሎች ከተሞች ወደቁ፤ ወዲያውም እነርሱን ተከትለው አሌፖ እና አንጾኪያም ወደቁ፡፡ በ636 ዓ.ም ማብቂያ ላይ ኢየሩሳሌም እና መላው ፍልስጥኤም ከዓረቢያ ዕጅ በመጡ ወራሪዎች ዕጅ ወድቀው ነበር፡፡

ኦማር በ636 ዓ.ም ኢራቅን ወረረ፡፡ ከሁለት ዓመታት በኋላ አል-ቃዲሲያ የተባለው ጦርነት እስኪደረግ ድረስ ከባድ ትግል የተካሄደበትን ጦርነት አስነሣ፡፡ በ637 ዓ.ም ኢራቅ በስተሰሜን እስከሚገኘው እስከ ሞስል ድረስ ተወረረች፤ ይህም ከጥንታዊው ነነዌ ሥፍራ በወንዝ ማዶ ያለውን ክልል ሁሉ የሚይዝ ነው፡፡ በቀጣዩ ዓመት በኢራቅ ባሳራህ እና ኩፋ የተባሉት ከተሞች ተቆረቆሩ፤ ደግሞም በእነርሱ ውስጥ ዓረቦች ሰፈሩባቸው፡፡

በባሕረ-ሰላጤው ግዛቶች በ640 ዓ.ም በደቡባዊትዋ ኢራን በምትገኘው በጥንታዊትዋ ሱሳ ከተማ መማረክ የተነሣ ጦርነቱ ቀጠለ፡፡ በስተመጨረሻም ታላቁ የፋርስ ሠራዊት በ642 ዓ.ም በተካሄደው በኒሐዋንድ ጦርነት ተሸነፈ፤ ደግሞም በዘመናዊቷ ቴህራን አቅራቢያ የምትገኘው የባዬ ዋና ከተማ በቀጣዩ ዓመት ወደቀች፡፡

በቀጣይነት በተደረጉ ተከታታይነት ባላቸው ውጊያዎች በኢራን ዙሪያ የሚገኙ ግዛቶችን ኦማር እንዲገዙ ወደ ማድረጉ መጣ፡፡ ይህም ደግሞ ከሺህ ዓመት ቀደም ባለው ጊዜ የዓለም ቀዳሚዎቹ ኃይላት የሚቆጣጠሩት የበረሃ ጦርነትን በማጠናቀቅ የተከናወነ ነገር ነው፡፡

ምንም እንኳ መላው አገሪቱን በአገዛዝ ሥር ለማድረግ በቀጣይ ጥቂት ዓመታትን የፈጀ ቢሆንም፣ በ641 ዓ.ም ኦማር ግብፅን በመውረር እስክንድርያን ማረከ፡፡ በሰሜን አፍሪካ የባሕር ዳርቻዎችን ተያይዘው ያሉ መኖሪያ ሥፍራዎች ተገኙ፡፡ ይህም ደግሞ በአምሳ ዓመታት ውስጥ

የመላው የሰሜን አፍሪካ የባሕር ዳርቻዎችን ያጠቃለለ መስፋፋት በከፍተኛ ፍጥነት የተከሰተበት ሆነ።

## 3. ኡትማን ፦ ሦስተኛው ከሊፋ

ከእነዚህ ታላላቅ ድሎች በኋላ ኦማር አሳፋሪ በሆነ መልኩ በአንድ ባሪያ አማካይነት ተገደለ። እናም ኡትማን የእርሱ ተተኪ ሆኖ ተመረጠ። ኢትማን ለአሥራ ሁለት ዓመታት የገዥነት ተግባርን አከናወነ፤ ነገር ግን የመንግሥትን ሀብትና ንብረት በማስተዳደሩ ረገድ ደካማ ሆነ፤ ደግሞም ዐድሎአዊነት የሚታይበት ሆነ። ይህም የገዛ ራሱ ጎሳዎች የሆኑ ሰዎችን ወደ መንግሥት ባለ ሥልጣንነት አምጥቶ በመሸም የታየ ነገር ነው። ይህም ደግሞ ሰዎችን በእርሱ ላይ ተቃውሞ እንዲያነሡ ወደ ማድረጉ የሚመራ ሆነ። ውጤቱም በ82 ዓመቱ መገደሉ ዕውን እንዲሆን አደረገ።

በ651 ዓ.ም በቻይና ወደ ሚገኘው ወደ ታንግ ሥርወ-መንግሥት አንድ የሙስሊሞማኑ ወኪል የተላከው ኡትማን ከሊፋ በነበረበት ጊዜ ነበር። ወደ እስልምና የተቀየሩ ብዙዎች ነጋዴዎች በዚህ ጊዜ በየብስም ሆነ በባሕር በሁለቱም በኩል ወደዚህ ታላቅ ምድር ሰርገው ይገቡ ጀመር።

## 4. አሊ ፦ አራተኛው ከሊፋ

የገዥነት ዘመኑ ከ656 እስከ 661 ዓ.ም የቆየው አሊ በእስልምና ውስጥ የመጨረሻው ለሚባለው መከፋፈል ቀድሞውኑ በር የከፈተ ሰው ነበር።

ከኡትማን ነገድ የሚመደበውን ሙአዊሃን የሶርያ ገዥ አድርጎ ሾመው፤ ይህም ደግሞ የኡትማን ገዳዮችን እንዲሰቀሉ ማድረግን ቸል ብሏልና ለገዥነት የማይበቃ ሰው ነው የሚል ክስን ከሙአዊሃ ሊያስከትልበት ቻለ።

አሊ ዋና ከተማውን ከመዲና በኢራቅ ወደ ምትገኘው ወደ ኩፋ አሸጋገረ። የሙአዊሃ ዓመፀኞች የመሐመድ መበለት የሆነችውን አይሻን በሠራዊታቸው መካከል በግመት ላይ እንድትቀመጥ አደረጉዋት። የግመል ውጊያ ተብሎ በሚጠራው ጦርነት ላይ አሊ እነርሱን አሸነፋቸው። ምንም እንኳ አይሻ እርሱን በግልጽ የተቃወመችው ብትሆንም፣ አሊ እርሷን በአክብሮት ነበር የያዛት፤ እርስዋንም ወደ መዲና መለሳት። ምንም እንኳ ሙአዊሃ ብዙ ሠራዊት የላከበት ቢሆንም፣ ብዙም ሳይቆይ አሊ ሞተ።

ሙስሊሞች ተከፋፈሉ፤ ብዙዎች ሙአዊሃን ተከተሉ፤ ደግሞም ካሪያህ (ተከታዮች) ተብለው ተጠሩ። ሌሎች አሊን ተከተሉ፤ ደግሞም ሕጋዊነት ያለው ወራሽ በማድረግ ትልቁን ልጁን ሀሰንን ከሊፋ አደረጉት። እነዚህም ሺዓት አሊ (የአሊ ቡድን አባላት) በመባል ተጠሩ።

በኋላም ሙዓዊሃ በመዲና በመንግሥት ግምጃ ቤት ያለውን ገንዘብ ሁሉ እንደሚሰጠው ቃል በመግባት ሀሰንን አሳመነው። ሀሰን ከሥልጣኑ እንዲወገድ ከተደረገ በኋላ ከሚስቶቹ አንድዋ መርዝ አበላችውና ሞተ። የሺዓ ቡድን አባላት ከሊፋነቱ በመሐመድ ቤተሰብ ዘንድ ሊሆን እንደሚገባ በማመን የሀሰን ታናሽ ወንድም ሁሴንን ከሊኖ ሆኖ ወደ ኩፋ እንዲመጣ ጋበዙት። እርሱም ቤተሰቦቹን እና አነስተኛ ሠራዊት ይዞ ወደ ኩፋ ሄደ።

ነገር ግን ከአሁንዋ ባግዳድ አቅራቢያ በካራ ባላ ጦር ሠራዊቱን ከሶሪያ እየመራ የመጣው የሙዓዊሃ ልጅ ዛይድ በመንገድ ላይ ገጥሞ ገደለው። በሺዓ ብሎም በካሪያህ በስተኋላ ላይ ሱኒዎች በመባል በሚጠሩቱ መካከል ያለው መከፋፈል እስከ አሁኑ ዘመን ድረስ ቀጥሏል።

## III. የእስልምና ሥርወ-መንግሥት

### 1. የኦሜያድ ሥርወ-መንግሥት

የአሊ ሁለት ልጆች መሞት ፖለቲካዊ አገዛዝን ለሚያራምደው እስልምና ሙዓዊሃን ብቸኛው መሪ አደረገው። በትንሽዋ እስያ፣ በኢራቅ እና በግብፅ የሙስሊም ሠራዊት ወረራ እየቀጠለ በሄደ መጠን በደማስቆ ያለው የሙዓዊሃ ከሊፋነት እየበረታ ሄደ። በዚያን ጊዜ ውጤታማ በነበረው በሙስሊም ግዛት ውስጥ እርሱ የገዥነት ተግባሩን እየተወጣ ነበር።

መጨረሻው እንደ መጣም በመገንዘብ ልጁን ዚያድን የእርሱ ተተኪ አድርጎ መረጠው። በዚህም ደግሞ የሥርወ-መንግሥትን መርኅን ወደ እስልምና አመጣ። የኦሜያድ ሥርወ-መንግሥት ከ661 እስከ 750 ዓ.ም የገዥነት ተግባሩን አከናወነ።

በዚህ ወቅትም የእስልምና መስፋፋት እየቀጠለ ሄደ። በአንድ ክፍለ ዘመን ውስጥ የሮማ ንጉሠ ነገሥት ግዛት ከፍተኛ ደረጃ ላይ ከደረሰበት ሁኔታ በበለጠ በርካታ ሥፍራዎችን በግዛቱ ሥር አስገብቶ ነበር። በ711 ዓ.ም ሙስሊሞች ሰሜን አፍሪካን ተሻግረው ወደ ስፔን መጡ። በ720 ዓ.ም በፓይሬኒስ አድርገው ወደ ፈረንሳይ መንገዳቸውን በኃይል ከማቅናታቸውም በፊት ሰፋ ባለ መልኩ እንድትገዛ አደረጉዋት።

በ732 ዓ.ም በቱርስ በተደረገው ጦርነት ላይ ብቻ በቻርለስ ማርተል ዕጅ ሙስሊማውያን ሠራዊቶች ወሳኝ በሆነ መልኩ ድል ተመቱ። ይህም ደግሞ እስልምና ወደ ሰሜን አውሮጳ የሚያደርገውን ጉዞ ገታው። የቱርስ ጦርነት ከመሐመድ ሞት አንድ መቶ ዓመት በኂላ የተደረገ ውጊያ ነበር።

## 2. የአባ ሳይድ ሥርወ-መንግሥት

የሺዓ ቡድን አመራሩን ዳግመኛ በማግኘቱ ላይ ተስፋ አልቈረጠም ነበር። እናም በ750 ዓ.ም በሁለት ጦርነቶች የመጨረሻውን የኦሜዳድ ሥርወ-መንግሥት ከሊፋ አሸነፈ። ከዚህ በመቀጠልም የመሐመድ አጎት የአል-አባስ ልጅን ከሊፋነት በኩፋ አዘጋጁ። አዲሱ የአባሳይድ ሥርወ-መንግሥት ከ 500 ዓመታት ለበለጠ ጊዜ (750-1258 ዓ.ም) መቆየት ቻለ።

በ755 ዓ.ም አንድን ዓመፅ ለማምከን በመንግሥት አማካይነት ሰፊ የሆነ የሙስሊም ወታደሮቸችን የያዘ ሠራዊት ወደ ቻይና ተጠራ። ንብረት ተሰጥቶአቸው ሀይማኖታቸውን በዚያ ለማቋቋም ሰፈሩ። ዛሬ ላይ ምንም እንኳ ታላቅ ቍጥር ያላቸው ሙስሊሞች በሰሜን ምዕራብ ቻይና የሚገኙ ቢሆኑም፣ ሙስሊማኑ በእያንዳንዱ የቻይና ግዛት ውስጥ ይገኛሉ። ልክ በሌሎች አገራት እንደ ሆነው ሁሉ ሙስሊማኑ አጠቃላዩን ማኅበረሰብ /ሕዝብ/ ይመስላሉ።

ይሁንና የሆነ ልዩ የሆነ ልብስ ዐይነት የመልበሱን ነገር ሥራዬ ብለው ይዘውታል። ከዚህም መካከል በተለይ ልዩ ዐይነት ቆብ እንዲሁም የወገብ መቀነቶች፣ በተጨማሪም ደግሞ በፍጥነት እነርሱ ሙስሊማኑ እንደ ሆኑ የሚያሳውቁ ባህላዊ ልማዶችን ይዘው እናገኛቸዋለን።

የአባሳይድ ሥርወ-መንግሥት ሰላምን፣ ፍትሕን እና ብልጽግናን ዕውን እንዲሆኑ በማድረጉ አጠቃላይ የሆነ ተቀባይነትን አግኝቷል። በመጀመሪያዎቹ 350 ዓመታት የአገዛዝ ዘመኑ ጥንታዊውን የግሪክ ትምህርት ከፍልስፍና እና ከህክምና ሳይንስ ጋር በላቀ መልኩ በማቀናጀት ለዘመናዊትዋ ዓለም ትልቅ አስተዋጽኦ አድርጓል።

በቀደምት ዓመታቱ 8ኛው ክፍለ ዘመን በሚጀምርበት አካባቢ የሙስሊማኑ መስፋፋት ከአክሰስ ወንዝ በስቲያ ወደ ማዕከላዊ እስያ አምርቷል። ህንድ በ658 ዓ.ም ተጠቅታ ነበር፤ ዳሩ ግን እስከ አሥራ አንደኛው ክፍለ ዘመን ጅማሮ ድረስ በዚያ ክልል የተገኘ ምንም ስኬት አልነበረም። ስኬት የተገኘው የሩዝኒው ማህሙስ መጠነ-ሰፊ የሆነ ወረራ ባካሄደበት ጊዜ ብቻ

ነው። በአሥራ ሦስተኛው ክፍለ ዘመን መላው ሰሜናዊ ህንድ ከኢንዱስ በር ጀምሮ እስከ የጃንግል ዴልታ ድረስ ያለው ሁሉ በሙስሊማኑ ዕጅ ወደቀ፤ ደግሞም በምድር ዙሪያ ያለውን ሦስተኛውን መንገድ ጨምሮ ሰፊ ሥፍራዎችን /ግዛትን/ እስልምና ተቆጣጠረ።

የሰባተኛው ክፍለ ዘመን መገባደጃ ዓመታት ላይ የእስልምና ሀይማኖት ከሊፋ ክርስትናን በብሔራዊ ደረጃ ለመቀበል የመጀመሪያዪቱ አገር ለሆነችው ለአርሜንያን ገዠችን ሾመ። ይህ የበላይነት በአጭሩ በመስቀል አራማጆች አማካይነት ተቀለበሰ። በአሥራ አንደኛው ክፍለ ዘመን በሜድትራኒያን የሚገኙት ሲሲሊ እና ማልታ ደሴቶች በሙስሊማኑ ዕጅ መልሰው ወደቁ።

አውሮጳውያን የሆኑ ክርስቲያናዊ ኃይላት እነዚህን ደሴቶች መልሰው ወሰዱዋቸው፤ ደግሞም በ1099 ዓ.ም እስከ ኢየሩሳሌም ድረስ ሙስሊማኑን መልሰው እንዲያፈገፍጉ አደረጉዋቸው። በ1187 ዓ.ም ሳላዲን በሂቲን ጦርነት እስኪያሸንፍ ድረስ የተቀደሱ ሥፍራዎችን አውሮጳውያን ክርስቲያኖች ተቆጣጥረዋቸው ቆዩ። ከዚህ በኋላ የምሥራቅ ሜድትራኒያን ምድሮች ቀስ በቀስ ሙሉ በሙሉ በሙስሊሞች ኃይል ቁጥጥር ሥር ዋሉ።

በወታደራዊ መልኩ የመስቀል ጦርነት አድራጊዎች ጊዜያዊ የሆነ ስኬትን ማለፊያ በሆነ መልኩ ተቀዳጁ። በተጨማሪም በሙስሊማኑ እና በክርስቲያኖኑ መካከል እንደ አለመታደል ሆኖ የተከሰተውን ጠላትነት አተረፉ። ይህም የሁለቱም ሀይማኖቶች ወኪሎች ከቶውንም በሙላት ያላገገሙበት፣ እንዲሁም በእስላማዊ እና በምዕራብ አገራት መካከል ያለ ግንኙነት ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድር ሁኔታ የቀጠለበት ነው።

## IV. ተገዥ ሕዝቦች

እስላማዊ በሆነው "በመካከለኛው ዘመን" ከ 1280 እስከ 1480 ዓ.ም ድረስ በፍጥነት እንደ ገሰገሰ የሚቈጠርበት ሲሆን፣ የሙስሊም ግዛት በእስያ፣ በአፍጋኒስታን እና ራቅ ወዳለው የህንድ ግዛት ክፍል ተስፋፋ። በአሥራ አምስተኛው እና በአሥራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመናት በፍጥነት በርካታ ወደ እስልምና የተለወጡ ሰዎች ወደ ተገኙበት ወደ ጃቫ የእስልምና ሀይማኖት ገባ። በተጨማሪም እስልምና ወደ አጎራባች የሱሜትራ ደሴቶች ገባ፤ ከዚህም ደግሞ እስከ ፊሊፒንስ ድረስ ወደ ሌላው የህንድ ምሥራቃዊ ደሴቶች ተሰራጨ።

ሂጅራ ከተከናወነ ከስምንት ዓመት በኋላ "ተገዥ ሕዝቦች" የሚል መርኅን መሐመድ ወደ ገሃድ አወጣ ወይም አስተዋወቀ። በዚህ መርኅ ሥር ለሙስሊማኑ አገዛዝ የሚታዘዙ መሆናቸውን ለማሳየት የታዘዘውን ግብር የሚከፍሉ ከሆኑ፣ አንዳንድ የሌላ ሀይማኖት ተከታይ የሆኑ ማኅበረሰቦች የገዛ ራሳቸውን እምነት መያዝ ይችላሉ። ግብር ለሚለው የዓረቢኛ ቃሉ ጂዚያ ይሰኛል። ሥርወ-ቃሉ ከሆነው ከጃዛ የመጣ ሲሆን፣ ፍቺውም "ቅጣት" ማለት ነው። እንግዲያውስ ግብር የመክፈል ልምምድ ለታማኝነት ማጣት የሚሆን ቅጣት፣ እንዲሁም የእስልምና ሀይማኖትን ለመቀበል እንደ ጉርሻ የሚታይ ተደረጎ ተዘጋጀ።

እስልምና በጂዛ አማካይነት የሕይወት እና የንብረት ጥበቃ ሊያደርግላቸው ዋስትና የተሰጣቸው ሀይማኖቶች ክርስትና፣ የአይሁድ ሀይማኖት፣ ማጃይና፣ የሳምራውያን እና የሳቢያን ሀይማኖቶች ብቻ ነበሩ። ምንም እንኳ አንዳንድ አይሁዳውያን ቡድኖች እና ሶሮአስትሪያውያን ይህ የክብር ደረጃ የተሰጣቸው ቢሆንም፣ አንዳንዶቹ ቡድኖች ግን ከፍ ባለ መጠን የኦርየንታል ክርስቲያኖች ነበሩ። እነርሱ የክርስትና እምነታቸውን ለክፍለ ዘመናት በሁሉም ዐይነት አስቸጋሪ ሁኔታዎች እና ገደቦች ውስጥ ይዘው የዘለቁ ነበሩ።

በእስላማዊ መንግሥት አገዛዝ ሥር ሙስሊም ያልሆኑ ወገኖች ሆኖ መኖር ዋጋ ያስከፍላል፣ ደግሞም አሁንም እንኳ ይህ ነገር ዋጋ እያስከፈለ ነው። ይህም ግብርን ከመክፈል የበለጠ ነገር ነው። በከሊፋዎቹ አገዛዝ ሥር የእስልምና ሀይማኖትን መቀበላቸውን የማይናገሩ ሰዎች በማኅበራዊም ሆነ በግል ሕይወታቸው በሚጣሉባቸው ገደቦች ሳቢያ ይሰቃያሉ። ሱረቱ 9÷29 እነዚህን ገደቦች እያጸደቀ ሲናገር "በዕጃቸው ግብሩን እስኪከፍሉ ድረስ፣ ደግሞም የተዋረዱ እስኪሆኑ ድረስ" በማለት ይናገራል።

የኦማር ቃል ኪዳን ከእነዚህ ገደቦች አንዳንዶቹን ዘርዝሮአቸዋል። ይህም በአገር ላይ ነዋሪ የሆኑ ክርስቲያኖች ለሙስሊም ባለ ሥልጣናት መገዛት ከእነርሱ የሚጠበቅባቸው መሆኑን በሚገልጽ አንድ ደብዳቤ ላይ የሰፈረ ነው። ከረቂቆቹ አንዱ እንደሚከተለው ቀርቧል፦

> *"ወደ እኛ በመጣችሁ ጊዜ ለኑሮዋችን፣ ለቤተ ሰባችን፣ ለንብረታችን እና ለሀይማኖታችን ተከታይ ሰዎች በእነዚህ ቅድመ-ሁኔታዎች እናንተ ዋስትና እንድትሰጡን ጠየቅናችሁ። ይህም ራሳችሁን ትሑት ለማድረግ ግብርን በዕጃችሁ እንድትከፍሉ፣ በማምለኪያ ሥፍራ ላይ በቀንም ሆነ በማታ አንድን ሙስሊም ከመምጣት እንዳታስቆሙት፣ ወደዚያ እንዲገባ እንድታደርጉት እና ምግብ በመስጠት በዚያ እንዲያሳልፍ፣ እንዲሁም በሮቻችሁን ለእርሱ ክፍት*

*እንድታደርጉለት፣ ናኩስን /ሆድን/ እንዲመታ እንድታደርጉ፣ በምንም መልኩ በየትኞቹም ቤቶች የጣዖት አምልኮ እንዳታኖሩ እና ወደዚያ እንዳትጋብዙዋቸው፣ በማምለኪያ ሥፍራዎቻችን በየትኞቹም መንገዶቻችን ወይም በገባያ ሥፍራችን መስቀልን እንዳታኖሩ፣ ቍርዓንን እንዳትማሩና ለልጆቻችን እንዳታስተምሩ፣ የትኞቹንም ዘመዶቻችንን እነርሱ የሚፈልጉ ከሆኑ ከእስልምና እንዳይመለሱ እንዳትከለክሉ፣ ፊት ለፊት ጠጕራችንን እንዳትቈርጡ፣ በወገባችን ዙሪያ የምናደርገውን መቀነት እንዳታስሩ፣ በሀይማኖታችን ያሉ ነገሮችን እንዳትለማመዱ፣ በአለባበስ ሙስሊማኑን እንዳትመስሉ፣ በገጽታ፣ በኮርቻ፣ በማኅበረሰባችን ውስጥ ያሉ ቅርጾችን እንዳትጠቀሙ (እኛ እነዚህን በዓረብኛ ልናደርጋቸው የሚገቡ ናቸው)፣ ኩንያሳችንን (ማዕረጋችንን) እንዳትጠቀሙም ሆነ እነርሱን እንድታከብሩም ሆነ እንድትወድሱ፣ በአንድነት በምንገናኝ ጊዜ ስለ እነርሱ ጥብቅና እንዳትቆሙ፣ በመንገዳቸው እና በአካሄዳቸው እነርሱን እንዳታርሙ፣ ቤታችሁን፣ መሰብሰቢያ ሥፍራችሁን ከሰው ተገልሎ መቀመጫ ሥፍራችሁን ወይም ቡድናችሁን ከእነርሱ ቤት ከፍ ባለ መልኩ እንዳትሠሩ፣ የጦር መሣሪያዎችን እና ሰይፍን እንዳትይዙ፣ በሙስሊም አገራት በከተማም ሆነ በጕዞ ላይ ሳላችሁ እንዳትጠቀሙዋቸው፣ የወይን ጠጅን እንዳትጨልጡ፣ እንዲሁም በማሳያ ላይ እንዳትደራደሩ፣ ሙስሊማኑ በሚኖሩባቸው መንገዶች ላይ ለሙታን ሻማን እንዳታበሩ፣ በመቃብር ሥነ ሥርዓት ላይ ድምፃችሁን ከፍ እንዳታደርጉ፣ ወደ ሙስሊሞች አጠገብ እንዳታቀርቡዋቸው፣ ሙስሊሞችን እንዳታስደነግጡ፣ የሙስሊሞች ንብረት የሆኑ ባሮችን የገዛ ራሳችሁ አድርጋችሁ እንዳትይዙ" የሚሉ ናቸው።*[31]

እነዚህን ስምምነቶች በእኛ እና ተባባሪ በሆኑ ሀይማኖተኞች ላይ ተግባራዊ እንዲሆኑ አደረግናቸው። እነዚህን የማይጠብቅ ሰው ምንም ዐይነት ጥበቃ አይደረግለትም። እንደዚህ ያሉ መመሪያዎች ጠቅለል ባለ አነጋገር ለተራዘሙ ጊዜያት ወይም በበርካታ ግዛቶች ላይ ተግባራዊ የሚደረጉ አይደሉም። የዚህም ምክንያቱ በከፊል ቀዳሚ በሆኑቱ ዘመናት ብዙዎቹ የመንግሥት አገልጋዮች፣ መምህራን ወይም ሐኪሞች ክርስቲያኖች ወይም አይሁዳዊ በመሆናቸው ነው። ይህም ያለ ምንም ጥርጥር ሰፊ ቍጥር ያላው ክርስቲያኖችን በሙስሊም አገራት ውስጥ እንዲኖሩ አድርጓቸዋል። ይህም በግብፅ ያሉ ኮፕቲክ (ኦርቶዶክሳውያን) ክርስቲያኖችን የሚጨምር ጉዳይ ነው። በተጨማሪም በቱርክ ያሉ አርሜኒያውያንን፣ እንዲሁም በቱርክ የሚገኙ ንስጥሮሳውያንን የሚመለከት ጉዳይ ነው።

[31] ትሪተን ፣ ኤ፣ ኤስ፣ ካሊፎች እና እስላማዊ ያልኾኑ ርዕሰ ጉዳዮች( ለንደን፦ ፍራንክ ኬስ እና ኅ.የ.ኮ ፣ 1974)፣ ገጽ .5-8።

# V. በዘመናዊ ወቅት የተደረገ መስፋፋት

## 1. ከኂለኛው የአሥራ አምስተኛው ክፍለ-ዘመን እስከ አሁን ዘመን

በዚህ ዘመን እስልምና በብዙዎቹ የአፍሪካ አገሮች የተስፋፋበት ነው፤ ይህ ነገር የሆነው በመጀመሪያ በባሪያ ንግድ ሲሆን፣ በቀጣይ ደግሞ እነርሱ ራሳቸው ለእምነታቸው መልእክተኞች በሆኑ ነጋዴዎች ተነሣሽነት አማካይነት ነው። በቅርቡ እምነትን በማስፋፋት ረገድ መልእክተኛ የመሆን ጉዳይ ኢምንት ያህል ሥፍራ ያለው ነው። ይሁንና የእስልምና ሀይማኖት እና ባህል ተጽዕኖን የሚያሳድሩ በመሆናቸው በየዓመቱ የሕዝብ ብዛት ዕድገት ራሱ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ሰዎችን ወደ እስልምና የሚጨምር ሆኖአል።

ለእስልምና ጥንካሬን በመስጠት ረገድ ሌሎች ሁለት ምክንያቶች አስተዋጽኦ አድርገዋል። የመጀመሪያው ምንም እንኳ ለእምነት የመልእክተኝነት ተግባር የሚፈጽመው የእስልምናው ክፍል አናሳ ቢሆንም፣ ሰዎችን ወደ ራሳቸው ሀይማኖት በማምጣቱ ላይ ጠንክረው ይሠራሉ። ሁለተኛው ሙስሊም አሳታሚዎች እስልምናን በማስፋፋት ረገድም ሆነ የእምነቱ ተከታዮችን በማስተማሩ ረገድ ብርቱ መሣሪያ መሆናቸው ነው።

ፖለቲካዊ በሆነ መልኩ እስላማዊ መነቃቃት ተከሰተ፤ ይህም ደግሞ ሀብታም በሆኑ ነዳጅ አምራች አገሮች ጥላ ሥር እና በቅርቡ እንደ ሞቱት እንደ ሀያቶላ ሆሚኒ ባሉት ሃይማኖታዊ መሪዎች ተጽዕኖ አማካይነት የሚደረግ ነው። የዓረብ መንግሥታት እስልምናን ለማስፋፋት ከነዳጅ ዘይት ሽያጭ የሚገኝ ዶላርን ይጠቀሙበታል።

እስልምና ራሱ የመንግሥት መዋቅር በመሆኑ አክራሪ ሙስሊማኑ የሙስሊማኑን የሻሪያ ሕግ በጥብቅ የሚሠራበት ሃይማኖት እና መንግሥት የተደባለቁበትን የሆሚኒ ዐይነቱን አስተዳደር ዕውን እንዲሆን ይፈልጋሉ። ልክ እንደ ግብፁ ፕሬዚዳንት አንዋር ሳዳት ያሉቱ የዚህ አሳብ ተቃዋሚዎች አንዳንዴ ያለ ጊዜያቸው መሞት ያጋጥማቸዋል።

## 2. እስልምና በተባበሩት አሜሪካ መንግሥታት (በዩ. ኤስ. ኤ)

በፎርት ዋይን ኢንዲያና ባለው የሳሙኤል ዝዌመር የእስልምና ጥናቶች ኢንስቲቲዮት አባል የሆነው ጀምስ ሮማይኔ በጻፈው መጣጥፍ እስልምና በአሜሪካ ከ 7% - 10 % በመቶ የዕድገት

መጠን ዕያደገ ነው ሲል ይናገራል።[32] በጥቂት አሥርት ዓመታት ውስጥ ቊጥራቸው ከጥቂት መቶ ሺህዎች ወደ ስምንት ሚሊዮን ማደግ ችሎአል። በአሜሪካም ውስጥ የሚገኝ ትልቁ ሦስተኛ ሃይማኖት ለመሆን ችሎአል።

ብዙዎች እንደ ሙስሊማኑ ወደ አሜሪካ እንደ ተማሪዎች ሆነው መጥተዋል። ደግሞም በአሜሪካ በእያንዳንዱ ዩኒቨርሲቲ የሙስሊም ተማሪዎች ማኅበር ያለበት ነው። እያንዳንዱ ማኅበር ከሌሎች ጋር በብሔራዊ ጃንጥላ በኩል በተቋቋማት እና በኢንተርኔት በኩል ተያይዟል።

የሙስሊማኑ ሰፊ የሆነው ትኩረት ያለው በከተሞች አካባቢ ነው፤ ነገር ግን በእያንዳንዱ የአሜሪካ ትናንሽም ሆነ ትላልቅ ከተሞች ውስጥ ይገኛሉ። በትላልቅ ከተሞች ውስጥ የሚገኙ የአብያተ ክርስቲያናት ሕንጻዎችን ይገዛሉ፤ ደግሞም እነርሱን ወደ መስጅድነት ይቀይሩዋቸዋል።ለመሆኑ እስልምናን ለአሜሪካውያን እጅግ ተመራጭ እንዲሆን ያደረገው ምንድን ነው? ጄምሴ ሮማይኔ ይህንን በተመለከተ አምስት ነጥቦችን ይዘረዝራል፦

(1) ሙስሊማኑ የምዕራቡ ማኅበረሰብ ቀውስ ውስጥ ገብቷል፤ ደግሞም ምግባረ-ብልሹ ሆኖአል ብለው ያምናሉ። ለዚህ ማስረጃ ተደርጎ የሚቀርበውም የክርስትና ውድቀት ነው፤ በተጨማሪም ዕውነተኛ ከፈጣሪ የተሰጠ ሀይማኖት አይደለም በሚል የሚቀርበው መከራከሪያ ነው።

(2) ክርስትና ለሰው ልጆች ያለው አሉታዊነት መልእክት ብቻ ነው ሲሉ ሙስሊማኑ ያምናሉ። ሙስሊማኑ በጥንተ-አብሶ (በውርስ ኃጢአት) አያምኑም። ስለዚህም ሁሉም የሰው ልጅ እስልምናን ለመቀበል እና ለመዳን ይችላል ይላሉ።

(3) ሙስሊማኑ እስልምናን እንደ ዕውነተኛ ፣ ዓለም አቀፋዊ ፣ በፈጣሪ የተሰጠ ሀይማኖት እና ከፈጣሪ የመጣ የመጨረሻው መገለጥ ነው ብለው ያምናሉ።

(4) ሙስሊማኑ እስልምናን የንጽሕና እና የሰላም ሀይማኖት ነው ብለው ያስባሉ። እስልምና ቤተ ሰብን መሠረት ያደረገ፤ እንዲሁም ሴቶችን እና ልጆችን ከምግባረ-ብልሹነት ይጠብቃል ብለው ያምናሉ። በተጨማሪም ድሆችን ይረዳል፤ ወደ ጎረቤቶችም ሲገባ ያጸዳቸዋል ብለው ያምናሉ። ዕንክብካቤ የሚያደርግ ማኅበረሰብን ይፈጥራል፤ ይህ ማኅበረሰብ ለግለሰቦች እና ለቤተ ሰቦች የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ የሚያቀርብ ነው።

---

[32] ጄምስ ሮሜይን ፣ ሚሲዮናዊነት በየወሩ፣ ግራንድ ራፒድስ ፣ ጥር 1999።

(5) ሙስሊማኑ በሀይማኖት እና በመንግሥት መካከል ምንም ልዩነት አያደርግም፡፡ ይህም እስላማዊ ለሆነ መንግሥት ሃይማኖታዊ ሕጎችን ለማውጣት እና ሃይማኖታዊ ነፃነቶችንም ለመገደብ መብቱን ይሰጠዋል፡፡ እስልምና በአሜሪካ ሥነ-ትምህርታዊ እና ፖለቲካዊ መዋቅር ውስጥ እስላማዊ ትምህርት ቤቶችን ለመክፈት፣ አካባቢያዊ እና ብሔራዊ ባለ ሥልጣናትን ለማስመረጥ ይሠራል፡፡

ሮማይን ስለ እስልምና እንዲያውቁ የአገሬውን ሰዎች ይመክራል፡፡ በተጨማሪም ይበልጥ ስለ ሙስሊማኑ እንዲጸልዩ፣ በይበልጥም ሙስሊማኑን እንዲወድዱ ይጠይቃቸዋል፡፡ ከክርስቲያኑ ጋር በተቃረነ መልኩ እስልምና ሙስሊማኑን ከእነርሱ የተለዩ ሰዎችን እንዲወድዱ አያስተምርም፡፡

በሙስሊማኑ መካከል ሥራዎችን እንዲሠሩ፣ ሙስሊማኑን በወንጌል ለመድረስ አብያተ ክርስቲያናት ተሳትፎ ማድረጋቸውን እንዲያበረታቱ፣ እንዲሁም ክርስቲያናዊ ምስክርነቶችን እንዲደግፉ ለክርስቲያኖች ጥሪውን ያቀርባል፡፡ እርሱ የሚሰጠውን ምክርም በእነዚህ ቃሎች ይደመድማል፡- “የበረታችሁ ሁኑ! እግዚአብሔር ሙስሊማኑን እየለወጣቸው ነው! ከዚህ ቀደም ከሆነው በላይ በርካታ ሙስሊማኑ ወደ ክርስቶስ እየመጡ ናቸው፡፡”

**የግል ማስታወሻ**

# 5

# የሙስሊማኑ እምነት

## I. የእስልምና አስተምህሮ እና ህጎች መሰረት

ከቁርኣን ባሻገር ሦስት የእስላማዊ አስተምህሮ ህግ መሰረቶች አሉ፡-

- ሀዲስ ( የባሕል እንዱ አካል)፡፡
- ኪያስ( Quias) ( በሱኒዎች የቁርአንና ሀዲስ ህግ ነክ ጥያቄዎች፤ በሺአዎች መካካል ደግሞ አመክንዮአዊ አንድምታዎች)፡፡
- ኢጅማ ( የብዙኃኑ እስላማዊ ሊቃውንት ስምምነት)፡፡

### 1. ሀዲስ

ሀዲስ በእስልምና ከቁርኣን ቀጥሎ ሁለተኛው ባለስልጣን ሲሆን፣ መሐመድ የፈጸመውን፣ የፈቀደውን እና ያዘዛቸውን ኩነቶች ይዟል፡፡ ሀዲስ የመልካም ምግባራት ዝርዝር ብሎም የህግ መሰረቶች ጥቅል ሲሆን ፣ በእስላማዊ ህግ ዘንድ ያለው ተጽዕኖ የላቀ ነው፡፡ ሱኒዎች “ አንድም የቁርኣን ክፍል ከሀዲስ ጋር ከተጋጨ እንደሚሻር ”ይናገራሉ፡፡ በሙስሊማኑ እሳቤ ሀዲስ ተቀባይነት ሊኖረው የሚችለው ፡- (1) የእስላማዊ ባህል ክፍሎችን ሲደግፍ (2) በከፍተኛ አካላት በሚኖረው ቁቡልነት ወይም ተዐማኒነት ሠንሰለት ሲያልፍ ነው፡፡

ተዐማኒ ሠንሰለቱ ብዙ ጊዜ ረዥም ነው፡፡ ብዙኃኑ ባህሎች እስልምና በሚያድግበት እና በሚከፋፈልበት ወቅት የሚፈጠሩትን እምነቶች ወይም ልማዶች ለመደገፍ ታቅዶ የሚፈሩ ናቸው፡፡ በሥስተኛው ክፍለ ዘመን የባህል ተጽዕኖው በመስፋፋቱ ሱኒዎች ስንዴውን ከገለባው ማበጠር እንደሚገባ ወሰኑ፡፡ አል ቡኻሪ 600,000 ሀዲሶችን ለአስራ ስድስት ዓመት ያህል ሰምቷል፤ ሆኖም 7, 275 ያህሉን ብቻ ነው እውነተኛ አድርጎ የተቀበለው፡፡ አቡ ዳውድ ከ 500,000ዎቹ 4,800 ተቀብሏል፡፡ በሺዎች ከሚቆጠሩት የሐዲ ጥቅሎች ሱኒዎች የተቀበሉት መሐመድ ከሞተ በኃላ በሦስተኛው ክፍለ ዘመን የተዳራጁትን ስድስት መጽሐፎች ብቻ ነው ፡፡ እነርሱም ፡- ቡኻሪ (870 ዓ.ም)፣ ሙስሊም ( 892)፣ አቡ ዳወድ (888) ፣ አል-ቲርሚድ (892)፣ አል-ናሲ ( 915 ዓ.ም ) ኢቡን ማጃ ( 886 ዓ.ም)፡፡

የሺአ ክፍሎች  አምስት የተለያዩ መጽሐፍትን ፣ የሀዲስን ነብያት ብቻ ሳይሆን አስራ ሁለቱ ኢማሞች የተናገሩትን እና ያደረጉትን ጭምር ይቀበላሉ። ሺኣዎች የራሳቸው የሆነ ሀዲስ ጥቅል ያላቸው ሲሆን ፣ የሱኒዎችን ሀዲስ የሚመለከቱት በጥርጥር አይን ነው። የሺአዎች እጅግ ታዋቂው የሀዲስ ጥቅል  የአል- ካሊኑ  "አል-ካፊ ፊ ዑዝል  አል- ዲን" ነው ፤ በርካታ ጥቅሶች ከቁርኣን ጋር በማገናኘት የተቀዱትም ከዚሁ ነው።

## 2. ኪያስ

በሥነ-አመክንዮ ምስለት ሙግትን ለማስረገጥ ያግዛል። ለምሰሌ ፦ ከ X አንጻር A የBን ቢመስል፣ የ Bን ምስለት ከ Y አንጸር ማስቀመጥ ይቻላል።

ሙስሊማኑ የቁርኣንን ትምህርቶች አስመልክቶ ቁርኣን የማይደርሳቸውን ትምህርቶች ለማመልከት ይህን መርሕ ይጠቀማሉ። ለምሳሌ ፦ አንድ ሙስሊም " ሱስ የሚያስይዙ መድኃኒቶች ህጋዊ ቅቡልነት አላቸው ወይስ ፊጽሞ ተከልክለዋል? ብሎ ሊጠይቅ ይችላል። በሱረቱ 5፥90 መልሱን ማየት ይቻላል " እላንተ ያመናችሁ ሆይ! የሚያሰክር መጠጥ፣ ቁማርም፣ ጣዖታትም አዝላምም ከሰይጣን ሥራ የሆኑ እርኩስ ብቻ ናቸው፤ (እርኩስን) ራቁትም ልትድኑ ይከጀላልና።" ስለሆነም ከላይ በተገለጸው ምልሰት መርህ መሰረት ሱስ የሚያሲይዙ መድኃኒቶች የሚያሰክሩ በመሆናቸው የተከለከሉ መሆናቸውን ማስረገጥ ይቻላል።

## 3. ኢጂማ

በሌሎች መንገዶች ያልተቀመጡ ነጥቦችን አስመልክቶ ሙስሊማኑ የነብዩን ባልንጀራዎች ስምምነትን ይመሰክራሉ፤ ስምምነቶቹ  በሁለተኛው እና በሦስተኛው ክፍለ ዘመን በህግ አዋቂዎች እና ኡልማዎች  የተዘጋጁ ናቸው።

## 4. የሙስሊም ህግ ትርጓሜ

የእስላማዊ ህግ ትርጓሜ  በኢጅሀሃድ (ገዢ ህግን  ለማረጋገጥ  የሰው  አመክንዮአዊ  ሥራ) መርህ የሚንቀሳቀሱ አራት ትምህርት ቤቶች አሉት።

የአራቱ ትምህርት ቤቶች ጥቅል ስራዎች ከ750-850 ዓ.ም ጊዜ የወሰደ ሲሆን፣ እነርሱም ፦ ማሊክ በሰሜን እና በምዕራብ ትምህርት ቤቱ የተስፋፋ፣ አቡ ሀኒፋ በቱርክ እና ዱቡባዊ ኢስያ

ተጽዕኖ ያመጣ፣ ሻፊ በኢንዶኔዢያ ብሎም በምስራቅ አፍሪካ የገነነ፣ ኢብን ሀኒባል በአረቢያ ምድር ተጽዕኖ የነበረው ናቸው።

ላለፉት አምስት ክፍለ ዘመናት እነዚህ ትምህርት ቤቶች በዕኩል ደረጃ ቢታዩም፣ በመካከላቸው ጥቂት ልዩነት አለ ። አራቱም አይሁዳውያኑን ሆነ ክርስቲያኖኑን በእስላማዊ ምድር የአምልኮ ቦታዎች ሊኖራቸው እንደሚችሉ ይስማማሉ፤ አቡ ሀኒፋ የአምልኮ ስፍራዎቻቸው ከሙስሊማኑ ከተማ ራቅ ሊል እንደሚገባው ያመለክታል። በተጨማሪም ዓርብ ያልሆኑ ቁርአንን በራሳቸው ቋንቋ መጠቀም መረዳት እንዳለባቸው፣ ድንገተኛም በሆኑ ምክንያቶች ጾምን ሊያቋርጡ እንደሚችሉ ይገልጻል።

## II. የሙስሊማኑ እምነቶች

በሱኒ ትምርት ቤት የተቀረጸው ትልቁ የእስልምና እምነት መግለጫ ስድስት ገሃዳዊ እና ባለ ስልጣን አስተምህሮቶችን ይዟል። አንድ ሙስሊም በቁርኣን (በሁለተኛው ሱረቱ ክፍል) እንደተገለጸው እነዚህኑን አስተምህሮች ማመን ይጠበቅበታል።

### 1. አላህ

በመሐመድ ጊዜ በዓርብ ባህረ-ገብ መሬት ከሁሉ በላይ የሆነው አምላክ ስም አላህ ሲሆን ፤ ከእዕብራይስጡ ኤሎሂም ከሚለው ቃል የተወሰደ ነው። ይህ ቃል ከእስልምና በፊት የነበረ ፣ መአባት ስም ሳይቀር ጥቅም ላይ ነበር (የመሐመድ አባት አብደላህ ተብሎ ይጠራ ነበር፤ ትርጓሜውም "የአላህ ባሪያ " ማለት ነው ። ካአእባ ቤት አላህ ( የአላህ ቤት) ተብሎ ይጠራ ነበር፤ ይህ ስያሜ በጥንት ዓረብ ሥነ-ግጥም ውስጥ ከመሐመድ ብዙ ዓመት በፊት ተገልጿል። በአይሁድ ፣ በክርስቲያኑ እና በሌሎች ዓርቦች አንድ አምላክን ብቻ ማምለክ በዓረብ ባህረ -ገብ መሬት ከመሐመድ በፊት ነበር።

ስለሆነም መሐመድ በዓረብ ባህረ -ገብ መሬት በአንድ አምላክ ማመንም ሆነ አዲስ አምላክን ለዓረቡ ምድር ያስተዋወቀ የመጀመሪያው ሰው አይደለም። ከዚህ ይልቅ መሐመድ የነበረው የራሱን ሰዎች ጠርቶ ያደረገው አይሁዳውያኑ እና ክርስቲያኑ ያመልኩት የነበረውን አምላክ እንዲያመልኩ ነበር። ቁርኣን ለአይሁዳውየኑ እና ለክርስቲያኖኑ የሚያውጀው ይህንኑን ነው ፦ "አምላካችንም አምላካችሁም አንድ ነው" (ሱረቱ 29፥46)።

መሐመድ ሀሰተኛ አማልዕክትን ፣ ጣዖታትን እና ምስሎችን በሙሉ ተቃውሟል። አላህም አንድ መሆኑን በማስተማር ዓረቦችን ከጣዖት አምልኮ ነጻ አውጥቷል፦

*ሱረቱ 112፥ 1-4*

*"እርሱ አላህ አንድ ነው። አላህ (የሁሉ) መጠጊያ ነው። አልወለደም፤ አልተወለደምም። ለርሱም አንድም ብጤ የለውም።"*

ቁርዓን በየትኛውም ቦታ አላህን ፍልስፍናዊ በሆነ መልኩ መግለጽ አይሞክርም፤ ይልቁንም በስም እና በሌሎች ገላጭ ሐረጎች ባህሪውንም ሥራዎችንም መሰረት ባደረገ መልኩ የሚያሳይበት ሁናቴ እጅግ ገራሚ ነው። በሙስሊማኑች መካካል የጋራ የሆኑ "99 ውብ የአላህ ስሞች" [33]አሉ።

የአላህ ስሞች አጠቃቀም በቁርኣን ወይም አመኔታ ባላቸው ባህሎች ቅቡልነት ውጪ መሆን የለበትም። ለምሳሌ ፦ አላህ አል -ሻፊ (ፈዋሽ) ተብሎ ይጠራል፤ ነገር ግን አል -ታቢብ (ሐኪም) የሚለው መጠሪያ ቁርኣንም ሆነ መሐመድ ሲጠቀመውአይሰተዋልም።

## ሀ. 99ኙ የአላህ ስሞች

(1) መሐሪ (al-Rahman)፣ (2) ሩኅሩኅ (al-Rahim)፣ (3) ንጉስ (al-Malik)፣ (4) ቅዱስ (al-Quddus) ፣ (5) ሰላም (al-Salam)፣ (6) ታማኝ (al-Mu'min)፣ (7) ጠባቂ (al-Muhaimin) ፣ (8) ታላቅ (al -Aziz) ፣ (9) ከሁሉ በላይ (al-Jabbar) (10) ከፍ ያለ (al-Mutakabbir) ፣ (11) ፈጣሪ (al-Khaliq) ፣ (12) ሠሪ (al-Bari) ፣ (13) አበጂ (al-Musawwir)፣ (14) ይቅርባይ (al-Ghaffar)፣ (15) ገዢ (al-Qahhar)፣ (16) ሸላሚ (al-Wahhab) ፣ (17) አቅራቢ (al-Razzaq) ፣ (18) ከፋች (al-Fattah)፣ (19) አዋቂ (al-Alim) ፣ (20) ከልካይ (al-Qabid) ፣ (21) ለጋስ (al-Basit) ፣ (22) ዝቅ አድራጊ ( al-Khafid) ፣ (23) ከፍ አድራጊ (al-rafi) (24) ሿሚ ( al-Mu izz)፣ (25) ትሑት (al-Muzill) ፣ (26) ሰሚ ( al-Sami) (27) ሁሉን የሚያይ (al-Basir ) ፣ (28) ገዢ (al-Hakim) ፣(29) ጻድቅ(al-Adl) (30) ረቂቅ (al-Latif) ፣ (31) አዋቂ (al-Khabir)፣ (32) ቻይ (al-Halim)፣ (33) ክቡር (al-al-Azim) ፣ (34) ይቅር ባይ (al-Ghafur) ፣ (35) ጽኑ (al-Shakur) (36) ገናና (al-Ali) ፣

[33] ኢብኑ ሀኒባል፣ ሙሰንድ፣ 26216፣ 31062።

(37) ታላቅ (al-Kabir)፣ (38) ጠባቂ (al- Hafiz)፣ (39) ሰጪ (al-Muqit) ፣ (40) አሳቢ (al-Hasib)፣(41) ባለግርማ (al-Jalil) ፣ (42) ቸር (al-Karim)፣ (43) ተመልካች (al- Raqib)፣ (44) መላሽ (al-Mujib) ፣ (45) ጠቅላይ (al-Wasi)፣ (46) ጠቢብ (al-Hakeem) ፣ (47) አዛኝ (al-Wadud)፣ (48) እጅግ የተከበረ (al-Majid) ፣ (49) ከፍ አድራጊ (al-Baith)፣ (50) ምስክር (al-Shahid) ፣ (51) እውነት (al-Haqq)፣ (52) ጠበቃ (al-Wakil)፣ (53) ብርቱ (al-Qawi) ፣ (54) ጽኑ (al-Matin)፣ (55) ጠባቂ (al-Wali)፣ (56) ምስጋና የተገባው (al-Hamid)፣ (57) ቆጣሪ (AL-Muhsi) ፣ (58) ጀማሪ (al-Mubdi)፣ (59) አዳሽ (al-Mueid) (60)ፈጣን (al-Muhyi) ፣ (61) ገዳይ (al-Mumit) ፣ (62) ሕያው (al-Hayy)፣ (63) ሕይወት ሰጪ (al-Qaiyum) ፣ (64) ሁሉን አዋቂ (al-Wajid) ፣ (65) እጅግ ክቡር (al-Majid)፣ (66) አቻ የሌለው (al-Wahid)፣ (67) ዘላለማዊ (al-Samad)፣ (68) ኃያል (al-Qadir) ፣ (69) በሁሉ ዘንድ የሚገኝ (al-Muqtadir)፣ (70) የወደፊቱን የሚያውቅ (al-Muqaddim)፣ (71) የሚመራ (al-Muakhir)፣ (72) የሁሉ መጀመሪያ (al-Awwal) ፣ (73) የሁሉ መጨረሻ (al-Akhir) ፣ (74) ግልጽ (al-Zahir)፣ (75) ስውር (al-Batin) ፣ (76) ገዢ (al-Wali)፣ (77) ከፍ ያለ (al-Mutali)፣ (78) ጻድቅ (al-Bar) ፣ (79) የሚጸጸት (al-Tawwab)፣ (80) ተበቃይ (al-Muntaqim)፣ (81) ይቅርታ ሰጪ (al-Afu) ፣ (82) ርኅሩኅ (al-Rauf)፣ (83) ባለመንግስት ገዢ (Malikul Mulk)፣ (84) የጌቶች ጌታ (zul-Jalal wal -Ikram )፣ (85) ምክንያታዊ (al-Muqsit )፣ (86) ሰብሳቢ (al-Jami)፣ (87) ባለጠጋ (al-Ghani)፣ (88) ባለጠጋ የሚያደርግ (al-Mughni)፣ (89) ሰጪ (al-Muti) ፣ (90) ሚስጥረኛ (al-Mani) ፣ (91) አስጨናቂ (al-Darr) ፣ (92) ጠቃሚ (al-Nafi)፣ (93) ብርሃን (al-Noor)፣ (94) መሪ (al-Hadi) ፣ (95) ተወዳዳሪ የሌለው (al-Badi)፣ (96) ጽኑ (Al-B)፣ (97) ወራሽ (al-Warith)፣ (98) አለቃ (al-Rashid)፣ (99) ታጋሽ (al-Sabur)፡፡

ሙስሊማኑ በአምልኮ ስርአታቸው አዘውትረው እነዚህን 99 የአላህ ስሞች ይጠቀማሉ ፤ አንዳንዶቹ ግን 33ቱን ብቻ የሚጠቀሙበት ጊዜ አለ፡፡

### ለ. የአላህ ስሞች ይቃረናሉ

በ99ኞቹ የአላህ ስም መገለጫዎች መካከል በክርስቶስ ኢየሱስ ራሱን ከገለጠው እግዚአብሔር ጋር የሚመሳሰሉ አሉ፡፡ አንድ ሙስሊም ክርስቲያን “አምላካችንም አምላካችሁም አንድ ነው” (ሱረቱ 29፥46) ሲል እግዚአብሔር ማን እንደሆነ አለመገንዘቡን ያሳያል፡፡

አላህ ሥሉስ አሀዱ አምላክ አይደለም፡፡ በእስልምና አተያይ ለፈጣሪ አጋር ወይም እኩያ እንዳለው ማሰብ ይቅር የማይባል ውድቀት ነው (ሱረቱ 4፥48)፡፡ ይህ በክርስትና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በተገናኘ ከተገለጸው አሳብ ጋር ይጋራል ( ማቴዎስ 12፡31)፡፡ የእስልምና እምነት የአላህን አሃድነት ብቻ የሚገልጽ ሆኖ ሳለ ፣ የክርስቶስ እና መንፈስ ቅዱስ መለኮትነትን አይቀበልም፡፡

አል- ጋዛሊ ዘጠና ዘጠኙን የአላህ ስሞች ሁሉን ማለት እንደሆኑ አሰላስሎ ሲያበቃ አንዱ ከሌላው ሊጣረስ እንዲችል ግን መሸሽግ አልወደደም፡፡ በእርግጠኝነት ከሁሉ ገኖ ያለው ስም የአለህ ፍጹም ትልቅነት ነው፡፡ የቤዎዊን ነገዶች በአንድ ወቅት መሐመድን “በአላህ እናምናለን” ባሉት ጊዜ “ ለእርሱ እንገዛለን” ማለት እስካልቻላችሁ ድረስ “ ርሱን አታምኑትም” ሲል መልሷል (ሱረቱ 49 ፥14)፡፡

### ሐ. የአላህ ርህራሄ

ዘጠና ዘጠኙ ስሞች አላህን “አዛኝና ሩህሩህ” ሲሉ ይጠሩታል፡፡ እርሱ ደግ፣ ታገሽ እና ታማኝ ነው፤ ለጋስ ሰጪም ነውና ለሰው ዘር በሙሉ ያዘጋጃል፡፡ ለሚያመልኩቱ ጠባቂያቸው ነው፤ ንስሐ ለሚገቡ ተቀባይ እና ይቅር ባይ ነው ፤ ከእርሱም ጋር መልካም ግንኙነት ላላቸው ባለጸጋ!

አላህ ሁሉን ዐዋቂ ነው፡፡ ዕውቀቱ ማለቂያ የሌለው በመሆኑ ሁሉን ይሰማል፣ ያያልም፡፡ ኃይሉ ታላቅ ስለሆነ ማልማትም ማጥፋትም ሚችል ርሱ ብቻ ነው፡፡ ከሁሉ በላይ የከበረ፣ ልዑል፣ የማይለካ፣ ገናና እና ኃያል ነው፡፡ ከእርሱ ጋር ማንም አይተካከልም ፡፡ እርሱ ህያው ፣ ዘላለማዊ፣ አልፋ እና ኦሜጋ ነው፡፡ ምስጋና የተገባው ፣ ዐዋቂ፣ ቅዱስ ፣ ብርሃን እና ሰላም ነው፡፡ እርሱ የእውነት ሁሉ መሰረት እና መለኪያ ነው፡፡ ዐለምን በቃሉ ከምንም አስገኝቷል ፤ ህይወትንም ሞትንም ፈጥሯል፡፡ ሙቱን ያስነሳል፣ አጽናፍ-ዐለሙን ይጠቀልላልም፡፡

**መ. የአላህ ቁጣ**

አላህ በስልጣኑ ልዑል እና ንጉስ ነው። ከፍ ያደርጋል ያዋርዳል፣ ይጠብቃል ያጠፋል፣ ይመራል ይፈትናል፣ ያድናል ይገድላል ። ፈቃድ ሁሉ የእርሱ ነውና በመጨረሻ የፍርድ ቀን ይፈርዳል (ሱረቱ 16፥35፣76 ፥30፣ 3፡54፣ 8፡30፣10፡21፣13፡42)። ከእርሱ ፍቃድ ውጪ አንዳች ሊኾን አይችልም፤ በራሱ ኗሪ ነውና መካከለኛ ቢኾን አጋዥ አንዳች አያሻውም።

አንድ ሙስሊም አላህ በርህራሄ እንደሚመለከተው እርግጠኛ መሆን አይችልም፤ የአላህ በርካታ ስሞች አስፈሪዎች ናቸው። ልዩና የማይቀርቡት ስለሆነ እርሱን በመፍራት ከማምለክ ውጪ ለሰው ሌላ ዕድል የለውም!

***ሱረቱ 13፥13***

*ነጎድጓዳም አላህን በማመስገን ያጠራል። መላዕክትም እርሱን ለመፍራት (ያጠራታል)። መብረቆችንም ይልካል። እነርሱም (ከሓዲዎች) በአላህ የሚከራከሩ ሲሆኑ፣ በእርሷ የሚሻውን ሰው ይመታል፤ እርሱም ኀይለ ብርቱ ነው።*

***ሱረቱ 14፥4***

*አላህም የሚሻውን ያጠማል። የሚሻውንም ያቀናል።*

***ሱረቱ 17፥ 16***

*ከተማንም ለማጥፋት በፈለግን ጊዜ ባለ ጸጋዎችዋን እናዛለን። በውስጧም ያምጻሉ። በእርሷም ላይ ቃሉ(ቅጣቱ) ይፈጸምባታል እናጠፋታለንም።*

**ሠ. አላህ በሙስሊም ነገረ-መለኮት**

የሙስሊም ነገረ-መለኮት ሰዎች አላህን በሦስት ክፍሎች ይገልጡታል፦ ማንነቱ፣ ባህሪው እና ስራዎቹ።

የአላህን ማንነት ዓረብኛው ቃል ዳዛት ይለዋል ፤ ትርጓሜውም ባለቤት ማለት ነው። የተወሰኑ የነገረ-መለኮት ሙሁራን "የአላህን ፍጥረት እንጂ ማንነቱን አታሰላስሉ" የሚለውን የአል-ገዛሊን ብሂል ያደንቃሉ።

በርካታ የነረ-መለኮት ሊሂቃን ደግሞ በአላህ ባህሪ (ሲፋት) ላይ ያተኩራሉ። ቁርኣን በሦስት ነገሮች ላይ ትኩረት ያደርጋል፦ የአላህ አንድነት (አላሁ አሃድ)፣ የአላህ ልዩ እውነታነት (ሁዋዉል ሀቅ)፣ የአላህ ቀጥተኛ አድራጎት (ሁዋውል ፈይኬል)፣ የሱኒ ሙሁራን ሰባት

መሰረታዊ ባህሪያትን ያስረግጣሉ፦ "ህይወት" ፣ "ዕውቀት" ፣ "ኀይል"፣ "ፍቃድ"፣ "ማየት"፣ "መስማት"፣ "መናገር" ፤ ሺአዎች "ዘላለማዊ" ን ይጨምራሉ፡

ኹሉም የአላህ ባህሪያት ግቡሩን አመልካች ናቸው። በአጽናፍ-ዓለም ያለው ማንኛው መልካምና ክፉ መንስኤ ርሱው ነው። የሚሻውን ሰው ያጠማል ፣የሚሻውንም ሰው ያቀናል (ሱረቱ 16፥93)። የርሱ ፍቃድ ታላቅ ፣ የማይለወጥ ፣ ዓለም ከመፈጠሩ በፊት የነበረ ነው። አላህ ዓለምን ፈጥሯል፤ ይመግበዋልም። በዓለምም ሆነ በሰው ልጆች ፍላጎት አዘጋጁ ራሱ ነው ። የፍጥረት ስራው የሰው ዘር ምግባርን ኹሉ ያካትታል።

ይህ የእምነት እሳቤ ሁለት ክፍተቶች ይስተዋሉበታል፤ አንደኛው፦ የሰው ተግባር የአላህ ከሆነ ሰዎች ስለ ሚያደርጉት ነገር ሁሉ  ተጠያቂ እንደማይኮኑ ያመላክታል። ሁለተኛው፦ በአጽናፍ-ዓለም የሚሆነው ሁሉ የአላህ ቀጥተኛ ተግባርና ኃላፊነት ከሆነ የማሕበረሰብ ዕድገት አበርክቶ ከቶ አይታሰብም።

እስላማዊ እምነት በአማዛኙ ለሚመጣው ህይወት በሆነ ዝግጅት ላይ እንጂ ፣ በዚህም ሆነ በሚመጣው ህይወት ጥራት ላይ አያተኩርም። እስልምና መሰጠት፣ መማረክ ፣ መገዛት ማለት ነው። ሁሉም ነገር አስቀድሞ በመለኮት የተወሰነ ከሆነ  የምክንያትና ውጤት ግንኙነት ማጥናት ስለምን አስፈለገ? ቅድመ-ውሳኔ እሳቤ ጽንፍ በእስልምና የማወቅ ጉጉትን፣ ምርምርን እና ጥናትን አያበረታታም።

## 2. መልአክ

ቁርኣን ጥቂት መልአክትን በስም ይጠራል (ሱረቱ 89፥ 22)። መልአክት ጥዋትና ማታ ፈጣሪን ያመሰግናሉ (ሱረቱ 2፥30፣ 21፥19፣20) ፣ ትዕዛዛቱን ይተገብራሉ (ሱረቱ 21፥27፣ 66፡6)። ከእነርሱ መካከል የሰማይ ሰራዊት የሆኑቱ መንግስተ ሰማይን ከጂኒ እና ዲያብሎስ ይጠብቃሉ (ሱረቱ 37፥8)። ስምንት መልአክት የፈጣሪ ዙፋን ተሸካሚ ናቸው (ሱረቱ 69፥17)። ሃዲት መልአክት ከብርሃን የተፈጠሩ ታዛዦች ናቸው።

በእስልምና የሚታወቁ መልአክት የሚከተሉት ናቸው፦

- ***ጅብሪል***፦ የመገለጥ መልአክ እንደሆነ ሦስት ጊዜ በቁርአን ስሙ ተጠቅሷል (ሱረቱ 2፥97፣98፣ 66፡4)። ጅብሪል " ታማኝ መንፈስ" (ሱረቱ 26፥ 193-195)፣ "ቅዱስ መንፈስ" (ሱረቱ 16፥102)  ተብሎም ተጠርቷል። ከክርስቲያኑ አስተምህሮ

በተቃራኒው ጅብሪል ወደ ማርያም የተላከ የፈጣሪ መንፈስ እና የኢየሱስ ረጂ ተደርጎ ይወሰዳል (ሱረቱ 19፥17፣ 2፥253 ፣ 5፥110)።

- ***ሚካኤል*** ፦ ከጅብሪል እኩል ደረጃ ያለው መልአክ ነው (ሱረቱ 32፥11)
- ***ኢስራፊል*** ፦ በፍርድ ቀን መለከትን የሚነፋ መልአክ ነው (ሱረቱ 32፥11)።
- ***"ጠበኞች መልአክት"*** (አል-ዛቡኒያ) ፦የገሃነም ጠባቂ መላአክት ናቸው (ሱረቱ 96፥ 18)።
- ***"ቀራቢዎች መላእክት"*** (አል -ሙቁሩባሩን) ፦ እነዚህ መላአክት ጠዋትና ማታ ሳያቋርጡ ፈጣሪን የሚያመሰግኑ ናቸው (ሱረቱ 4፥172)። ይህ ስያሜ ኢየሱስ ለአላህ ቀራቢ በመሆኑ እንደተሰጠው ሱረቱ 3፥45 ይግለጻል። እነዚህ መላአክት ባለ ሁለት ወይም ሦስት ወይም አራት ክንፍ ያላቸው መልዕክተኞች ናቸው። የሰው ዘርን የሚጠብቁ ፣ ማንኛውም ሰው የሚጽፈውን እና የሚያደርገውን የሚመለከቱ ናቸው።
- ***ሙንከር እና ናኪር*** ፦ በሀዲስ እንጂ በቁርኣን አልተጠቀሱም ። እነዚህ ሁለት መላእክት ሰው ከሞተ በኃላ በምሽት ወደ መቃብሩ በመሄድ ሰለ እምነቱ የሚጠይቁ ናቸው። አማኝ ከሆነ በመጨረሻው ቀን ወደ ገነት እስኪሄድ ድረስ በማቆያ ስፍራ ያኖሩታል። ቅዱስ ከሆነ ደግሞ የማቆያ ስፍራውን ገነት ያደርጉለታል። ይህ የጥያቄ ሂደት ሱአል ይባላል።
- ***ሸይጣን (ኢብሊስ)*** ፦ ሰይጣን ከኤደን ገነት ፈጣሪን ባለ መታዘዙ ምክንያት የተባረረ መልአክ ነው (ሱረቱ 7፥10-17)።
- ***ሀሩት እና ማሩት*** ፦ በቁርኣን አስተምህሮ መሰረት እነዚህ ሁለቱ መላእክት በዝሙት ምክንያት የወደቁ እና በባቢሎን የተጣሉ ናቸው (ሱረቱ 2፥102)።
- ***ጂን*** (ኢንግሊዘኛው ጂኒ ይለዋል)፦ ከሰው ዘር የሚልቁ፣ ከእሳት የተፈጠሩ፣ የመሐመድን ስብከት የሰሙ ናቸው። አንዳንዶች አምነው ሙስሊም ሲሆኑ፣ ሌሎች ባለማመናቸው ወደ ገሃነም ተጥለዋል። በጂን ማመን በእስልምና ተለምዶአዊ ነው። ምክንያታዊው የእስልምና ክፍል (አል-ሙተዚላህ) እና ጥንታዊያኑ ሙስሊም ፈላስፎች ሳይቀር የጂን ታሪክ ይቀበላሉ። ጂኒን ከሰው ዘር ጋር በጋብቻ እና በንብረት ግንኙነት ያላቸው እንደሆነ ይታመናል ( እነዚህ ጂኒዎች ጎውል ወይም ኦግሬ ተብለው ይጠራሉ)።

## 3. መጻሓፍት

በሙስሊም እምነት እሳቤ በዘመናቱ የፈጣሪ መገለጥ ተኪ መጻሓፍት በነብያት አማካኝነት ለሰዎች ተሰጥተዋል፡፡ አንድ መቶ ገደማ ቅጾች እና አራት መጻሕፍት በአላህ መልዕክተኞች አማካኝነት ለሰዎች እንደተሰጡ ይታመናል፡፡ ከእነዚህም ለአዳም 10፣ ሴት (በቁርዐን ስሙ አልተጠቀሰም) 50፣ እድሪስ (ሔኖክ) 30፣ አብርሃም 10 ተሰጥተዋል፤ ሁሉም ግን አሁን የሉም፡፡

አሁን ያሉት ሌሎች መገለጦች (አልቢት) የሚከተሉት ናቸው፡-

- ***ቶራህ (ህግ)*** ፡- ለሙሴ የተሰጠ ሕግ ነው፡፡ አብዛኛውን ሙስሊማኑ ብሉይ ኪዳንም ሆነ የአይሁድ መጽሓፍት ቅዱስ መጽሓፍት አድርገው ነው የሚወስዱት፡፡ ሆኖም አይሁዳዊያኑ ቶራህን እንደቀየሩት ነው የሚገነዘቡት!
- ***ዘቡር*** ፡- ለዳዊት የተሰጠ መዝሙር፡፡
- ***ኢንጅል***፡- ለኢየሱስ የተሰጠ ወንጌል ነው፡፡ ሙስሊማኑ መላውን የአዲስ ኪዳን መልዕክት በኢየሱስ ላይ የወረደ ወንጌል (ቅዱስ መጽሐፍ) ብለው ነው የሚጠሩት፡፡ ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲያርግ ወንጌሉን ይዞት እንደሄደ፤ አሁን በክርስቲያኖች እጅ የሚገኘው እንደለወጡት አድረገው ነው የሚወስዱት፡፡
- **ቁርኣን** ፡- ለመሐመድ የተሰጠ መጨረሻው መገለጥ ነው፡፡ ከዘላለም በአላህ ሙዚየም ተጽፎ እንደነበር፤ አላህ በጅብርል አማካኝነት ከሰማይ በኃያሊቱ ምሽት በረመዳን የመጨረሻ አስር ቀናት እንዳወረደው ይታመናል፡፡ ለሃያ ሶስት ዓመታት ጅብሪል ለመሐመድ ቁጥር በቁጥር አውርዶለታል፤ በሙስሊማኑ እሳቤ መሐመድ በተቀበለው መገለጥ ይዘት ላይ አንዳች ከራሱ የሆነ አስተዋጽኦ አላደረገም፤ ይልቁንም ጅብሪል ያወረደለትን ይናገር እና ያስጠነቅቅ ነበር፡፡

ሙስሊማኑ ቁርኣን ቀድሞ የነበሩትን መገለጦች ሁሉ እንደላቀም እንደሻረም ይገነዘባሉ፡፡ ሆኖም ሀዲስም ሆነ ቁርኣን በአንዳንድ ክፍሎች ላይ ያለውን አመኔታ በሚከተሉት ነጥቦች ጥያቄ ውስጥ እንዲገባ አድርገውታል ፤ ስድስት እክሎችን እንመልከት፡፡

## *ሀ. የምንባቡን እውነተኝነት የሚያጠራጥሩ ስድስት ጥቅሶች( ቁጥሮች)፡-*

- ***መሐመድ አንዳንድ መገለጦችን ዘንግቷል***፡- ቁርኣን እንዲህ ይላል "(ቁርኣንን) በእርግጥ እናስነብብሃለን፤ አትረሳምም፡፡ አላህ ካሻው ነገር በስተቀር ፡፡ እርሱ ግልጹን የሚሸሸገውንም ሁሉ ያውቃልና" (ሱረቱ 87፥6፣7)፡፡ አል-ዛማኽሻሪ

"መሐመድ ቁርኣንን በጸሎት ሲያናብ ቁጥር (ጥቅስ) ጥሏል፤ ኡባይ ጥቅሱ ተሸሯል ፡፡ 'ዘንግቻለሁ ያለው ማነው' ሲል መሐመድን ይጠይቃል፡፡"

ይህን መዘንጋት አላህ ይሆንን የፈቀደው? ሱረቱ 16፥101 እንደሚናገረው የተዘነጋው ጥቅስ በሌላ መገለጥ ተተክቶ ይሆንን? ወይስ ፈጽሞ ተወግዷል? (ሱረቱ13፥39)፡፡ በተጠበቀው መዝገብ (ጽላት) ላይ የነበረው ምንድ ነው? የተደመሰሰው ወይም የጸናው የቱ ነበር?

- ***መሐመድ በአንዳንድ መገለጦች ላይ ተጣድፏል*** ፡- ቁርኣን " እውነተኛው ንጉስ አላህም (ከሓዲዎች ከሚሉት) ላቀ፡፡ ወደ አንተ መውረዱም ከመፈጸሙ በፊት በማንበብ አትቸኩል፡፡ ጌታዩ ሆይ ! ዕውቀትንም ጨምርልኝ በል" ይላል (ሱረቱ 20፥ 114)፡፡ አክሎም፡- "በእርሱ (በቁርኣን ንባብ ልትቸኩል ምላስህን በእርሱ አታላውስ፡፡ (በልብህ ውስጥ) መሰብሰቡንና ማንበቡ በእኛ ላይ ነውና ፡፡ ባነበብነውም ጊዜ (ካለቀ በኃላ) ንባቡን ተከተል፡፡ ከዚያም ማብራራቱን በእኛ ላይ ነው" (ሱረቱ 75፥16-19)፡፡

አል-ባይዳዊ " መገለጡ ሙሉ እስኪሆን ድረስ ምላስህን በእርሱ አታለውስ" ሲል ይተረጉመዋል፡፡ የመሐመድን ችኩልነት የሚገስጽ ክፍል ነው፤ ታዲያ ይህ ችኩልነት የአላህ ፍቃድ ነውን? አል-ሱዩቲ በአስባብ አል ኑዙል (ምክንያቶች -የዘር) ሱረቱ 20፡14 "መሐመድ የራሱን ወይስ አላህ ያዘዘውን ነው የመዘገበው?" ሲል ይጠይቃል፡፡ ራሱም ሲመልስ " በእርግጥ መሐመድ የራሱን መዝግቧል፤ ኃላ ግን አላህ ገልጦለታል" ሲል ይመልሳል፡፡

- ***የመሐመድ ፍርድ የሚወዛወዝ ነበር*** ፡- በቁርኣን አላህ መሐመድን እንዲህ ሲል ይመክረዋል " እነሆ ከዚያም ወደ አንተ ካወረድነው ሌላን በዕኛ ላጥ ትዋሽ ዘንድ ሊፈትኑህ በእርግጥ ተቃረቡ፡፡ ያን ጊዜም ወዳጅ አድርገው በያዙህ ነበር፡፡ ባለረጋንም ኖቶ ወደነሱ ጥቂትን (ዝንባሌ) ልትዘነበል በእርግጥ በተቃረብክ ነበር፡፡ ያን ጊዜ የሕይወትን ድርብ (ቅጣት) የሞትንም ድርብ (ቅጣት) ባቀመስንህ ነበር፡፡ ከዚያም ላንተ በኛ ላይ ረዳትን አታገኝም ነበር" (ሱረቱ 17፥73-75)፡፡ አል-ሱዩቲ በኢነዚህ ሦስት ቁጥሮች ላይ የሚከለተውን ያስቀምጣል " የቁረይሽ ሰዎች በአንድ ወቅት ለመሐመድ እስልምናን በተመለከተ የሚከተለውን ድርድር አቅርበውለት ነበር 'ከአማልክቶቻችን ራስን አብር እኛም ወደ አንተ ኃይማኖት እንመጣለን' መሐመድ እንዲለወጡ ጉጉት ስለ ነበረው ድርድራቸውን ተቀብሏል::"

- ***መሐመድ አንዳንድ መገለጦችን ትቷቸዋል*** ፡- አላህ መሐመድን ሲመክር " በእርሱ ላይ የገንዘብ ድልብ ለምን አልተወረደም ወይም ከርሱ ጋር መልአክ ለምን አልመጣም ማለታቸውንም በመፍራት ወደ አንተ ከሚወርደው ከፊሉን ልትተው በእርሱም ልብህ ጠባብ ሊኾን ይፈራልሃል። አንተ አስፈሪ ብቻ ነህ። አላህም በነገሩሁሉ ተጠባባቂ ነው"(ሱረቱ11፥12)።
- ***መሐመድ ቁርኣንን ቀይሮት ይኾናል***፡- ቁርኣን ሲናገር "በአንቀጽም ስፍራ አንቀጽን በለወጥን ጊዜ አላህም የሚያወርደውን ነገር አዋቂ ነው። 'አንተ ቀጣፊ እንጂ ሌላ አይደለህም' ይላሉ። በእውነቱ  አብዛኞቻቸው አያውቅም" ይላል (ሱረቱ 16፥101)። አል-ዋሃዲ " ጣዖት አምላኪዎቹ በመሐመድ ላይ ያፌዙ ነበር።  ተከታዮቹ አንድ ነገር እንዲፈጽሙ ያዛል፣ በሌላ ጊዜ ደግሞ ያዘዘውን እንዳያዳርጉ ይከለክላል ፤ ነገሮችን ከራሱ በመፍጠር ነው የሚናገረው" ሲሉ ይሞግታሉ።

እዚህ ላይ በቁርኣንና  በ አል-ማህፉዝ (የተጠበቀው መዝገብ፡- ከመጀመሪያ ጀምሮ በሰማይ የዋናው ቁርኣን መዝገብ) መካከል ያለው ቁርኝት ጥያቄ የሚያስነሳ ነው። የተተካና  አዲሱ ምንባብ  ሁለቱም በተጠበቀው መዝገብ  ላይ ነበሩን? ስረዛ እና ልወጣ ከፈጣሪ  የማይለወጥ ጥበብ እንዲሁም ከእውነተኛ ነብያቱ አንጻር እንዴት ይታረቃል?

- ***መሐመድ ለሰይጣን ጣልቃ ገብነት ተጋላጭ ነበር*** ፡- ሱረቱ 16፥98 " ቁርኣንንም ባነበብህ ጊዜ እርጉም ከኾነው ሰይጣን በአላህ ተጠበቅ" ይላል። ይህ የአላህ ቃል ሰይጣንን እንደሚያሸሽው አመልካች ነው፤ ነገር ግን ቁርኣን ቦታ የሚሰጥበት ጊዜ አለ ። ሱረቱ 53፥19-20 " አል-ላትንና አል-ዑዛን አያችሁን? ሦስተኛይቱንም አነስተኛዋን መናትን (አያችሁን? የምትግገዟቸው ኃይል አላቸውን?)::" ሰይጣን "እነዚህ አማልእክት በእውነት ምልጃቸው ያስፈልጋል!" የሚለውን በአንደበቱ ጨምሯል።

አማልእክት ተከታዮች ለአላህ ቢንበረከኩም፣ መሐመድ በግልጽ ቅነሳን አድርጎአል። በዚህም ምክንያት የሚከተለው መገለጥ ወርዶለታል፡-

*ሱረቱ 22፥52*

*ከመልክተኛ እና ከነብይም ከአንተ በፊት አንድንም አላክንም ባነበበ (እና ዝም ባለ) ጊዜ ሰይጣን በንባቡ ላይ ( ማጥመሚያን ቃል) የሚጥል ቢሆን እንጂ። ወዲያውም አላህ ሰይጣን*

*የሚጥለውን ያስወግዳል። ከዚያም አላህ አንቀጾችን ያጠነክራል ። አላህም ዐዋቂ ጥበበኛ ነው።*

ሰይጣን በንባቡ (መገለጡ) ሂደት ላይ ማጥመሚያን ቃል ማኖሩ፣ አላህም ሐሰተኛውን ቃል ሽሮ መተካቱ መሐመድ የተቀበለው መገለጥ ያለውን ስልጠና ጥያቄ ውስጥ እንዲገባ ያደርገዋል። ሱረቱ 52፥ 22 ሰይጣን በቁርኣን መገለጥ ሂደት ውስጥ ጣልቃ መግባቱን አስመልክቶ አል-ዋሃዲ የሚከተለውን ያስቀምጣል "መሐመድ ጅብሪል ወደ እርሱ በምሽት ሲመጣ በቤቱ ተቀምጦ ነበር፤ መሐመድ ሱረቱ 53 ን ባመላከተው ጊዜ፣ ጅብሪል 'እነዚህን ቁጥሮች (ጥቅሶች) ወደ አንተ አውርጃለሁን?' ሲል ይጠይቃል፤ መሐመድም መለሰ፡- ' ቃልን በአላህ አፍ ዘንድ አኑሬአለሁ" ሙስሊሞች ቁርኣንን ከማንበባቸው በፊት ፈጣሪ ከሰይጣን እንዲታደጋቸው የሚጸልዩት በዚህ ምክንያት ነው።

ሱረቱ 81፥19፣20 "እርሱ (ቁርኣን) ይክቡር መልዕክተኛ ቃል ነው። የኀይል ባለቤት ዘንድ ባለሟል የኾነ።" አል- ራዚ  አል-ካህዚህን ጠቅሶ ሲናገር " አጋንንት (አል-ባይድ -ነጩ) በጅብሪል ተመስሎ ወደ መሐመድ በመምጣት ደካማ አሳብን አኑሮበታል፤ ነገር ግን ጅብሪል መጥቶ ወደ ህንድ ምድረ በዳ አባሮታል"ይላል።

በሱረቱ 22፥53 "ሰይጣን የሚጥለውን ነገር ለእነዚያ በልቦቻቸው ውስጥ በሽታ ላለባቸው ልቦቻቸውም ደረቆች ለሆኑት ፈተና ሊያደርግ (ይጥላል)" ይላል። አል-ባዳዊ ይህን ክፍል " ነብያት የዕውቀት ውስንነት እና የዲያብሎስ ውንጀላ ሊያጋጥማቸው  ይችላል"  ሲል ይተነትናል።

## ለ. በቁርኣን ምንባብ ክፍሎች እውነታ ላይ ጥርጥር የሚያነሱ ሰባት የሀዲስ አስተያየቶች፡-

- እንደ አናስ ኢብን ማሊክ  አገላላጽ አንድ ሙስሊም  ክርስቲያን " መሐመድ እኔ ያልኩትን ብቻ ነው የሚፈልገው" ሲል ቁርኣንን ለመሐመድ እንደጻፈ  በሳሂ ይገልጣል።
- ሱረቱ 6፥93 " በአላህም ላይ እብለትን ከቀጣጠፈ ወይም ወደርሱ ምንም ያለተወረደለት ሲኾን 'ወደኔ ተወረደልኝ' ካለ ሰው ይበልጥ በዳይ ማን ነው" በአሳባብ አል-ኑዙዑል አል -ስዩቲ የዚህን ክፍል ዋና ቅጂ እንዲህ ሲል ያብራራል። አብደላህ ኢብኑ ሳድ ኢብኑን (የሳራ አባት) ለመሐመድ መገለጡን (ምንባቡን) ይጽፍ ነበር፡፤ መሐመድ "አዚዙን

ሀኪም” (ኃያል እና ጥበበኛ) ብሎ ሲናገር ፣ አብደላህ “ሀፉሩን ራሂም” (ይቅር ባይ እና መሀሪ) ሲል ጽፏል፡፡ መሐመድ በምላሹ ይህ ቃል “አንድ እና ተመሳሳይ” ነው ሲል አሳወቀ፡፡ ያን ጊዜ አብደላህ እስልምናን በመተው አረማዊውን የቁራይሽ ነገደ ተቀላቀለ፡፡ አብደላህ “ መሐመድን በፈለኩት መንገድ አጭበርብሬዋለሁ፣ እርሱ ‘አዚዙን ሀኪም’ ብሎ ተናገረ፤ እኔ ደግሞ ‘አሊሙን ሀኪም’ !” መሐመድ “ አዎን ! ሁለቱም ትክክል ናቸው፤ የወደድከውን ጻፍ ” አለ፡፡ አብደላህ “ለመሐመድ ተገልጦለት እንደሆነ እኔም ተገልጦልኛል፤ አለህ በቁራአን የሚናገር ከሆነ የተናገርኩት (የተቀበልኩት መገለጥ) አላህ የገለጠውን ነው” ሲል ይሞግታል፡፡

- አል-ስዩቲ አል-ኢትካን በሚለው መጽሐፉ አብደላህ ኢብን መስዑድ አንዱ የቁርአን ጸሐፊ እንደሆነ ይገልጻል፡፡[34] መሐመድ በአንድ ወቅት ጥቅስን (ቁጥርን) አስነብቦታል፤ ሆኖም በነጋታው ኢብን መስዑድ ጥቅሱን (ምንባቡን) ቢያስሰው ሊያገኘው አልቻለም፡፡ ጥቅሉ ባዶ ሳለ መሐመድን በጠየቀው ጊዜ “ በዚያው ምሽት ተሽሮአል” ሲል መልሶለታል፡፡
- የቡኻሪ ሀዲስ ፣ ሙስሊም ፣ አል-ዳሪሚ እና ኢብኑ ሀኒባል መጽሐፍት የዑመር ኢብኑ ከጣብ [35] ቃላትን ዘግበዋል፡፡ “ ከጌታ ጋር በሦስት ነገሮች ተስማማቻለሁ ...የአላህ መልዕክተኛ ሆይ ከኢብራሂም መቆመያ መስገጃን ባደረግህ ጊዜ፡፡” ሱረቱ 2፥125 ይንኑን ያስነብባል “ ቤትንም ለሰዎች መመለሻና ጸጥተኛ ባደረግን ጊዜ (አስታውስ)፡፡ ከኢብራሂምም መቆሚያ መስገጃን አድርጉ፡፡” “ ታዛዦችን እና ተጸጻቾች ፣ የአላህ መልእክተኛ ሆይ! ዓይነ ርግባቸውን እንዲሸፍኑ እዛዛቸው ፡፡” ሱረቱ 66፥12 የሚከተለውን ያስነብባል “ (መላችሁንም) ቢፈታችሁ ከእናንተ የበለጡ ሚስቶችን ሙስሊሞች አማኞች ፣ ታዛዦች፣ ተጸጻቾች ፣ (ለአላህ) ተገዢዎች ፣ ጾመኛዎችም ፈቶች፣ ደናግልም የኾኑትን ጌታው ሊለውጠው ይከጅላል፡፡”
- አል-ስዩቲ ፣ አል- ኒሳቡሪ እና አቡ ዳውድ አቡ ሁራይራን በሱረቱ 2:284 ላይ ያሰቀመተውን ትንታኔ ዘግበዋል፡- “አላህ በአእምሮ የተገለጠውንና የተሰወረውን ሁሉ ይገጥማል፤” ይህ በመጀመሪያዎቹ አማኞች ዘንድ ካበድ ነበርና [36] በጉልበታቸው

---

[34] ኢብኑ ሀኒባል፣ ሙሰንድ፣ 26216፣ 31062፡፡

[35] ቡኻሪ ሳላት 32፣ ሙስሊም፣ ፈዳኢል አል-ሻዓባ 24፣ አል-ዳሪም ፣ ማናኒክ 33፣ ኢብኑ ሃኒባል ሙሰንድ 1.23፣24፣26፡፡

[36] አል- ስዩቲ ፣ ኣሻብ አል ኑዑዙል፣ ሱረቱ 2:284 እና ቡ ዳወድ ፣ ዘካት 32፡፡

ተንበርክከው " አላህ ይህን ክፍል ለአንተ ግልጦልሃል ፣ እኛ ግን መቀበልና (መታገስ) አንችልም" ሲሉ መሐመድን ጠይቀዋል። ወዲያውኑ ምንባቡ ተሸሮ ሱረቱ 2፥286 ተሰጠ "አላህ ነፍስን ከችሎታዋ በላይ አያስገድዳትም ለርስዋ የሰራችው አላት።"

- ሱረቱ 33፥50 " አንተ ነብይ ሆይ! እኛ እነዚያን መህሮቻቸውን የሰጣሃቸውን ሚስቶችህን .... ለአንተ ፈቅደናል" ይላል። አል-ስዩቲ ኡም ሹራክ አል-ደውሲያ ለመሐመድ ራስዋን እንደሰጠች፤ ቆንጆም ስለ ሆነችም እንደተቀበላት ይናገራል፡ አይሻ "ሴት ራስዋን ለወንድ መስጠቷ ትልቅ ነገር አይደለም" ትላለች። ስለ መሐመድም " አላህ ለአንተ ስሜት ፈጣን ምላሽ አለው" ስትል ትገልጻለች።
- አል-ስዩቲ የአብዱራህማን ኢብኑን አውፍ ቃል እንዲህ ይዘግባል " ቅዱስ ጦርነት ስለ መዋጋት' የተሰጠውን መገለጥ አናገኝም፤" ከሌሎች ጥቅሶች ጋር ከቁርኣን የተተወ ነው። ኢብኑን ዑማር "ማናችንም በቁርኣን የተገለጠው እንጂ ሁሉም ቁርኣን አለኝ ማለት አንችልም" ይላል።

## 4.ነብያት

ሁሉም መልዕክተኞች ነብያት ነበሩ፤ ሁሉም ነብያት ግን መልዕክተኞች አልነበሩም። ሀዲስ የነብያት ቁጥር 124,000 ሺህ ወይም 224,000 ሺህ ወይም የማይታወቅ እንደሆነ ይገልጻል። ነብያት ለሰዎች የተፈቀደውን ዕውቀት የሚለግሱ ናቸው፡፤ በእስልምና ትክክል የሆነውና ትክክል ያልሆነው የሚወሰነው በአላህ ፍቃድ ነው። በነብያቱ የማይደረሱ ፍጥረታት በራሳቸው ገነት ተጠብቀው (ድነው) አሉ። ነገር ግን አላህ ለአዳምና ዘሩ ኪዳንን ገብቷል (ሱረቱ 2፥27፣3:81 )።

ቁርኣን 28 ነብያቶችን በስም ይጠቅሳል ፤ ከእነዚህም መካካል ሦስቱ ዐረቦች (መሐመድ፣ ሳሊ እና ሹዓይብ) ናቸው። የነብያቱ ዝርዝር በሚከተሉት ክፍሎች ተገልጿል፡-

***ሱረቱ 3፥33***

*አላህ አደምን፣ ኑሕንም የኢብራሂምንም በቤተሰብ፣የዒምራንንም ቤተሰብ በዓለማት ላይ መረጠ።*

***ሱረቱ 4፥163***

*እኛ ወደ ኑሕና ከርሱ በኃላ ወደ ነበሩት ነብያት እንዳወረድን ወደ አንተም አወረድን ። ወደ ኢብራሂምም፣ ወደ ኢስማኢልም፣ ወደ ኢሰሓቅም ፣ ወደ ያዕቆብም ፣ ወደ ነገዶችም ፣ ወደ ኢሳም፣ ወደ አዩብም ፣ ወደ ዩኑሰም፣ ወደ ሃሩንና ፣ ወደ ሱለይማንም አወረድን። ለዳውድም ዘቡርን ሰጠነው።*

***ሱረቱ 6፡84-87***

*ለርሱም ኢሰሐቅን (ልጅ ልጁን) ያዕቁብንም ሰጠነው። ሁሉንም መራን። ኑሕንም በፊት መራን፡፤ ከዘሮቹም ዳውድን ፣ ሱለይማንንም፣ እብንም፣ ዩሱፍንም ፣ሙሳንም፣ ሀሩንንም (መራን) ....ዘከሪያንም ፣የሕያንም ፣ ኢሳንም ፣ኤልያስንም (መራን)......ኢስማኢልንም፣ አልየሰዕንም ፣ዩኑሰንም፣ሉጥንም (መራን ። ሁሉንም በዓለማት ላይ አበለጥናቸውም።*

እነዚህ ሦስት ዝርዝሮች ብሉይ ኪዳን እና አዲስ ኪዳን ነብያት ስሞችን የያዙ ናቸው። የብሉይ ኪዳን በርካታ ታላላቅ ነብያት ስም አልተጠቀሰም። በቁርኣን አስተምህሮ ነብያት በአይሁዳውያኑ እና ክርስቲያኑ መካከል ነው የሚገለጡት ፤ መሐመድ መዲና እስከ መጣበት ድረስ ራሱን ነብይ ብሎ አልሰየመም።

በአስልምና አስተምህሮ መሰረት ክብር ያላቸውን ስድስት ነብያቶች ናቸው፡-

- አዳም፡- የአላህ ምርጫ ( ሳፊ አላህ)።
- ኖህ ፡- የአላህ ሰባኪ (  ነብይ አላህ)።
- አብራሃም ፡- የአላህ ጓደኛ ( ካሊል አላህ)።
- ሙሴ ፡- የአላህ አፍ ( ካሊም አላህ) ።
- ኢየሱስ ፡- የአላህ ቃል ( ካሊማት አላህ)።
- መሐመድ ፡- የአላህ መልዕክተኛ (ራሱል አላህ)።

ምንም እንኳ ሌሎቹ ነብያት በቁርኣን ክብርና ተቀባይነት ያላቸው ቢሆን እስልምና ትኩረት (ማዕከል) የሚያደርገው  መሐመድ ላይ ነው፡ ቁርአን " የነቢዮች መደምደሚያ" (ሱረቱ 33፥40) ይለዋል። ከሁለት መቶ ስሞቹ መካከል ሙስሊማኑ "የዘመኑ ክብር"  እና  "የዓለም ሰላም" ብለው ይጠሩታል።

መሐመድ በሀዲስ ጭምር ገኖ የሚታይ ምልክት ነው። ቁርኣን እንደሚያረጋግጠው በአሁኑ ሰዓት በእስልምናው ዓለም ከፍጥረታት በፊት የነበረ መልአክ ተደርጎ ነው የሚታየው። ባህሪያቱ ምንም እንኳ ቁርኣን ስለ ኃጢአቱ ይቅርታን መጠየቁን ቢገልጽም (ሱረቱ 40፥55፣ 48፥2፣ 110፥ 3) ባህሪያቱ ኃጢአት የለሽ እና ተስማሚ ተደርጎ ይወሰዳል።

በሕይወቱ ከተዘገቡት ድንቅ ምስክርነቶች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል ፡-

- ጠጠሮች በእጁ ላይ እንዲናገሩ አድርጓል።
- ሰውነቱ በማንኛውም ጊዜ ጥላ የለሽ ነበር።
- ዛፎች በአጠገባቸው ሲያልፍ ይሰግዱለት ነበር።

- በምሽት እስከ ሰባተኛው (ዘጠነኛው ) ሰማይ ተነጥቋል፡፡

የመሐመድ አንዳንድ መገለጦች (ንባቦች) ከነብዩ ባህሪያት እና ኃይማኖታዊ ስብከቱ ስምምነት በላይ አይታዩም፡፡ ሀዲስ መሐመድን የሥነ-ምግባር የመጨረሻ ባለስልጣን፣ የሕይወት መመሪያ፣ የፍርድ ቀን ማላጅ አድርጎ አይወስድም፡፡

የመሐመድ ቃላት እና ባህሪያት በሀዲስም ሆነ በቁርኣን የሙስሊማኑ ዕለት ተዕለት ሕይወት እስከ መቃብር ድረስ የሚገዛ ሀይማኖታዊ ደንብ ነው፡፡ የትኛውም የሕይወት አካሄድ፣ ከምግብ ራስን ማንጻት ፣ሰውነትን መንከባከብ እና አለባበስ ሁሉ የራሱ መመሪያ አለው፡፡

በተጨማሪም ሺአ ሙስሊማኑ ለመሐመድ አክስት ልጅ አማች ለሆነው አሊ ልዩ ክብር አላቸው፤ የእምነት ምስክርነታቸው (መግለጫቸው) የሚከተለውን ይመስላል፡-

*ከአላህ በቀር ሌላ አምላክ የለም*

*መሐመድ የአላህ መልእክተኛ ነው*

*አሊ ምክትል ፈላጊው ነው*

ሀዲስ የአሊን አስደናቂ ስኬታማ ታሪኮች ከመሐመድ ባልተናነሰ መልኩ ከትቧል፤ የአስራ ሁለቱ ኢማሞች ድርጊት እና ቃልም እንዲሁ ተዘግቧል፡፡ በሙሲሊማኑ ዘንድ በአመዛኙ መሐመድ አዲስ ሀይማኖት እንደ ጀመረ ሳይኾን፣ በዘመናት ሂደት የተበላሸው ዋናው እና እውነተኛው ሀይማኖት እንዳደሰ ነው የሚታመነው፡፡ ሱረቱ 41፥43 አላህ ለመሐመድ የተናገረውን እንዲህ ያስቀምጣል "ካንተ በፊት ለነበሩት መልክተኞች የተባለው ብጤ እንጅ ለአንተ ሌላ አይባልም ፡፡ ጌታህ የምህረት ባለቤት እና የአስማሚ ቅጣት ባለቤት ነው፡፡"

## 5.የፍርድ ቀን

ሙስሊማኑ በፍርድ ቀን ትንሳኤ ፣ የዘላለም ህይወት በጀነት ( ገነት) ወይም ጀሃነም ( እሳት )እንዳለ ያምናሉ፡፡ የማይታዘዙ አማኞች መጨረሻቸው እሳት የሚቆዩ ሲሆን፣ ጂሃዲስቶች (በጦርነት የገደሉ)፣ የመቅሰፍት ሰለ ባዎች፣ በስራ ጫና የሞቱ ሴቶች በፍርድ ቀን መቆም ሳይጠበቅባቸው በቀጥታ ጀነት እንደሚገቡ ይታመናል፡፡

በአመዛኙ የእስልምና እምነት እሳቤ መሐመድ በመጨረሻው ፍርድ ቀን ብቸኛው አማላጅ እንደሆነ ይነገራል፡፡ በእስልምና የነገረ-ፍጻሜ ክስተቶች ቅድመ ተከተል የሚከተለውን ይመስላል፡-

መጀመሪያ፡- የመጨረሻው ቀን ሰውን ሁሉ በሚያስተው የክርስቶስ ተቃዋሚ (ዳጃል) መምጣት ምልክት የሚታወቅ ይሆናል፡፡ ተከትሎም ኢየሱስ ወደዚህ ምድር ይመጣል ፣ ተቃዋሚውንም ይገድለዋል ፣ በምድርም ሰላም ይሆናል፣ ኢየሱስም ሰላምንና እስልምናን ይመሰረታል፡፡

ሁለተኛ፡- የፍርድ ጥሪ ይሆናል፡፡ አላህ እያንዳንዱን ሰው ይጠይቃል፡፡ የመጀመሪያ መለከት ይነፋል፤ በህይወት ያሉ ሁሉ ይሞታሉ፤ በሁለተኛው መለከት የሞቱ ሁሉ ዳግም ወደ ህይወት ይመለሳሉ (ሱረቱ 39፥68) እንዲሁም በማህሻር (የመሰብሰቢያ ቦታ) በአንድነት ይሰበሰባሉ፡፡ በዚያ በአላህ ፊት ለብዙ ጊዜ ይቆማሉ፡፡

ሦስተኛ፡- ፍርድ ይሆናል፡፡ አላህ እያንዳንዱን ሰው ይጠይቃል ፤ የመዝግብ መጽሐፍ ይከፈታል፡፡ በሚዛንም የሰው ስራ ሁሉ ይመዘናል፡፡ ሰው ከሰው ፣ ሰው ከእንስሳ የሰራው ሁሉ በሚመዝን ክፉ እና መልካም ሚዛን ይበየናል፡፡

አራት ፡- ሁሉም ሰው በአል-ሲራት (ከእሳት ወይም ገሀነም ወደ ጀነት በሚወስደው) ድልድይ ያልፋሉ፡፡ ከስለትም ከሰይፍም እጅግ በሳለው አል-ሲራት በሚያልፉበት ጊዜ የዳኑቱ ሲጠበቁ ተላላፊዎቹ ወደ እሳት ቁልቁል ይወድቃሉ፡፡ ስፍራው ሰባት ደጃፎች (ሱረቱ 15፥44) እና ሰባት ታሪኮች ወይም ዛኩም (የሚፈላ እሳት እና አጋንት የሰፈኑበት) (ሱረቱ 37፥ 62) ያሉት ሆኖ ምንም ማምለጫ የለውም፡፡ "እነዚያ መናጢ የሆኑትማ ፣ በእሳት ውስጥ ናቸው፡፡ ለእነርሱም በእርሷ ውስጥ ማነፋትና መንሰቅሰቅ አላቸው፡፡ ጌታህ ከሻው (ጭምራ ) ሌላ ሰማያት እና ምድር እስከ ዘወትሩ ድረስ በውስጧ ዘወተሪዎች ሲኾኑ (በእሳት ይኖራሉ)፡ ጌታህ የሚሻውን ሠሪ ነውና" (ሱረቱ 11፥106፣ 107)፡፡

ጀነት (ገነት) የቡሩካን ስፍራ እንደሆነ ቁርአን ያስረግጣል፡-

*ሱረቱ 47፥15*

*የዚያች ጥንቁቆቹ ተስፋ የተሰጧት ገነት ምስል በውስጧ ሽታው ከማይለወጥ ውሃ ወንዞች ፣ ጣዕሙ ከማይለወጥ ፣ወተትም ወንዞች ፣ለጠጪዎች ሁሉ ጣፋች ከኾነች የወይን ተጅም ወንዞች ከተነጠረ ማርም ወንዞች አልሉባት፡፡*

በዚህ ክፍል ቡሩካን “ከወፍራም ሐር በኾኑ ምንጣፎች ሲኾኑ ምንጣፎች ላይ የተመቻቹ ሲኾኑ (ይንፈላሰሳሉ)፡፡ የሁለቱም ገነቶች ፍሬ (ለለቃሚ) ቅርብ ነው፡፡ በውስጣቸውም ከበፊታቸው ሰውም ጃንም ያልገሰሳቸው ዓይኖቻቸውን አሳጣሪዎች አልሉ” (ሱረቱ 55፥54-58)፡፡

*ሱረቱ 56፥ 15-24*

*በተታቱ አልጋዎች ላይ ይኾናሉ፡፡ በእርሷ ላይ የተመቻቹና ፊት ለፊት የተቅጣጭ ሲኾኑ፡፡ በእነርሱ ላይ ሁል ጊዜ የማያረጁ ወጣቶች ልጆች ይዘዋወራሉ፡፡ ከጠጅ ምንጭም በብርጭቆዎችና በኩስኩስቶች በጽዋም (በእነርሱ ላይ ይዝዞራሉ)፡፡ ከእርሷ የራስ ምታት አያገኛቸውም ፤ አይሰክሩምም፡፡ ከሚመርጡትም ዓነት በእሸቶች ፡፡ ከሚሹትም በኾነ የበራሪ ሥጋ (ይዞሩባቸዋል)፡፡ ዓይናማዎች የኾኑ ነጫጭ ቆንጆዎችም አሏቸው፡፡ ልክ እንደተሸፈነ ሉል መስሎች የኾኑ ፡፡ በዚያ ይሠሩት በነበሩት ምክንያት ዋጋ ይኾን ዘንድ (ይህንን አደረግንላቸው)፡፡*

የሙስሊም ገነት ቆነጃጃት ሴቶች፣ የተዋቡ አልጋዎች እና ጣፋጭ ፍራፍሬዎች የሞሉበት የደስታ ቦታ ነው፡፡ ነገር ግን የቁርኣን ምንባባት በገነት የፈጣሪን መኖር (መታየት) አይናገሩም፡፡ ሶሪያዊው አፊፍ ታብባራ የሰማይ ደስታ ከምድር የሚለይ መኾኑን ይጠቅሳል፡፡[37] ይህ አጽዕኖት በቁርኣን አስረጅ ምንባብ የለውም፤ ሆኖም በቡኻሪ የተብራራውን ሀዲስ መሰረት አድርጎ ፈጣሪ “ለጻድቃን አምላኪዎች ሰዎች  በአይን ያላዩት እና በጆሮ ያልሰሙት ድንቅ ስፍራ” እንዳዘጋጀላቸው ይናገራል (ይህ ክፍል የመጀመሪያው ቆሮንቶስ 2፡9 ጋር ይመሳሰላል)፡፡ ታብባራ “ ፈጣሪን መገናኘት ” (ዓረብኛው ፡- ሊኹዋ ፤ ፈረንሳይኛው ፡-ሪቪል) በሱረቱ 10፥47 ፣11 እና 18፥110 እንደተገለጸው ክርስቲያኑ እንደ ራዕይ መሰል መንፈሳዊ ልምምዶች ጋር የሚተካከል እንደሆነ ይናገራል ፤ ሱረቱ 75፥ 22፣23ን “በመጥቀስም  የማይታየው ፈጣሪ ራሱን ካልገለጠልን በቀር እንዴት ማየት ይቻለናል ” ሲል አሳቡን ያጸናል፡፡

## 6. ቃዳእዋ ቃድር (የበጎ እና እን ክፉ ብይን)

ይህ አስተምህሮ በአጭሩ በዕጣ ፈንታ ማመን ተብሎ ይጠራል፡፡ ቃዳ (Qada) ማለት መወሰን፣ ማዘዝ እና መፍረድ ማለት ነው፡፡ የዳኛ ተግባር ወይም ቢሮን ያመለክታል፡፡ ቃድር መመዝን ወይም በመመዘኛ ላይ ማኖር ማለት ነው፡፡ ሁለቱም ቃሎች በአንድነት አላህ ደስ ያለውን ሁሉ በራሱ ፍቃድ የሚያደርግ መኾኑን ያመላክታሉ፡፡ ቃዳ የአላህን ዕውቀት እና ፍቃድ ሲወክል፤ ቃድር በዕውቀቱ እና በፍቃዱ ነገሮችን ወደ መኖር የሚያመጣበትን ተግባር ያሳያል፡፡

[37] አፊፍ ታባራራ፣ ረሁ አል-ዲን አል-ኢስላም( ደማስከስ ፣1972)፡፡

በሙስሊም አስተምህሮ በጎ እና ክፉ ክንዋኔ (ክስተት) ኹሉ በአላህ ብይን ላይ ነው የሚመሰረተው፡፡

በአያሌ ሙስሊም ነገረ-መለኮት ሙሁራን የክፉ ነገር ሁሉ ባለቤት አላህ እንደኾነ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ሙሁራኑ የሰውን ነጻ ፍቃድ ሙሉ ለሙሉ አይቀበሉም፡፡ የሺአ እስልምና እሳቤ ለሰው ነጻ ፍቃድ የጠወሰነ ቦታ ይሰጣል፡፡

በቁርኣን የአላህ ፍቃድ ምልዐት (ሁሉ የሚሆነው በርሱ ፍቃድ ነው እሳቤ) ጎልቶ ይታያል፦

*ሱረቱ 17፥16*

*ከተማንም ለማጥፋት በፈለግን ጊዜ ባለ ጸጋዎችዋንም እናዛለን፡፡ በውስጧም ያምጻሉ፡፡ በእርሷም ላይ ቃሉን (ቅጣቱ) ይፈጸምባታል፡፡ ማጥፋትንም እናጠፉታለን፡፡*

**ሱረቱ 14፡4**

*ከመልክተኛ ማኛውም ለእነርሱ ያብራራላቸው ዘንድ በወገኖቹ ቋንቋ እንጂ በሌላ አልላክንም ፡፡ አላህም የሚሻውን ያጣማል፡፡ የሚሻውንም ያቀናል፡፡ እርሱም አሸናፊዎች ጥበበኛው ነው፡፡*

በዕጣ ፈንታ የማመን ፍልስፍና በሙስሊማኑ የዕለት ተዕለት ህይወት እና ርዕዮተ -ዓለም እጅጉን ስፍራ ይዞ ይገኛል፡፡ በዚህም አስከፊ ጥፋቶች ሁሉ በትዕግስት ትከሻ እንዲያልፉት (እንዲቀበሉት) ይደረጋል፡፡ በሙስሊም መሬት ሁሉ ላይ ያለጥርትር አስተምህሮው የማይንቀሳቀስ እና የማያድግ ማህበረሰባዊ ሁናቴ እንዲሰፍን መንስኤ ኾኗል፡፡

**የግል ማስታወሻ**

# 6

# የሙስሊማኑ ተግባራት

እስልምና ለተከታዮቹ አምስት ሀይማኖታዊ እና ሕዝባዊ ተግባራትን እንዲያከናውኑ ያዝዛል፡፡

እነዚህም ተግባራት በሁሉም ጤነኛ እና ነፃ የሆኑ ትላልቅ የልጅነት ዕድሜን ለጨረሱ በሁሉም ያታዎች ለሚገኙ ሰዎች ግዴታ ናቸው፡፡ ለማይመቹ ነባራዊ ሁኔታዎ ለአብነትም ያህል ለበሽታ እና ለረሃብ ከግዴታ ነፃ የመደረግ ሁኔታ ይኖራል፡፡

## I. ሻሃዳ (“የሀይማኖት መግለጫ”)

*መሠረታዊ የሆነው የሙስሊማኑ የሀይማኖት መግለጫ*

*“ላ ኢላሃ ኢላ አላህ*

*መሐመድ ራሱል አላህ”*

*[ከአላህ በቀር አምላክ የለም፤*

*መሐመድም የእርሱ መልእክተኛ ነው፡፡]*

ይህ እንደ ሻሃዳ (“የምስክርነት ቃል”) በመሆን ይታወቃል፡፡ ይህንን በተደጋጋሚ መናገር የእያንዳንዱ ሙስሊም ቀዳሚ ተግባር ነው፡፡ በሙአድሂን (የአምልኮ ጥሪን በሚያስታውቀው ሰው) በአምልኮ ወቅት በሚነገር ጊዜ፣ ይህንን የሚሰሙ አማኞች ሁሉ በቃላት ወይም በሹክሹክታ ደግመው ሊናገሩት ይገባል፡፡ አዲስ በተወለደ ልጅ ጆሮ ላይ በተደጋጋሚ ይነገራል፡፡ ደግሞም እየሞቱ ባሉ ሰዎች ከንፈር ላይ በተደጋጋሚ ይነገራል፡፡ ግለሰብ በሆነ አማኝ ዘንድ እጅግ በጣም የተለመደ ንግግር ነው፡፡ ዳርዊሾች በስብሰባ ሥርዓታቸው ላይ ያነበንቡታል (ቻንት ያዜሙታል)፡፡ ደግሞም በሳውዲ ዓረቢያ ብሔራዊ ባንዲራ ላይ ሊገኝ ይገባል፡፡ በየሥፍራው ለሚገኙ ሙስሊሞች የዚህ አጭር የሃይማኖት መግለጫ ሥነ-ልቡናዊ እና ሀይማኖታዊ ጉልህነት ከስሌት ያለፈ ነገር ነው፡፡

ሸሃዳው ወይም የእምነት መግለጫው የእስልምናን ነገረ-መለኮታዊ መረዳት አሳጥሮ ያቀርበዋል፡፡ የሃይማኖት መግለጫው ንግግር እስላማዊ ሕግ በሚሠራባቸው ግዛቶች ውስጥ ብቻ የሚተገበር ነው፡፡ ይህም ሸሪያው ከሚታዩ የመታዘዝ ወይም የአለመታዘዝ ተግባራትን ብቻ የሚመለከት በመሆኑ ነው፡፡ ሸሃዳውን ወይም የሀይማኖት መግለጫውን ማብራራት፣

መትርጉምም ሆነ ማስፋፋት ለሙስሊም የነገረ-መለኮት ምሁራን እና ሊቃውንቱ የተተወ ነገር ነው፡፡

## II. አል-ሶላት ("ጸሎት")

ሁለተኛው የሙስሊማኑ ተግባር አል-ሶላትን ("ጸሎት") መፈጸም ነው፡፡ ሶላት የሚለው ቃል "ይቅርታ መጠየቂያ አምልኮ ወይም የንስሐ ጸሎት" የሚል ፍቺ ካለው የአረማይክ ቋንቋ ሥርው-ቃል የተወሰደ ነው፡፡ ቀላል ፍቺ ካለው የእንግሊዝኛ ቃል ጋር አብሮ በማይሄድ መልኩ ልዩና አድራጊነትን አመልካች ቃል ነው፡፡ ልዩ ተግባራትን እና ንግግሮችን በቅደም ተከተል መያዝን ያመለክታል፡፡ ሙስሊማኑ በተገቢው መንገድ እንዲጠቀሙበት የሚያደርጉ አምስት መርኖች አሉ፡-

- በታዘዘው የመንጻት ሥነ -ሥርዓት ሊቀደም ይገባል፡፡
- የመጸለያው ሥፍራ ከየትኛውም ንጽሕና ከጐደለው ነገር ነፃ መደረግ አለበት፡፡
- ሰውነት እና አልባሳት ንጹሕም ሆነ ጽዱ ሊሆኑ ይገባል፡፡
- ፊትን በመካ በሚገኘው በካእባአ አቅጣጫ ማድረግ ይገባል፡፡
- ጸሎቱ ሥርዓት በተጠበቀበት መልኩ ሊከናወን ይገባል፡፡ በጸሎት ጊዜ ማውራት፣ መሳቅ፣ መጫወት ወይም ምግብ መብላት ውጤታማነቱን ይቀንሰዋል፡፡

አል-ሶላትን ለመፈጸም ሙስሊሙ ሥርዓታዊ ንጽሕና ማድረግ ይኖርበታል፡፡ የሙስሊሞች መጽሐፍ ወይም ሕግ ሁለት ዐይነት መተጣጠብን ወይም ንጽሕና መጠበቅን ይፈቅዳል፡፡ አነስተኛው መተጣጠብ ወይም ንጽሕናን መጠበቅ (*ዑዱ)* ፡- ራስን፣ ጢምን፣ ዕጆችን (ከጣቶች እስከ ክርን ድረስ ያለውን)፣ እንዲሁም ዕግሮችን (ከዕግር ጣቶች እስከ ቁርጭምጭሚት ድረስ ያለውን)፣ ማጽዳትን ይዝዛል፡፡

ዋናው መተጣጠብ ወይም ንጽሕናን መጠበቅ (*ግሁስል)* ፡- ሙሉ የሆነ የሰውነት መታጠብን ያዝዛል፡፡ ይህም ደግሞ መታጠብን ሕዝባዊ በሆነ መልኩ በሙስሊም አገሮች ታዋቂ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ በበረሃ ያሉ እረኞች ዘወትር በተደጋጋሚ በውኃ ጉድጓዶች ውስጥ ጠልቀው ይገባሉ፡፡ አልፎ አልፎ ኃይለኛ መርዝን የያዘ የጠጉር ማስወገጃ የጽዳቱን ተግባር ይበልጥ ጥልቀት ያለው እንዲሆን ለማድረግ ጥቅም ላይ ይውላል፡፡

ውኃ በማይኖርበት ጊዜ በአሸዋ የሚደረግ ተምሳሌታዊነት ያለው እጥበት ሊደረግ ይችላል። ይህም ደግሞ ***ታያሙም*** ተብሎ ይጠራል። የአይሁድ ታልሙድም እንደዚሁ አሸዋን መጠቀምን በተመሳሳይ መንገድ ይፈቅዳል። አንድ ክርስቲያን የሆነ ታሪክ ጸሐፊ በበረሃ በሚደረግ ጊዜ ወቅት በአሸዋ የተከናወነ አንድ የጥምቀት ሥነ ሥርዓትን ይገልጻል።

የሥርዓተ መንጻት ወይም መተጣጠብ መንገድን በተመለከተ የእስልምና ሕግን የሚያብራሩ አራቱ አሳባዊ ትምህርት ቤቶች አሥራ አራት ልዩነቶችን ይፈቅዳሉ። ይሁን እንጂ፣ አምልኮ ፈጻሚው ሰው የራሱን ወይም የራስዋን ማንነት መደበቅ እና በንጹሕ ሥፍራ ላይ መገኘትን በተመለከተ ሁላቸውም በአንድነት ይስማማሉ። ስለሆነም በሙስሊማኑ ዘንድ ጸሎት ማድረጊያ ጨርቅ ወይም ምንጣፍ መጠቀም የተለመደ ነገር ሆኖአል። ሙሉ የሆነ ሥርዓተ መንጻት የሚከተለውን የአሠራር መንገድ ሊከተል ይገባል፦

- ዕጆችን መታጠብ።
- አፍን መጉመጥመጥ።
- የአፍንጫን የውስጥ ክፍል ማጠብ።
- ፊትን ማጠብ።
- ክንድን ማጠብ።
- ዕጆችን ወደ ጠጉር መውሰድ።
- ጆሮዎችን ማጠብ።
- ዕግሮችን ማጠብ።

## 1. አንድ ምሳሌ እንውሰድ ፦ የማለዳ ጸሎት ዝርዝር!

ለየቀኑ የሚታዘዙ አምስት የአምልኮ ጊዜያት አሉ፦ እነዚህም ልክ ከመንጋቱ በፊት፣ ከዕኩለ ቀን በኋላ፣ በከሰዓት በኋላው ጊዜ መካከል ላይ፣ ልክ ፀሐይ ስትጠልቅ እና በምሽት ወቅት ያሉ ናቸው። ምንም እንኳ የጸሎት ጊዜያቱ ካለፉ በኋላ ጸሎቱ ሊደረግ የሚችል ቢሆንም፣ ከእነዚህ ተግባራት የቱም ቢሆን ከትክክለኛው ጊዜ በፊት ሊደረጉ አይገባም። ጸሎቱ ልማዳዊነት ባለው መልኩ በዙሮች ተከፋፍሎ የሚደረግ ነው። ለእያንዳንዱ ጸሎት ጊዜም የተወሰኑ ቍጥሮች የሚፈለጉ ናቸው።

- የማለዳ ጸሎት በ 2 ዙር ይደረጋል፡፡
- የቀትር ወቅት ጸሎት በ 4 ዙር ይደረጋል፡፡
- የዕኩለ ከሰዓት በኋላ ጸሎት በ 4 ዙር ይደረጋል፡፡
- የጀንበር መጥለቂያ ጸሎት በ 3 ዙር ይደረጋል፡፡
- የምሽት ጸሎት በ 4 ዙር ይደረጋል፡፡
- የዕለቱ አጠቃላይ በ17 ዙር ይደረጋል፡፡

ብዙ ሰዎች አምላኪው በዕውነተኛው መልኩ ምን እያደረገ እንደ ሆነ ሳይረዱ ሙስሊማኑ ዕለታዊ ጸሎታቸውን ሲያደርጉ ይመለከቱዋቸዋል፡፡ የሙስሊማኑ የማለዳ ጸሎት/ሥርዓት-አካሄድ ይህ ነው፡-

- በትክክለኛው ሥርዓት የታዘዘውን ሥርዓተ-መንጻት ከፈጸመ በኋላ ሙስሊሙ በመካ አቅጣጫ ለጸሎት ይነሣል፤ ዕጆቹን እስከ ጆሮዎቹ ድረስ ወደ ላይ ያነሣ እና "አላሁ አክበር" ("አላህ ታላቅ ነው!") ይላል፡፡
- ከዚያም በጸጥታ አል-ፋቲያን ይቀራል (ይህም የቊርኣን የመጀመሪያው ምንባብ ያለበት ክፍል ነው)፤ እርሱም መሐሪ እና ሩኅሩኅ በሆነው በአላህ ስም፡፡ የሁሉም ፍጡራን ጌታ ለሆነው፣ መሐሪ ለሆነው፣ ርኅራኄን ለተመላው፣ በጥፋት ቀን ላይ ጌታ ለሆነው ለአላህ ክብር ይገባዋል፡፡ አንተን ብቻ እናገለግላለን፡፡ ለሱኮር ወደ አንተ ብቻ እንጸልያለን፡፡ በቀጥተኛው መንገድ፣ አንተ በባረክሃቸው ሰዎች መንገድ ምራን! አንተ በተቈጣህባቸው ሰዎች ወይም በተጣሉቱ ሰዎች መንገድ አትምራን!" የሚል ነው፡፡
- ሙስሊሙ ምናልባት ሌላ አጭር ቊርኣናዊ ምንባብ ሊቀራ ይችላል፡፡ በአጠቃላይ አነጋገር ሱረቱ 112ን የሚጠቀም ሲሆን፣ ይህም "እርሱ አላህ ነው፤ ዘላለማዊ እና ፍጹም የሆነ አንድ አምላክ ነው፤ እርሱ አይወልድም፤ አልተወለደምም፤ ደግሞም እርሱን የሚያክለው ማንም የለም" የሚል ነው፡፡
- ከዚያም ሙስሊሙ እንዲህ ይላል፡- "አላሁ አክበር!" ወደ ታች ወደ ምድር ጎንበስ ይልና "ብርቱው ጌታዬ የተባረከ ይሁን!" የሚለውን ይደጋግመዋል፡፡
- ይህን ተከትሎ ሰውነቱ ቀጥ ባለበት ሁኔታ እንዲህ ይላል፡- "አምላክ እርሱን የሚያመሰግነውን ሰው ያደምጠዋል፡፡"

- ከዚያም “አላሁ አክበር!” የሚለውን በተደጋጋሚ ይለዋል፡፡ ግንባሩ ምድርን እስኪነካ ድረስ በጉልበቱ ይንበረከካል፤ ደግሞም “ልዑል ለሆነ ጌታዬ ምስጋና ይግባው!” የሚለውን ሦስት ጊዜ በመደጋገም ይናገራል፡፡
- እርሱም እንዲህ ይላል፡- “አላሁ አክበር!” ደግሞም የላይኛውን አካሉን ቀና ያደርጋል፤ ዳሩ ግን በተንበረከከበት ይቆያል፡፡
- ከዚያም ራሱን ለሁለተኛ ጊዜ ለስግደት ዝቅ ያደርጋል፡፡ “ልዑል ለሆነው ጌታዬ ምስጋና ይግባው!” የሚለውን ሦስት ጊዜ በመደጋገም ይናገራል፡፡
- ከዚያ በኋላ “አላሁ አክበር!” ይልና ይነሣል፤ ደግሞም ሁለተኛውን የጸሎት ዙር ይጀምራል፡፡ ይህንን ለመጀመር አል-ፈቲሐውን ወይም አጭሩን ሱረት (ቍርኣናዊ ምንባብ) በድጋሚ በጸጥታ ይቀራዋል፡፡
- ከዚያ በኋላ “አላሁ አክበር!” ይላል፤ ይንበረከካል፤ ደግሞም በዚህ የአካል ቁመና መልኩ ቆይቶ “ብርቱ ለሆነው ጌታዬ፣ ምስጋና ይግባው!” የሚለውን ሦስት ጊዜ በመደጋገም ይናገራል፡፡
- ከዚያም ቀጥ ብሎ ይቆምና “አላህ የሚያመሰግነውን ሰው ያዳምጣል!” ይላል፡፡ ከዚያም ወደ ምድር ይደፋል፤ ደግሞም ልዑል ለሆነው ለጌታዬ ምስጋን ይግባው! የሚለውን ሦስት ጊዜ በመደጋገም ይናገራል፡፡ “አላሁ አክበር!” የሚለውን በመደጋገም ካለ በኋላ እንደ ገና በጉልበቱ ተንበርክኮ ሳለ የላይኛውን የሰውነት ክፍሉን ቀና ያደርጋል፡፡
- ከዚያም ለአራተኛ ጊዜ ይሰግዳል፤ ደግሞም “ልዑል ለሆነው ለጌታዬ ምስጋን ይግባው!” በማለት ሦስት ጊዜ ይናገራል፡፡
- ከዚህ በኋላ ራሱን ያነሣል፤ ደግሞም አሁንም ተንበርክኮ ሳለ የሚከተለውን የሀይማኖት መግለጫ ይናገረዋል፡- “ሰላምታዎች፣ ስጦታዎች፣ በአምልኮ ጊዜ የሚቀርቡ ስጦታዎች፣ ጸሎቶች ሁሉ ለአላህ ይገቡታል፡፡ ኦ! የአላህ ሰላም፣ ምሕረቱ እና በረከቶቹ በአንተ በነቢዩ ላይ ይሁን! ከአላህ በቀር ሌላ አምላክ እንደ ሌለ እኔ እመሰክራለሁ፡፡ እርሱ ብቸኛ እና አጋር የሌለው እንደ ሆነ እመሰክራለሁ፡፡ መሐመድ የእርሱ አገልጋይና መልእክተኛ እንደ ሆነ እኔ እመሰክራለሁ” ይላል፡፡
- በመጨረሻም አሁንም በጉልበቱ ተንበርክኮ ሳለ ራሱን ወደ ቀኝ ያዞርና “የአላህ ሰላም እና ምሕረት በአንተ ላይ ይሁን! ይላል፡፡ በዚህም የማለዳው ጸሎት ያበቃል፡፡

የዝግጅት ተግባራቱ እንደ ተጠናቀቀ አራት የመግቢያነት ሚና ያላቸው የአምልኮ ክፍሎች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡ እነዚህም፡-

- ቆሞ ፊትን ወደ ካእባአው ማድረግ፡፡
- "ቢስሚላሂ" ማለት ("መሐሪና ሩኅሩኅ በሆነው በአላህ ስም") ከአንዱ ከ9ኛው ሱረቱ በስተቀር ሁሉም (114 ቱም ሱረቱዎች) በዚህ አባባል ይጀምራሉ፡፡ ከየትኛውም ተግባር በፊት በመጀመሪያ ላይ በተገቢው መንገድ ይባላል (ይቀራል)፡፡ ማሻሻያ በተደረገበት መልኩ ሥጋን የተቀደሰ /ንጹሕ/ ለማድረግ ጥቅም ላይ ይውላል፡፡ ይህም ሥርዓታዊ በሆነ መልኩ ሊመገቡት የሚችሉት እንዲሆን ለማድረግ ነው፡፡
- ኢስቲያዛውን መናገር ("መጠጊያን መፈለግ")፡፡ ይህ አባባል ጊዜውን እና ሁኔታውን ከሰይጣን ጣልቃ-ገብነት የተጠበቀ እና የተቀደሰ እንዲሆን ማድረጊያ ነው፡፡
- የአድሃን ንግግር ("ለአምልኮ የሚሆን ጥሩ") ንግግር፡፡ ይህም በሌሎች ሃይማኖቶች ያሉ ተመጣጣኝነት ያላቸው ሥርዓተ-አምልኮዎች ፡- አረማዊ የእሳት ማንደድ፣ የአይሁድ ቀንድን ማራገፍ፣ የክርስቲያኖች ቀጭን እንጨት (እንጨት፣ ወይም ሦስት ጎን መጠቀም) እንዲወገዙ ከተደረገ በኋላ በመዲና የተደነገገ ነው፡፡ አድሃን (የአምልኮ ጥሪው) ተለምዶአዊነት ባለው መልኩ ሰባት ዐርፍተ ነገሮችን ይይዛል፡፡ ከመንጋቱ በፊት የሚደረገው ጸሎት ስምንተኛውን ዐረፍተ ነገር ያክላል፤ ይህም "ጸሎት ከመተኛት ይሻላል!" የሚለው ነው፡፡

ጸሎቱ ራሱ አራት ተግባራትን እና አራት ንግግሮችን ይይዛል፡፡ አራቱ ተግባራት፡- መቆም፣ መንበርከክ፣ በግንባር ምድርን መንካት እና መቀመጥ ናቸው፡፡ እያንዳንዳቸውም በልዩ አኳኋን ይደረጋሉ፡፡ ንግግሮቹ የኒያት አባባልን (ጸሎትን ማድረጊያው አሳብን)፣ የሚቀራው የቁርዓኑ ክፍልን እና ልዩ ልዩ የሆኑ የምስጋና ማቅረቢያ መንገድን ያካትታሉ፡፡ ወደ ምድር በሚደፉበት ጊዜ የግል ልመናዎች ሊካተቱ ይችላሉ፡፡

## 2. የጉባኤ አምልኮ

በየዓርቦቹ የጉባኤው አገልግሎት የዕኩለ ቀን ጸሎትን የሚያካሄድ ይሆናል፡፡ ቁጭ ብሎ ሳለ አንድ ክሃቲብ ("ሰባኪ") በአብዛኛው ደረጃውን የጠበቀ ስብከትን ዜማዊነት ባለው መልኩ ያቀርባል፤ ከዚያም ይቆማል፤ በስሙ የተጠቀሰ ገዥ ወይም አስተዳዳሪን ለመባረክ እንደ ገና ይቆማል፡፡ ከታሪክ አንጻር ስንመለከተው ይህ አዳዲስ ገዥዎችን የማስተዋወቂያ ጊዜ ነው፡፡

አራቱ የጸሎት ሥነ ሥርዓት  አቅጣጫዎች ራካህን (ዙረትን ወይም ዑደትን) ይይዛል፡፡ በየቀኑም ደግሞ ሰባት ዙሮችን ያብጃሉ፡፡ በፈቃደኝነት የሚፈጸም ተጨማሪ አምልኮ እንዲደረግ ይመከራል፡፡ መቃብሮችን፣ ድርቅን፣ ፀሐይና የጨረቃ ግርዶሽን ጨምሮ በበዓል ቀናት ተጨማሪ የሆኑ ልዩ የበዓል አከባበር ሥነ ሥርዓቶች ይፈጸማሉ፡፡ በሙስሊማኑ ሕግ አንድ የሚከበር    ሥነ ሥርዓት እንዲያጥር ሊደረግ ወይም ሁለት ሥነ-ሥርዓቶች በአንድ ላይ ሊጠቃለሉ ይችላሉ፡፡

ሙስሊማኑ ዐይኖቻቸውን ከፍተው ይጸልያሉ፡፡ በመስጅድ በሚደረግ አምልኮ ወቅት ወደዚያ የሚወሰድ ምንም ስጦታ የለም፡፡ የመስጅድ ወጭዎች በሙሉ የሚሸፈኑት በዋቅፍ (ማለትም ከእስልምና ሀይማኖታዊ እና ከሕዝብ በሚሰበሰብ ገቢ) ነው፡፡ መስጅድ ከአምልኮ ውጭ ማስተማርን፣ ገለጻ መስጠትን፣ የመንግሥት ዐዋጅ ማሰማትን፣ ምስኪን ተጓዦችን ማስጠለልን አካትቶ ለሌሎች ሕዝባዊ ዓላማዎች ጥቅም ላይ ይውላል፡፡ የአርብ የጉባኤ አምልኮ በይፋ በተለየ መስጅድ ይከናወናል፤ በግል መስጅድ አይደረግም፤ ደግሞም አምልኮው ዋጋ ያለው እንዲሆን ቢያንስ  ነፃ የሆኑ አርባ ወንዶች ሊካፈሉበት ይገባል፡፡

### 3. አንድ ሙስሊም በየዕለቱ ምን ያህል ጊዜ ያጠፋል?

በየዕለቱ ጥቅም ላይ የሚውሉ የጸሎት ጊዜያት በስፋት ይለያያሉ፡፡ አንድ ሁሉንም ነገር የሚረዳ ሙስሊም የሚያጠፋው ጊዜ በቅርቡ በሚከተለው መልኩ ተገምቶአል፡-

- መደበኛ ሙስሊም (ከሙስሊሙ ማኅበረሰብ 70 % ገደማ የሚሆነው) መደበኛነት ያላቸውን ጸሎቶች ለመጸለይ በቀን 80 ደቂቃ ጊዜን ይወስዳል፡፡
- አክራሪ ያልሆነ ሀይማኖተኛ ሙስሊም (ከሙስሊሙ ማኅበረሰብ 6-8 % ገደማ የሚሆነው) የሱረቶችን ምንባባት አካትቶ ለመጸለይ በቀን 150 ደቂቃ ጊዜን ይወስዳል፡፡
- አክራሪ ሙስሊማኑ (ከ 1 % በታች የሚሆኑቱ) የቂያም አል ላይልን  ማለትም የምሽት ጸሎቶችን ጨምረው ይጸልያሉ፡፡ እነዚህ ጸሎቶች በረመዳን ወር ብቻ የሚጸለዩ ናቸው፡፡ ጸሎቱ በቀን 300 ደቂቃዎችን ይወስዳል፡፡
- ሌሎች ሙስሊማኑ  ወደ 21 % ገደማ የሚሆኑቱ  በአርብ ቀናት እና በሁለቱ በዓላት (በኢድ አድሀ እና በኢድ አልፈጥር)  በዓላት ወቅት ብቻ ይጸልያሉ፡፡

## III. ሳውም (ፆም)

ሦስተኛው የአንድ ሙስሊም ተግባር መፆም ነው። ይህ ሳውም ይባላል ፣ ፍችው መፆም ማለት ነው። ቍርኣን እንዲህ ይላል፡-

***ሱረቱ 2÷183-85***

*"ኦ፣ እናንተ የምታምኑ ሰዎች ሆይ÷ ፆም ከእናንተ በፊት ለነበሩት ሰዎች እንደ ታዘዘላቸው ሁሉ እንዲሁ ለእናንተም ታዝዞላችኋል፤ ይህም ደግሞ ምናልባት ራሳችሁን መከላከል እንድትችሉ ነው። የሚፆምባቸው የተወሰኑ ቍጥሮች ያሉባቸው ቀናት ናቸው። ነገር ግን ከእናንተ አንዱ ቢታመም ወይም በጉዞ ላይ ቢሆን፣ በሌላ ጊዜ ተመሳሳይ ቍጥር ያላቸውን ቀናት በፆም ያሳልፍ። ፆም ሊያደርጉት ለሚችሉቱ ሰዎች የሚሆን ክፍያ አለው። ይህም ችግረኛ ሰውን መመገብ ነው። ነገር ግን የገዛ ራሱን ፍላጎት ማሟላት የቻለ ሰው፣ ይህ ለእርሱ የተሻለ ነገር ነው። ዳሩ ግን መፆም ለእናንተ መልካም ነገር ነው። የምታደርጉትም ከሆነ ይህን ዕወቁ። ይህም የረመዳን ወር ቍርዓን የተገለጠበት፣ ለሰው ልጆች ምሪት የተሰጠበት፣ ምሪትና ሊሟሉ የሚገባቸው መሥፈርቶች በግልጽ የተረጋገጡበት ወር መሆኑ ነው። በዚያ ወር የተገኛችሁ ማናችሁም ብትሆኑ ፁሙ፤ ነገር ግን የታመመ ወይም በጉዞ ላይ የነበረ ሰው በሌላ ጊዜ እነዚያኑ ያህል ቀናት ይፁም። አላህ ለእናንተ ቀላል የሆኑ ነገሮችን ይመኝላችኋል፤ እርሱ ለእናንተ መከራን አይመኝላችሁም፤ ስለዚህም የፆሙን ጊዜ ልትፈጽሙ ይገባችኋል። እርሱ ምሪቱን ስለ ሰጣችሁ፣ አላህን ከፍ ከፍ ልታደርጉት ይገባል። በዚህም ደግሞ እናንተ አመስጋኞች ትሆናላችሁ።"*

ፆም ሁለት ፍሬ ጉዳዮችን ይይዛል፡- ከሁሉም አካላዊ መደሰቻዎች የሚራቅበት አሳብ አንደኛው ነው፤ ሁለተኛው ደግሞ በቀኑ ብርሃናም ሰዓታት የሚደረገው ዕውነተኛ ፆም ነው። ሀይማኖታዊም ተግባር ነው። (የቍርዓን መውረድ ተከናውኗል ተብሎ የሚታሰበው "በኃይል ምሽት ነው"፤ ይህም በኋለኛው የወሩ ሦስተኛ ክፍል ወቅት ነው። ሁሉም የስሜት ህዋሳቶቹ ለሚሠሩ ሙሉ ሰው ነው ለሚባል ወንድ ሁሉ ፆም ግዴታ የሆነ ተግባር ነው። በተመሳሳይ ጊዜም በወር አበባዋ ጊዜ ካልሆነ በቀር ሁሉም የስሜት ህዋሳቶችዋ የሚሠሩ ለሆነች ሙስሊም ሴት ግዴታ ነው። ፆም በሚከተሉት ምክንያቶች ዋጋ-ቢስ ይሆናል፡-

- ውኃንም ሆነ የትኛውንም ፈሳሽ ነገር መጠጣት።
- ማጤስ።
- መብላት።

- ምራቅን መዋጥ፡፡
- ሆን ተብሎ የሚደረግ ማስታወክ፡፡
- በፍትወታዊ ግንኙነት፡፡
- ፆታዊ በሆነ ንኪኪ ሆን ተብሎ በሚደረግ ብልትን ማርጠብ፡፡
- መስከር፡፡

ፆሙ በማለዳ ይጀምራል፡፡ ይህም በክንድ ርዝመት አንድ ነጭ ክር ከጥቁሩ ክር ሊለይ በሚችልበት ፍጥነት የሚሆን ነው፡፡ እስከሚጨልም ድረስም ይቀጥላል፡፡ በግልባጩም ተመሳሳይ ሙከራ ይደረጋል፡፡ በብዙዎቹ እስላማዊ ከተሞች የፆሙ መጀመርና መጠናቀቅ ለማሳየት የእሳት ምልክት ይደረጋል፡፡

ምፀታዊነት ባለው መልኩ ብዙ ሙስሊማኑ በምሽት ከተለመደው በላይ የሆነ ምግብ በሚመገቡበት ማኅበራዊ በሆነ የምሽት መሰብሰብ የቀኑ ፆም ምሽት ላይ ይካካሳል፡፡ በውጤቱም የረመዳን ወቅት አንዳንድ ጊዜ የግብዣ ወር በመባል ይጠራል፡፡ እስላማዊ ሕግ ከቀኑ የፆም ሰዓቶቻቸው ጥቂቶቹን በዕንቅልፍ እንዲያሳልፉ ይፈቅዳል፡፡ የጨረቃ (ሉናር) ዓመት ከፀሐይ (ሶላር) ዓመት ይልቅ አጭር በመሆኑ ምክንያት የረመዳን ፆም በየትኛውም ወር ላይ ሊከሰት ይችላል፡፡ ህሙማን መፆም አይጠበቅባቸውም፡፡ ሌሎች ግን መፆም አለባቸው፡፡ ደግሞም በጣም ሞቃት በሆነ ወር ሙሉውን ቀን ያለ ምግብ እና ውኃ መሥራት አበሳ ነው፡፡ ፆምን በተመለከተ ሌሎቹ መመሪያዎች፡-

- በአንዳንድ ሁኔታዎች የሀጅ ምትክ በማድረግ ቁርኣን ፆምን ያዝዛል ("የሀይማኖት ጉዞ" ፣ ሱረቱ 2÷196)፡፡
- አንድን አማኝ በዐደጋ መልኩ ስለ መግደል ለሁለት ተከታታይ ወራት መፆም ግዴታ ነው (ሱረቱ 4÷92)፡፡

## IV. ዘካ (ስጦታ-ግብር)

አራተኛው የአንድ ሙስሊም ተግባር ስጦታ - ግብር መክፈል ነው፤ ይህም ዘካ በመባል ይጠራል፡፡ (ቃሉ በቁሙ ወይም በጥሬው ሲተረጎም "ንጹሕ መሆን" ማለት ነው፤ መልካምነትን ለማመልከት በቁርኣን ውስጥ በየሥፍራው ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ ስጦታን ለድሆች የመስጠትን ልምምድ መሐመድ ራሱ ይተገብረውም ያበረታታውም ነበር፡፡ ብድራትን የሚያስገኝ ተግባርም

ተደርጎ ቀጥሏል። እንዲህ ያለው ለጋስነት መልካም የሆነ ዕድል በሚያጋጥም በየትኛውም ጊዜ የሚካካስ ይሆናል።

ይህም ከጉዞ ሲመለሱ፣ በወሊድ ጊዜያት፣ በሰርግ ቀናት፣ በግብዣ ቀናት እና በዓመት በዓላት ወቅቶች የሚተገበር ነው። በአንዳንድ ሥፍራዎች ላይ ስጦታን የመስጠት ልምምዱ ችግሮችን አስነሥቷል። ይህም ሙያተኞች የሆኑ ለማኞችን በመፍጠር፣ እንዲሁም ለችግረኞች እና የአካል ጉዳት ላለባቸው ሰዎች መደበኛነት ያለውን ዕንክብካቤ መስጠትን እንዳይበረታታ በማድረግ የተከሰተ ችግር ነው።

ምንም እንኳ በገዛ ፈቃዳችን የሚደረገው የለጋስነት ልምምድ ወደ ብዙኀኑ የተሰራጨ ቢሆንም፣ የቅንጅት ዕጦት ረሃብንም ችግርንም ከማስወገድ ይልቅ እነዚህን ነገሮች ወደ መፍጠሩ የሚያዘነብል እንደ ሆነ ብዙዎች የተማሩ ሙስሊማኑ ማጉረምረም በተሞላበት መልኩ ይናገራሉ።

በሱረቱ 9÷60 መሠረት ስጦታ መስጠት ግዴታነት ያለው ተግባር ነው። ስጦታዎች ሊሰጡ የሚገባው፡-

- ለድሆች እና ችግረኞች።
- ገንዘቦችን ለማስተዳደር ለተቀጠሩ ሰዎች።
- "ልቦቻቸው ሊታረቁ ለሚገቡ ሰዎች።"
- ምርኮኞችን እና ባለ ዕዳዎችን ነፃ ለማድረግ።
- ለመንገደኞች።

ምን ያህል ሊሰጥ ይገባል? የሚለውን መወሰኛ የሆነው የአሠራር ዘዴ ውስብስብ ነው። ሕጉን በተመለከተ የሻፊ እምነት ዐቋም ሙስሊማኑ ብቻ ዘካ መክፈል አለባቸው ይላል። እንደ ተምር፣ ወይን፣ በለስ ያሉትን ፍራፍሬዎች ጨምሮ ከምግብ ሰብሎች አሥር በመቶ ይሰበሰባል። ይህም ምድሪቱ እርጥበት አዘል የአየር ንብረትን በማግኘት ላይ የተመሠረተች እስከ ሆነ ድረስ ዕውን የሚሆን ነው።

በመስኖ ከሚደረግ እርሻ የሚደረግ ዘካ እስከ 5 በመቶ የሚቀንስ ይሆናል። በሁለቱም ሁኔታዎች ክፍያው የሚፈጸመው በመከር ጊዜ ነው። የቤት እንስሳት መላውን ዓመት ግጦሽን ሊመገቡ ይገባል፤ ደግሞም ሥራ እንዲሠሩ ሊደረጉ አይገባም። 5 ግመሎች፣ 20 ከብቶች፣

ወይም 40 በጎችን ወይም ፍየሎችን አሟልቶ የተገኘ ሰው 5 በመቶ ዘካ መክፈል ይኖርበታል። በገንዘብ ከሚፈጸም ክፍያ ላይ በወርቅ፣ ወይም በብር ከቊሳቊሶች ሽያጭ ሊከፈል የሚገባው ዘካ 2 በመቶኛ ሁለት ተኩል ብቻ ነው።

ተጨማሪ ምጽዋቶች በኑዛዜዎች፣ ከስጦታዎች እና ከሌሎች ከሥራ በሚገኙ ገቢዎች የሚከፈሉ ይሆናሉ። በተጨማሪም ሀብታም የሆኑ ሙስሊማኑ ለበጎ አድራጎቶች ወይም ለበጎ-ዐድራጎት ወኪሎች፣ እንዲሁም ለሀይማኖታዊ ማምለኪያ ሥፍራዎች በተደጋጋሚ ትልቅ ድምር ያለውን በገንዘብ ስጦታም ይሁን በቁሳቁስ መልኩ ያወርሳሉ። በብዙዎቹ እስላማዊ አገራት እንደዚህ ያሉቱ ተቋማት በቅርቡ በመንግሥት ተወርሰዋል፤ ደግሞም ልዩ የሆነ የሥራ ክፍል /ዲፓርትመንት/ እንዲሆኑ የአስተዳደር ተግባር ይከናወንላቸዋል።

በጥንታውያን የሙስሊም መለኮታዊ አስተዳደር ስጦታዎች ዘወትር እንደ ግብር ይሰበሰቡ ነበር። ዛሬ ላይ ይህ እምብዛም ዐይታይም፤ ደግሞም የዘካ መስጠት ልምምድ በአብዛኛው ለግለሰቡ ተትቷል። ግለሰቦቹ ናቸው ለድሀ ወይም ለመስጅድ ወይም ለሀይማኖታዊ ተቋም መውሰድ እንዳለባቸው የሚወስኑት።

## V. ሀጅ ("ሀይማኖታዊ ጉዞ")

አምስተኛው የእስልምና ምሠሦ ሀጅ፣ ወደ መካ የሚደረገው ሀይማኖታዊ ጉዞ ነው። ይህ ጉዞ ሀይማኖቱን ከሚጠብቅ ሙሉ ሰው ከሆነ ወንድም ይሁን ሴት ሙስሊም ቢያንስ በሕይወት ዘመን አንድ ጊዜ የሚጠበቅ ነገር ነው። ይኸውም ጉዞውን ለማድረግ በአካላዊ ብቃት ረገድ ማለፊያ ሁኔታ ላይ ካለ ሰው የሚጠበቅ ነገር ነው (ሱረቱ 3÷97)። ባሮች፣ የአእምሮ ህሙማን፣ መበለቶች እና ዘመድ-ዐልባ ሴቶች ከዚህ ግዴታ ነፃ ናቸው።

የሀጅ ማድረጊያ ቀናት በዘል-ሂጃ ወር በሚገኙት ከመጀመሪያው እስከ አሥራ ሁለቱ ቀናት ያሉት ናቸው። ይህ በጨረቃ (ሉናር) ዓመት የሚገኘው የመጨረሻው ወር ነው። በመካ ልዩ ሥርዓቶች የሚደረጉባቸው ሦስት ቀናት አሉ፤ እነዚህም ከሰባተኛው እስከ አሥረኛው ወር ድረስ ባሉት ጊዜያት የሚገኙ ናቸው። ሀጅ በዓመቱ በሌሎች ጊዜያት ሊደረግ ይችላል። ዳሩ ግን ተመሳሳይ ብድራትን የሚያስገኝ አይሆንም።

የሀይማኖት ጉዞ አድራጊው ሰው መካ ከመድረሱ በፊት ሥርዓታዊ በሆነ የመንጻት ተግባር ውስጥ እንዲያልፍ ይደረጋል፤ ደግሞም ለዚያ ወቅት የሚሆን ልብስ እንዲለብስ ይደረጋል፡፡ ይህም ደግሞ ሁለት መጋጠሚያ-ዐልባ ካፖርቶች የያዘ ነው፡፡ ታላቁ መስጅድን ይጎበኛል፤ ታዋቂውን ጥቁር ድንጋይ ይስማል፤ ከዚያም ከእባኣውን ሰባት ጊዜ ይዞረዋል፡፡ ሦስቱ ዙረቶች በፍጥነት ይደረጋሉ፤ አራቱ ደግሞ በቀስታ ይደረጋሉ፤ ልዩ ጸሎቶች ይደረጋሉ፡፡ ከዚያም የሀይማኖት ጉዞ አድራጊው ሰው አብርሃም ለጸሎት ይቆምበት የነበረውን ሥፍራ ይጎበኛል፤ በሳፋ እና በማራዋ ዐቀበት መካከልም ሰባት ጊዜ ከመሮጡ በፊት ከዘምዘም የውኃ ጉድጓድ ውኃን ይጠጣል፡፡ ተመልሶ በሚመጣበት ጊዜ ከመካ በርካታ ማይል ርቆ በሚገኘው በዐረፋት ምሽቱን ያሳልፋል፤ በኋላም ደግሞ በማይና የመጀመሪያው ምሠሦ፣ መካከለኛ ምሠሦ እና ታላቁ ዲያብሎስ ተብለው በሚጠሩቱ ሦስት የግንበኛ ምሠሦዎች ሰባት አነስ ያሉ ድንጋዮችን ይጥላል፡፡ ሥነ ሥርዓቱ በኢድ አል አድሀ (“የመሥዋዕት ግብዣ”) ይደመደማል፡፡ ይህም የእንስሳ መሥዋዕት በማቅረብ የሚደረግ ነው፡፡ ከዚህ በኋላ ብዙዎቹ የሀይማኖት ተጓዦች በመዲና ያለውን የመሐመድን መቃብር ይጎበኛሉ፡፡

አንድ ሙስሊም ዑምራ ማለትም “አጭር ጉብኝት” በመባል የሚጠራውን ጉብኝት በመካ ማድረግ ይችላል፡፡ የሀይማኖት ጉዞ አድራጊው በመጀመሪያ ወደ ካኣባ ይጓዛል፡፡ በሰሜኑ በር አድርጎ ወደ መስጅድ ይገባል፤ በካእባአ ግድግዳ ላይ ወደ ተገነባው ወደ ጥቁሩ ድንጋይ ይቀርባል፤ ከዚያም ወደ ቀኝ ይታጠፋል፤ ሰባቱን ዙረቶች ማድረግ ይጀምራል፤ በዙረቱም ላይ ሳለ ጸሎትን ያቀርባል፤ በማጠቃለያውም በፀጥታ ወይም ዙረታዊነት ባለው ድግግሞሽ መልኩ ሁለት ራካስን ይጸልያል፡፡ ይህንንም የሚያደርገው አብርሃም ለጸሎት በቆመበት ሥፍራ ነው፤ ምሥጢራዊነት ካለው ከዘምዘም የውኃ ጉድጓድ ውኃ ይጠጣል፡፡ ደግሞም ጥቁሩን ድንጋይ በስንብት መልኩ በድጋሚ ይነካል፡፡ ከዚህ በኋላ ሁለተኛውን አስፈላጊ የሆነ የዑምራ፣ ማለትም በአል ፣ ሳፋን እና በማራዊ መካከል የሚደረገውን የሩጫ ተግባር ለመፈጸም በአል-ሳፋ በር በኩል ከመስጅዱ ይወጣል፡፡ በእነዚህ ሁለት ዐቀበቶች መካከል ሰባት ዙሮችን በሚያደርግበት ሁሉ በሁለቱም ሥፍራዎች በእያንዳንዱ ጊዜ ይጸልያል፡፡ በመጨረሻም ጠጉሩን ይላጫል፡፡የሁለቱም የሀጅ እና ዑምራ ሥነ-ሥርዓቶች ከቅድመ-እስላማዊ ወቅት የተወሰዱ ናቸው፡፡

## VI. ጂሃድ (“ቅዱስ ጦርነት”)

ጂሃድ እስላማዊ ውጊያ ነው፡፡ ሙስሊሞች ዓለምን በሦስት ምድቦች ይከፍላሉ፡- እነዚህም “ዳር አል -ኢስላም” (የእስላም ቤት)፣ “ዳር አል - ሀርብ” (የጦርነት ቤት) እና “ዳር አል -ሱልህ” (የስምምነት ቤት) ተብለው ይጠራሉ፡፡

“የእስልምና ቤት” ሁሉም የእስልምና ሥርዓቶች ሁሉ የተመሠረቱበት እና የሙስሊም ሉዓላዊ አገዛዝ ቀድሞውኑ የሰፈነበትን ሥፍራ ይሸፍናል፡፡ በዚህ ሥፍራ ነዋሪዎቹ በዋነኝነት ሙስሊማኑ ናቸው፡፡ በሙስሊማኑ ቁጥጥር ሥር ሆነው የሚገዙ ሙስሊም ያልሆኑ ሰዎች የሕይወትና የንብረት ዋስትና በመንግሥት ይሰጣቸዋል፤ ዳሩ ግን ሙሉ የሆነ የዜግነት መብት አያገኙም፡፡ እነዚህ ሙስሊም ያልሆኑ ሕዝቦች አህል አል -ኪታብ (አይሁዳውያኑ እና ክርስቲያኑ ፡-የመጽሐፉ ሰዎች ተብለው የተጠሩቱ ሊሆኑ ይገባል) ጣዖት አምላኪያን ሊሆኑ አይገባም፡፡

በንድፈ አሳብ ደረጃ የሙስሊም መንግሥት እስላማዊ ካልሆነው ዓለም ጋር በቋሚነት ጦርነት ላይ ነው፡፡ ነገር ግን “የሙስሊም ቤት” መሆኑን ያቆመ ምድር “የጦርነት ቤት” ከሚሰኘው ጋር ኅብረት እስካልገጠመ ድረስ “የጦርነት ቤት” አይሆንም፡፡ አንድ እስላማዊ አገር “የጦርነት ቤት” በሚሆንበት ጊዜ ሙስሊማኑ ሁሉ ከእርሱ ሊለዩ ይገባል፡፡ በዚህ ረገድ ባልዋን የማታጅብ ሚስት ልትፈታ ይገባታል፡፡

አንዳንድ ቀኖናዊ ሕግን መሠረት ያደረጉ ናቸው የሚባሉ የአሳብ ትምህርት ቤቶች “የመስማማት ቤት” የሚለውን ሦስተኛውን ደረጃ ይቀበላሉ፡፡ በዚህም እስላማዊ ያልሆነ መንግሥት ከእስልምና ጋር በግብር ክፍያ በተገናኘበት መልኩ ብቻ ይኖራል፡፡ ምናልባትም ይህ መሐመድ በትራጃን ካሉ ክርስቲያኑ ጋር ባደረጉት ስምምነት የጀመረ ሳይሆን አይቀርም፡፡ እነዚህ ክርስቲያኖኑ ጀዚያ የሚባል ግብርን በመክፈል ለደኅንነታቸው ዋስትና አግኝተዋል፡፡

በንድፈ-አሳብ ደረጃ ጂሃድ አጠቃላይ የሆነ ተግባር ነው (ምንም እንኳ ይህ ከማኅበረሰቡ መካከል ጥቂት በሆኑ ወኪል አባላት አጥጋቢ በሆነ ሁኔታ የሚከናወን ቢሆንም)፣ መላው ዓለም ሙስሊም እስከሚሆን ድረስ ግዴታ ሆኖ ይኖራል፡፡ ይህ ቀደም ሲል የእምነት ጠባቂ እንደ መሆኑ የከሊፋው ተግባር ነበር፡፡

ይህም ሠራዊቱን በየዓመቱ በአንድነት ለማሰለፍ፣ ደግሞም የትኛውንም ዐይነት ስኬታማ የሚያደርግ ማረጋገጫ ካለ፣ ሙስሊም ካልሆነ አገር ጋር ጦርነት ለመጀመር ነው፡፡ ከሊፋዎቹ ጎረቤት ከሆኑ አገራት ጋር የሚያደርጉዋቸው ስምምነቶች የጊዜ ገደብ ያለባቸው ናቸው፡፡ ዓለማዊ የሆነው የቱርክ ሪፐብሊክ እስኪመሠረት ድረስ ቋሚነት ያለው ስምምነት ማድረግ የማይቻል ነገር ነበር፡፡

እስልምና ለጠላቶች በሚያደርገው አያያዝ ረገድ ኀዘኔታ የሌለው ነው፡-

*ሱረቱ 5÷33*

*በአላህ እና በመልእክተኛው ላይ ጦርነት የሚያደርጉ፣ በምድሪቱ ላይ ምግባረ-ብልሹነትን ዕውን ለማድረግ የሚታገሉ ሰዎች ብቸኛው ክፍያቸው መገደል ወይም መሰቀል ነው፡፡ ወይም በሁለቱም አቅጣጫዎች ያሉ ዕጆቻቸው እና ዕግሮቻቸው የሚቈረጡባቸው መሆኑ ነው፡፡ ወይም ከምድሪቱ እንዲወገዱ ማድረግ ነው፡፡ በዓለም ላይ ያለው የመጨረሻው መዳረሻቸው እንዲህ ያሉቱ ነገሮች ይሆናሉ፤ ደግሞም ከሞት በኋላ ባለው ሕይወት በእነርሱ ላይ የሚመጣው ቅጣት እጅግ ከባድ ይሆናል፡፡*

በተጨማሪም አስቀድሞ ግንዛቤ እንደ ተያዘበት ቍርኣን አይሁዳውያኑ ወይም ክርስቲያኖኑ ጓደኛ እንዳያደርጉ ሙስሊማኑን ይመክራል፡፡ የቱንም ሙስሊም ያልሆነ ሰው ያለማመኑ ነገር በመላው ቍርኣን ውስጥ አጽንኦት የተሰጠበት ነው (ሱረቱ 3÷118፤ 5÷51)፡፡ ለጅሀድ ከተሰጠ ጥሪ ታሪካዊ ዳራ በተቃራኒው እንዲህ ያለው ያለመቀበል ነገር ከሙስሊማኑ ማኅበረሰብ አባል ከሆነ ሰው ጋር መተማመን ያለበት ግንኙነት (መስተጋብር) ማድረግ ለሙስሊማኑ ልክ እንደማይቻል ያደርገዋል፡፡

አንዳንድ ዘመናዊ አስተሳሰብ ያላቸው ሰዎች በሌሎች ምንባባት ቍርኣን ስለ ክርስቲያኖች እና ስለ አይሁድ መልካም ነገር ይናገራል በሚል ይህን አይቀበሉም፡፡ ይህ ዕውነት ነው፡፡ ይሁን እንጂ፣ ቀጥተኛ ሙስሊማኑ የሚባሉቱ ወገኖች (ኦርቶዶክስ ሙስሊማኑ) በስተኋላ ላይ ያሉትን ይበልጥ በጥላቻ የተሞሉ ክፍሎች ያምናሉ (እነዚህም ከላይ ያሉትን እና ሱረቱ 6÷33 ን ይጨምራሉ)፡፡ እነዚህ የኋለኞቹ የቀደሙትን ቍጥሮች ይሽሩዋቸዋል ወይም ይሰርዙዋቸዋል ብለው ያምናሉ፡፡

የአይሁድ ሀይማኖት እና ክርስትና ፈጣሪ በሰጠው በመጨረሻው መገለጥ ተበልጠዋል ሲል እስልምና ያስተምራል። ዕውነተኛውን እምነት በብቸኝነት እንደ ያዙም ሆነ እንደሚጠብቁ ወገኖች ተደርገው ሙስሊማኑ በፈጣሪ ተልእኮ ተሰጥቷቸዋል፤ ይህም በቍርኣን አማካይነት መላው ዓለምን እንዲወስዱ እና እንዲያስገዙ ነው። ጂሀድም የዚህ እምነት አመክንዮአዊ መግለጫ ነው።

**የግል ማስታወሻ**

7

# እስላማዊ አንጻራዊ እምነቶች

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ እስከ አሁን ሱኒ እስልምናን በተመለከተ ተነጋግረናል፤ ምክንያቱም በዓለም ላይ ያሉት አብዛኞቹ ሙስሊማኑ ሱኒዎች ስለሆኑ ነው፡፡ ሱኒ የሚለው ቃል “የሕይወት መንገድ ወይም አካሄድ”፣ በተለይም በሀዲስ አማካይነት የተላለፈ የመሐመድ ልማድ የሚለውን ይወክላል፡፡ ሱኒ ሙስሊማኑ ሱናን እና ታሪካዊ በሆነ መልኩ የተተካኩ ከሊፋዎችን የሚቀበሉ ናቸው፡፡[38] ዳሩ ግን ተመሳሳይ ሥር ያላቸው ቢያንስ ሁለት ትውፊቶች አሉ፡፡ እነርሱም ሺዓ እና ሱፊ ናቸው፡፡

## I. ሺዓ ሙስሊማን

በአንዳንድ በግልጽ በሚታዩ ጉዳዮች ረገድ ሱኒዎች ከሺዓ ይለያሉ፤ ሺዓዎች አምስት የተለያዩ የሀዲት ስብስቦች እንዳሉ ይቀበላሉ፤ የመሐመድ ሴት ልጅ የሆነችውን ፋጡማን እና ልጅዋን ሁሴንን ጨምረው በጥሞናቸው ላይ ትኩረትን ያደርጋሉ፡፡ ይሁንና በቡድኖቹ መካከል ሰፊ መጠን ያለ ስምምነት አለ፡፡ ሁለቱም ወገኖች ለብዙዎቹ አንድ ዐይነት ልማዶች እና ወጎች ዋጋ ይሰጣሉ፡፡ ሁለቱም የእምነታቸው የመጨረሻው መሥራች የሆነውን የመሐመድን ትውስታ ያከብራሉ፡፡

በእነርሱ መካከል ያለ ታሪካዊ ልዩነት ሥረ-መሠረቱን በመሐመድ ሚስቶች መካከል ባለ ቅንዓት እና ውሸት ላይ ያደረገ ነው (ሱረቱ 33÷28-34)፡፡ መሐመድ የአጎቱ ልጅ እና የልጁ ባል ለሆነው ለአሊ ትልቅ ፍቅር ነበረው፤ እርሱም በምላሹ ያለበትን የፍቅር ዕዳ በእስልምና ጉዳይ ላይ በታማኝነት እና በጽናት መልሶ ከፍሎአል፡፡ በአንድ አጋጣሚ መሐመድ “አሊን መመልከት ጥሞና ነው፡፡ እኔ ከተማዪቱ ነኝ፤ አሊ ደግሞ የከተማዪቱ በር ነው” በማለት ተናግሯል፡፡

[38] ይህ ምዕራፍ የተመሰረተው በዶክተር ሪቻርድ ቶማስ ፣ ገጾች118-155፡፡

ከመሐመድ ሞት በኋላ የኃይል ጥቃት ተፈጽሞ ነበር፡፡ ሙስሊማኑ የማያምኑ ሰዎች በሚኖሩባቸው ግዛቶች ላይ ወጥተው ለእስልምና ፈጥኖ መስፋፋት ተዋጉ፡፡ ዳሩ ግን እስልምና በውስጣዊ መከፋፈል ተሰነጣጥቆ ነበር፡፡ ከአራቱ ከሊፋዎች መካከል ሦስቱ ተገድለዋል፡፡ የመሐመድ ተወዳጅ ሚስት አይሻ በመጀመሪያ በኡትማን ላይ ሤራ ጠነሰሰች፤ ከዚያም በአሊ ላይ ይህን አደረገች፡፡ አሊ ጅሃድን እንዲደግፉ ተከታዮቹን በጠራ ጊዜ (በዚያ ምሽት እና ቀን በመሸሸግም ሆነ በግልጽ) እንድትዋጉ አዝዣችኋለሁ፡፡ እነርሱ ሳያጠቁዋችሁ በፊት አጥቁዋቸው የሚል ጥሪ ነበር ያስተላለፈው፡፡ ወረራቸውን በማያምኑቱ ላይ ሳይሆን፣ ነገር ግን እንደ ርሱው ሙስሊሞች በሆኑት ላይ ነበር እንዲያነጣጥሩ ያደረገው)፡፡

የአሊ ጦር ሰፈር ያለው በኢራቅ ኩፋ በሚባለው ሥፍራ ላይ ነበር፡፡ በኋላም ላይ ይህ ሥፍራ የሺዓ ማዕከል ሆነ፡፡ አሊ በ661 ዓ.ም በተገደለ ጊዜ ልጁ ሁሴን የበቀል ጥቃትን አዘጋጀ፡፡ ዕርዳታም እንዲያደርጉለት ለኩፋውያን ከመካ ደብዳቤ ጻፈ፡፡ እነርሱም ልመናውን አንቀበልም አሉ፡፡ እናም አናሳ የሆነ የጦር ኃይል በመያዝ በኤፍራጥስ ላይ በካራባላ በውጊያው ወደቀ፡፡ ያም የተደረገው በ680 ዓ.ም ሙሐራም በተባለው በአሥረኛው ወር ነው፤ ይህም የፆም እና የሺዓውያን ኀዘን የሚደረግበት ቀን ሆኖ ይኖራል፡፡ ምንም እንኳ በጊዜው የነበረው ፖለቲካዊ ጉልህነት ኢምንት ቢሆንም፣ የሁሴን ሞት እርሱ ይህን ላደረገበት ምክንያት ማብላያ መሆኑን አረጋገጠ፡፡

ያ ምክንያት ቢያንስ ሦስት ስሞችን ወደ መሸከሙ መጣ ፤ እነዚህም፡- አህል አል -ቤይት (የመሐመድ ቤተሰቦች ቡድን)፣ ኢማሞች (መሪዎች) እና አሥራ ሁለቱ (ሺዓውያን የሚያከብሩዋቸው አሥራ ሁለቱ ኢማሞች ቊጥርን የሚያመለክት) ናቸው፡፡ በርካታ ቊልፍ የሆኑ ባሕርያት ሺዓውያንን ከሱኒያውያን ይለዩዋቸዋል ፡፡ እነርሱም፡- ግዛት፣ ዘር፣ ምሥጢራዊነት፣ መሢሐዊነት እና አስተምህሮ ናቸው፡፡

## 1. ግዛት

በሱኒ እና በሺዓ መካከል ያለው የመጀመሪያውና ቀዳሚው ውዝግብ ፖለቲካዊ ነው ፡፡ ይህም እስላማዊ አገራትን (ሕዝቦችን) ማን ሊመራ ይገባል? ከሊፋዎች በዘር ሐረግ መሠረትነት ሊሾሙ ይገባል ወይ? የሥልጣን መተካካቱ በመካ ላሉቱ የተወሰነ ሊሆን ይገባል ወይ? ወይስ ይህን ዕድል ለሚፈልግ ለየትኛውም ሀይማኖተኛ ሙስሊም ክፍት ሊሆን ይገባል ወይ?

በሺዓውያን አመለካከት ሁለቱም መንፈሳዊውም ሆነ ጊዜያዊው መሪነት በመብት ደረጃ ለአሊ ቤተ ሰቦች የሚገቡ ናቸው፡፡ መሐመድ ሥልጣኑን ለአሊ አስተላልፎታል፡፡ በዚህም ደግሞ ለአሊ ዝርያዎች ተላልፎአል፡፡ ከሴት ልጃቸው ከፋጡማ የተወለደ በመሆናቸው ምክንያት የአሊ ወንዶች ልጆች የነቢዩ የልጅ ልጆች ናቸው፡፡ በእነርሱ ላይ መለኮታዊ የሆነ ብርሃን ከመሐመድ ተላልፎባቸዋል፤ ደግሞም ወደ አሊ የዘር ሐረግ ወዳሉ ኢማሞች (ሀይማኖታዊ መሪዎች) ተላልፎአል፡፡

አል ግሃዝሊ "መሐመድ÷ አንተ አሊ÷ ለእኔ አሮን ለሙሴ እንደ ሆነው ያለህ ነህ!" ብሎ እንደ ተናገረ ይጠቅሳል፡፡ እንደ ዕውነቱ ከሆነ ይህ ሀዲት ዘር ሐረጋዊ መርኅን የሚያበጅ አይደለም፡፡ - ይሁንና በሺዓውያን አእምሮ ውስጥ ተተክሏል፡፡

ሺዓውን የአሥራ ሁለቱ ወገኖች ተብለዋል፤ ምክንያቱም ዕውነተኛ እና ሥልጣን ባለው የአመራር መሥመር ውስጥ አሊ ከአሥራ ሁለቱ ኢማሞች (የሀይማኖት መሪዎች) የመጀመሪያው ተደርጎ ተቈጥሮአል፡፡ ከሚስቶቹ በአንድዋ የተመረዘው ትልቁ ልጁ ሀሰን ሁለተኛው ኢማም ሆነ፡፡ ከእርሱ ቀጥሎ ያለው ልጅ፣ ማለትም በካራባላ የተከሰተው የርሱ ሞት የመጀመሪያው ሰማዕት የሆነ ቅዱስ የሚባለውን ዕንቅስቃሴ እንዲነሣ ያደረገው ሦስተኛው ኢማም ሆነ፡፡ ከዚያም የሁሴን ልጅ በአሊ (አራተኛው ኢምም)፣ እንዲሁም የሁሴን የልጅ ልጅ በሆነው መሐመድ (አምስተኛው ኢማም) በኩል የኢማምነቱ መስመር ሳይፋለስ መቀጠል ችሎአል፡፡

ነገር ግን ውስብስቦሻዊነት ተከስቷል፡፡ ኢማም የሆነው መሐመድ ታላቁ ዛይድ ከአባቱ በፊት የሞተው የአሊ ሁለተኛ ልጅ ነበር፡፡ ስለዚህም መሐመድ ኢምም በነበረበት ጊዜ የመሪነት መተካካት በታላቅ ልጅ ነው ብለው የሚያምኑ ከሺዓውያን መካከል ያሉ ወገኖች ተከፋፈሉ፤ ደግሞም ባላንጣ የሆኑትን ዛይዳውያንን ወይም ፋይቨርስን (ባለ አምስቱ የሚባሉትን) መሠረቱ፡፡ ከአንድ ትውልድ በኋላም ተመሳሳይ የሆነ መለያየት ተከሰተ፡፡ ስድስተኛው ጃፋር የሚባለው ኢማም (የመሐመድ ተተኪ) ጭምር ልጁ እርሱን ቀድሞት ሞተ፤ ደግሞም ሌላ ባላንጣነት ያለበት መከፋፈል ተከሰተ፤ ደግሞም ለሞተው ለእስማኤል ሰባተኛ የሆነ የኢማምነትን ሥፍራ በመስጠት ራሳቸውን ኢስማኤላውያን ብለው ጠሩ፡፡ በመካከሉ በዋናው የሺዓውያን ዕንቅስቃሴ ውስጥ የነበረው የጃፋር ልጅ ሙሳ (ሰባተኛው ኢማም) ተተካ፡፡ እርሱም በስተኋላ ላይ የሀይማኖት ጉዞ ይደረግበት በሜሽድ ሰማዕት ሆነ፡፡

ከዚያም አል-ጃዋድ፣ አል-ናቂ፣ አል-አስካሪ የተባሉቱ ዘጠነኛው፣ አሥረኛውና አሥራ አንደኛው ኢማሞች በቅደም ተከተል መጡ። እነዚህ ሁሉም ኢማሞች ማለት ይቻላል በሱኒ ባላንጣዎቻቸው ወይ ተመርዘው አሊያም ደግሞ ታርደው ተገድለዋል። ነገር ግን አሥራ ሁለተኛው ኢምም እንዲህ አልተደረገም። የኢማሞች የመሪነት መሥመርን የሚደመድመው ወደ 880 ዓ.ም ከዕይታ የጠፋው መሐመድ አል-መሐዲ መጣ፤ ስለሆነም አል-ሙንታዛር ይጠበቅ የነበረው የሚለው አፈ-ታሪክ ተፈጠረ። ይህ የመጨረሻው ዘመን ሲደመደም ይመጣል፤ ደግሞም የአል-ዘመን (የጊዜ መሪ) እና ሁጃቱላህ (የፈጣሪ የማረጋገጫ ምልክት) የሚባሉ ማዕረጎች ተሰጥተውታል የሚል ነው።

## 2. ዘር

በጥንት ዘመን ብዙዎች ሺዓውያን ዓረቦች ነበሩ። ይሁን እንጂ፣ በቍጥር እያደጉ ይሄዱ የነበሩ ዓረብ ያልሆኑ ሕዝቦች ወደ እስልምና ተመለሱ፤ ደግሞም እነዚህ ባላገር ማዋሊ (ደንበኞች) በመባል ይታወቃሉ። የአምልኮ ማከናወኛ ቋንቋቸው ዓረቢኛ ነበር፤ ነገር ግን እንደ አራማውያን፣ ከለዳውያን እና ፋርሳውያን ያለውን የዘር ማንነታቸውን ለመጠበቅ ችለው ነበር።

ዓራቦች የተወረሩ ምድሮችን ምጣኔ ሀብት (ኤኮኖሚ) መቆጣጠር ችለው ነበር። ደግሞም የፖል ግብርን ጥለው ነበር። ለጥቃት የተጋለጡ ግዛቶችን የሚያስተዳድሩ ገዦች እነርሱን እየጨቆኑ ሳሉ ምግባረ-ብልሹ የሆኑ ግብር ሰብሳቢዎች ተጠቂዎቻቸውን ይበዘብዙዋቸው ነበር። እነዚህን ተላላፊዎች በመቃወም ብዙዎቹ ማዋሊዎች ሺዓዎችን ተቀላቀሉ። ይህም ሺዓዊነት ቀስ በቀስ  የፋርስ እና የደቡባዊ ኢራቅ ብሔራዊ ሀይማኖት የሆነበት አንዱ ምክንያት ነው። ሌላው ምክንያት ትክክለኛ የሆነው የሱኒ እስልምና ለፋርሳውያን ቍጡ የሆነ ባሕርይ የነበረው ተቀባይነት ኢምንት መሆኑ ነው። ፋርሳውያን ሥነ-ጥበባዊ፣ ምናባዊ እና ምሥጢራዊነት ወዳለው ሀይማኖት አዘነበሉ። በሰማዕታት እና በቅዱሳን አጊጦ ይህን ያልረካውን የሙስሊማኑ እምነት እንደ ማግኘት ለመሳብ ሺዓዊነት አገለገለ። ሌላ ሰፊ የሆነ የሺዓ ማኅበረሰብ በሊባኖስ ሊገኝ ይችላል ። እነዚህ በእርግጠኝነት ዓረብ ያልሆኑ ወገኖች ናቸው ማለት ይቻላል ፤ ሺዓውያን እንዲሁ በህንድ እና በፓኪስታንም ጭምር ይገኛሉ።

## 3. ምሥጢራዊነት

የሺዓ እስልምና የተወሰነ “ኢሶታዊ (esoteric) ዕውቀትን” በመያዙ ይመካል፤ ይህም ደግሞ በውስጡ ያሉ ሰዎች ወይም የውስጥ ሰዎች ብቻ የሚካፈሉት ነው። የሺዓ ሙስሊማኑ ፈጣሪ የነቢዩ ሴት ልጅ ለሆነችው እና የአሊ ሚስት ለሆነችው ለፋጡማ ልዩ የሆነ መገለጥን ወደ ውስጥዋ አስርጾአል። የመጨረሻው ኢማም ሁሉም ነገር የሚታየው እንደሆነ እንዲሁም የፍጥረተ ዓለማት ምሥጢራትን የሚቈልፍ እንደ ሆነ አድርገው ያምናሉ። በተጨማሪም የመተርጐም ስጦታ እንዳላቸው ይጠበቃሉ። የኢራኑ አያቶላ ሆሚኒ ለሕዝቡ የአላህን እና የመሐመድን አሳብ ማስታወቅ እንደሚችል ይናገራል። የመተካካት መሥመሩ በተቋረጠበት ሁኔታ የማይወድቅ ዐይነት ኢማም መሆኑ ነው።

የሺዓ እስልምና የቤተ ሰቦቹን ድርሻ ከፍ የሚያደርግ በቊርኣን ምንባብ ውስጥ በአንድ ሐረግ ላይ አክለዋል። ሱረቱ 4፥166 እንዲህ ይላል፡- “አላህ ዕውቀቱን በተመለከተ ለአንተ በገለጠልህ ነገር ምስክር ነው። አሊን በተመለከተ ሺዓ የሚከተለውን ያስከትላል፡- “ኦ፣ መልእክተኛ ሆይ፥ በጌታህ ለአንተ የተገለጠልህን ነገር አስተላልፈው።” ሱረቱ 5፥67 “ስለ አሊ በዚህ ላይ ሺዓ ይህንን ያክላል፡- “እናንተ በምድር ላይ የተነሣችሁ ምርጥ ሕዝቦች ነበራችሁ። መልካም የሆነውን አዝዛችኋል፤ ከንቱ የሆነውን ነገር ከልክላችኋል። ሺህ “ሕዝብ” (ኡማህ) የሚለውን ወደ “ኢማሞች” (አይማህ) ለውጦታል። እነዚህ ለውጦች ምንም መሠረት በሌለበት ሁኔታ አሁንም አሉ።

በአሁኑ ዘመን እስማኤላውያን እና ድሩዜ ከሺዓውያን ወገን መካከል ለምሥጥራዊ አንጻራዊ እምነት ግልጽ የሆኑ ምሳሌ ሆነው ይኖራሉ። እስማኤላውያን ከጥቂት ኖስቲካውያን ጥራዝ-ነጠቅነትን እና ልሂቃን የሆኑትን ከሚጠቅም የማናኪያን ሀይማኖቶን ከኢራናውያን አስተሳሰብ ጋር አደባልቀዋል። ቊጥር ሰባት ምሥጢራዊነት ያለው ጉልህነት እንዳለው ይታሰባል፤ ይህም እስማኤላውያን ሰባት ሕጋዊ ነቢያት እንዳሉ አድርገው ከሚቀበሉበት ሁኔታ ጋር የተያያዘበት ሁኔታ ተፈጥሮአል። እነዚህም (አዳም፣ ኖኅ፣ አብርሃም፣ ኖኅ፣ ኢየሱስ፣ መሐመድ እና መሐመድ አል-ታሚም) ናቸው።

በተጨማሪም ከላይ የዓለም መዋቅር ከላይ ወደ ታች ሰባት ደረጃዎች አሉት የሚለውም አብሮ ተያይዟል። ይህም (ፈጣሪ፣ አጠቃላይ አሳብ፣ አጠቃላይ ነፍስ፣ ቀዳሚው ቃል፣ ህዋ፣ ጊዜ፣

ዓለም) ነው። ተዛማጅነት ያለው አንጻራዊ እምነት የሆነው ኗርማታይንስ የፍቅር ግብዣ ያካሄዳል፤ ደግሞም ይህ ግብዣ በሰባት ደረጃዎች የሚካሄድ ነው።

ድሩዛውያን ካበደው እና እርሱ ራሱ አላህ እንደ ሆነ ከተናገረው የፋቲማይድ ገዥ ከነበረው ከሐኪም መነሣሣታቸውን አገኙ። ድሩዛውያን ማኅበረሰባቸውን በሁለት ይከፍላሉ። አንደኛው የኳል (ምሥጢራትን የያዘ) ፣ ሌላኛው ወገን ደግሞ ሹሃል ("ዕውቀት-የለሽ") ይባላል። ይህ ዐይነተኛ የሆነ የጥቂቶች መደባዊ ክፍል ነው።

## 4. መሢሓውያን

ለክርስቲያኖች ይህ የሺዓ ሀይማኖት እጅግ የሚስብ ገላጭ ባሕርይን የያዘ ነው። የሺዓ መሢሕ አንዳንዴ መሐዲ ይባላል። በኢማማውያኑ በተለይም በመጀመሪያው፣ በሦስተኛው እና በመጨረሻው ኢማም ውስጥ ልብ የሚባል ውሑድ የሆነ አካል ነው። እነዚህ ሦስት ተቀባይነት ያለው መሢሕን ምልክቶች ያንጸባርቃሉ። ሰማዕት የሆነ መሐዲ ከሕይወት ይበልጥ ይልቃል። በአሳብ ይውጠነጠናል፤ በጣም ይወደዳል፤ ለአምልኮ ጥቂት የሚያንስ የአምልኮ ጥሪ ይደረግለታል። በተጨማሪም ለሕዝቡ የታረደ፣ ተጠቂ፣ ስቃይን እና ፈተናን እምነትን እና ትዕግሥትን የተቀበለ ነው። በስተመጨረሻም ወደ ምድር ማላጅ፣ መካከለኛ እንዲሁም አዳኝ ሆኖ እንኳ ይቀመጣል።

ከሺዓ አንጻራዊ እምነቶች አንዳንዶቹ የገዛ ራሳቸውን ኢምም መለኮታዊ ባሕርያትን ተካፋይ እንደ ሆነ አድርገው ይመለከቱታል። የአሥራ ሁለቱ ኢማሞች ዕንግዳ የሆነ መጥፋት (ልክ የእርሱ ጥንቆላዊ አሠራር እንደ ሆነ ተደርጎ ይጠቀሳል።) የኢማሞች ሥፍራ በመቶ ለሚቈጠሩ ዓመታት ምሥጢራዊ የሆነ ቃናን እንዲላበስ አድርገውታል።

አክራሪ ከሆኑ የሺዓ ቡድን አባላት መካከል አንዳንዶቹ አሊ፣ ፋጡማ እና ሁሴን ከአዳም በፊት የተፈጠሩ ናቸው ብሎ ወደ መናገሩ ዘልቀው ሄደዋል። በመለኮት የሚመራው መሢሕ በሚለው ውስጥ የቅድመ -መኖር እና ኳሳይ-መለኮታዊነት አስተሳሰቦች በብዛት ይገኛሉ።

መሢሑን እንደ ተሰዋ አካል እና ሰማዕት የሚወሰድበት አሳብ በብዙ ተያይዞ የሚመለከተው ከሁሴን ጋር ነው ደግሞም አሹራ ተብሎ ለሚጠራው ስሜት ነኪ ለሆነው የሺዓ ተግባር መነሻ ሆኖታል። በሙስሊሞች የመጀመሪያ ወር የሆነው መሐራው በሚጀምርበት ጊዜ፣ ሺዓውያን ለአሥር ቀናት ሙሾ ይወርዳሉ፤ በዚህም የሁሴንን በካራባላ ሰማዕት መሆኑን ያስታውሳሉ።

በበረሃ ያለፉበትን ፈተና፣ ብርታቱ እንዲሁም በጭካኔ የተሞላ የመጨረሻ ጊዜውን ከሞቱ ታሪክ ጋር ተውኔታዊነት ባለው መልኩ እያቀረቡ ያስቡታል፡፡ ብዙዎቹ የዚህ ተካፋዮች ሰውነታቸውን ይቈርጣሉ፤ ደግሞም በደም ተበክለው በመንገዶች ላይ ሰልፍ ያደርጋሉ፡፡ ይህ ለኃጢአት መሥዋዕት የቀረበበት ቀን ነው ነገር ግን ለጠላቶቻቸው ምንም ዐይነት የይቅርታን አሳብ ያስወግዳሉ፡፡

ከሁሴን የሙከራ ድራማ  የምናገኛቸው ነገር የሺዓውያን ስሜት ግሎትን ያሳያል፡፡ ሁሴን እንዲህ ብሎ ጮኸ "እኔ ለፍቅር ቀስት የተጣልሁ ገዳይ ነኝ፡፡ ለወንጀልም ሆነ ለበደል ሳይሆን፣ የነቢዩ የልጅ ልጅ ስለ መሆኔ ይገድሉኛል፡፡ ስላለንበት ሁኔታ የሚያዝን ሰው ይኖር ይሆን? የሚቻል ቢሆን ጨረቃን እንድትወድቅ አደርግ ነበር፡፡ ነገር ግን እኔ ለሕዝቡ ኃጢአት እንደ ቀረበ መሥዋዕት ሆኜ እሞታለሁ፡፡ ይኸውም ከቍጣ ይድኑ ዘንድ ነው፡፡ በትንሣኤ እኔ የእነርሱ ማላጅ ነኝ፡፡"

ስለዚህም ሁሴን እርሱን የሚጠብቀውን ዕድለኛ አጋጣሚ ሳያውቅ፣ የኃጢአት ማስተስረያ ሆኖ ተነሣ፡፡ በሰዎች አእምሮ ውስጥ በእግዚአብሔር እና በሰዎች መካከል ያለ የመካከለኛ መኖር አስፈላጊነት በሆኑ መልኩ ሊሟላ ነው ይህም በካራባላ በተፈጠረ አፈ ታሪክም ይህን በጕልጕታ በተሠራው ታሪክ አማካይነት ነው፡፡

ቡኻሃሪ በአንድ አጋጣሚ መሐመድ ከሰጠው ተስፋ ጋር ያዛምደዋል፡፡ ይህም "ከእኔ አንድ መሐዲ ይነሣል፤ ደግሞም እርሱ ለሰባት ቀናት የሚገዛ ይሆናል፡፡" የሚል ነው፡፡ የኢማሞቹ የመጨረሻው፣ አል-ሙንታዛር ("እንደሚመጣ የሚጠበቀው")፣ በባግዳድ አቅራቢያ በሚገኝ የውኃ ጕድጕድ ገብቶ ጠፍቷል፡፡ ሺዓውያን እርሱ ሕያው እና በመጨረሻው ቀን እንደሚገለጥ ያምናሉ፡፡ ኢብኑ ከሀልዱን በእርሱ ትውልድ ውስጥ ለሀይማኖታቸው ራሳቸውን የሰጡ ባላገሮች በጕድጕዱ አጠገብ በመሰብሰብ በዚያ የሌለውን ኢማም እንዲመጣ እንደሚለምኑ ዘግቧል፡፡ የሺዓ ትውፊት ዋናው የጥንቆላ አሠራር ሲያበቃ መሐዲው እና ኢየሱስ፣ ሁለቱ ንጹሕ ፍጡራን፣ የክርስቶስ ተቃዋሚን ያጠፉታል፤ ደግሞም ዓለም ወደ ዕውነተኛው ሀይማኖት ጥምረት የምትገባ ይሆናል፡፡

## 5. አስተምሮአዊነት

በሺዓዊያን እና በሱኒያውያን መካከል ዐብያተ አስተምሮአዊ ልዩነቶች አሉ፡፡

- ***የኢማም ሚና*** ፡- ለሱኒዎች ኢማም የጉባኤ ጸሎቶች መሪ ነው፡፡ በሀዲስ አነጋገር "ከእግዚአብሔር ቃል ጋር በጣም የተለመደው ሠው፣ ለሕዝቡ ኢማም ሊሆን ይገባል፡፡" በሺዓውያን መካከል፣ ኢማም አድናቆት የሚቸረው አካል ነው፤ ደግሞም በከፊል መለኮት ተደርጐ ይቆጠራል፡፡ ሁሉም ኢማሞች ቀድመው ከነበሩ ብሣናት የተፈጠሩ ናቸው፣ ደግሞም ኃጢአት የለሽ እና ስሕተት-ዐልባ ተደርገው ይጠበቃሉ የሚል የእምነት አንቀጽ አላቸው፡፡ በሱኒዎች ዘንድ አዳዲስ ዕውነቶች ይመጣሉ የሚለው ተቀባይነት የሌለው ነገር ሆኖ ሳለ፣ ሺዓውያን አዳዲስ ዕውነቶች ወኪል በሆኑት ኢማሞች በኩል ሊተላለፉ ይችላሉ የሚለውን ይቀበላሉ (ይህም ልክ በኢያቶላ ሆሚኒ እንደሆነው ማለት ነው)፡፡
- ***የዕውነተኛው ሀይማኖተኞች መሳት*** ፡- ሺዓውያን ሀይማኖታዊ ማስመሰል፣ መስሎ መገኘት (ዕውነተኛ ሀይማኖተኛ ሰው መምሰል) የሚሰኘውን መርኅ ይቀበላሉ፡፡ በዚህም ሺዓውያን "አንድ ሙስሊም በስደት ጊዜ ወይም በአስጨናቂ /ጫና አስዳሪ/ ጊዜ ዐቋሙን ሊቀይር ወይም ከጉዳት ለማምለጥ የሀይማኖት መግለጫውን ሊክድ ይችላል" ይላሉ፡፡
- ***ሙታህ ጋብቻዎች ("መደሰቻ ጋብቻዎች")*** ፡- በአንዳንድ ዝርዝር ጉዳዮች ረገድ የጋብቻ ሕጐች በሱኒ እና በሺዓ ሙስሊማኑ መካከል ምንም ምስክር በሌለበት ጊዜያዊ የጋብቻ ውል ማድረግ ይችላል የሚለውን ሺዓውያን መቀበላቸው ነው፡፡ ሙታ ማለት "መደሰት" ማለት ነው፤ ይህ የግንኙነቱ ብቸኛው ዓላማ ይመስላል፡፡ ምንም እንኳ መሐመድ ሙታ እንደ ፈቀደ የሚነገር ቢሆንም፣ ሱኒዎች እንዲህ ብሎ በሚነገር ነገር ላይ ክርክር ያቀርባሉ፡፡ ምንባቡ አሻሚ ነው፡- "ያገቡ ሴቶች ሁሉ የተከለከሉ ናቸው፤ ለእናንተ ከእነዚያ ምርኮኞች ቀኝ ዕጃችሁ የሚይዛትን ሴት አድኑ፡፡ ይህ ለእናንተ የተሰጠ የአላህ ዐዋጅ ነው፡፡" ከእነዚያ ከተጠቀሱት [ቍ.23] በላይም ለእናንተ የተፈቀዱ ናቸው፤ ስለዚህም ታማኝነት ባለው የጋብቻ ጥምረት ከሀብታችሁ ጋር ትፈልጉዋቸቻቸዋላችሁ፤ ወደ መጥፎ መንገድ የሚመራ አይደለም፡፡ ከእነርሱ ደስታን የምትሹባቸውን ሴቶች አንድን ተግባር እንደ ተወጣ ሰው ድርሻቸውን ስጡዋቸው፡፡ በጋራ ስምምነት ባደረጋችሁበት ነገር ተግባሩን ከፈጸማችሁ በኂላ በእናንተ ላይ ምንም ኃጢአት የለም፡፡

አላህ ሁሉን ዐዋቂ፣ በሁሉም ረገድ ጠቢብ ነው (ሱረቱ 4÷24)፡፡ ሙታህ በሁለቱ ወገኖች የሚወሰን ወቅትን ይፈልጋል፡፡ ወቅቱ ሲያልፍ ግን ግንኙነቱ ከባድ ይሆናል፡፡ እንደዚህ ያለው በስምምነት የሚደረግ ጋብቻ ገጠራማ በሆነው ኢራን የተለመደ ነው፡፡ በውጤትነት የሚከተለው መበዳደልን መገመት ቀላል ነው፡፡ ልምምዱ የሴቶችን ክብር ይቀንሣል፤ በተለይም ዘማውያንን በገሃድ የማውገዝ ልምምድ በግብዝነት የሚተገበር ይሆናል፡፡

## II. ሱፊዝም (የሱፊ እምነት)

ሱፊዝም አንድን የሚያድግ ፍቅር በመያዝ የሚደረስበት መለኮታዊ ዕውቀት ነው፡፡ በሱፊዝም ተከታዮች መረዳት መሠረት የተራበችን ነፍስ በማጥገቡ ረገድ ስለ እግዚአብሔር የሆነ የአእምሮ ዕውቀት የወደቀ ነገር ነው፤ ስለዚህም ደግሞ መደበኛ የሆነን የሀይማኖት መግለጫ ወይም ምክንያታዊ የሆነ ታሪክን ከመፈለግ በላይ ለመጓዝ ምናባዊ መንገድ የሚባል ፍለጋን በዝርዝር አስቀመጠ፡፡

ልክ የሰው ቅንጣት በውቅያኖስ ላይ እንደሚወድቅ አንድ ምናባዊ ሰው የተለያዩ ስያሜዎችን በሚሰጠው በአንድ አካል ግዙፍነት ውስጥ ገብቶ መሟሟትን ይጠብቃል፡፡ ግለሰባዊ ነባራዊነቱን ሁሉን በሚያውቅ አንድነት፣ የግል ሕይወትን አንድ ወደሚያደርግ ፍቅር ገብቶ መቅለጡን በጉጉት ይፈልገዋል፡፡

በርካታ ምናባዊ የሆኑ መንገዶች አሉ፤ እነዚህም በእስልምና ውስጥም ሆነ ከእስልምና ውጭ ያሉ መንገዶች ናቸው፡፡ በሌሎች እምነቶች ውስጥ ካሉ ምናባውያን ጋር በአንድነት በመሆን የሱፊዝም ተከታዮች ወደ አንድነት እና በረከት የሚመራውን መንገድ ለማግኘት ይታገላሉ፡፡

### 1. የሱፊዝም አጀማመር እና ያሳደራቸው ተጽዕኖዎች

ቀጥተኛው የሙስሊም አስተምህሮ ምን ያህል የሱፊ እምነት ላይ ተጽዕኖ አሳድሯል? የሚለውን በእርግጠኝነት ዐናውቅም፡፡ በሱፊዝም ላይ ምን ያህል የክርስትና ተጽዕኖ አድሮበታል? የሚለውንም ጭምር በእርግጠኝነት ዐናውቅም፡፡

ሱፊ የሚለው በስም መልኩ የምናገኘው ቃል ምናልባትም ሱፍ (የልብስ ሱፍ) ከሚለው የዓረቢኛ ቃል የመጣ ሊሆን ይችላል፡፡ ቀደምት ሱፊያውያን በገዳም የሚኖሩ ሰዎች የሚለብሱት

ሻካራ የሆነ ልብስን የሚጠቅስ ነው፡፡ ሌሎች ሥርወ-ቃላትም በአሳብነት ይሰነዘራሉ፤ ዳሩ ግን የዐርኪነታቸው ጉዳይ ኢምንት ነው፡፡

ለአብነት ያህል ሳፋ የሚለው ቃል የሚጠቀስ ሲሆን፣ ፍቺውም ("ንጽሕና") የሚል ነው፡፡ ሱፋህ (በመዲና በመጀመሪያው መስጅድ አምልኮ ይፈጽሙ የነበሩ ሰዎች የሚቀመጡበትን መደዳ) ለመግለጽ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ ወይም የግሪኩ ሶፎስ (ጥበብ) በዚህ ረገድ ተጠቃሽ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡

በሌላ አግባብ ስናየው ጥንታዊው "በእስልምና ውስጥ ምንም የምንኩስና ዕንቅስቃሴ የለም" ከሚለው የሙስሊማኑ ትውፊት ባሻገር ሱፊዝም የክርስትናን የምንኩስና ዕንቅስቃሴ አርአያ አድርጎ የወሰደ ይመስላል፡፡ ሱፊያውያን በንስሐ ጸሎቶች ድግግሞሻዊ ንግግርን ወሰዱ፡፡ ከምንኩስና ድግግሞሻዊ ተግባር ጋር የተቀራረበ አንድን ነገር ለራሳቸው በሚሆን መልኩ አጎለበቱ፡፡ የድንግልናም ሕይወትን ደገፉ፡፡

አል-ባስሪ "አምላክ ለአገልጋዩ መልካም ነገርን የሚፈልግ ከሆነ፣ እርሱን በቤተሰብ እና በልጆች የተዋከበ እንዲሆን አይፈቅድለትም" ብሎ ጽፏል፡፡ ነገር ግን ሱፊዝም (የሱፊ እምነት) ብዙ መልኮችን ወስዷል፤ ደግሞም መቆየት ወይም በውጭ ካለው ማኅበረሰብ ተነጥሎ በመሄድ ላይ አጽንኦትን ከሚያደርገው ከዛሂድ ("መለየት") የተለዩ መንገዶችን በመፈለግ ሊገኝ ይችላል፡፡

አንዳንድ የሱፊ ተከታዮች የፋቂር (የእኔ-ብጤ) ድህነትን ይከተላሉ፡፡ ይህንንም ደግሞ ምንም ነገርን በባለቤትነት መያዝ ወይም በምንም ነገር መያዝ ባለመፈለግ የሚያደርጉት ነው፡፡ ሌሎች እነዚህን ሁለቱንም መንገዶች ይይዛሉ፤ ዳሩ ግን የሱፊ እምነት ፍሬ-ጉዳይ ከምድራዊ ደስታ ከመራቅና ከድህነት በተለየ በአንድ ነገር ላይ የተደገፈ እንደ ሆነ ደግሞም ንስሐ መግባታቸው እና ራሳቸውን ለእግዚአብሔር መስጠታቸውን ለማሳየት እነዚህ ሁለት ነገሮች መነሻዎች ብቻ እንደ ሆኑ አበክረው ያምናሉ፡፡

## 2. የሱፊ እምነት ፈር-ቀዳጅ

እስከ 700 ዓ.ም ባለው ቀደምት ጊዜ በሙስሊማኑ ታሪክ ውስጥ ሻካራ የሆነ የሱፍ ልብስ የሚለብሱ ሀይማኖተኛ የሆኑ ባላገሮች እንደ ነበሩ እናገኛለን፡፡ ከአንድ ክፍለ ዘመን በኋላ በኢራቅ ሱፊያ ተብለው የሚጠሩ የመነኮሱ ቡድኖች እንደ ነበሩ እንሰማለን፡፡ ወደ 900 ዓ.ም

ገደማ ታላቁ የሱፊ ተከታይ አል-ጁናይድን ጨምሮ የምናባውያን መረዳጃ ማኅበራት እዚህም እዚያም ሰፍረው ነበር፡፡

የሱፊ እምነት በጊዜ ውስጥ ተቀየረ፤ በቀደመው የምንኩስና ፅንቅስቃሴ ገንኖ በነበረበት ጎዳናው፣ የሱፊ እምነት ተከታዮች አሳባቸው እና ፍቅራቸውን ሁሉ ከሞት በኋላ ባለ ተስፋ ላይ አድርገው ነበር፡፡ ወደ ፓንተይስቲክ (ሁሉንም ነገር አምላክ አድረጎ የሚያይ እምነት) ምናባውያን የተሻገረው የኋለኛው ጎዳና ከእግዚአብሔር ጋር በሚደረግ አሁናዊ አንድነት የሚገኝን ፍንደቃ ለማግኘት ይጥራሉ፡፡ በዚያም በመካከል የሽግግር ወቅት እንዳለ ሆኖ ይታያል፡፡

በዚያም በመካከል የሽግግር ወቅት እንዳለ ሆኖ ይታያል፡፡ ከጥንታውያን የአንድ አምላክ አምላኪያን አንዱ ዳራኒ፦ "ማሰላሰል የእኔነት መቀበር ፍሬ ነው ብሏል፡፡ ፓንተይስት የሆነው (ሁሉም ነገር አምላክ ነው ብሎ የሚያምነው) አል-ሩሚ በስተኋላ ላይ "አካላችሁ ይሞታል፤ ሥጋችሁ በስቃይ ይበላል … የእግዚአብሔር አንድነትም ዳግመኛ የእናንተ ሆኖ ታገኙታላችሁ" ሲል ይመክራል፡፡ እነዚህ ሁለት የሱፊ እምነት ተከታይ የሆኑ ምናባውያን ቢያንስ በአንድ ነጥብ ላይ ስምምነትን ያሳያሉ፡፡

ሰፋ ባለ መልኩ የሱፊ እምነት በእስልምና ውስጥ ያለ ትክክለኝነትን የሚቃወም አጽፌታዊ ምላሽ ነው፡፡ ቀጥተኛ የሚባለው እስልምና ውስጥ ያሉ የነገረ-መለኮት ዐዋቂዎች የእምነት መዋቅራቸውን ሲያጎለብቱ ስለ እግዚአብሔር ያላቸው ፅንሰ-አሳብ ይብልጥ ከምሥጢራዊነት እና የግል አምላክ መሆን የፀዳ አድርገው ነው፡፡ በእርግጥም ቀጥተኛ የሚባለው እስልምና አላህን በተመለከተ ሲናገር የግለኝነት ጉዳይ ሥፍራ ያጣል፡፡ በአንጻሩ ኋላ ቀር የሚባለው የሱፊ እምነት ከጌታው ጋር የሞቀን እና የተቀራረበ ግንኙነትን በብርቱ የሚፈልግ ነው፡፡ ደግሞም ለዚህ ተስፋ የሚሆን በቊርዓናዊ ምንባቦች ውስጥ ጥቂት ፍትሐዊነት ያለው ነገርን ለማግኘት ችሎ ነበር፡፡ ለምሳሌ፦ "ያመኑቱ ሰዎች አላህን ይበልጥ በጽናት ይወድዱታል" (ሱረቱ 2÷165)፤ ደግሞም "አላህ የሚወድዳቸውን እና እነርሱም እርሱን የሚወድዱትን ሰዎች፣ ለአማኞች ትሑት የሆኑትን፣ በማያምኑ ሰዎች ላይ ፊታቸውን የሚመልሱትን፣ በአላህ መንገድ ላይ የሚታገሉትን ሰዎች ያመጣቸዋል" (ሱረቱ 5÷54) የሚሉትን ምንባቦች አግኝተዋል፡፡

በተጨማሪም በሁለተኛው እና በሦስተኛው የሙስሊማኑ የአገዛዝ ክፍለ ዘመን ዓረቦች የስኬታቸውን ትሩፋቶች እያጨዱ ነበር፡፡ ከሊፋዎቹ በድሎት፣ በተትረፈረፈ ሁኔታ እና ክብርን በሚሹበት መልኩ ይኖሩ ነበር፤ ደግሞም ለጽሞናዊ ማሰላሰል የነበራቸው ጊዜ አናሳ ነበር፡፡ በዚህ መሠረትም በምሥራቁ የሙስሊም ክፍል በብዙ ቦታዎች የተቃውሞ ምላሽ ተቀስቅሶ ነበር፡፡ ይህም ደግሞ ሰዎችን እያደገና እያሸነፈ ከምግባረ-ብልሹነት ወደ ተቀደሰ ኑሮ ይመልሳቸው ነበር፡፡

## 3. ከፍርሃት ወደ ፍቅር

ሰዎች ለምን ለአንድ ወይም ከሁለት ምክንያቶች በአንዱ ነገሮችን ያጣጥላሉ? እግዚአብሔርን በመፍራት ይመላለሳሉ ወይም በእርሱ ፍቅር የተሞሉ ይሆናሉ፡፡ በሱፊ እምነት ውስጥ ካሉ ሰዎች መካከል ብዙዎቹ ራሳቸውን ለሀይማኖት የሰጡ ሰዎች በእግዚአብሔር ፍቀር የተሞሉ ነበሩ፡፡

የባስራው ራቢያህ አል-አዳዋያ (d. 801AD) ተሞክሮዎች ተጠቃሽ ናቸው፡፡ የዚህች ሴት መቃብር በኢየሩሳሌም ውስጥ ሲሆን፣ በስተኋላ ላይ በሌሎች የሀይማኖት ጉዞ አድራጊዎች ተከታታይነት ባለው መልኩ ይጎበኛል፡፡ ርስዋ ለእግዚአብሔር ባላት የማያባራ እና ሁልጊዜም በሚገኝ ፍቅር የምትታወቅ ከሱፊ እምነት ተከታዮች መካከል እጅግ ታዋቂዋ ሴት ነበረች፡፡

ወደ እስልምና ከመለወጥዋ በፊት ታዋቂ ሙዚቀኛ ነበረች፡፡ የፍቅር ዘፈኖችን ትዘፍን ነበር፡፡ ዳሩ ግን ያ ፍቅር ከዓለም ተመልሶ በራሱ በእግዚአብሔር ፍቅር ላይ የሚያተኩር ሆነ፡፡ ንጹሕም ተደረገና ወደ ሰማይ አቅጣጫ ከፍ አለ፡፡ እርስዋ ስትጸልይ፡- “እግዚአብሔር ሆይ÷ እኔ ገሃነምን በመፍራት የማመልክህ ከሆነ፣ በገሃነም አቃጥለኝ፤ መንግሥተ ሰማይን ተስፋ አድርጌ የማመልክህ ከሆነ፣ ከመንግሥተ ሰማይ ውጭ አድርገኝ፡፡ ነገር ግን አንተኑ ራስህን ፈልጌ የማመልክህ ከሆነ፣ ዘላለማዊ የሆነውን ውበትህን ከእኔ አትውሰድብኝ” ትል ነበር፡፡

አንድ ሰው “ዲያብሎስን ትጠዪዋለሽ?” ሲል ጠየቃት፡፡ እርስዋም እንዲህ ስትል መለሰች፡፡ “ለእግዚአብሔር ያለኝ ፍቅር ዲያብሎስን የምጠላበትን ጊዜ አይተዉልኝም፡፡” በተጨማሪም “ነቢዩ መሐመድን በሕልም ዐየኋቸው፤ ደግሞም “ትወድጂኛለሽ?” ብለው ጠየቁኝ፡፡ እኔም “ኦ፣ የእግዚአብሔር መልእክተኛ ሆይ÷ እርስዎን የማይወድድ ማን አለ! ነገር ግን

የእግዚአብሔር ፍቅር በእኔ ላይ እጅግ ከመጥናቱ የተነሣ ለየትኛውም ነገር የሚሆን ፍቅርም ሆነ ጥላቻ የሚሆን ሥፍራ በልቤ ውስጥ የለም" በማለት እንደ መለሰችላቸው ትናገራለች።

## 4. *ታሪቃ ("ጎዳና") እና ደረጃዎች*

*ታሪቃ የሱፊ እምነትን የሚሻ ሰው የሚከተለው ጎዳና ነው። የሱፊ እምነት አቀንቃኞች በአንድነት ሰብሰብ ያለ ድርጅት መኖር እንዳለበት ሲሰማቸው ለዚህ አርአያ የሚሆን ነገርን ለማግኘት ፊታቸውን ወደ ምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት መለሱ። በማኅደር ቡድን (ሴል ግሩፕ) በአንድነት ይሰባሰባሉ። ይህንንም የሚያደርጉ ቍርኣንን ለመቅራት እና በሀይማኖታዊ ጉዳዮች ላይ ውይይት ለማካሄድ ነው።*

የቅዳሴ መልክ ያለውን ነገር አጎለበቱ፤ ደግሞም ደህክር (እግዚአብሔርን ማሳሰቢያ) የጉባኤያቸው መደበኛነት ያለው ገላጭ ባሕርይ ሆነ። ተጠቃሽ የሆነው የንስሐ ጸሎት እንዲህ ያለው ነው። "ሁሉን ከሚችል አምላክ ከእግዚአብሔር ይቅርታን እጠይቃለሁ። ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን። እግዚአብሔር መሪያችንን መሐመድን፣ ቤተ ሰዎቹን እና ወዳጆቹን ይባርክ!" እያንዳንዱ ሐረግ መቶ ጊዜ በመደጋገም ይነገራል።

ከድህክር ጋር የሱፊ እምነት ተከታዮች ሳማን አበጁ፤ ይህም ፍንደቃን ለማምጣት የታለመ ሀይማኖታዊ ጉባኤ ሲሆን፣ በመደነስ ወይም ልብስን በማወዛወዝ ተለይቶ ይታወቃል። የቀጥተኛ ሙስሊም ተከታዮች ድህክር እና ሳማ በመስጅዶች ውስጥ የሚካሄደውን የጋራ አምልኮ ሊተኩት ይችላሉ ብለው በመፍራት እነዚህን ነገሮች አይለማመዱዋቸውም።

ታሪክ ራሱ በርካታ ደረጃዎች አሉት። አል-ግሃዚ ራሱ አንድ ሰው ወደ ግቡ ለመድረስ ሰባት ባሕሮችን ማለፍ አለበት ብሎ ይናገራል። እነዚህም፦ ንስሐ፣ መራቅ (አልፎ አልፎ ከደስታ ውጭ መኖር)፣ በይፋ መተው (ሁሉንም ምግባረ-ብልሹ የሆኑ ተግባራት መተዉ)፣ ረሃብ (በፈቃደኝነት የሚቀበሉት በእግዚአብሔር ላይ የሚደረግ መደገፍን ማበረታታት)፣ ትዕግሥት፣ በእግዚአብሔር መታመን እና ዕርካታ ናቸው።

አንድ ሼህ ("መሪ") መደበኛነት ባለው መልኩ አንድን በእምነት ጎዳና ላይ መሄድ የሚፈልግ ሰው በእነዚህ አማካይነት ይመራዋል። አንድ ሰው ሁሉንም ደረጃዎች እስኪያጠናቅቅ እና ሁሉንም ተገቢዎቹን ስሜቶች እስኪለማመድ ድረስ የሱፊ እምነት ጎዳና አያልቅም። ከዚያም እርሱ ከፍ ወዳለ ንቃተ-ሕሊና ይመጣል። በዚህም ፈላጊ የሆነው ሰው "ዐዋቂ" ወደሚሆንበት

ነው የሚመጣው፡፡ "ዐዋቂው" እና "የሚታወቀው ነገርም" አንድ ናቸው፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር ወደሚሆነው አንድ መሆን የሚደረስበት የመጨረሻው ግብ ለአንዳንዶች ፍንደቃ ሲሆን፣ ለሌሎች ደግሞ ሞት ነው፡፡

ህንዳውያን የሱፊ እምነት ተከታዮች ፋና ("ሞትን") ብለው የሚጠሩትን ፅንሰ-አሳብ አነሡ፡፡ ይህንንም ኒርቫና ከሚሰኘው የቡድሃውያን ዕሳቤ ነው የወሰዱት፡፡ ነገር ግን ፋና በእግዚአብሔር ዘንድ በባቃ ("በመኖር") ብድራትን የሚያስገኝ ነው፡፡ ይህም በአግዳዳዊው ታላቁ የሱፊ እምነት ተከታይ ጁንያድ "እግዚአብሔር ለእኔነት እንድትሞቱ እና በእርሱ ውስጥ እንድትኖሩ ያደርጋችኋል" ብሎ እንደ ገለጸው ነው፡፡ ለአንድ የሱፊ እምነት ተከታይ እኔነት ከሁሉም ነገር በላይ ሊጨቆን ወይም ሊካድ የሚገባው የመጨረሻው ጠላት ነው፡፡

## 5. በሱፊ እምነት ላይ የሚሰነዘር ትችት

እንደ ሁሉም ምናባዊ እምነቶች ሁሉ የሱፊ እምነትንም በቀላሉ መተቸት ይቻላል፡፡ ከዕለታዊ የኑሮ ውስብስቦሽ ፊቱን በመመለስ መሸሽን ሥራዬ ብሎ የተያያዘ እምነት ነው፡፡ ለቤተ ሰብ እና ለማኅበራዊ ሊኖር የሚገባን ኀላፊነት ቸል ይላል፡፡ ግለሳባዊ ለሆኑ ተሞክሮዎች ተገቢነት የሌለው አጽንኦት ይሰጣል፡፡ በተጨማሪም በተለይም በመካከለኛው ዘመን ቅርጹ ማስመሰል እና ማታለል ይፈጸምበታል፡፡

ሆኖም "በወርቃማ ዘመኑ" የሱፊ እምነት እነዚያን ከመረዳት በላይ የሆነ ሰለም፣ ሊገለጽ የማይችል ደስታ፣ እንዲሁም ከሞት የሚጠነክረውን ፍቅር ፈላጊ ብዙዎች ቅን ደቀ-መዛሙርት ስቧቸዋል፡፡ ደግሞም ከመለኮት ጋር ባለ አንድነት እነዚህን ነገሮች ለማግኘት ተስፋ ያደርጋል፡፡ ይህንን በእስልምና ውስጥ አላገኘውም፡፡ እናም ራሱን በሆነ መልኩ በክህደት ቅጣት ሥር ወድቆ እንዳያገኘው እስልምናን ማጣጣልን ይፈራል፡፡ ነገር ግን ስለ ክርስቶስ አምላክነት፣ ስለ ማስታረቅ ሥራው እና ስለ ሥላሴ በሚናገረው በክርስቲያናዊ አስተምህሮም ውስጥ ይህንን አላገኘውም፡፡ በእስልምናም ሆነ በክርስትና ውስጥ የፈለገውን ነገር ባለማግኘት እርሱ ወደ ሱፊ እምነት ተከታይነት ፊቱን መልሷል፡፡

**የግል ማስታወሻ**

# 8

# የክርስቶስ ሉዐላዊነት በእስልምና

ቁርኣን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሁሉም ነብያት፣ ሐዋሪያት እና መሐመድ ጭምር የበላይ አድርጎ ያስቀምጠዋል። በቁርኣን ለኢየሱስ የተሰጡት ስያሜዎች፣ ትምህርቶች ፣ባህሪያትና ምግባራት ከሌሎች እንዲልቅ አድረገውታል። አንድ ሙስሊም ስለ ክርስቶስ ያለው ግንዛቤ ዘጠና ሶስት ያህል ጊዜ ስሙ ከተጠቀሰበት ክፍሎች ጋር የተገናኘ ነው።

ሱፊዎች ኢየሱስ  ታላቅ እና ከነብያት ሁሉ የበላይ አድርገው ይቀበላሉ። ጃዋድ ኑርባካሽ “ ኢየሱስ በሱፊዎች አይን” በሚለው መጽሐፉ ፣ በእርሱ ደረጃ ጸጋን የተመላ ምንም ቀዳሚ ነብይ እንደሌለ ያትታል። እርሱ ፍጹም ሰው ፣ የእውነተኛ መምህር አይነተኛ ምሳሌ ነው ። ለሱፊዎች ኢየሱስ  የንጽህና ጥግ ተምሳሌት ተደርጎ ይወሳደል፤ በዚህም እውነተኞቹ ሱፊዎች እንደርሱ ንጹህ ለመሆን በእጅጉ ይጓጓሉ።  ኣታር የተባለው  ሱፊ  “ ጌታ ሆይ እንደ ኢየሱስ ሕያው ንጹህ እሆን ዘንድ፣ ከዚህ ዕድፋም ነፍስ አንጻኝ” ብሎ ጸሎት አድርጓል።

በሱፊዎች አፈ ታሪክ /ልማድ/ ደቀመዛሙርቱ ኢየሱስን ያናገሩበት ታሪክ አለ፦ “ መምህር ፣ እያንዳንዳችን የገዛ ራሳችን ቤት አለን፤ አንተ ግን ምንም የለህም።”  ኢየሱስ ምንም እንኳ ግድ ቢሉትም ፣ ቤት እንዲሰሩለት አልፈቀደም። በስተመጨረሻ ጥያቄቸውን በመቀበል“ ቦታውን እኔ እመርጣለሁ፣ እናንተ ደግሞ ቤቱን ትሰራላችሁ ” አላቸው።

አንድ ቀንም ከርሱ ጋር ድልድይን በማቋረጥ ላይ ሳለ “ የመረጥኩት ቦታ ይሄ ነው በማለት ድልድዩን አሳያቸው ።”  ዳመዛሙርቱ ግን “ መምህር ፣ ይህ ቦታ ቤት ለመስራት አያመችም፣ ሰዎችን ለማሻገር እንጂ” ብለው በጩኸት ተናገሩ። ኢየሱስም “ ሁላችንም ከዚህኛው ህይወት ወደሚመጣው ህይወት ተሻጋሪዎች ነን ” ብሎ መለሰ።

መሐመድ እራሱ ኢየሱስን ለማየት እጅግ ከመጓጓቱ የተነሳ  “ ዕድሜዬ ቢረዝም ኖሮ የማሪያም ልጅ ፣  ኢየሱስን ለማየት ተስፋ አደርግ ነበር፣ ነገር ግን ሞት ቢቀድመኝ፣ ኢየሱስን የሚያገኘው ሰው አክበሮቴን ይግለጽልኝ ” [39]ይል ነበር።  ማንም ነብይ ይህን የመሰለ አክብሮት

[39] ኑርባባሽ ዣዋድ ፣ ኢየሱስ በሱፊዎች ፊት ፣ ካኒቃህ ከኻኒኸዋአ-ንማቱላይ ማተሚያ፣ ሎንደን ፣1983፣ ገጽ 25፣53።

በልቡ አላሳደረም፡፡ ነብያት ከተለያዩ እናቶች የተወለዱ ቢሆንም ፣ ኃይማኖታቸው ግን አንድ ነው ፡፡ አክሎም " ከሁሉም ሰው ይልቅ የኢየሱስ ወንድም መሆን የተገባኝ እኔ ነኝ፤ በእኔና በእርሱ መካካል ማንም ነብይ የለምና ነው" [40] ብሎ ይናገራል፡፡ ቁርኣን ለኢየሱስ መጠሪያ የሰጠው ቦታ ኢየሱስ ክርስቶስ በእስልምና ያለውን ቅድመ-ዝና ማረጋገጫ ነው፡፡

## I. ኢየሱስ ክርስቶስ የፈጣሪ ቃል ነው

በሱረቱ 3፥45 መልአኩ ለመርየም " አላህ ከርሱ በኾነው ቃል ስሙ አል መሲህ ዒሳ የመርየም ልጅ በዚህ ዓለምና በመጨረሻው ዓለም የተከበረ ከባለሟሎችም በኾነ (ልጅ) ያበስርሻል" ይላል፡፡ በተጨማሪም "የመርየም ልጅ አል-መሲሕ ዒሳ የአላህ መልዕክተኛ ወደ መርየም የመጣላት "የኹን" ቃሉም ከእርሱ የመንፈስም ብቻ ነው " የሚለውን በሱረቱ 4፥171 እናገኛለን፡፡ በቁርኣን ማንም ሰው " የአላህ ቃል" የሚል መጠሪያ አልተሰጠውም ፣ ይህ መጠሪያ ሐዋሪያ፣ ነብይ ወይም ሰባኪ ከሚለው ስያሜ በእጅጉ ይልቃል፡፡

በአዲስ ኪዳን "ቃል" የሚለው ሀረግ ቢያንስ ሦስት መገለጫዎች አሉት ፡-

- ***ኢየሱስ ዘላለማዊ ነው*** ፡- እግዚአብሔር ቃል ወይም ንግግር አልባ ሆኖ አያውቅም ፤ ምክንያቱም ምንግዜም ቢሆን የተግባቦት አምላክ ነውና ! ስለሆነም ኢየሱስ የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ቃል ነው ፡፡ " በመጀመሪያው ቃል ነበረ፣ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፡፡ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ " / ዮሐንስ 1፥1-2/ ፡፡
- ***ኢየሱስ ሙሉዕ የእግዚአብሔር ስልጣን አለው*** ፡- ቃል የተናጋሪውን ሥልጣን ተሸካሚ ነው፤ ስለዚህም ኢየሱስ የእግዚአብሔር ሙሉዕ ስልጣን አለው! የእግዚአብሔር ቃል ትዕዛዛቶቹን በሙሉ የያዘ ነው ፤ በዚህም ኢየሱስ ድንቆችን ይፈጽም ነበር ! እንዲህም ብሉ ተናገራቸው ፡- "ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ" (ማቴዎስ 28፥18)፡፡
- ***ኢየሱስ እግዚአብሔርን ይገልጣል*** ፡- የሰው ቃል ባህሪውን የሚገልጽ፣ ማንነቱንም የሚናገር ነው ፤ቃሉ ራሱን ይገልጣል፡፡ የእግዚአብሔር ቃል እግዘአብሔርን ይገልጥልናል፡፡ "እኔን ያየ አብን አይቶአል" (ዮሐንስ 14፥9)፤ "መቼም ቢሆን

---

[40] ካነዙል ኡማን ፣ ሀዲስ፣ 1033፡

እግዚአብሔርን ያየው አንድ ስንኳ የለም፣ በአባቱ እቅፍ ያለ አንድ ልጅ እርሱ ተረከው" (ዮሐንስ 1፥18)።

አል ራዚ ፣ አል ጃሌላን እና ሌሎቹ ኢየሱስ " የአላህ ቃል " የሆነው በአላህ ይኹን በሚል የትዕዛዝ ቃል ነው ይላሉ። ሆኖም ይህ እውነት ሊሆን አይችልም። የመጀመሪያው ይህ ቃል ለአዳም ጥቅም ላይ አልዋለም፣ ምንም እንኳ በእግዚአብሔር የተፈጠረ ቢኾንም ። ሁለተኛው ቁርኣን "አላህ ከርሱ በኾነው ቃል ስሙ አል -መሲህ ዒሳ " በማለት በራሱ ስብዕና ያለው እንደሆነ ይገልጣል። " ቃሉ" በራሱ አንድ አካል ወይም ሰብዕና ነው፤ አረብኛው ቃል ኢስሙሁ ("ስሙ") ተባዕታይ ጾታን ሲያመለክት፣ ካሊማ ("ቃል") ደግሞ አንስታይ ጾታን ይፈልጻል። ሦስተኛው አንድ ነገር ከተፈጠረ በኃላ የተፈጠረበትን መንገድ ስም መስጠት ምንም ፋዳ የለውም። ለምሳሌ ፦ ይህ መጽሐፍ በቃል መጻፊያ ሂደት (መሳሪያ ) ነው የተጻፈው፣ ነገር ግን መጽሐፍ ተብሎ ነው የሚጠራው እንጂ ፣ ቃል መጻፊያ መሳሪያ ተብሎ አይጠራም። ሙስሊማኑ እንደሚሉት ኢየሱስ የተፈጠረው በአላህ ቃል ትዕዛዛዝ ነው ቢባል ስንኳ ፣ ኢየሱስ ካሊማ ("ቃል ተብሎ") መጠራት የለበትም ፤ ምክንያቱም እርሱ በራሱ ትዕዛዝ ሳይኾን የትዕዛዙ ውጤት ነውና።

## II. ኢየሱስ ፈጣሪ ነው

ቁርኣን "የመርየም ልጅ አል-መሲሕ ዒሳ..... ከእርሱ የመንፈስም ብቻ ነው " (ሱረቱ 4፥171) ይላል። በቁርኣን የሚለውን በሱረቱ 4፥171 እናገኛለን። በቁርአን "ከእርሱ የመንፈስም ብቻ ነው" የሚለው መጠሪያ ከኢየሱስ በስተቀር ሌላ ለማንም አልተሰጠም ። "ከእርሱ የመንፈስም ብቻ "እንደመሆኑ ኢየሱስ እንደፈጣሪ ሁሉ የፈጣሪን ሚናን ጭምር ይካፈላል። ቁርኣን ለእስራኤል ልጆች ኢየሱስ የተናገረውን " እኔ ለናንተ ከጭቃ እንደ ወፍ ቅርጽ እፈጥራለሁ(አኽለክ) ። በርሱም እተነፍስበታለሁ። በአላህም ፈቃድ ወፍ ይኾናል" (ሱረቱ 3፥49) ይላል፤ አላህም "ከጭቃም የወፍ ቅርጽ ብጤ በፍቃዴም በምትሠራ (ታኽለክ) " በማለት ሲያረጋግጥለት እንመለከታለን ( ሱረቱ 5፥110)።

አኽለክ እኔ ቀርጻለሁ ወይም እሰራለሁ ወይም ፈጥራለሁ የሚለውን ትርጓሜ ይይዛል። አፈጣሪ ሁሉም ወንዶችና ሴቶች የእርሱ የሆኑቱን ባህሪያት ማለትም ሩኅሩኅነት፣ ፍትህ፣ ምህረትና ለጋስነትን አካፋሏል። የእርሱ ለሆኑቱ ነብያት ልዕለ- ተፈጥሮ ተአምራቶችን እንዲያደርጉ ፣ የወደፊቱን እንዲተነብዩ አብቅቶአቸዋል። የመፍጠርን ሥራ አስመልክቶ ግን

የራሱ የሆነ ባህሪይ ብቻ ነው። ኢየሱስ ከጭቃ የወፍ ቅርጽ ቢጤ መፍጠሩ፣ ፈጣሪ አዳምን ከአፈር ከፈጠረበት በእጅጉ አንድ ነው፤ ይኸውም ኢየሱስ እንደ ፈጣሪ ሁሉ ከምንም ነገር መፍጠር የሚችል ፈጣሪ መሆኑን ያስረግጣል።

ቁርኣን በአንጻረሩ ጣዖታትን ስለሚያመልኩ ሰዎች ሲናገር እንዲህ ይላል፡-

*ሱረቱ 22፥73*

*እናንተ ሰዎች ሆይ! አስደናቂ ምሳሌ ተገለጸችሁ ። ለእርሱም አድምጡት። እነዚያ ከአላህ ሌላ የምትግገዟቸው (ጣዖታት) ዝንብን ፈጽሞ አይፈጥሩም ። እንርሱን (ለመፍጠር) ቢሰበሰቡም እንኳን (አይችሉም)። አንዳችንም ነገር ዝንቡ ቢነጥቃቸው ከእርሱ አያስጥሉም። ፈላጊውም ተፈላጊውም ደከሙ።*

በአዲስ ኪዳን ኢየሱስ ታዕማራትን በእግዚአብሔር ፍቃድ አልፈጠረም። ሙሴ በትሪቱን ወደ እባብ የቀየረው በእግዚአብሔር ትዕዛዝ ነበር። ኢየሱስ አላዘርን ከመቀባር ሲያስነሳውም (ዮሐንስ 11) ሆነ አይነሰውሩን ሲያበራ (ዮሐንስ 9) እግዚአብሔር አላዘዘውም።

## III. ኢየሱስ በማህጸን የታወቀ ነበር

ኢየሱስ በማህጸን ሳለ ብቸኛው ታዋቂ ነብይ እንደኾነ ይታመናል። ቁርኣን ስለ መጥምቁ ዮሐንስ ታሪክ በሚነግረን ክፍል ላይ፣ ጅብሪል (መላዕኩ) ለዘካሪያሰ ልጁ " ከአላህ በኾነ ቃል የሚያረጋግጥ " (ሱረቱ 3፥39)። አል -ራዚ "ከአላህ በኾነ ቃል' ኢየሱስ ነው ፤ ሰላም በርሱ ላይ ይሁን። ብዙኃኑ ጸሓፍት በዚህ አሳብ ይስማማሉ።" ማረጋገጫው ኢየሱስ በዮርዳኖስ ባህር ከመድረሱ በፊት የተከናወነ ነበር። እንደ ኢብኑ ኻቲር ፣ አል-ራዚ የማሪያምን እና አሌሳቤጥ መገናኘት ዘግቧል፡- " የኢየሱስ እናት ከዮሐንስ እናት ጋር ተገናኘታለች ፤ ሰላም በእነርሱ ላይ ይሁን። ሁለቱም ነፍሰ -ጥሩ ነበሩ፡- አንዷ ኢየሱስን፣ ዮሐንስን ደግሞ ሌላዋ። የዘካሪያስ ሚስት ማርያምን 'በማህጸኔ ያለው በማህጸንሽ ላለው ይሰግዳል' ስትል ተናግራለች።" የመሐመድ አጎት ልጅ ኢብኑ አባስ ፣ አል -ራዚ ይህን ሲናገር ፡- ዮሐንስ ኢየሱስን በስድስት ወር የሚቀድመው ታላቅ ኾኖ ሳለ "ኢየሱስ የአላህ ቃል" እና "የአላህ መንፈስ" መኾኑን ያረጋግጣል።

ሙስሊማኑ መጥምቁ ታላቅ ነብይ እንደሆነ ይቀበላሉ። አል -ሱይቲ በሱረቱ 3፥39 ላይ አሳቡን እንደሚከተለው ያስቀምጣል፡- " ከሰማይ የሆነው ከሴቶች ከተወለዱት መካካል የአማኞች መሪ

ትልቁ ነብይ ዮሐንስ ነው። ጃላላን እንዲሁ “ መጥምቁ የሀይማኖት ተምሳሌት እና ከፍተኛ ስልጣን ምልክት” ተደርጎ የሚወስድ እንደሆነ አሳቡን ያክላል። ዮሐንስ ምንም አንኳ ያን ያክል ታላቅ ጥሪ እንዳለው በዘመናት ቢታመንም ፣ ቁርኣን በማህጸን ሳለ ለኢየሱስ መስገዱን ይቀበላል። ኢየሱስ ከነብይ ይልቅ ክብር የተገባው ከነብይ በላይ “ የአላህ ቃል” ነውና!

## IV. ኢየሱስ የተወለደው በተዐምር ነው

ቁርኣን በሱረቱ 19፡19-21 መልአኩ ጂብሪል ወደ መርየም መጥቶ “ንጹሑን ልጅ ለአንቺ ልሰጥሽ የጌታሽ መልዕክተኛ ነኝ” እንዳላት ይገልጸል።መርየምም “(በጋብቻ) ሰው ያልነካኝ ሆኜ አምንዝራም ሳልሆን ለእኔ እንዴት ልጅ ይኖረኛል ?” ስትል ትጠይቃለች። ጅብርልም አላት፡- “ (ነገሩ) እንደዚህሽ ነው። ጌታሽ እርሱ በእኔ ላይ ገር ነው። ለሰዎችም ታምር ከእኛም ችሮታ ልናደርገው (ይህንን ሠራን) የተፈረደም ነገር ነው። ”

ቁርኣን አክሎም ይናገራል ፡-

*ሱረቱ 66፡12*

*የዒምራን ልጅ መርየምንም ያችን ብልቷን የጠበቀችውን (ምሳሌ አደረገ) ። በእርሱም ውስጥ ከመንፈሳንዊ ነፍፋን፡፧ በጌታዋ ቃላትና በመጻሐፍቱም አረጋገጠጭ። ከታዛዦቹም ነበረች ።*

አል-ሳዲ ክፍሉን ሲገልጽ “ ጅብሪል የመርየምን ሽመልጌ በመውሰድ እፍ እንዳለበት፣ በዚህም እፍ ያለባት ወደ ደረቷ ደርሶ ልጅ እንደ ወለደች” ይናገራል። ቁርኣን ኢየሱስ “የአላህ መልክተኛ ወደ መርየም የጠላት የኹን ቃሉም ከእርሱ የኾነ መንፈስም” እንደሆነ ያረጋግጣል (ሱረቱ 4፥171)። ይህ እውነት ኢየሱስ በሰው ወይም በሰብአዊ አባት ፍቃድ ሳይሆን ፣ በመንፈስ ቅዱስ ፍጹም ልዕለ ተፈጥሮአዊ ተዐምር እንደተወለደ ያስረግጣል።

የኢየሱስ ተዐምራዊ መጸነስ እና ውልደት አሳንሰው የሚመለከቱ ሙስሊማኑ ያለ አባት እና እናት ከነበረው ከአዳም ጋር ያነጻጽሩታል። አዳም እንደ ሔዋን ሁሉ በተአምር ተፈጥሯል። ሆኖም የኢየሱስ ውልደት ፍጥረታዊ ሳይሆን፣ በእግዚአብሔር ዘላላማዊ አሳብ ወደ አለም የመጣበት ተዐምራዊ መንገድ ነው “ለሰዎችም ታምር ከእኛም ችሮታ ልናደርገው (ይህን ሠራን) የተፈረደም ነገር ነው” (ሱረቱ 19፥21)። ኢየሱስ ከሰዎች መከካል የሚተካከለው ስለ ሌለ ከፍተኛውን ቦታ ብቻውን ይይዛል። አል -ባይዳዊ የኢየሱስ ውልደት ተዐምራዊና መለኮታዊ እንደ መሆኑ ከአላህ መልዕክተኞች ሁሉ እጅጉን የሚለይ እንደሆነ ያስረግጣል።

## V. ኢየሱስ በዚህም በሚመጣውም ዓለም የተከበረ ነው

ቁርኣን የኢየሱስን የበላይነት /ክቡርነት / መዝግቧል ፡- "አላህ ከርሱ በኾነው ቃል ስሙ አል-መሲሕ ዒሳ የመርየም ልጅ በዚህ ዓለምና በመጨረሻውም ዓለም የተከበረ ከባለሟሎችም በኾነ (ልጅ) ያበስርሻል" (ሱረቱ 3፥45)፡፡

አል ራዚ "በተመሳሳይ ታላቅ ምስጋና ለመላእክት የተሰጠ ሲሆን፣ ፣ አላህ ኢየሱስን ከመላዕክት እኩል ክብርና ቦታ ሰጥቷል፡፡ ጅብሪል ኢየሱስን ያገዘው ፣ ከአላህ ቀጥሎ ቅርብ እና ታላቅ የኾነ መልአክ ነው፡፡ ሙስሊማኑ መንፈስ ቅዱስ አድርገው ይወስዱታል፡፡

በአል-ራዚ ገለጻ መሰረት ጅብሪል ከአላህ ጋር ጥልቅ ህብረት ያለው ነው፡- "መንፈሳችንንም (ጂብሪልን) ወደርሷ ላክን ፡፡ ለእርሷም ትክክለኛ ሰው ሆኖ ተመለሰላት" (ሱረቱ 19፥17)፡፡ አል-ራዚ አክሎም " አላህ ጅብሪል የርሱ መንፈስ አድርጎ ስለ ሚጠራው፣ የሀይማኖት ህይወት ሰበብ ፣ የአላህ ፍቅር መገለጫ እና የአላህ ቅርበት /ወዳጅ/ ምልክት ተደርጎ እንደሚወሰድ " ይገልጻል፡፡

እግዚአብሔር ጅብሪልን ለኢየሱስ አጋር አድርጎ ፣ ኢየሱስ በአላህ ዘንድ ያለውን ውድ ዋጋ ያመለክታል፡፡ የስጦታ ዋጋ የተቀባዩን ክቡርነትን /ውድ ዋጋ/ ያሳያል፤ ከመንፈስ ቅዱስ ዘላለማዊ አብሮነት የሚበልጥ ውድ ነገር የለምና!

የላቀ ወይም ዝነኛ (Eminet- ኢሚኔት) የአረብኛውን ዋጅሃ (Face-ፌት) ስርወ ቃል መሰረት ያደርጋል፡፡ ሱረቱ 3፥45 ከሰውነት ክፍሎች መካከል ፊት ያለውን ፍጹም ክቡርነት በማሳየት ፣ ዋጅሃ አንድ የተለየን ነገር አመላካች እንደሆነ አል-ራዚ ይናገራል፡፡ ከሰውነት ክፍሎች መካከል አንድ ፊት ብቻ እንዳለ ኹሉ፣ በምድርም በመጪውም አለም አንድ አለ፣ እርሱም ኢየሱስ ነው፡፡ የኢየሱስ ቅድመ ክቡርነት ቀጣይ እና ዘላለማዊ ነው፡፡ ኢየሱስ ዋጃሃ (ክቡር እና የተለየ) ነው፤ በህይወቱ ሁሉ ጸሎቱ የተሰማ፣ ሙታንን ያስነሳ፣ አይነ -ስውራን እና ለምጻሞችን የፈወሰ ነው፡፡ በሚመጣው አለም ክቡር የኾነ ፣ እግዚአብሔር ምልጃውን የተቀበለው፤ በዚህም በእውነተኛ ህዝቡ ምትክ የራሱ ብቸኛ አስታራቂ ያደረገው ነው፡፡

ኢየሱስ በምድር ቆይታው የማስታረቅ አገልግሎቱ ከሞትየበረታ ነበር፤ በሚመጣው አለም ይኸው የማስታረቅ ሥራ ከገሃነም ይልቃል፡፡ በምድር ህይወት ቆይታው ኢየሱስ የነበረው ክብር በሚመጣው አለም ጭምር የሚኖረው ክብር ማሳያ ነው፡፡

አል-ባይዳዊ ሱረቱ 3፥43ን ጠቅሶ የኢየሱስ የምድርም ኾነ የሚመጣውም አለም ክቡርነት ወደር የለሽ መኾኑን ያስረግጣል፡፡ "የኢየሱስ ግልጽ እና ታላላቅ ተዐምራቶችን አስምልክቶ አላህ ክቡርነቱን እንዲገለጽበት አድርጓል ፤ ምክንያቱም ተአምራቶቹ በሙሉ በሌላ በማንም የተደረጉ አይደሉም" (ሱረቱ 2፥235፡፡

አል- ዛማክሻሻሪ በበኩሉ " ክቡርነት በዚህ ምድር ትንቢትን እና በሰው ላይ ቀዳሚነትን ፣ በሚመጣው አለም የአስታራቂነት እና ክብር ስፍራን ያመላክታል" (ሱረቱ 3፥45፡፡ ቁርኣን በሱረቱ 39፥44 የማስታረቅን ሥራ በዋናነት የአላህ ብቻ እንደሆነ የናገራል፡፡ ኾኖም ሱረቱ 3፥45 ኢየሱስ የማስታረቅ ስልጣን እንዳለው ያስገነዝባል የኸውም ኢየሱስ በዚህም ሆነ በሚመጣው አለም ክቡር መሆኑን ያሳያል፡፡

የእስልምና ነገረ- መለኮት ታሪክ (ፊቅህ) ለማስታረቅ ስራ (መካከለኛነት) የሚሰጠው ስፍራ ከፍ ያለ ነው፡፡ ሱረቱ 37፥107 " በታላቅ ዕርድም (መስዋዕት) ተበገዝነው" ይላል፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቸኛው መካከለኛ መስዋዕት በመኾኑ ፣ የማስታረቁን ስራ (መካከለኛነት) ፈጽሟል፡፡ " እናንተ ያመናችሁ ሆይ ! እንደነዚያ ሙሳን እንዳሰቃዩት ሰዎች አትኹኑ፤ ካሉትም ነገር ሁሉ አላህ አጠራው፡፡ አላህም ዘንድ ባለ ሞገስ ነበር " (ሱረቱ 33፥69)፡፡ የሙሴ ክቡርነት በአጸደ ሥጋው ውስን ነው፤ በአንጻሩ አል-ራዚ " የኢየሱስ ነብይነት፣ የበላይነት እንዲሁም የማስታረቅ ሥራ፣ በዚህም በሚመጣውም አለም ወደር የለሽ " እንደሆነ ይናገራል፡፡ ሁሉም ሰው በገነት እኩል ክብር እና ስፍራ የለውም ፣ አላህ ሲናገር "ሦስት ዓይነቶችም በኾናችሁ ..ቀዳሚዎቹም (ለገነት) ቀዳሚዎች ናቸው" (ሱረቱ 56፥ 7፣ 10፣11)፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ በተመሳሳይ በሙሴ እና በኢየሱስ መካከል ያለውን ልዩነት ሲናገር "ሙሴስ በኋላ ስለ ሚነገረው ነገር ምስክር ሊሆን በቤቱ ሁሉ እንደሌለ የታመነ ነበር፣ ክርስቶስ ግን እንደ ልጅ በቤቱ ላይ የታመነ ነው" (ዕብራውያን 3፥5-6)፡፡ ቁርኣን የማስታረቅን ሥራ በተመለከተ ኢየሱስን ከመሐመድ በላይ ያስቀምጠዋል፡፡ አላህ ለነብዩ ሲናገር "ለእነርሱ ምሕረትን ለምንላቸው፤ ወይም ለእነርሱ ምሕረትን አትለምንላቸው (እኩል ነው) ፡፡ ለሰባ ጊዜ ምሕረትን ብትለምንላቸው አላህ ለነሱ በፍጹም አይምርም " ይላል (ሱረቱ 9፥80)፡፡

## VI. ኢየሱስ ስሑት-አልባ ነው

በሱረቱ 19፥19 መልአኩ መርየምን ኢሳን ዛኪያን ("ቅዱስ፣ ስሑት አልባ ፣ ያለ ኃጢአት የኾነ ልጅ) እንደሆነ ሲነግራት እንመለከታለን፡፡ ቁርኣንና ሀዲስ በኢየሱስ ኃጢአት-የለሽ ሰብዕና ላይ ይስማማሉ፡፡ አል-ባደዊ " ቅዱሱ ልጅ " ከ`ኃጢአት ነጻ" የኾነ ልጅ መኾኑን ያበክራል፡፡ ዛኪያን በሱረቱ 18፥ 74 ብላቴናውን ለመግለጽ ስራ ላይ የዋለ ቃል ነው፤ አል- ጃላላን እንደተረጎመው"ሌላ ነፍስን ከማጥፋት ነጻ መሆንን " ያመላክታል፡፡ ቡኻሪ መሐመድ " ከመርየም ልጅ ኢሳ በስተቀር ማንኛውም የአደም ልጅ በሰይጣን ሁለት ጣጦች ተወግተዋል፤ በኢየሱስ ላይ ግን አልተቻለውም::"[41]

እንደ ብሉይ እና አዲስ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ ቁርኣን ነብያት እና ሐዋሪያት ኃጢአት ያለባቸው መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ ለምሳሌ ፡- አዳም (ሱረቱ 20፥121)፣ ኖህ (ሱረቱ 71፥26-28)፣ አብርሐም( ሱረቱ 37፥89)፣ አሮን (ሱረቱ 7፥150-152)፣ ሙሴ (ሱረቱ 28፥15፣16) እና ዳዊት (ሱረቱ 38፥20-25) ስህተት ወይም ኃጢአት የተገኘባቸው እንደሆነ መረዳት ይችላል፡፡ መሐመድ ሳይቀር በኃጢአት /በሸክም/ እንደነበር ቁርኣን ይናገራል፡- " ልብህን ለአንተ አላሰፋንልህምን ?( አስፍተንልሃል)፡፡ ሸክምህንም ካንተ አውርደንልሃል፡፡ ያንን ጀርባህን ያከበደውን (ሸክም)፡" አላህ ራሱ "ከኃጢአትህ ያለፈውን እና የሚመጣውን ላንተ ሊምር ጸጋውንም ባንተ ላይ ሊሞላ ቀጥጠኛውንም መንገድ ሊመራህ (ከፈተልህ) (ሱረቱ 48፥2፣ 40፥5 ፣4፥106፣ 47፥19 )፡፡" በሱረቱ 9፥43 "አላህ ከአንተ ይቅር አለ፡፡ እነዚያ እውነተኛዎቹ ላንተ እስከ ሚገለጹልህና ውሸታሞቹንም እስከምታውቅ ድረስ ለነርሱ (እንዲቀሩ) ለምን ፈቀድክላቸው" ሲል ፤ በተጨማሪም ሱረቱ 80፡1-4 አይነስውሩን ሰው ፊት ከነሳው በኃላ " ፊቱን አጨፈገገ፤ ዞረም ፡፡ ዕውሩ ስለ መጣው፡፡ ምን ያሳውቅሃል? (ከኀጢአቶቹ) ሊጥራራ ይከጅላል፡፡ ወይም ሊገሠጽ ግሣጼይቱም ልትጠቅመው (ይከጅላል)፡፡" መሐመድን ሲናገረው እንመለከታለን፡፡

ሀዲስ መሐመድ " ከሰባ ጊዜ በላይ ይቅርታን እንደጠየቀ፣ በንስሐም ወደ አላህ አንደተመለሰ" ይገልጣል፡፡ ቡኻሪ እነዚህን የመሐመድ ጸሎቶች ዘግቧል፡-

---

[41] ቡኻሪ ፣ ሳሂ ፣ቅጽ IV፣506፡፡

*አላህ ሆይ! ስህተቶቼን፣ አላዋቂነቴን እና በጽድቅ ስላልሆነው ምግባራቶቼ ይቅር በለኝ፤ ከኔም ይልቅ የምታይብኝን ሁሉ ይቅር በለኝ። አላህ ሆይ! በማወቅም ባለ ማወቅም ስለ ሰራሁትና ስለ ተገኘብኝ በደል ይቅር በለኝ።*

*አላህ ሆይ ! ኃጢአቴን በበረዶ ዝናብ እጠብልኝ፤ ልቤንም ነጭ ልብስ ከዕድፍ እንደሚነጣ ልቤን ከኃጢአት ሁሉ አንጻልኝ ፣ ምስራቅ ከምዕራብ እንደሚርቅ እንዲሁ በእኔና በኃጢአቴ መካከል አርቅልኝ።*[42]

ቡኻሪ አክሎም " መሐሙድ የህይወት መጨረሻ እስትንፋሱ ድረስ ይቅርታን ይጠይቅ" እንደነበር ይገልጻል። ቁርኣን ስለ ሰው ዘር ውድቀት አበክሮ ይናገራል (ሱረቱ 2፥36፣ 7፥24፣ 11፥9፣ 12፥53፣ 100፥6)። ሀዲስ "ሰይጣን ደም በሰውነት ውስጥ እንደሚዘዋወር በሰው አእምሮ እንዲሁ እንደሚዘዋወር"[43] ይናገራል ። ቁርኣንም ሆነ ሀዲስ ኢየሱስ ኃጢአት እንዳለበት ፈጽሞ አልጠቀሱም ፤ በአንጻሩ ሁለቱም የሚሰጡት ምስክርነት የኢየሱስ ቅድስና እና ንጽህና ወደር የለሽ መሆኑን ነው። ማንኛውም ነብይ ወይም ሐዋሪያ ስሑት አልባ ስለ መሆኑ አልተናገረም። ኢየሱስ ግን " ከአናንተ ስለ ኃጢአት  የሚወቅሰኝ ማን ነው " (ዮሐንስ 8፥46) ፤ ጠላቶቹንም አስምልክቶ  " የዚህ ዓለም ገዢ ይመጣልና፤ በእኔ ላይም አንዳች የለውም " (ዮሐንስ 14፥30) ብሎ ሰይጣንን ጭምር ስለ ራሱ ምስክርነት ሲሰጥ እንመለከተዋለን። አይሁዶች በኢየሱስ ላይ ክስን ባቀረቡ ወቅት፣ አንዳች ስሕተት እንዳልተገኘበት ምስክርነቱን በመስጠት (ዮሐንስ 18፥38፣ 19፥4፣6) ፤ "እኔ ከዚህ ጻድቅ ሰው ደም ንጹሕ ነኝ፤ እናንተ ተጠንቀቁ " (ማቴዎስ 27፥24) ሲል እንመለከታለን።

## VII. ኢየሱስ በክበር ያረገ ነው

ቁርአን ሲናገር ፦

***ሱረቱ 2፥253***

*እነዚህን መልእክተኞች ከፊላቸውን በከፊሉ ላይ አበለጥን። ከእነርሱ ውስጥ አላህ ያነጋገረው አልለ። ከፊሎቻቸውንም በደረጃዎች ከፍ አደረገ። የመርየምን ልጅ ዒሳንም ግልጽ ታምራቶችን ሰጠነው። በቅዱሱ መንፈስም  አበረታነው።*

[42] ቡኻሪ ፣ ሳሂ ፣VIII፣408,379።

[43] ቡኻሪ ፣ ሳሂ ፣V፣715።

ቁርኣን ኢየሱስ በክብር ከፍ ያለ /ያረገ /፣ አሁን ከእግዚአብሔር ጋር በህይወት ያለ መኾኑን ይናገራል፡- "በመጠርጠር ውስጥ ናቸው፡፡ ጥርጣሬን ከመተከል በስተቀር በእርሱ ነገር ምንም ዕውቀት የላቸውም፡፡ በእርግጥም አልገደሉትም፡፡ይልቁንም አላህ (ኢሳን) ወደርሱ አነሳው፡፡ አላህም አሸናፊ ጥበበኛ ነው" (ሱረቱ 4፥157፣158)፡፡ ቁርኣን አላህ ራሱ "ዒሳ ሆይ! እኔ ወሳጂህ ወደ እኔም አንሺህ ነኝ"ብሎ መናገሩን ይጠቅሳል (ሱረቱ 3፥55)፡፡

ሙስሊማኑ ሌሎች ነብያት ሳይቀሩ ከሞት እንደተነሱ አድርገው ይቆጥራሉ ፤ ነገር ግን ይህን የሚሉበት አውድ በእጅጉ ይለያል፡፡ ለምሳሌ ፡- ቁርኣን መሐመድን " መወሳትህንም ላንተ ከፍ አድርገንልሃል" ይላል (ሱረቱ 94፥4)፡፡ በዚህ ክፍል አላህ መሐመድን ሳይኾን ዝናውን ከፍ እንዳደረገው ማስተዋል አያዳግትም፡፡ ሌላው ነብይ እድሪስ (ሔኖክ) አስመልክቶ ወደ "ከፍተኛም ስፍራ አነሳው " የሚለው አሳብ ቢነሳ እንኳ ወደ የት ስፍራ እንዳነሳው ግልጽ አይደለም (ሱረቱ 19፥57)፡፡ አል-ራዚ በዚህ ክፍል "አስነሳው" የሚለው ቃል "ከፍ አደረገው" ማለት እንደሆነ በመግለጽ ፣ የእድሪስ አካላዊ አንጂ መንፈሳዊ ሁኔታ የማያሳይ እንደሆነ ያሰስረግጣል፡፡

ኢየሱስን በተመለከተ ግን ቁርኣን አላህ " ወደ እኔም አንሺህ ነኝ" እንዳለው እናስተውላለን፡፡ ስለሆነም የኢየሱስ ከፍ መደረግ /መነሳት/ ከእግዚአብሔር ጋር እንደሆነ መረዳት አያዳግትም፡፡ መነሳት" ማረጋገጫ ከሱረቱ 3፥55 እጅጉን ይስማማል፡፡ የኢየሱስ መነሳት በገነት ከመሆን ደስታ በላይ መንፈሳዊ አንድምታ ያለው ነው፡፡ "ወደ እኔም አንሺው ነኝ" ማለቱ " ያነሳሁ በእኔ



ዘንድ ባለ ክብር ኃለዎት" እንድትሆን የሚል ትርጓሜን ያሰጣል። ሱረቱ 4፥157 መነሻ በማድረግ አል-ራዚ " የኢየሱስ መንፈስ ቅዱስ ፣ ክቡር፣ ሰማያዊ፣ መለኮታዊ ብርሃን እና ለመላእክት ቅርብ "መሆኑን ያስረግጣል።

## VIII. ኢየሱስ ቡሩክ ነው

ቁርኣን ኢየሱስን ከልደት አንስቶ ብሩክ መሆኑን ያስታውቃል ፡- " በየትም ስፍራ ብሆን ቡሩክ አድርጎኛል ። በሕይወትም እስካለሁ ሶላትንም በመስገድ ዘካንም በመስጠት አዞኛል" (ሱረቱ 19፥31)። አል-ታባሪ "ቡሩክ አድርጎኛል" የሚለው ሐረግ " የመልካም ነገር ሁሉ መምህር አደረገኝ" ትርጉምን ይይዛል፤ ኢየሱስ ኃጢአት የለሽ ቡሩክ ነው። ፍጹምነቱ የነበረ ብቻ ሳይሆን ያለና የሚኖር ነው። ቡሩክነቱ ያለ ቅድመ-ሁኔታ፣ ምንግዜም "በየትም ስፍራ" የተገለጠ ነው። አል ባይዳዊ "ቡሩክ" "ለብዙዎች መትረፈን" አመልካች ሐረግ እንደሆነ ይገልጣል። አል-ራዚ ሱረቱ 3፥39ን ሲያብራራ፣ አይህ ሐረግ "ለብዙዎች መትረፍ"ን አንደሚገልጥ ያረጋግጣል። ስለሆነም " እግዚአብሔር በኢየሱስ በኩል ሰዎችን ከመታለል ወደ ህይወት በማውጣት በእውነተኘ መንፈስ አንዲኖሩ" አድርጓል ፤ የኢየሱስም አገልግሎት ለሚሞተው ሰውነት ህይወት በሚሰጥ መንፈስ እንዲሆን ሆኗል። ሱረቱ 3፥49 በመጥቀስ አል-ባይዳዊ ኢየሱስ " የሞቱ ሰዎችን እና የሞቱ ልቦችን ወደ ህይወት ያመጣ እንደ ነበር" ይገልጣል። ከኃጢአትም ነጻ በመሆኑ ሰዎችን ከሰይጣን መታለል ነጻ ያወጣቸው ነበር።

በቁርኣን የተጠቀሰው ብቸኛው "ቡሩክ" ኢየሱስ ብቻ ነው። ይህ ሐረግ በቁርአን ለሌላ ጥቅም በሚከተሉት ላይ ውሏል ፡-

- ቡሩክ መጽሐፍ (ሱረቱ 6፥92)።
- የመጀመሪያው ቅዱስ ቤት በመካ (ከአዳም በፊት በመላዕክት የተገነባ ተደርጎ ይታመናል (ሱረቱ፥ 3፡96)።
- ቁርኣን የተገለጠበት ኃያል ምሽት ( Lailat al-Qadr) (ሱረቱ 44፥3) እና
- የአላህ ብርሃን አንጸባራቂ የወይራ ዛፍ (ሱረቱ 24፥35) ፤ በየትኛው የቁርአን ክፍል አይገኝም ። ሆኖም "ቡሩክ" የሚለው መጠሪያ ለሰው ወይም ለሰብዕና የተሰጠው ለኢየሱስ ብቻ ነው

## IX. ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ መታገዝ

ቁርኣን ኢየሱስ ሦስት ጊዜ ያህል በመንፈስ ቅዱስ እንደበረታ ይናገራል። እስልምና አሁንም ኢየሱስ ልዩ መኾኑን ይገልጣል (ሱረቱ 2፥253) ። የአላህ ቃላት እንደሚከተለው መረዳት ይቻላል፦

***ሱረቱ 5፥110***

*የመርየም ልጅ ዒሳ ሆይ! በአንተና በእናትህ ላይ (የዋልኩላቸሁን) ጸጋዬን አስታውስ …በቅዱስ መንፈስ ባበረታሁ ጊዜ።*

***ሱረቱ 2፥87***

*የመርየምን ልጅ ዒሳንም በግልጽ ታምራቶችን ሰጠነው። በቅዱስ መንፈስም አበረታነው፡*

አል-ራዚ ሱረቱ 2፥87ን ሲያብራራው "ጅብሪል (መንፈስ ቅዱስ) ኢየሱስን በማበረታታት ስራው መገለጡ ኢየሱስን ከሌሎች ነብያት የተለየ ያደርገዋል። በዚህ ደረጃ የተጠቀሰ ሌላ ነብይ የለም። ጅብሪል የኢየሱስን ልደት መልካም ዜና ለማርያም አበሰረ፤ በጅብሪል እስትንፋስም ኢየሱስ ተጸነሰ። እርሱ ኢየሱስን አበረታው ፣ በየትኛውም ስፍራ አብሮት ይሆን ነበር" በማለት ይገልጣል።

ሱረቱ 3፥52-55 " ጅብሪል ለአንድ አፍታ አንኳ ኢየሱስን አልተለየውም ፤ በአንጻሩ ጅብሪል መሐሙድን ከመጉብኘት ባሻገር ያደረገው ምንም ነገር የለም። መገለጥ ባቆመ ወቅት፣ መሐመድ ጅብሪልን ' አሁን ከጎበኘኸም በላይ ደጋግመህ እንዳትጎበኘኝ የሚከለክልህ ምንድነው ? ብሎ ጠይቆታል። ጅብሪል ' እኛ መላዕክት በጌታህ ትዕዛዝ ካልሆነ በቀር መውረድ/መጎብኘት/ አንችልም"[44] በማለት መልሶለታል።

አቡ ሙስሊም " መንፈስ ቅዱስ ንጹህ መንፈስ ነው፤ እግዚአብሔር በኢየሱስ ላይ እፍ በማለት ኢየሱስ ከውልደቱ ጀምሮ ከሰው ሁሉ እንዲለይ አድርጓል።" ኢብኑ አባስ " ይህ መንፈስ በኢየሱስ ላይ እፍ የተባለ ፣ እግዚአብሔርም ኢየሱስን ያከበረበት እና የቀደሰበት ነው።" እንደ አል-ሳዲ አገላለጽ "መንፈስ ቅዱስ ጅብሪል ሲሆን፣ ኢየሱስን ረድቷል፣ በየትኛው ስፍራ አብሮት ሆኗል፣ ወደ ሰማይም ከፍ እንዲል /እንዲነሳ/ አድርጓል። ኢብኑ ኅብሲር አክሎም

[44] ቡኻሪ ፣ ሳሂ ፣ ቅጽ IV፣ 501።

“መንፈስ ቅዱስ ኢየሱስን ከሞት ያስነሳ የእግዚአብሔር ስም” እንደሆነ ይናገራል። ኢብኑ አባሰ “ መንፈስ ቅዱስ የራሱ ስም ያለው ኢየሱስን ከሞት ያስነሳው ቅዱስ” መሆኑን ይስማማበታል።

## X. ኢየሱስ አዳኝ ነው

በቁርኣን አስተምህሮ ከመወለዳቸው በፊት አላህ የሰየማቸው ስብዕናዎች ሁለት ብቻ ናቸው፡- መጥምቁ ዮሐንስ እና ኢየሱስ። መላእኩ ለማርያም ሲናገር “አላህ ከርሱ በኾነው ቃል ስሙ አል-መሲሕ ዒሳ (ኢየሱስ) የመርየም ልጅ” (ሱረቱ 3፥45) ፡፡

አል-ቃሲም በዚህ ክፍል ላይ አሳቡን ሲያስቀምጥ “ዒሳ  ከግሪክ ቃል የመጣ አረብኛ ይዘት ያለው ሲሆን፣ ትርጓሜው አዳኝ ማለት ነው፤ ከዕብራይስጡ ጀሹዋ ጋር አቻ ቃል ነው። ” እግዚአብሔር ይህን ስም የሰጠው ኢየሱስ ከመወለዱ በፊት ነው። “ የጌታህም ቃላት እውነተኛ እና ትክክለኛ ስትኾን ተፈጸመች። ለቃላቱም ለዋጭ የለም ”(ሱረቱ 6፥116)። ሁሉን ዐዋቂ እግዚአብሔር “አዳኝ” የሚለውን ስም አለም ከክርስቶስ ተቃዋሚው /Dajjal/ ይታደግ ዘንድ ለኢየሱስ ሰጥቷል።

ሱረቱ 3፥48 ሲያብራራው ፣ አል-ሱዩቲ “ ኢየሱስ እና መጥምቁ ዮሐንስ ወደ መንደሮች ሲመጡ፣ ኢየሱስ ኃጢአተኞችን ፣ዮሐንስ ደግሞ አድራጊዎችን ይፈልግ ነበር። ዮሐንስ ኢየሱስን ‘ ስለምን ኃጢአተኞችን ትፈልጋለህ ብሎ በጠየቀው ጊዜ ፤ ኢየሱስ ‘ እኔ ባለ መድኃኒት ነኝ ፣ የመጣሁት ህመምተኞችን ብቻ ለማዳን ነው” ብሎ መለሰለት።

አል-ባይዳዊ በበኩሉ ሱረቱ 4፥171 ሲገልጽ “ዒሳ የሞቱ ሰውነቶችን እና ልቦችን ወደ ህይወት ያስነሳ መንፈስ ተብሎ ተጠርቷል::”  ሱረቱ 5፥110ን በማከል  አል-ባይዳዊ መንፈስ ቅዱስ ጅብሪል እንዳልሆነ በማስረገጥ ፣ እርሱ “ ህይማኖት የተመሰረተበት ቃል፣ ለሰው ነፍስ ዘላላምን የሚሰጥ፣ ሰዎችን ከኃጢአት የሚያነጻ፣ ኢየሱስን ከሞት ያስነሳ መለኮት”  እንደሆነ ያበክራል።

የኢየሱስ ቃል አካለዊ እና ዘላላማዊ ህይወት ሰጪ ሰዎችንም ከኃጢአት የሚያነጻ ኃይል ነው። ቁርኣን ይህ ኃይል የኢየሱስ ብቻ አንደኾነ ፣ በባህሪውም መለኮታዊ እንደሆነ ያረጋግጣል ፡- “አላህ ምእመናንነን እና ምእምናትን ከሥሮቻቸው ወንዞች የሚፈሱባቸውን ገነቶች በውስጣቸው ዘውታሪዎች ሲኾኑ በመኖሪያ ገነቶችም ውስጥ መልካም መኖሪያ ቤቶችን ቃል ገብቶላቸዋል” (ሱረቱ 9፥72) ፡፡

ሱረቱ 3፥52 ሲናገር “ ዒሳ ከነርሱ ክህደት በተሰማውም ጊዜ ፡- ‘ወደ አላህ (ተጨምረው) ረዳቶቼ እነማን ናቸው’ አለ፤ ሐዋርያት ፡- ‘ እኛ ትክክለኛ ታዛዦች መኾናችንን መስክር’ አሉ” ይላል፡፡ አል-ራዚ ክፍሉን እንደሚከተለው ይገልጻል፡- “የኢየሱስ ደቀመዛሙርት አስራ ሁለት ናቸው፡፡ ከእነዚህም መካከል አሳ አጥማጆች የነበሩት ስሞዖን፣ ያዕቆብ እና የዘብዴዎስ ልጅ ዮሐንስ ይገኙበታል፡፡ ኢየሱስም አለ፡- ‘አሁን አሳ አጥማጆች ናችሁ ፣ ከእናንተ የሚከተለኝ ቢኖር ለዘላለም ህይወት ሰዎችን የሚያጠምድ ይሆናል::’ ደቀመዛሙርቱ ኢየሱስ ተአምራት እንዲያደርግላቸው ጠይቀውታል፡፡ ስምዖን ሌሊቱን በሙሉ ዓሳ ለማግኘት ቢደክምም፣ አንዳች ሊያገኝ አልቻለም፡፡ ኢየሱስ ስምዖንን መረቡን እንደገና እንዲጥል ባዘዘው ጊዜ መረባቸው እስኪቀደድ ድረስ ብዙ ዓሳ መያዝ ቻሉ፡፡ ባጠጋባቸው ያለውን ጀልባ እገዛ ቢጠይቁም ፣ ሁሉም ጀልባዎች በዓሳዎች ሞልቶ ስለ ነበር ፣ደቀመዛሙርቱ በእርሱ አመኑ::”

አል -ባይዳዊ በዚህ ክፍል ላይ አክሎ ሲናገር “ የኢየሱስ ቃል ዘላለም ህይወት የሚሰጥ ቃል ነው፡፡ ቃሉ የዘላለም ህይወት የሚሰጥ፣ ሙታንን የሚያስነሳ መለኮታዊ ኃይል ነው፡፡ ደቀመዛሙርቱ ኢየሱስ የሚያደርጋቸው ተዐምራት በሌላ በማንም ፍጡር የማይደረግ እንደሆነ ተገንዝበዋል፡፡ ኢየሱስን ተዐምራት እንዲያደርግ መጠየቃቸው ነብይ እንደሆነ ለማረጋገጥ ሳይሆን፣ የዘዛለም ህይወት የሚሰጥ ኃይል በርሱ ዘንድ እንዳለ ይህንንም እንገልጠው ነው”

አል -ራዚ “አሁን ዓሳ አጥምዳችኃል፤ ነገር ግን እኔን ብትከተሉ ለዘላላም ህይወት ሰዎችን የምታጠምዱ ትሆናላችሁ” የሚለውን ቃል በማውሳት፣ ኢየሱስ አዳኝ እንደሆነ ይገልጣል፡፡ ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረ ወቅት ሰዎችን ከኃጢአታቸው አድኗል፣ አሁንም በሰማያት ከፍ ብሎ ሳለ ሰዎችን ከኃጢአታቸው የማዳን ስራን ይሠራል፡፡ በአንጻሩ ቁርኣን ሰለ መሐመድ “ለራሴ ጉዳትንም ጥቅምንም አላህ ካሻው በስተቀር አልችልም፡፡” (ሱረቱ 10፥49)፡፡

## XI. ኢየሱስ ዳግም ይመጣል

በትክክለኛው እስልምና አስተምህሮ መሐመድ ወይም ሌሎች ነብያት ሳይኾኑ ፣ ኢየሱስ ነው ዳግም እንደሚመጣ የሚታመነው፡፡ ኢየሱስ ወደ ምድር በአለምና በክርስቶስ ተቃዋሚ ላይ ይፈርዳል / Anti-Christ: Dajjal/::[45]

[45] ቡኻሪ ፣ ሳሂ ፣ቅጽ VI፣ 225::

በሀዲስ  አል- ሂንዲ ለመሐመድ ባረጋገጠው ጽሑፍ  ይህን መረዳት ይቻላል ፡

*“ በእግዚአብሔር ፍቃድ  ኢየሱስ የማርያም ልጅ በጽድቅ ለመፍረድ ዳግም ይምጣል።”*

*“ ኢየሱስ የማርያም ልጅ ጻድቅ ፈራጅና ጻድቅ መሪ ሆኖ እስኪመጣ ድረስ የመጨረሻው ሰዓት አይሆንም።”*

*“ ኢየሱስ የማርያም ልጅ ጻድቅ ፈራጅና መሪ ሆኖ ይመጣል። ወደ መቃብሬም መጥቶ ሰላም ይለኛል፣ እኔም እመልስለታለው።”*

*“ እግዚአብሔር የክርስቶስ ተቃዋሚ (*Dajjal)ን በማርያም ልጅ ኢየሱስ እጅ ይቀጣል*”*

*“ ኢየሱስ የማርያም ልጅ ዳግም ይምጣል የክርስቶስ ተቃዋሚ (*Dajjal) ሲያየውም ወዲያው እንደ ሰም  በፊቱ ይቀልጣል፣ ኢየሱስም ይገድለዋል።”[46]

በኢብኑ ማጃህ ገለጻ መሰረት  መሐመድ የሚከተለውን ተናግሯል “ የክርስቶስ ተቃዋሚ በምድር ላይ አይኖርም ፣ በመካ- መዲና አግሩን ለማስገባት ይታትራል ፣ መላዕክትም በሰይፋቸው  ይገናኙታል፤ እርሱም  ወደ ቀይ ኮረብታዎችም ይወጣል ። በዚህ ጊዜ ከተማዋ ሦስት ጊዜ ትንቀጠቀጣለች፣ ያም ቀን የድነት ቀን ይሆናል። ነብዩም ተጠየቀ ፦ ‘የአላህ ነብይ ሆይ! በዚያን ጊዜ ዓረቦች ወዴት አሉ? ፣ ነብም ሲመልስ ‘በዚያን ጊዜ ዓረቦች ጥቂት ናቸው፤ ኢየሱስ የክርስቶሰ ተቃዋሚን ሲመለከተው በፊቱ ጨው በውሃ እንደሚሟሟ ሆነ፣ ሊያመልጥ ቢሞክርም ኢየሱስ ይገድለዋል።”[47]

አል-ሂንዲ በድጋሚ የመሐመድን ንግግር ያስቀምጣል ፦ “ኢየሱስ የማርያም ልጅ በእኔ ህዝብ ላይ ጻድቅ ገዢና መሪ ይሆናል። ጥልና ጥላቻም ይወገዳል፤ ምድርም ሰሃን በውሃ እንደሚሞላ በሰላም ትሞላለች። ጦርነት ይቆማል፤ በኢየሱስ አገዛዝ ጊዜም የሚነድፍ ነገር ዳግም አይነድፍም፦ ይኸውም ልጅ ከእባብ ጋር ይጫወታል አይነደፍም፣ አንበሳን ይነካል አንዳችም አይጎዳም። ቀበሮውች እንደ ውሾች ሁሉ በበጎች መከካል ይሆናሉ፤ እጽዋቶች በአዳም ዘመን እንደሆነው በምድር ሁሉ ላይ ፍሬን ማፍራት ይጀምራሉ።”[48]

---

[46] ሙስሊም  ሳሂ  ክፍል 23፣ ቁጥር. 116።

[47] አል-ሂንዲ፣ቅጽ .17፣ ቁጥር 1017 ፣ ቅጽ 18፣ ቁጥር 1037፤ ቅጽ 17፣ቁጥር 1028፣ ቅጽ 18፣ቁጥር 791።

[48] ኢብኑ፣ ማጃ፣ II ፣4077።

ኢየሱስ ገዢም መለኮታዊ ፈራጅም ነው፡፡ በአንጻሩ መሐመድ ከክርስቶስ ተቃዋሚ /Dajja/ እንደሚጸልይ ሀዲስ ይናገራል፤ ኢየሱስ ሉዑል ነው![49]

## XII. ኢየሱስ ክርስቶስ ነው

ኢየሱስ "ክርስቶስ" እንደሆነ አስር ጊዜ ያህል በቁርኣን ተጽፏል፡፡ አል- ባይዳዊ በሱረቱ 3፥ 45 ስሙ "አል- መሢሕ" ("ክርስቶስ") የሚለው መጠሪያ ከዕብራይስጡ መሢሕ (Mashih) የመጣ ፣ ትርጓሜውም የተቀባ /"Anoited"/ ማከት እንደሆነ ይገልጻል::

የማርያም እናት ማርያም ከወለደች በኃላ የሚከተለውን ጸሎት ጸልያለች ፦ "እርሰዋንና ዘርዋን ከተጠላው /ከተባረረው/ ሰይጣን ጠብቃት" (ሱረቱ 3፥36):: አል-ሱዩቲ ኢብኑ አባስን ጠቅሶ አንዳስቀመጠው " ከተወለዱት ኹሉ በሰይጣን ያልተነካው እና ያልተገዛው የማርያም ልጅ ኢየሱስ ብቻ ነው፡፡" የሙስሊም ጸሓፍት ኢየሱስ የተቀባ በመሆኑ በሰይጣን እንዳልተነካ ይስማማሉ፡፡

አል-ራዚ በሱረቱ 3፥45 በስም መጠሪያው ላይ ተጨማሪ አሳቦችን ያክላል፦

- ኢየሱስ ክርሰቶስ ተብሎ የተጠራው ስለ ተቀባ በዚህም ከኃጢአት ነጻ ስለሆነ ነው፡፡
- ኢየሱስ ክርስቶስ የሚል መጠሪያ የተሰጠው በጅብሪል ክንፍ ስለ ተቀባ በሰይጣንም እንዳይነካ ስለተጋረደ ነው፡፡
- ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፣ ምክንያቱም ምድር እንድትኖር አድርጓታል፣ በዐጭር ጊዜ ምድርና ሞላዋን ሞላዋን ደርሷል፡፡
- ኢየሱስ ክርስቶስ የተባለው ክርስቶስ "ንጉስ" ወይም "ጻድቅ" የሚለውን ትርጉም ስለ ሚይዝ ነው፤ ከእናቱ ማህጸን ከመውጣቱ በፊት የተቀባ ነበር፡፡

አል-ቁርቱቢ ተጨማሪ አሳቦችን እንደሚከተለው ያስፍራል፦

- ኢየሱስ ክርስቶስ እንደመኾኑ እጆቹን የሚጭንባቸው ድውያን ሁሉ ይፈወሱ ነበር፡፡
- ኢየሱስ ክርስቶስ ተብሎ የተጠራው የሙት ልጆችን ራሱ ለእግዚአብሔር ይቀባ ስለ ነበር ነው፡፡

[49] አል -ሂኒዲ፣ ቅጽ.17.ቁጥር፣919፡፡

- ኢየሱስ ክርስቶስ የሆነው የተቀባ እና ከኃጢአት ነጻ በመሆኑ ነው።
- ኢየሱስ ክርስቶስ የተባለው ነብያቶች በሚቀቡት ንጹህ እና ቡሩክ ቅባት ስለተቀባ ነው።

አል-ቃሲም በሱረቱ 3፥45 አሳቡን ሲያኖር "ለአይሁድ በተገለጠው ሕግ 'ክርስቶስ' የሚለው መጠሪያ ቀዳሚ ትርጉሙ የሚያመለክተው ማንኛውም የሀይማኖት መሪ በቅዱስ ቅባት ሲቀባ ፦ ንጹህ፣ ለመንግስትም ለዕውቀትም ብቁ፣ ብጹእ እና ቡሩክ ይሆናል። ልዑል እግዚአብሔር በዚህ መጠሪያ ኢየሱስን መጥራቱ በራሱ ኢየሱስ አልተቀባም ቢባል እንኳ ፣ በክበረ እና ቡሩክ በሆነ አቻ የለሽ ስፍራ ላይ ያስቀምጠዋል።

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር 'ክርስቶስ' የሚለውን መጠሪያ ለኢየሱስ የሰጠው ከመወለዱ በፊት ነው። ኢየሱስ ንጉስ እንዲሆን የቀባው እግዚአብሔር እንጂ ሰው አይደለም። ሰው ሰውን ቢቀባ የተቀባው ያው ሰው እንደመሆኑ ሁሉ፣ ኢየሱስ በህያው እና ዘላለማዊ አምላክ በመቀባቱ እርሱም ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖር ዘላለማዊ ንጉስ /መለኮት / ነው።

## XIII. የኢየሱስ መልዕክት በተአምራቶች የጸና ነው

ቁርኣን የኢየሱስ መጠሪያ ስሞቹ፣ ባህሪዎቹና ቃሎቹ ርሱ ልዩ መሆኑን ያመላክታል። አላህ የተናገረውን ሲያስቀምጥ "የመርየም ልጅ ዒሳን ግልጽ ታምራቶች ሰጠነው ። በቅዱስ መንፈስም አበረታነው" (ሱረቱ 2፥253):: አል-ባይዳዊ አሳቡን ሲያጠናክር " እግዚአብሔር ግልጽ እና ታላላቅ ተአምራቶች የሰጠው ለኢየሱስ ብቻ ነው፤ ኢየሱስ ያደረጋቸው ተአምራቶች በሌሎች በማናቸውም ስም ነብያት አልተገለጸም።"

በእስልምና የኢየሱስ ተዓምራቶች እንደ ክርስትና አንድ ዓይነት እንደምታ ያላቸው አይደሉም። ክርስቲያኖኑ በምድር የክርስቶስ ተልዕኮ ሰዎችን ከእግዚአብሔር ጋር ማስታረቅ እንደሆነ ያበክራሉ። እርሱም የተሰጠው ልዩ ኃይል ከሰይጣን ባርነት ሰዎችን ነፃ ማውጣት ነው፤ ኃይሉም የሰዎችን አካላዊ ፈውስ በማፅናት ተአምራቶች መገለጡ የእግዚአብሔርን ክብካቤ እና ፍቅር ለማሳየት እንደሆነ ይታመናል። በአንፃሩ ሀዲስ ኢየሱስ የገለጣቸው ተዓምራቶች ርህራሄን ወይም ችግረኞችን ከማገልገል የመነጨ ሳይሆን በዋናነት የእግዚአብሔርን ኃይል መግለጥ ነው፤ መልዕክታቸውም የእስልምና መልዕክት፦ "አላህ ትልቅ ነው" የሚል እንጂ ወንጌል እንደሚያረጋግጠው "እግዚአብሔር ፍቅር ነው" የሚል አይደለም።

ቁርኣን የኢየሱስ ተዓምራቶች የእግዚአብሔር ኃይል “ግልፅ ምልክቶች” እንደሆኑ ፣ ለነቢያቶች ግን እንዳልተሰጡ ይናገራል፡፡ ሱረቱ 2፥252 -253 ሲናገር “እነዚህ (አንቀጾች) በውነት በአንተ ላይ የምናነባቸው ሲኾኑ የአላህ አንቀጾች ናቸው….የመርየምን ልጅ ዒሳን ግልጽ ታምራቶችን ሰጠነው” ይላል፡፡ አል-ባይዳዊ “ እግዚአብሔር የኢየሱስን ተአመራቶች እርሱ ከሌሎች ነብያት ቀዳሚ እና በላጭ እንደኾነ ያረጋገጠበት ነው፤ ግልጽ ምልክቶቹ እና ተአምራቶቹ በሌላ በማንም አልተገለጹም፡፡ ”

የቁርዐን ሁለት ክፍሎች በኢየሱስ ስለ ተሰሩት ተዐምራቶች ይናገራሉ፡፡ የመጀመሪያው ኢየሱስ ራሱ የተናገረው ነው፡-

***ሱረቱ 3፥49***

*እኔ ከጌታዬ ዘንድ በተዓምር ወደ እናንተ መጣሁ፡፡ እኔ ለእናንተ ከጭቃ እንደ ወፍ ቅርጽ እፍጥራለሁ፡፡ በርሱም እተነፍስበታለሁ ፡፡ በአላህም ፈቃድ ወፍ ይኾናል፡፡ በአላህም ፈቃድ ዕውር ኾኖ የተወለደን፡- ለምጸኛንም አድናለሁ፡፡ ሙታንም አስነሳለሁ፡፡ የምትበሉትንና በቤታችሁ የምታደልቡትንም ሁሉ እነግራችኃለሁ፡፡ የምታምኑ እንደኾናችሁ ለእናንተ በዚህ ውስጥ በእርግጥ ተዓምር አለበት፡፡*

ሁለተኛው አላህ የተናገረው ነው፡-

***ሱረቱ 5፥110***

*የመርየም ልጅ ዒሳ ሆይ! በአንተና በእናትህ ላይ (የዋልኩላችሁን) ጸጋዬን አስታውስ፡፡ በሕጻንነትና በከፈኒሳነት (የበሰለ ሰው ኾነህ) ሰዎችን የምትናገር ስትኾን በቅዱስ መንፈስ (በገብሬል) ባበረታሁህ ጊዜ ፤ ጽሕፈትንና ጥበብንም ተውራትንና ኢንጅልንም ባስተማርኩህ ጊዜ ፣ ከጭቃም የወፍ ቅርጽ ብጤ በፈቃዴ በምትሠራና በውስጧ በምትነፋ በፈቃዴም ወፍ በምትኾን ጊዜ ፤ ዕውርም ኾኖ የተወለደንና ለምጻምንም በፈቃዴ በምታሽር ጊዜ፣ ሙታንም በፈቃዴ (ከመቃብራቸው) በምታወጣ ጊዜ፣ የእስራኤልንም ልጆች በተአምራት በመጣህባቸውና ከእነርሱ እነዚያ የካዱት ይህ ግል ድግምት እንጂ ሌላ አይደለም ባሉ ጊዜ፣ (ሊገድሉህ ሲያስቡህ) ከአንተ ላይ በከለከልኩልህም ጊዜ (ያደግሁልህን ውለታ አስታውስ)፡፡*

የኢየሱስ ተዐምራቶች በሙስሊማኑ አዋልድ በተለይ በአቡ-አሻቅ አህመድ አል-ተዓላቢ (d.1035 ዓ.ም) ስብስቦች ተዘግበዋል፡፡ በቁርኣን እና በአዲስ ከተዘገቡት ተአምራቶች መካከል የሚከተሉት ዋናዎቹ ናቸው፡-[50]

## (1) ኢየሱስ በህጻንነቱ (በአንቀልባ ሳለ) ተናግሯል

ቁርኣን የማርየም ቤተሰቦች ከጋብቻ በፊት ልጅ በመውለዷ ምክንያት ተጨንቃው እንደነበር ይናገራል፡- "የሃሩን እኅት ሆይ! አባትሽ መጥፎ ሰው አልነበረም፡፡ እናትሽም አመንዝራ አልነበረችም' አሏት፡፡ ወደ ርሱም ጠቀሰጭ፡፡ 'በአንቀልባ ያለን ሕጻን እንዴት እናናግራለን!' አሉ፡፡ (ሕጻኑም) አለ 'እኔ የአላህ ባሪያ ነኝ፡፡ መጽሐፍን ሰጥቶኛል ነቢይም አድርጎኛል፡፡' 'በየትም ስፍራ ብሆን ብሩክ አድርጎኛል፡፡ በሕይወትም እስካለሁ ሶላትን በመስገደ ዘካንም በመስጠት አዞኛል፡፡ ለእናቴም ታዛዥ (አድርጎኛል)፡፡ ትዕቢተኛ እምቢተኛም አላደረገኝም፡፡ሰላም በእኔ ላይ ነው፡፡ በተወለድሁ ቀን፣ በምሞትበትም ቀን ፣ ሕያው ኾኜ በምቀሰቀስበትም ቀን፡፡"

## (2) ኢየሱስ ሙታንን አስነስቷል፣ ለምጻሞችን እና ዕውራንን ፈውሷል

ቁርኣን ሲናገር " ዕውር ኾኖ የተወለደን ፣ ለምጸኛንም አድናለሁ፡፡ ሙታንንም አስነሳለሁ" ይላል፡፡ ኤክራማ አክሎም " ኢየሱስ ይህን የተናገረው ነብይ እንደሆነ የሚያረጋግጡ ተአምራቶቹን ለተቃወሙ እስራኤላውያን ነው፡፡ ማንም ሙታንን አላስነሳም፣ ለምጻሞችንና ዕውራንንም አለፈወሰም" በማለት ተአምራቶቹ የመልዕክቱን እርግጠኝነት ምንኛ እንደሚያጸኑ ያስገነዝባል፡፡

ሀዲስ ኢየሱስ ከሞት ያሳነሳቸውን ሰዎች ስም ሳይቀር ዘግቧል፡፡ የሙስሊም ታዋቂ ጸሐፍት ተአምራቶቹ በእግዚአብሔር ዘንድ ብቻ ያሉ መሆናቸውን ይስማሙበታል፡፡

አላህ እንዲህ ይላል ፡-

***ሱረቱ 36፥78-79***

*አጥንቶችን እነርሱ የበሰበሱ ሲኾኑ ሕያው የሚያደርጋቸው ማነው?፡፡ ያ በመጀመሪያ ጊዜ (ከኢምንት) ያስገኛት ሕያው ያደርገታል፡፡*

አል-ሱዩቲ በሱረቱ 3፥48-49 ላይ የኢየሱስን ሙታን ማስነሳት ኃይል አስመልክቶ ሁለት ጉዳዮችን ያወሳል፡፡ አንደኛው የኢየሱስ ወንድም ሲሆን፣ ሌላው የኖኅ ልጅ ሴም ነው፡-

[50] አል- ቡኻሪ፣ IX፣244፡፡

“የእስራኤል ልጆች ወደ ኢየሱስ መጥተው ‘የኖህ ልጅ ሴም ከዚህ ብዙ ሳይርቅ ተቀብሮአል፤ እግዚአብሔር እንዲያስነሳው አድርግ አሉት፡፡’ ኢየሱስም ሴምን ከመቃብር ጠራው እርሱም ከመቃብር ከሽበት ጸጉሩ ጋር ወጣ፡፡ ህዝቡም ‘ወጣት ሆኖ ሳለ ነበረ የሞተው፣ ይህ ሽበት ጸጉር ከወዴት መጣ?’ ጠየቁ፡፡ ሴምም ‘የኢየሱስን ድምጽ ሰማሁ!” አለ፡፡

በእርግጥ ድምጹ በመጨረሻው ቀን ሙታንን ከሞት ያስነሳል፤ ይህ በመጨረሻው ዘመን የሁሉም ነገር ፍጻሜ እና ትንሳኤ አመላካች ነው፡፡ ሱረቱ 73፥17፡- “ ብትክዱ ልጆችን ሽበቶዎች የሚያደርገውን ቀን (ቅጣት) እንዴት ትጠብቃላችሁ፡፡” እስልምና ኢየሱስ በሞት ላይ ስልጣን እንዳለው (ይኸውም ሌላ ማም ነብይ ከእግዚአብሔር ፍቃድ ውጪ ሰዎችን ከሞት እንዳላስነሳ ቁርኣን ይገለጻል) ፣ ድምጹም በኃይል /በስልጣን/ እንደሆነ ያስረግጣል፡፡

ከይሁዲነት ወደ እስልምና የተለወጠው፣ በሙስሊማኑ ታላቅ የታሪክ ሊቅ ተደርጎ የሚወሰደው ዋሂብ ኢብኑ ሙናቢ (732 ዓ.ም) ኢየሱስ ከአምሳ ሺህ በላይ ህሙማን ይከቡት ፣ነገር ግን ሁሉንም ይፈውስ እንደነበር ይናገራል፡፡ ዋሂብ ስለ ኢየሱስ የልጅነት ወቅት ታሪክ የሚከተለውን ዘግቧል ፡፡ “ በሁለት ልጆች መካከል በነበረ ጥል አንዱ ሌላውን ልጅ ይገድላል፡፡ ገዳዩም ልጅ የሚመጣበትን ቅጣት በመፍራት የልጁን አስክሬን በኢየሱስ ጭን ላይ ጥሎ ይሸሻል፡፡ የሟች ልጅ ቤተሰቦችም ኢየሱስን ለፍርድ ያቀርባሉ፡፡ ኢየሱስም እንዳልገደለው ቢናገርም ፣ በደም የተነከረ ልብስ ስለ ተገኘበት ሊገድሉት አሰበ ፡፡ ኢየሱስ የሞተውን ልጅ ከሞት አስነሳው ፣ ከሞት የተነሳው ልጅም ማን እንደገደለው ከተናገረ በኃላ መልሶ ሞተ፤ኢየሱስም ተለቀቀ፡፡”

አል-ካልቢ “ ኢየሱስ ‘ ሕያው ታላቅ አምላክ ሆይ!’ በማለት ሙታንን አስነስቷል፣ ወዳጁን አልዐዛርን አስነስቷል፣ የኖኅ ልጅ ሴምን ከመቃብሩ በትዕዛዝ ቃል ጠርቶ አስነስቷል፣ በሞተ ልጅ አጠገብ የአግዚአብሔርን ስም እየጠራ ሲያልፍ የሞተው ልጅ ከአልጋ ተነስቶ ከቤተሰቡ ጋር ተቀላቅሏል ፡፡”

## (3) ኢየሱስ የተራቡትን መግቧል

በቁርኣን ደቀመዛሙርቱ ኢየሱስን “ የመርየም ልጅ ዒሳ ሆይ! ጌታህን በዕኛ ላይ ከሰማይ ማዕድን ሊያወርድን ይችላልን ?” ብለው እንደጠየቁት ይናገራል፡፡

*ሱረቱ 5 ፥115-118*

*ኢየሱስ መለሰ፦ "ምዕመናን እንደ ኾናችሁ አላህን ፍሩ" አላቸው፡፡ እነርሱም " ከእርሷ ልንበላ ልቦችንም ሊረኩ እውነት ልከንም መኾንህን ልናውቅና በእርሷም ላይ ከመስካሪዎች ልንኾን እንፈልጋለን" አሉ፡፡ ኢየሱስም አለ፦ "ጌታችን አላህ ሆይ! ለእኛ ለመጀመሪያዎቻችንና ለመጨረሻዎቻችን ባዕል (ፍንደቃ) የምትኾንን ከአንተም ተአምር የኾነችን ማዕድ ከሰማይ በእኛ ላይ አውርድ፡፡ ስጠንም ፡፡ አንተ ከሰጪዎች ሁሉ በላጭ ነህና፡፡" አላህም ፦ " እኔ ( ማዕድዋን) በናንተ ላይ አውራጅዋ ነኝ፡፡ በኋላም ከእናንተ የሚክድ ሰው እኔ ከዓለማት አንድንም የማልቀጣውን ቅጣት እቀጣዋለሁ" አለ፡፡*

## (4) ኢየሱስ የተሰወረውን ያውቃል

ቁርኣን የኢየሱስን ንግግር በሱረቱ 3፡49 ላይ ሲገልጽ "የምትበሉትን እና በቤታችሁ የምታደልቡትንም ሁሉ እነግራችኃለሁ፡፡ የምታምኑ እንደኾናችሁ ለእናንተ በዚህ ውስጥ በእርግጥ ተዓምር አለበት፡፡" የተሰወረውን ማወቅ መለኮታዊ አቅም መሆኑን ቁርኣን ያበክራል፡፡ ሱረቱ 6፥59 "የሩቅ ነገርም መክፈቻዎች እርሱ ዘንድ ናቸው፡፤ ከእርሱ በቀር ማንም አያውቃቸውም::" `በአንጻሩ መሐመድ ስለ ራሱ ሲናገር "ሩቅንም (ምስጢር) ማውቅ በነበርኩ ኖሮ ከመልካም ነገር ባበዛሁና ክፉም ነገር ባልነካኝ ነበር" (ሱረቱ 7፥188) ይላል፤ በዚህም የኢየሱስን ሉዐላዊነት መረዳት ይቻላል፡፡

የሙስሊም ጸሓፍት በሱረቱ 3፥49 ላይ ሁለት አሳቦችን ይሰነዝራሉ፡፡ የመጀመሪያው ኢየሱስ ከህጻንነቱ ጀምሮ የተሰወረውን ያውቅ ነበር የሚል ነው፡፡ አል-ሳዲ ህጻኑ ኢየሱስ ለጓደኞቹ ቤተሰቦቻቸው በቤት ምን እያደርጉ ፣ ምን አይነት ምግብ እያዘጋጁላቸው እንደሆነ ይነግራቸው እንደነበር ይገልጻል፡፡ ከዚህ የተነሳ ጎረቤቶቹ እንደጠንቋይ ይቆጥሩት ስለ ነበር ፣ ልጆቻቸውን በአንድ ቤት ሰብስበው እንዲጠበቁ አደረጉ፡፡ ኢየሱስ ልጆቹ ወዳሉበት ቤት መጥቶ የት እንዳሉ ሲጠይቅ እንደሌሉ ይነገረዋል፡፡ "በቤት ውስጥ የሚስቁት ታዲያ እነማን ናቸው?" ብሎ ይጠይቃል:: "አሳማዎች ናቸው" የሚል ነበር መልሱ ፤ ኢየሱስም ልጆችን ወደ አሳማነት እንደቀየራቸው ይነገራል፡፡

ሁለተኛው ነጥብ የተሰወረውን ማወቅ ተአምራዊ ኃይል እንደሆነ ነው፡፡ ከዋክበት አጥኚዎች የከዋክበትን ሁናቴ በማጥናት የሚሰጡት መላምት ብዙ ጊዜ ስህተት አይታጣበትም፡፡ ኢየሱስ ምንም መሳሪያ ሳይጠቀም እና ማንንም ሳይጠይቅ ስህተት ተግኝቶበት አይታወቅም ፤ አብዛኛው ጸሓፍት እንደሚስማሙበት ይህ የመለኮታዊ መገለጥ ውጤት ነው፡፡

## (5) ኢየሱስ የመጨረሻውን ሰዓት ያውቃል

ሀዲስ ስለ መጨረሻው ሰዓት /ዘመን/ ምልክቶች ዝርዝር ይናገራል፤ ሱረቱ 43፥61ም ዒሳ ስለ ሰዓቲቱ (ማወቂያ) በእርግጥ ምልክት ነው" ይላል፡፡ በርካታ የሙስሊም ጸሓፍት ይህ ክፍል ስለ ኢየሱስ የሚናገር እንደሆነ ይስማማሉ፡፡ አል ጃላላን በዚህ ክፍል ላይ አሳቡን ሲያሰፍር "ይህ የመጨረሻው ዘመን የሚኾነው በኢየሱስ መገለጥ ጊዜ" እንደሚሆን ያስገነዝባል፡፡ ዘማኽሻሪ እና ባይዳዊ " ኢየሱስ የመጨረሻው ሰዓት ምልክት እና አብይ ምክንያት " እንደሆነ አሳቡን ያጠናክራሉ፡፡ አል-ራዚ "ኢየሱስ የመጨረሻው ሰዓት የምናውቅበት መንገድ ነው ፤ ሰዓቲቱም በመገለጡ ጊዜ ይሆናል:: እርሱ ራሱ የመጨረሻው ሰዓት ምልክት ወይም ምክንያት ነው፡፡"

ኢየሱስ ከመለኮታዊ ተአምራቱ የተነሳ ስለ መጨረሻው ሰዓት ዕውቀቱም ጭምር እንዳለው በአንዳንዶች ይታመናል፡፡ ሾካኒ " ኢየሱስ ከድንግል መወለዱ እና ሙታንን ማስነሳቱ ፣ በመጨረሻ ትንሳኤ እንዳለ የሚያረጋግጥ እውነት ነው" ይላል፡፡ ኢብኑ ካቲር " እግዚአብሔር በኢየሱስ እጅ ሙታንን በማስነሳት እና ህሙማንን በመፈወስ የገለጣቸው ተዐምራቶች የፍርድ ሰዓት ስለ መኖሩ አይነተኛ ማረጋገጫዎች" እንደሆኑ ይናገራል፡፡ ከላይ የተመለከተው ክፍል ስለ ኢየሱስ የሚናገር ሲሆን፣ ኢየሱስ ከትንሳኤ በፊት እንደሚመጣ ያመላክታል፡፡

ቁርኣን ኢየሱስን በእግዚአብሔር ደረጃ ይመስለዋል፤ የፍጹም ሰብኣዊነት ምሳሌ አድርጎም ይወስደዋል፡፡ ሱረቱ 5፥ 116፣117 " በውስጣቸውም እስካለሁ ድረስ በነርሱ ላይ ተጠባባቂ ነበርኩ፡፡ በተሞላኸኝም ጊዜ (ባነሳኸኝ ጊዜ) አንተ በነሱ ላይ ተጠባባቂ ነበርክ፡፡ አንተም በነገሩ ሁሉ ላይ ዐዋቂ ነህ፡፡" በአንጻሩ መሐመድን አስመልክቶ አላህ የሚናገረውን እናጢን፡- "ከመልዕክተኞች ብጤ የሌለኝ አይደለሁም፡፡ በእኔም በእናተም ምን እንደሚሠራ አላውቅም ፡፡ ወደ እኔ የሚወርደውን እንጂ ሌላን አልከተልም ፡፡ እኔም ግልጽ አስፈሪ እንጂ ሌላ አይደለሁም በላቸው" (ሱረቱ 46፥9)::

የግል ማስታወሻ

# 9

# እስልምና እና የክርስቶስ መለኮትነት

ቁርኣንም ኾነ ሀዲስ የኢየሱስ ሉዐላዊነት ከመሐመድ በላይ መኾኑን ያረጋግጣሉ፡፡ በመካ ለመሐመድ የተገለጹት ቀደምት የቁርኣን ክፍሎች ስለ ክርስትና ፣ ክርስቶስ እና ተከታዮች እጅጉኑ ይናገራሉ ፡፡ በመዲና የመሐመድ የመጨረሻ አገልግሎት ተከትሎ ግን ሁለቱም የማይታረቁ ሀይማኖቶች ኾኑ ፡፡ መሐመድ ክርስቲያኖችን ወደ እስልምና እንዲመጡ ማሳመን ሳይችል ሲቀር፣ የሥላሴ እና የክርስቶስ መለኮትነት አስተምህሮ የፈጣሪን አንድነት መካድ እንደሆነ አድርጎ በመቁጥር ጀመረ፡፡ በዚህም ስለ ክርስትና የሚናገሩ የቁርኣን ክፍሎች ፣ ክርስቲያኖኑ በብዙ አማልእክት አምልኮ እምነት ውስጥ እንዳሉ አድረጎ በመቁጠርና እና በማግነን ለተቃውሞ ጥቅም እንዲውሉ የማድረግ መሰረት ተጣለ፡፡

## I. የክርስቶስ መለኮትነትን የሚቃወሙ የቁርዐን ምንባብ ክፍሎች

የክርስቶስ መለኮትነትን የሚቃወሙ በርካታ የቁርኣን ክፍሎች አሉ፡፡ ክፍሎቹን ከግበረ-መልሶቻቸው አነሆ፡-

### 1. ቁርአን ኢየሱስን በአዳም ይመስለዋል፡፡

*ሱረቱ 3፥59*

*አላህ ዘንድ የዒሳ ምሳሌ እንደ አዳም ብጤ ነው፡፡ ከዐፈር ፈጠረው ፡፡ ከዚያም ለርሱ (ሰው) “ኹን” አለው፤ ኾነም፡፡*

አል-ሳዲ በክፍሉ ላይ አሳቡን ሲያሰፍር፣ አራት ሰዎች ከኒጅራን ወደ መሐመድ መጥተው ስለ ኢየሱስ ሊኖረው የሚችለውን አሳብ እንደ ጠየቁት ያወሳል፡፡ መሐመድም “ እርሱ የአላህ መልዕክተኛ፣ የአላህ መንፈስ እና የአላህ ቃል ነው” ሲል ይመልስላቸዋል፡፡ እነርሱም በቁጣ ቃል፡-“ በፍጹም! እርሱ መለኮት /እግዚአብሔር/ ነው፤ ከአባት ውጪ የተወለደ እንደርሱ አይተሃልን?” ብለው መለሱ ፡፡ መሐመድም ሱረቱ 3፥59 እንደተሰጠው፣ ኢየሱስ እንደ አዳም ሁሉ ከአፈር እንደተፈጠረ መግለጽ ጀመረ፡፡ ይህ አሳብ ከድንግል ስለ መወለዱ ከሚናገሩ ሌሎች የቁርኣን ክፍሎች ጋር ይቃረናል (ሱረቱ 3፥35-55 እና ሱረቱ 19፥1-34)፡፡

## 2. ቁርኣን ኢየሱስን በሐዋሪያነት ይገልጸዋል፡፡

*ሱረቱ 4፥171*

*እናንተ የመፅሐፍ ሰዎች ሆይ በሃይማኖታችሁ  ወሰንን አትለፉ፡፡ በአላህም ላይ እውነትን እንጂ አትናገረ፡፡ የመርየም ልጅ አልመሲ ዒሳ የአላህ መልዕክተኛ ወደ መርየም የጣላት የኹን ቃሉም  ከእርሱ የኾነ መንፈስም ብቻ ነው፡፡ በአላህና በመልዕክተኞቹም እመኑ፡፡ (አማልክት) ሦስት ናቸው  አትበሉም፡፡ ተከልከሉ፤ ለእናንተ የተሻለ ይኾናልና፡፡ አላህ አንድ አምላክ ብቻ ነው፡፡ ለእርሱ ልጅ ያለው ከመኾኑ የጠራ ነው፡፡ በሰማያትና በምድር ያለ ሁሉ የርሱ ነው፡፡ መመኪያም በአላህ በቃ፡፡*

ይህን ክፍል አል-ታባሪ " እናንተ የመጽሐፍ ሰዎች ፣ ከእውነት ወሰን አትለፉ፤ ስለ ኢየሰሱ ከተነገረው እውነት በላይ እትናገሩ፣ አልያ የአላህ ቁጣ በእናንተ ላይ ነው" በሚል ገልጾታል፡፡ ሆኖም ክርስቲያኖኑ የእውነት ወሰን አንደማያልፉ ከቶውን መዘንጋት የለበትም፡፡ ክርስቲያኑ ኢየሱስ ክብሩን በገዛ ፍቃዱ በመተው ፣ የእግዚአብሔር ባሪያ እና ነብይ ሆኖ ወደ ምድር እንደመጣ ነው የሚያምኑት አንጂ፣ በብዙ አማልእክት አያመልኩም፡፡ እግዚአብሔር አንድ ነው፤ ክብርም ሁሉ ለእርሱ!

## 3. ቁርኣን ኢየሱስ ሰው እንጂ አምላክ እንዳልሆነ ይሞግታል፡፡

*ሱረቱ 5፡17*

*እነዚያ አላህ የመርየም ልጅ አል-መሲሕ ነው ያሉ በእርግጥ ካዱ፡፡ የመርየም ልጅ አል-መሲሕን እናቱንም በምድር ያለንም ሁሉ ለማጥፋት ቢሻ ከአላህ ማዳንን የሚችል ማነው በላቸው፡፡ የሰማያትና የምድር የመካከላቸውም ንግሥና የአላህ ብቻ ነው፡፡*

በዚህ ክፍል ምንም ተቃርኖ እንደሌለ ግልጽ ነው፡፡ ክርስቲያኖኑ እግዚአብሔር ክርስቶስ ነው አላሉም፤ ይህ አብንና መንፈስ ቅዱስን ማግለል ነው፡፡ ሆኖም ግን ክርስቲያኖኑ የሚያረጋግጡት ክርስቶስ እግዚአብሔር ነው የሚለውን እውነታ ነው፡፡

## *4.* ቁርኣን ክርስቶስ አምላክ መኾን እንደሚሳነው ያስረግጣል፡፡

*ሱረቱ 5፡75፣76*

*የመርየም ልጅ አል-መሲሕ ከበፊቱ መልዕክተኞች በእርግጥ ያለፉ የኾነ መልዕክተኞች እንጂ ሌላ አይደለም፡፡ እናቱም በጣም እውነተኛ ናት፡፡ (ሁለቱም) ምግብን የሚበሉ ነበሩ፤ አንቀጾችን ለነርሱ (ለከሓዲዎች) እንዴት እንደምናብራራ ተመልከት ከዚያም (ከእውነት) እንዴት እንደሚመለሱ*

*ተመልከት። ከአላህ ሌላ ለእናንተ መጉዳትንና መጥቀምን የማይችልን ትገዛላችሁን በላቸው። አላህም እርሱ ሰሚው ዐዋቂ ነው።*

በዚህ ክፍል ዙሪያ አል-ራዚ የሚከተሉትን ሶስት ነጥቦች ይሰነዝራል፡-

- ኢየሱስ እናት ስላለው ፍጡር ነው፤ በዚህም አምላክ ሊሆን አይችልም።
- ኢየሱስ እና እናቱ ምግብ አስፍልጓቸው ነበር፣ ይኸውም እግዚአብሔር ፈጽሞ ምግብ የሚያስፈልገው አይደለም፤ ስለሆነም ኢየሱስ አምላክ አይደለም።
- ኢየሱስ እና እናቱ ምግብ ተመግበዋል ፣ በዚህም ወደ መጻዳጃ ቤት ሄደዋል፤ ይህን ከአምላክ ማንነት ጋር ማገናኘት እርሱን እንደመስደብ ይቆጠራል።

ሙስሊማኑ ፍጡር የኾነው ማንነት ማንንም አይጎዳም አይጠቅምም ብለው ያስባሉ። ስለዚህም "ለመጉዳትም ለመጥቀምም ምንም ኃይል የሌለውን ማንነት እንዴት ከአምላክ እኩል እናመልካለን?' አይሆዳውያኑ ኢየሱስን እንዴት ሊሰቅሉት ቻሉ? ተጠማሁ ባለ ጊዜ በአፍንጫው ኮምጣጤ ሲያፈሱበት ስለ ምን ፈቀደ? አምላክ እንዲህ አይነቱ ደካማነት እንዴት ሊገኝበት ቻለ? ፈጣሪ በራሱ ማንም የማያስፈልገው ኾኖ ሳለ፣ ኢየሱስ ስለ ምን ለመጸለይ ወደ ቤተ-መቅደስ መሄድ አስፈለገው? ይህ አምላክ የሚያስፈለገው ነብይ እንደሆነ በቂ አስረጂ ነው" ይላሉ።

ለክርስቲያኖኑ የሙስሊማኑ ሙግቶቹ በአስተምህሮተ ትስጉት (Incarnation) የሚመለሱ ናቸው። ኢየሱስ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው ነው። ከኃጢአት በቀር እንደ ሰው አካላዊ ባህሪያትን ይካፈላል፤ እንደ መለኮትነቱ /አምላክነቱ/ ለተቀበሉት ድነትን፣ ለሚቃወሙት ጥፋትን ያደርጋል። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ አማኞች ይናገራል፡-

*1ኛጴጥሮስ 2፥4-10*

*በሰውም ወደ ተጣለ በእግዚአብሔር ዘንድ ግን ወደ ተመረጠ እና ክቡር ወደ ሆነ ድንጋይ ወደ እርሱ እየቀረባችሁ፣ እናንተ ደግሞ እንደ ሕያዋን ድንጋዮች ሆናችሁ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ለእግዚአብሔር ደስ የሚያሰኝ መስዋዕትን ታቀርቡ ዘንድ ቅዱሳን ካህናት እንድትሆኑ መንፈሳዊ ቤት ለመሆን ተሰሩ። በመጽሐፍ ፡- እነሆ የተመረጠ እና የከበረ የማዕዘን ራስ ድንጋይ በጽዮን አኖራለሁ በእርሱም የሚያምን አያፍርም ተብሎ ተፅፎአልና። እንግዲህ ክብሩ ለእናንተ ለምታምኑት ነው፤ ለማያምኑ አናጢዎች የጣሉት ድንጋይ እርሱ የማዕዘን ራስ የእንቅፋትም ድንጋይ የማሰናከያም አለት ሆነ፤ የማያምኑ ስለሆኑ በቃሉ ይሰናከሉበታልና*

*ለዚህ ደግሞ የተመደቡ ናቸው። እናንተ ግን ከጨለማ ወደ ሚደነቅ ብርሃን የጠራችሁን የእርሱን በጎነት እንድትነግሩ የተመረጠ ትውልድ፣ የንጉስ ካህናት፣ ቅዱስ ሕዝብ ለርስቱ የተለየ ወገን ናችሁ፤ እናንተ ቀድሞ ወገን አልነበራችሁም አሁን ግን የእግዚአብሔር ወገን ናችሁ፤ እናንተ ምህረት ያገኛችሁ አልነበራችሁም አሁን ግን ምህረት አግኝታችኃል።*

## 5. ቁርኣን ኢየሱስ ራሱ ከአንድ አምላክ ሌላ እንደሌለ ይመሰክራል።

***ሱረቱ 5፥116***

*አላህም፡- የመርየም ልጅ ዒሳ ሆይ አንተ ለሰዎቹ፡- እኔንና እናቴን ከአላህ ሌላ ሁለት አምላኮች አድርጋችሁ ያዙ ብላሃልን በሚለው ጊዜ (አስታውስ)። ጥራት ይገባህ፤ ለእኔ ተገቢዬ ያልኾነን ነገር ማለት ለኔ አይገባኝም። ብዬው እንደ ኾነም በእርግጥ ዐውቀኸዋል። በነፍሴ ውስጥ ያለውን ሁሉ ታውቃለህ፡፤ ግን አንተ ዘንድ ያለውን አላውቅም። አንተ ሩቆችን ሁሉ በጣም ዐዋቂ አንተ ብቻ ነህና ይላል።*

አል-ራዚ የአላህ ጥያቄ ክርስቲያኖኑ ምንኛ በኑፋቄ እንዳሉ በእማኝነት ይገልጻል። የማሪያማይትስ ኑፋቄ /Mariamites/ ሥላሴ፡- አባትን፣ እናትን እና ልጅን የያዘ መኾኑንም ያስገነዝባል። ኑፋቄው ከቬነስ አምላኪዎች ወደ ክርስትና የመጣ ሲሆን፣ የግሪኩን ቬነስ ጣኦት /አምላክ/ በድንግል ማርያም ስም ተክቷል።

## 6. ቁርዐን ኢየሱስ የፈጣሪ ልጅ እንዳይደል ይሞግታል።

***ሱረቱ 6፥101***

*ለእርሱ ሚስት የሌለችው ሲኾን እንዴት ለእርሱ ልጅ ይኖረዋል ?*

***ሱረቱ 19፥35***

*ለአላህ ልጅን መያዝ አይገባውም ። (ከጎደሉት ሁሉ) ጠራ። ነገር ግን በሻ ጊዜ ለርሱ የሚለውን ‘ኹን’ ነው ወዲያውም ይኾናል።*

***ሱረቱ 19፥88-93***

*‘አልረሕማነም ልጅን ያዘ (ወለደ)’ አሉ። ከባድ መጥፎን ነገር በእርግጥ አመጣችሁ። ከእርሱ (ከንግግራቸው) ሰማያት ሊቀደዱ ፣ ምድርም ልትሰነጠቅ ፣ ጋራዎችም ተንደው ሊወድቁ ይቃረባሉ። ለአልረሕማን ልጅ አልልው ስለ አሉ። ለአልረሕማን ልጅን መያዝ አይገባውም ።*

*በሰማያትና  በምድር ያለው ሁሉ (በትንሣኤ ቀን) ለአልራሕማን ባሪያ ኾነው የሚመጡ እንጂ ሌላ አይደሉም።*

ሱረቱ 6፡101ን በማጠናከር አል-ባይዳዊ “አላህ ልጅ እንዳለው አድርጎ ማሰብ ፣ አላህ ከሴት ጋር ግንኙነት አለው እንደማለት ነው፤ ይህ ደግሞ ፈጽሞ የማይቻል” ነው ሲል ይሞግታል።

አል-ታባሪ እንዲሁ “ልጅ ከአባት እና እናት የሚገኝ ነው፤ አላህ ፈጽሞ አጋር ሴት ሳይኖረው እንዴት ልጅ ሊኖረው ይችላል? እርሱ ሁሉን ፈጥሯል፣ በሁሉ ላይም ዐዋቂ ነው ፤ እንዴትስ ልጅ ይኖረዋልን?

ክርስቲያኖኑ እግዚአብሔር ከሴት ጋር ግንኙነት እንዳለው ፈጽሞ አልተናገሩም፣ አያምኑምም። ወንጌል “ በመጀመሪያው ቃል ነበረ፣ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፣ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ። ኢየሱስ ከእግዚአብሔር ጋር የነበረው ህብረት መንፈሳዊ ነው።

## 7. ቁርኣን ኢየሱስ የአላህ ባሪያ መኾኑን ያስገነዝባል።

*ሱረቱ 19፡30፣31*

*(ሕጻኑም) አለ ‘እኔ የአላህ ባሪያ ነኝ። መጽሐፍን ሰጥቶኛል ነቢይም አድርጎኛል።’ ‘በየትም ስፍራ ብሆን ብሩክ አድርጎኛል። በሕይወትም እስካለሁ ሶላትን በመስገድ ዘካንም በመስጠት አዞኛል።’*

አል-ራዚ ኢየሱስን አስመልክቶ የሚከተሉትን  አራት ነጥቦች ያሰፍራል፡-

- ክርስቲያኖች ኢየሱስ አምላክ ነው በማለታቸው ስተዋል።
- ኢየሱስ ራሱ የፈጣሪ ባሪያ እንደሆነ ተናግሯል።
- ኢየሱስ እናቱ ማርያም ሴተኛ አዳሪ እንደሆነች አስተባብሏል።
- አምላክ ቅዱስ ልጅን ለመጥፎ ሴት አይሰጥም።

ክርስቲያኑ ለሙስሊማኑ ሁለት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን መሰረት በማድረግ ለመሞገት መዳዳት የለባቸውም፡-

የመጀመሪያው የማርያም ልጅ እንደመኾኑ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ባሪያ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ “የሰማነውን ነገር ማን አምኖአል? የእግዚአብሔር ክንድ ለማን ተገልጦአል? .... ከነፍሱ ድካም ብርሃን ያያል፣ ደስም ይለዋል፣ ጻድቅ ባሪያዬም በዕውቀቱ ብዙ ሰዎችን ያጸድቃል፣ ኃጢአታቸውንም ይሸከማል” (ኢሳያስ 53፡11) ይላል።

ሁለተኛው የእግዚአብሔር ባሪያ መኾኑ ከልጅነት ማንነቱ ሊነጥለው አይችልም። የሮሜ ምዕራፍ የመጀመሪያዎቹ ቁጥሮች ይህን አሳብ ይበልጥ ያጠናክራሉ ፡- "ሐዋርያ ሊሆን የተጠራ የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ ጳውሎስ በነብያቱ አፍ በቅዱሳን መጻሕፍት አስቀድሞ ተስፋ ለሰጠው ለእግዚአብሔር ወንጌል ተለየ። ይህም ወንጌል በሥጋ ከዳዊት ዘር ስለ ተወለደ እንደ ቅድስና መንፈስ ግን ከሙታን መነሣት የተነሣ በኃይል የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ ስለ ተገለጠ ስለ ልጁ ነው፤ እርሱም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው" (ሮሜ 1፡1-4)።

## 8. ቁርኣን ኢየሱስ ሰው እንደመኾኑ መለኮትን መካፈል እንደማይችል ይሞግታል።

*ሱረቱ 43፡15*

*ከባሮቹም ለእርሱ ቁራጭን (ልጅን) አደረጉለት ። ሰው በእርግጥ ግልጽ ከሓዲ ነው።*

ለሙስሊማኑ ኢየሱስ " የእግዚአብሔር ልጅ" እንደሆነ መናገር ፈጣሪን አንደ መስደብ፣ የመለኮት አንዱ ክፍል አድረጎ እንደ መቁጥርም ነው የሚወሰደው። በእርግጥ የትኛውም ፍጡር የፈጣሪ አካል /ፈጣሪ/ ሊሆን አይችልም። ክርስቲያኑ አብ እና ወልድ ከመጀመሪያው ጀምሮ አንድ እንደሆኑ ያምናሉ (ዮሐንስ 10፥30)። በኢየሱስ እና በእግዚአብሔር መካከል ልዩ ግንኙነት እንዳለ ቁርኣን ራሱ ይናገራል፤ ኢየሱስ "የአላህ ቃልና መንፈስ" ነው (ሱረቱ 4፥171)::

## II. መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ምን ይላል

ኢየሱስ ልዩ ነው፤ ከማንም ጋርም አይወዳደርም። ወደ ዓለም የመጣበት፣ የኖረበት፣ ያስተማረበት፣ ተአምራቶችን ያደረገበት ፣ ከዚህ ዓለም የተለየበት ፣ ወደ ፊትም ተመልሶ የሚመጣበት ሁናቴ ኹሉ ልዩ ነው። አንዳንዶች ይህ ከቁርኣንም ከሀዲስም የተለየ አንደኾነ ያስባሉ፤ የእስልምና አስተምህሮ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደማንነቱ እንዲረዱት ስለ ማይፈቅድም፣ ሙስሊማኑ በሙላት ሊረዱት አይችሉም ። ኢየሱስ ሊታወቅ የሚችለው መለኮታዊው መገለጥ በኾነው መጽሐፍ ቅዱስ ነው።

*1ኛ ጢሞቴዎስ 3፥16*

*እግዚአብሔርን የመመስል ምሥጢር ያለ ጥርጥር ታላቅ ነው፤ በሥጋ የተገለጠ፣ በመንፈስ የጸደቀ፣ለመላዕክት የታየ፣ በአሕዛብ የተሰበከ፣ በዓለም የታመነ፣ በክብር ያረገ።*

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ከቁርኣን የተለየ ስዕል አለው። ስድስት ወሳኝ እውነታን እንመልከት፡-

## ሀ. መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ ከመወለዱ በፊት ሕያው እንደኾነ ያስገነዝባል።

*ቁርኣን ፣ ሱረቱ 4:171*

*የመርየም ልጅ አል-መሲሕ ዒሳ የአላህ መልዕክተኛ ወደ መርየም የጣላት “ የኹን” ቃሉም ከእርሱ የኾነ መንፈስም ብቻ ነው።*

ሕይወት የሌለው ነገር መስጠት አይቻለውም። ኢየሱስ ከመወለዱ በፊት ለማርያም የተሰጠ ፤ በመጀመሪያም ከእግዚአብሔር ዘንድ የነበረ ነው። “ነገር ግን የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን ከሕግም በታች የተወለደውን ልጁን ላከ፣ አንደ ልጆችም እንሆን ዘንድ ከሕግ በታች ያሉትን ይዋጅ ዘንድ” (ገላትያ 4:4-5)።

መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ በምድር ከመወለዱ በፊት ልጅ ነው ። “እግዚአብሔር አለኝ፦ አንተ ልጄ ነህ ፣ እኔ ዛሬ ወለድሁህ” (መዝሙረ ዳዊት 2፥7፣ ዕብራውያን 1:5)። አባት ልጅ እስካልተወለደ ድረስ አባት፤ ልጅ እስካልተወለደ ድረስ ልጅ ሊሆን አይችልም! ኢየሱስ ልጅ የኾነው ከመጀመሪያው፣ ከመወለዱ በፊት ነው!

## ለ. መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ በስጋ የተገለጠ አምላክ እንደኾነ ያበክራል።

ኢየሱስ በአንድ ጊዜ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው ነው። እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ ተገልጧል ፦ “በእርሱ የመለኮት ሙላት ሁሉ በሰውነቱ ተገልጦ ይኖራልና” (ቈላስይስ 2፥9)።

*ዕብራውያን 1፥1-3*

*ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ዓይነትና በብዙ ጎዳና ለአባቶቻችን በነብያት ተናግሮ ሁሉን ወራሽ ባደረገው ደግሞም ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ በዚህ ዘመን መጨረሻ ለእኛ ተናገረን ፣እርሱም የክብሩ መንጸባረቅ እና የባሕርዩ ምሳሌ ሆኖ ሁሉን በሥልጣኑ ቃል እየደገፈ ፣ ኃጢአታችን በራሱ ካነጻ በኃላ በሰማያት በግርማው ቀኝ ተቀመጠ።*

ኢየሱስ በመለኮታዊ ኃይሉ ተአምራቶችን አድርጓል። እንደሰው ተመግቧል፣ ጠጥቷል ፣ተኝቷል። ኢየሱስ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው ስለኾነም ፦ እንደ አምላክም እንደ ሰውም ተናግሯል። ለተቃዋሚዎቹ ሲናገር “ነገር ግን እላችኃለሁ ከእንግዲህ ወዲህ የሰው ልጅ በኃይል ቀኝ ሲቀመጥ በሰማይም ደመና ሲመጣ ታያላችሁ” (ማቴዎስ 26፡ 64) ይላል። ለደቀመዝሙሩ ሲናገርም ይህን አለ ፦ “አንተ ፊልጶስ ይህን ያህል ዘመን ከእናንተ ጋር ስኖር አታውቀኝምን ? እኔን ያየ አብን አይቶአል፤ እንዴትስ አንተ ፦ አብን አሳየን ትላለህ?” (ዮሐንስ 14:9)።

ኢየሱስ አምላክ ወይም ሰው ነው የሚል ኣሳብ ከፊል እውነት ነው፡፡ እውነታው ኢየሱስ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው ነው ፤ ሁለቱ ባህሪያት በአንዱ ማንነት ውስጥ አለ፡፡ ለምሳሌ፡-

*ማርቆስ 4፥35-41*

*በዚያም ቀን በመሸ ጊዜ፡- ወደ ማዶ እንሻገር አላቸው፡፡ ሕዝቡንም ትተው በታንኳ እንዳያው ወሰዱት፣ ሌሎች ታንኳዎችም ከእርሱ ጋር ነበሩ፡፡ ብርቱ ዐውሎ ነፋስም ተነሣ ውኃ በታንኳይቱ እስሊሞላ ድረስ ማዕበሉ በታንኳይቱ ይገባ ነበር፡፡ እርሱም በስተኋላዋ ትራስ ተተንርሶ ተኝቶ ነበር፣ አንቅተውም ፡- መምህር ሆይ ስንጠፋ አይደገድህምን? አሉት፡፡ ነቅቶም ነፋሱን ገሠጸው፣ ባሕሩንም ፡- ዝም በል ጸጥታም ሆነ ፡፡ እንዲህ የምትፈሩ ስለ ምን ነው? እንዴትስ እምነት የላችሁም? አላቸው፡፡ እጅግም ፈሩና፡- እንግዲህ ነፋስም ባሕርም የሚታዘዙለት ይህ ማን ነው? ተባባሉ፡፡*

ኢየሱስ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው ነው፤ "ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬ እስከ ለዘላለምም ያው ነው" (ዕብራውያን 13፡8)፡፡ ዮሐንስ እንደሚልም እርሱ "ስጋ የለበሰ ቃል" ነው፡-

*ዮሐንስ 1፡1-4፣14*

*በመጀመሪያው ቃል ነበር፣ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር፣ቃልም እግዚአብሔር ነበር፡፡ ይህ በመጀመሪያው በእግዚአብሔር ዘንድ ፡፡ ሁሉ በእርሱ ሆነ፣ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም፡፡ በእርሱ ሕይወት ነበረች፣ሕይወትም የሰው ብርሃን ነበረች፡፡.... ቃልም ሥጋ ሆነ፣ ጸጋንና እውነትንም ተሞልቶ በእኛ አደረ ፣ አንድ ልጅም በአባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር የሆነውን ክብሩን አየን፡፡*

## ሐ. መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ በፍቃዱ " ስጋን እንደ ለበሰ" ፣ በትንሳኤም ወደ መለኮታዊ ክብሩ እንደተመለሰ ይናገራል፡፡

ሰው አምላክ አልኾነም፣ አምላክ ሰው እንጂ! ኢየሱስ ሰው የኾነው በገዛ ፍቃዱና ስልጣኑ ነው፡- "ነፍሴን ደግሞ አነሣት ዘንድ አኖራለሁና፣ ስለዚህ አብ ይወደኛል ፡፡ እኔ በፈቃዴ አኖራታለሁ እንጂ ከእኔ ማንም ዐይወስዳትም ፡፡ ላኖራት ሥልጣን አለኝ፣ ደግሞም ላነሣት ሥልጣን አለኝ፡፡ ይህችን ትዕዛዝ ከአባቴ ተቀበልሁ" (ዮሐንስ 10፡17፣18)፡፡

ኢየሱስ ወደ እኛ ጊዜና ቦታ ሁናቴ የመጣው የመቤዠትን ሥራ ለመግለጥ ነው፡፡ ይህን በፈጸመ ጊዜ " እኔ ላደርገው የሰጠኸኝን ሥራ ፈጽሜ በምድር አከበርሁህ ፤ አሁንም አባት ሆይ ዓለም ሳይፈጠር በአንተ ዘንድ በነበረኝ ክብር አንተ በራስህ ዘንድ አክብረኝ" ሲል ተናግሯል (ዮሐንስ 17፡4፣5)፡፡

ኢየሱስ “ ስጋ የለበሰበት” ኹነት ክቡሩን ከፍ አድርጎለታል፤ አምላክ ሰው ኾኖ የተወለደበት፣ ራሱንም በሰው መልክ ትሑት ያደረገበት ምስጢር ከሰው መረደት በላይ ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ይህ እውነት በእግዚአብሔር ፍቃድ የተከናወነ መሆኑን ያስረግጣል፡-

***ፊልጵስዩስ 2፥5-11***

*እርሱ በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን መቀማት እንደሚገባው ነገር አልቆጠርም ፣ ነገር ግን የባሪያን መልክ ይዞ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ባዶ አደረገ፣ በምስሉም እንደ ሰው ተገኝቶ ራሱን አዋረደ፣ለሞትም ይኸውም የመስቀል ሞት እንኳ የታዘዘ ሆነ ፤ በዚህ ምክንያት ደግሞ እግዚአብሔር ያለ ልክ ከፍ ከፍ አደረገው፣ ከስምም ሁሉ በላይ ያለውን ስም ሰጠው ፤ይህም በሰማይና በምድር ከምድርም በታች ያሉት ሁሉ በኢየሱስ ስም ይንበረከኩ ዘንድ መለሰም ሁሉ ለእግዚአብሔር አብ ክብር ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደሆነ ይመሰክር ዘንድ ነው፡፡*

ኢየሱስ በምድር ሳለ በሰው መልክ ቢመላለስም እንኳ ፣ መለኮታዊ ክብሩ አልተሰወረም ፡-

***ማቴዎስ 16፡13-18***

*ኢየሱስም ወደ ፊልጶስ ቂሣሪያ አገር በደረሰ ጊዜ ደቀመዛሙርቱን ፡- ሰዎች የሰውን ልጅ ማን ይሉታል? ብሎ ጠየቀ፡፡ እነርሱም፡- አንዳንዱ መጥምቁ ዮሐንስ፣ ሌሎችም ኤልያስ ፣ ሌሎችም ኤርሚያስ ወይም ከነብያቱ አንዱ ነው ይላሉ አሉት ፡፡ እርሱም ፡- እናንተስ እኔን ማን እንደ ሆንሁ ትላላችሁ? አላቸው፡፡ ሰምዖን ጴጥሮስም መልሶ ፡- አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ አለ፡፡ ኢየሱስም መልሶ በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልህምና ብጹዕ ነህ፡፡ እኔም እልሃለሁ ፣ አንተ ጴጥሮስ ነህ ፣ በዚህችም ዓለት ላይ ቤተክርስቲያኔን እሠራለሁ፣ የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም፡፡*

## መ. መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ ስለ አምላክነቱ የሰጠውን ምስክርነት ያጸናል፡፡

የኢየሱስ ደቀመዛሙርት ምስክርነት ለመቀበል የሚዳዳቸው ሙስሊማኑ ኢየሱስ ስለ ራሱ የሰጠውን ምሰክርነት ልብ ሊሉ ይገባል፡-

***ማርቆስ14፥61-64***

*ደግሞ ሊቀ ካህናቱ ጠየቀውና፡- የቡሩክ ልጅ ክርስቶስ አንተነህን? አለው፡፡ ኢየሱስም እኔ ነኝ የሰው ልጅም በኃይል ቀኝ ሲቀመጥ በሰማይም ደመና ሲመጣ ታያላችሁ አለ፡፡ ሊቀ ካህናቱም ልብሱን ቀደደና ፡- ከእንግዲህ ወዲህ ምስክሮች ምን ያስፈልገናል? ስድቡን ሰማችሁ ምን ይመስላችኃል? አለ ፡፡ እነርሱም ሁሉ ፡- ሞት ይገባዋል ብለው ፈረዱበት፡፡*

*ዮሐንስ 5፥17፣18*
*ኢየሱስ ግን አባቴ እስከ ዛሬ ይሠራል፣ እኔም ደግሞ እሠራለሁ ብሎ መለሰላቸው ። እንግዲህ ሰንበትን ስለ ሻረ ብቻ አይደለም ፣ ነገር ግን ደግሞ ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር አስተካክሎ ፦ እግዚአብሔር አባቴ ነው ስላለ ፤ ስለዚህ አይሁድ ሊገድሉት አብዝተው ይፈልጉት ነበር።*

*ዮሐንስ 8፥56-59*

*አባታችሁ አብርሃም ቀኔን ያይ ዘንድ ሐሤት አደረገ፣ አየም ደስም አለው። አይሁድም ገና አምሳ ዓመት ያልሆነህ አብርሃም አይተሃልን? አሉት ። ኢየሱስም ፦ እውነት እውነት እላችኃለሁ ፣ አብርሃም ሳይወለድ እኔ አለሁ አላቸው። ስለዚህ ሊወግሩት ድንጋይ አነሡ፣ ኢየሱስ ግን ተሰወራቸው፣ ከመቅደስም ወጥቶ በመካከላቸው አልፎ ሄደ።*

ቅዱስ ኦገስቲን ራሱን እግዚአብሔር ብሎ የሚጠራ ሰው የአእምሮ ህመምተኛ ወይም ውሸታም ወይም እውነት ተናጋሪ ሊሆን እንደሚችል ይናገራል፡ ሙስሊማኑ ኢየሱስ ከአምላክ /ፈጣሪ/ ጋር እኩል እንደኾነ የሰጠውን ምስክርነት በአንክሮ ሊመለከቱት ይገባል ፡

## ሠ. መጽሐፍ ቅዱስ የኢየሱስ መለኮትነት በቃልም በሥራም የጸና መኾኑን ያስረግጣል።

ኢየሱስ በሚገልጣቸው ተአምራቶች ራሱን በብዙ መንገድ አስተዋውቋል ፦

- ***ዮሐንስ 6፥35*** ፦ *"ኢየሱስም አላቸው ፦ የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ ፣ ወደ እኔ የሚመጣ ከቶ አይራብም ፣ በእኔ የሚያምን ሁል ጊዜ ከቶ አይጠማም።"* ይህ የሆነው በአምስት እንጀራ እና በሁለት አሳ 5000 ሺህ ሰዎችን ከመገበ በኃላ ነው።
- ***ዮሐንስ 8፥12*** ፦ *" ኢየሱስ ፦ እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ ፣ የሚከተለኝ የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ በጨላማ አይመላለስም ብሎ ተናገራቸው።"* ከዚያም ከመወለዱ ጀምሮ ዕውር የነበረውን ሰው አይን አበራ።
- ***ዮሐንስ 11፥25፣26*** ፦ " ኢየሱስም ትንሣኤ እና ሕይወት እኔ ነኝ የሚያምንብኝ ቢሞት እንኳ ሕያው ይሆናል፤ ሕያው የሆነም የሚያምንብኝም ሁሉ ለዘላለም አይሞትም።" ይህን ከተነጋረ በኃላም አላዛርን ከሞት አሰነሳ።

## ረ. መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ መኾኑን ይመሰክራል።

ሙስሊማኑ ማንንም " የእግዚአብሔር ልጅ" ብሎ መጥራትን በጽኑ ይቃወማሉ ፤ ምክንያቱም አምላክ የትዳር አጋር እንዳለው ተደርጎ ስለሚታሰብ ነው። አምላክን "አባት" ብለውም አይጠሩም።

***ሱረቱ 2፥116***

*አላህም ልጅ አለው አሉ። (ከሚሉት) ጥራት ተገባው። አይደለም በሰማያትና በምድር ያለው ሁሉ የርሱ ነው። ሁሉም ለርሱ ታዛገች ናቸው።*

***ሱረቱ 39፡4***

*አላህ ልጅን መያዝ በፈለገ ኖሮ ከሚፈጥረው ውስጥ የሚሻውን ይመርጥ ነበር። ጥራት ተገባው ። እርሱ አሸናፊው አንዱ አላህ ነው።*

የኢየሱስ ልጅነት መንፈሳዊ ግንኙነት አንጂ አካላዊ አይደለም። አባት የሚለው ምሳሌያዊ ብሂል በዕለት ኑሯችን የምንጠቀምበት ጊዜ በርካታ ነው። ለምሳሌ ፦ የሱዳንና ግብጽ ሕዝቦች " የአባይ ልጆች" ተብለው ይጠራሉ። "አባት" የሚለው ስያሜ በአረብኛ ሕጋዊውንም ሆነ አካላዊውን አባትነት ያመላክታል። ቁርኣን የመሐመድ ጠላት የሆነው አቡ- ለሀብ " የመንቀልቀል አባት" ሲል ይሰይመዋል (ሱረቱ 111)። በተመሳሳይ ድሆች " የመንገድ ልጆች" (ሱረቱ 2፥177) ተብለዋል። በገነት እንደተጠበቀ የሚነገረው ጽላት ለሦስት ያህል ጊዜ ኡም አል-ኪታብ :- "የመጽሐፍ እናት" ተብሏል (ሱረቱ 3፥7፣ 13፥39 እና 43፥4)።

ሱረቱ 93፥6-8 አላህ ለመሐመድ ሲናገር "የቲም ኾነህ አላገኝህምና አላስጠጋህምን? (አስጠግቶሃል)" ይላል። መዝሙረ ዳዊት 68፡5ም እንዲሁ "እግዚአብሔር የድሀ አደጎች አባት" መኾኑን ያስረግጣል።

የእግዚአብሔር አባትነት በበርካታ የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት ተገልጿል (ምሳሌ 23፥26፣ ሆሴዕ 11፥1፣ መዝሙረ ዳዊት 68፥5፣ 103፥13)። ዕብራውያኑ እንደ ሙስሊማኑ በመለኮታዊ አንድነቱ ዙሪያ ያላቸው አረዳድ ተቃርኖአዊ አይደለም ። ቁርኣን ኢየሱስ " የማርያም ልጅ" በሚል ለሃያ ሁለት ጊዜ መጠራቱን ይገልጻል (ሱረቱ 2፥87፣253፣3፥45፣4፥157፣171፣5፡17) ፤ ይኸውም ከእናቱ ጋር ያለውን ግንኙነት ያሳያል። ከአባቱ ጋርም እንዲሁ ያለውን ህብረት ለማመላከት የእግዚአብሔር ልጅ መጠሪያን ይጠቀማል ። የኢየሱስ ትስጉነት (ሰጋ መልበስ) አመክንዮአዊ ነው!

ይህ መጠሪያ በኢየሱስ እና በሰማያዊ አባት መካካል ያለውን ግንኙነት በብዙ መልኩ ያስገነዝባል፡-

- አይሁዶች " የእግዚአብሔር ልጅ" ምንነት እና መጠሪያ " ከእግዚአብሔር ጋር እኩል" መኾን አድርገው ነው የሚወስዱት ፡፡ " እንግዲህ ሰንበትን ስለ ሻረ ብቻ አይደለም ፣ ነገር ግን ደግሞ ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር አስተካክሎ ፡- እግዚአብሔር አባቴ ነው ስላለ፣ ስለዚህ አይሁድ ሊገድሉት አብዝተው ይፈልጉት ነበር" ( ዮሐንስ 5፥ 18)፡፡
- " ልጅ" የአባትን ባህሪያትን ይዟል፡፡ " መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው አንድ ስንኳ የለም፣ በአባቱ እቅፍ ያለ አንድ ልጁ እርሱ ተረከው" ( ዮሐንስ 1፥ 18)፡፡
- "ልጅ" የአባት ተልዕኮ ወካይ ነው፡፡ አግዚአብሔር አብ የመቤዠት ሥራውን እንዲፈጽም ልጁን እንደላከው መገንዘብ አያዳግትም ( ዮሐንስ 19፥30)፡፡

### ሰ. መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ በተከታዮች ዘንድ እንደሚኖር ይናገራል፡፡

ክርስትና የሀይማኖት መግለጫዎች እና ሥርዐቶች ደርዝ ብቻ አይደለም፡፡ ክርስትና ኢየሱስ አዳኝና ቤዛ አድርገው በተቀበሉት ሰዎች ልብ ሕያው ኾኖ የሚኖረው ህይወት ነው፡፡ ሐዋሪያው ጳውሎስ ይህን ያረጋግጣል ፡- " እኔም አሁን ሕያው ሆኜ አልኖርም ፣ ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል ፣ አሁንም በሥጋ የምኖርበት ኑሮ በወደደኝና ስለ እኔ ራሱን በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለ እምነት የምኖረው ነው"( ገላትያ 2፡20)፣ " ለእኔ ሕይወት ክርስቶስ ነው" (ፊልጵስዩስ 1፡21) ፡፡ ኢየሱስ ሕያው ነው፤ " ራስህን ግለጠልኝ" ብሎ ለሚማጸነው ሁሉ ራሱን ይገልጣል፡፡

## III. ኢየሱስ አንደ ሰው ስጋ መልበሱን ሙስሊማኑ እንዲረዱት ማስቻል

እስልምና አምላክ ሰው ኾነ የሚለውን አሳብ በእጅጉ የሚቃወሙት ስለ ፈጣሪ ልዑላዊነት ባላቸው ጽኑ እምነት መሰረት ነው፡፡ እንደ ሰው አምላክ ስጋ መልበሱን ማስረዳት ፈጽሞ የፈጣሪን ምንነት እና ባህሪ አይቃረንም፡፡

### 1. የዕለታዊ ሕይወት ምሳሌያዊ ገለጻ

ቤተክርስቲያን ድንጋይ እና ቁጥቋጦ የሞላበትን መሬት መግዛት አሰበች እንበል፡፡ አባላቶቿም መሬቱን በአትክልቶች ለማልማት ከቀዶ ጠጋኝ ሀኪም እና መጋቢ መሪዎች ጭምር ፈቀዱ ፡፡ በጎ ፍቃደኛ ሰራተኞቹ ቦታውን የማልማት ስራ አጠናቀቅው እስኪ መለሱም

፣ የለበሱት የስራ ልብስ ትክክለኛ ማንነታቸውን ሊገልጽ አይችልም። ምናልባት መጋቢው በስራው ወቅት እጁ ቢቆረጥ አንኳ ፣ ቀዶ ጠጋኝ ሀኪሙ የሙያ ልብሱ በአጠገቡ ሳይኖር መጋቢውን እንዳያክም አላገደውም ። በአጠቃለይ የበነ ፍቃድ ስራው አንቅስቃሴ የተሳታፊዎችን ትክክለኛ ማንነት ማጥፋት አይችልም፤ ምክንያቱም ሁሉም ማንነታቸውን፣ ክብራቸውን፣ ሙያቸውን እና ፍቃዳቸውን በመተው ነበር ስራውን የሰሩት!

ኢየሱስ ለኃጢአታችን መስዋአት ለመኾን የሰው ስጋን ለብሷል ፤ የመበዤቱን ስራ በመፈጸመ ጊዜ ወደ ዘላለማዊ ክብሩ ተመልሷል። ራሱ ሲናገር እንዲህ ይላል ፦ “ነፍሱን ስለ ወዳጆቹ ከመስጠት ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም ። …እናንተ ወዳጆቼ ናችሁ” (ዮሐንስ 15፥13፣14)።

## 2. ሁለት ቁርኣናዊ ምሳሌዎች

ሱረቱ 28፡29፣30 “ ሙሳም ጊዜውን በጨረሰና ከቤተሰቦቹ ጋር በኼደ ጊዜ ከጡር ተራራ ጎን እሳትን አየ። ለቤተሰቡ (እዚህ) ‘ቆዩ። እኔ እሳትን አየሁ። ከእርሷ ወሬን ወይም ትሞቁ ዘንድ ከእሳት ትታግን አመጣላችኃለሁ’ አለ ። በመጣትም ጊዜ ከሸለቆው ቀኝ ዳርቻ ከዛፊቱ በኩል በተባረከችው ስፍራ ውስጥ ‘ሙሳ ሆይ! እኔ የዓለማት ጌታ አላህ እኔ ነኝ’ በማለት ተጣራ።” ይኸው ተመሳሳይ ታሪክ በሱረቱ 20፥9-12ም ይገኛል። ፈጣሪ በሸሎቆው ቀኝ ዳርቻ ከዛፊቱ በኩል ለሙሳ ከተገለጠ፣ እንዴት በኢየሱስ በኩል አይገለጥም?

ሌላው በሱረቱ 6፥9 የሚገኘው የአላህ ቃል ነው ፦ “ (መልዕክተኛውን) መልአክም ባደረግነው ኖሮ ወንድ (በሰው ምስል) ባደረግነው ነበር። በእነርሱም ላይ የሚያመሳስሉትን ነገር ባመሳሰልናባቸው ነበር።” መሐመድ ዋግዲ ይህን ክፍል “ መሐመድን መልዐክ አድርገን ፈጥረነዋልን፤ ሰዎች ይረዱትም ዘንድ ሰው አድረገን ፈጥረነዋል” በሚል አስቀምጦታል። በተመሳሳይ ኢየሱስ የድነት መልካም ዜና ሊያበስረን በሰው መልክ ተገልጧል።

የግል ማስታወሻ

# 10

## የመጽሐፍ ቅዱስ ተዓማኒነት እንዴት ሊረጋገጥ ይቻላል

ኹሉም ሀይማኖት አስተምህሮው ስልጣናዊ እና ተዐማኒ መኾኑን ያውጃል ። አይሁድ፣ ክርስትና እንዲሁም እስልምና የአምላክ መገለጥ የኾነው ቅዱስ መጽሐፍ እንዳላቸው ይታመናል ። የክርስቲያኑ እምነት በብሉይ እና አዲስ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት መገለጥ ላይ የተመሰረት ነው። አስተምህሮአችን እውነተኛ እንዲኾን በቅዱሳት መጻሕፍት መመሰረቱን እና ተዐማኒ መኾኑን ማረጋገጥ ይኖርብናል ። የክርስቲያኑ እና ሙስሊማኑ አስተምህሮ በተለያዩ ቅዱሳት መጻሐፍት በመመስረቱ በመካካላቸው አንዳች የአስተምህሮ ተቃርኖ መኖሩ ሊያስደንቅ አይገባም። ሙስሊማኑ የሚሟገቱባቸው ዐብይት ነጥቦች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡-

- የመጽሐፍ ቅዱስ ተዐማኒነት።
- የክርስቶስ መለኮትነት።
- የመስቀሉ ሥራ / ስቅለት/ ገሃዳዊነት።
- አስተምህሮተ ሥላሴ።

ክርስቲያኑ በየቤተ-እምነቱ በመካከላቸው የማይስማሙባቸው ጉዳዮች ከሙስሊማኑ ይልቅ የበዛ ነው። በካቶሊኮች፣ ፕሮቴስታንቶች እና ኦርቶዶክሶች መካከል ባሉ ልዩነቶች ዙሪያ እንደጻፈው “ እስልምና የሚሞግትባቸው ርዕሰ ጎዳዮች ሦስቱም ሀይማኖቶች ግን ይስማሙበታል፤ በመጽሐፍ ቅዱስ ተዐማኒነት፣ በኢየሱስ እንደ ሰው ስጋ መልበስ፣ መሰቀል፣ መሞት፣ መቀበር፣ ከሞት መነሳት ብሎም በአስተምህሮተ ሥላሴ በሁሉም ዘንድ ስምምነት አለ።”

ሙስሊማኑ አንደ ሁል ጊዜው የክርስትና አስተምህሮ መሰረት የኾነው መጽሐፍ ቅዱስ ተዐማኒነት አንደ ሌለው አድርገው ይቆጥራሉ። ስለሆነም መጽሐፍ ቅዱስ ትክክለኛ እና ተዐማኒ የእግዚአብሔር መገለጥ መኾኑን ፣ ለቅዱሳኑ ነብያት እና ሐዋሪያት መሰጠቱንም ማስገንዘብ ያስፈልጋል። የሙስሊማኑ ሙግት በአመዛኙ ግንዛቤ ከማጣት እና ትክክለኛውን ባለመረዳት የመነጨ ነው።[51]

---

[51] በዚህ ምዕራፍ በርዕሰ ጉዳዩ ላይ ተቃሚው ምንጭ ጆሽ ሜክ ዳዉል ነው፣ ምክንያት የሚሻ ፍርድ( ሳን በርናሪዲኖ ፡ - ህይወት በዚህ አሳታሚዎች ኢንክ. 1972)።

## I. የ“መገለጥ” የተለያየ እሳቤ በክርስትና እና እስልምና

መገለጥ በይሁዲ እና ክርስትና ሁለት መልክ አለው፡- መለኮታዊ እና ሰዋዊ፡፡ ሐዋሪያው ጴጥሮስ ይህን ያስገነዝባል ፡- “ ትንቢት ከቶ በሰው ፍቃድ አልመጣምና ፣ ዳሩ ግን በእግዘኢብሔር ተልኮው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ” (የሁለተኛው መልዕክት ጴጥሮስ 1:21)፡፡ የመገለጥ ሂደትን የሚነግሩን ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች፡-

*ዘዳግም31፥24-26*

*እንዲህም ሆነ ሙሴ የዚህን ሕግ ቃሎች በመጽሐፍ ከጻፈ ከፈጸመም በኃላ ሙሴ የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን ታቦት የሚሸከሙትን ሌዋውያንን እንዲህ ብሎ አዘዘ፦ ‘ይህን መጽሐፍ ውሰዱ፣ በዚያም በእናንተ ላይ ምስክር እንዲሆን በአምላካችሁ በእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ታቦት አጠገብ አኑሩት”*

*ኤርሚያስ36፥1፣32*

*አንዲህም ሆነ በይሁዳ ንጉሥ በኢዮስያስ ልጅ በኢዮአቂም በአራተኛው ዓመት ይህ ቃል ከእግዚአብሔር ዘንድ ወደ ኤርሚያስ መጣ፡፡ ኤርሚያስ ሌላ ክርታስ ወሰደ ለኔርያም ልጅ ለጸሐፊው ለባሮክ ሰጠው፤ እርሱም የይሁዳ ንጉሥ ኢዮአቂም በእሳት ያቃጠለውን የመጽሐፉን ቃል ሁሉ ከኤርሚያስ አፍ ጻፈበት፣ ደግሞም እንደ ቀድሞው ያለ ቃል ብዙ ቃል ተጨመረበት፡፡*

*ሉቃስ1፥1-4*

*የከበርህ ቴዎፍሎስ ሆይ ፣ ከመጀመሪያው በዓይን ያዩትና የቃሉ አገልጋዮች የሆኑት እንዳ ስተላለፉልን በእኛ ዘንድ ስለ ተፈጸመው ነገር ብዙዎች ታሪክን በየተራው ለማዘጋጀት ስለ ሞከሩ እኔ ደግሞ ስለተማርኸው ቃል እርግጡን እንድታውቅ በጥንቃቄ ሁሉን ከመጀመሪያው ተከትዩ በየተራው ልጽፍልህ መልካም ሆኖ ታየኝ፡፡*

በተመሳሳይ በራዕይ መጽሐፍ ዮሐንስ የእግዚአብሔርን መልዕክት አንደጻፈ ያረጋግጣል “በኤፌሶን ወዳለው ወደ ቤተ ክርስቲያን መልአክ አንዲህ ብለህ ጻፍ” (ራዕይ 2፥1፣3፥14፣ 14፥13)፡፡

ሁሉም ቅዱሳን ጸሓፍት እግዚአብሔር ስለሰጣቸው መገለጥ ሙሉ መረዳት ነበራቸው፡፡ አንደ ዳዊት እና ሰለሞን ያሉቱ የእግዚአብሔርን መገለጥ በግጥም መልክ ሲዘግቡ፣ ሌሎቹ በትረካ መልክ ጽፏል፡፡ አንዳንዶች በርቱዕ አንደበት፣ ሌሎች ደግሞ በተራ ቋንቋ አንዲጽፉ ሆኗል፤ እግዚአብሔር የሁሉንም ተሰጥዖ ተጠቅሟል፣ ጸሓፍቱን እና መልዕክቱን ከስህተት ጠብቋል፡፡

በአንጻሩ ሙስሊማኑ ቁርኣን ከዘላላም ጀምሮ በከበረ ድንጋይ በተጠበቀው ሰሌዳ ላይ በአላህ ዘንድ ተጠብቆ (አላህ አል- ማፉዙ) መኖሩን ይሞግጻሉ፡፡ ከሰማይ ሰማያት በሌሊት (ሌይሌታት አል- ኺዲርል) ታላቁ ምሽት ቁርኣን እንደ ወረደ ይናገራሉ፡፡ ቁርኣን ሲናገር " እኛ (ቁርኣኑን) በመወሰኛይቱ ሌሊት አወረድነው፡፡ መወሰኛይቱም ሌሊት ምን እንደ ኾነች ምን አሳወቀህ? መወሰኛይቱ ሌሊት ከሺህ ወር በላጭ ናት፡፡ በርሷ ውስጥ መላዕክትና መንፈሱ በጌታቸው ፈቃድ በነገሩ ሁሉ ይወርዳሉ፡፡ እርስዋ እስከ ጎህ መውጣት ድረስ ሰላም ብቻ ናት" ይላል (ሱረቱ 97፥1-5)፡፡ ቁርኣን ለሃያ ሦስት ዓመታት ለመሐመድ ደረጃ በደረጃ የተሰጠው ሲሆን፣ በአመዛኙ የመሐመድ ድርሻ የለበትም፡፡ አላህ ለመሐመድ እንደህ ይላል ፡- " በእርሱ (በቁርኣን ንባብ) ልትቸኩል ምላስህን በእርሱ አታለውስ፡፡ (በልብህ ውስጥ) መሰብሰቡ እና ማንበቡ በእኛ ላይ ነውና፡፡ ባነበብነውም ጊዜ (ከላቀ በኃላ) ንባቡን ተከተል፡፡ ከዚያም ማብራራቱ በእኛ ላይ ነው" (ሱረቱ 75፥16-19)፡፡

እንደ ሙስሊማኑ እምነት መሐመድ አላህ የሰጠውን ነው ያስተለለፈው፤ ሬዲዮ ከጣቢያው ከማስተላለፉ ውጪ ሚና እንደሌለው ሁሉ በመገለጡ ሂደት መሐመድ ምንም ድርሻ አንዳች ድርሻ አልነበረውም፡፡ የእርሱ ዐብይ ሚና መልዕክቱን በጥራት ማስተላለፉ ላይ ነበር፡-" ቁርኣንም ባነበብህ ጊዜ እርጉም ከኾነው ሰይጣን በአላህ ተጠበቅ" (ሱረቱ 16፥98)፡፡

## II. እግዚአብሔር መገለጡን እንዲዛባ አልፈቀደም

መጽሐፍ ቅዱስም ሆነ ቁርኣን አምላክ መለኮታዊውን መገለጥ ከመዛባት እንደጠበቀው ያስረግጣሉ፡፡

ቁርኣን ሲናገር "የአላህንም ንግግሮች ለዋጭ የለም" (ሱረቱ 6፥34) ፣ እኛ ቁርኣንን እኛው አወረድነው፡፡ እኛም ለእርሱ ጠባቂዎች ነን" (ሱረቱ 15፥9)፡፡ "አወረድነው" የሚለው ቁርአንን ሲሆን መጽሐፍ ቅዱስን አካቶ ፈጣሪ ለሰው ዘር በሙሉ የተናገረውን የሚወክል እንደሆነ ይነገራል፡፡

"ከአንተም በፊት ወደ እነሱ ወሕይን (ራዕይን) የምናወርድላቸውን ሰዎችን እንጂ ሌላን አልላክንም ፡፡ የማታዉቁም ብትኾኑ የዕውቀትን ባለ ቤቶች ጠይቁ፡፡ በግልጽ ማስረጃዎችና በመጻሕፍት (ላክናቸው)፡፡ ወደ አንተም ለሰዎች ወደ እነሱ የተወረደውን (ፍቺ) ልትገልጽላቸውና ያስተነተኑትም ዘንድ ቁርኣንን አወረድን" (ሱረቱ 16፡43-44)፡፡ እነዚህ ቃላት በሱረቱ 21፡7 እና 21፡48 ላይ ተደግሟል፡- " ከአንተም በፊት ወደ እነሱ የምናወርድላቸው

የኾነን ሰዎችን እንጂ ሌላን አላክንም ። የማታውቁም ብትኾኑ የመጽሐፉን ባለቤቶች ጠይቁ።" ሱረቱ 21፥48 ፦ "ለሙሳና ለሃሩንም እውነትንና ውሸትን የሚለይን ብርሃንንም ለጥንቁቆችም መገሰጫን በእርግጥ ሰጠናቸው።" መዝሙረ ዳዊት 37፡29 በማጣቀስ ሱረቱ 21፥105 " ምድንም መልካሞች ባሮቼ ይወርሷታል ማለትም ከመጽሐፉ (ከተጠበቀው ሰሌዳ) በኋላ በመጽሐፎቹ በእርግጥ ጽፈናል" የላል።

ከቁርኣን በፊት እግዚአብሔር የርሱ መገለጥ የሆነውን መጽሐፍ ቅዱስ እንደጠበቀው መገንዘብ ግድ ይላል። እግዚአብሔር ኢሳያስ 40 ፥8 ላይ ሲናገር "ሣሩ ይደርቃል ፣ አበባውም ይረግፋል፣ የአምላካችን ቃል ግን ለዘላለም ጸንታ ትኖራለች።" ለኤርሚያስም  የተነገረውም ይኸው ነው፦ " እፈጽመው ዘንድ በቃሌ እተጋለሁና" (ኤርሚያስ 1፥12)። " ሰማይና ምድር እስኪያልፍ ድረስ ከሕግ አንዲት የውጣ ወይም አንዲት ነጥብ ከቶ አታልፍም ሁሉ እስኪፈጸም ድረስ" (ማቴዎስ 5፥18) ፤ "መጽሐፉ ሊሻር አይችልምና" (ዮሐንስ 10፥35)።

መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር መገለጥ /ቃል/ ንጽህና እንዲጠበቅ ያዛል። እግዚአብሔር ሕዝቡን እንዲህ ሲል አዟል፦ "እኔ ያዘዝኋችሁን የአምላካችሁን የእግዚአብሔር ትእዛዝ ትተብቃላችሁ አንጂ ባዘዝኋችሁ ቃል ላይ አትጨምሩም" (ዘዳግም 4፥2)። በመጽሐፍ ቅዱስ የመጨረሻው ክፍል የምናገኘው ማስጠንቀቂያም ይህንኑን ነው የሚያስነብበን፦

*ዮሐንስ ራዕይ 22፥18፣19*

*በዚህ መጽሐፍ የተጻፈውን የትንቢት ቃል ለሚሰማ ሁሉ እኔ እመሰክራለሁ። ማንም በዚህ ላይ አንዳች ቢጨምር እግዚአብሔር በዚህ መጽሐፍ የተጻፉትን መቅሥፍቶች ይጨመርበታል፣ማንምም በዚህ ትንቢት መጽሐፍ ከተጻፉት ቃሎች አንዳች ቢያጎድል ፣ በዚህ መጽሐፍ ከተጻፉት ከሕይወት ዛፍና ከሕይወት ዛፍና ከቅድስቲቱ ከተማ እግዚአብሔር ዕድሉን ያጎድልበታል።*

ክርስቲያኑ እግዚአብሔር ሰውን ከመውደዱ፣ ለማዳን ከመፈለጉ እና ከምሪቱ የተነሳ ራሱን የገለጠ አምላክ መኾኑን ያምናሉ። እግዚአብሔር በተጻፈው መጽሐፍ ቅዱስ እንዲሁም በሕያው ቃል በልጁ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን ገልጧል ፤ ሁለቱም የማይለወጡ ናቸው!  በተጻፈው ቃል የተላለፈው መልእክት እንዳይዛባ ተጠብቋልም። እግዚአብሔር መጽሐፍ ቅዱስ እንዲዛባ ፈቅዶ ቢኾን ኖሮ፣ እምነታችን ስልጣናዊ እና ተዐማኒ መሰረት አይኖረውም ነበር። ምንነቱ ያልታወቀ በመድኃኒት ብቻ የተሞላ አይነት ጠርሙስ ነበር የሚኾነው። ተጠቃሚው ጠርሙሱ

ምን እንደሆነ ላይረዳ ይችላል፣ መውሰድ የሚገባው መጠን ምን ያህል እንደሆነም አያውቅ ይሆናል፣ በጠርሙስ ውስጥ ያለው መድኃኒት ይሁን መርዝም አይታወቅም፡፡ እግዚአብሔር እንዲህ አይነቱን ሁኔታ /መዛባት/ እንዲከሰት አልፈቀደም፤ እርሱ ሰውን ይወዳል፣ ይጠነቀቃልም፡፡

## III. እስልምና ቀደምት ቅዱሳት መጻሕፍትን ያጸድቃል

ቁርኣን ኢየሱስ እና መሐመድ ከእነርሱ በፊት ለነበሩት ቅዱሳት መጽሐፍት አጽድቀዋል፡፡

ኢየሱስ የብሉይ ኪዳን ቅዱሳት መጽሐፍትን አጽድቋል፡-

*ሉቃስ 4፥16-21*

*ወደ ገብባትም ወደ ናዝሬት መጣ፣ እንደልማዱም በሰንበት ቀን ወደ ምኵራብ ገባ፣ ሊያነብም ተነሣ፡፡ የነቢዩንም የኢሳያስን መጽሐፍ ሰጡት፣ መጽሐፉንም በተረተረ ጊዜ፡- የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው፣ ለድሆችም ወንጌልን እሰብክ ዘንድ ቀብቶኛልና፣ ለታሰሩትም መፈታትን ለዕውሮችም ማየትን እሰብክ ዘንድ ፣ የተጠቁትንም ነጻ አወጣ ዘንድ የተወደደችውንም የጌታን ዓመት እሰብክ ዘንድ ልኮኛል፤ ተብሎ የተጻፈበትን ስፍራ አገኘ፡፡ መጽሐፉንም ጠቅልሎ ለአገልጋዩ ሰጠውና ተቀመጠ፤ በምኵራብም የነበሩት ሁሉ ትኵር ብለው ይመለከቱት ነበር፡፡ እርሱም ፡- ዛሬ ይህ መጽሐፍ በጆሮአችሁ ተፈጸመ ይላቸው ጀመር፡፡*

ቁርኣን መሐመድ ብሉይ እና አዲስ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍትን እንዳጸደቃቸው ፣ አንደ ጠበቃቸውም ይናገራል፡-

***ሱረቱ 5፥43-49***

*እነርሱም ዘንድ ተውራት እያለች በውስጧ የአላህ ፍርድ ያለባት ስትኾን እንዴት ያስፈርዱሃል! ከዚያም ከዚህ በኋላ እንዴት ይሸሻሉ! እነዚህም በፍጹም ምእምናን አይደሉም፡፡ እኛ ተውራትን በውስጥዋ መምሪያና ብርሃን ያለባት ስትኾን አወረድን፡፡ እነዚያ ትዕዛዝን የተቀበሉት ነቢያት በእነዚያ አይሁዳውያን በኾኑት ላይ በርሷ ይፈርዳሉ፡፡ ሊቃውንቱና ዐዋቂዎቹም ከአላህ መጽሐፍ እንዲጠበቁ በተደረጉትና በርሱም ላይ መስካሪዎች በኾኑት (ይፈርዳሉ)፡፡ ሰዎችንም አትፍሩ ፡፡ ፍሩኝም ፡ በአንቀጾቼም አነስተኛን ዋጋ እትለውጡ፡፡ አላህም ባወረደው ነገር ያልፈረደ ሰው እነዚያ ከሓዲዎቹ እነርሱ ናቸው፡፡ በእነርሱም ላይ በውሰጧ ‘ ነፍስ በነፍስ ዓይንም በዓይን አፍንጫም በአንፍጫ ጆሮም በጆሮ ጥርስም በጥርስ (ይያዛል)፡፡’ ቁስሎችንም ማመሳሰል አለባቸው ማለትን ጻፍን፡፡ በእርሱም የመጸወተ (ያማረ) ሰው እርሱ ለርሱ (ለሠራው ኃጢአት) ማስተማሪያ ነው፡፡*

*አላህም ባወረደው ነገር የማይፍርድ ሰው፣ እነዚያ በደለኞቹ እነርሱ ናቸው። በፈለጎቻቸውም (በነቢያቶቹ ፈለግ) ላይ የመርየምን ልጅ ዒሳን ከተውራት በስተፊቱ ያለውን አረጋጋጭ ሲኾን አስከተልን። ኢንጂልንም በውስጡ ቀጥታና ብርሃን ያለበት በስተፊቱ ያለችውን ተውራትንም የሚያረጋግጥ ለጥንቁቆችም መሪ ገሳጭ ሲኾኑ ሰጠነው። የኢንጅልም ባለቤቶች በውስጡ አላህ ባወረደው ሕግ ይፍረዱ። አላህም ባወረደው የማይፈርድ ሰው እነዚያ አመጸኞች እነርሱ ናቸው። ወደ አንተም መጽሐፉን ከበፊቱ ያለውን መጽሐፍ አረጋጋጭና በእርሱ ላይ ተጠባባቂ ሲኾን በእውነት አወረድን ። በመካካላቸውም አላህ ባወረደው ሕግ ፍረድ። እውነቱም ከመጣልህ በኃላ ዝንባሌዎቻቸውን አትከተል ። ከእናንተም ለሁሉም ሕግንና መንገድን አደረግ። አላህም በሻ ኖሮ አንድ ሕዝብ ባደረጋቸሁ ነበር። ግን በሰጣችሁ ሕግጋት ሊሞክራችሁ (ለያያችሁ)። በጎ ሥራዎችንም (ለመሥራት) ተሽቀዳደሙ፣ መመለሻችሁ በጠቅላላ ወደ አላህ ነው። በእርሱም ትለያዩበት የነበራችሁትን ነገር ይነግራችኃል። በመካከላቸውም አላህ ባወረደው ሕግ ፍረድ። ፍላጎቶቻቸውም አትከትል። አላህም ወደ አንተ ካወረደው ከከፊሉ እንዳይሳስቱህ ተጠንቀቃቸው (ማለትን አወረድን)። ቢዞሩም አላህ የሚሻው በከፊሉ ኃጢአታቸው ሊቀጣቸው መኾኑን ዕወቅ። ከሰዎቹም ብዙዎቹም አመጸኞች ናቸው።*

ኢብኑ ኻቲር አቡ ዳውድ በሱረቱ 5፡43-48 ላይ ሀዲስን (4449) በመጥቀስ የሚከተለውን አስተንትኖት ያሰፍራል፡- አይሁዶች በዝሙት የወደቁ ወንድ እና ሴትን ወደ መሐመድ አመጡ። እነዚህ ሰዎች ከዝነኛ ቤተሰብ ወገን ስለሆኑም በድንጋይ መውገር አልቻሉም። መሐመድ አይሁዶችን የሕጉ መጽሐፍ እንዲያመጡለት ጠየቀ። ከዚያም ያመጡለትን የሕግ መጽሐፍ ከፍ አድረጎ እንዲህ አለ "እኔ በእናተ እና ራሱን በገለጠላቸሁ አምናለሁ።" በትራስ /መከዳ/ ላይ ተቀምጦ፣ ጸሐፊውን ከሕጉ መጽሐፍ በዝሙት የሚገኝ በድንጋይ ይወገር የሚለው ክፍል አስኪደርስ እንዲያነብ አዘዘው። ከዚያም በዝሙት የተገኙትን ወንድ እና ሴት በሕጉ መሰረት አንዲወገሩ አደረገ።

ይህ የሚያመለክተው አንኳር እውነት ክርስቲያኑ እና አይሁዶች "ፈጣሪ በገለጠው" መኖር እንደሚገባቸው ነው። ሁለቱም ሕጉ (መመሪያ እና ብርሃን) እንዲሁም ወንጌል (መመሪያ እና ፈሪኃ እግዚአብሔር መር) የፈጣሪ መገለጥ እንደሆኑ የረገልጻሉ። በሙስሊማኑ እንደሚታመነው ፡-አይሁዳዊያኑም ሆነ ክርስቲያኑ አላህ የገለጠውን በመታዘዝ እና በመታመን ሊኖሩት ስላልቻሉ፣ መሐመድ እነዚህኑን ቀደምት ቅዱሳት መጻሕፍት አንዲጠብቅ፣ እንዲያስታርቅ እና እንዲዳኝ ተሰጠው።

## IV. መጽሐፍ ቅዱስ እምነት የሚጣልበት መኾኑን ቁርዐን ያበክራል

- ሱረቱ 29፥46 ሙስሊማኑን ያዛል፦ “የመፅሐፉን ባለቤቶች በዚያች እርሷ መልካም በኾነችው ክርክርእንጂ አትከራከሩ፡፡ ከነርሱ እነዚያን የበደሉትን ሲቀር፡፡ በሉም ‘በዚያ ወደኛ በተወረደው ወደ እናንተም በተወረደው አመንን፡፡ አምላካችንም አምላካችሁም አንድ ነው፡፡ እኛም ለእርሱ ታዛዦች ነን፡፡ ”ይህ ክፍል በግልፅ የሚያረጋግጠው ለአይሁዶችና ክርስቲያኑ “የተሰጠው የእግዚአብሔር መገለጥ” ምንኛ ተዐማኒ እንደሆነ ነው፡፡
- ሱረቱ 10፥94 ፣95 መሐመድን ያዛል፦ “ወደ አንተም ካወረድነው በመጠራጠር ውስጥ ብትሆን እነዚያን ካንተ በፊት መፅሐፉን የሚያነቡትን ጠይቅ፡፡ እውነቱ ከጌታ ዘንድ በርግጥ መጥቶልሃል፡፡ ከተጠራጣሪዎችም አትሁን፡፡ ከነዚያም የአላህን አንቀጾች ካስተባበሉት አትሁን፡፡ ከከሳሪዎቹ ትሆናለህና፡፡” በዚህ ክፍል መሐመድ የአይሁዳውያኑን እና ክርስቲያኑ ቅዱሳን መፅሐፍት እርሱ ለተቀበለው መገለጥ መለኪያ መሆኑን መገንዘቡን መረዳት ይቻላል፡፡
- ሱረቱ 16፥ 43፣44 መሐመድን እና ሙስሊማኑን ይናገራል፦ “ከአንተም በፊት ወደ ወሕይን (ራዕይን) የምናወርድላቸውን ሰዎችን እንጂ ሌላን አልላክን፡፡ የማታውቁም ብትኾኑ የእውቀትን ባለቤቶች ጠይቁ በግልፅ ማስረጃዎችን እና በመፅሐፍት ላክናቸው፡፡” አሁንም ቁርአን ስለ ነቢያት እና ስለኢየሱስ ክርስቶስ ተዓምራት የሚናገሩትን ቀደምት ቅዱሳን መፅሐፍት ሙሉ ማረጋገጫ ይሰጣል (ሱረቱ 3፥49፣5፥110)፡፡
- ሱረቱ 26፥193-196፦ “እርሱን ታማኙ መንፈስ (ጅብሪል) አወረደው፤ ከአስፈራሪዎቹ (ነቢያት) ትኾን ዘንድ በልብህ ላይ አውርደው፡፡ ግልፅ በኾነ ዐረብኛ ቋንቋ፡፡ እርሱም (ቁርአን በቀድሞዎቹ <u>መፅሐፍት</u>) ውስጥ የተወሳ ነው፡፡” በተመሳሳይ በቁርአን የሚገኙ እውነቶች በቀድሞዎቹ መፅሐፍት ይገኛሉ፡፡ ሱረቱ 41፥43 “ከአንተ በፊት ለነበሩት መልዕክተኞች የተባለው ብጤ እንጅ ለአንተ ሌላ አይባልም፡፡” ሱረቱ 87፥18፣19 “ይህ በፊተኞቹ መጽሐፍት ውስጥ ያልለለህ ነው፡፡ በኢብራሂም እና በሙሳ ጽሑፎች ውስጥ”፡፡
- ሱረቱ 19፥ 12 እና ሱረቱ 66፥12 በመጥምቁ ዩሐንስ እና ድንግሊቱ ማርያም ዘንድ መጽሐፉ ተዐማኒ መኾኑ ተረጋግጧል፡፡ አላህ ለመጥምቁ ተናገረ፦ “የሕያ (መጥምቁ) ሆይ! መጽሐፉን በጥብቅ ያዝ!’ (አልነው)፡፡ ጥበብንም በሕጻንነቱ ሰጠነው፡፡” ለመርየም ሲናገርም “የዒምራንን ልጅ መርየም ያችን ብልቷን የጠበቀችውን (ምሳሌ አደረገ)፡፡

በእርሱም ውስጥ ከመንፈሳችን ነፍፋን። በጌታዋ ቃላት እና በመጻሕፍቱም አረጋገጠች ። ከታዛገቹም ነበርች።”

## V. ቁርኣን መጽሐፍ ቅዱስን አያሳብቅም

አብዛኞቹ ሙስሊማኑ ከላይ የተቀመጡትን የቁርኣን ክፍሎች ወደ ጎን በመተው ቁርኣን የመጽሐፍ ቅዱስ ተአማኒነት ጥያቄ ውስጥ እንደከተተው ፣ አይሁድ እና ክርስቲያኑም ቅዱሳት መጻሓፍትን እንደለወጡት ይናገራሉ። ቁርአን መለወጥ የሚለውን ቃል የሚጠቀመው የአረብኛውን *ተሓሪፍ* ቃል በመዋስ ስለሆነ በጥንቃቄ መረዳት ያሻል። ዶክተር ቶማስ የሚከተለውን አሳብ ያነሳል፡-

ተሓሪፍ የሚለው ቃል ምን ማለት ነው? የጽሑፍ ትችት እንዳስቀመጠው ብሉሽነትን፣ መፈናቀልን እና ሽግግርን የወክላል። እነዚህ ቃላት በሽግግር ጊዜ ሊከሰት የሚችለውን ስህተት እንጂ ሆን ተብሎ የተደረገውን ማዛባት አያመለክቱም። በሽግግር ወቅት ሊከሰት የሚችለው አደጋ (እክል) የነገረ-መለኮት ምንባባትን አይጎዳም። የየብሉይ ኪዳን እና አዲስ ኪዳን ቅዱስ መጻሕፍት መጀመሪያ ቋንቋ በቅጡ ያልተረዳ “ብሉሽነት” የሚለውን ቃል ሊጠቀም ቢችል አያስደንቅም። ሙስሊማኑ ኢንጅል የሚለው ቃል የሚጠቀሙት ኢየሱስ ኢንጅልን (ወንጌላትን) እንደጻፈው በመረዳት ነው። ነገር ግን ሙህራን አራቱ ወንጌለካት በአራቱ ወንጌላውያን እንደተጻፈ ያበክራሉ። “ ወንጌል” በዘመናት ተከታዮቹ የኖሩበት እና የሰበኩት የኢየሱስ ክርስቶስ የምስራች ነው።

ተሓሪፍን አስመልክቶ የምናገኘው ማንኛውም ቁርኣናዊ ጥቅስ በሁለት አቅጣጫ በጥንቃቄ መመልከት ይኖርብናል፡-

- ክፍሎቹ (ጥቅሶቹ) አዲስ ኪዳንን ፈጽሞ የማያጠቁ ናቸው
- ቶራህን (ሕግን) የሚያጠቁ ክፍሎች (ጥቅሶች) በመሐመድ ዘመን የነበሩትን የዐይሁድ ሥነ-አፈታቶች (ትርጉሞችን) ነው።

በሰባተኛው ክፍለ ዘመ በዓረብ-ሰላጤ የነበሩ አይሁድ ከታልሙድ ታሪኮችን ይጠቅሱ ነበር። በዚህም ከዋናው የብሉይ ኪዳን መጽሓፍት ቅጪ ጋር የሚጋጩ አንዳንድ ክፍሎች እንዲገኙ ሆኗል። መሐመድ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በሚተችበት ሁናቴ (አቋም) ላይ አልነበረም፤

ስለዚህ ቁርኣን ምንኣልባት በመጽሐፍ ቅዱስ የተለወጡ ትርጉሞች ላይ መሞገት (ማጥቃት) ይችል እንደሆን እንጂ ፈጽሞ የተለወጠ አንዳች የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ የለም።

ሙስሊማኑ ሦስት የተለያዩ ስብዕናዎች እና ደረጃዎች የሚጠቅሱአቸው ሙግቶች፡-

## 1. እስልምናን ተቀብለው ወደኋላ ስለተመለሱ፣ ቁርኣንንም ስላዛነፉ አይሁዶች የሚናገር ክፍል

***ሱረቱ 3፥70-72***

*የመጽሐፉ ባለቤቶች ሆይ! እናንተ የምታውቁ ስትኾኑ በአላህ አንቀጾች ለምን ትክዳላችሁ። 'የመጽሐፉ ሰዎች ሆይ! እውነቱን በውሸትለምን ትቀላቅላላችሁ እውነቱንም እናንተ የምታውቁ ስትኾኑለምን ትደበቃላችሁ።' ከመጽሐፉ ባለቤቶች የኾኑ ጭፍሮች አሉ፡- 'በነዚያ በአመኑት ላይ በተወረደው (ቁርኣን) በቀኑ መጀመሪያ ላይ እመኑበት ። በመጨረሻም ካዱት ። እነርሱ ሊመለሱ ይከጀላልና።'*

***ሱረቱ 37፥8***

*ከእነሩስም እርሱ ከመጽሐፉ ያይደለ ሲኾኑ ከመጽሐፉ መኾኑን እንድታስቡ በመጽሐፉ ምላሶቻቸውን የሚያጣምሙ ክፍሎች አሉ። እርሱ ከአላህ ዘንድ ያልኾነ ሲኾኑ ' እርሱ ከኣላህ ዘንድ ነውም' ይላሉ። እነርሱ የሚያውቁ ሲኾኑም በአላህ ላይ ውሸትን ይናገራሉ።'*

***ሱረቱ 31፥99***

*ከመጽሐፉም ባለቤቶቹ ለአላህ ፈሪዎች በአላህ አንቀጾችም ጥቂቱን ዋጋ የማይለወጡ ሲኾኑ በአላህና በዚያ ወደ እናንተ በተወረደው በዚያም ወደ እነርሱ በተወረደው የሚያምኑ ሰዎች አሉ። እነዚያ ለእነርሱ በጌታቸው ዘንድ ምንዳቸው አላቸው። አላህ ምርመራው ፈጣን ነው።*

## 2. አይሁዳዊያኑ የሕጉን ክፍሎች በማጣመማቸው የሚገስጽ ክፍል

***ሱረቱ 2፥40-44***

*የእስራኤል ልጆች ሆይ! ያችን በናንተ ላይ የለገስኳትን ጸጋዬን አስታውሱ። በቃል ኪዳኔም ሙሉ፣ በቃል ኪዳናችሁ እሞላለሁና፣ እኔንም ብቻ ፍሩ። ከናንተ ጋ ያለውን (መጽሐፍ) የሚያረጋግጥ ሆኖ ባወረድኩትም ከሓዲ አትሁኑ። በአንቀጾቼም ጥቂቱን ዋጋ አትለዉጡ። እኔንም ብቻ ተጠንቀቁ። ከናንተ ጋር ያለውን (መጽሐፍ) የሚያረጋግጥ ሆኖ ባወረድኩትም (ቁርኣን) እመኑ ። በርሱም የመጀመሪያው ከሓዲ አትሁኑ። በአንቀጾቼም ጥቂቱን ዋጋ አትለዉጡ ። እኔንም ብቻ ተጠንቀቁ። እውነቱንም በውሸት አትቀላቅሉ። እናንተም የምታውቁ ስትሆኑ እውነቱን አትደበቁ። ሶላትንም ደንቡን ጠብቃችሁ ሰገዱ። ዘካንም (ግዴታ ምጽዋትን) ስጡ።*

*(ለጌታችሁ) ከአጎንባሾች ጋርም አጎንብሱ፡፡ አናንተ መጽሐፉን የምታነቡ ሆናችሁ ሰዎችን በበጎ ሥራ ታዛላችሁን? ነፍሶቻችሁንም ትረሳላችሁን? (የሥራችሁን መጥፎነት) አታውቁምን?*

***ሱረቱ 2፡ 75-79***

*(አይሆዶች) ከነሱ የኾኑ ጭፍሮች የአላህን ቃል የሚሰሙና ከዚያም ከተረዱት በኃላ እነርሱ እያወቁ የሚለዉጡትን ሲኾኑ ለናንተ ማመናቸውን ትከጅላላችሁን? እነዚያንም ያመኑትን ባገኙ ጊዜ 'አምነናል' ይላሉ፡፡ ከፊላቸውም ወደ ከፊሉ ባገለለ ' ጊዜ አላህ በናንተ ላይ በገለጸላችሁ ነገር እጌታችሁ ዘንድ በርሱ እንዲከራከሩዋችሁ ትነግሩዋችሁ ትነግሩዋቸዋላችሁን? አታውቁምን' ይላሉ፡፡ አላህ የሚደብቁትንና ሚገልጹትን የሚያውቅ መኾኑን አያውቁምን? ከነሱም መጽሐፉን የማያወቁ መሃይማን አሉ፡፡ ግን ከንቱ ምኞቶችን (ይመኛሉ)፤ እነርሱም የሚጠራጠሩ አንጂ ሌላ አይደሉም፡፡ ለነዚያም መጽሐፉን በእጆቻቸው ለሚጽፉና ከዚያም በርሱ ጥቂትን ዋጋ ሊገዙበት 'ይህ ከአላህ ዘንድ ነው' ለሚሉ ወዮላቸው፤ ለነርሱም ከዚያ እጆቻቸው ከጻፉት ወዮቸው፡፡ ለነሱም ከዚያ ከሚያፈሩት (ኃጢኣት) ወዮላቸው፡፡*

***ሱረቱ 6፡92***

*'አላህ (አወረደው) በላቸው፡፡ ከዚያም በውሸታቸው ውስጥ የሚጫወቱ ሲኾኑ ተዋቸው፡፡ ይህም ያወረድነው የኾነ ብሩክ ያንንም በፊቱ የነበረውን (መጽሐፍ) አረጋጋጭ መጽሐፍ ነው፡፡ የከተሞችን እናት (መካን) እና በዙሪያዋ ያሉትንም ሰዎች ልታስጠነቅቅበት (አወረድነው)፡፡ እነዚያም በመጨረሻይቱ ዓለም የሚያምኑት እነርሱ በሶላታቸው ላይ የሚጠባበቁ ሲኾኑ በርሱ ያምናሉ፡፡*

## 3. የሕጉን ክፍሎች በትክክለኛው መንገድ ለማይተረጉሙ አይሁዶች የሚናገር ጥቅስ

***ሱረቱ 4፥44-47***

*ወደነዚያ ከመጽሐፉ (ዕውቀት) ዕድልን ወደ ተሰጡት አላየህምን ጥመትን (በቅንነት) ይገዛሉ፡፡ መንገድንም እንድትሳሳቱ ይፍለጋሉ፡፡ አላህም ጠላቶቻችሁን ዐዋቂ ነው፡፡ ጠባቂነትም በአላህ በቃ፡፡ ረዳትነትም በአላህ በቃ፡፡ ከነዚያ አይሁዳውያን ከኾኑት ሰዎች ንግግሮችን ከስፍራዎች የሚያጣጥሙ አልሉ፡፡ 'ሰማንም አመጽንም የማትሰማም ስትኾን ስማ' ይላሉ፡፡ በምላሶቻቸውም ለማጣመምና ሃማኖትንም ለመዝለፍ ራዒና ይላሉ፡፡ እነሱም ' ሰማን ታዘዝንም ሰማም ተመልከተንም' ባሉ ኖሮ ለነሱ መልካምና ትክክኛ በኾነ ነበር፡፡ ግን በክህደታቸው አላህ ረገማቸው፡፡ ጥቂትንም እንጅ አያምኑም፡፡ እናንተ መጽሐፉን የተሰጣችሁ ሆይ! ፊቶችን ሳናብስና በጀርባቸው ላይ ሳንመልሳቸው ወይም የሰንበትን ባለቤቶች (ያፈረሱትን) እንደረገምን ሳንረግማቸው በፊት ከእናንተ ጋር ያለውን ሚያረጋግጥ ኾኖ ባወረድነው (ቁርኣን) እመኑ ፡፡ የአላህም ትዕዛዝ ተፈጻሚ ነው፡፡*

*ሱረቱ 5፥13*

*ቃል ኪዳናቸውንም በማፍረሳቸው ረገምናቸው፡፡ ልቦቻቸውንም ደረቆች አደረግን፡፡ ቃላትን ከቦታዎቻቸው ይለውጣሉ፡፡ በርሱም ከታዘዙበት ነገር ፈንታን ተው፡፡ ከእነርሱም ጥቂቶች ሲቀሩ ከነርሱ የኾኑ ከነርሱ የኾነን ክዳት የምታውቃውቅባቸው ከመኾን አትወገድም ፡፡ ከእነርሱም ይቅርታ አድርግ እለፋቸውም ፡፡ አላህ መልካም ሠሪዎችን ይወዳልና፡፡*

*ሱረቱ 5፥41-43*

*አንተ መልዕክተኛ ሆይ! እነዚያ በክሕደት የሚቻኮሉት ከእነዚያ ልቦቻቸው ያላመኑ ሲኾኑ በአፎቻቸው 'አመንን' ካሉትና ከእነዚያም አይሁድ ከኾኑት ሲኾኑ አያሳዝኑህ፡፡ (እነርሱ) ውሸትን አዳማጮች ናቸው፡፡ ለሌሎች ወዳንተ ላልመጡ ሕዝቦች አዳማጮች ናቸው፡፡ ንግግሮችን ከቦታቸው ሌላ ያጣምማሉ፡፡ 'ይህንን (የተጣመመውን) ብትሰጡ ያዙት፡፡ ባትሰሰቱም ተጠንቀቁ' ይላሉ፡፡ አላህም መፈተኑን የሚሻበትን ሰው ለእርሱ ከአላህ (ለመከላከል) ምንንም አትችልም ፡፡ እነዚህ እነዚያ አላህ ልቦቻቸውን ማጥራትን ያልሻላቸው ናቸው፡፡ ለእነርሱ በቅርቢቱ ዓለም ውርደት አላቸው፡፡ ለእነርሱም በመጨረሻይቱ ዓለም ከባድ ቅጣት አላቸው፡፡ ውሸትን አዳማጮች እርምን በላተኞች ናቸው፡፡ ወደ አንተ ቢመጣም በመካከላቸው ፍርድ ወይም ተዋቸው፡፡ በትተዋቸውም ምንም አይጎዱህም ፡፡ ብትፈርድም በመካካለቻቸው በትክክል ፍረድ፡፡ አላህ በትክክል ፈራጆችን ይወዳልና፡፡ እነርሱም ዘንድ ተውራት እያለች በውስጧ የአላህ ፍርድ ያለባት ስትኾን እንዴት ያስፈርዱሃል! ከዚያም ከዚህ በኃላ እንዴት ይሸሻሉ! እነዚያም በፍጹም ምእምናን አይደሉም፡፡*

## VI. መጽሐፍ ቅዱስ የሚጋጩ አሳቦች የሉትም

የመጽሐፍ ቅድስን ተዐማኒነት የሚሞግቱ አሳቦች በአመዛኙ የሚመነጩት በክርስትናው ካሉ ለዘብተኛ ነገረ-መለኮት አቀንቃኞች (ከፍተኛ እና መለስተኛ ሙግት ተከታዮች) ዘንድ ነው፡፡ የላዕላይ ሙግት መጽሐፍ ቅዱስ ጸሓፍት እንደሌሎቹ የታሪክ ወይም ከርሰ ምድር ተመራማሪዎች ድርሳናት ይመሰላል፤ መለስተኛው ሙግት በበኩሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ አስተንትኖት ላይ ያተኩራል፡፡ ሁለቱም በመጽሐፍ ቅዱስ ተስማሚና ተቃርኖአዊ አሳቦች እንዳሉ ያስረግጣሉ፡፡ ሆኖም በዚህ አሳብ ዙሪያ በክርስቲያኑ የነገረ-መለኮት ሙህራን አጥጋቢ ምላሽ ቢኖርም ፣ በሙስሊማኑ ዘንድ መጽሐፍ ቅዱስ ተቃርኖአዊ አሳቦች እንደያዘ ይታመናል፡፡

በመጽሐፍ ቅዱስ ተቃርኖአዊ ቃሎች የሉም፡፡ "ሁለት አረፍተ ነገሮች በማንኛውም ሁኔታ ተቃርኖአዊ መስለው ቢታዩ፣ የመጀመሪያው ከሌላው አንድ ሆኖ ባይገኝ ፣ እንደ ልዩነት እንጂ ተቃርኖ ተደርጎ መወሰድ አይኖርበትም፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ እርስ በርሱ

የሚስማማ እንዳልሆነ /ተቃርኖ እንዳለበት) የሚያስቡ ሰዎች በ 'ልዩነት' እና 'ተቃርኖ' ትርጉም መካከል ያለውን ልዩነት ማወቅ የተሳናቸው ናቸው" [52]

ተቃርኖ እንዳላቸው የሚገመቱ ክፍሎች፦

- ***ተደጋጋሚ ስሞች፦*** በሐዋሪያት ሥራ ምዕራፍ አስራ ሁለት ላይ ሄሮዶስ ያዕቆብን እንደገደለው ይናገራል፡፡ ምዕራፍ 15 ደግሞ በቤተክርስቲያን መማክርት ጉባኤ ላይ ያዕቆብ ንግግር ሲያደርግ ይታያል፡፡ ይህ ተቃርኖአዊ አሳብን አይመለከተም፤ ነገር ግብ በሐዋሪያት ሥራ ምዕራፍ አስራ ሁለት የተጠቀሰው ያዕቆብ የዘብዲዮስ ልጅ ነው፤ በሐዋሪያት ሥራ አስራ አምስት የተጠቀሰው ያዕቆብ ግን የኤልፋስ ልጅ መሆኑን መረዳት አያዳግትም፡፡
- ***ተመሳሳይ ሰው የተጠራባቸው የተለያዩ ስያሜዎች*** ፦ በአስራ ሁለቱ ደቀመዛሙርት ዝርዝር ላይ ልዩነቶች መኖራቸውን ሙግቶች ያስቀምጣሉ፡፡ ሆኖም አንድ ሰው በተለያዩ ስሞች ሊጠራ አንደሚችል በቂ ምክንያቶች አሉ፡፡ ለምሳሌ፦ የአብራሃምን አባት ቁርአን አዘር (ሱረቱ 6፥74)፣ መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ ታራ (ዘፍጥረት 11፥27) ብሎ ይጠራዋል፡፡
- ***ትይዩ መዛግብት*** ፦ በዮሐንስ 20፥12 እና ማርቆስ 16፥5 በኢየሱስ መቃብር የታዩት መላእክት ትርክት ተቃርኖአዊ ተደርጎ ይወሰድ ይሆናል፡፡ ዮሐንስ ሁለት መላዕክትን ሲጠቅስ፣ ማርቆስ አንድ መላእክን ይዘግባል፤ በስፋት እና በዝርዝር አንደኛው ከመግለጹ በቀር በሁለቱም መዛግበት አንዳች ልዩነት የለም፡፡
- ***የትረጉም መፋለስ*** ፦ በትርጉም ሥራ ሂደት የትርጉም መፋለስ ችግር የሚገጥምበት ጊዜ አለ፡፡ በዚህ ጊዜ የመጀመሪያ ቋንቋ ዕውቀት ያለው ሰው ችግሩን ሊፈታው ይችላል፡፡ የዕብራይስጥ እና ግሪክ ቃላት ፍቺ ቃል በቃል ሆነ ትርጓሜው ከአንግሊዘኛው ጋር አንድ አይደለም፡፡ ስለሆነም ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ፍቺ ያላቸው የዕብራይስጥ እና ግሪክ ቃላት አንዱን የእንግሊዘኛ ቃል በሚጠቀሙበት ጊዜ ትክክለኛው ፍቺ ሊዛነፍ ይችላል፡፡ ለምሳሌ፦ የሳውልን ታሪክ በተመለከተ ሐዋሪያት ሥራ 9፥7 " ከእርሱም ጋር በመንገድ የሄዱ ሰዎች ድምጹን እየሰሙ ማንንም ግን ሳያዩ እንደ ዲዳዎች ቆሙ" ይላል፡፡ ሐዋሪያት ሥራ 22፥9 ደግሞ " ከእኔ ጋር የነበሩትም ብርሃኑን አይተው ፈሩ፣ የሚናገረኝን የእርሱን ድምጽ ግን አልሰሙም" ብሎ ይናገራል፡፡ እነዚህ አሳቦች እርስ በእርሳቸው የሚጣረሱ ሊመስል ይችላል፦ የመጀመሪያው ከጳውሎስ

---

[52] በብሉይ ኪዳን የሀሰት ሙግት ፣ " እውነተኛ መመሪያ ( ቪሊች ፦ የህይወት ብርሃን ፣ 1992) ገጾች 8-11)፡፡

ጋር ሲጓዙ የነበሩ ሰዎች ድምጽ እንደሰሙ ሲገልጽ፣ ሁለተኛው ድምጽ ሰሚው ጳውሎስ እንደሆነ ይናገራል፡፡ የግሪኩን ስርው-ቃል ወይም ትርጉም የተመለከትን እንደሆነ፣ “መስማት” በመጀመሪያው ንባብ ክፍል መሰረት በጆሮአችን አካላዊ ድምጽን መቀበል ያመለክታል፡፡ በሁለተኛው ክፍል የተጠቀሰው “ መስማት” አካላዊ ድምጽን ከመቀበል ባሻገር መረዳትን ጭምር ይገልጻል፡፡ በሌላ አባባል ከጳውሎስ ጋር የነበሩ ሰዎች ድምጹን ቢሰሙም፣ ምን ማለት እንደሆነ ግን መረዳት አለመቻላቸውን ልብ ይሏል፡፡

- ***የቅርሶች ጥናት እማኝነት፡-*** ብልጣሶር በመንግስቱ ላይ ዳንኤልን ሦስተኛ ገዢ እንዳደረገው (ዳንኤል 5፥7፣10፣29) መጽሐፍ ቅዱስ መናገሩ ስህተት እንዳለበት የሚሞግቱ አሉ፡፡ ዮሴፍ በፈርኦን ሁለተኛው ገዢ አንደነበረ ሁሉ (ዘፍጥረት 41፥40፣43) ዳንኤልም እንዲሁ መግለጽ ነበረበት ሲሉ ምክንያታቸውን ያስቀምጣሉ፡፡ የቅርስ ጥናት ተመራማሪዎች በቅርቡ ብልጣሶር የአባቱ ናቡከደነጾር ምክትል እንደራሴ እንደሆነ አረጋግጠዋል፤ በዚህም ዳንኤል ሦስተኛ ገዢ መደረጉ፣ የመጽሐፍ ቅዱስን ተዐማኒነት ይበልጥኑ ያጎላዋል፡፡
- ***ስታትስቲክ*** ፡- 1ኛ ነገስት 7፡26 የተሰራው ኩሬ /ገላ መታጠቢያ/ ከንፈር ሁለት ሺህ የባዶስ መስፈሪያ እንደሚይዝ ሲገልጽ ፣ በ2ኛ ዜና 4፡5 የሚገኘው ተመሳሳይ የንባብ ክፍል ደግሞ ሶስት ሺህ መሆኑን ይናገራል፡፡ ሆኖም ሶስት ሺህ መስፈሪያ የሚይዝ ገላ መታጠቢያ፣ በሁለት ሺህ መስፈሪያ መጠን ሰው እንዲጠቀም ሊከለክለው እንደማይችልም መረዳት ያስፈልጋል፡፡

በመጽሐፍ ቅዱስ የሚቃረኑ አሳቦች እንዳሉ የሚያሳብቅ አንዳች ክፍተት የለም፡፡ የሚከተሉትን ምክረ አሳቦች ልብ ማለት ያሻል፡-

- የብሉይና አዲስ ኪዳን ቅዱሳት መጽሓፍት መጀመሪያ ቅጂ ጽሑፍ የማስተላለፍ ሥራ ተአማኒነትን ለማረጋገጥ ብዙ ተደክሞበታል፡፡
- በቃላት ሆሄያት ረገድ ጥቃቅን ስህተቶች በጽሑፍ ማስተላለፍ ወቅት ሳይታሰብ ሊከሰት ይችላል፡፡ ለምሳሌ፡- በዕብራይስጡ “d” እና “r” ቃላት ተወራራሽ ሊሆኑ ይችላሉ፤ ነገር ግን የንባብ ክፍሉን ትርጉም አያፋልሱም፡፡
- ግር የሚያሠኙን ተቃርኖአዊ አሳቦች ሊገጥሙን ይችላሉ፡፡ እውቀታችን ውስን መሆኑ ላፍታ መዘንጋት የለበትም፤ በቀጣይ ትውልዶች እኛ ያልፈታነው በቃሉ መልስ ሊያገኝ ይችላልና!

- ○ እግዚአብሔር ራሱን የገለጠው በቃሉና በሥራው ነውና እውነትን የሚሹ ብቻ ያገኙታል፡፡ ግር የሚሉን ነገሮች በሚገጥሙን ጊዜ ሁሉ ራሳችንን ዘላለማዊና ጠቢብ በሆነው አምላክ ፊት በአክብሮት ራሳችንን ዝቅ ልናደርግ ይገባል፡፡ ልባችን የእግዚአብሔርን መገለጥ መቀበላችን መፈተሻ ስፍራ ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን ከመንፈስ ቅዱስ ምሪት ውጪ በአእምሮ ለማወቅ መዳዳት ግር የሚያሰኙ አሳቦች እንዲበራከቱ በር ይከፍታል፡፡

## VII. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትንቢቶች ተፈጽመዋል

*መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትንቢቶች የመጽሐፍ ቅዱስ ተአማኒነት እማኞች ናቸው፡፡ የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢቶች በትክክል መፈጸማቸው እግዚአብሔር ቃሉ ፈጽሞ እንዳይዛባ ያደረገውን ጥበቃ ማሳያ ናቸው ፡፡ ከመቶ ዓመታት በኃላ የተፈጸሙ ትንቢቶች የዚህ እውነት ዐብይ ማሳያዎች ናቸው ፡፡*

በብሉይ ኪዳን የኢየሱስ ህይወት በተመለከተ የተነገሩ ትንቢቶች በትክክል ተፈጽመዋል፡-

- ***የኢየሱስ ልደት ቦታ፡-*** ሚክያስ 5፡2 "አንቺም ቤተልሔም ኤፍራታ ሆይ አንቺ በይሁዳ አእላፋት መካካል ትሆኚ ዘንድ ታናሽ ነሽ፤ ከአንቺ ግን አወጣቱ ከቀድሞ ጀምሮ ከዘላላም
  የሆነ፣ በእስራኤል ላይ ገዥ የሚሆን ይወጣልኛል፡፡ "ከአመታት በኃላ ኢየሱስ በቤተልሔም ተወለደ፡፡
- ***የድንግል መውለድ*** ፡- ኢሳያስ 7፡14 " ስለዚህ ጌታ ራሱ ምልክት ይሰጣችኃል ፣ እንሆ ድንግል ትጸንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች፣ ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች፡፡" ከሰባት መቶ አመታት በኃላ ድንግል ማርያም ኢየሱስን ወለደች (ማቴዎስ 1፡18፣ ሉቃ. 1፡35)፡፡
- ***የቤተልሔም ህጻናት መታረድ*** ፡- ነብዩ ኤርሚያስ የቤተልሔም ህጻናት ግድያን አስመልክቶ ትንቢት ተናግሮአል " የዋይታና የመራራ ልቅሶ ድምጽ በራማ ተሰማ ፣ ራሔል ስለ ልጆችዋ አለቀሰች፣ የሉምና፤ ስለ ልጆችዋ መጽናናትን እንቢ አለች" (ኤርሚያስ 31፡15)፡፡ በማቴዎስ 2፡16-18 መሰረት ይህ ትንቢት ከስድት መቶ አመታት በኃላ ተፈጸመ፡፡

- ***የግብጽ ስደት፡-*** ነብዩ ሆሴዕ ኢየሱስ ወደ ግብጽ እንደሚሔድ ተናግሯል። “ልጄንም ከግበጽ ጠራሁት” (ሆሴዕ 11፡1)። ከሰባት መቶ አመታት በኃላ ይህ መፈጸሙን ማቴዎስ 2፡15 ይናገራል።
- ***የኢየሱስ ድል በአል በኢየሩሳሌም*** ፡- ዘካሪያስ 9፡9 “ አንቺ የጽዮን ልጅ ሆይ ፣ እጅግ ደስ ይበልሽ ፣ አንቺ የኢየሩሳሌም ልጅ ሆይ እልል በዪ ፣ እነሆ ንጉስሽ ጻድቅና አዳኝ ነው፤ ትሑትም ሆኖ በአህያም ፣ በአህያይቱም ግልገል በውርንጫይቱ ላይ ተቀምጦ ወደ አንቺ ይመጣል።” በማቴዎስ 21፡1-11 መሰረት ከስድስት መቶ ዓመት ትንቢቱ ተፈጸመ።



- ***የሸክላ ሰሪው መሬት ግዢ*** ፡- በዘካሪያስ ትንቢት መሰረት  በሠላሳ ብር መሬት ተገዝቷል፤ “እግዚአብሔርም የተስማሙበትን የከበረውን ዋጋ በግምጃ ቤቱ ውስጥ አኑረው  አለኝ። እኔም ሠላሳውን ብር ወስጄ በእግዚአብሔር ቤት ባለው በግምጃ  በቤቱ ውስጥ አኖርሁ።” ይህ ከስድስት መቶ አመታት በኃላ ተፈጽሟል (ማቴዎስ 27፡7)።
- ***ከኃጢአተኞች ጋር መሰቀል፡-*** ኢሳያስ 53፡ 12 “ ከኃያለን ጋር ምርኮን ይከፋፈላል፣ ነፍሱን ለሞት አሳልፎ ሰጥቶአልና፣ ከዓመጸኞችም ጋር ተቆጥሮአልና፤ እርሱ ግን የብዙ ሰዎችን ኃጢአት ተሸከመ፣ ሰለ ዓመጸኞችም ማለደ።” ሉቃስ 23፡33 ከሰባት አመታት በኃላ ይህ ትንቢት ፍጻሜ እንዳገኘ ይዘግባል።
- ***የኢየሱስ እጆችና እግሮች መቸንከር***፡- መዝሙር 22፡1 “ብዙ ውሾች ከብበውኛልና ፣ የክፋተኞችጉባኤምያዘኝእጆቼንናእግሮቼንቸነከሩኝ።” ዘካሪያስ 12፡10 “በዳዊት ቤት ላይ በኢየሩሳሌምም በሚኖሩት ላይ የሞገስንና የልመናን መንፈስ አፈስሳለሁ፣ ወደ እርሱም ወደ ወጉት ይመከታሉ።” እነዚህ ትንቢቶች ከመቶ አመታት በኃላ በስቅለት ወቅት ተፈጽሟል (ዮሐንስ 19፡18)።
- ***ከባለጠጋው ጋር መቀበር*** ፡- ኢሳያስ 53፡9 “ከክፎዎች ጋር መቃብሩን አደረጉ፣ከባለጠጎችም ጋር በሞቱ ሆኖም ግፍን አላደረገም ነበር፣ በአፉም ተንኮል አልተገኘበትም ነበር።” “በመሸም ጊዜ ዮሴፍ የተባለው ባለጠጋ ሰው ከአርማትያስ መጣ፣ እርሱም ደግሞ የኢየሱስ ደቀመዝሙር ነበር፤ ይኸውም ወደ ጲላጦስ ቀርቦ የኢየሱስን ሥጋ ለመነው። ጲላጦስም እንዲሰጡት አዘዘ። ዮሴፍም ሥጋውን ይዞ በንጹሕ በፍታ ከፈነው። ከዓለት በወቀረው በአዲሱ መቃብርም አኖረው፣ በመቃብሩም ደጃፍ ታላቅ ድንጋይ አንከባሎ ሄደ ”(ማቴዎስ 27፡57-60)።
- ***ትንሣኤ*** ፡- መዝሙር 16፡10 “ ነፍሴን በሲኦል አትተዋትምና ፣ ቅዱስንም መበስበስን ያይ ዘንድ  አትተወውም።” ጴጥሮስ ይህ ትንቢት መበስበስን ላየው ለዳዊት ሳይሆን ፍጻሜው ለኢየሱስ አንደሆነ አረጋግጧል (ሐዋሪያት ሥራ 2፡25-36)።
- ***ዕርገት*** ፡- መዝሙር 68፡18 “ ወደላይ ዓረግህ  ምርኮን ማረክህ ፣ ስጦታንም ለሰዎች ሰጠህ፣ ደግሞም ለዓመጸኞች በዚያ ያድሩ ዘንድ፤” ትንቢቱ በሉቃስ 24፡50፣51 እና ኤፌሶን 4፡8-11 ተፈጽሟል።

# VIII. መጽሐፍ ቅዱስ አልተለወጠም

መጽሐፍ ቅዱስ እንደተለወጠ የሚሞግቱ ሰዎች በቂ ማስረጃ ሊኖራቸው ብሎም የሚከተሉትን ጥያቄዎች ሊመልሱ ይገባቸዋል፦

## 1. መጽሐፍ ቅዱስ የተለጠው መቼ ነው?

መጽሐፍ ቅዱስ የተለወጠው ከቁርአን በፊት ነው ወይስ በኃላ? ቀደም ብሎ ከሆነ ፡- ቁርኣን ሙስሊማኑን እውነት ለመፈለግ መጽሐፍ ቅዱስን ተመልክቱ (ሱረቱ 16፡43፣44) ባለለም፤ አላህም የሙሐመድን መጠራጠር አስመልክቶ የመጽሐፉ ሰዎችን አማክር ብሎ ባለነገረው ነበር (ሱረቱ 10፡95፣96)። በሺዎች የሚቆጠሩ ቅዱሳት መጻሕፍት ከቁርኣን በፊት የነበሩ፣ አሁን ካለው መጽሐፍ ቅዱስም እጅጉን አንድነት ያላቸው ናቸው።

## 2.መጽሐፍ ቅዱስ የለወጠው የት ነው?

ሙስሊማኑ እንደሚሉት መጽሐፍ ቅዱስ ተለውጦ ቢሆን ኖሮ አለም አቀፋዊው የአይሁድና ክርስቲያን መሪዎች ማረጋገጫ አካል ፣ የዋና ቅጂውን ክለሳ (በጠፉ ጽሑፎች የመተካት ሥራ) ካሊፍ ኡትማን የቁርአን ዋና ቅጂ እንዳዘጋጀው ባደረጉ ነበር! ይህ ከቶ በክርስትና ታሪክ ተዘግቦ አይገኝም።

## 3.መጽሐፍ ቅዱስን የለወጠው ማነው?

አይሁዶች የብሉይ ኪዳን መጽሐፍትን ቢቀይሩ (የመቀየር ዝንባሌ ቢኖራቸው) እንኳ የዕብራይስጥና ግሪክ ቅጂው ያለ አንዳች ጣልቃ ገብነት በእጃቸው መኖሩ መዘንጋት የለበትም። ክርስቲያኑ አዲስ ኪዳንን ለውጠዋልን? ቁርአን በክርስቲያኑ መካካል ክፍፍልና ግጭት መኖሩን ብቻ ነው የሚናገረው፦

*ሱረቱ 5:14*

*ከእነዚያም እኛ ክርስቲያኖች ነን ካሉት የጠበቀ ቃል ኪዳናቸውን ያዝን። በእርሱም ከታዘዙበት ነገር ፈንታን ተውት። ስለዚህ እስከ ትንሣኤ ቀን ድረስ በመካካለቻው ጠብንና ጥላቻን ጣልንባቸው። አላጅም ይሠሩት የበሩትን ሁሉ በእርግጥ ይነግራቸዋል።*

*ሱረቱ 61፡14*

*እናንተ ያመናችሁ ሆይ! የመርየም ልጅ ዒሳ ለሐዋሪያቶቹ 'ወደ አላህ ረዳቱ ማነው?' እንዳለ ሐዋሪያቶቹም ' እኛ የአላህ ረዳቶች ነን' እንዳሉት የአላህ ረዳቶች ኹኑ ። ከእስራኤልም ልጆች አንደኛዋ ጭፍራ አመነች። ሌላይቱም ጭፍራ ካደች። እነዚያን ያመኑትንም በጠላታቸው ላይ አበረታናቸው፤ አሸናፊዎችም ኾኑ።*

በክርስቲያኑ ዘንድ መካፈፈል እንዳለ በአይሁድ ዘንድ ሳይቀር መጽሐፍ ቅዱስን እንደመለወጥ መታሰብ የለበትም ። ኢየሱስ ለኒቆዲሞስ ሲናገር፡-

*ዮሐንስ 3፡5-8*

*እውነት እውነት እልሃለሁ ፤ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግስት ሊገባ አይችልም። ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው፤ ከመንፈስም የተወለደ መንፈስ ነው። ዳግመኛ ልትወለዱ ያስፈልጋችኃል ስልልሁ አታድንቅ ። ነፋስ ወደሚወደው ይነፍሳል፣ ድምጹንም ትሰማለህ፣ ነገር ግን ከወዴት እንደመጣ ወዴትም እንዲሄድ አታውቅም ፤ከመንፈስ የተወለደ ሁሉ እንዲሁ ነው።*

መንፈስ ቅዱስ አዲስ ሕይወትን በመስጠት አማኙኑ ወደ እውነትና ታማኝነት ይመራል። ታዲያ ዳግም የተወለደ ታማኝ ተከታይ መጽሐፍ ቅዱስን ለመለወጥ እንዴት ይዳዳል፣ የሕይወትን ቃል አስመልክቶ የተሰጠውን ማስጠንቀቂያ ችላ ካለለ በቀር ?

### 4. የተለወጠውና ያልተለወጠው ምንድነው?

የመጽሐፍ ቅዱስን ማናቸውም ቃላት መለወጥ አይቻልም። መጽሐፍ ቅዱስ እንደተለወጠ የሚያስቡ ሰዎችምን እንደተለወጠ ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል። ከሰላሳ ሺህ በላይ ጥንታዊ የአዲስ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት የዮሐንስ ደሴት ስብስብ (130ዓ.ም)፣ የቼስተር ቤይቲ ስብስብ (200 ዓ.ም)፣ የሳይናቲክ ጽሑፍ (350ዓ.ም)፣ የአሌክሳንደሪያ ጽሑፍ (400 ዓ.ም) እና የቫቲካን ጽሑፍ ጭምር በሮም ተጠብቀው ይገኛሉ። እነዚህ ጽሑፎች አሁን በክርስቲያኑ አብያተክርስቲያናት ጥቅም ላይ ካሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ፈጽሞ የተለዩ አይደሉም። ሁሉም ከመሐመድ በፊት መቶ አመታትን ያስቆጠሩ ናቸው። ሁሉም የአዲስ ኪዳን መጻሓፍት ከአስራ አንድ ጥቅሶች በቀር በጥንት ቤተክርስቲያን አባቶች የተካከተቱ ናቸው።

## IX. ቁርኣን መጽሐፍ ቅዱስን አይሽርም

በአብዛኛው ሙስሊማን ዘንድ ቁርኣን መጽሐፍ ቅዱስን እንደሻረው ተደርጎ ይወሰዳል። መሻር አንድን ህግ ፣ ስልጣን ወይም መመሪያ በሌላ መተካትን የሚያመላክት እሳቤ ነው። በቁርኣን ስለ መሻር የሚናገሩ ሁለት ክፍሎች ቢኖሩም፣ አንዳቸውም ስለ መጽሐፍ ቅዱስ አይናገሩም ፤ ስለ ቁርኣን እንጂ! ቁርኣን ሰለ ብሉይ እና አዲስ ኪዳን መሻር ፈጽሞ አይናገርም። ሰለ መሻር የሚናገሩ የቁርኣን ክፍሎች፡-

*ሱረቱ 2፥106*

*ከአንቀጽ ብንለውጥ ወይም እርሷን ብናስረሳህ ከርሷ የሚበልጥን ወይም ብጤዋን እናመጣለን፤ አላህ በነገሩ ሁሉ ላይ ከሃሊ(ቻይ) መኾኑን አታውቅምን?*

ኢብኑ አባስ እንደሚያስረዳው ይህ ክፍል መሐመድ በምሽት የሚሰጠውን አንዳንድ አንቀጾች ይረሳቸው ስለነበር፤ አላህ የተረሱትን አንቀጾች በተመሳሳይ ወይም ሌላ በተሻለ ቃላት ይለውጠው እንደ ነበር ነው፡፡[53] ይህ እውነት በራሱ የቁርኣንን ተዐማኒነት ጥያቄ ውስጥ ይከታል እንጂ፣ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ አንዳች አይናገርም፡፡

*ሱረቱ 22፥52*

*ከመልክተኛ እና ከነቢይም ከአንተ በፊት አንድንም አላክንም ባነበበ (እና ዝም ባለ) ጊዜ ሰይጣን በንባቡ ላይ (ማጥመሚያን ቃል) የሚጥል ቢሆን እንጅ፡፡ ወዲያውም አላህ ሰይጣን የሚለውን ያስወግዳል፡፡ ከዚያም አላህ አንቀጾችን ያጠናክራል፡፡ አላህም ዐዋቂ ጥበበኛ ነው፡፡*

ይህ ክፍል (አሳባ አል -ኑዙል በሱዩት እና ቡኻሪ) በሱረቱ አልነጅም 53፡ 19 እና 20 ያለውን በመጥቀስ ስለ ሦስቱ የአረብ እምነት የለሽ ጣኦታት አንቀጽ ጨምሯል፡፡ ሰይጣን ይህን መሰል አንቀጽ በመሐመድ መገለጥ ላይ ስለ ጨመረ፣ አላህ እንዲሰራው ሆኗል፡፡ ሳልማን ረሺድ ይህን አንቀጽ በአነጋጋሪ መጽሐፉ የሰይጣን አንቀጽ ብሎ ይጠራዋል፡፡

መሻር የሚለው እሳቤ የቁርኣንን አስተምህሮ ጽኑነት ለመጠበቅ ጥቅም ላይ የዋለ ቃል ነው፡፡ ስለ ወይን መጠጣት ከዚህ በታች የተቀመጡት አራት የቁርአን አንቀጾች መካካል አራተኛው በሙስሊማኑ ሊቃውንት ተሽሯል፡-

*ሱረቱ 16፥67*

*ከዘምባባዎችና ከወይኖችም ፍሬዎችን (እንመግባችኋለን)፡፡ ከእርሱ ጠጅንና መልካም ምግብንም ትሠራላችሁ፡፡ በዚህም ውስጥ ለሚያስቡ ሕዝቦች በእርግጥ ተዓምር አለለ፡፡*

*ሱረቱ 2፥219*

*አእምሮን ከሚቃወም መጠጥና ከቁማር ይጠይቁሃል፡፡ በሁለቱም ውስጥ ታላቅ ኃጢኣትና ለሰዎች ጥቅሞች አሉባቸው፡፡ ግን ኃጢኣታቸው ከጥቅማቸው በጣም ትልቅ ነው' በላቸው፡፡ ምንን እንደሚመጸውቱም (መጠኑን) ይጠይቁሃል፡፡ 'ትርፍን (መጽውቱ)' በላቸው፡፡ እንደዚሁ ታስተነትኑ ዘንድ አላህ ለናንተ አንቀጾችን ይገልጽላችኋል፡፡*

*ሱረቱ 4፡43*

*እናንተ ያመናችሁ ሆይ ! እናንተ የሰከራችሁ ኾናችሁ የምትሉትን ነገር እስከ ምታውቁ የረከሳችሁም ስትኾኑ መንገድን አላፊዎች ካልኾናችሁ በስተቀር (አካላታችሁን) እስከምትታጠቡ ድረስ ስግደትን አታቅርቡ፡፡ በሽተኞች ወይም በጉዞ ላይ ብትኾኑም ፣*

---

[53] **አል-ስዩቲ ፣ አሻብ አል ኑዙዑል ሱረቱ 2፡106፡፡**

*ወይንም ከእናንተ አንዱ ከዓነምድር ቢመጣ ፣ ወይንም ሴቶችን ብትነካኩና ዉሃን ባታገኙ ፣ንጹሕ የኾነ የምድር ገጽ አስቡ። ፊቶቻችሁንና እጆቻችሁንም (በርሱ) አስቡ። አላህ ይቅር ባይ መሐሪ ነውና።*

***ሱረቱ 5፥90***

*እናንተ ያመናችሁ ሆይ! የሚያሰክር መጠጥ ቁማርም ጣዖታትም አዝላምም ከሰይጣን ሥራ የኾኑ እርኩስ ብቻ ናቸው። (እርኩስን) ራቁትም ልትድኑ ይከጀላልና። በተመሳሳይ አል-ቂብላ (ወደ ጸሎት የሚያመሩበት ሥፍራ) አስመልክቶ የመጨረሻው አንቀጽ የተቀሩትን ሁለት አንቀጾች እንደሻረው ማስተዋል ይቻላል፡-*

***ሱረቱ 2፥125***

*ከኢብራሂምም መቆሚያ መስገጃን አድርጉ።*

***ሱረቱ 2፥142***

*ምሥራቁም ምዕራቡም የአላህ ነው።*

***ሱረቱ 2፥144***

*ወደ ምትወዳትም ቂብላ እናዞርሃለን። ስለዚህ ፊትህን ወደ ተከበረው መስጊድ (ወደ ካዕባ) አቅጣጫ አዙር።*

የሙስሊማኒ ነገረ-መለኮት ሊሂቃን የአንቀጾችን መሻር በሦስት መልክ ያስቀምጣሉ፡-

- ***ህጎች የሚሻሩበት አንቀጽ፡-*** ምንም እንኳ ቃሎች በቁርአን ቢገኙም፣ በዕለት ተዕለት ኢስላማዊ ህይወት የማይተገበሩ ሕጎች አሉ። ለምሳሌ፡- ሱረቱ 7፥19 "ገርን ጠባይ ያዝ። በመልካምም እዘዝ ። ባለጌዎቹንም ተዋቸው።" ሙስሊም ሊቃውንቱ "በመልካምም እዘዝ" እና "ባለጌዎቹንም ተዋቸው" ን ሲሽሩ ፣ "ገርን ጠባይ ያዝ" የሚለውን ቃል አልሻሩቱም።
- ***ህጎችም ቃሎችም የሚሻሩበት አንቀጽ፡-*** እነዚህ አንቀጾች በቁርኣን ውስጥ አይገኙም። ለምሳሌ፡- "በአላህ ዘንድ በላጭ ሀይማኖት ሀኒፋይት /hanifite/" የሚለው ቃልም ሆነ ሕግ በቁርኣን ላይ አይገኝም ፤" የአደም ልጅ በሸለቆ የሞላ ብር ቢሰጠው፣ ለሁለተኛ እና ለሶስተኛ ጊዜ ጭምር ይጠይቅ ነበር" የሚለው አንቀጽም እንዲሁ!
- ***ቃሎች የሚሻሩበት አንቀጽ*** ፡- ለምሳሌ፡- "አዋቂ ወንድ እና ሴት በዝሙት ኃጢአት ቢገኙ በድንጋይ ይወገሩ" የሚለው ቃል በቁርኣን አይገኝም ፤ ሆኖም በእነዚህ ቃላት ውስጥ ያለው ህግ ወይም መመሪያ ሊታዘዙት እንደሚገባ ግልጽ ነው።

## X. አራቱ ወንጌላት?

ሙስሊማኑ በአመዛኙ "ኢንጅል / ወንጌል/" ለ "ኢየሱስ የተሰጠ መጽሐፍ" አድርገው ይወስዳሉ፡፡ በዚህም ክርስቲያኑ እውነተኛውን ኢንጅል ከመጠበቅ ይልቅ፣ አራት ኢንጅሎችን ፡- ማቴዎስ፣ ማርቆስ ፣ሉቃስ እና ዮሐንስ መጽሓፍት እንዳላቸው ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

እነዚህኑን መንታ እውነታዎች ለሙስሊማኑ በግልጽ ለማስረዳት አስቀድሞ ኢንጅል (ወንጌል) የሚለውን ቃል መፍታት ያሻል፡፡ ቃሉ "የምስራች" ማለት ነው፤ ኢንጅላችን (ወንጌላችን) ኢየሱስ ሰውን ለማዳን ወደ አለም እንደመጣ ያበስራል፡፡ ኢየሱስ የምስራች ሊጽፍልን አልምጣም፣ እርሱ ራሱ የምስራች /መልካም ዜና/ ነው፡፡

አራት ክርስቲያን ጸሓፍት የምስራቹን (ኢየሱስን) ጻፉልን፡፡ ሀኪሙ ሉቃስ ይህን በመልዕከቱ አጉልቶ ያስቀምጣል፡-

*ሉቃስ 1፥1-4*

*ቴዎፍሎስ ሆይ ኢየሱስ የመረጣቸውን ሐዋሪያትን በመንፈስ ቅዱስ ካዘዛቸው በኃላ እስከ ዐረገበት ቀን ድረስ ያደረገውና ያስተምረው ዘንድ ስለ ጀመረው ሁሉ መጀመሪያውን ነገር ጻፍሁ፤ ደግሞ አርባ ቀን እየታያቸው ስለ እግዚአብሔርም መንግስት ነገር እየነገራቸው በብዙ ማስረጃ ከሕማመቱ በኃላ ሕያው ሆኖ ለእነርሱ ራሱን አሳያቸው ፡፡*

በመንፈስ ቅዱስ መሪነት በአራቱ ጸሓፍት የተዘገበውን አንዱን ታሪክ ቤተክርስቲያን ጠብቃለች፤ አራቱ መጻሓፍት አንዱን ወንጌል /የምስራች/ ይናገራሉ፡፡

## XI. ሙስሊማኑ ተዐማኒ -የለሹን የበርናበስ ወንጌል ለምን ይመስላሉ

የበርንባስ ወንጌል ስለ ኢየሱስ የሚናገር ተዐማኒ አልባ መጽሐፍ ነው፤ እውነተኛ ወንጌልም አይደለም፡፡ መጽሐፉ በ15ኛው ክፍለ ዘመን ወደ እስልምና በተለወጠ የጣሊያን መነኩሴ አዲስ እምነቱን ለማስተዋወቅ የተጻፈ ነው፡፡ ጄ. ኤፍ . ክራመር የተባለ የፕሩስያ (Prussia) መሪ በጣሊያን ቋንቋ 1970 ላይ የተጻፈውን የመጀመሪያ ቅጂ አገኘ፤ ኢዩገን ለተባለ የሳቮይ ልዑል ቅጂው በ1713 ቀረበ፤ በቬና ለሚገኝ ብሔራዊ ቤተመጻሕፍትም በ1738 ተሰጠ፡፡

መሐመድ ጎርባል መጽሐፉን አስመልክቶ የሚከተለውን አስቀምጧል ፡- "የበርናባስ ወንጌል በአውሮፓ ሰው የተጻፈ የውሸት ወንጌል ነው፡፡ መጽሐፉ በኢየሱስ ዘመን የነበረውን ፖለቲካዊ እና ሀይማኖታዊ አውድ አዛንፏል፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዳልሆነ

መናገሩንም ያትታል፡፡"[54] ጥንታዊያን ሙስሊም ጸሓፍት የበርንባስን ወንጌል አንዳችም በምንጭነት አልጠቀሱም፣ በርካቶቹ ከመጻፉ በፊት ያለፉ ነበሩ፡፡ የሙስሊም ጸሓፍት የሆኑቱ አል -ታብሪ ኢን ኢብኑ ኻቲር የእውነተኛ ወንጌል ጸሓፍት ዝርዝር ውስጥ አላካተቱትም፡፡

ዘመናዊ ሙስሊማን ይህን የውሸት ወንጌል በቀኖና ደረጃ የሚቀበሉበት አምስት ምክንያቶች ይጠቀሳሉ፡-

(1) ኢየሱስ ነብይ (በርናባስ 1፥4) እንጂ ፣ አምላክ (92፥17-20) ወይም የእግዚአብሔር ልጅ (2125፥፣6) እንዳልሆነ ያስተምራል፡፡

(2) የአስቆሮጡ ይሁዳ ኢየሱስን እንደሚመስል፣ ኢየሱስ ያለምንም ጉዳት ወደ ሰማይ በሚወሰድበት ጊዜ እንደታሰረ አንደተሰቀለም ያስተምራል (112፣ 139፥4-9) ፡፡

(3) ብሉይ ኪዳን (72፥11፣ 124፥ 6-10) እንደ አዲስ ኪዳን ሁሉ (52፥14. 96፥9-11) እንደተለወጠ ይናገራል፡፡

(4) የእግዚአብሔር ኪዳን ለሂሳቅ ሳይሆን፣ ለኢስማኤል እንደሆነ ያስተምራል (43፥20-31)፡፡

(5) ኢየሱስ የመጣው ለመሐመድ ጥርጊያ መንገድ ለማዘጋጀት ነው ፣ በዚህም ኢየሱስ ራሱ ስለ መሐመድ መምጣት እንደተነበየ ያስተምራል (42 ፥10-13፣ 72፥ 10-72)፡፡

በበርናባስ የውሸት ወንጌል በርካታ ተቃርኖአዊ አሳቦች ይገኛሉ፤ በመጽሐፉ ከሚገኙ ስህተቶች መካከልም ፡-

- *በርናባስ 201፥-2 እና 92፥3* ፡- ናዝሬትና ኢየሩሳሌም ሁለት የባህር ዳርቻዎች እንደሆኑ ይናገራል፡፡
- *በርናባስ 152፥75* ፡- አይሁድ ወይንን በበርሜል እንደሚያስቀምጡ ይነገራል፤ በእርግጥ ወይን የሚቀመጠው በወይን አቁማዳ ነው፡፡ በበርሜል የማስቀመጥ ተግባር በመካካለኛው ዘመን የነበረ ልማድ ነው፡፡
- *በርናባስ 82 ፥18* ፡- ኢዮቤልዩ በአንድ መቶ አመት አንድ ጊዜ የሚከበር እንደሆነ ይናገራል፤ መጽሐፍ ቅዱስ ግን በአምሳ አመት አንድ ጊዜ መሆኑን ይናገራል ( ዘሌዋውያን 25 ፥11)፡፡
- *በርናባስ 3፥5-20* ፡- ማርያም ያለምንም ህመም ኢየሱስን እንደወለደች ይናገራል ፤ ሱረቱ 192፥2፣23 ግን ለሞት እስክትዳረግ ድረስ በጽኑ ህመም አንዳለፈች ያስታውቃል፡፡

[54] መሐመድ ጎርባል፣ አል -ማውሳ፣ አል-ዓረቢያ፣ አል- ሙያሳ (ካይሮ፣ የግል ህትመት፣ 1986)፣ ገጽ 354፡፡

- *በርናባስ 1053፥08* ፡- ዘጠኘ ሰማያት እንዳሉ ይናገራል፡፡ ይህ በሱረቱ 17፥44 ሰባት ሰማያት እንዳሉ ከሚናገረው አሳብ ይቃረናል፡፡

## XI. መጽሐፍ ቅዱስ ሕይወት ይለውጣል

የመጽሐፍ ቅዱስ ተዐማኒነት የመጨረሻው ማረጋገጫ ሕይወትን መለወጡ ነው፡ ኢስላም የቀደመውን የአረብ ጠብ አጫሪ ባህሪ ሊቀይር አልቻለም ነበር፡፡ ከአራቱ ሦስቱ ካሊፎች ተገድለዋል፣ የአረብ ጦረኞች ሙስሊም ሲሆኑ፣ ሌሎች ጎሳዎችና ሀገራትን በጦርነት መግዛት አላቆሙም፣ በመሐመድ እጅ ይሞግተው የነበረው (አይሁዳዊ ገጣሚ) ሕይወት አልፏል፡፡

የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል በታወጀ ቁጥር ግን የሰሚዎች ህይወት ይለወጣል፡፡ መንፈስ ቅዱስ በሚታወጀው ቃል ሰዎችን ለንስሃ ያዘጋጃል፡፡ "የሰረቀ ከእንግዲህ አይስረቅ ፣ ነገር ግን በዚያ ፈንታ ለጎደለው የሚያካፍለው እንዲኖርለት በገዛ እጆቹ መልካምን እየሠራ ይድከም" (ኤፌሶን 42፥8)፡፡ መዝሙረኛው እንዲህ ይናገራል፡-

***መዝሙር 19፥7-11***

*የእግዚአብሔር ሕግ ፍጹም ነው፣ ነፍስን ይመልሳል፤ የእግዚአብሔር ምስክር የታመነ ነው፣ ሕጻናትን ጠቢባን የደርጋል፡፡ የእግዚአብሔር ሥርዓት ቅን ነው፣ ልብንም ደስ ያሰኛል፡፡ የእግዚአብሔር ትእዛዝ ብሩህ ነው፣ ዓይንንም ያበራል ፡፡ የአግዚአብሔር ፍርድ እውነትና ቅንነት በአንድነት ነው ፡፡ ከወርቅና ከክቡር ዕንቁ ይልቅ ይወደዳል፣ ከማርና ከማር ወለላም ይጣፍጣል፡፡ ባሪያህ ደግሞ ይጠብቀዋል፣ በመጠበቁም እጅግ ይጠቀማል፡፡*

**የግል ማስታወሻ**

11

# ሙስሊማኑ መስቀልን እንዴት ያዩታል

ሙስሊማኑ ለኢየሱስ ካላቸው ጥልቅ አክብሮት የተነሳ መሰቀሉን አያምኑም። ሐዋሪያው ጴጥሮስ በመንፈስ ቅዱስ ከመሞላቱ በፊት "ከዚያን ቀን ጀምሮ ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ይሄዱ ዘንድ ከሽማግሌዎች እና ከካህናት አለቆች ከጻፎችም ብዙ መከራ ይቀበል እና ይገድል ዘንድ፣ በሦስተኛውም ቀን ይነሣ ዘንድ እንዲገባው ለደቀመዛሙርቱ ይገልጥላቸው ጀመር። ጴጥሮስም ወደ እርሱ ወስዶ ፦ አይሁንብህ ጌታ ሆይ ፣ ይህ ከቶ አይደርስብህም ብሎ ሊገሥጸው ጀመረ" (ማቴዎስ 16፥21-23)።

ፈጣሪን /አምላክን/ ፍጹም ንጹህና ልዑል አድረገው በሚመለከቱ እንደ እስልምና እና አይሁድ ሀይማኖቶች የፈጣሪ መከራ መቀበል እና የመሞት እውነታ መቀበል እጅጉን ያስቸግራል፤ እንደምን ታላቅ እና ልዑል ፈጣሪ በዚህ አይነት ሽንፈት /ድካም/ ሊገኝ ቻለ? የሚለውን ጥያቄ እንዲያነሱ ያደርጋል።

ሙስሊማኑና አይሁድ ይህን ጥያቄ ዘወትር ያነሳሉ፤ ክርስቲያኑ የነገረ-መለኮት ሊሂቃን ለዚህ በቂ መልስ አላቸው። የኒቂያ እምነት መግለጫ አዘጋጅ አሌክሳንደሪያ አትናሲየስ የሚከተለውን ማብራሪያ ያስቀምጣል፦ " አንጥረኛ ማቅለጫ ብረቱን በእሳት ውስጥ በማኖር ቅርጽ ያላቸውን ብረቶች ይሰራል፤ ማቅለጫው ብረቱን በመቀጥቀጥ ሲሰራው ብረትን እንጂ እሳትን አይቀጠቅጥም። የኢየሱስ መስቀል ስቃይም እንዲሁ ነው።"[55] ከዘመናት በኃላ በ820 ዓ.ም በአብዱል ራህማን ካሊፍ አብዱ ማሌክ አልሃሺም እና ኢብራሂም አል-ታባርኒ መካከል ክርክሮች ነበሩ። ክርክሩ በአል-ባዳዊ አል-ባህሊ በተነገረው " የኢየሱስ መለኮታዊ ባህሪይ በጦር በሚወጋበት ጊዜ ትቶት ሄዷል፣ አሊያም መለኮታዊ ባህሪው ከኢየሱስ ጋር አብሮ ታሟል፣ ሞቷልም" አሳብ ላይ ነበር። መኖክሴው "ግመል በጸሐይ ወቅት በስለት ቢላ ቢመታ፣ ጸሐይዋ ብርሃንዋን ከመስጠት ትቆማለችን? በኢየሱስ መከራ የሆነው እንዲሁ ነው"[56] ሲል ይናገራል።

[55] ቅዱስ አትናቲዮስ ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ተስጉት (ማክታባት አል- መሃቢ፣ ካይሮ፣ ቀ.አልተጠቀሰም ) ገጽ.5።
[56] አል-ታባራኒ፣ ኢብራሂም፣ የነገረ መለኮት ሙግት፣ (ቪሊች፣ የህይወት ብርሃን) ፣ገጽ 42።

## I. ስቅለት እና ቁርኣን

ሙስሊማኑን በርዕሰ ጉዳዩ ዙሪያ የሚያግዙ ጥቂት የቁርኣን ክፍሎችን እንመለክት፡-

***ሱረቱ 4157፣158***

*እኛ የአላህን መልዕክተኛ የመርየምን ልጅ አል-መሲሕ ዒሳን ገደልን በማለታቸውም (ረገምናቸው)። አልገደሉትም አልሰቀሉትምም። ግን ለእነሱ (የተገደለው ሰው በዒሳ) ተመሰለ። እነዚያም በእርሱ ነገር የተለያዩት ከእነርሱ (መገደል) በመጠራጠር ውስጥ ናቸው። ጥርጣሬን ከመከተል በስተቀር በእርሱ ነገር ምንም ዕውቀት የላቸውም። በእርግጥም አልገደሉትም። ይልቁንስ አላህ (ዒሳን) ወደርሱ አነሳው። አላህም አሸናፊ ጥበበኛ ነው።*

በዚህ ክፍል አሳብ ላይ የተሚገተው የመጀመሪያ ሰው መሐመድ አይደለም። የጥንት ክርስቲያን አማኞች ሳይቀሩ "በተገደለው ሰው ተመሰለ" የሚለውን አሳብ ተቀብለውት ኖረዋል። በዚህ ርዕስ ላይ በተጻፈው መጽሐፉ፣ ኪራዋኒ "በተገደለው ሰው ተመሰለ' የሚለው ተረት በቁርኣን የሚገኝ ብቻ ሳይሆን፣ ከእስልም መጸነስ ፊት በክርስቲያን መናፍቃን ዘንድ የተሰራጨ እንደነበር" ይገልጻል።[57]

ኪራዋኒ በርካታ ምሳሌዎችን ያወሳል፡-

- ኖስቲሳዊው ቤዝላይድስ የክርስቶስን መስቀል የተሸከመው ስሞዖን በክርስቶስ ፈንታ ተሰቅሏል፤ ፈጣሪም በእርሱ ላይ ክርስቶሰን መስሎታል ይላል።
- ዶሴቴስትስያውያን ኢየሱስ ፈጽሞ እንዳልተሰቀለ ይሞግታሉ። ዶሰቲክ (Docetic) የግሪክ ቃል ሲሆን "መመሰል"ን ይወክላል።
- በ185 ዓ.ም ከካህናቱ ዘንድ የመነጨው ኑፋቄ "እግዚአብሔር ክርስቶስ እንዲሰቀል አልፈቀደም፣ ወደ ራሱም ወስዶታል" ይላል።
- በ276 ዓ.ም ማኒ የተባለ ነብይ የተሰቀለው ኢየሱስ ከሞት ያስነሳው የናይን ከተማ ባልቴት ልጅ ነው ብሏል። በማንሲያን ልማድ ሰይጣን ኢየሱስን ለመስቀል ሞክሮ ስላልተሳካለት፣ እርሱ ራሱ እንደተሰቀለ ይናገራል።
- በ370 ዓ.ም የኖስቲክ ክፍል የኢየሱስ ስቅለትን ይክዳል "ኢየሱስ አልተሰቀለም፣ በሚመለከቱት ሰዎች ዘንድ እንደተሰቀለ ተመስሎ ነው" ይላል።

---

[57] ኹራዋይኒ ፣ኢየሱስ ተሰቅሏልን?(ቪ.ሲ.ች፣ የህይወት ብርሃን፣1994)፣ ገጽ 27።

- በ520ዓ.ም የሶሪያ ጳጳስ ሲቨረስ ወደ አሌክሳንደሪያ ሄዶ ያገኛቸው ፈላስፎች ኢየሱስ አልተሰቀለም፣ በመስቀል ለቸነከሩት ሰዎች ታይቷል እንጂ የሚል አስተምህሮ ገጥሞት ነበር፡፡
- በ560 ዓ.ም ቲዮዶር የተባለ መኖክሴ የክርስቶስን ሰዋዊ ባህሪ ሆነ ስቅለት ክዷል፡፡
- በ610 ዓ.ም ዮሐንስ የተባለ የሳይብረስ ጳጳስ ክርስቶስ አለመሰቀሉን ፣ በፈንታው መመሰሉን ይሞግታል፡፡

እነዚህ ኑፋቄዎች በመሐመድ ዘመን በዓረብ ምድር እጅጉን የተስፋፉ ትምህርቶች ነበሩ፡፡ በ380 ዓ.ም የኮንስታትኖፕል ጉባኤ በዓረብ እና ኢየሩሳሌም የሚገኙ አብያተክርስቲያናት መካካላቸው ስላለው መከፋፈል እና ስጋት እንዲጎበኝ ልኮት ነበር፡፡ እነዚህ ኑፋቄዎች ምንም አይነት ታሪካዊ መሰረት የሌላቸው፣ ከግል ከንቱ አሳብ የሚመነጩ፣ በክርስቶስ ኢየሱስ ሰዋዊ ባህሪይ ላይ የሚያነጣጥሩ ናቸው፡፡

## II. ሱረቱ 4፥157፣158 ትርጓሜ

እነዚህን ሁለት ቁጥሮች በጥንቃቄ በመመልከት የሚከተሉትን እውነታዎች ማስረገጥ ይቻላል፡-

### (1) አይሁድ መሲሑን ገድለናል አይሉም ነበር

ቁጥር 157 አይሁድ "እኛ የአላህን መልዕክተኛ የመርየምን ልጅ አል-መሲሕ ዒሳን ገደልን" ማለታቸውን ይናገራል፡፡ ኢየሱስ መሲሓቸው እንደሆነ ቢገነዘቡ ኖሮ አይገድሉትም ነበር፡፡ የቁርኣን ክፍሎች በዚህ መልክ ነው የሚገልጻቸው፡፡

### (2) የስቅለትን ታሪካዊ እውነት መካድ አይቻልም

"አልገደሉትም አልሰቀሉትም" የሚለው ሐርግ በብዙ መልኩ ሊተረጎም ይችላል፡-

- ኢየሱስን የሰቀሉት አይሁዶች ሳይሆኑ ሮማውያን ናቸው፡፡
- አይሁዶች የኢየሱስ ስቅለት መንገዶች አልነበሩም፤ የኢየሱስ ስቅለት በራሱ ነጻ ፍቃድ ላይ የተመሰረተ ነው፡- "እኔ በፈቃዴ አኖራታለሁ እንጂ፣ ከእኔ ማንም አይወስዳትም" (ዮሐንስ 10፡18)፡፡
- ኢየሱስን  የመግድል ሙከራ ውጤታማ ያልሆነው በሶስተኛው ቀን ከሞት በመነሳቱ ነው፡፡

ቁርኣን የሰማዕት ሞት ፍጻሜን ሲናገር "እነዚያን በአላህ መንገድ የተገደሉትን ሙታን አድርገህ አትገምታቸው፡፡ በእርግጥ እነርሱ እጌታቸው ዘንድ ሕያውን ናቸው፣ ይመገባሉ" (ሱረቱ 3፥169)፡፡ በተጨማሪም ሱረቱ 2፥154 " በአላህ መንገድ (ለሀይማኖቱ) የሚገድሉትን

ሰዎችም ሙታን ናችሁ አትበሉ፡፡ በእውነቱ ሕያውን ናቸው፣ ግን አታውቁም፡፡ ሰማዕታት በእግዚአብሔር ፊት ሕያዋን ስለሆኑ፣ሙታን አድርገን መቁጠር እንደሌለብን ክፍሎቹ ያስገነዝባሉ፡፡ በመስቀል ላይ የኢየሱስን ሞት በተመሳሳይ መንገድ መረዳት ይቻላል፡፡ መቶ አለቃው ለጲላጦስ ኢየሱስ መሞቱን መስክሯል (ማርቆስ 15፥44)፡፡ በመቃብር ውስጥ እንደነበረ፣ የመቃብር ደጅ ድንጋይ እንደ ተንከባለለም መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል (ማርቆስ15፥46)፡፡ መቃብሩ በጠባቂዎች ተጠብቆ አንደ ነበር ማቴዎስ 27፡66 ዘግቧል፡፡ አይሁዶች በኢየሱስ ሞት፣ ትምህርቶቹና ተአምራቶቹ ማብቃት ደስተኞች ነበሩ፡፡ ጭካኔ የሞላበት የኢየሱስ አሟሟት ተከታዮቹን የሚያስጠነቅቅ ነበር፡፡ የኢየሱስ ትንቢት ፍጻሜ አግኝቷል እኔም ከምድር ከፍ ከፍ ያልሁ እንደሆነ ሁሉን ወደ እኔ እስባለሁ" (ዮሐንስ 12፡32)፡፡ ከዚህ አንጻር አይሁድ "አልገደሉትም አልሰቀሉትምም፡፡"

### (3) ስቅለት እስላማዊ እንጂ ክርስቲያናዊ ሙግት አይደለም

ቁጥር 157 "በእርሱ ነገር የተለያዩት ከእነርሱ (መገደል) በመጠራጠር ውስጥ ናቸው፡፡" ክርስቲያኑ ስቅለትን አስመልክቶ ከሚጠራጠሩቱ አንዳልሆነ ልብ ይሏል፡፡ አራቱ ወንጌላት በስቅለቱና ተያያዥ ክስተቶች ዙሪያ የዘገቡት እውነት አንድ ነው፡፡ ሙስሊማኑ በዚህ እውነት የማይስማሙ ተጠራጣሪዎች ናቸው፤ "ጥርጣሬን ከመከተል በስተቀር በእርሱ ነገር ምንም ዕውቀት የላቸውም ፡፡"

## III. የሙስሊማኑ ሻቢህ/SHABIH/ ተቃርኖአዊ እሳቤ

ሙስሊማኑ ፈጣሪ ክርስቶስን በሌላ ሰው (ኢየሱስ በተወሰደ ጊዜ  በሞተ ሌላ ሰው ላይ ክርስቶስን እንደመሰለው ይናገራሉ፡፡ ሻቢህ ምንነት ላይ በክርስቲያኑ ካሉ ኑፋቄዎች ይልቅ በቁርኣን ጸሓፍት መካከል ስምምነት የለም፡፡

- አል ጃላላን "ለእነሱ (የተገደለው ሰው በዒሳ) ተመሰለ" የሚለውን ሲያብራራ፣አላህ ራሱ ኢየሱስን በአንድ ሌላ ሰው ላይ እንዳደረገው፣ ያም ሰው እንዲታሰር እንደተደረገ ፣ በዚህም ምክንያት አይሁዳውያኑ ሳይቀር ኢየሱስ ስለ መሰላቸው ማስቃየታቸውን እና መግደላቸውን ይናገራል፡፡ "እነዚያም በእርሱ ነገር የተለያዩት ከእነርሱ (መገደል) በመጠራጠር ውስጥ ናቸው" በማለት አንዳንድ አይሁዳውያን የተሰቀለው ሰው " ፊቱ የኢየሱስ  ይመስላል ፣ አካሉ ግን የርሱ አይደለም" ሲሉ ቢያስታውቁም ፣ ሌሎቹ ግን " እርሱ ራሱ ነው" የሚለውን ሃቅ አጽንተዋል፡፡

- አል -ባይዳዊ “ የተወሰኑ የአይሁድ ክፍሎች ኢየሱስን እና እናቱን ማረኩ ፣ ኢየሱስም በረገማቸው ጊዜ ወደ ዝንጀሮ እና አሳማነት ተቀየሩ፡፡ አይሁድ ኢየሱስን ለመግደል በተሰበሰቡ ጊዜ ፈጣሪ ኢየሱስን እንደሚወስደው ተናገረ፡፡ ኢየሱስም ለጓደኞቹ ‘ከእናንተ መካከል የእኔን አምሳያ ወስዶ የሚሰቀል እና የሚሞት በዚህም ገነት መግባት የሚፈልግ ማነው?’ ብሎ ጠየቀ፡፡ ከእነርሱም ፍቃደኛ የሆነውን ሰው ፈጣሪ ኢየሱስን በመመስል እንዲሰቀል፣እንዲሞትም አደረገ” ሲል ይናገራል፡፡
- አል-ዛማኽሻሪ “ሻቢህ ላሁም” ኢየሱስ እንደሞተ እና እንደተሰቀል እንደመሰላቸው የሚያመላክት ሐረግ ነው፡፡ እርሱ ግን ፈጣሪ ስለ ወሰደው ህያው ነው” የሚለውን አሳብ ያስቀምጣል፡፡

አል-ራዚ ሻቢህን በተመለከተ አራት የተለያዩ አሳቦችን ይሰነዝራል፡-

1. ኢየሱስን ለማሰር በሚሞክሩበት ጊዜ አላገኙትም፤ በምትኩ በቤት ውስጥ የተገኘው ጁዳስ ፈጣሪ ኢየሱስን እንዲመስል አድርጎታል፡፡ ከቤት በሚወጣበት ጊዜም ኢየሱስ ስለ መሳላቸው ሊሰቅሉት ወስደውታል፡፡
2. አይሁዶች ኢየሱስን ባሰሩት ጊዜ ጠባቂን አኑረው ነበር፡፡ ፈጣሪም እርሱን ተአምራዊ በሆነ መንገድ ሲወስደው፣ ጠባቂውን በመስሉ እንዲገኝ አድርጎታል፡፡ ጠባቂውም “እኔ እየሱስ አየደለሁም! እኔ ኢየሱስ አይደለሁም!” እያለ በመጮህ ተሰቅሏል፡፡
3. ኢየሱስ ከወዳጆቹ ለአንዱ በምትኩ የሚሞት ከሆነ፣ በገነት ቦታ እንደሚያዘጋጅለት ቃል ገብቶአል፡፡ ፈጣሪም ይህን ፈቃደኛ ሰው በኢየሱስ እንዲመሰል አደረገ፤ ሰውየውም ታሰረ ተሰቀለም፡፡ ኢየሱስ ግን ወደ ሰማይ በፈጣሪ ተወስዷል፡፡
4. ኢየሱስን የካደው ተካታይ ኢየሱስ ያለበትን ቦታ ለአይሁዶች መርቷል፡፡ ሆኖም በስፍራው ኢየሱስ በታጣ ጊዜ ፈጣሪ ከሀዲውን ተከታይ ኢየሱስ እንዲመስል አድርጎታል፤ በኢየሱስም ፈንታ ተይዞ ተሰቅሏል፡፡

የኢየሱስን የሞት ጊዜ ገድብ አላህ በቁርኣን እንደሚከተለው ገልጿል፡-

***ሱረቱ 3፥ 55***

***አላህም ባለ ጊዜ (አስታውስ) ፡፡ ዒሳ ሆይ! እኔ ወስጂህ ወደ እኔም አንሺህ ነኝ፡፡ ከእነዚያም ከካዱት ሰዎች አጥሪህ ነኝ እነዚያንም የተከተሉህን እስከ ትንሣኤ ቀን ድረስ ከነዚያ ከካዱት በላይ አድራጊ ነኝ፡ ከዚያም መመለሻችሁ ወደ እኔ ነው፡፡ በርሱ ትለዩበትም በነበራችሁት ነገር በመካከላችሁ እፈርዳለሁ፡፡***

ይህን ክፍል በመንተራስ አል-ራዚ የሞቱን ጊዜ አስመልክቶ የተለያዩ አመለካከቶችን ያስቀምጣል፡-

- ውሃቢ ኢብኑ ሙናቢ ኢየሱስ ለሦስት ሰዓታት መሞቱን በፈጣሪ መወሰዱን ያስረግጣል፡፡
- መሐመድ ኢብኑ አይዛክ የኢየሱስ ሞት ለሰባት ሰዓታት መቆየቱን፣ ፈጣሪም እንዳስነሳው እና እንደ ወሰደው ይናገራል፡፡
- አል ራቢ ኢብኑን አናስ ፈጣሪ "ኢየሱስ እንዲሞት አድርጎታል፣ ወደ ሰማይም ወስዶታል" ሲል ይናገራል፡፡ "አላህ ነፍሶችን በሞታቸው ጊዜ ይወስዳል፡፡ ያችንም ያልሞተች በእንቅልፏ ጊዜ ይወስዳታል" (ሱረቱ 39 ፥42)፡፡
- እድሪስ ኢየሱስ የሞተው ለሦስት ሰዓታት አንደሆነ ፣ አላህም አስነስቶ እንደወሰደው ያስታውቃል፡፡

በ10ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ በባስራና ኢራቅ የተመሰረተው የዓረብ ወንድማማች ክፍል የሆነው ኢክዋን አል-ሳፋ (አል-ሳፋ ወንድሞች) "ኢየሱስ መሞቱን ፣ ለወገኖቹም መታየቱን" ያስረግጣል፡፡[58]

## IV. የአልራዚ ስድስቱ የሻቢህ እሳቤ ክፍተቶች

አል-ራዚ የኢየሱስ ስቅለት በተመለከተ "መሰለ" የሚለው አሳብ ስድስት ችግሮች እንዳሉበት ይጠቁማል፡-[59]

### (1)የመረዳት አቅም አጠራጣሪነት

አንድ ሰው በሌላ ሰው እንዲመሰል የማድረግ እሳቤ አደናጋሪ ነው፡፡ ልጄን በመጀመሪያም ሆነ ሁለተኛ ጊዜ ብመለከተው፣ ለሁለተኛ ጊዜ ያየሁት የመጀመሪያው ልጄ ሳይሆን ፣ እርሱን የሚመስለው ነው ብሎ መውሰድ እውነታውን እንደመካድ (መካድ) ይቆጠራል፡፡ በተመሳሳይ የመሐመድ ባልደረቦች ሲያስተምር እና ሲመክር ያዩት መሐመድ እውነተኛው መሐመድ ሳይሆን፣ እርሱን እንዲመስለው የተደረገው ነው ብሎ መቀበል እንዴት ይቻላል? ሕግን ማጣመም ካልሆነ በቀር ! ባጠቃላይ እንደነዚህ ያሉ አደናጋሪ እሳቤዎች የትንቢት ፍጻሜን እንድምታ ትርጉም የለሽ ያደርጉታል፡፡


አል-ራዚ በፈጣሪ ሁሉ ቻይነት የሚያምን ሁሉ በሌላ ሰው አምሳያ አንድን ሰው መፍጠር እንደሚችል መቀበል አያዳግተውም፡፡ ሆኖም ይህ ከላይ ለተቀመጠው አደናጋሪ አሳብ አስረጂ አድርጎ መውሰድ አስፈላጊ አለመሆኑን ያስረግጣል፡፡

[58] አክዋን አል-ሳፍ፣ ኢንሳክሎፒዲያ ፣ ራሳል ኢክዋን አል-ሳፍ ዋ ኪሂላን ለ-ዋፋ፣ቅጽ 4፣ገጽ 30፡፡
[59] ኹራዋይኒ፣ገጽ. 23- 26፡፡

### (2) ኢየሱስ መለኮታዊ ኃይሉን አለመጠቀሙ

ፈጣሪ ኢየሱስን እንዲያብር ጅብሪልን አዞታል፤"በቅዱስ መንፈስ (በገብሬል) ባበረታሁ ጊዜ" (ሱረቱ 5፥110)። የጅብሪል አንዱ ክንፍ ጫፍ ብቻ የሰው ዘርን በሙሉ መጠበቅ ይችላል፤ ታዲያ ኢየሱስን ከአይሁድ እንዴት ሊጠብቀው ተሳነው? ኢየሱስ ከሞት የማስነሳት ስልጣን፣ አይነ-ሰውራን እና ለምጻምን የመፈወስ ኃይል እያለው ስለ ምን ለሞት እና ለስቃይ የዳረጉትን አይሁዳውያኑ መከልከል አልቻለም?

አል-ራዚ ጅብሪል ኢየሱስን ቢያግዝ፣ፈጣሪም ኢየሱስ አይሁዳውያንን እንዲበቀል ቢያደረግ ኖሮ፣ የኢየሱስ ተአምራቶች በአስጋዳች ኃይል ይፈጸሙ እንደነበር ይናገራል፤ ይህ ፈጽሞ ተቀባይነት



የሌለው እንደሆነ ማስተዋል አያዳግትም፡፡

### (3) አላስፍላጊ ኹነቶች

ልዑል ፈጣሪ ኢየሱስን ወደ ሰማይ በመውስድ ከጠላቶቹ ሊያድነው ይችል ነበር፤ ያለ ምንም ዓላማ በሌላ ሰው እንዲመሰል፣ እንዲሰቃይ እና እንዲሞት ማድረግ አንዳች ረብ የለውም፡፡

አል-ራዚ ፈጣሪ ኢየሱስን ከወሰደው፣ በሌላ ሰውም እንዲመሰል ካላደረገው፣ ተአምራቱ በሌላ አስገዳጅ ኃይል ይፈጸም ነበር ይላል፡፡

### (4) መለኮታዊ መታላል

ፈጣሪ ኢየሱስን በሌላ ሰው እንዲመስል በማድረግ ወደ ሰማይ ቢወስደው ሰዎች ኢየሱስ ሊመስላቸው ይችላል፡፡ ይህም እንዲታለሉ እና አንዲጠራጠሩ ያደርጋል፣ ሆኖም መለኮታዊ ጥበብን በዚህ ደረጃ ማሰብ ያዳግታል፡፡

አልራዚ የኢየሱስ ደቀመዛሙርት በዙሪያቸው ስለ ነበረው ክስተት ሁሉ ዕውቀቱ ያላቸው ህያው ምስክሮች ስለ ነበሩ አሻሚ አሳቦች ሊኖሩ እንደማይችሉ ይገልጻል፡፡

### (5) ሀይማኖታዊ ባህልን ዋጋ ማሳነስ

በምስራቅ እና ምዕራብ ንቅፈ ክበብ የሚገኙ በርካታ ክርስቲያኖኑ ለክርስቶስ ኢየሱስ ካላቸው ጥልቅ ፍቅር እና አክብሮት ኢየሱስ እንደሞተ እና እንደተሰቀለ ማየታቸውን ዘግበዋል፡፡ ይህን አለመቀበል የባህልን፣ የመሐመድን፣ የኢየሱስ እና ሌሎች ነብያት ታሪካዊነት መካድ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ፈሬ-ቢስነት ነው፡፡

በዚያን ጊዜ የነበሩ እማኞች ጥቂት ከመኾናቸው የተነሳ የመታለል ዕድላቸው ከፍተኛ ነው፡፡ አፈ- ታሪክ ወደ ጥቂቶች በሚተላለፍበት ጊዜ ዕውቀት ያለው ጠቀሜታ ዋጋ- የለሽ ይሆናል፡፡

### (6) የሚሰቀለው ሰው ማምለጥ አለመዳዳቱ

አፈ-ታሪክ እንደሚናገረው የተሰቀለው ሰው ብዙ ጊዜ ኖሯል፡፡ የተሰቀለው ሰው ኢየሱስ ካልነበረ በፍርሃት ቃል "እኔ ኢየሱስ አይደለሁም! እኔ ሌላ ሰው ነኝ!" በማለት ባወጀ፤ በህዝቡ መካካልም ታዋቂ በሆነ! ነገር ግን ይህ አለመከሰቱ ጉዳዩን እርባና ቢስ ያደርገዋል፡፡

አል-ራዚ ኢየሱስን እንዲመስል የተደረገው ሰው አማኝ እና ፍቃደኛ ስለ ነበር እውነቱን ማወጅ አላስፈለገውም ይላል፡፡ ባጭሩ በዚህ ረገድ የሚነሳው ጥያቄ በርካታ መላምቶችን የሚፈጥር ሲሆን፣ ቁርኣን የመሐመድን እውነተኛነት ያልምንም ተቃርኖ ዘግቧል፡፡

ኢስላማዊው ሊቅ ከላይ ያሉትን ሙግቶች ለመፍታት ቢሞክርም፣ ውስብስብነቱ ግልጽ መኾኑ መረዳት አያዳግትም፡፡ ግልጽ የመፍትሄ አሳቦችን መቀበል አመቻል የሻቢህ እሳቤን የማይጋፈጡት እንደሆነ ቢያሳብቅም፤ ለቁርኣን ስልጣን ያለውን ወገንተኝነት እንዲሁም መሐመድ ያለው ትክክል ነው ብሎ ማክረርን ያመላክታል፡፡

## V. የኹያራዋን ምላሽ ለአል-ራዚ

ኹያራዋን "በውኑ ክርስቶስ ተሰቅሏልን?" በሚለው መጽሐፉ ለአል-ራዚ ስድስት ምላሾችን ያቀርባል፡-

### 1. ኢየሱስ አምሳያ አላስፈለገውም

አል-ራዚ በመጀመሪያ ምላሹ ፈጣሪ የሚመሳሰሉ ብዙ ሰዎችን ሊፈጥር ይችላል የሚለውን አሳብ ብንስማም በክርስቶስ ረገድ እንዳች ፋይዳ የለውም፡፡ ክርስቶስ በምንም ሁኔታ ስቅለትን ለማስወገድ አልጣረም ፤ በመጀመሪያ ደረጃ እርሱ ወደ ምድር የመጣው ለሰው ዘር ድነት ነውና በራሱ ፍቃድ ሁሉን ፋጸመ ፡፡ ክርሰቶስ ስቅለትን ለማስቀረት ጥረት አድርጎ ቢሆን፣ የመጣበትን ኃላፊነት ባላሳካ ነበር፡፡ ይህ በእግዚአብሔር ቃል ከሚታወቀው ክርስቶስ ባህሪይ ፈጽሞ የተለየ ነው፡፡ ፈጣሪ በዚህ ረገድ ኢየሱስን እንዲመስል ተአምራት ማድረግ ከቶውን እንዳላስፈለገው መገነዘብ ያሻል፡፡

### 2. ኢየሱስ ኃያል ራሱን አልተከላከለም

ኢየሱስ ከጠላቶቹ ለመዳን የመልአኩ ጅብሪል እገዛ ፈጽሞ አላሻውም፡፡ ኢየሱስ ኃይል ያልነበረው አልነበረም፤ ከሞቱ በፊት ያደረጋቸው ተዓምራቶች እርሱን ከሞት ለማዳን ከሚፈለገው ተዓምራት በላይ የሚልቁ ነበሩ፡፡ በወንጌል ተከትቦ የምናገኘው እውነት የኃይሉን ገደብ ,የለሽነት ነው፡፡ ጠላቶቹ ሊያስሩት በመጡ ጊዜ ከአፉ የወጣው ቃል ወደ መሬት ጥሎአቸዋል (ዮሐንስ 18፥6)፡፡ ኢየሱስ በራሱ መንገድ መሄድ ይችል ነበር፤ አይሁዳውያኑ ኢየሱስን የሚተናኮሉበት ጊዜ በርካታ ነው፣ በእነዚህ ሁሉ ግን ኢየሱስ ጊዜው ስላልደረሰ አንዳች ሊያደርጉት አልቻሉም ነበር፡፡ ሰዓቲቱ ስትደርስ ኢየሱስ በፍቃዱ ለመጣበት ዓላማ ራሱን አሳልፎ ሰጥቷል፡፡ አል-ራዚም ሆነ ሌሎች ኢየሱስ ስጋ ሆኖ የመጣበትን ዓላማ በቅጡ ማጥናት ይኖርባቸዋል፤ ያን ጊዜ ***በመስቀል ሞት የኃጢአት ይቅርታ ማስገኘት*** ክርስቶስ ሰው ኾኖ የመጣበት፣ ከድንግል የተወለደበት ዐብይ ዓላማ መኾኑን ይገነዘባሉ፡፡

## 3. ሻቢህ ዕውን አይደለም

በውኑ ፈጣሪ ኢየሱስን እንዲመስል የሌላ ሰው አካል መጠቀም አስፈልጎታልን? አንዳንዶች ክህደት የፈጸመውን አስቆሮቱ ይሁዳ ለመቅጣት ይህ አስፈላጊ እንደነበር ያስታውቃሉ፡፡ ወንጌል ይሁዳ ራሱን ማጥፋቱ በግልጽ ዘግቧል፤ ስለ ምን በሌላ ሰው ላይ ኢየሱስን እንዲመስል አስገደጋጅ ኃይል አስፈለገ? ኢየሱስ ወደ ሰማይ በአይሁዶች ፊት መወሰዱ በራሱ ጥርጥሮችን ያስወግዳል፡፡ የሀይማኖት እና ፖለቲካ መሪዎች ስለ ሞቱም ሆነ ስለ መቃብሩ የተሰነዘሩ አሳች ግምቶች ከ "እግዚአብሔር ቃል" አኳያ የሚጣረሱ መኾኑን አረጋግጠዋል፡፡

## 4. የክርስቶስ ስቅለት ታሪካዊ ማረጋገጫ

የኢየሱስ ደቀመዛሙርት እና ተከታዮች በእርሱ ስለ ሆነው ሁሉ ህያው ምስክሮች ናቸው፡፡ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት የክርስቶስን ስቅለት በትክክል በወንጌላት ከትበውታል፡፡ የወንጌል ትርክት በተዐመኒ ምንጮች ሳይቀር ድጋፍ አለው ፤ ሆኖም ከኢስላማዊ አንቀጾች፣ ሐዲስ እና ከሙስሊም በርካታ ጸሓፍት ጋር ይቃረናል ፡፡ ወንጌል የክርስቶስን ስቅለት አስመልክቶ ወሳኝ እውነቶችን ጠብቋል፡፡

## 5. የአይን እማኝ ቅቡልነት

የአል-ራዚ ምላሽ እርስ በእርሱ የሚጋጭ ነው፡፡ ለምስሌ፡- "የኢየሱስ ደቀመዛሙርት በዙሪያቸው ስለ ነበረው ክስተት ሁሉ ህያው ምስክሮች ስለ ነበሩ አሻሚ አሳቦች ሊኖሩ አይችልም" የሚለው አራተኛው ምላሽ በአምስተኛው የተነሳውን፡- "በዚያን ጊዜ የነበሩ እማኞች ጥቂት ከመሆናቸው የተነሳ የመታለል ዕድላቸው ከፍተኛ ነው" አሳብ ውድቅ ያደርገዋል፡፡ አፈ-ታሪክ ወደ ጥቂቶች በሚተላለፍበት ጊዜ ጠቀሜታው ዋጋ- የለሽ ይሆናል" ከሚለው አሳብም ጋር ይጣረሳል፡፡ አል-ራዚ ደቀመዛሙርቱ የአይን እማኞች መኾናቸው አሻሚ አሳቦችን ያስወግዳል ብሎ ሲያበቃ ፣ጥቂት መኾናቸው ደግሞ ለመታለል ያለውን ተጽዕኖ ያመላክታል ማለቱ አስገራሚ ነው፡፡ የስቅለት ህያው አይን እማኞች ኢየሱስ በትንሳኤው የተገለጠላቸው፣ ወደ ሰማይም ሲሄድ የተመለከቱት ከ500 በላይ ናቸው፡፡ የደቀመዛሙርት የስቅለት መዛግብት ያለጥርጥር ተዐማኒነት ያለው ነው፡፡

## 6. የስህተተኛው ቅጣት እምቢ ባይነት

በኢስላማዊ መዛግብት መሰረት ኢየሱስን እንዲመስል የተደረገው ሰው የክርስቶስ አማኝ አይደለም፡፡ በርካት የኢስላም ጸሓፍት የኢየሱስ ጠላት እንደነበር ይገልጻሉ ፤ አልያማ እኔ ክርስቶስ አይደለሁም ሲል ባወጀ (የክስተቱን እውነታ ባልተጋራ) ነበር!

በውሸት ለቅጣት አልፎ የተሰጠ ሰው ከቅጣት ራሱን ለማዳን የሚቻለውን አማራጭ ሁሉ የሚጠቀም  እምቢ ባይ ነውና!

ኹያራዋን ሙግቱን እንዲህ ያጠቃላላ ፡- "አል-ራዚ ስለ ስቅለት ታሪክ የሚናገረውን የመሐመድን አንቀጾች ድጋፍ ቢያደርግም፣ ክርስቲያኑ ግን የወንጌል እውነተኛ ጸሓፍትን መሰረት ማድረግ አለባቸው፡- ከስድስት ክፍለ ዘመን በኃላ የተዘገበው የቁርኣን አንቀጽ በእጃችን የሚገኘውን ቀደምት የመጽሐፍ ቅዱስ እውነታ ሊያሳንሰው አይችልምና::"

## VI. ስቅለትን የሚያጸኑ የቁርኣን ምንባባት

ስለ ስቅለት ጥርጣሬን ከሚያነሳ የቁርኣን ምንባብ ክፍል ይልቅ በወንጌል የተገለጠውን እውነት የሚያጉሉ (ስቅለትን የሚያጸኑ) የቁርኣን ክፍሎች አሉ፡-

*ሱረቱ 2፥87*

*ሙሳንም መጽሐፍን በእርግጥ ሰጠነው:: ከበኋላውም መልእክተኞችን አስከታተልን:: የመርየምን ልጅ ዒሳንም ግልጽ ታምራቶችን ሰጠነው:: በቅዱሱ መንፈስም አበረታነው:: ነፍሶቻችሁ በማትወደው ነገር መልእክተኛ በመጣላችሁ ቁጥር (ከመከተል) ትኮራላችሁን? ከፊሉን አስተባበላችሁ፤ ከፊሉንም ትገድላላችሁ::*

ይህ ክፍል ስለ ሙሴ፣ ኢየሱስ ፣ ክህደት እና ግድያ ይናገራል:: ቁርአን የኢየሱስ ሞት እንዴት እንደነበር ባይገልጽም ፣ ጅብሪል ብቸኛው እና ዐይነተኛው ምንጭ  መሆኑ ያስረግጣል:: ኢየሱስ የተከዳ፣ ኋላም የተገደለ  መልእክተኛ ነበር::

**ሱረቱ 3፥55**

*አላህም ባለ ጊዜ (አስታውስ):: ዒሳ ሆይ! እኔ ወሳጂህ ወደ እኔም አንሺህ ነኝ:: ከእነዚያም ከካዱት ሰዎች አጥሪህ ነኝ እነዚያንም የተከተሉህን እስከ ትንሣኤ ቀን ድረስ ከነዚያ ከከዱት በላይ አድራጊ ነኝ:: ከዚያም መመለሻችሁ ወደ እኔ ነው:: በርሱ ትለያዩበትም በነበራችሁት ነገር በመካካላችሁ እፈርዳለሁ::*

"ወሳጂህ" የሚለው ቃል ሰብሳቢህ የሚለውን ተኪ ቃል ይወክላል:: አልራዚ የኢስላም ሊቃውንት ያስቀመጡትን የተለያዩ ትርጓሜዎች ይገልጻል፡-

- ***ጊዜህ እደመድማለሁ***፡- (Mutawaffika-*ሙታዋፊፊካ*) ወሳጂህ  "በምድር ያለህን ቆይታ እንዲያበቃ አደርጋለሁ፤ ጠላቶችህ አይሁዳውያን እንዲገድሉህ አልተውህም " የሚለውን አሳብ ያንጸባርቃል::
- ***እንድትሞት አደርጋለሁ*** ፡- ይህ የቁርኣን ተንታኝ የሆነው ኢብኑ አባስ እና  የመሐመድ ግለ-ታሪክ ጸሐፊ ኢብኑ አይዛክ ትርጓሜ ነው:: ኢየሱስ እንዲሞት የተደረገበት ዋና

አላማ ጠላቶቹ አይሁዳውያን እንዲገድሉት ነው፤ ሆኖም ፈጣሪ ኢየሱስን ወደ ሰማይ በመውሰድ እንዳከበረው ይገልጻል።

- ***ለኃጢአት እንድትሞት አደርጋለሁ*** ፡- አቡ በከር አል -ዌሲቲ " ለኃጢአት ዝንባሌህ እና ለነፍስ ፍቃድ እንድትሞት አደርጋለሁ ፣ ለእኔም አስነሳሃለው። ለፈጣሪ ባይሞት ወደ ፈጣሪ ዕውቀትና ስፍራ አይደርስም ነበር። ኢየሱስ ወደ ሰማይ በሚወሰድበት ጊዜ እንደ መላእክቱ ሁሉ ከኃጢአት ነጻ ሆኗል።" ይህ ትርክት ቁርኣን ስለ ነብያትም ሆነ ስለ ኢየሱስ ፍጽምና /ስህተት- አልቦነት/ ከሚናገረው መርህ ጋር ይቃረናል (ሱረቱ 19፥19)።
- ***እንድታርግ አደርጋለሁ፡-*** ኢየሱስ የመርየም ልጅ በአካልም በመንፈስም እንደ ተወሰደ /እንዳረገ/ ብዙዎች ያስባሉ። ፈጣሪም " አንዳች እንዳይጎዱህ" ሲል እንደተናገረ ማስረጃ ያቀርባሉ።
- ***እንደሞተ አይነት አደርግሃለሁ፡-*** ኢየሱስን ወደ ሰማይ መውሰድ በምድር ያለው ህይወቱ ማብቃቱ ፣ እንደሞተ ተደርጎ ሊወሰድ እንደሚችል ይገልጻል።
- ***ሽልማት*** ፡- የኢየሱስ ከምድር ወደ ሰማይ መወሰድ እንደ ክፍያ ወይም ሽልማት ተደርጎ ይወሰዳል።
- ***ካሳ፦*** ኢየሱስ ስለ መታዘዙ እና መልካም ስራው ከፈጣሪ ዘንድ የተሰጠ የምስራችን ያመላክታል። ፈጣሪ ኢየሱስ የሚገጥመውን መከራ እና ጠላቶችን አስቀድሞ ገልጾለታል። ከላይ የተጠቀሱት ተቃርኖአዊ ትርጓሚዎች በአንባቢው ላይ ግርታን የሚፈጥሩ ናቸው። በተመሳሳይ ቃል የሚስሊማኒ ሊሂቃን የተለያዩ ትርጓሚዎች ስለ ምን ተከሰቱ? ችግር በሚገጥማቸው ጊዜ ሁሉ ለምንድነው "ፈጣሪ ያውቃል" በሚል ቃል ሽፋን የሚሰጡት? "ወሳጅህ" የሚለው ቃል በቁርኣን ለሃያ አምስት ጊዜ የተጠቀሰ ሲሆን ሞትን ለማመላከት ስራ ላይ ውላል። ከማሸለብ ጋር የተገናኘው ለሁለት ጊዜ ብቻ ነው፡-

  ***ሱረቱ 6፥60***

  *እርሱም ያ በሌሊት የሚያስተኛችሁ በቀንም የሠራችሁትን ሁሉ የሚያውቅ ከዚያም የተወሰነው ጊዜ ይፈጸም ዘንድ በእርሱ (በቀን) ውስጥ የሚቀሰቅሳችሁ ነው። ከዚህም መመለሻችሁ ወደ እርሱ ነው። ከዚያም ትሠሩት የነበራችሁትን ሁሉ ይነግራችኃል።*

*ሱረቱ 39፥42*

*አላህ ነፍሶችን በሞታቸው ጊዜ ይወስዳል፡፡ ያችንም ያልሞተችውን በእንቅልፏ ጊዜ (ይወስዳታል)፡፡ ታዲያ ያቺን ሞትን የፈረደባትን ይይዛታል፡፡ ሌላይቱንም እስከ ተወሰነ ጊዜ ድረስ ይለቅቃል፡፡ በዚህ ውስጥ ለሚያስተነትን ሕዝቦች ምልክቶች አልሉበት፡፡*

ሱረቱ 3፥55 በምናጠበት ወቅት ወሳጅህ የሚለው ቃል ምሳሌያዊ ትርጉም እንደሌለው ማስተዋል ግድ ይላል፡፡ ቀጥተኛ ትርጉሙ በተፈጥሮም ሆነ በስቅለት የሚመጣውን ሞት ያመለክታል፤ በሀዲስ ቃሉ "እንድትሞት አደርጋለሁ" የሚለውን ይወክላል ፡፡ አል- ቡኻሪ ኢብኑ አባስ መሐመድን ጠቅሶ ያስፈረውን ይተነትናል "ለመጽሐፎቹ የኾኑ ገጾች እንደሚጠቀለሉ ሰማይን የምንጠቀልልበት ቀን (አስታውስ)፡፡ የመጀመሪያን ፍጥረት እንደ ጀመርን እንመልሰዋለን፡፡ (መፈጸሙ) በእኛ ላይ የኾነን ቀጠሮ ቀጠርን፡፡ እኛ የቀጠርነውን ሠሪዎች ነን (ሱረቱ 21፥104)፡፡ ሱረቱ 5፥117 " በእርሱ ያዘዝከኝን ቃል ጌታዩን እና ጌታችሁን አላህን ተገዙ ማለትን እንጂ ለነርሱ ሌላ አላልኩም፡፡ በውስጣቸው እስካለሁ ድረስ በነርሱ ላይ ተጠባባቂ ነበርኩ ፡፡ በተሞላኸኝም ጊዜ (ባነሳኸኝ ጊዜ) አንተ በነሱ ላይ ተጠባባቂ ነበርክ፡፡ አንተም በነገሩ ሁሉ ላይ ዐዋቂ ነህ፡፡"

ሀዲስ ኢየሱስ የተናገረውን በቁርኣን ውስጥ አንደተጠቀመው ያመላክታል፡፡ መሐመድ ሞቷል፣ ነገር ግን ወደ ሰማይ እንደተወሰደ ማንም ሲናገር አይስተዋልም፡፡ "እንድሞት አደረገኝ" የሚለው ቃል የቁርኣን ቃል ስለ ሞቱ እንጂ ወደ ሰማይ ስለ መወሰዱ አይናገርም፤ ቃሉ ለኢየሱስም ለመሐመድም ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ በሁለቱም መካካል ያለው ልዩነት ኢየሱስ ከሞት በሦስተኛው ቀን መነሳቱ፣ በህይወት ባሉ እና በሞቱ ሁሉ ላይ ሊፈርድ ዳግም እንደሚመጣ የክርስቲያን እና እስልምና አስተምህሮዎች ያስረግጣሉ፡፡

*ሱረቱ 3፥183*

*እነዚያ ማንኛውም መልእክተኛ እሳት የምትበላው የኾነን ቁርባን እስከሚያመጣልን ድረስ ላናምን አላህ ወደኛ አዟል ያሉ ናቸው፡፡ መልክተኞች ከእኔ በፊት በተዓምራት እና በዚያ ባላችሁት (ቁርባን) በእርግጥ መጥተውላችኋል፡፡ እውነተኞች ከኾናችሁ ታዲያ ለምን ገደላችኋቸው በላቸው፡፡*

የቁርኣን ታሪኮችን በምንመዝንበት ጊዜ ከፈጣሪ ዘንድ ከሰማይ የተሰጠ መልዕክተኛ ኢየሱስ እንደሆነ እንገነዘባለን ፡፡ ሱረቱ 5፥114 "ለመጨረሻዎቻችን ባዕል (ፍንደቃ) የምትኾንን ከአንተም ተአምር የኾነችን ማዕድ ከሰማይ በእኛ ላይ አውርድ፡፡ ሰጠንም፡፡ አንተ ከሰጪዎች ሁሉ በላጭ ነህና::" ኢየሱስ ከሰማይ የተሰጠ ኾኖ ሳለ፣ አይሆዶያውያኑ የገደሉት ነው፡፡

*ሱረቱ 5፥116፣117*

*አላህም የመርየም ልጅ ዒሳ ሆይ! አንተ ለሰዎቹ ፦ እኔን እናቴን ከአላህ ሌላ ሁለት አምላኮች አድርጋችሁ ያዙ ብላህልን በሚለው ጊዜ አስታውስ ። ጥራት ይገባህ፤ ለእኔ ተገቢዩ ያልኾነን ነገር ማለት ለኔ አይገባኝም። ብዩው እንደ ኾነም በእርግጥ ዐውቀኸዋል። በነፍሴ ውስጥ ያለውን ሁሉ ታውቃለህ። ግን አንተ ዘንድ ያለውን አላውቅም ። አንተ ሩቆችን ሁሉ በጣም ዐዋቂ አንተ ብቻ ነህና ይላል። በእርሱ ያዘዝከኝን ቃል ጌታዩን እና ጌታችሁን አላህን ተገዙ ማለትን እንጂ ለነርሱ ሌላ አላልኩም። በውስጣቸውም እስካለሁ ድረስ በነርሱ ላይ ተጣባባቂ ነበርኩ ። በተሞላኸኝም ጊዜ (ባነሳኸኝ ጊዜ) አንተ በነሱ ላይ ተጠባባቂ ነበርክ። አንተም በነገሩ ሁሉ ላይ ዐዋቂ ነህ።*

በቁጥር 117 መሰረት የኢየሱስን ተከታዮች የመጠበቅ ኃላፊነት የፈጣሪ ስራ መኾኑን መገንዘብ ይቻላል። ይህ የሚያመለክትው ኢየሱስ ከሞቱ በኃላ ተከታዮቹን የመጠበቅ ኃላፊነት የእርሱ ሳይሆን የፈጠራ መሆኑን ነው። በኢስላማዊ እሳቤ ኢየሱስ ወደ ሰማይ ተወስዷል እንጂ አልሞተም።

*ሱረቱ 19፥33*

*ሰላምም በእኔ ላይ ነው። በተወለድሁ ቀን በምሞትበትም ቀን፣ ሕያው ኾኜ በምቀሰቀስበትም ቀን።*

ይህ ክፍል ስለ ኢየሱስ ሰው ኾኖ መምጣት፣መሞትና ከሞት መነሳት የሚናገር ግልጽ የቁርአን ክፍል ነው፤ ተአምራዊና ከወንጌል መዛግብት ጋር በእጅጉ ይስማማል። ቁርኣን ስለ መጥምቁ ዮሐንስም በሱረቱ 19:15 በተመሳሳይ ሲገልጽ “በተወለደበት ቀንና በሚሞትበትም ቀን ሕያው ሆኖ በሚነሳበትም ቀን ሰላም በእሱ ላይ ይሁን” ይላል። በርካታ ሙስሊማኑ የክርስቶስን ታሪክ በቅጡ የተረዱ አይደሉም። “በምሞትበትም ቀን” አመልካችነቱ የኢየሱስ ሞት ዳግም ከመጣ እና ከፍርድ በኃላ (dajjal-ዳጅጅያል) እንደሆነ ያስባሉ። አል-ታባሪ ፣ ኢቢኒ ኻቲር ፣ አል -ዛማኽሻሪ እና አል- ባይዳዊ ይህን ጥቅስ ለማብራራት ብዙ መረጃዎችን አደርጅተዋል።

**የግል ማስታወሻ**

12

# ስቅለት ተዓማኒነቱ

## I. መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት

ስልሳ ስድስቱ የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት የኢየሱስን ስቅለት ያረጋግጣሉ። ሰላሳ ዘጠኙ ቅዱሳት መጻሕፍት ስለ ስቅለት እና መስቀል ኩነቶች ተንብየዋል፤ ሃያ ሰባቱ መጻሕፍት ደግሞ የኢየሱስን ስቅለት ኩነቶች በሙሉ ዘግበዋል። አራቱ ቅዱሳት መጻሕፍት የኢየሱስን ሕይወት እስከ መጨረሻው ሳምንታት በአይናቸው ሳይቀር የተመለከቱትን እውነት አስፈላጊነት በብዙ ማስረጃ ገልጸዋል።

### 1. ስለ ስቅለት የሚመሰክሩ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትንቢቶች

መዝሙር 22 (ከክርስቶስ ልደት አንድ ሺህ አመት በፊት) እና ኢሳያስ 53 (ከክርስቶስ ልደት ሰባት መቶ አመት በፊት) ስለ ኢየሱስ የሚናገሩ አይነተኛ የብሉይ ኪዳን ምንባባት ናቸው። ስለ ኢየሱስ ስቅለት /ሞት/ የሚናገሩ ሌሎች በርካት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አሉ፡-

#### ሀ. ኢየሱስ በሰላሳ ብር አልፎ መሰጠት

***ዘካሪያስ 11፥12***

*እኔም። ደስ ብሎአችሁ እንደ ሆነ ዋጋዬን ስጡኝ፤ ያለዚያ ግን ተውት አልሁ። እነርሱም ለዋጋዬ ሣላሳ ብር መዘኑ።*

**የትንቢት ፍጻሜ፡-**

***ማቴዎስ 26፥14-15***

*በዚያን ጊዜ የአስቆሮቱ ይሁዳ የሚባለው ከአሥራ ሁለቱ አንዱ ወደ ካህናት አለቆች ሄዶ። ልትሰጡኝ ትወዳላችሁ እኔም አሳልፌ እሰጣችኋለሁ እነርሱም ሠላሳ ብር መዘኑለት።*

#### ለ. የሸክላ ሠሪ መሬት መገዛት

***ዘካሪያስ 11፥13***

*እግዚአብሔርም የተስማሙብትን የከበረውን ዋጋዬን በግምጃ ቤቱ ውስጥ አኑረው አለኝ። እኔም ሠላሳውን ብር ወስጄ በእግዚአብሔር ቤት ባለው በግምጃ ቤቱ ውስጥ አኖርሁት።*

*የተንቢት ፍጻሜ*

*ማቲዮስ 27፡-3-8*

*በዚያን ጊዜ አሳልፎ የሰጠው ይሁዳ እንደ ተፈረደበት አይቶ ተጸጸተ ሠላሳውንም ብር ለካህናት አለቆችና ለሽማግሌዎች መልሶ ንጹሕ ደም አሳልፌ በመስጠት በድያለሁ አለ፡፡ እነርሱ ግን እኛስ ምን አግዶን አንተው ተጠንቀቅ አሉ፡፡ ብሩንም በቤተ መቅደስ ጥሎ ሄደና ታንቆ ሞተ፡፡ የካህናት አለቆችም ብሩን አንሥተው፡፡ የደም ዋጋ ነውና ወደ መባ ልንጨምረው አልተፈቀደም አሉ፡፡ ተማክረውም የሸክላ ሠሪውን መሬት ለእንግዶች መቃብር ገዙበት፡፡ ስለዚህ ያ መሬት እስከ ዛሬ ድረስ የደም መሬት ተባለ፡፡*

## ሐ. የኢየሱስ ስቅለት ስላቅ

*መዝሙረ ዳዊት 22፥16-18*

*ብዙ ውሾች ከብበውኛልና፤ የክፋተኞች ጉባኤም ያዘኝ፤ እጆቼንና እግሮቼን ቸነከሩኝ፡፡ አጥንቶቼ ሁሉ ተቆጠሩ እነርሱም አዩኝ ተመለከቱኝም፡፡ ልብሶቼን ለራሳቸው ተከፋፈሉ በቀሚሴም ላይ ዕጣ ተጣጣሉ፡፡*

**የትንቢት ፍጻሜ**

*ማቴዎስ 27፥39-42*

*የሚያልፉትም ራሳቸውን እየነቀነቁ ይሰድቡት ነበርና፡፡ ቤተ መቅደስን የምታፈርስ በሦስት ቀንም የምትሠራው፡- ራስህን አድን፤ የእግዚአብሔር ልጅስ ከሆንክ ከመስቅል ውረድ አሉት፡፡ እንዲሁም ደግሞ የካህናት አለቆች ከጻፎችና ከሽማግሎች ጋር እየዘበቱበት እንዲህ አሉ፡፡ ሌሎችን አዳነ እራሱን ሊያድን አይችልም፤ የእስራኤል ንጉሥ ከሆነ አሁን ከመስቀል ይውረድ እኛም እናምንበታለን፡፡*

## መ. የኢየሱስ ጩኸት የአባቱ ዝምታ

*መዝሙረ ዳዊት 22፥1*

*አምላኬ አምላኬ ለምን ተውኸኝ እኔን ከማዳንና ከጩኸቴ ቃል ሩቅ ነህ፡፡*

*የትንቢት ፍጻሜ*

*ማቴዎስ 27፥46*

*በዘጠኝ ሰዓትም ኢየሱስ፡፡ ኤሎሄ ኤሎሄ ላማ ሰበቅታኒ ብሎ በታላቅ ድምፅ ጮኸ፡፡ ይህም አምላኬ አምላኬ ስለ ምን ተውኸኝ ማለት ነው፡፡*

## ሠ. ኮምጣቴ እንዲጠጣ መደረጉ

*መዝሙር 69፡21*

*ለመብሌ ሐሞት ሰጡኝ ፣ ለጥማቴም ሆምጣጤ አጠጡኝ።*

***የትንቢት ፍጻሜ***

*ዩሐንስ 19፥28*

*ከዚህ በኋላ ኢየሱስ አሁን ሁሉ እንደተፈጸመ አውቆ የመጽሐፉ ቃል ይፈጸም ዘንድ። ተጠማሁ አለ።*

## ረ. የልብሶቹ መከፋፈል ዕጣ መጣጣል

*መዝሙር 22፥18*

*ልብሶቼን ለራሳቸው ተከፋፈሉ በቀሚሴም ላይ ዕጣ ተጣጣሉ።*

### የትንቢት ፍጻሜ

*ዩሐንስ 19፥23*

*ጭፍሮችም ኢየሱስን በሰቀሉት ጊዜ ልብሶቹን ወስደው ለእያንዳንዱ ጭፍራ አንድ ክፍል ሆኖ በአራት ከፋፈሉት፤ እጀ ጠባቡን ደግሞ ወሰዱ። እጀ ጠባቡም ከላይ ጀምሮ ወጥ ሆኖ የተሠራ ነበረ እንጂ የተሰፋ አልነበረም።*

## ሰ. ከአጥንቶቹ አንዳች አለመሰበሩ

*መዝሙር 34፥20*

*እግዚአብሔር አጥንቶቻቸውን ሁሉ ይጠብቃል ከእነርሱም አንድ አይሰበርም።*

### የትንቢት ፍጻሜ

*ዩሐንስ 19፥32*

*ጭፍሮችም መጥተው የፊተኛውን ጭን ከእርሱም ጋር የተሰቀለውን የሌላውን ጭን ሰበሩ፤*

## ሸ. ጎኑን በጦር መወጋቱ

*ዘካሪያስ 12፥10*

*በዳዊትም ቤት ላይ በኢየሩሳሌምም በሚኖሩት ላይ የሞገስንና የልመናን መንፈስ አፈስሳለሁ፤ ወደ እርሱም ወደ ወጉት ይመለከታሉ፤ ሰውም ለአንድያ ልጁ እንደሚያለቅስ ያለቅሱለታል ሰውም ለበኵር ልጁ እንደሚያዝን በመራራ ኃዘን ያዝኑለታል።*

### የትንቢት ፍጻሜ

*ዩሐንስ 19፥34*

*ነገር ግን ከጭፍሮች አንዱ ጎኑን በጦር ወጋው፤ ወዲያውም ደምና ውኃ ወጣ።*

### ቀ. ከኃጢአተኞች ጋር መስቀሉ መክበሩ

*ኢሳያስ 53፥9*

*ከክፉዎቹም ጋር መቃብሩን አደረጉ፣ ከባለጠጎችም ጋ በሞቱ ሆኖም ግፍን አላደረግም ነበር። በአፉ ተንኮል አልተገኘበትም ነበር።*

**የትንቢት ፍጻሜ**

*ማቴዎስ 27፥57-60*

*በመሸም ጊዜ ዮሴፍ የተባለው ባለ ጠጋ ሰው ከአርማቲያስ መጣ፤ እርሱም ደግሞ የኢየሱስ ደቀ መዝሙር ነበረ፤ይኸውም ወደ ጲላጦስ ቀርቦ የኢየሱስን ሥጋ ለመነው። ጲላጦስም እንዲሰጡት አዘዘ። ዮሴፍም ሥጋውን ይዞ በንጹሕ በፍታ ከፈነው፤ ከዓለት በወቀረው በአዲሱ መቃብርም አኖረው፤ መቃብሩም ደጃፍ ታላቅ ድንጋይ አንከባሎ ሄደ።*

## 2 የኢየሱስ ምስክርነት

ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም እንደሚሄድ፣ በዚያም በሽማግሌዎች፣ በሊቀካህናት እና በጻሐፍት መከራና ሞት እንደሚገጥመው፣ በሦስተኛው ቀን ግን እንደሚነሳ ያውቅ ነበር።

*ማቴዎስ16፥21*

*ከዚያን ቀን ጀምሮ ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ይሄድ ዘንድ ከሽማግሎችና ከካህናት አለቆች ከጻፎችም ብዙ መከራ ይቀበልና ይገደል ዘንድ በሦስተኛውም ቀን ይነሣ ዘንድ እንዲገባው ለደቀ መዛሙርቱ ይገልጥላቸው ጀመር።*

*ማቴዎስ 17፥22*

*በገሊላም ሲመላለሱ ኢየሱስ የሰው ልጅ በሰዎች እጅ አልፎ ይሰጥ ዘንድ አለው፣ ይገድሉትማል።*

*ማቴዎስ 26፥1-2*

*ኢየሱስም እነዚህን ቃሎች ሁሉ በፈጸመ ጊዜ ለደቀመዛሙርቱ። ከሁለት ቀን በኃላ ፋሲካ እንዲሆን ታውቃላችሁ የሰው ልጅም ሊሰቀል አልፎ ይሰጣል አለ።*

*ማርቆስ 8:31*

*የሰው ልጅ ብዙ መከራ ሊቀበል ከሽማግሌዎችም ከካህናት አለቆችም ከጻፎችም ሊጣል ሊገደልም ከሦስት ቀንም በኋላ ሊነሣ እንዲገባው ያስተምራቸው ጀመር፤ ቃሉንም ገልጦ ይናገር ነበር።*

*ማርቆስ 9፥31*

*ከዚያም ወጥተው በገሊላ በኩል አለፉ፤ ደቀ መዛሙርቱ ምንም ያስተምር ስለ ነበር ማንም ያውቅ ዘንድ አልወደደም፤ ለእነርሱም የሰው ልጅ በሰዎች እጅ አልፎ ይሰጣል ይገድሉትማል ተገድሎም በሦስተኛው ቀን ይነሣል ይላቸው ነበር።*

*ማርቆስ 10፥32-34*

*ወደ ኢየሩሳሌምም ሊወጡ በመንገድ ነበሩ ኢየሱስም ይቀድማቸው ነበርና ተደነቁ፤ የተከተሉትም ይፈሩ ነበር። ደግሞም አስራ ሁለቱን ወደ እርሱ አቅርቦ ይደርስበት ዘንድ ያለውን ይነግራቸው ጀመር።     እነሆ ወደ ኢየሩሳሌም እንወጣለን የሰው ልጅም ለካህናት አለቆችና ለጻፎች አልፎ ይሰጣል የሞት ፍርድም ይፈርዱበታል ለአሕዛብም አሳልፈው ይሰጡታል ይዘብቱበትማል ይተፉበትማል ይገርፉትማል ይገድሉትማል በሦስተኛውም ቀን ይነሣል አላቸው።*

*ሉቃስ 9፥22*

*እርሱ ግን የሰው ልጅ ብዙ መከራ ሊቀበል በሽማግሌዎችም በካህናት አለቆችም በጻፎችም ሊጣል ሊገደልም በሦስተኛውም ቀን ሊነሣ ይገባዋል ብሎ ለማንም ይህን እንዳይናገሩ አስጠንቅቆ አዘዘ።*

*ዮሐንስ 3፥13-14*

*ከሰማይም ከወረደ በቀር ወደ ሰማይ የወጣ ማንም የለም እርሱም በሰማይ የሚኖረው የሰው ልጅ ነው። ሙሴም በምድረ በዳ እባብን እንደ ሰቀለ እንዲሁ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖው እንጂ እንዳይጠፋ የሰው ልጁ ሊሰቀል ይገባዋል።*

*ዩሐንስ 12፥24፣32*

*እውነት እውነት እላችኋለሁ የስንዴ ቅንጣት በምድር ወድቃ ካልሞተች ብቻዋን ትቀራላች ብትሞት ግን ብዙ ፍሩ ታፈራለች ። እኔም ከምድር ከፍ ከፍ ያልሁ እንደ ሆነ ሁሉን ወደ እኔ እስባለሁ።*

*ሙስሊማኑ ኢየሱስ የእውነት መገለጫ እንደሆነ ያምናሉ* (ሱረቱ 19፥34)። እርሱ እውነት ጭምር እንደሆነ ትልቅ አክብሮት ቢኖራቸውም ፣ እርሱ ስለ ስቅለቱ የተናገረውን *ግን መቀበል ያዳግታቸዋል*።

## 3. የኢየሱስ ተከታዮች ምስክርነት

*የመጀመሪያዎቹ* የኢየሱስ ደቀመዛሙርት በአይሁዶች መካካል የእርሱ ሞትና ትንሳኤ ሕያው ምስክር ነበሩ ፤ አንድም አይሁዳዊ ምስክርነታቸው ሀሰት ነው ሲል አልከሰሳቸውም። ከክርስቶስ እርገት አስር ቀናት በኃላ፣ ሐዋሪያው ጳውሎስ ለአይሁዶች "እርሱንም በእግዚአብሔር በተወሰነው አሳቡና በቀደመው እውቀቱ ተሰጥቶ በዓመጸኞች እጅ ሰቅላችሁ ገደላችሁት" ብሎ ሲናገር እንመለከታለን (ሐዋሪያት *ሥራ* 2፥23)። በሐዋሪያት *ሥራ* 3፥14፣15 እንዲሁ " እናንተ ግን ቅዱሱን ጻድቁንም ክዳችሁ ...የህይወትንም *ራስ* ገደላችሁት ፣ እርሱን ግን እግዚአብሔር ከሙታን አስነሣው ፣ ለዚህም ነገር እኛ ምስክሮች ነን።"

የአይሁድ መሪዎች ይህን እውነት አልካዱም፣ አልተቃወሙም፡፡ ነገር ግን ደቀመዛሙርቱ ዝም እንዲሉ ነበር የሚያስጠነቅቋቸው (ሐዋሪያት ሥራ 4፥18፣5፥28፣40)፤ ደቀመዛሙርት ይህን ትዕዛዝ በተላለፉ ወቅት ነበር ጽኑ መከራ ያመጡባቸው( ሐዋሪያት ሥራ 7፥59፣8፡4)፡፡

## 4.የተፈጥሮ ምስክርነት

ኢየሱስ በሚሞትበት ወቅት ጸሐይ ለሦስት ቀን ጨልሟል፣ የቤተ መቅደስ መጋረጃ ከላይ እስከ ታች ለሁለት ተተርትሮአል ፣ ምድር ተንቀጥቅጧል፣ መቃብሮች ተከፍተዋል፡፡

*ማቴዎስ 27፥51-54*

*እነሆ የቤተመቅደስ መጋረጃ ከላይ እስከ ታች ከሁለት ተቀደደ፣ ምድርም ተናወጠች ዓለቆችም ተሰነጠቁ፣ መቃብሮችም ተከፈቱ፣ ተኝተው ከነበሩትም ከቅዱሳን ብዙ ሥጋዎች ተነሡ፣ ከትንሣኤውም በኃላ ከመቃብሮች ወጥተው ወደ ቅድስት ከተማ ገቡና ለብዙዎች ታዩ ፡፡ የመቶ አለቃም ከእርሱም ጋር ኢየሱስን የሚጠብቁ መናወጡንና የሆነውን ነገር አይተው ፡- ይህ በእውነት የእግዚአብሔር ልጅ ነበረ ብለው እጅግ ፈሩ፡፡*

## 5. የጥንታዊያን መዛግብት ምስክርነት

በሐዋሪያው ጳውሎስ የተሰጠው ተዋቂ ምስክርነት በ1ኛ ቆሮንቶስ 15፥1-4 ይገኛል፡- “ወንድሞች ሆይ የሰበክሁላችሁን ደግሞም የተቀበላችሁትን በእርሱም ደግሞ የቆማችሁበትን በእርሱም ደግሞ የምትድኑበት ወንጌል አሳስባችኃለሁ፣ በከንቱ ካላመናችሁ በቀር ብታስቡት በምን ቃል እንደ ሰበክሁላችሁ አሳስባችኃለሁ፡፡ እኔ ደግሞ የተቀበልሁትን ከሁሉ በፊት አሳልፌ ሰጠኃችሁ እንዲህ ብዩ ፡- መጽሐፍ እንደሚል ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን ሞተ፣ ተቀበረም ፣ መጽሐፍም እንደሚል በሦስተኛው ቀን ተነሣ፡፡”

## 6. የቅዱሳት ሚስጥራት ምስክርነት

የጥንት ቤተክርስቲያን ሁለት ቅዱሳት ሚስጥራት ማለትም ቅዱስ ጥምቀትን እና ቅዱስ እራትን ትለመማድ ነበር፡፡ ጥምቀት “ከክርስቶስ ጋር የመቀበር” ምልክት ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር “ከክርስቶስ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ እንደ ተጠመቅን አታውቁምን? እንግዲህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሙታን እንደ ተነሣ እንዲሁ በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስ ከሞቱም ጋር አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበርን” (ሮሜ 6፥3-5)፡፡ ቅዱስ እራት በክርስቶስ የተጀመረ ስቅለቱን ለማሰብ የሚደረግ ስርአት ነው፡- “ ሲበሉም ኢየሱስ እንጀራን አንሥቶ ባረከ፣ ቆርሶም ለደቀመዛሙርት ሰጠና፡-

እንካችሁ ብሎ ይህ ሥጋዩ ነው አለ፡፡ ጽዋንም አንስቶ አመስግኖም ሰጣቸው፤ እንዲሁም አለ ብዙዎች ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው" ( ማቴዎስ 26፥26-28)፡፡

## 7. የማልኮስ ጆሮ መቆረጥ ምስክርነት

ኢየሱስ አልፎ በሚሰጥበት ጊዜ ጴጥሮስ የካህናት አለቃ ባለሚል የሆነውን የማልኮስ  ቀኝ ጆሮ በሰይፍ ቆርጧል፤ ኢየሱስም ጴጥሮስን  " ሰይፍህን ወደ ስገባው ክተተው አብ የሰጠኝን ጽዋ አልጠጣትምን? " (ዮሐንስ 18፥10፣11)፡፡ኢየሱስ "ጆሮውን ዳስሶ ፈወሰው (ሉቃስ 22፥51) ፡፡ ከኢየሱስ ሌላ ይህን ተአምራት ሊያደርግ ከቶውን የሚቻለው ማንም የለም፡፡ ኢየሱስን እንዲመስል ተደርጓል ተብሎ የሚገመተው ሰው ይህን ተአምራት ከቶውን ሊያደርግ አይችልም፡፡

## 8. ሰባቱየመስቀል መግለጫዎች ምስክርነት

ወንጌላት የኢየሱስን የመስቀል ላይ ሰባት መግለጫዎች  ዘግቧል፡፡አሁንም በኢየሱስ ተመስሎአል ተብሎ የሚገመተው ሰው በመስቀል ላይ ሳለ ፣ እነዚህን ንግግሮች ማድረግ ከቶውን አይቻለውም፡-

- ✓ ***መግለጫ*** *1 ፡- ኢየሱስም "አባት ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው " አለ (ሉቃስ 23፥34)፡፡*
- ✓ ***መግለጫ*** *2 ፡- ወንበዴው ኢየሱስን ጌታ ሆይ በመንግስትህ በመጣህ ጊዜ አስበኝ ባለው ጊዜ፣ ኢየሱስ "እውነት እልሃለሁ ፣ ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናልህ " (ሉቃስ 23፥42፣43)፡፡*
- ✓ ***መግለጫ*** *3፡- እናቱን ይወደው የነበረውንም ደቀመዝሙር በአጠገቡ ቆሞ ባየ ጊዜ፣ እናቱን፡- "አንቺ ሴት እነሆ ልጅሽ" አላት (ዮሐንስ 19፥26፣27)፡፡*
- ✓ ***መግለጫ*** *4 ፡- በዘጠኝም ሰዓት ኢየሱስ "ኤሎሄ ኤሎሄ ላማ ሰበቅታኒ? ብሎ በታላቅ ድምጽ ጮኸ፡፡" ይህም ፡- " አምላኬ አምላኬ ስለ ምን ተውኸኝ?" ማለት ነው (ማቴዎስ 27፡46)፡፡*
- ✓ ***መግለጫ*** *5፡- ኢየሱስ ሁሉ እንደተፈጸመ አውቆ "የመጽሐፉ ቃል ይፈጸም ዘንድ፡- ተጠማሁ" አለ (ዮሐንስ 19፡23)፡፡*
- ✓ ***መግለጫ*** *6፡- "ሆምጣጤውን ከተቀበለ በኃላ፡- ኢየሱስ ተጠማሁ" አለ(ዮሐንስ 19፡ 30)፡፡*
- ✓ ***መግለጫ*** *7፡- ኢየሱስም በታላቅ ድምጽ ጮኸ ፡- " አባት ሆይ ነፍሴን በእጅህ አደራ እሰጣለሁ" (ሉቃስ 23፡46)፡፡*

የኢየሱስ እናት ማርያም እና ደቀመዝሙሩ ዮሐንስ ከክርስቶስ መስቀል ግርጌ ነበሩ ፤ መቼም በኢየሱስ እንደ ተመሰለ የሚገመተው ሰው እንዳልሆነ በቅጡ ይለያሉ። እናቱ የልጇን ድምጽ በትክክል ትለያለች ፤ ቅርበት ያለው ደቀመዝሙሩም እንዲሁ!

## 9. ባዶ መቃብር ትንሣኤ ምስክርነት

ሙስሊማኑና ክርስቲያኑ የተሰቀለው ሰው ማንነት ዙሪያ ካልሆነ በቀር አንድ ሰው እንደተሰቀለ ይስማማሉ። ሙስሊማኑ በሦስተኛው ቀን የሞተው ሰው መቃብር ባዶ እንደኾነ በድኑም እንደሌለ መገንዘብ ይኖርባቸዋል። ክርስቲያኑ ጌታቸው እንደተነሳ ጽኑ ምስክርነት አላቸው። ሙስሊማኑ በኢየሱስ ምትክ አንድ ሰው እንደሞተ ቢገምቱም፣ መቃብሩ ግን ባዶ መሆኑ ጥያቄ ሳይፈጥርባቸው እንደማይቀር ልብ ይሏል።

በጴንጤቆስጤ ቀን ጴጥሮስ በመጀመሪያው ስብከት (ሐዋሪያት ሥራ 2፥14-36) በምድር የኢየሱስን ህይወት አስመልክቶ “የእስራኤል ሰዎች ሆይ ይህን ቃል ስሙ ራሳችሁን እንደምታውቁ የናዝሬቱ ኢየሱስ እግዚአብሔር በመካከላችሁ በእርሱ በኩል ባደረገው ተአምራትና በድንቆች በምልክቶችም ከእግዚአብሔር ዘንድ ለእናንተ የተገለጠ ሰው ነበር ፤ እርሱንም በእግዚአብሔር በተወሰነው አሳቡና በቀደመው እውቀቱ ተሰጥቶ በዓመጸኞች እጅ ሰቅላችሁ ገደላችሁት::” የኢየሱስን ህይወት እና ሞት በማስታወቅ ፣ ስለ ትንሣኤው በቀጣይ ዘጠኝ ጥቅሶች ላይ ያስረግጣል፡-

*ሐዋሪያት ሥራ 2፥24-32*

*እግዚአብሔር ግን የሞትን ጣር አጥፍቶ አስነሣው ሞት ይይዘው ዘንድ አልቻለምና። ዳዊት ስለ እርሱ እንዲህ ይላልና። ጌታን ሁል ጊዜ በፊቴ አየሁት እንዳልታወክ በቀኜ ነውና። ስለዚህ ልቤን ደስ አለው ልሳኔም ሐሤት አደረገ ደግሞም ሥጋዬ በተስፋ ያድራል፤ ነፍሴን በሲኦል አትተዋትምና ቅዱስህንም መበስበስን ያይ ዘንድ አትሰጠውም። የሕይወትን መንገድ አስታወቅኸኝ፤ ከፊትህ ጋር ደስታን ትሞላብኛለህ። ወንድሞች ሆይ ስለ አባቶች አለቃ ስለ ዳዊት እንደ ሞተም እንደ ተቀበረም እናንተ በግልጥ እናገር ዘንድ ፍቀዱልኝ፤ መቃብሩም እስከ ዛሬ በእኛ ዘንድ ነው። ነቢይ ስለ ሆነ ከወገቡም ፍሬ በዙፋኑ ያስቀምጥ ዘንድ እግዚአብሔር መሐላ እንደ ማለለት ስለ አወቀ፤ ስለ ክርስቶስ ትንሣኤ አስቀድሞ አይቶ ነፍሱ በሲኦል እንዳልቀረች ሥጋውም መበስበስን እንዳላየ ተናገረ። ይህን ኢየሱስን እግዚአብሔር አስነሣው ለዚህም ነገር እኛ ሁላችን ምስክሮች ነን፤*

*ሐዋሪያት ሥራ 2፥33-36*

*ስለዚህ በእግዚአብሔር ቀኝ ከፍ ከፍ ብሎና መንፈስ ቅዱስን የተስፋ ቃል ከአብ ተቀብሎ ይህን እናንተ አሁን የምታዩትንና የምትሰሙትን አፈሰሰው። ዳዊት ወደ ሰማያት አልወጣምና ነገር ግን እርሱ ጌታ ጌታዬን ጠላቶችህን የእግርህ መረገጫ እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ አለው፤ አለ እንግዲህ ይህን እናንተ የሰቀላችሁትን ኢየሱስን እግዚአብሔር ጌታም ክርስቶስም እንዳደረገው የእስራኤልወገን ሁሉ በእርግጥ ይወቅ።*

*1ኛ ቆሮንቶስ ሰዎች 15፥14-15*

*ክርስቶስም ካልተነሣ እንግዲያስ ስብከታችን ከንቱ ነው፤ እምነታችሁም ደግሞ ከንቱ ናት፤ ደግሞም ክርስቶስን አስነሥቶታል ብለን በእግዚአብሔር ላይ ስለ መሰከርን ሐሰተኞች የእግዚአብሔር ምስክሮች ሆነን ተገኝተናል፤ ሙታን ግን የማይነሡ ከሆነ እርሱን አላስነሣውም።*

***1ኛ* ቆሮንቶስ ሰዎች 15፥3-8**

*እኔ ደግሞ የተቀበልሁትን ከሁሉ በፊት አሳልፌ ሰጠኋችሁ እንዲህ ብዬ፦ መጽሐፍ እንደሚል ክርስቶስ ስለ ኃጢያታችን ሞተ ተቀበረም፤ መጽሐፍም እንደሚል በሦስተኛው ቀን ተነሣ፤ ለኬፋም ታየ በኋላም ለአሥራ ሁለቱ፤ ከዚያም በኋላ ለአምስት መቶ ለሚበዙ ወንድሞች በአንድ ጊዜ ታየ፤ ከእነርሱም የሚበዙቱ እስከ አሁን አሉ አንዳንዶች ግን አንቀላፍተዋል፤ ከዚያም በኋላ ለያዕቆብ ኋላም ለሐዋሪያት ሁሉ ታየ፤ ከሁሉም በኋላ እንደ ጭንጋፍ ለምሆን ለእኔ ደግሞ ታየኝ።*

የትንሣኤ ማረጋጋጫ ከሚናገሩ ክስተቶች መካካል የማይረሳው የኢየሱስ ደቀመዝሙር ቶማስ ታሪክ ነው። እርሱ አንድን ነገር ከማመኑ በፊት ማረጋገጫን የሚጠይቅ ሰው ነበር ፤ ሌሎች ደቀመዛሙርት "ጌታን አይተነዋል " ባሉት ጊዜ " የችንካሩን ምልክት ካላስገባው ፣ እጄንም በጎኑ ካለገባሁ አላምንም" ብሎ ተናግሯል።

ደቀመዛሙርቱ ከሳምንት በኃላ ዳግም በቤት ተሰብስበው ሳለ፣ ቶማስም አብሮ ነበር። ደጆችም ተዘግተው ሳለ ኢየሱስ በመካከላቸው ቆሞ "ሰላም ለእናንተ ይሁን አላቸው። ከዚያ በኃላ ቶማስን፦ ጣትህን ወደዚህ አምጣና እጆቼን እይ፤ እጅህንም አምጣና በጎኔ አግባው ፤ ያመንህ እንጂ ያላመንህ አትሁን አለው። ቶማስም፦ ጌታዩ አምላኬም ብሎ መለሰለት። ኢየሱስም ስለ አየኸኝ አምነሃል፤ሳያዩ የሚያምኑ ብፁአን ናቸው አለው" (ዮሐንስ 20፥24-29)።

## II. የስቅለት ሳይንሳዊ ማረጋገጫ

የኢየሱስ ስቅየት እና ቁስል የሞቱ ማረጋገጫዎች ናቸው። በጅራፍ መገረፉም መሰቀሉም በጽኑ ህማም እና ድካም ውስጥ እንደነበረ ያስረዳሉ ። ለዘጠኝ ሰአታት ያህል በመስቀል ተንጠልጥሏል፣ ከእጆቹ፣ እግሮቹ እና ጭንቅላቱ ደም ይፈስስ ነበር። መሞቱን ለማረጋገጥም ከጭፍሮቹ አንዱ ጎኑን ደም እና ውሃ እስኪወጣ ድረስ ወግቶታል። በርካታ የተከበሩ ሀኪሞች የኢየሱስን የመስቀል ላይ ሞት በመጻሕፍቶቻቸው አረጋግጧል።[60] የአሜሪካ ህክም እና ማህበር በመጽሔቱ የሚከተለውን አስፍሯል፡- ታሪክ፣ ሳይንስ እና ህክምና በግልጽ ኢየሱስ የተወጋው ጎኑ ከመቁሰሉ በፊት እንደሞተ ያረጋግጣሉ። ተለምዷዊውን አመለካከት በመደገፍም በቀኙ ጎን በሚወጋበት ጊዜ የቀኝ ሳንባው ብቻ ሳይሆን ልቡ አካባቢም ጭምር አንደሆነ ፤ ይህ ደግሞ ለሞቱ አይነተኛ ማረጋገጫ መሆኑን ያስረግጣሉ። ኢየሱስ በመስቀል ላይ አልሞተም የሚለው አመለካከት ፈጽሞ ከዘመናዊው የህክምና እውቀት ጋር ይጋጫል።[61]

## III. የስቅለት ሥነ-ልቦናዊ ማረጋገጫ

የመሪውን አሳፋሪ ሞት እውነታ ጠቃሚ ካልሆነ በቀር ማንኛውም ቡድን ኩራቱን በገሃድ አያውጅም።

ቅዱስ ጳውሎስ በገላትያ 6፥14 ላይ በክርስቶስ ኢየሱስ መስቀል ያለውን ኩራት በገሃድ ያውጃል። ክርስቲያኑ የኢየሱስ ክርስቶስ ሞት የእምነቱ መሰረት እና ምልክት መኾኑን በጽናት ያስታውቃል። በአንገታቸው የሚያንጠለጥሉት፣ በእጃቸው የሚቀርጹት ብሎም በቤተክርስቲያን ላይ ከፍ አድረገው የሚሰቅሉት ለዚህ ነው፤ የኃፍረት መገለጫ የሆነው መስቀል የደስታ እና ኩራት ምልክት ነውና!

አንድ ስዕላዊ ማብራሪያ እንመልከት፡- አንድ ጨካኝ አምባገነን አንድን ጎረቤት ሀገር በመውረር ዜጎችዋን በግፍ ማሰቃየት ጀመረ እንበል! ታማኝ የሆነው ሃገር ወዳድ አርበኛ ህዝቡን ለአመጽ በማነሳሳት ትግል ያደርጋል፤ ነገር ግን አምባገነኑ አሰረው ፣ ኃላም በስቅላት እንዲቀጣ አደረገ። በዚህም የህዝቡ አመጽ እጅጉን ተቀጣጥሎ ጨካኙን አምባገነን አስወገዱ፤ ሃገሪቱም ነጻ ወጣች።

---

[60] ዶክተር ስትራውድ የክርስቶስ ኢየሱስ በስጋ መሞት መንስዔ እና የክርስትና አስተምህሮ (መመሪያ)፣ (ሎንደን፣ ሐመሊተን እ አዳማስ ፣1871)፣ ገጽ 28- 156፣489 -494።

[61] የአማሪካን ሜዳካል አሶሴሽን ጆርናል፣ መጋቢት 21 ፣ 1986፣ ገጽ 1463፤ እስልምናን ለመመለስ ከተጻፈ መጽሐፍ የተወሰደ፣ ኖርማን ፣ ኤል፣ ገይስለር እና አብዱል ሳልበ ፣ ቤከር ሃውስ ፣ ግረናንድ ራፒድስ ፣1993፣ ገጽ 230።

ከተማይቱም መስዋዕት በሆነላት ሃገር ወዳድ አርበኛዋ መታሰቢያ " የተሰቀለው ሰው ሃገር " ተብላ ተሰየመች፤ የተሰቀለበትንም ምስል በባንዲራዋ ላይ አኖረችው።

በክርስትና የምናገኘውም እውነታ ይኸው ነው። የክርስቲያኑ መሰረታዊ መልዕክት "ኢየሱስ እና ስቅለቱ" ነው (1ኛ ቆሮንቶስ 2:2) ። መስቀሉ የክርስቲያኑ አይነተኛ ምልክታቸው በመኾኑ፣ ያለ ጥርጥር የመሪያቸው ሞት እውነት እና ታሪካዊ ማረጋገጫ ያለው ሆኗል፤ ከምንም ጋር የማያወዳደሩት በረከታቸውም ነው!

## IV. የስቅለት ማረጋገጫ ክርስቲያን ባልኾኑ ሰዎች

በርካታ የአህዛብ ታሪክ የስቅለቱን ታሪካዊ ማረጋገጫ አጽንተዋል፦

- *ኮርነሊየስ ታሲተስ ( 55-120ዓ.ም)* ፦ በታማኝነቱ እና መልካምነቱ የጥንታዊት ሮም ታላቅ የታሪክ ሰው የሚል ስያሜ አግኝቷል። *The Annals and The Histories* እጅግ ታዋቂ ስራው ነው፤ ስለ ክርሰቶስ እና ክርስቲያኖች ያወቀው የትንሿ ኢስያ ገዢ በነበረት ጊዜ እንደበር ይነገራል። " *ኔሮ በሪፖርቱ* ( ሮምን ማቃጠሉ ይታወቃል) እራሱን ነጻ ለማድረግ ፣ በዘመኑ በብዙኃኑ እንዲጠሉ የተደረጉትን ክርስቲያኖች ተጠያቂ አድርጓል። ክርስቶስ በጴንጤናዊው ጲላጦስ ዘመን በሀስት አልፎ ተሰጥቷል፤ በሀሰት አልፎ የተሰጠበት ሁኔታ በይሁዳ ብቻ ሳይሆን በሮም ብሎም በተቀረው ዓለም ሁሉ የታወቀ ነው።" [62] በሀሰት አልፎ የተሰጠበት ሁኔታ ስለ ትንሣኤው የሚነሱትን ጥርጣሬዎች የሚያስወግድ መሆኑን ታሲተስ ያስታውቃል።
- *ታሉስ (52 ዓ.ም)፦* ታሉስ እንደ ታሲተስ ሁሉ በጥንት ክርስቲያኖች ወቅት ነበር። ከቶርጃን ጦርነት አንስቶ እስከ ራሱ ዘመን ያለው የምስራቅ ሜድትሪያን ታሪክ ጽፏል። ጁሊየስ አፊሪካነስ የመሳሰሉ ጸሓፍት በድራሳኖቻቸው የታሉስን ቀሪ ስራዎች ጠቅሰዋል። በስቅለት ወቅት ምድርን ሰለ ሸፈነው ጨለማ በ221 ዓ.ም ጁሊየስ ሲጽፍ "ታሉስ በሦስተኛው ግለ ታሪኩ ይህ ጨለማ የጸሐይ ግርዶሽ ይመስላል" የሚለውን አስፍሯል። [63]ጁሊየስ የጸሐይ ግርዶሽ ጨረቃ ባላበት እንደማይከሰት በመሞገት፣ በኢየሱስ ስቅለት ወቅት ሙሉ ለሙሉ ጨለማ ምድርንን ሸፍኖ እንደነበር ያስታውቃል።[64] ጨላማ መከሰቱን ታሉስ ብቻ ሳይሆን ሌሎች ጥንታዊ ጸሓፍት ጭምር ዘግበዋል፤ ዲዮኒየስ ምድር በጨለማ ፦ " በምትሸፈንበት ወቅት "የፍጥረት

---

[62] ጌሪይ አ ሀበርማስ ፣ የታሪክ

[63] ኤፍ ኤፍ ብሩስ፣ የአዲስ ኪዳን ሰነድ (ካምብሪጅ፣ ።ቲንዳል፣ 1965)፣ ገጽ319።

[64] --------፣ ገጽ 113።

ሁሉ አምላክ ጣልቃ እየገባ ወይም ሃዘኑን እየገለጸ " እንደነበር ይገልጻል፡፡ ፊሊዮፎን እንዲሁ "ኢየሱስ በሚሰቀልበት ጊዜ ከዚህ በፊት ሆኖ የማያውቅ ጨለማ ምድርን ሸፍኖ ነበር" ሲል የተናገረውን፣ ኢብኑ ኻቲር Al-Bidaya wal —Nihaya (አል-ባይዳያ ዋል ኒሄያ) በተሰኘው መጽሐፉ ጠቅሷል፡፡ ኢብኑ አል -አቴር *የተራሊዎችና እናተንታኞች* ስልጣን ላይ በጻፈው ትርክት ዘግቦታል፡፡

- ***ጆሴፈስ*** ፡- ከስቅለቱ ጥቂት አመታት በኃላ የተወለደው አይሁዳዊ ጆሴፈስ የክርስቶስን ስቅለት እና የራሱን ህዝብ *ታሪክ* በ66 *ዓ.ም* ሲጽፍ የሚከተለውን አስፍሯል ፡- "ኢየሱስ ጥበበኛ፣ በባህሪውም መልካም እና ደግ አድራጊ ነበር፡፡ በዚህም ከአይሁድ እና ከተቀረው አለም አያሌ ህዝብ ደቀመዛሙርቱ ሆነዋል፡፡ ጲላጦስ እንዲሰቀል እና እንዲሞት አደረገ፤ ደቀመዛሙርቱ ግን እርሱን ከመከተል አላቆሙም ፡፡ ኢየሱስ ከስቅለቱ በኃላ ከሞት በመነሳት ለደቀመዛሙርቱ ሕያው መሆኑን ዘግበዋል፤ እርሱ ነብያት የተናገሩለት እውነተኛ መሲህ ነው"[65]
- ***ሉሲየን (100 ዓ.ም)*** ፡- ግሪካዊው የታሪክ ሰው ሉሲየን የፍልስፍ እና ትምህርት ቤት ተከታይ ነበር፡፡ ሉሲየን ክርስቲያኖኑ ለክርስቶስ ለመሞት ዝግጁ የኾኑበትን፣ የዘላላም ህይወትንም ተስፋ ያደረጉበትን እምነት ያልተረዳ ሰው ነበር፡፡ ክርስቲያኖኑ የተታለሉ፣ በምድር አሁናዊ ኑሮን ከመኖር ይልቅ እርግጠኛ ያልኾነውን ተስፋ የሚከተሉ አድርጎ ይቆጥር ነበር፡፡ ክርስቶስን አስመልክቶ "ክርስቲያኖኑ እስከ መጨረሻው የተሰቀለውን ማምለካቸው፣ በሕጉም እንደኖሩ በዚህም የግሪክ ጣዖታትን መክዳታቸውን…" ይናገራል፡፡[66] የክርስቶስ ስቅለት እውነታ የክርስትናን እምነት በማይቀበሉ ሰዎች ዘንድ ሳይቀር አሻሚ አይደለም፡፡
- ***ጲላጦስ*** ፡- በመጀመሪያው የዐቀብተ እምነት ስራው ሰማዕቱ ጀስቲን (150 ዓ.ም) የጴንጤናዊው ጲላጦስ ስራን ሲጠቅስ የኢየሱስ ስቅለት በጲላጦስ ሪፖርት ላይ መረጋገጡን ያስታውቃል፡፡ "የጴንጤናዊው ጲላጦስ ስራዎች ኢየሱስ ተአምራቶችን እንደፈጸመ" ማረጋገጡን ይናገራል፡፡
- ***ሲሊሲየስ (140 ዓ.ም)፡-*** ፈላስፋ እና የክርስትና ጠላት የሆነው ሲሊሲየስ በ " *እውነተኛው ንግግር"* መጽሐፉ " የክርስቶስ የመስቀል ላይ ስቅየት ለሰዎች ድነት መዋሉን" ይጠቅሳል፡፡

---

[65] ኢብኑ ካቲር፣ አል- ቢዶያ ፣ዋል- ኒባያ ፣ቅጽ፣ 1፣ ገጽ 182፡፡
[66] ጌሪይ አር ሀበርማስ ፣ገጽ 91ፊ፡፡

- ***ማራ ባር ሴራፒዮን*** ፡- በመጀመሪያው እና በሦስተኛ ክፍለ ዘመን መካካል ከእስር ቤት ለልጁ በጻፈው ደብዳቤ " አይሁዳውያን  ጠቢብ ንጉሳቸውን በመግደላቸው ያገኙት ጥቅም ምንድነው? ጥበበኛው ንጉስ ለመልካም ዓላማ ሞተ ፤ አንዳ ስተማሪውም ኖረ" ሲል በመግለጽ ፣ ከሶቅራጥስ እና ፕሌቶ ጋር ያመሳስለዋል፡፡[67]

## V. የስቅለት መንፈሳዊ ማረጋገጫ

በኢየሱስ ሞት ወደ እርሱ የመጡ ሰዎች በቅዱስ ሕይወቱ እና ድንቅ ትምህርቱ ተማርከው ከመጡት በቁጥር ይበልጣሉ፡፡ የኢየሱስ ሞት ሰዎች እንዳይከተሉት አላገዳቸውም ፡፡ "እኔም ከምድር ከፍ ከፍ ያልሁ እንደሆነ ሁሉን ወደ እኔ እስባለሁ" (ዮሐንስ 12፥32)፡፡ "አንዲያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና" (ዮሐንስ 3፥16)፡፡ ሰዎች የሚማረኩት በፍቅር ነው፤ ስቅለቱ የእግዚአብሔር ጥልቅ ፍቅር መገለጫ ነው፡፡

***1ኛ ዮሐንስ 4፥8-10***

*እግዚአብሔር ፍቅር ነውና፡፡ በዚህ የእግዚአብሔር ፍቅር በእኛ ዘንድ ተገለጠ፣ በእርሱ በኩል በሕይወት እንኖር ዘንድ እግዚአብሔር አንድ ልጁን ወደ ዓለም ልኮታልና፡፡ ፍቅርም እንደዚህ ነው፤ እግዚአሔር እርሱ ራሱ እንደ ወደደን ስለ ኃጢአታችንም ማስተሪያ ይሆን ዘንድ ልጁን እንደ ላከ እንጂ እኛ እግዚአብሔርን እንደ ወደድነው አይደለም፡፡*

## VI. ስቅለት እስላማዊ ማረጋገጫ

### 1. ቁርኣናዊ አስረጅ

በክርስቶስ ምትክ ሌላ ሰው እንደሞተ አድርጎ መውሰድ ፈጣሪን እንደማታለል ይቆጠራል፡፡ ድነት በክርስቶስ የመስቀል ስራ ብቻ እንደኾነ በደቀመዛሙርቱ የተሰበከው እውነት ፤ ቀደም ሲል  ክርስቶስ በሌላ ሰው እንዲመስል ተደርጓል የሚለው የሻቤህ እሳቤ መሐመድ እስከ መጣበት ለስድስት መቶ አመታት ያህል ክርስቲያኖኑ እንደ ተታለሉበት በበርካታ ሙሰሊማኑ ዘንድ ይታመናል፡፡

ቅዱስ ፣ ጠቢብ እና ፍቅር የተሞላ ፈጣሪ እንዴት ይህን ሊያደርግ ይችላል? ፈጣሪ ሰውን የማታለሉ እሳቤ በቁርአን ተቀምጧል፡፡ "መናፍቃን አላህን ያታልላሉ፡፡ እርሱም አታላያቸው ነው" (ሱረቱ 4፥142)፡፡ ሱረቱ 3፥54፣55 ሲናገር  "አይሁዳውያኑ አደሙ

[67] አዋርድ ሱማን ፣ኳዲታል ገፍራም ፣ ፊል- ማሽያ (ካይሮ፣ 1951 ፣ የግል ህትመት ፣ገጽ 109፡፡

አላህም አድማቸውን መለሰባቸው ፡፡ አላህም ከአድመኞች ሁሉ በላጭ ነው፡፡ ዒሳ ሆይ! እኔ ወሳጅህ ወደ እኔም አንሺህ ነኝ" ይላል፡፡

በቁርአን መሰረት የስቅለት ስህተት አስተምህሮ እስልምና መጥቶ እውነትን እስኪገልጥ ድረስ ፣ ኢየሱስ እንደተሰቀለ ሁሉም ሰው እንዲያምን ያደረገው ፈጣሪ /አላህ/ ራሱ ነው፡፡ ከስድስት መቶ አመት በኃላ ሆነ ፊት ይህ ተዐማኒነት የለውም፡

## 2. ሙስሊማኑ ማረጋገጫ

ከላይ ከተቀመጠው ሙግት በተቃራኒው በርካታ ሙስሊማኑ በስቅለት ያምናሉ፡፡ የባንጋሊው ገጣሚ እና የኖብል ተሸላሚ የሆነው ራቢንድራናት ታጎር የሚከተሉትን መሳጭ ነጥቦች ጽፏል፡-

*ክርስቶስ ከዘላለሙ ዙፋን ወደ ምድር መጣ፤ ወደ እርሱ ለሚመጡም ለሚርቁም ሁሉ የሞት ጽዋን ይወስድ ዘንድ ራሱን ለሞት አሳልፎ ሰጠ፡፡ ሞት ሊይዘው የማይችለውን ውድ ሕይወቱን እና ጥሪውን ለተቀበሉ ሆነ ርቀው ላሉ አፈሰሰ፡፡*

*ራሱንና ትውልዱን ያቆሰለውን የክፉው መሳሪያ ተመለከተ፡፡ የእብሪተኞች የሾለ ብረት፣ ጦር፣ የሰላ ቢላዋ፣ ቆልማማ ዱላ በቀጭኑ ሰው ላይ በመንኮራኩር (ጎማ) እንደተሰነቀሩ ስለታም ጫፎች የእሳት ፍንጣቂ ጭከናዎች በእርሱ ላይ ዘነቡ፡፡ ከሁሉ አስከፊው አሳልፈው የሰጡቱ ስሙን እና ቃሉን አዋቂ ነን ባዮች ክፉ ጥላቻ እና ግብዝ ማንነት ነው፡፡*

*እጆቹን በልቡ ላይ በማኖር የሞት ጣሩ እንዳላለቀ በሚሰማ ስሜት ዛሬም በአያሌዎች አዳዲስ ሚስማር ጎኖቹ እየተቸነከሩ ነው፡፡ በቤተ መቅደሶቻቸው ጥላ በመቆም ጎዱት አዲሰ ሕዝብንም በማነሳሳት "ስቀለው" ብለው ጮኹ፡፡ የሰውም ልጅ በታላቅ ስቃይ ' አምላኬ አምላኬ ሰለምን ተውኸኝ አለ*[68]

[68] ራብሪድናት ታጎር፣ የግጥም ስብስብ፣ (ኒው ዮርክ፣ ማክሚለን፣1937)፣ ገጽ .45፡፡

*የግል ማስታወሻ*

13

## ኢየሱስ ለምን ሞተ

መጽሐፍ ቅዱስም ቁርአንም በሰው ተፈጥሮአዊ ኃጢአተኝነት ላይ ይስማማሉ። ቁርአንየሰውበኃጢአት መውደቅ በኤደን ገነት መጀመሩን ይገልጻል። በሱረቱ 2፥35-38 እና 7፥19-26 ላይ አዳምን እና ሔዋንን “ ሰይጣን እንዳዳለጣቸው” ይናገራል። በዘሮቻቸውም ያስከተለውን በሱረቱ 2፥36፣ 7፡24 “ ሁላችሁም ኹናችሁ ከርሷ ውረዱ” ሲል ይገልጻል።

ቁርኣን ሰው በኃጢአት ምክንያት መጉደሉን (መለየቱን) ያስረግጣል፦

***ሱረቱ 11፥9***

*ሰውንም በእርግጥ ተስፋ ቆራጭ ክህደት ብርቱ ነው።*

***ሱረቱ 12፥53***

*ነፍሱ ሁሉ በመጥፎ ነገር በእርግጥ አዛዥ ናትና።*

***ሱረቱ 14፥34***

*ሰው በጣም በደለኛ ከሓዲ ነው።*

***ሱረቱ 17፥67***

*ሰውም በጣም ከሓዲ ነው።*

***ሱረቱ 33፥72***

*እርሱ /ሰው/ በጣም በደለኛ ተሳሳች ነውና፡፤*

***ሱረቱ 100፥6***

*ሰው ለጌታው ብርቱ ከሓዲ ነው።*

ብሉይ ኪዳን በኢሳያስ 53፥6 ላይ “ እኛ ሁላችን እንደ በጎች ተቅበዝብዘን ጠፋን ከእኛ እያንዳንዱ ወደ ገዛ መንገዱ አዘነበለ፤ እግዚአብሔርም የሁላችንን በደል በእርሱ ላይ አኖረ” ይላል። አዲስ ኪዳን በሮሜ 3፥10-20 እዲህ ይላል፦ “ጻድቅ የለም አንድስ እንኳ፤ አስተዋይም የለም፤ እግዚአብሔርንም የሚፈልግ የለም፤ ሁሉ ተሳስተዋል፤ በአንድነትም የማይጠቅሙ ሆነዋል፤ ቸርነት የሚያደርግ የለም፦ አንድ ስንኳ የለም፤ ጉሮሮአቸው እንደ ተከፈተ መቃብር ነው። በምላሳቸውም ሸንግለዋል፤ የእባብ መርዝ ከከንፈሮቻቸው በታች አለ፤ አፋቸውም እርግማንና መራርነት ሞልቶበታል፤ እግሮቻቸው ደምን ለማፍሰስ ፈጣኖች ናቸው፤ ጥፋት እና ጉስቁልና በመንገዳቸው ይገኛል፤ የሰላምንም መንገድ አያውቁም። በዓይኖቻቸው ፊት እግዚአብሔርን መፍራት የለም። አፍም ሁሉ ይዘጋ ዘንድ ዓለምም ሁሉ

ከእግዚአብሔር ፍርድ በታች ይሆን ዘንድ ሕግ የሚናገረው ሁሉ ከሕግ በታች ላሉት እንዲናገር እናውቃለን። ይህም የሕግን ሥራ በመሥራት ሥጋ የለበሰ ሁሉ በእርሱ ፊት ስለ ማይጸድቅ ነው፤ ኃጢአት በሕግ ይታወቃልና።"

በዚህም ምክንያት ሁሉም ሙስሊም "ጌታችን ሆይ! ኃጢአቶቻችንንም ለኛ ማር። ክፉ ሥራዎችንንም ከኛ አብስ። ከንጹሖቹም ሰዎች ጋር ግደለን" ብለው ይጸልያሉ (ሱረቱ 3፥193)። ነገር ግን ትልቁ ጥያቄ ይህ ጸሎት ተቀባይነት የሚያገኘው እንዴት ነው? የሚለው ነው።

## I.መልካም ሥራ አያድንም

ቁርኣን መልካም ስራ ክፉውን እንደሚሽር ያስተምራል። ሱረቱ 11፥114 "ሶላትንም በቀን ጫፎች ከሌሊትም ክፍሎች ፈጽም። መልካም ሥራዎች ኃጢአቶችን ያስወግዳሉና ። ይህ ለተገሳጮች ግሳጼ ነው። ከዚህ በታች ያሉ ክፍሎች መልካም ሥራ ክፉን ለማስወገድ ያለውን አንድምታ ይመክራል፡-

***ሱረቱ 2፥271***

*ምጽወአቶችን ብትገልጹ እርሷ ምንኛ መልካም ናት። ብትደብቋት እና ለድኾች ብትሰጧትም እርሱ ለእናንተ በላጭ ነው። ከኃጢአቶቻችሁም ከእናንተ ያብሳል።*

***ሱረቱ 5፥12***

*ሶላትን ብታስተካክሉ ግዴታ ምጽዋትንም ብትሰጡ በመልዕክቶቼም ብታምኑ ብትረዱዋቸውም ለአላህም*

*መልካም ብድር ብታበድሩ ኃጢአቶቻችሁን ከናንተ በእርግጥ አብሳለሁ።*

***ሱረቱ 5፥45***

*ዓይንም በዓይን.....በእርሱም የመጸወተ (ማረ) ሰው እርሱ ለርሱ (ለሰራው ኃጢአት) ማስተሰሪያ ነው።*

***ሱረቱ 5፥89***

*አላህ በመሀላቸው በወደቁ አይዛችሁም። ግን መሀላዎችን (ባሰባችሁት) ይይዛችኃል። ማስተሰሪያውም ቤተሰቦቻችሁን ከምትመግቡት ከመካከለኛው (ምግብ) ዐስርን ምስኪኖች ማብላት ወይም እነሱን ማልበስ ወይም ጫንቃን ነጻ ማውጣት ነው፤ (ከተባሉት አንዱን) ያላገኘ ሰው ሦስት ቀኖችን መጾም ነው።*

*ሱረቱ 29፥7*

*እነዚያም ያመኑ ፣ መልካሞችንም የሠሩ መጥፎዎቹን ሥራዎቻቸውን ከእነሱ ላይ እናብስላቸዋለን። በዚያም ይሠሩት በነበሩት መልካም ስራ በእርግጥ እንመነዳቸዋለን።*

እነዚህ ክፍሎች ጸሎት፣ ልግስና፣የፈጣሪ መልዕክተኞችን መደገፍ፣ በቀልን ማስወገድ፣ ባሮችን ነጻ ማውጣት እና መጾም የኃጢአትን ይቅርታ እንደሚያስገኝ ይናገራሉ። መጽሐፍ ቅዱስ መልካም ሥራ የኃጢአትን ይቅርታ ፈጽሞ እንደማያስገኝ ያስገነዝባል፡-

*ኤፌሶን 2፥8-9*

*ጸጋው በእምነት አድኖአችኋልና፣ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤ ማንም እንይመካ ከሥራ አይደለም ። እኛ ደግሞ አስቀድመን የማናስተውል ነበርንና፣ የማንታዘዝ፣ የምንስት ፣ ለምኞትና ለልዩ ልዩ ተድላ አንደባሪያዎች የምንገዛ፣ በክፋትና በምቀኝነት የምንኖር ፣ የምንጣላ፣ እርስ በእርሳችን የምንጠላላ ነበርን። ነገር ግን የመድኃኒታችን የእግዚአብሔር ቸርነትና ሰውን መውደዱ በተገለጠ ጊዜ እንደምህረቱ መጠን ለአዲስ ልደት በሚሆነው መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ በመታደስ አዳነን አንጂ እኛ ስላደረግነው በጽድቅ ስለነበረው ስራ አይደለም፤ ያን መንፈስም በጸጋው ጻድቀን በዘላለም ሀይወት ተስፋ ወራሾች እንድንሆን በመድሃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በእኛ ላይ አትርፎ አፈሰሰው። ቃሉ የታመነ ነው።*

እግዚአብሔር መልካም ስራችን እና ክፉ ስራችንን የሚመዝን መስፈሪያ አይጠቀምም። አንድ ሰው መልካም ስራዎቹ ከክፉ ስራዎቹ በሚዛን በልጦ ቢገኝ እንኳ አይድንም፤ አይጸድቅምም!

ሁለት ዐበይ ምክንያቶችን መመልከት ይቻላል፡-

*አንደኛ፦* ማንኛውም የምንፈጽመው መልካም ስራ ከእግዚአብሔር የተሰጠ ነው። እርሱ የሕይወት እና መልካም ስራ ሁሉ ኃይል ሰጪ ነው። የምንለግሰው ገንዘብ፣ የምንጠቀመው ኃይል፣ ደስተኛ የሚያደርገን መልካም ጤና፣ ጊዜያችን ሁሉ ሳይቀር ከእርሱ ዘንድ የተቀበልናቸው መለኮታዊ ስጦታዎች ናቸው። ዳዊት በኢየሩሳሌም ለእግዚአብሔር ቤተመቅደስ ግንባታ ሲለግስ ፣ ይህን ተናግሮ ነበረ ፡- "ከሁሉ ከአንተ ዘንድ ነውና፣ ከእጅህም የተቀበልነው ሰጥተንሃልና ይህን ያህል ችለን ልናቀርብልህ እኔ ማን ነኝ" (1ኛ ዜና 29:14)። ከላይ የተጠቀሱት የእግዚአብሔር ስጦታ መንፈሳዊ ዕዳዎቻችን መክፈል አይችሉም።

*ሁለተኛ* ፡- በአለም በአንዳቸውም ፍርድ ቤት ወንጀለኛን በሰራው መልካም ስራዎች ምክንያት ከፍርድ ነጻ አያደርግም። ያለውን ገንዘብ ለሌሎች ሰለ ለገሰ ወንጀለኛው ከጥፋጠኝነት ነጻ ሊወጣ

ይችላልን? በፍጹም ፡- ፍርድ ቤቱ ስለ ፈጸመው ወንጀል ተገቢውን ፍርድ ይሰጠዋል እንጂ፤ ማንኛውም መልካም ስራ የኃጢአት ይቅርታን አይሰጥም ፤ ኃጢአታችንን እና መተላለፋችንን ይቅር ሊል የሚችለው ኢየሱስ ብቻ ነው፡- " ኃጢአተኞችን ሊያድን ክርስቶስ ኢየሱስ ወደ አለም መጣ የሚለው ቃል የታመነና ሁሉ እንዲቀበሉት የተገባ ነው " (1ኛ ጢሞቴዎስ 1፡15)፡፡

## II. ቤዛ ያስፈልገናል

### 1.ቤዛነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትዕዛዝ ነው ፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ "ደምም ሳይፈስ ስርየት የለም" ይላል (ዕብራውያን 9፡22)፡፡ አዳም እና ሔዋን በኃጢአት በወደቁ ጊዜ በእግዚአብሔር ፊት እራቆታቸውን / አፍረታቸውን/ ሆኑ፤ አግዚአብሔር ግን እንስሳን በመሰዋት የእንስሳውን ቆዳ ወስዶ አፍረታቸውን አለበሰ (ዘፍጥረት 3፡20)፡፡ በዚህም እግዚአብሔር የቤዛነትን ስራ በራሱ ማዘጋጀቱን እንረዳለን፡፡

የአዳም ልጆች የሆኑት አቤልና ቃየን በእግዚአብሔር ፊት መሰዋአትን ሰው፡፡ እግዚአብሔር በመስዋእት የቀረበውን የአቤልን መስዋእት ተቀበለ ፤ ደም ስላልፈሰሰ የቃየንን መስዋእት አልተቀበለም (ዘፍጥረት 4፡3፣4)፡፡

ጥንታዊያን ነብያት ከእግዚአብሔር ዘንድ ይቅርታን ለመቀበል፣ ጸጋውን እና ማዳኑን ለማመስገን እንስሳትን ይሰው ነበር (ዘፍጥረት 8፡20)፡፡ ኖህ (ዘፍጥረት 8፡20)፣ ኢዮብ (ኢዮብ1፡5)፣ አብርሃም (ዘፍጥረት 12፡8)፣ ሂሳቅ ( ዘፍጥረት 22፡13፣26፡ 25)፣ያዕቆብ (ዘፍጥረት 35፡3)፡፡

የዘሌዋውያን መጽሐፍ በአመዛኙ አግዚአብሔር የህዝቡን ኃጢያት ይቅር ለማለት የእንስሳ መስዋእት ህጎችን /ስርአቶችን/ ይናገራል፡፡ የእስራኤል ልጆች ከፈርኦን ባርነት ነጻ ለመውጣት የፋሲካን በግ መስዋእት ያቀርቡ ነበር፤ከግብጽ ባርነት የዳኑበትን ይህን ስርዐት በየአመቱ እንዲያደርጉትም ታዘዋል (ዘጸአት 12፡1፣2)፡፡ አሮን እና ዘሩ የኾኑት ሌዋውያን ለእግዚአብሔር መስዋዕት እንዲያቀርቡ የተቀደሱ ነበሩ፡፡

መሰዋዕቶች በሙሉ እውነተኛው መስዋዕት ወደ ኾነው ኢየሱስ ክርስቶስ አመላካቾች ናቸው፡፡ መጥምቁ ዮሐንስ ኢየሱሰን ባየው ጊዜ በሙሴ የተደነገጉት መስዋዕቶች ሁሉ ፍጻሜ አንደሆነ መስክሯል፡- "እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ፡፡" 1ኛ ቆሮንቶስ 5፡7 " ፋሲካችን ክርስቶስ ታርዷልና" ሲል ያጸናዋል፡፡

*ዕብራውያን 9፥22- 28*

*እንደ ሕጉም ከጥቂቶች በቀር ነገር ሁሉ በደም ይነጻል፤ ደምም ሳይፈስ ስርየት የለም። እንግዲህ በሰማያት ያሉትን የሚመስለውን ነገር በዚህ ሊነጻ እንጂ በሰማያት ያሉት ራሳቸው ከእነርሱ ይልቅ በሚበልጥ መሰዋዕት ሊነጹ የግድ ነበረ። ክርስቶስ በእጅ ወደ ተሰራች ፣የእውነተኛይቱ ምሳሌ ወደ ምትሆን ቅድስት አልገባምና፤ ነገር ግን በእግዚአብሔር ፊት ስለ እኛ አሁን ይታይ ዘንድ ወደ እርስዋ ወደ ሰማይ ገባ። ሊቀ ካህናትም በየዓመቱ የሌላውን ደም ይዞ ወደ ቅድስት እንደሚገባ ፣ራሱን ብዙ ጊዜ ሊያቀርብ አልገባም፤ እንዲህ ቢሆንስ፣ ዓለም ከተፈጠር ጀምሮ ብዙ ጊዜ መከራ ሊቀበል ባስፈለገው ነበር ፤ አሁን ግን በዓለም ፍጻሜ ራሱን በመሠዋት ኃጢአትን ሊሽር አንድ ጊዜ ተገልጦአል። ለሰዎችም አንድ ጊዜ መሞት ከእርሱ በኋላም ፍርድ እንደ ተመደበባቸው፣ እንዲሁ ክርስቶስ ደግሞ ፣የብዙዎችን ኃጢአት ሊሸከም አንድ ጊዜ ከተሰዋ በኋላ ፣ያድናቸው ዘንድ ከተሰዋ በኋላ ፣ያድናቸው ዘንድ ለሚጠባበቁት ሁለተኛ ጊዜ ያለ ኃጢአት ይታይላቸዋል።*

“

## 2. የአብራሃም ልጅ መስዋዕት በቁርአን

ቁርአን የአብራሃምን ታላቅ መስዋዕት አስመልክቶ የመስዋዕት አሳብን ይደግፋል። ሱረቱ 37፥107 “በታላቅ ዕርድም (መስዋዕት) ተቤዠነው” ሲል ፈጣሪ ስለ መቤዠት መናገሩን ይገልጻል።

መስዋዕት የኮነው ልጅ ማነው? የአል-ቁርጡቢ ጽሑፍ መሐመድን ጨምሮ ፣ኢቢኑ አባስ ፣ አሊ- ኦማር፣ አቡደላ ኢብኑ ማሱድ ፣ አቡደላህ ፣ ኢብኑ ኦማር፣ ማሱድ እና ሎሎችም የመስሊም መሪዎችን ጠቅሶ የአል-ኩርቱቢ መስዋዕት የኮነው ልጅ **ኢሳቅ** እንደሆነ ይገልጻል። ነገር ግን መሐመድን ጨምሮ ኢብኑ አባስ ፣ አቡ-ሁረይራ እና አቡ - ቴፋይል ከኢስማኤል ጋር ያገናኛሉ። አቡደላህ የሱፍ አሊ በጽሑፉ “ መስዋዕት በሰው ሳይኾን በፈጣሪ ተመስርቷል፤ ተቤዢውም ራሱ ነው” ይላል።

አል- ባይዳዊ “ በሚሰዋው ልጅ ፈንታ መስዋዕት በመዘጋጀቱ ፍጻሜ” ማግኘቱን ይገልጻል። አል- ሳዲን ጠቅሶ አል- ራዚ “ አብርሃም ፈጣሪ በጠራው ወቅት በዙሪያ ሲያማትር ሳለ ከተራራ ነጭ እና ጥቁር መልክ ያለው ጠቦት በግ ተመለከተ፤ ልጁንም በመተው የተዘጋጀውን ጠቦት ሰዋ። ልጁንም ነጻ በማድረግ ‘ ዛሬ ለእኔ የተሰጥህ ስጦታ ነህ’ ሲል ተናገረ፤ ጠቦቱ በአብርሐም ልጅ ፈንታ ፈጣሪ የተቀበለው ታላቅ መስዋዕት አንደሆነ” ያስቀምጣል።

ሙስሊማን ሁለት ዓመታዊ በዓላት አሏቸው ፦ ኢድ አል-ኻቢር (ታላቁ በዓል) እና ኢድ - ሳገ (ታናሹ በዓል) ። ሁለተኛው በረመዳን ጾም ወር መገባደጃ የሚከወን ኢድ አል-ፊጥር (ጾም ፍቺ) በዓል ነው። የመጀመሪያው ኢድ አል-አደሃ (የመስዋዕት በዓል) የአብርሃም ልጅ መስዋዕትን የሚዘክር ሆኖ በበዓሉ የእንስሳት እርድ ይከወናል። ሐጂ የሚሄዱ ሰዎች ይህን መስዋዕት በመካ እንደፈጸሙ ይቆጠራል። ይህን አስመልክቶ ቁርኣን የሚከተለውን ያስቀምጣል ፦

*ሱረቱ 22፥32-36*

*የአላህንም የሃይማኖት ምልክቶች የሚያከብር ሰው እርሷ ከልቦች የኾነች ጥንቃቄ ናት። ለእናንተ በእርሷ እስከ ተወሰነ ጊዜ ድረስ ጥቅሞች አሏችሁ። ከዚያም (የማስረጃ) ስፍራዋ እጥንታዊው ቤት አጠገብ ነው። ለሕዝብም ሁሉ (ወደ አላህ) መስዋዕት ማቅረብን ደነገግን። ከቤት እንስሳት በሰጣቸው ሲሳይ ላይ የአላህን ስም ብቻ ያወሱ ዘንድ (አዘዝናቸው)። አምላካችሁም አንድ አምላክ ብቻ ነው። ለእርሱም ብቻ ታዘዙ። ለአላህ ተዋራጆችንም አብስራቸው። እነዚያን አላህ በተወሳ ጊዜ ልቦቻቸው የሚጨነቁትን፣ በደረሰባቸውም (መከራ) ላይ ታጋሾችን፣ ሶላትንም አስተካክለው ሰጋጆችን፣ ከሰጠናቸውም ሲሳይ የሚለግሱትን (አብስር)። ግመሎችንም ለእናንተ ከአላህ ሃይማኖት ምልክቶች አደረግናቸው። በእርሷ ለእናንተ መልካም ጥቅም አላችሁ። በእርሷም ላይ (ስታርዷት) በሶስት እግሮችዋ ቆማ የተሰለፈች ሆና የአላህን ስም አውሱ። ጎኖቻቸውም በወደቁ ጊዜ ከእርሷ ብሉ። ለማኙንም ለልመና የሚያገዳድምንም አብሉ። እንደዚሁ ታመሰግኑ ዘንድ ለእናንተ ገራናት።*

አል-ጋህዛሊ ሱረቱ 37፥107ን ሲተነትን የሚከተለውን ያስረግጣል ፦“መስዋዕት ማቅረብ ወደ ፈጣሪ በመታዘዝ መቅረብን ፣እርሱን ተስፋ በማድረግም ከገሃነም ነጻ መውጣትን ያመለክታል። የሚቀርበው መስዋዕት በበዛ ቁጥር ወደ ፈጣሪ ይበልጥኑ የመቅረብ ብሎም ከገሃነም ሙሉ ለሙሉ ነጻ መውጣትን ያስገኛል፤ ይህ እንስሳን መስዋዕት በማድረግ ወደ ፈጣሪ መቅረብ የሚደረግ ስርዐት ነው”[69]

አንደ አይሻ እማኝነት ስለ ኢድ አል-ደኸአ መስወዕት ሙሐመድ “ሰው አንዳች ማድረግ አይቻለውም፤ በመስዋዕቱ ቀን ፈጣሪ ደስ ይሰኛል፤ የተሰዋው አንስሳ በትንሳኤ ቀን ቀንዱ፣ ጸጉሩና ኮቴው የሰዋውን ሰው ተግባር ለመመዘን አብሮ ይቀርባል። ደሙ በመስዋዕት ቀን ወደ

[69] አል- ጋዛሊ፣ አሂሃ፣ ኡለም ለ-ዲን ፣ ቅጽ .1 (ካይሮ፣ ቀ.ኣ. ) ገጽ፣ 243፣250።

ፈጣሪ ቀድሞ የሚደርስ ስለሆነ ፣ በዚህ ደስተኞች ልትሆኑ ይገባል"[70] ሲል መናገሩን ታስረዳለች፡፡

አል-አዳሕ በኢስላም መንፈሳዊ ትርጉሙ አብራሃም የታላቁን መስዋዕት እንስሳ ስጋ መብላቱን፣ ለድሆች መስጠቱን ወይም ከገሃነም ነጻ የመሆን ማረጋገጫን እንዳገኘ አመልካች አይደለም ፤ ይልቁንም የምትክ አገልግሎት ማሳያ አንዷ! ጠቦት እንስሳው ሂሳቅን የመቤዠት ምሳሌ ነው፡፡ አግዚአብሔር አንዲያ ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስ መስዋዕት አድርጓል ፡- "እነሆ የአለምንኃጢአት የሚያስወገድ የእግዚአብሔር በግ" (ዮሐንስ 1፥29፣36)፡፡

የአል-አዳሕ በኣል ምትክ ሆኖ የተሰዋውን የእግዚአብሔር ብቸኛ የማዳን መንገድ ማሳያ ነው፡፡ "ነገር ግን ገና ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቶአልና" (ሮሜ 5፥8)፡፡ ሙስሊማኑ የሙሴ ሕግ መስዋዕቶች በኢየሱስ ክርስቶስ መፈጸሙን ፣ በአል -አድሀ በዓል እውነተኛ ትርጉሙን ሰጥተዋል፡፡

## III. የእግዚአብሔር ፍርድ እና ምህረት ዕርቅ ተገቢነት

ቁርኣን ፈጣሪ ትክክለኛ ፈራጅ መኾኑን ያስተምራል "እነዚያንም የካዱትን ሰዎች በቅርቢቱ ዓለምና በመጨረሻይቱ ዓለም ብርቱን ቅጣት እቀጣቸዋለሁ፡፡ለእነርሱም ምንም ረዳቶች የሏቸውም" (ሱረቱ 3፥56)፡፡ ፍጹም ፍርድ መፈጸም አለበት፡፡ ጻድቅ እግዚአብሔር ኃጢአትን ፈጽሞ አያልፍም፤ ኃጢአተኛው ስለ ኃጢአቱ መክፍል ወይንም በምትኩ ሌላ ሰው መክፈል ይኖርበታል፡፡

ቁርኣን ፈጣሪ መኃሪም እንደሆነም ጭምር ይናገራል "እነሆ ከእናንተ ውስጥ በስሕተት ክፉን ሥራ የሠራ ሰው ከዚያም ከእርሱ በኃላ የተጸጸተ እና ሥራውን ያሳመረ እርሱ (አላህ) መሓሪ አዛኝ ነው በላቸው፤...... በቅርቢቱም በመጨረሻይቱም ዓለም በእናንተ ላይ የኣላህ ችሮታ እና እዝነቱ ባልነበረ ኖሮ በውስጡ በገባችሁበት ወሬ ምክንያት ታላቅ ቅጣት በእርግጥ በደረሰባችሁ ነበር" (ሱረቱ 6፥54፣ 24፥14)፡፡

ቁርአን ፍርድንም ምህረትንም በአንድነት የተናገረበት ሁኔታ አለ "አላህ ቅጣት ብርቱ መኾኑን አላህም መኃሪ አዛኝ መኾኑን እወቁ ፤ ....ጌታህ በእርግጥ ቅጣተ ፈጣን ነው፣ እርሱም በእርግጥ እጅግ መሓሪ አዛኝ ነው" (ሱረቱ 5፥98፣ 7፥167)፡፡

---

[70] ሚሻቅ፣ መጥሐፍ ፣ ቅጽ፣ IV. ምእራፍ 42፣ ክፍል .2፡፡

ቁርኣን ፈጣሪ ፈራጅም መኃሪም መኾኑን መጽሐፍ ቅዱስ ከሚሰጠው ምስክርነት ጋር ተስማሚ ነው። መኃሪነቱም ፈራጅነቱም በእርሱ ባከህሪ ውስጥ ጎን ለጎን በአንድነት የሚሄዱ ናቸው። ኃጢአተኛውን በሚምርበት ጊዜ ምህረቱ እንጂ ፈራጅነቱ አይሠራም። ኃጢአተኛውንም በሚቀጣበት ጊዜ ፍርዱ እንጂ ምህረቱ አይሠራም። ስለዚህ እነዚህን ባህሪያት እንዴት ነው ማስታረቅ የሚቻለው?

ቁርኣን ለዚህ ጥያቄ መልስ የለውም። መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ምህረት እና ፍርድ በአንድነት በመስቀል ላይ መገለጹን ይናገራል። ምህረቱ እና ፍርዱ የታረቀው የሰውን ኃጢአት ቅጣት በተሸከመው በኢየሱስ ነው። ኢየሱስ ይህን ማድረግ ችሏል፤ እርሱ አምላክ ሰውን ከኃጢአት ለማዳን ሰው ሆኖ የተገለጠ ነውና! "እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ ዓለሙን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበርና" (2ኛ ቆሮንቶስ 5፡19)።

አንድ ሙስሊም " መኃሪ አምላክ ቅዱስ የሆነውን መልዕክተኛ መስዋዕት ማድረግ ሳያስፈልግ የሰውን ኃጢአት ለምንድ ነው ይቅር ማለት ያልቻለው?" የሚል ጥያቄ ሊያስነሳ ይችላል። ይህ እሳቤ የኢየሱስ ሞት አስገዳጅ ኃይል ያለው አንደሆነ እንዲታሰብ ያደርጋል፤ ሆኖም ኢየሱስ ሰዎችን ማዳን ህይወቱን አሳልፎ የሰጠው በገዛ ፍቃዱ ብቻ ነው። ጴጥሮስ ኢየሱስን ሊይዙት በመጡ ጊዜ ለመከላከል በሚሞክርበት ወቅት ኢየሱስ " አባቴን እንድለምን እርሱም አሁን ከአሥራ ሁለት ጭፍሮች የሚበዙ መላእክት እንዲሰድልኝ የማይችል ይመስልሃልን ?" ሲል ተናግሯል (ማቴዎስ 26፥51-54)። ቀድም ሲል " ነፍሴን ደግሞ አነሣት ዘንድ አኖራለሁና ስለዚህ አብ ይወደኛል ። እኔ በፍቃዴ አኖራታለሁ እንጂ ከእኔ ማንም አይወስዳትም። ላኖራት ሥልጣን አለኝ ፤ ደግሞም ላነሣት ሥልጣን አለኝ" ( ዮሐንስ 10፥17፣18)።

ኢየሱስ በገዛ ፍቃዱ በመስቀል ላይ ምህረቱን እና ፍርዱን አስታርቋል፡-

> ***ኢሳ 53፥ 4-6***
>
> *በእውነት ደዌያችንን ተቀበለ ሕመማችንንም ተሸክሞአል፤ እኛ ግን እንደ ተመታ በእግዚአብሔርም እንደ ተቀሠፈ እንደ ተቸገረም ቆጠርነው። እርሱ ግን ስለ መተላለፋችን ቆሰለ። ስለ በደላችንም ደቀቀ፤ የደኅንነታችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበረ፡ በእርሱም ቁስል እኛ ተፈወስን።እኛ ሁላችን እንደ በጎች ተቅበዝብዘን ጠፋን፡ ከእኛ እያንዳንዱ ወደ ገዛ መንገዱ አዘነበለ፤ እግዚአብሔርም የሁላችንን በደል በእርሱ ላይ አኖረ።*

መዝሙረኛው " ነገር ግን ክብር በምድራችን ያድር ዘንድ ማዳኑ ለሚፈሩት ቅርብ ነው፤ ምሕረትና እውነት ተገናኙ ጽድቅና ሰላም ተስማሙ።" ይህ የመዝሙረኛው ትንቢት ከብዙ

ሺህ ዓመታት በኃላ ምህረቱና ፍርዱ በታረቁበት በኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል ተፈጽሟል፡፡ በመስቀል ላይ በተሰራው ስራ ክርስቶስ በሚያምኑት ሁሉ ላይ የመለወጥ እና ማዳን ስራ ይሰራል፡፡

*2ኛ ቆሮንቶስ 5፥17-21*

*ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፎአል፤ እነሆ፡ ሁሉም አዲስ ሆኖአል፡፡ ነገር ግን የሆነው ሁሉ፡ በክርስቶስ ከራሱ ጋር ካስታረቀን የማስታረቅም አገልግሎት ከሰጠን ከእግዚአብሔር ነው፤ እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ ዓለሙን ከራሱጋር ያስታርቅነበርና፡፡ በደላቸውንአይቆጥርባቸውምነበር፤በእኛም የማስታረቅ ቃል አኖረ፡፡ እንግዲህ እግዚአብሔር በእኛ እንደሚማልድ ስለ ክርስቶስ መልዕክተኞች ነን፤ ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ ብለን ስለ ክርስቶስ እንለምናለን፡፡ እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንሆን ዘንድ ኃጢአት ያላወቀውን እርሱን ስለ እኛ አደረገው፡፡ ኢየሱስን ወደ እኛ ዓለም ያመጣውና እንዲሞት ምክንያት የሆነው ኃጢአታችን ነው፡፡ ስሞኦን ህጻኑን አቅፎ እግዚአብሔር ሲባርክ እንዲህ አለ፡- "ጌታ ሆይ አሁን እንደ ቃልህ ባሪያህን በሰላም ታሰናብተዋለህ ፤ አይኖቼ በሰዎች ሁሉ ፊት ያዘጋጀኸውን ማዳንህን አይተዋልና፤ ይህም ለአሕዛብህም ለእስራኤል ክብር ነው፤.... ይህ ለእስራኤል ላሉት ለብዙዎቹ ለመውደቃቸውና ለመነሣታቸው ለሚቃወሙትም ምልክት ተሾሞአል፣ በአንቺም ደግሞ በነፍስሽ ሰይፍ ያልፋል አላት"( ሉቃስ 2፥25-35)፡፡ ሰይፉ የመስቀል ሰይፍ ነው፡፡*

ኢየሱስ "ሙሴም በምድረ በዳ እባብን እንደሰቀለ እንዲሁ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ የሰው ልጅ ሊሰቀል ይገባዋል፡፡ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጅን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና" (ዮሐንስ 3፥14-16)፡፡ ይህ ኢየሱስ በመስቀል ስላዘጋጀው የድነት ዝግጅት ምንነት ያመላክታል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ይህን እውነት ያስረግጣል፡-

*ዕብ 10፥19-23*

*እንግዲህ ወንድሞች ሆይ፡ በመረቀልን በአዲስና በሕያው መንገድ ወደ ቅድስት በኢየሱስ ደም በመጋረጃው ማለት በሥጋው በኩል እንድንገባ ድፍረት ስላለን፤ በእግዚአብሔርም ቤት ላይ የሆነ ታላቅ ካህን ስላለን፤ ከክፉ ሕሊና ለመንጻት ልባችንን ተረጭተን ሰውነታችንንም በጥሩ ውኃ ታጥበን በተረዳንበት እምነት በቅን ልብ እንቅረብ፤ የተስፋን ቃል የሰጠው የታመነ ነውና እንዳይነቃነቅ የተስፋችንን ምስክርነት እንጠብቅ፡፡*

አንድ መጋቢ ወደ አንድ ትንሽ መደር ይንቀሳቀሳል፤ በዚያም መንደር ስለ ክርስቶስ አዳኝነት እያስተማረ ይቆያል፡፡ ብዙ ሰራተኞች ወደሚገኙበት መስክ በመሄድ "ከእናንተ መካከል ድነት

ምን እንደሆነ የሚነግረኝ ማነው" በማለት ይጠይቃል፡፡ በመንደርዋ የሚገኝ አንድ ሰው አንድን ትል በሰንበሌጥ ወስዶ ባኖረው የክብ ቅርጽ ላይ ያስቀምጣል፡፡ ሰንበሌጡንም በእሳት ያያይዛል፡፡ ትሏም መርመስመስ ትጀምራለች፤ራስዋንም ማዳን ሳትችል ትቀራለች፡፡ ከነዋሪዎቹም መካከል አንዱ ደርሶ ትሏን ከሞት ይታደጋል፡፡ ሰውየውም "ድነት ማለት ልትጠፋ ያለቸውን ነፍስ በጸና እጅ መታደግ፣ ከእሳት እውጥቶ ወደ ድነት መለወጥና መንከባከብ " እንደሆነ ይመልሳል፡፡ የመጋቢው ልብ በእጅጉ ተነካ፣ በምለሹም ተደነቀ፡፡ "እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ ዓለሙን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበረና፣ በደላቸውን አይቆጥርባቸውም ነበር፡፡ በእኛም የማስታረቅ ቃል አኖረ" (2ኛ ቆሮንቶስ 5፥19)፡፡

### IV. ሙስሊማኑ የክርስቶስን መስቀል ሥራ የሚገፉት ለምንድነው

ሙስሊማኑ የክርሰቶስን የመስቀል ሥራ የሚገፉበት ሁለት ምክንያት አለ፡-

### (1) ሙስሊማኑ ኃጢአት ፈጣሪን የማይጉዳ ሕጉንም የማይተላለፍ እንደሆነ ያስባሉ፡፡

ለሙስሊማኑ ፈጣሪ ታላቅ ነው፡፡ ምንም አይነት ኃጢአት እርሱን አይረብሸውም አያሳዝነውም፡፡ ኃጢተኛውን መቅጣት ምንም ትርጉም የለውም፡፡ "እግዚአብሔርን በቃላችሁ አታክታችኃል" (ሚልኪያስ 2፥17)፡፡ ማንም ሙሲሊም "አንተን ብቻ በደልሁ፣በፊትህም ክፋትን አደረግሁ" (መዝሙር 51፥4) አይልም፡፡

ለሙስሊማኑ ኃጢአት ማድረግ በጽሑፍ ፈተና ወቅት የተሳሳተ መልስ እንደመስጠት ነው የሚቆጠረው፡፡ "2+2=5" የሚለው ውጤት ስህተት ነው፤ ሆኖም የሂሳብ መመህሩንም ሆነ የሂሳብ ስሌት ህግጋትን አይጎዳም፡፡ አይዳውያኑ እና ክርስቲያኑ ኃጢአትን በማግዘፍ ችግር እስከ መፍጠር የሚደርሱ ተደርገው ነው በሙስሊማኑ ዘንድ የሚታዩት፡፡

### (2) ሙስሊማኑ ፈጣሪ የፈቀደውን ይቅር ባይ እንደኾነ ያስባሉ

በሙስሊማኑ ዘንድ ይቅርታ መስጠትም ሆነ በገነት ማኖር የፈጣሪ ውሳኔ ብቻ ነው፡፡ በእርሱ ፍቃድ ላይ በጽኑ ይደገፋሉ ፤ ስለዚህ የክርስቶስ መስቀል ሥራ ስለ ምን አሰፈለገ? ኃጢአትን በማወሳሰብ እና በማግዘፍ ክርስቲያኑ ራሳቸውን ችግር ውስጥ በመከተተት ፣ ፈጣሪ ኃጢአተን ይቅር ለማለት ስለ ምን መሞት አስፈለገው? ሲሉ ይሞግታሉ፡፡

ከላይ ለተጠቀሱት ሁለት ሙግቶች ክርስቲያናዊ ምላሻችን የሚሆነው በፈጣሪ ዘንድ ኃጢአት ምን ያህል ውስብስብ አንደሆነ የምንወስነው እኛ አይደለንም የሚል ነው፡፡ ይህ የፈጣሪ ስራ ነው፤ እርሱ ስለ ኃጢአት ተናግሯልና! በብሉይ ኪዳን ሙሴ፣ በመዝሙራት ዳዊት እና

በወንጌላት ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ማዳን ዕቅድ ገልጸውልናል። መጽሐፍ ቅዱስ "በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም….መዳንም በሌላ በማንም የለም እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና" (ሐዋሪያት ሥራ 4፥10፣12)።

## V. ስቅለት ወደ ቅድስና ሕይወት ይመራል

የክርስቶስ መስቀል ኃጢአት ትልቅ ዋጋ የሚያስከፍል መሆኑን ያመላክተናል። እግዚአብሔር "ለገዛ ልጁ ያልራራለት ነገር ግን ስለ ሁላችን አሳልፎ ሰጠው" (ሮሜ 8፥32)። ኃጢአት በእግዚአብሔር ላይ ማመጽ ነው። ዳዊት ኃጢአት አደረገ ፣ ወደ እግዚአብሔርም ንስኃ ገባ " አንተን ብቻ በደልሁ ፣ በፊትህም ክፉትን አደረግሁ በነገርህ ትጸድቅ ዘንድ በፍርድም ንጹሕ ትሆን ዘንድ" ( መዝሙር 51፥4)።

ከክርስቶስ ጋር በጥምቀት አንድ በመሆናቸው አማኞች "እኔም አሁን ሕያው ሆኜ አልኖርም ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል ፤ አሁንም በሥጋ የምኖርበት ኑሮ በወደደኝ እና ስለ እኔ ራሱን በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለ እምነት ምኖረው ነው" (ገላትያ 2:20)።

የእግዚአብሔር ቃል ይናገራል፦

*ሮሜ 6፥ 3-12*

*ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ የተጠመቅን ሁላችን ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ እንደ ተጠመቅን አታውቁምን? እንግዲህ በክርስቶስ በአብ ክብር ከሙታን እንደ ተነሣ እንዲሁ እኛም በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስ ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበርን። ሞቱንም በሚመስል ሞት ከእርሱ ጋር ከተባበርን ትንሣኤውን በሚመስል ትንሣኤ ደግሞ ከእርሱ ጋር እንተባበራለን፤ ከእንግዲህስ ወዲያ ለኃጢአት እንዳንገዛ የኃጢአት ሥጋ ይሻር ዘንድ አሮጌው ሰዎችን ከእርሱ ጋር እንደ ተሰቀለ እናውቃለን፤ የሞተስ ከኃጢአቱ ጸድቋልና። ነገር ግን ከክርስቶስ ጋር ከሞትን ከእርሱ ጋር ደግሞ በሕይወት እንድንኖር እናምናለን፤ ክርስቶስ ከሙታን ተነሥቶ ወደ ፊት እንዳይሞት ሞትም ወደ ፊት እንዳይገዛው እናውቃለንና። መሞትን አንድ ጊዜ ፈጽሞ ለኃጢአት ሞቶአልና፤ በሕይወት መኖር ግን ለእግዚአብሔር ይኖራል። እንዲሁም እናንተ ደግሞ ለኃጢአት እንደ ሞታችሁ፡ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን ሆናችሁ ለእግዚአብሔር ሕያዋን እንደ ሆናችሁ ራሳችሁን ቁጠሩ። እንግዲህ ለምኞቱ እንድትታዘዙ በሚሞት ሥጋችሁ ኃጢአት አይንገሥ፤*

*2ኛ ቆሮንቶስ 5፥ 14-21*

*ይህን ስለ ቆረጥን የክርስቶስ ፍቅር ግድ ይለናልና፤ አንዱ ስለ ሁሉ ሞተ፤ እንግዲያስ ሁሉ ሞቱ፤ በሕይወትም ያሉት ስለ እነርሱ ለሞተውና ለተነሣው እንጂ ወደ ፊት ለራሳቸው እንዳይኖሩ ስለ ሁሉ ሞተ። ስለዚህ እኛ ከአሁን ጀምሮ ማንንም በሥጋ እንደሚሆን አናውቅም፤ ክርስቶስንም በሥጋ እንደ ሆነ ያወቅነው ብንሆን እንኳ አሁን ግን ከእንግዲህ ወዲህ እንደዚህ አናውቀውም። ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፎአል፤ እነሆ ሁሉም አዲስ ሆኖአል። ነገር ግን የሆነው ሁሉ በክርስቶስ ከራሱ ጋር ካስታረቀን የማስታረቅም አገልግሎት ከሰጠን ከእግዚአብሔር ነው፤ እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ ዓለሙን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበርና፣ በደላቸውን አይቆጥርባቸውም ነበር፤ በእኛም የማስታረቅ ቃል አኖረ። እንግዲህ እግዚአብሔር በእኛ እንዲማልድ ስለ ክርስቶስ መልዕክተኞች ነን፤ ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ ብለን ስለ ክርስቶስ እንለምናለን። እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንሆን ዘንድ ኃጢያት ያላወቀውን እርሱን ስለ እኛ ኃጢአት አደረገው።*

በተሰቀለው ክርስቶስ አዲስ ህይወት ስላለንም " ዓለም ለእኔ የተሰቀለበት ፣እኔም ለዓለም የተሰቀልሁበት ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በቀር ሌላ ትምክህት ከእኔ ይራቅ" እንላለን (ገላትያ 6፥14)።

## VI. መስቀል የፍቅር ሥነ -አመክንዮ


ሁለት ዶክትሬቶች ያሉት የዩኒቨርስቲ ፕሮፌሰር ሙስሊም ሦስተኛውን በመስራት ላይ ነበር። ለምርምር ስራው ይረዳው ዘንድ አንድ ክርስቲያን መጋቢን ቃለ መጠይቅ ያደርጋል። መጋቢው በጸጋ ተቀብሎ መጠይቆቹን በሙሉ በዝርዝር ይመልስለታል። ፕሮፌሰሩም በስተመጨረሻ መጋቢውን ይጠይቀዋል ፦ "ይህ ያህል ትልቅ አሳቢ ሆነህ ሳለ እንዴት ክርስቲያን ልትሆን ቻልክ ?" "ልዑል ፈጣሪ ልጅ እንዳለው ወይም በመስቀል ላይ እንዲሞት ሲፈቅድ ስለ ምን ከኃጢአተኞች እጅ ሊያድነው አልቻለም? ተኣምራት አድራጊው ኢየሱስ ጠላቶቹን መግደል፣ ራሱንም ማዳን እንዴት ተሳነው?"

መጋቢው በጸሎት ምሪትን ከተቀበለ በኃላ ፕሮፌሰሩን ይጠይቃል ፦"ልጆች አሉህን" ፕሮፌሰሩም "አዎን ሴት ልጅ አለኝ " ሲል መለሰ። " ልጅህን በጆርባህ አዝለሃት ታውቃለህን?" በታላቅ ፈገግታ "አዎን! ይህን የማያደረግ አባት ለመሆኑ አለ?" ፕሮፌሰሩ መለሰ።

መጋቢውም “ አሳቤን ግልጽ ለማድረግ ተጨማሪ ጥያቄ ብጠይቅህ ቅር እንደማይልህ ተስፋ አደርጋለሁ”:: ፕሮፌሰሩ “እባክህ ጠይቅ ሲል መለሰ፤” መጋቢው “ ታዲያ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎችህን ለምን በጀርባህ እንዲታዘሉ አታደርግም? ብሎ ጠየቀው፡፡

ፕሮፌሰሩም በጥያቄው ተናዶ ሳለ መጋቢው በማቋረጥ “ አእምሮና ልብ ለየቅል አመክንዮ እንዳላቸው ማስረግጥ እወዳለሁ፡፡ በቤትህ የተገበርከው አመክንዮ ልባዊው ስለ ነበር ልጅህን በጀርባህ ለማዘል ፍቃደኛ ነበርክ ፤ ይህ ትክክል ነው የፍቅር አመክንዮ ነውና!፡፡ በዩኒቨርስቲ የተገበርከው ክብርህን ማስጠበቅህ አእምሮአዊውን አመክንዮ ያሳያል፤ ይህ ትክክል ነው፡፡”

መጋቢውም በማጠቃለያው የሚከተለውን እውነት አስተላለፈ ፡- “መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ፍቅር መኾኑን ያስተምራል፡፡ የልብን አመክንዮ በመተግበር የሚራራልን አምላክ አንደኾነ ያስረግጣል፡፡ የሮሜ መጽሐፍ ሲናገር ፡-“ገና ደካሞች ሳለን ክርስቶስ ዘመኑ ሲደርስ ስለ ኃጢአተኞች ሞቶአልና፡፡ ስለ ጻድቅ የሚሞት በጭንቅ ይገኛልና ፣ ስለ ቸር ሰው ግን ሊሞት አንኳ የሚደፈር ምናልባት ይገኝ ይሆናል፡፡ ነገር ግን ገና ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቶአልና እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል” ይላል(ሮሜ 5፡6-8)፡፡



*የፍቅር አመክንዮ*

ሙስሊም የኾነች ሴት በተመሳሳይ ይኽንኑን መጋቢ በመጎብኘት ጥያቄ አቅርባለታለች፡- “እንዴት ክርስቲያን ልትኾን ቻልክ? ልዑል ፈጣሪ ልጅ እንዳለው፣ ይሞትም ዘንድ እንደላከው ልታምን እንዴት ቻልክ ? መጋቢው የሦስት ወር ልጅሽ ባንቺ ላይ ሙሉ ለሙሉ ጥገኛ ነች ፤ በመንፈቀ ሌሊት ከእንቅልፍ በመቀስቀስ ስታለቅ ምላሽሽ እንዴት ነበር? ሲል ይጠይቃል፡፡ እናት ከልጅዋ የምታተርፈው ነገር ሳይኖር ምቾቷን ሁሉ የምትቀማበት ጊዜ አለ ፡፡ እናት ቀኑን ሙሉ ስትሰራ ትቆያለች፣ በነጋታው ረዥም ሥራ ይጠብቃታል፡፡ ሌሊቱን በሙሉ ልጇን ስትንከባከብ የምታሳልፍበት ወቅት ያለውን ድካም መገመት አያዳግትም፡፡ መጋቢው በእምሮአዊው አመክንዮ የማትጠቅመውን እና ረባሿን ልጅ አውጥቶ መጣል መፍትሄ እንደኾነ ተናገረ፡፡

ሴቲቱም በመጀመሪያ በመጋቢው ምላሽ ግራ ተጋብታ ሳለ ፣ መጋቢው ልጇን የተንከባከበችው በፍቅር አመክንዮ መንገድ አንጂ አምሮአዊው አንዳልኾነ ገለጸ፡፡ ፍቅር እናቲቱ ለምታለቅሰው ልጇ ምቾት ማንኛውም ዋጋ እንድትከፍል የሚያደርጋት ኃይል ነው ፤ ልጇ ፍጹም እስክትረካ ድረስ አትተዋትምና! እግዚአብሔር ስለ ፍቅሩ በኃጢት ስቅየት ያለውን ኃጢአተኛ የማይተወውም ለዚሁ ነው፡፡ 1ኛ ጢሞቴዎስ 2፥4 እግዚአብሔር “ሰዎች ሁሉ ሊድኑና እውነቱን ወደማወቅ ሊደርሱ በሚወድ በእግዚአብሔር” ሲል ይገልጸዋል፡፡

የእግዚአብሔር ፍቅር አመክንዮ በመስቀል ላይ መገለጹን አንዳንዶች ቢረዱትም፣ ሌሎች ግን ያለ በቂ ማስረጃ ሲገፉት ይስተዋላል፡፡ “የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉት ሞኝነት ለእኛ ለምንድን ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነውና.....መቼም አይሁድ ምልክትን ይለምናሉ፣ የግሪክ ሰዎችም ጥበብን ይሻሉ ፣ እኛ ግን የተሰቀለውን ክርስቶስን አንሰብካለን ፤ ይህም ለአይሁድ ማሰናከያ ለአሕዛብም ሞኝነት ነው፤ ለተጠሩት ግን አይሁድ ቢሆኑ የግሪክ ሰዎችም ቢሆኑ የእግዚአብሔር ኃይልና የእግዚአብሔር ጥበብ የሆነው ክርስቶስ ነው” (2ኛ ቆሮንቶስ 1፥18፣22-24)፡፡

ቤተሰቦቻችን በአእምሮአዊው ሳይኾን በፍቅር አመክንዮ እኛን በመውደዳቸው ዕድለኞች አይደለንምን? የፍቅርን አመክንዮ ተቀብለን ወደ ልጆቻን እንደምናስተላልፈው ሁሉ፣ መስቀሉ የእግዚአብሔርን ፍቅር አመክንዮ በዙሪያችን ላሉ ሰዎች ሁሉ የምናስተላልፍበት አቅም ሰጪያችን ነው፡፡

*1ኛ ዮሐንስ 3፥16-18*

*እርሱ ስለ እኛ ነፍሱን አሳልፎ ሰጥቶአልና ፤ በዚህ ፍቅርን አውቀናል፣ እኛም ስለ ወንድሞቻችን ነፍሳችንን አሳልፈን እንድንሰጥ ይገባል። ነገር ግን የዚህ ዓለም ገንዘብ ያለው ፣ ወንድሙም የሚያስፈልገው ሲያጣ አይቶ ያልራራለት ማንም ቢሆን ፣የእግዚአብሔር ፍቅር በእርሱ እንዴት ይኖራል? ልጆቼ ሆይ በሥራና በእውነት እንጂ በቃልና በአንደበት አንዋደድ።*

*1ኛ ዮሐንስ 4፡7-12*

*ወዳጆች ሆይ ፍቅር ከእግዚአብሔር ስለ ሆነ የሚወደውም ሁሉ ከእግዚአብሔር ስለ ተወለደ እግዚአብሔርንም ስለ ሚያውቅ እርስ በእርሳችን እንዋደድ። ፍቅር የሌለው እግዚአብሔርን አያውቅም፣ እግዚአብሔር ፍቅር ነውና። በዚህ የእግዚአብሔር ፍቅር በእኛ ዘንድ ተገለጠ ፣ በእርሱ በኩል በሕይወት እንኖር ዘንድ እግዚአብሔር አንድ ልጁን ወደ ዓለም ልኮታልና። ፍቅርም እንደዚህ ነው ፣ እግዚአብሔር እርሱ ራሱ እንደ ወደደን ስለ ኃጢአታችንም ማስተሰሪያ ይሆን ዘንድ ልጁን አንደ ላከ እንጂ እኛ እግዚአብሔርን እንደ ወደድነው አይደለም። ወዳጆች ሆይ እግዚአብሔር እንዲህ አድርጎ ከወደደን እኛ ደግሞ እርስ በእርሳችን ልንዋደድ ይገባናል። እግዚአብሔርን ማንም ከቶ አላየውም ፤ እርስ በእርሳችን ብንዋደድ እግዚአብሔር በእኛ ይኖራል፣ፍቅሩም በእኛ ፍጹም ሆኖአል።*

*1ኛ ዮሐንስ 4፡19-21*

*እርሱ አስቀድሞ ወዶናልና እኛ እንወደዋለን ።ማንም ፦እግዚአብሔርን እወዳለሁ እያለ ወንድሙን ቢጠላ ሐሰተኛ ነው፤ ያየውን ወንድሙን የማይወድ ያላየውን እግዚአብሔርን ሊወደው እንዴት ይችላል? እግዚአብሔርንም የሚወድ ወንድሙን ደግሞ እንዲወድ ይህች ትእዛዝ ከእርሱ አለችን።*

ዮሐንስ 3፥16 የወንጌል አጠቃላይ መልእክት ነው ። "በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና::" ከትእዛዛቱ ሁሉ ፊተኛይቱ ትእዛዝ ማናችይቱ ናት? ተብሎ ኢየሱስ በተጠየቀ ጊዜ እንዲህ ሲል መልሷል፦ "ከትእዛዛቱ ሁሉ ፊተኛይቱ ፦እስራኤል ሆይ ስማ ጌታ አምላካችን አንድ ጌታ ነው፤ አንተም በፍጹም ልብህ ፣ በፍጹምም ነፍስህ ፣ በፍጹምም አሳብህ ፣ በፍጹምም ኃይልህ ጌታ አምላክህን ውደድ የምትል ናት። ፊተኛይቱ ትእዛዝ ይህች ናት። ሁለተኛይቱም ፦ ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ የምትል እርስዋን የምትመስል ይህች ናት። ከእነዚህ የምትበልጥ ሌላ ትእዛዝ የለችም" (ማርቆስ 12፥29-31)።

## VI. መስቀል ፍቅርን ያስተምረናል

### 1.መስቀል ቤተሰባችንን ስለመውደድ ያስተምራል

መጽሐፍ ቅዱስ ወደ ክርስቶስ ፍቅር በማመልከት ቤተክርስቲያን የእውነተኛ ቤተሰብ ፍቅር ምሳሌ መሆኗን ይናገራል፡-“ ባሎች ሆይ ክርስቶስ ደግሞ ቤተክርስቲያንን እንደ ወደዳት ሚስቶቻችሁን ውደዱ ፤ በውኃ መታጠብ እና ከቃሉ ጋር አጽንኦት እንዲቀድሳት ስለ እርስዋ ራሱን አሳልፎ ሰጠ፤ እድፈት ወይም የፊት መጨማደድ ወይም እንዲህ ያለ ነገር ሳይሆንባት ቅድስትና ያለ ነውር ትሆን ዘንድ ክብርት የሆነችን ቤተክርስቲያን ለራሱ እንዲያቀርብ ፈለገ። እንዲሁም ባሎች ደግሞ እንደ ገዛ ሥጋቸው አድርገው የገዛ ሚስቶቻቸውን ሊወዱአቸው ይገባቸዋል። የገዛ ሚስቱን የሚወድ ራሱን ይወዳል፤ ማንም የገዛ ሥጋውን የሚጠላ ከቶ የለምና ፣ ነገር ግን የአካሉ ብልቶች ስለ ሆንን፣ ክርስቶስ ደግሞ ለቤተክርስቲያን እንዳደረገላት ይመግበዋል፣ ይከባከበውማል። ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል ፤ ከሚስቱም ጋር ይተባበራል፤ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ። ይህ ሚስጥር ታላቅ ነው፤ እኔ ግን ይህን ስለ ክርስቶስና ስለ ቤተክርስቲያን እላለሁ። ሆኖም ከእናንተ ደግሞ እያንዳንዱ የገዛ ሚስቱን እንዲህ እንደ ራሱ አድርጎ ይውደዳት ፣ሚስቱም ባልዋን ትፍራ ( ኤፌሶን 5፥25-32)።

### 2.መስቀል ጠላቶቻችንን ስለመውደድ ያስተምራል

“ነገር ግን ገና ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቶአልና” (ሮሜ 5፥8)። ታላቁ ምስሌአችን ጠላትን ስለ መውደድ እንዲህ ይላል ፡-“ ባልንጀራህን ውደድ ጠላትህንም ጥላ እንደተባለ ሰምታችኃል ። እኔ ግን እላችኃለሁ በሰማያት ላላ አባታችሁ ልጆች ትሆኑ ዘንድ ጠላቶቻችሁን ውደዱ የሚረግሙአችሁንም መርቁ ፣ ለሚከተሉአችሁም መልካም አድርጉ ፣ ስለሚያሳድዱአችሁም ጸልዩ፣ እርሱ በክፎዎች እና በበጎዎች ላይ ፀሐይን ያወጣልና ፣ በጻድቃን እና በኃጢአተኞችም ላይ ዝናቡን ያዘንባልና። የሚወዱአችሁን ብትወዱ ምን ዋጋ አላችሁ? ቀራጮችስ ያንኑ ያደርጉ የለምን ? ወንድሞቻችሁንም ብቻ እጅ ብትነሡ ምን ብልጫ ታደርጋላችሁ ? አሕዛብስ ያንኑ ያደርጉ የለምን ? እንግዲህ የሰማዩ አባታችሁ ፍጹም እንደሆነ እናንተ ፍጹማን ሁኑ” (ማቴዎስ 5፥43-48)።

ሐዋሪያው ጳውሎስም አክሎ ይናገራል፡- “ተወዳጆች ሆይ ራሳችሁ አትበቀሉ ፣ ለቁጣው ፈንታ ስጡ እንጂ ፤ በቀል የእኔ ነው፣እኔ ብድራቱን እመልሳለሁ ይላል ጌታ ተብሎ ተጽፏልና።

ጠላተህ ግን ቢራብ አብላው ቢጠማ አጠጣው ፤ይህን በማድረግህ በራሱ ላይ የእሳት ፍም ትከምራለህና። ክፉውን በመልካም አሸንፍ እንጂ በክፉ አትሸነፍ (ሮሜ 12፥19-21)።

በመስቀል ላይ የፍቅር አመክንዮ መመልከትም መዳሰስም እንችላለን። እግዚአብሔር ስለ ወደደን ነው ማፍቀርን የተማርነው። የኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅር ታሪክ ብቻ አይደለም፤ ህይወት ለዋጭ እውነት አንጂ! እመነታችሁን በኢየሱስ የመስቀል ስራ ላይ ስታደርጉ ፣ የማዳኑን ኃይል መለማመድ ትጀምራላችሁ፤ በታላቁ መስዋዕቱ ውስጥ ኃይል አለና!

የግል ማስታወሻ

# 14

## ክርስቲያኑ በቅዱስ ሥላሴ ለምን ያምናሉ

አንድ አምላክ ሦስት አካላት (ሥላሴ) አስተምህሮ ሙግት ምንም እንኳ በአንዳንዶች ዘንድ አስቸጋሪ ቢመስልም ፣ ማንኛውም ክርስቲያን በዕለታዊ የጸሎት ህይወት ልምምዱ ሊረዳው እንደሚችል ልዊስ ይናገራል ፡-

ክርስቲያን ለጸሎት በሚንበረከክበት ጊዜ ከእግዚአብሔር ጋር ይገናኛል፡፡ እንዲጸልይ የሚያደርገው በውስጡ የሚናገረውም ራሱ እግዚአብሔር እንደሆነ ጭምር ያውቃል፡፡ ስለ እግዚአብሔር ያለው እውነተኛ እውቀት ሰው በኾነው ክርስቶስ በኩል ይገለጣል፡፡ ኢየሱስ በአጠገቡ እንዳለና እንደሚረዳው ያውቃል፤ በውስጡ እንዲጸለይ የሚያነሳሳው ኃይል ራሱ እግዚአብሔር ነው፡፡ [71]

ክርስትና በሥላሴ አስተምህሮው እጹብ ነው፡፡ ጥንታዊያኑ ግብጻዊያን በሥሉስ ጣዖታት ማለትም ዖስሪስ (አባት)፣ አይሲስ (እናት) እና ሆረስ (ልጅ) ያምኑ ነበር፡፡ ዖስሪስ እና አይሲስ ልጅን እንደወለዱ ቤተሰብ አካላት እንጂ እንደ አንድ መለኮት አልተቆጠሩም፡፡ ሒንዱ፣ ብራማ፣ ቬሹ እና ሺቫ ሀይማኖቶች በክብ ምስል የሚገለጹ ሥሉስ ማንነቶች ቢኖሩትም "ሶስቱ በአንድ" የሚገለጹ አይደሉም፡፡ መለኮታዊ ሥሉስ በሌሎች ሀይማኖቶች የእውነተኛው አምላክ ጥላ ተደርገው ይወሰዳሉ፤ እውነተኛ መገለጡን የሚነግረን ክርስትና ብቻ ነው፡፡

### I. ሥላሴ በብሉይ ኪዳን

በአዲስ ኪዳን የምናገኘው ግልጽ የሥለሴ አስተምህሮ በብሉይ ኪዳን እምብዛም ቢሆንም እንኳ የሚከተሉት ምሳሌዎች የሚያሰምሩት እውነት አለ፡-

- ***የእግዚአብሔር ስም***፡- በዕብራይስጥ የእግዚአብሔር ስም (ኤሎሂም) በብዙ ቁጥር ነው የተገለጸው፡፡ አንዳንዶች በብዙ ቁጥር መጠቀሱ አክብሮትን ለመግለጽ ነው የሚል ሙግት ይቀርባሉ፤ የዕብራይስጥ ቋንቋ ህግ ግን ይህን አይደግፍም፡፡ እግዚአብሔር ብዙ ጊዜ በነጥላ ቁጥር ቢናገርም፣ አንድነቱ ከነጠላ በላይ መኾኑን ለማመላከት ብዙ ቁጥርን ጭምር ይጠቀማል፡፡ እግዚአብሔርም አለ፡- " ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌያችን

[71] ሲ. ኤስ ሊዊስ ፣ ክርስትና ፣ (ግላሰጎው ፡- ፎንታና መጽሐፍ ፣1975)፣ ገጽ፣137፡፡

እንፍጠር፣ የባሕር ዓሦችንና የሰማይ ወፎችን እንስሳትንና ምድርን ሁሉ በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ይግዙ” ( ዘፍጥረት1፥26)።

- ***ባቢሎን፦*** በዓለም ጥበብ የተሞሉ ሰዎች እርስ በእርሳቸው “ ኑ ጡብ እንሥራ ፣ በእሳትም እንተኩሰው ተባባሉ … ጡቡም እንደ ድንጋይ ሆነላቸው፤ የምድር ዝፈት እንደ ጭቃ ሆነላቸው።” እግዚአብሔርም አለ፦“ ኑ እንውረድ አንዱ የአንዱን ነገር እንዳይሰማው ቋንቋቸውን በዚያ እንደባልቀው” ( ዘፍጥረት 11፥3፣6)።
- ***ጥበብ*** ፦ ብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔርን ገዢነትና እውቀት “በጥበብ” ይመስለዋል፦ “ እኔ ጥበብ በብልሃት ተቀምጫለሁ ፣ እውቀትንም ጥንቃቄንም አግኝቻለሁ። እግዚአብሔርን መፍራት ክፋትን ይጠላል፤ ትዕቢትንና እበሪትን ክፉንም መንገድ ጠማማውንም አፍ እጠላለሁ። ምክርንና መልካም ጥበብ የእኔ ነው፤ ማስተዋል እኔ ነኝ ፣ብርታትም አለኝ። ነገሥታት በእኔ ይነግሣሉ፣ ሹማምንቶችም የቀናውን ነገር ይደነግጋሉ። አለቆች በእኔ ያዝዛሉ ፣ ክቡራንና የምድር ፈራጆችም ሁሉ። እኔ የሚወዱኝን እወድዳለሁ፣ተግተው የሚሹኝም ያገኙኛል። ብልጥግና ክብር በእኔ ዘንድ ነው፤ ብዙ ሀብትና ጽድቅም ። ፍሬዩም ከምዝምዝ ወርቅ ይሻላል። ቡቃያዩም ከተመረጠች ብር። እኔ በጽድቅ መንገድ እሄዳለሁ ፣በፍርድም ጎዳና መካካል፣ለሚወዱኝ ርስት አወርሳቸው ዘንድ ቤተመዛግብታቸውንም እሞላ ዘንድ። እግዚአብሔር የመንገዱ መጀመሪያ አደረገኝ፣ በቀድሞ ሥራው መጀመሪያ። ከጥንቱ ከዛላለም ጀምሮ ተሸምሁ፤ምድር ከመፈጠርዋ አስቀድሞ። ቀላያት ገና ሳይኖሩ እኔ ተወልድሁ፣የውኃ ምንጮች ገና ሳይፈልቁ። ተራሮች ገና ሳይመሠረቱ ፣ ከኮረብቶች በፊት እኔ ተወለድሁ፣ ምድሪቱም ሜዳውን ገና ሳይፈጥር ፣የመጀመሪያውንም የዓለም አፈር። ሰማዩችን በዘረጋ ጊዜ አብሬ ነበርሁ፣ በቀላያት ፊት ክበብን በደነገገ ጊዜ ፣ደመናትን በላይ ባዘጋጀ ጊዜ ፣የቀላይን ምንጮች ባጸና ጊዜ ፣ ለባሕርም ዳርቻን በወሰነ ጊዜ ውኃ ከትእዛዙ እንዳያልፍ ፣ የምድርን መሠረት በመሠረተ ጊዜ ፣ የዚያን ጊዜ እኔ በእርሱ ዘንድ ዋና ሠራተኛ ነበርሁ ፤ ዕለት ዕለት ደስ አሰኘው ነበርሁ፣ ደስታዩም በምድሩ ተድላዩም በሰው ልጆች ነበረ (ምሳሌ 8፥12-31)።
- ***የእግዚአብሔር መንፈስ፦*** ብሉይ ኪዳን መንፈስ ቅዱስ የበረከት፣ የጥንካሬ፣ የተስፋ ፣ ባህል እና መልካም አገዛዝ ምንጭ መሆኑን ይናገራል። እግዚአብሔር ከይሁዳ ነገድ የሚሆን የሆር የልጅ ልጅ ፣ የኡሪ ልጅ ባስልኤልን አስመልክቶ “ በሥራ ሁሉ በብልሃትም ፣ ጥበብም ፣ ማስተዋልም፣ በእውቀትም የእግዚአብሔር መንፈስ ሞላሁበት” ብሎ ሲናገር እንመለከታለን (ዘጸአት 31፡3)። መንፈስ ቅዱስ በዚህ ጊዜ በሌላ መንገድ መገለጹንም

ዘኀልቁ 11፥24፣25 ያመላክታል፡- " ሙሴም ወጣ የእግዚአብሔርም ቃሎች ለሕዝቡ ነገረ፤ ከሕዝቡ ሽማግሌዎችም ሰባውን ሰዎች ሰብስቦ በድንኳኑ ዙሪያ አቆማቸው ። እግዚአብሔር በደመናው ወረደ፣ ተናገረውም ፣ በእርሱም ላይ ከነበረው መንፈስ ወስዶ በሳባው ሽማግሌዎች ላይ አደረገ ። መንፈሱንም በላያቸው ባደረ ጊዜ ትንቢቱ ተናገሩ፣ ከዚያ በኃላ ግን አልተናገሩም" (ዘኀልቁ 11፥24-25)።

- *ኢሳያስ* ፡- ነብዩ ኢሳያስ የእግዚአብሔርን ድምጽ በሚሰማበት ወቅት " ማንን እልካለሁ? ማንስ ይሄድልናል? ሲል ሰማሁ። እኔም እነሆኝ እኔን ላከኝ" በማለት ተናግሯል። ስለ ኢየሱስ አስቀድሞ በተመለከተው ትንቢት "ወደ እኔ ቅረቡ ፣ ይህንም ስሙ እኔ ከጥንት ጀምሬ በስውር አልተናገርሁም ፣ ከሆነበት ዘመን ጀምሮ እኔ በዚያ ነበረሁ፣አሁንም ጌታ እግዚአብሔርና መንፈሱ ልከውኛል" (ኢሳያስ 48፥16)።

## II. ሥላሴ በአዲስ ኪዳን

ሥላሴን በተመለከተ ብሉይ ኪዳን በብዙ ቁጥር መግለጽ ቢሞክርም፣ በዝርዝር ተቀምጦ የምናገኘው ግን በአዲስ ኪዳን ውስጥ ነው።

በመጀመሪያ መንፈስ ቅዱስ ከባህሪይ ይልቅ በማንነቱ ተገልጿል። መጥምቁ ዮሐንስ "እኔስ ለንስሐ በውኃ አጠምቃችኃለሁ ፣ ጫማውን እሸከም ዘንድ የማይገባኝ ከእኔ በኃላ የሚመጣው ግን ከእኔ ይልቅ ይበረታል፣ እርሱ በመንፈስ ቅዱስ በእሳትም ያጠምቃችኃል" (ማቴዎስ 3፥11)።

ቀዳሚው የእግዚአብሔር ሥሉስነት የተገለጠው በኢየሱስ ጥምቀት ወቅት ነው። "ኢየሱስም ከተጠመቀ በኃላ ወዲያው ከውኃ ወጣ ፤ እነሆም ሰማያት ተከፈቱ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንደ ርግብ ሲወርድ በእርሱ ላይም ሲመጣ አየ፤ እነሆም ድምጽ ከሰማያት መጥቶ ። በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው አለ" (ማቴዎስ 3፥16-17)።

አዲስ ኪዳን አብ፣ ወልድ  እና መንፈስ ቅዱስ ሰውን በማዳን ስራ ላይ የተለያየ ሚና እንዳላቸው በግልጽ  ያስተምራል። እግዚአብሔር አብ የድነት ዕቅድ ነደፈ፣ እግዚአብሔር ወልድ ድነትን ፈጸመ፣ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ድነትን በሰው ህይወት ውስጥ እውን አደረገ። የሚከተሉት ምንባባት ክፍሎች ይህ በግልጽ ያስቀምጣሉ፡-

*ኤፌሶን 1፥3-14*

*በክርስቶስ በሰማያዊ ስፍራ በመንፈሳዊ በረከቶች ሁሉ የባረከን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ።*

**አብ**

*ዓላም ሳይፈጠር በፊቱ ቅዱሳንና ነውር የሌለን በፍቅር እንሆን ዘንድ በነክርስቶስ መረጠን ። በበጎ ፈቃዱ እንደ ወደደ ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ እንሆን ዘንድ በክርስቶስ መረጠን። በበጎ ፈቃዱ እንደወደደ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ ለእነርሱ ልጆች ልንሆን አስቀድሞ ወሰነን። በውድ ልጁም እንዲያው የሰጠን የጸጋው ክብር ይመሰገን ዘንድ ይህን አደረገ።*

***ወልድ***

*በውድ ልጁም እንደ ጸጋው ባለጠግነት መተን ፣ በደሙ የተደረገ ቤዛነታችን አገኘን እርሱም የበደላችን ስርየት። ጸጋውንም በጥበብና በአእምሮ ሁሉ አበዛልን ። በክርስቶስ ለማድረግ እንደወደደ እንደ አሳበ የፈቃዱን ምሥጢር አስታውቆናልና፣ በዘመን ፍጻሜ ይደረግ ዘንድ ያለው አሳቡም በሰማየና በምድር ያለውን ሁሉ በክርስቶስ ለመጠቅለል ነው። እንደ ፍቃዱ ምክር ሁሉን የሚሠራ እንደእርሱ አሳብ ፣አስቀድመን የተወሰንንነ በክርስቶስ ደግሞ ርስትን ተቀበልን። ይኸውም በክርስቶስ አስቀድመን ተስፋ ያድርገን እኛ ለክብሩ ምስጋና እንሆን ዘንድ ነው።*

**መንፈስ ቅዱስ**

*እርሱም የርስታችን መያዣ ነው፤ ለእግዚአብሔር ያለውን ሁሉ እስኪ ዋጅ ድረስ ፣ ይህም ለክብሩ ምስጋና ይሆናል።*

## III. የሥላሴ አስተምህሮ ታሪክ

**ሥ**ላሴ የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ አይገኝም፤ ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እግዚአብሔር የሚያስተምረውን አጠቃላይ እውነት ይገልጻል። ቃሉ በሁለተኛው ክፍለ ዘመን በተርቱሊያን የተገኘ ሲሆን ሥላሴን ለማብራራት ተጠቅሞበታል፦ “ በአንድ አምላክ እናምናለን፤ አንዱ አምላክ ከእርሱ ዘንድ የሰረጸ ቃሉ የኾነ ልጅ አለው፤ አንዱ ልጅ (ወልድ) እንደ ተስፋው ቃል ጰራቂሊጦስ መንፈስ ቅዱስን ከአብ ዘንድ ልኳል።” ተርቱሊያን መለኮታዊ አንድነትን “ በሥላሴ ፦ አብ፣ ወልድ ፣ መንፈስ ቅዱስ ሦስትነት” አስረድቷል።[72]

---

[72] አር. ቲ፣ ነገረ-መለኮትን መረዳት (ለንደን ፦ የክርስትና ትኩረት ፣ ፣1999)፣ቅጽ፣29።

ከጥንታዊ የእምነት መግለጫዎች ቀዳሚው የሐዋሪያት እምነት መግለጫ ነው ፡- " ሁሉን በሚችል እግዚአብሔር አብ፤ በአንድ ልጁ በመንፈስ ቅዱስ ከድንግል ማርያም በተወለደ …….በመንፈስ ቅዱስ አምናለሁ።"

መግለጫው በመላው ክርስቲያን አብያተክርስቲያናት ዘንድ ተቀባይነትን አላገኘም። የአሌክሳንደሪያው መነኩሴ ፣ አርዮስ (250-336 ዓ.ም) "ቃሉ" የእግዚአብሔር ትልቁ ፍጥረት ነው በማለት መግለጫውን ክዷል።

አሌክሳንደሪያዊው ብጽዕ አትናቴየስ (293-373 ዓ.ም) "ቃሉ" እና አብ አንድ ማንነት፣ ዕኩል ስልጣን እና ዘላለማዊነት እንዳላቸው፣ መንፈስ ቅዱስም ፍጹም መለኮታዊ መኾኑን በማስረገጥ የአርዮስን ኑፋቄ ረታ። በ325 አትናቲየስ የኒቂያን እምነት መግለጫ በማዘጋጀት የአርዮስ ኑፋቄ እንዲወገዝ በማድረግ ሥላሴ መሰረታዊ የቤተክርስቲያን አስተምህሮ እንዲሆን አደረገ፡-

> *" በእግዚአብሔር አብ ሁሉን በሚችል ሰማይና ምድር በፈጠረ አምናለሁ.....*
>
> *በአንዱ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ዓለም ሳይፈጠር በነበረ ፣ ከአምላክ በተገኘ አምላክ፣ ከብርሃን በተገኘ ብርሃን፣ ከአብ ጋር አንድ በሆነና ሁሉን በፈጠረ አምናለሁ … በመንፈስ ቅዱስ አምናለሁ…*

የኮንስታቲኖፕል ጉባኤ በ381 የመንፈስ ቅዱስን አስተምህሮ አስረግጧል። የአብያተክርስቲያናቱ ጉባኤ በሲባሊየስ ሥላሴን አስመልክቶ የተነሳውን ሌላኛውን ኑፋቄ ፡- አብ፣ ወልድ ፣ መንፈስ ቅዱስ የአንዱ መለኮት ሦስት መገለጫዎች ናቸው የሚለውን አውግዘዋል። የአብ ጊዜ ክርስቶስ ስጋ ለብሶ በመጣበት ጊዜ የተገባደደ ሲሆን፣ የመንፈስ ቅዱስ ጊዜ በጴንጤቆስጤ ቀን ጀምሯል። ቤተክርስቲያን የሥላሴ ሦስቱ አካላት ከዘላላም በፊት በራሳቸው የነበሩ እንደኾነ በማስረገጥ የሲባሊየስን ኑፋቄ ውድቅ አድርጋለች።

ከ323 — 381 ዓ.ም በነበረው ጉባኤ ቤተክርሰቲያን በአለም አቀፍ ደረጃ የሥሉስ አህዱ ፡- አብ ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ አስተምህሮን አጽድቃለች። ቤተክርስቲያን " አብ አምላክ ነው፤ ወልድ አምላክ ነው፤ መንፈስ ቅዱስ አምላክ ነው፤ ሦስት አማላክት የሉም ፣ አምላክ አንድ ነው። አብ ዘላለማዊ ነው፤ ወልድ ዘላለማዊ ነው፤ መንፈስ ቅዱስ ዘላላማዊ ነው ፣ ነገር ግን አንድ ዘላላማዊ አለ" የሚለውን (የአትናቲየስ ቃል በመጠቀም ) ታምናለች።

## IV. *የሥላሴ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አሰረጂዎች*

***የ**ሥላሴ አስተምህሮን አንድ መነኩሴ መምህር " ሦስት አንድ ፣ አንድ ሦስት እንዴት ሊኾን ይችላል?" ሲል ተሳለቀ። ከአድማጮች መካካል አንዱም " ሻማ እንዴት ነው የሚባረው?" ሲል መለሰ። "ሰም፣ ክር እና አየር የምናየውን ብርሃን ያስገኛሉ" መምህሩ መለሰ። አድማጩ እንደገና "እነዚህ ሦስት ቁሶች አንድ ብርሃን እንዴት እንደሚያስገኙ ታውቃለህን?" ሲል ጠየቀ፤ መምህሩም መለሰ " በፍጹም!" ታዲያ "ብርሃን ከየት እንደተገኘ ሳታውቅ በብርሃን እንዴት ልታምን ቻልክ?" አለ።*

*የእግዚአብሔርን (መለኮት) ባህሪይ በጥልቀት መንገዘብ አዳጋች ሊሆን ይችላል፤ ሥላሴን መረዳት አዳጋች ነው ማለት ግን የሥላሴን አስተምህሮ እውነታ ዘበት ሊያደርገው አይችልም። የአቶሚክ ንጥረ ቁሶችን፣ የሰው አእምሮ ስራ ብሎም የጊዜ ተፈጥሮ መረዳት አዳጋች ሆኖ ሳለ፣ በምድራዊ (አካላዊ) ኑሮአችን ግን አምነናቸው እና ተተግነንባቸው እየኖረን ነው። ወደ መንፈሳዊው አለም ስንመጣም እንዲሁ!*

*የሥላሴ አስተምህሮ በስድስት ነጥቦች ማጠቃለል ይቻላል፡-*

- *መጽሐፍ ቅዱስ አንድ አምላክ ሦስት አካላትን ያስተዋወቅናል።*
- *ሥለሴ አንድ እንጂ ሦስት አምላኮች አይደለም።*
- *እያንዳንዱ የሥላሴ አካል የራሳቸው ልዩ ስብዕና አላቸው።*
- *ሥላሴ እውነት እና ዘላለማዊ እንጂ ውስን ማንነት አይደለም።*
- *ሦስቱ አካላት፡- አብ፣ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ እኩል ናቸው።*
- *የሥላሴ አስተምህሮ ሁሉንም የክርስትና አስተምህሮ ለመረዳት ወሳኝ ነው ።*

### 1. *አምላክ አንድ ነው*

*አዲስ ኪዳን አምላክ አንድ ነው የሚለውን አስተምህሮ በግልጽ ያስቀምጣል፡-*

- ***ኢየሱስ** ፡- ኢየሱስ ከሁሉ ፊተኛይቱ ትዕዛዝ ምን እንደሆነች በተጠየቀ ጊዜ " እስራኤል ሆይ ስማ ፤ጌታ አምላካችን አንድ ጌታ ነው፤ አንተም በፍጹም ነፍስህ በፍጹምም አሳብህ በፍጹምም ኃይልህ ጌታ አምላክህን ውደድ የምትል ናት ። ፊተኛይቱ ትእዛዝ ይህች ናት። ሁለተኛይቱም ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ የምትል እርስዋን የምትመስል ይህች ናት። ከእነዚህ የምትበልጥ ሌላ ትእዛዝ የለችም" ብሏል (ማርቆስ 12፥29-31)። ከዕርገቱ በፊት ኢየሱስ "ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፣ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ*

እያስተማራችኃቸው ደቀመዛሙርት አድርጓቸው፣ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ" ብሎ አዟል ( ማቴዎስ 28፥19)፡፡

- ***ጳውሎስ ፦*** ሐዋሪያው ጳውሎስ " በእምነት የሚያጸድቅ አምላክ አንድ ስለሆነ የአሕዛብ ደግሞ አምላክ ነው"( ሮሜ 3፥30) እና " አንድ እግዚአብሔር አለና" (1ኛ ጢሞቴዎስ 2፥5) ሲል ይገልጻል፡፡ በክርስቲያናዊ ቡራኬው ይህንኑን ያተናክራል " የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ የእግዚአብሔርም ፍቅር የመንፈስ ቅዱስም ኅብረት ከሁላችሁ ጋር ይሁን፡፡ አሜን" (2ኛ ቆሮንቶስ 13፥14)፡፡
- ***ያዕቆብ፦*** ሐዋሪያው ጳውሎስ " እግዚአብሔር አንድ እንደ ሆነ አንተ ታምነለህ ፡፡ መልካም ታደርጋለህ ፤ አጋንንት ደግሞ ያምናሉ ይንቀጠቀጡማል" ይላል (ያዕቆብ 2፥19)፡፡
- ***ዮሐንስ ፦*** ሐዋሪያው ዮሐንስ " መንፈስም እውነት ነውና የሚመሰክረው መንፈስ ነው፡፡ ሚመሰክሩት መንፈሱና ውኃው ደሙም ሦስት ናቸውና፤ ሦስቱም በአንድ ይስማማሉ" ይላል(1ኛ ዮሐንስ 5፥7)፡፡

## 2. አብ አምላክ ነው

መጽሐፍ ቅዱስ የአምላክን አንድነት በማጽናት በሥላሴ ስላሉ አካላት ማንነት እና ሚና ያስረግጣል፡፡ ስለ አብ የሚገልጡ ነጥቦችን እንመልከት፡-

- ***አብ ምዕመናንን ይባርካል፦*** " በክርስቶስ በሰማያዊ ስፍራ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ የባረከን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ" (ኤፌሶን 1፥3)፡፡
- ***አብ አዲስ ልደትን ይሰጣል፦*** "ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን በመነሣቱ ለሕያው ተስፋና ለማይጠፋ፣ እድፈትም ለሌለበት፣ ለማያልፍ ርስት እንደ ምሕረቱ ብዛት የወለደን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ" (1ኛ ጴጥሮስ 1፥3)፡፡
- ***አብ በሁሉ ይኖራል፦*** "ከሁሉ በላይ የሚሆን በሁሉም የሚሠራ በሁሉም የሚኖር አንድ አምላክ የሁሉም አባት አለ" (ኤፌሶን 4፥6)፡፡
- ***አብ አምልኮ የተገባው ነው፦*** ኢየሱስ "በእውነት የሚሰግዱ ለአብ በመንፈስ እና በእውነት የሚሰግዱበት ጊዜ ይመጣል አሁንም ሆኖአል፤ አብ ሊሰግዱለት እንደ እነዚህ ያሉትን ይሻልና" (ዮሐንስ 4፥23) ይላል፡፡
- ***አብ ቅዱስ ነው ፦*** " ቅዱስ አባት ሆይ እነዚህን የሰጠኸኝን እንደ እኛ አንድ እንዲሆኑ በስምህ ጠብቃቸው" (ዮሐንስ 17፥ 11)፡፡

## 3. ኢየሱስ አምላክ ነው

መጽሐፍ ቅዱስ የኢየሱስን አምላክነት በግልጽ ያስቀምጣል፡-

- ***ኢየሱስ አምላክ ከእኛ ጋር ነው፡-*** "እነሆ ድንግል ትፀንሳለች፣ወንድ ልጅም ትወልዳለች፣ ስሙንም አማኑኤል (እግዚአብሔር ከእኛ ጋር) ብላ ትጠራዋለች" (ኢሳያስ 7፥14)፡፡
- ***ኢየሱስ ኃያል አምላክ ነው፡-*** "ህጻን ተወልዶልናልና፣ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና፤ አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል፤ ስሙም ድንቅ መካር ፣ ኃያል አምላክ፣ የዘላለም አባት ፣ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል" (ኢሳያስ 9፥6)፡፡
- ***ኢየሱስ ዘላለማዊ ነው ፡-*** " አንቺም ቤተልሔም ኤፍራታ ሆይ ፣ አንቺ በይሁዳ አእላፋት መካካል ትሆኚ ዘንድ ታናሽ ነሽ ፤ ከአንቺ ግን አወጣጡ ከቀድሞ ጀምሮ ከዘላለም የሆነ ፣ በእስራኤልም ላይ ገዥ የሚሆን ይወጣልኛል" (ሚኪያስ 5፡2)፡፡
- ***ኢየሱስ ለዘላለም ይገዛል፡-*** የዕብራውያን ጸሐፊ መዝሙር 45፥6ን በመጥቀስ ስለ ኢየሱስ የሚከተለውን ያስረግጣል ፡- " ስለ ልጁ ግን አምላክ ሆይ ዙፋንህ እስከ ዘላለም ድረስ ይኖራል፤ የመንግስትህ በትር የቅንነት በትር ነው" ይላል (ዕብራውያን 1፥8)፡፡
- ***ኢየሱስ የመለኮት ሙላት ነው፡-*** "በእርሱ የመለኮት ሙላት ሁሉ በሰውነቱ ተገልጦ ይኖራልና" (ቆስይስ 2፥9)፡፡
- ***ኢየሱስ አልፋ እና ኦሜጋ ነው ፡-*** ኢየሱስ ስለራሱ "ያለውና የነበረው የሚመጣውም ሁሉንም የሚገዛ ጌታ አምላክ ፡፡ አልፋና ዖሜጋ እኔ ነኝ" ይላል (ራዕይ 1፥8)፡፡
- ***ኢየሲስ ጌታ ነው ፡-*** " የሁሉ ጌታ በሚሆን በኢየሱስ ክርስቶስ ሰላምን እየሰበከ ይህን ቃል ወደ እስራኤል ልጆች ላከ" (የሐዋሪያት ሥራ 10፥36)፡፡
- ***ኢየሱስ በሁሉ ይኖራል ፡-*** "ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በሚሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው እሆናለሁና" (ማቴዎስ 28፥20)፣ " እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁል ጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ" (ማቴዎስ 28፥ 20)፡፡
- **ኢየሱስ አምልኮ የተገባው ነው፡-** "ይህም በሰማይና በምድር ከምድርም በታች ያሉት ሁሉ በኢየሱስ ስም ይንበረከኩ ዘንድ፣ ምላስም ሁሉ ለእግዚአብሔር አብ ክብር ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደሆነ ይመሰክር ዘንድ ነው" (ፊልጵስዩስ 2፥10-11)፡፡

- **ኢየሱስ ቅዱስ ነው ፦** "መልአኩም መልሶ እንዲህ አላት ፤ መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል ፣ የልዑልም ኃይል ይጸልልሻል፤ ስለዚህ ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል" (ሉቃስ 1፥35)።
- **ኢየሱስ ጌታ እና አምላክ ነው፦** ኢየሱስ የቶማስን አምልኮ ተቀብሏል "ጌታዬ አምላኬም ብሎ መለሰለት" ( ዮሐንስ 20፥28)።

4. **መንፈስ ቅዱስ አምላክ ነው**

መጽሐፍ ቅዱስ የመንፈስ ቅዱስ መለኮትነትን ያጸናል፦

- ***መንፈስ ቅዱስ በእግዚአብሔር ህዝቦች ላይ ይኖራል*** ፦ በክርስቶስ የአማኞች ሰውነት በየትኛውም ዘመን የመንፈስ ቅዱስ መኖሪያ ነው። በአማኞች ሕይወት ሁልጊዜ ይኖራል ። "ሥጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት በእናንተ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደሆነ አታውቁምን ...ለራሳችሁ አይደላችሁም " (1ኛ ቆሮንቶስ 6፥19)።
- ***መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ነው፦*** በመንፈስ ቅዱስ ላይ ማመጽ (ኃጢአትን መፈጸም) በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት መፈጸም ነው ። ጳውሎስ ሐናንያን የተናገረበት እውነታ ይህን ያረገግጣል "መንፈስ ቅዱስን ታታልልና ከመሬቱ ሽያጭ ታስቀር ዘንድ ሰይጣን በልብህ ስለ ምን ሞላ? ሳትሸጠው የአንተ አልነበርምን? ይህን ነገር ስለምን በልብህ አሰብህ? እግዚአብሔርን እንጂ ሰውን አልዋሸህም አለው" (ሐዋሪያት ሥራ 5፥3፣4)።
- ***መንፈስ ቅዱስ በነብያት ተናግሯል*** ፦ ጳውሎስ ስለ ልብ ደንዳናነት በሚናገረው ክፍል ይህን ያስረግጣል "መንፈስ ቅዱስ በነብዩ ኢሳያስ ለአባቶቻችን ወደዚህ ሕዝብ ሂዱና መስማትን ትሰማላችሁና አታስተውሉም ፣ ማየትንም ታያለችሁና አትመለከቱም" (ሐዋሪያት ሥራ 28፥25፣26)።
- **መንፈስ ቅዱስ ዘላለማዊ ነው ፦** " ነውር የሌለው ሆኖ በዘላላም መንፈስ ራሱን ለእግዚአብሔር ያቀረበ የክርስቶስ ደም እንዴት ይልቅ ሕያዋን እግዚአብሔርን ልታመልኩ ከሞተ ሥራ ሕያውን እግዚአብሔርን ልታመልኩ ከሞተ ሥራ ሕሊናችሁን ያነጻ ይሆን? (ዕብራውያን 9፥14)።
- **መንፈስ ቅዱስ ሁሉን ያውቃል ፦** " ነገር ግን ዓይን ያላየችው ጆሮም ያልሰማው በሰውም ልብ ያልታሰበው እግዚአብሔር ለሚወዱት ያዘጋጀው ተብሎ እንደ ተጻፈ እንዲህ እንናገራልን። መንፈስም የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር ስንኳ ሳይቀር ሁሉን

ይመረምራልና ለእኛ እግዚአብሔር በመንፈሱ በኩል ገለጠው። በእርሱ ውስጥ ካለው መንፈስ በቀር ለሰው ያለውን የሚያውቅ ሰው ማነው ፣እንዲሁም ደግሞ ከእግዚአብሔር መንፈስ በቀር ለእግዚአብሔር ያለውን ማንም አያውቅም" (2ኛ ቆሮንቶስ 2፥9-11)

- ***መንፈስ ቅዱስ ጌታ ነው*** ፦ *" ጌታ ግን መንፈስ ነው ፣ የጌታም መንፈስ ባለበት በዚያ አርነት አለ"* ( 2ኛ ቆሮንቶስ 3፥17)።
- ***መንፈስ ቅዱስ በሁሉ ይኖራል*** ፦ *መዝሙረኛው ለእግዚአብሔር ሲናገር* " ከመንፈስህ ወዴት እሄዳለሁ? ከፊትህስ ወዴት እሸሻለሁ? ወደ ሰማይ ብወጣ ፣ አንተ በዚያ አለህ። ወደ ሲኦልም ብወርድ ፣ በዚያ አለህ። እንደ ንስር የንጋትን ክንፍ ብወስድ እስከ ባሕር መጨረሻም ብበርር፣ በዚያ እጅህ ትመራኛለች ብል ቀኝህም ትይዘኛለች" ( *መዝሙር* 139፥7-10)።

## V. የሥላሴ አካላት ግንኙነት

**መ**ጽሐፍ ቅዱስ የአምላክን አንድነት አበክሮ ይናገራል፦ "እስራኤል ሆይ ስማ አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው" (ዘዳግም 6፥4)። "እግዚአብሔር ጌታዬን ጠላቶች ለእግር መቀመጫ እስካ ደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ አለው" (*መዝሙር* 110፥1)። ምሳሌ 30፥ 4 " ወደ ሰማይ የወጣ የወረደስ ማን ነው?..... ስሙ ማን የልጁስ ስም ማን ነው? (ምሳሌ 30፥ 4)።

ከጥንት ጀምሮ ስለ አምላክ አንድነት ያለው መረዳት ሙስሊማኑ አላህን እንደሚያምኑት አይነት አይደለም። አምላክ አብ፣ ወለድ እና መንፈስ ቅዱስ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የሥላሴ አካላት ያላቸውን ግንኙነት እንደሚከተለው ያቀርባል፦

- ***የሥላሴ አካላት ይከባበራሉ*** ፦ አብ ወልድን ያከብራል ( ማቴዎስ 3፥17፣17፥5፣ዮሐንስ 5፥20-23)፣ ወልድ አብን ያከብራል ( ዮሐንስ 5፥19፣30፣31፣ 12፥ 28)። ***መንፈስ ቅዱስ*** ወልድን ያከብራል ( ዮሐንስ 15፥26፣ 16፥8-10፣14)።
- ***የሥላሴ አካላት ይማልዳሉ፦*** ጳውሎስ እንደሚናገር *"መንፈስ ድካማችንን ያግዛል፤እንዴት እንድንጸልይ እንደሚገባን አናውቅምና፣ ነገር ግን መንፈስ ራሱ በማይነገር መቃተት ይማልድልናል ፣ ልብንም የሚመረምረው የመንፈስ አሳብ ምን እንደሆነ ያውቃል፣ እንደ እግዚአብሔር ፍቃድ ስለ ቅዱሳን ይማልዳልና"*

( ሮሜ 8፥26፣27)።ኢየሱስም ይማልዳል ፦ “ እግዚአብሔር የመረጣቸውን ማን ይከሳቸዋል? የሚያጸድቅ እግዚአብሔር ነው፣ የሚኮንንስ ማን ነው? የሞተው ይልቁንም ከሙታን የተነሣው በእግዚአብሔር ቀኝ ያለው ደግሞ ስለ እኛ የሚማልደው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው”(ሮሜ 8፡33፣34)። “ስለ እነርሱም ሊያማልድ ዘወትር በሕይወት ይኖራልና ስለዚህ ደግሞ በእርሱ ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል” (ዕብራውያን 7፥25)።

- ***የሥላሴ አካላት ዘላለማዊ ፍቅር አላቸው ፦*** “ አባት ሆይ ዓለም ሳይፈጠር ስለ ወደድኸኝ የሰጠኸን ክብሬን እንዲያዩ እኔ ባለሁበት የሰጠኸኝ እነርሱ ደግሞ ከእኔ ጋር ይሆኑ ዘንድ እወዳለሁ” (ዮሐንስ 17፥24)።
- ***የሥላሴ አካላት የጋራ አክብሮት አላቸው ፦*** “ አሁንም አባት ሆይ ዓለም ሳይፈጠር በአንተ ዘንድ በነበረኝ ክብር አንተ በራስህ ዘንድ አክብረኝ” (ዮሐንስ 17፥ 5)።
- ***የሥላሴ አካላት ዕውቀት እና ምክር ይከፋፈላሉ፦*** “ እምነት እንዲሆንላቸው በዘለላም ሕይወት ተሰፋ እንደ አምልኮት ያለውን እውነት እንዲያውቁ የተላከ ፤ ስለዚህም ሕይወት የማይዋሽ እግዚአብሔር ከዘላለም ዘመናት በፊት ተስፋ ሰጠ” (ቲቶ 1፥2)። በሮሜ መጽሐፍ መጨረሻ ቡራኬውን ጳውሎስ ሲያስቀምጥ “ እንግዲህ እንደ ወንጌሌ ስለ ኢየሱስ ክርስቶሰም እንደተሰበከ ፣ ከዘላለም ዘመንም የተሰወረው አሁን ግን የታየው ..” (ሮሜ 16፥25)።
- ***የሥላሴ አካላት ፍቅርን ይካፈላሉ ፦*** “በክርስቶስ ለማድረግ እንደ ወደደ እንደ አሳቡ የፍቃዱን ሚስጢር አስታውቆናልና” (ኤፌሶን 1፥9)።

**የግል ማስታወሻ**

15

# ሥላሴን ለሙስሊማኑ ማሳወቅ

በመጨረሻ ሙስሊማኑ የሚቃወሙት ሥላሴ በመጽሐፍ ቅዱስ ያለውን ሥላሴ እንዳልሆነ ልብ ማለት ያስፈልግል። የሙስሊማኑ ተቃውሞ ሥላሴን ካለ መረዳት ይመነጫል፤ ይህ ችግር በክርስቲያኑም ይስተዋላል። ያለመረዳቱ ችግር ሁለት መሰረቶች አሉት ፡-

## I. ሙስሊማኑ ሥላሴን ለምን አይቀበሉም

### 1. ሙስሊማኑ ሥላሴ በሰዋዊ -ቤተሰብ መዋቀር እንዳለበት ያስባሉ።

ለሙስሊማኑ አምላክ አብና ወልድ ነው ማለት አብ የትዳር አጋር አለው እንደ ማለት ይቆጠራል። ስለሆነም ልጁ ዘላለማዊ አይደለም ፤ የመለኮት አካል ለማድረግ የሚደረግ ጥረት እንጂ! ክርስቲያኑ እንደሙስሊማኑ አይደለም የሚያምኑት። በመለኮት ማንነት ውስጥ የአምላክ አባትነት አካላዊ ሳይኾን መንፈሳዊ ነው፤ ሰዋዊው አባትነት ስለ እርሱ ባህሪይ የተወሰነውን እንድንረዳ የሚያግዝ አገላለጽ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ "አባት" እና "ልጅ"ን የሚገልጸው በአብ እና በዘላለማዊው "ቃል" መካከል ያለውን ግንኙት በማመልከት ነው፤ ሁለቱም ከጊዜ ወሰን በላይ ናቸው፤ ሁለቱም በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት አንድና ፍጹም እኩል ናቸው።

"አባት" በአረብኛው ቋንቋ አውድ ብዙዎች የሚስማሙበት ገለጻ አለው፤ የጉዲፈቻ ልጅ አባት ሊኖረው ይችላል፤ አባትነቱ ግን አካላዊ ላይሆን ይችላል። በቁርኣን አባት የሚለው መገለጫ የመሐመድ ጠላት አቡ -ለሃብን "የነበልባል አባት" በሚል ይጠራዋል (ሱረቱ 111፥1-5)። የተጠበቀው ጽላት " ኡም አል-ኪታብ" ወይም "የመጽሐፉ እናት" (ሱረቱ 3፥7፣ 13፥39፣ 43፣16) ብሎ ይጠራዋል። ክርስቲያኑ እንዲሁ የጥንት ኤጵስቆጶሳትን " የቤተክርስቲያን አባቶች" ብለው ይጠራሉ። መጽሐፍ ቅዱስ አብራሐምን "የሁሉም አማኞች አባት " ይለዋል።

የአምላክ ማንነትን በቤተሰብ እና ልጆች ግንኙነት አውድ መገንዘብ ከክርስትና አስተምህሮ ውጪ ነው። በጥንታዊው ኢስላም አረብ ትርክት አላህ ሦስት ልጆች እንዳሉት ይነገራል ፡- አል-ላትን፣ አል -ዑዛን እና መናት (ሱረቱ 53፥19-20) ። ሌሎች አላህ ከጂኒዎች ጋር ባለው ግንኙነት አባት የሆናቸው ሌሎች እንዳሉ ይነገራል (ሱረቱ 6፥101) ። በሦስተኛ ደረጃ ከመልአክቶች ዘንድ አላህ ልጆች እንዳሉት ይታመናል (ሱረቱ 17፥ 40) ፤ አራተኛው አላህ

ለራሱ ሴት ልጆች እንዳሉት ለመካ ወንድ ልጆችም እንደሰጣቸው ይነገራል ( ሱረቱ 37፥151-153፣ 43፥ 16)።

መሐመድ እነዚህን አስተምህሮቶች ክፉኛ ይቃወማቸው ነበር። የ“ አካላዊ አባትነትን” ወደ ክርስትናው የሥላሴ አስተምህሮ ያሰረጸውን ማርያማይት አስተምህሮ አውግዟል። እንደርሱ አረዳድ የሥላሴ አስተምህሮ አብ ( አምላክ) ፣ እናት (ማርያም) እና ልጅ (ኢየሱስ ) ነው። ይህ አስተምህሮ ኢየሱስ እኔ እና እናቴ ከአላህ ሌላ ሁለት አምላኮች ነን ብላሃልን የሚለውን የሚቃወም እንደሆነ ይታመናል (ሱረቱ 5፥116)። የኦርቶዶክስ ክርስትና ሁለቱንም አጽንቶ ይቃወማል፤ እስልምናም እነዚህኑን ይቃወማል ፤ ነገር ግን የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት መቃወም አይቻልም።

## 2. ሙስሊማኑ ሦስት ፈጽሞ አንድ አለመኾኑን ይሞግታሉ

በሙስሊማኑም በክርስቲያኑም 1+1+ 1 ሦስት እንዳይደል ይታወቃል። ክርስቲያኑ ከሙስሊማኑ ባላነሰ በአምላክ አንድነት ላይ አጽኖኦት ይሰጣሉ ፤ መጽሐፍ ቅዱስም እንዲሁ! ሁለቱም “አንድነት” የአምላክ አንድ ባህሪይን ከመግለጽ አንጻር ነው የሚተረጉሙት። ዶክተር ቶማስ እንደሚከተለው ያብራራዋል፡-

“አንድ” ክርክር የሚያስነሳ ቃል ነው። ሙስሊማኑ አካላዊውን (ስሌታዊ) አንድነት ነው የሚያጸኑት። እንደ ክርስቲያን አንድነትን የምንመለከተው ፍጹም የሆነውን አንድነት (ግንኙነት) ለመግለጽ ነው ፤ እግዚአብሔር ሁሉ በሁሉ ነውና! ሙስሊማኑ አንድነትን የሚረዱት ከሌላው ተነጥሎ ያለውን ፍጹም ማንነትን ነው። ሙስሊማኑ አላህ ከሰው ሩቅና ኩሩ እንጂ የፍቅር ፣የርህራሄ ብሎም የመከራ አምላክ እንደሆነ አይረዱትም። በተቃራኒው ቁርአን ስለ ፈጣሪ ቁጣ ፣ ፍርድ፣ ጥላቻና ፍቅር ይናገራል።

ተፈጥሮው በራሱ በአንድነት እሳቤ ግንኙነት ላይ የተመሰረተ ነው። በራሱ ተነጥሎ ያለ ፍጹም አንድነት አለን? ጠፈር በራሱ ሦስት አቅጣጫዎች አሉት፡- ርዝመት፣ ወርድና ቁመት ። ጊዜ ኃላፊ፣ አሁናዊ እና መጻዒ ክፍሎች አሉት ። አብይ እና ቀዳሚ ቀለማት ሦስት ናቸው ። የአእምሮአችን ዋና ስራ በማሰብ ፣ በመፍቀድ እና በስሜት ነው የሚከናወነው ፣ ሆኖም እኛነታችን አንድ እንጂ ሦስት አይደለም።

አያሌ የአንድነት ደረጃዊች በሙሉ እርስ በእርሱ የሚገናኝ መዕከል አለው፡፡ ዐተም (ንጥረ-ነገር) የማይከፋፈል ነገር ሆኖ ሳለ በውስጡ ኤሌክትሮን ፣ ፕሮቶን እና ኒውትሮን የሚባሉትን ይዟል፡፡ ከላይ የተጠቀሱት ማሳያዎች አንድ አምላክ ሦስት አካላት የሚለውን የሥላሴ አስተምህሮ እንድንረዳው ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡

ቁርኣን ክርስቶስ የማርያም ልጅ፣ የፈጣሪ ቃል እና መንፈስ መኾኑን ይቀበላል (ሱረቱ 4፥171)፡፡ ይህ ስለ ክርስቶስ እውነታ ሙሉ መረዳት ባይሰጥም፤ አማኞች ቃል እና መንፈስ የአምላክ አንድ ማንነት ክፍል እንደኾነ መነሻ አሳብ ይለግሳል፡፡[73]

## II. የሥላሴን ሓሳዊ አስተምህሮ የሚቃወሙ የቁርኣን ምንባባት

አንዳቸውም የቁርኣን ምንባባት እውነተኛውን የክርስትና አስተምህሮተ ሥላሴ (አብ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ እና መንፈስ ቅዱስ አንድነት) አይቃወሙም፡፡ ከዚህ በታች የተቀመጡት ምንባባት ሓሳዊውን የሥላሴ አስተምህሮ የሚቃወሙ ናቸው ፡-

***ሱረቱ 2፥116 ፣117***

*አላህም ልጅ አለው አሉ፡፡ (ከሚሉት) ጥራት ተገባዉ፡፡ አይደለም በሰማያትና በምድር ያለው ሁሉ የርሱ ነዉ፡፡ ሁሉም ለርሱ ታዛዦች ናቸው፡፡ ሰማያትንና ምድርን ያለብጤ ፈጣሪ ነው፤ ነገርንም (ማስገኘት) በሻ ጊዜ ለርሱ የሚለዉ፡- ‹‹ኹን ነው፤›› ወዲያውም ይኾናል፡፡*

- ክርስቲያኑ ፈጣሪ “ልጁን ወሰደ” ብለው ፈጽሞ አይናገሩም፤ ልጁ ከዘላለም በፊት ከአባት ዘንድ እንደ ነበረ ይታመናሉ እንጂ! “ በመጀመሪያው ቃል ነበረ፤ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፤ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ፡፡ ይህ በመጀመሪያው በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፡፡ ሁሉ በእርሱ ሆነ፣ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም፡፡ በእርሱ ሕይወት ነበረች፣ ሕይወትም የሰው ብርሃን ነበረች” (ዮሐንስ 1፥1-4)፡፡

***ሱረቱ 3፥59***

*“ አላህ ዘንድ የዒሳ ምሳሌ እንደ አዳም ብጤ ነው፡፡ ከዐፈር ፈጠረው ፡፡ በዚያም ለርሱ (ሰው) “ኹን” አለው፤ ኾነም፡፡*

[73] አር ፣ቶማስ ገጽ፣ 180፡፡

- ይህ ምሳሌያዊ ጥቅስ ኢየሱስ እና አዳም ሁለቱም ልዩነት አላቸው። አዳም ከአፈር፤ ኢየሱስ ደግሞ ከመንፈስ ቅዱስ ነው ከሚለው ሌላ የቁርኣን ክፍል ጋር ይጋጫል።
- ስለ ኢየሱስ ቁርኣን የሚከተለውን ያስቀምጣል፦ "የመርየም ልጅ አል-መሲሕ ዒሳ የአላህ መልዕክተኛ ወደ መርየም የጣላት ' የኹን' ቃሉም ከእርሱ የኾነ መንፈስም ብቻ ነው። በአላህና በመልክተኞቹም እመኑ" (ሱረቱ 4፥171)። መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር መልአኩን ገብርኤል ወደ ማርያም በላከው ጊዜ እንዲህ ነበር የተናገው ፦ "ማርያም ሆይ፣ በእግዚአብሔር ፊት ጸጋ አግኝተሻልና አትፍሪ ። እነሆም ትፀንሻለሽ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ ፣ስሙንም ኢየሱስ ትዪዋለሽ። እርሱ ታላቅ ይሆናል የልዑል ልጅም ይባላል፣ጌታ አምላክም የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል፤ በያዕቆብ ቤትም ላይ ለዘላላም ይነግሣል፣ ለመንግስቱም መጨረሻ የለውም ። ማርያምም መልአኩን ። ወንድ ልጅ ስለ ማላውቅ ይህ እንዴት ይሆናል? አለችው። መልአኩም መልሶ እንዲህ አላት ። መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል፣ የልዑልም ኃይል ይጸልልሻል ስለዚህ ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል" (ሉቃስ 1፥26-35)።
- ሱረቱ 7፥12 ከዘፍጥረት 2፥7 ጋር ተስማሚ ነው " (በአላህ) 'ባዘዝኩህ ጊዜ ከመስገድ ምን ከለከለህ' አለው። 'እኔ እርሱ የበለጥኩ ነኝ። ከእሳት ፈጠርኸኝ። እርሱን ግን ከጭካ ፈጠርከው' አለ።" ሱረቱ 2፥36 አክሎ አዳም ኃጢአትን እንደሰራ ለሰው ዘርም የጥፋት ምክንያት እንደሆነ ይናገራል፤ሱረቱ 19፥19 ግን ኢየሱስ ቅዱስ እና ስህተት የሌለበት መኾኑን ያስረግጣል።

***ሱረቱ 3፡64***

*የመጽሐፉ ባለቤቶች ሆይ ! በእኛና በእናንተ መካካል ትክክል ወደ ኾነች ቃል ኑ። (እርሷም) አላህን እንጂ ሌላን ላንገዛ ፣ በርሱም ምንንም ላናጋራ ፣ ከፊላችንም ከፊሉን ከአላህ ሌላ አማልክት አድርጎ ላይይዝ ነው፤ በላቸው። እመቢ ቢሉም፦ እኛ ሙስሊሞች መኾናችንን መስክሩ በሏቸው።*

***ሱረቱ 9፡31***

*ከእርሱ በቀር ሌላ አምላክ የሌለውን አንድን አምላክ ሊገዙ እንጂ ያልታዘዙ ሲኾኑ ሊቃውንቶቻቸውንና መነኮሳታቸው፣ የመርየምን ልጅ አል-መሲሕንም ከአላህ ሌላ አማልክት አድርገው ያዙ። ከሚያጋሩት ሁሉ የጠራ ነው።*

***ሱረቱ 4፡171፣172***

*እናንተ የመጽሐፉ ሰዎች ሆይ! በሃይማኖታችሁ ወሰንን አትለፉ። በአላህም ላይ እውነትን እንጂ አትናገሩ። የመርየም ልጅ አል-መሲሕ ዒሳ የአላህ መልክተኛ ወደ መርየም የጣላት "የኹን"*

*ቃሉም ከእርሱ የኾነ መንፈስም ብቻ ነው፡፡ በአላህና በመልክተኞቹም እመኑ፡፡ (አማልክት) ሦስት ናቸው አትበሉም፡፡ ተከልከሉ ፣ ለእናንተ  የተሸለ ይኾናልና፡፡ አላህ አንድ አምላክ ብቻ ነው ፡፡ ለእነርሱ ልጅ ያለው ከመኾን የጠራ ነው፡፡ በሰማያትና በምድር ያለ ሁሉ የርሱ ነው፡፡ መመኪያም በአላህ በቃ፡፡*

- የሥላሴ እምነት መግለጫ "ሦስት" አማልዕክትን አያመለክትም፤ " አንድ አምላክ በሦስት አካላት" እንጂ! በዚህ ክፍል ላይ አል-ባይዳዊ የሚከተለውን ትንታኔ ያስቀምጣል ፡- " አላህ፣ ክርስቶስ እና መርየም ሦስት ናቸው አትበሉ፤ ወይም አምላክ ሦስት ነው አትበሉ፡፡" አባት ዲኅት (ማንነት)፣ ኢልም ( ዕውቀት)፣ መንፈስ ቅዱስ ሃያት ( የአምላክ ሕይወት) ነው፡፡
- "ልዑል  ሩቅ ኾኖ ሳለ ልጅ አለው መባሉ  አካላዊ ግንኙነትን ወይም  ፈጣሪ ከሚስት (ከሴት) ዘንድ ልጅ መውለዱን አይደለም የሚያመለክተው፡፡ ይህ አሳብ በሱረቱ 6 ፥ 102 እና  72፡ 3 የአህዛብን አስተምህሮ ከክርስትናው ጋር በማገናኘት ገልጾታል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር መንፈስ መኾኑን በዮሐንስ 4፡24 ላይ ይናገራል፡፡ ኢየሱስ ከአብ ጋር ያለው ግንኙነት መንፈሳዊ ነው፡፡

  *ሱረቱ 5፡17*

  *እነዚያ አላህ እርሱ የመርም ልጅ አል-መሲሒ ነው ያሉ በእርግጥ ካዱ፡፡ የመርየምን ልጅ አል-መሲሕን እናቱንም በምድር ያለንም ሁሉ ለማጥፋት ቢሻ ከአላህ ማዳን የሚችል ማነው በላቸው፡፡ የሰማያትና የምድር የመካከላቸውም ንግሥና የአላህ ብቻ ነው ፡፡ ሚሻውን ይፈጥራል፡፡ አላህም በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነው፡፡*
- " አላህ የመርየም ልጅ መሲሕ ነው፡፡" ክርስቲያኑ ግን እግዚአብሔር መሲሑ ክርስቶስ እንደኾነ አያምኑም፤ እግዚአብሔር አብ፣ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ እንደኾነ ብቻ እንጂ! ኢየሱስ እግዚአብሔር ነው ፣ እግዚአብሔር ሥሉስ አሃዱ እንጂ  ኢየሱስ አይደለም!
- " ፈጣሪ የመርየም ልጅ መሲሑን፣ እናቱን እንዲሁም በምድር ያሉ ሰዎችን ማጥፋት ቢሻ ሊቃወመው የሚችል ኃይል ማነው?" መልሱ ፈጣሪ ኢየሱስንም ሆነ እናቱን እንዲያጠፋ የሚያደርግ ባህሪይ የለውም የሚል ነው! እግዚአብሔር ማርያም የመሲሑ እናት እንድትኾን በመምረጥ ኢየሱስ የዓለም መድኅን እንዲኾን ፈቅዷል፡፡ የእግዚአብሔር ኃይል፣ ቅድስና እንዲሁም ፍቅር በአንድነት ነው የሚሰሩት፡፡

ሱረቱ 5:72 -76

*እነዚያ "አላህ እረሱ የመርያም ልጅ  አል-መሲሕ ነው" ያሉ በእርግጥ ካዱ፡፡ አል-መሲህም አለ፡- "የእስራኤል ልጆች ሆይ! ጌታዩንና ጌታችሁን አላህን ተገዙ፡፡" እነሆ በአላህ የሚያጋራ ሰው አላህ በርሱ ላይ ገነትን በእርግጥ እርም አደረገ፡፡ መኖሪያውም እሳት ናት፡፡ ለበዳዮችም ምንም ረዳቶች የሏቸውም ! እነዚያ "አላህ የሦስት ሦስተኛ ነው"ያሉ በእርግጥ ካዱ፡፡ ከአምላክም እንጅ ሌላ የለም፡፡ ከሚከተሉትም ነገር ባይከለከሉ ከነሱ እንዚያን የካዱትን  አሳማሚ ቅጣት በእርግጥ ይነካቸዋል፡፡ ወደ አላህ አይመለሱምና ምሕረትን  አይለምኑትምን አላህም መሐሪ ኣዛኝ ነው፡፡ የመርየም ልጅ አል-መሲሕ ከበፊቱ መልክተኞች በእርግጥ ያለፉ የኾነ መልክተኛ እንጂ ሌላ አይደለም ፡፡ እናቱም በጣም እውነተኛ ናት፡፡ (ሁለቱም) ምግብን የሚበሉ ነበሩ፤ አንቀጾችን ለነርሱ (ለከሓዲዎች) እንዴት አንደምናብራራ ተመልከት ከዚያም (ከእውነት ) አንዴት እንደሚመለሱ ተመልከት፡፡ "ከአላህ ሌላ ለእናንተ መጉዳትንና መጥመቅን የማይችልን ትገዛላችሁን" በላቸው፡፡ አላህም እርሱ ሰሚው ዐዋቂ ነው፡፡*

- "አላህ ክርስቶስ ነው በማለታቸው እርሱን ተሳደቡ (ካዱ) " የሚለው አሳብ እግዚአብሔር አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ  ስለኾነ ክፍሉ የክርስቶስን መለኮት አይቃረንም፡፡
- ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ " ጌታዬን እና ጌታችሁን አምልኩ" ብሏል፡፡ በዕርገቱ ወቅት "እኔ ወደ አባቴ እና ወደ አባታችሁ ወደ አምላኬ እና ወደ አምላካችሁ ዓርጋለሁ " (ዮሐንስ 20፥17)፡፡ ኢየሱስ " አባታችን እና አምላካችን" አላለም ምክንያቱም ከአብ ጋር ያለው ግንኙነት ከደቀመዛሙርቱ እጅጉን ይለያልና ነው፡፡ የእርሱ ልጅነት ከዘላላም የነበረና የተገባው ሲሆን፣ የእኛ ልጅነት ያልተገባን በጸጋው የተቀበልነው ነው፡፡ በስጋ እንደተገለጠ መለኮት  ኢየሱስ  መለኮታዊ እና ሰብኣዊ ባህሪይ ነበሩት፡፡ ኢየሱስ እንደሰው ልጅ  " አባቴና እና አምላኬ" ያለው በሰው መልክ በመገኘቱ እራሱን ትሁት ለማድረግ ነው ፡- "የባሪያን መልክ ይዞ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ባዶ አደረገ" (ዮሐንስ 2፥7)፡፡
- ኢየሱስ " ከአላህ ጋር የሚጋራ " አይደለም፡፡ ኢየሱስ የአላህ ጋር ተጋሪ  ሳይኾን ራሱ መለኮት (እግዚአብሔር ) ነው ፡፡ የመለኮት አንዱ ክፍልም አይደለም፤ በራሱ መለኮት እንጂ!
- ክርስቲያኑ  እግዚአብሔር " ከሦስት ሦስተኞች ነው" አላሉም፤  አምላካችን እግዚአብሔር አንድ ነው፡፡

- ኢየሱስም እናቱም "ምግብ ተመግበዋል" ምክንያቱም በስጋ የተገለጠ አምላክ ነበረና! "በመጀመሪያ ቃል ነበር፣ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ ፣ቃልም እግዚአብሔር ነበር……ቃልም ሥጋ ሆነ ጸጋንና እውነትንም ተሞልቶ በእኛ አደረ፣ አንድ ልጅም ከአባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር የሆነውን ክብሩን አየን (ዮሐንስ 1፥ 1፣2፣14)።
- "በአላህ ምትክ ማምለክ" አስመልክቶ ክርስቲያኑ ኢየሱስን በአላህ ምትክ አላመለኩም፤ አላህ (መለኮት) አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ ነውና!
- ኢየሱስ አዳኝ ነው ። የተቀበሉት ቤዛነትን ያገኛሉ ፤ ላልተቀበሉት ግን ጥፋት ይሆናል።
  " *በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና። ዓለም በልጁ እንዲድን ነው እንጂ ፣ በዓለም እንዳይፈርድ እግዚአብሔር ወደ ዓለም አልላከውምና። በእርሱ በሚያምን አይፈረድበትም ፤በማያምን ግን በአንዱ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ስላላመነ አሁን ተፈርዶበታል" (ዮሐንስ 3፥ 16-18)።*

  ***ሱረቱ 5፥116-118***

  *አላህም ፡- " የመርም ልጅ ዒሳ ሆይ! አንተ ለሰዎቹ፡- እኔና እናቴን ከአላህ ሌላ ሁለት አምላኮች አድርጋችሁ ያዙ ብለሃልን " በሚለው ጊዜ (አስታውስ) ። " ጥራት ይግባህ፤ ለእኔ ተገቢ ያልኾነን ነገር ማለት ለኔ አይገባኝም። ብዬው እንደ ኾነም በእርግጥ ዐውቀኸዋል። በነፍሴ ውስጥ ያለውን ሁሉ ታውቃለህ ። ግን አንተ ዘንድ ያለውን አላውቅም ። አንተ ሩቆችን ሁሉ በጣም ዐዋቂ አንተ ብቻ ነህና" ይላል። "በእርሱ ያዘዝከኝ ቃል ጌታዩንና ጌታችሁን አላህን ተገዙ ማለትን እንጂ ለነርሱ ሌላ አላልኩም። በውስጣቸውም እስካለሁ ድረስ በነርሱ ላይ ተጠባባቂ ነበርኩ። በተሞላኸኝም ጊዜ (ባነሳኸኝ ጊዜ) አንተ በነሱ ላይ ተጠባባቂ ነበርክ። አንተም በነገሩ ሁሉ ላይ ዐዋቂ ነህ።" " ብትቀጣቸው እነርሱ ባሮች ናቸው። ለነርሱ ብትምርም አንተ አሸናፊው ጥበበኛው ነህ" (ይላል)።*
- ኢየሱስ "እኔና እናቴን ከአላህ ሌላ ሁለት አምላኮች አድርጋችሁ ያዙ" አላለም ፤ ክርስቲያኑም እርሱ እንደተናገረው አይቀበሉም። የእግዚአብሔር መገለጥ በኾነው መጽሐፍ ቅዱስ ይህ ብሂል ከቶውን አይገኝም።
- መጽሐፍ ቅዱስ ለድንግል ማርያም ከበሬታን ከመስጠት በዘለል በቅዱስ ሥላሴ ፈጽሞ አያካትታትም።
- "በውስጣቸውም እስካለሁ ድረስ በነርሱ ላይ ተጣባባቂ ነበርኩ።" ኢየሱስ አብ የሚከውነውን ኹሉ ይከውናል ፤ በዚህ አንዱ ለአንዱ ምስክር ነው። የኢየሱስ ስልጣን ከአብ ስልጣን እኩል ነው።

*ሱረቱ 6፥101*

*(እርሱ) ሰማያትንና ምድርን ያለ ብጤ ፈጣሪ ነው ። ለእርሱ ብጤ ፈጣሪ ነው ። ለእርሱ ሚስት የሌለችው ሲኾን እንዴት ለእርሱ ልጅ ይኖረዋል ነገርንም ሁሉ ፈጠረ ይህ ጌታችሁ አላህ ነው። ከእርሱ በቀር አምላክ የለም። ነገርን ሁሉ ፈጣሪ ነው። ስለዚህ ተገዙት ። እርሱም በነገሩ ሁሉ ላይ ተጠባባቂ ነው።*

- ሱረቱ 72፥3 በተመሳሳይ ከላይ የተለጸውን ክፍል ያስረግጣል። የመሲሑ ልጅነት መንፈሳዊ እንጂ አካላዊ አይደለም። በእግዚአብሔር እና በማርያም መካካልም እንዲሁ አካላዊ ግንኙነት የለም።

*ሱረቱ 9፥30*

*አይሁድ ዐዚይር የአላህ ልጅ ነው አለች። ክርስቲያኖችም አል-መሲሒ የአላህ ልጅ ነው። ይህ በአፎቻቸው (የሚናገሩት) ቃላቸው ነው። የእነዚያን ከነሱ በፊት የካዱትን ሰዎች ቃል ያመሳስላሉ። አላህ ያጥፋቸው። (ከእውነት) እንዴት ይመለሳሉ!*

- በብሉይ ኪዳን አንዳችም ክፍል ዐዚይር የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ አይናገርም። አንዳንድ ሙስሊም ጸሓፍት ዐዚይር ዕዝራ እንደሆነ ይገልጻሉ። ዐዚይር በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሰው ዕዝራ ከሆነ አይሁድ የእግዚአብሔር ልጅ መኾኑን አያረጋግጡም! ይህ በመሐመድ ወቅት በአረብ -ሰላጤ አካባቢ የተፈጠረ የስህተት አስተምህሮ እሳቤ ነው።
- በኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅነት እና በዐዚይር ልጅነት መካከል ምንም አይነት አንድነት የለም!

**ሱረቱ 112፥1-4**

*በል እርሱ አላህ አንድ ነው፣ አላህ (የሁሉ ) መጠጊያ ነው። አልወለደም ፤ አልተወለደምም ፤ ለእርሱም አንድም ብጤ የለውም።*

- ክርስቲያኑ ይህን ኣሳብ የሚጋሩት “እግዚአብሔር አንድ ነው ፤ ዘላለማዊ እና ፍጹም ነው፤ አልተወለደም አይወለድምም፤ የሚተካከለው ማንም የለም” በማለት ነው። በዚህ መልኩ መረዳት አስፈላጊ የሆነበት ምክንያቶች አሉ፡- (1) “አልወለደም ፤ አልተወለደምም” ቅድመ ተከተሉ ተፋልሷል፤ ማንም ሳይወለድ አይወልድምና! (2) “አልወለደም” ኃላፊ ጊዜን ብቻ ሳይኾን የአሁን ጊዜን ሊያመለክት ይችላል።

## III. የሥላሴ እስላማዊ አስረጂዎች

### 1. ቁርኣን ቅዱስ ሥላሴን ይገልጻል

አይሁዳዊያኑ፣ ክርስቲያኑ እና ሙስሊማኑ ስለ ፈጣሪ የሚገልጹበት መንገድ ቢለያይም፣ በፈጣሪ፣ በቃሉ እና በመንፈስ ቅዱስ ያምናሉ፡፡

የአይሁዳዊያኑ መጽሐፍ "እነሆ ደግፌ የያዝሁት ባሪያዩ ፤ ነፍሴ ደስ የተሰኘበት ምርጤ ፤ በእርሱ ላይ መንፈሴን አድርጌአለሁ፣ እርሱም ለአሕዛብ ፍርድን ያወጣል" (ኢሳያስ 42፥1) ይላል፡፡ የክርስቲያኑ መጽሐፍ " እግዚአብሔር የናዝሬቱን ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ በኃይል ቀባው" ይላል፡፡

ቁርኣን እንዲህ ይላል ፡- "የመርየምን ልጅ ዒሳንም ግልጽ ታምራቶችን ሰጠነው ፡፡ በቅዱስም መንፈስም አበረታበው" (ሱረቱ 2፥87)፡፡ ይህ ቃል በቁጥር 253 ላይ ተደግሟል፡፡ ሱረቱ 5፥110 አላህ ራሱ " የመርየም ልጅ ዒሳ ሆይ ! በአንተና በእናትህ ላይ (የዋልኩላችሁን) ጸጋዩን አስታውስ ….በቅዱስ መንፈስ ባበረታሁህ ጊዜ" ብሏል፡፡
እነዚህ ሦስት የቁርኣን ክፍሎች አብ ኢየሱስን በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት እንዳበረታው ያስረግጣሉ፡፡

### 2. ቁርኣን ክርስቲያኑ አንድ አምላክ ማምለካቸውን ይመክራል

*ሱረቱ 29፡46*

*የመጽሐፉን ባለቤቶችም በዚያች እርሷ መልካም በኾነችው ክርክር እንጂ አትከራከሩ፡፡ ከእነርሱ እነዚያን የበደሉትን ሲቀር፡፡ በሉም " በዚያ ወደኛ በተወረደው ወደ ናንተም በተወረደው አመንን፡፡ አምላካችንም አምላካችሁ አንድ ነው፡፡ እኛም ለእርሱ ታዛዦች ነን፡፡"*

በዚህ ክፍል መጀመሪያ ሙስሊማኑ መልካም አይሁዳዊያንኑ እና ክርስቲያኑን በጥሩ ሁኔታ በመመልከት የተሰጡአቸውን ብሉይ ኪዳን እና አዲስ ኪዳን መጻሓፍት እንዲያምኑ ይመክራል፡፡ በተጨማሪም እነርሱ የሚያመልኩት አንድ አምላክ አምላካቸው እንዲያደርጉና እንዲታዘዙትም ይመክራል፡፡

*ሱረቱ 5፡5*

*ዛሬ መልካሞች ሁሉ ለናንተ ተፈቀዱ፡፡ የእነዚያም መጽሐፍን የተሰጡት ሰዎች ምግብ (ያረዱት) ለእናንተ የተፈቀደ ነው፡፡ ምግባችሁም ለነሱ የተፈቀደ ነው፡፡ ከምእመናት ጠብቆ ከእነዚያ ከእናንተ በፊት መጽሐፍን ከተሰጡት ሴቶች ጥብቆቹም፤ ዘማሚዎችና (ዝሙተኞች) የምስጢር ወዳጆች ያዢዎች ስትኾኑ ጥብቆች ኾናችሁ መምህሮቻችውን በሰጣችኋቸው*

*የተፈቀዱ ናቸው)። በእምነትም የሚመለስ ሰው በእርግጥ ሥራው ተበላሸ። በመጨረሻም ቀን እርሱ ከከሳሪዎቹ ነው።*

ቁርኣን ሙስሊም ወንድ ክርስቲያን ወይም አይሁድ ሴት እንዲያገባ ቢፈቅድም፣ ብዙ አማልእክት የሚያመልኩትን ግን እንዲያገባ አይፈቅድም ። ሱረቱ 2፥221 "(በአላህ) አጋሪ የሆኑ ሴቶች እስከ ሚያምኑ ድረስ አታግቡአቸው። በአጋሪይቱ ምንም ብትደንቃችሁም እንኳ ያመነችው ባሪያ በእርግጥ በላጭ ናት። ለአጋሪዎቹም እስከሚያምኑ ድረስ አትዳሩላቸው። በአጋሪው (ጌታ) ምንም ቢደንቃችሁ ምእምኑ በላጭ ነው። እነዚያ (አጋሮች) ወደ እሳት ይጣራሉ። አላህም በፈቃዱ ወደ ገነት እና ወደ ምሕረት ይጣራል። ሕግጋቱንም ለሰዎች ይገልጻል እነርሱ ሊገስጹ ይከጀላልና።"

*ሱረቱ 4፥48*

*አላህ በእርሱ ማጋራትን በፍጹም አይምርም። ከዚህ ሌላ ያለውንም (ኀጢአት) ለሚሻው ሰው ይምራል። በአላህም የሚያጋራ ሰው ታላቅን ኀጢአት በእርግጥ ቀጠፈ።*

*ይህ ክፍል አላህ በእርሱ ማጋራት (ብዙ አማልእክት ማምለክ) ኃጢአት በቀር ሌሎችን ይቅር የሚል እንደሆነ ያመላክታል። ቁርአን አይሁዳዊያኑ ፣ ክርስቲያኑ እና ሳቢያኑን አንድ አምላክ ስለሚያመልኩ ኃጢአታቸውን ይቅር እንደሚል ያስረግጣል። " እነዚያ ያመኑ እነዚያም አይሁዳውያኑ የኾኑ ክርሰቲያኖችም ፣ ሰቢያኖችም (ከእነርሱ ) በአላህና በመጨረሻው ቀን ያመነ መልካምንም ሥራ የሠራ ለነርሱ በጌታቸው ዘንድ ምንዳቸው አላቸው። ከነርሱም ላይ ፍርሃት የለባቸውም ፤ እነርሱም አያዝኑም" (ሱረቱ 2፥62)። ይህ አሳብ በሱረቱ 5፥69 እና ሱረቱ 22፥17 ላይ ተደግሟል።*

## IV. የሥላሴ አስተምህሮ ፍቱንነት

*ሙስሊማኑ ፈጣሪ አንድ አምላክ፣ ባህሪያቱ ግን ዘላለማዊ እና በርካቶች እንደኾኑ ያምናሉ። ከባህሪያቶቹ መካከል ህይወት፣ ዕውቀት ፣ ኃይል፣ ፍቃድ፣ መስማት፣ ማየት፣ መናገር እና ፍቅር ይገኙበታል። ፈጣሪ ለሙሴ ሲናገር "ባንተ ላይም ከእኔ የኾነን መውደድ ጣልኩብህ። (ልትወደውና) በእኔም ጥበቃ ታድግ ዘንድ" (ሱረቱ 20፥39)።*

*ፈጣሪን ጨምሮ እነዚህኑ ባህሪያት (ማየት፣ መስማት፣ ማወቅ፣ መድረስና ማፍቀር) ትርጉም የሚኖራቸው ሌላ አካል በተገኘበት ነው። ፈጣሪ አንድ ከሆነ (አምልኮተ አሃዱ አምላክ) ባህሪያቶቹ ፍጥረቱ ለኾኑት መላዕክትም ሆነ የሰው ዘር በሙሉ የማይንቀሳቀሱ (ጥቅም ላይ*

የማይውሉ) ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡ በሌላ አባባል የፈጣሪን ባህሪያት ሁኔታ ለማንቀሳቀስ ፍጥረት እንደ ምክንያት ሊቆጠር ይችላል፡፡ እንደሙስሊማኑ አረዳድ የፈጣሪ ባህሪያት ወጥና ቀላል ነው፡፡ ይኸውም ፈጣሪ ከፍጥረት በፊት ማንንም አልወደደም፣ አላናገርም፣ አልሰማም ፤ ከእርሱም በፊት ማንም አልነበረም፡፡

በዚህ ረገድ  ለሚነሱ ጥያቄ የሥላሴ አስተምህሮ ፍቱን ነው፡፡ አልጄራዊው ቅዱስ አግስቲን የሚከተለውን ያስቀምጣል፡- " እግዚአብሔር ፍቅር ነው፤ ፍቅር ዘላለማዊ ነው፤ እግዚአብሔር ዘላለማዊ ፍቅሩን የሚገልጽበት አስፈልጎታል፤ አብ ወልድን ወደደ፤ ወልድ መንፈስ ቅዱስን ወደደ፤ መንፈስ ቅዱስ አብን ወደደ ፡፡ እግዚአብሔር አለ ፡- "ሰውን በመልካችን እንፍጠር፡፡"

የሥላሴ አስተምህሮ እግዚአብሔር የማይለወጥ አምላክ እንደኾነ ያበክራል፡፡ ፍጥረት የእግዚአብሔር ባህሪያት አንቀሳቃሽ አይደለም፡፡ እርሱ ዘላለማዊ ፣የማይለወጥ፣ በአንድነቱ ማንነት የሚኖር አምላክ ነው፡፡

በአብ፣ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ መካካል ፍቅር፣ ንግግር፣ መሰማማት ከፍጥረት በፊት ነበር፡፡  ፍጥረት የእግዚአብሔር ፍቅር ውጤት ነው (ፍጥረት ከመጀመሪያው በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር)፡፡ ፍቅር የእግዚአብሔር ባህሪይ ነው፡፡ አብ ወልድን ዓለም ሳይፈጠር በፊት ወደደ፤ ወልድ አብን ይወዳል፤ አብ እና ወልድ መንፈስ ቅዱሰን ይወዳሉ፡፡ በሦስቱ አካላት መካካል ያለው ዘላላማዊ ፍቅር እግዚአብሔር ከሰው ጋር ላለው ግንኙነት መሰረት ነው፡፡

ይህ ፍቅር ጸሎትን ይመልሳል፤ ቁርኣን በሱረቱ 40፥60 "ጌታችሁም አለ 'ለምኑኝ ፤ እቀበላችኃለሁና፡፡" (ሱረቱ 40፥60)፡፡ እግዚአብሔር ሕዝቡን እንደሚሰማ ማቴዎስ 6፥6 ይናገራል፡- "አንተ ስትጸልይ ፣ ወደ እልፍኝህ ግባ  መዝጊያህንም  ዘግተህ በስውር ላለው አባትህ ጸልይ ፤ በስውር የሚያይ አባትህም በግልጥ ይከፍልሃል::"

ከዘላለም እግዚአብሔር በራሱ የሚታወቅ እና የሚያውቅ፤ የሚፈለግ እና የሚፈልግ፣ የሚወደድ እና የሚወድ ፣ የሚታይ እና የሚያይ፣ የሚሰማ እና የሚሰማም አምላክ ነው፡፡ እርሱ ፍጹም የማይታወቅ አሃዱ አምላክ አይደለም፡፡ ሙስሊማኑ በእርግጥ ስለ አንድነቱ እንዳላቸው አረዳድ ሁሉ የፈጣሪ ባህሪያቶች አንድ አይደሉም፡፡ ለምሳሌ ፡- ፈጣሪ ለፍጥረታት ያለው ፍቅር ከፍጥረት በፊት አልነበረም ፤ ፈጣሪ እራሱ ከጊዜ ወደ ጊዜ ከአንድ ማንነት ወደ ሌላው ማንነት ተለውጧል ይላሉ፡፡

## V. የሥላሴ አስተምህሮ ማሳያ

የሥላሴን አስተምህሮ የሚያሰርጹ በርካታ ማሳያዎች አሉ። ማሳያዎቹ ውስንነት አላቸው፣ ኾኖም የማይታየውን እውነት እንድንረዳው እጅጉን ይጠቅማሉ። ሥላሴን ሊያስረዱ የሚችሉ ማሳያዎችን እንመልከት፡-

- ሰው፡- የአካል፣ ዕውቀት እና መንፈስ ስሪት ነው፤ ሆኖም አንድ ማንነት አለው።
- አእምሮ፡- ምናብ፣ ማስተዋል እና ማስታወስ ነው፤ ነገር ግን ደርጊቱ አንድ ነው።
- እሳት፡- ሙቀት፣ ብርሃን፣ የእሳት ነበልባል ነው፤ ነገር ግን አንድ እሳት ነው ያለው፡
- ጸሐይ፡- አንድ አካል አላት፤ ሆኖም ሙቀት፣ ብርሃን እና ኃይል ትሰጣለች።
- ፈራፍሬ፡- የራሱ የሆነ ቅርጽ ፣ ጣዕም እና ሽታ አለው፤ ሆኖም አንድ አካል ነው።
- ዉኃ፡- አንድ ንጥረ ነገር ሆኖ ሳለ በፈሳሽ፣ በእንፋሎት እና በበረዶ መልክ ይገኛል።
- (Cube) ኩይብ :- አንድ ቅርጽ ያለው ቁስ ሲሆን ሶስት ማዕዘናት አሉት።

  ሥላሴን ይበልጥ የሚያስረዳን ማሳያ ሲ. ኤስ ሊዊስ “Mere Chrstianity” በሚለው መጽሐፉ ያሰቀመጠው ነው፡-[74]

በጠፈር መንቀሳቀስ የሚቻለው በሦስት መንገድ ነው፡- ግራ ወይም ቀኝ፣ ወደ ኋላ ወይም ወደ ፊት፣ ወደ ላይ ወይም ወደታች ፤ ማንኛውም እንቅስቃሴ ከእነዚህ ሦስትዮሽ አቅጣጫ ውጪ ሊሆን አይችልም። አንዱን አቅጣጫ ስትጠቀሙ ቀጥ ያለ መስመር መሳል ትችላላችሁ። ሁለት አቅጣጫዎችን የምትጠቀሙ ከሆነ ደግሞ ምስልን (ካሬን) ትሰራላችሁ (ካሬ ከአራት ቀጥታ መስመሮች ነው የሚሰራው)። ሦስት አቅጣጫዎችን ስትጠቀሙ ደግሞ ባለ ስድት ካሬ ኪዩብ ቁስ ትሰራላችሁ። አስተዋላችሁን? ባለ አንድ አቅጣጫ ዓለም ባለ አንድ ቀጥታ መስመር ነው ። ባለ ሁለት አቅጣጫንም የተመለከትን እንደሆነ አሁንም የሚጠቀመው ቀጥታ መስመሮችን ነው። ባለ ሦስት አቅጣጫው አለም ሳይቀር አሁንም የሚጠቀመው ብዙ መስመሮችን ነው ። በሌላ አባባል የተሻለ እና ውስብስብ ደረጃዎችን ለማግኘት ፣ ቀላል የነበረውን ደረጃ አንተወውም፤ ሁለቱንም አቀናጅተን አዲስ መንገድ እንፈልጋለን እንጂ!

በክርስቲያኑ ነገረ-መለኮት ይህ መርህ ይሰራል። በሰው ደረጃ አንድ ሰው አንድ አካል ነው፤ ማናቸውም ሁለት ሰዎች ደግሞ ሁለት የተለያዩ አካላት ናቸው (በሁለቱ አቅጣጫዎች እንደሆነው አንድ ካሬ አንድ ስዕል አካል) ሲሆን፣ ሁለት ካሬዎች ደግሞ ሁለት ምስሎች ናቸው)። ወደ መለኮት ስንመጣ በመለኮት ዘንድ ሦስት አካላት (ሰብዕናዎች) እናገኛለን።

---

[74] ሲ. ኤስ ፣ ሊዊስ ፣ ገጽ 137።

በእግዚአብሔር አቅጣጫ ሦስት አካላት ነገር ግን አንድ መለኮት (ማንነት) ነው ያለው፡፡ በአንድ ኪዩብ (ማንነት) ስድስት ካሬዎች እንዳሉት ኹሉ!

በእርግጥ ሦስት አካላት በአንድ መለኮት ያለውን ሚስጥር ከላይ በተገለጸው መሳያ ሙሉ ለሙሉ መረዳት አይቻል ይሆናል፡፡ ብዙ ጊዜ አንድ አዎንታዊ (ትክክል) እና ከአእምሮአችን በላይ የኾነ እውነታ ሲገጥመን እንደናገጣለን፡፡ ቀደም ብለን ያልተገነዘብነው አሁን ግን እውነታውን እንድንቀበለው (ቀደም ብለን ከምናቀው) የምንገደድበት ጊዜ ብዙ ነው፡፡

"ሦስት አካላትን በአንድ ማንነት በአእምሮ ልንረዳው የማንችለው ከሆነ፣ ስለ እርሱ ማወቅም ሆነ መስማት ስለ ምን አስፈለገ?" የሚለውን ጥያቄ ታነሱ ይሆናል፡፡ ደህና ስለ ሥላሴ ማንሳት (ማውራት) በራሱ ጥሩ ነገር ላይሆን ይችላል፡፡ ቁልፉ ነጥብ በማንኛውም ጊዜ (ዛሬ ጭምር) ከፈቀድክ የሦስቱ አካላት (ሥላሴ) ህይወት በአንተ ህይወት መጀመሩ ነው፡፡

በመጨረሻም (በማጠቃለያ) ይህ የነገረ-መለኮት ጥናት መነሻ መኾኑን መዘንጋት የለብንም፡፡ ሰዎች ብዙ ጊዜ ስለ እግዚአብሔር ያላቸው ግንዛቤ አናሳ ነው፡፡ ሰው ኾኖ የመጣው እርሱ አምላክ ነኝ በማለቱ እንደ ዕብድ ሊቆጠር አይገባውም ነበር፡፡ እንዲያምኑት አድርጓል፤ ከገደሉት በኋላ እንካ አይተውታል፡፡ ከዚያም እንደ ማህበረሰብ ወይም ቤተሰብ ተመስርተው ሳሉ እግዚአብሔርን በውስጣቸው (በህይወታቸው) አገኙት፡፡ ይመራቸውም፣ ከዚህ ቀደም ማድረግ የማይችሉትን እንዲሰሩ ያደርጋቸውም ጀመር፤ በዚህም ወደ ትክክለኛው ክርስቲያናዊ የሥላሴ (ሦስት አካላት አንድ አምላክ) አስተምህሮ ብርሃን ደረሱ!

**የግል ማስታወሻ**

**ሀ**

# የእስልምና ታሪክ ቁልፍ ቀናት

| | |
|---|---|
| 570 (ዓ.ም) | መሐመድ ተወለደ:: |
| 595 | መሐመድ ከድጃን አገባ: |
| 610 | መሐመድ መጀመሪያውን መገለጥ ተቀበለ:: |
| 622 | ሂጅራ፡- መሐመድ ወደ መዲና ተጓዘ፤ የእስልምናስላም ዘመን የመጀመሪያ ዓመት:: |
| 624 | የባድር ጦርነት ፡ ሙስሊማኑ የመካን ጦር ድል ነሱ:: |
| 625 | የመካ ጦር ሙስሊማኑን ኃይል በኡድ ረታ:: |
| 627 | የደች ጦርነት፣ የመካ መከበብ፣ የሙስሊማኑ ድል:: |
| 629 | የቤዛንታይን ኃይል ሙስሊማኑን ጦር አሸነፈ:: |
| 630 | የመሐመድ ኃይል መካን ማረከ:: |
| 632 | የመሐመድ የመጨረሻ ጉዞ ወደ መካ እና ሞት:: |
| 632-634 | ካሊፌት አቡ -በከር:: |
| 634- 644 | ካሊፌት ዑመር:: |
| 644-656 | ካሊፌት ዑትማን:: |
| 656 -661 | ካሊፌት አሊ:: |
| 661-750 | የኦማይድ ሥረወ- መንግስት አገዛዛ:: |
| 674 | ሙስሊማኑ ኮንስታትኖፕልን ከበቡ:: |
| 680 | የሁሴን ሞት ኬርባላ |
| 711 | ሙስሊማኑ ከሰሜን አፍሪካ ወደስፔን ተጓዙ:: |
| 732 | የታዎር ጦርነት ፡ ቻርለስ ማርቴል ሙስሊማኑን ድል ነሳ:: |
| 750 -12 58 | የአባሲድ ሥርወ -መንግስት:: |
| 786-809 | ካሊፌት ሀሩን አል -ራሽድ በባግዳድ |
| 870 | ሙስሊማኑ ማልታን ወረሱ |
| 1091 | የክርስቲያኑ ኃይል ሲሲሊን እና ማልታን አስመለሱ |
| 1099 | ክሩሴደርስ (መስቀል) ጦረኞች ኢየሩሳሌምን ማረኩ |
| 1187 | የሂትቲን ጦርነት ፡- ሰላዲን ክሩሴደሮችን ድል ነሳ |

| | |
|---|---|
| 1203 | የሚስሊማኑ ጅማሮ በሰሜናዊ ህንድ |
| 1227 (ዓ.ም) | የጋንገስ ካን ሞት |
| 1405 | የታመርለን ሞት |
| 1453 | የኮንስታቲኖፕል ውድቀት |
| 1492 | ሙስሊማኑ ከስፔን ተባረሩ፡፤ |
| 1517 | ካሊፌት በኦቶማን ሱልጣኖች ተወሰደ። |
| 1923 | የካሊፌት መጥፋት። |

# ለ

# የቃላት መፍቻ

**አቡ** (ABU)

በበርካታ የአረብ ወንድ ስም ሲሆን ትርጓሜው "አባት" ማለት ነው። ለምሳሌ ፡- አቡ ዳውድ "የዳውድ አባት" ማለት ነው።

**አድሃን** (ADHAN)

ሙስሊማኑ የአደባባይ (የሕዝብ) ጸሎት ብለው ይጠሩታል።

**አህሉ አል-ኪታበን**

" የመጽሐፉ ሰዎች ፡-" ቁርአን አይሁዳዉያኑን እና ክርስቲያኑን መለኮታዊ መገለጥ ስለ ተቀበሉ የሚጠራበት ስም ነው (ሱረቱ 3፡72፣ 113). በመጀመሪያ ሙሐመድ " አይሁዳውያኑ እና ክርስቲያኑን የሚተናኮል በፍርድ ቀን እኔ ራሴ እከሰዋለሁ" ብሎ ነበር። በመጨረሻ የህይወት ጊዜው ግን አሳቡን በመቀየር " በአረብ ሰላጤ ሁለቱን ኃይማኖቶች አትታገሱ " ሲል ተናግሯል። አቡ በከር ይህን መመሪያ በመጽሐፉ ሰዎች ላይ በአረብ ሰላጤ ተግብሮታል።

**አሕመዲያ** (AHMADIA)

በሚርዚ ጉላም (ካዲያን ፓንጃብ) አህመድ የተመሰረተ ኢስላማዊ ኑፋቄ ነው። በኢስላም አይነተኛው የልዩነት አሳብ ማዕከል (ነጥብ) ነገረ-ክርስቶስ ፣ ማህዲ (መሲህ) እና ጅሃድ (ቅዱስ ጦርነት) ናቸው። አሕመዲያ ኢየሱስ በመስቀል ላይ አልሞተም ነገር ግን ከሞተና ከተነሳ በኃላም ወደ ካሽሚር ሄዶ ወንጌል ሰብኳል ፤ በዚያም 120 ዓመት ኖሯል ይላል። ኑፋቄው ኢየሱስ በሲሪንጋር ስፍራ እንደተቀበረ፣ መቃብሩንም የይዞ አሳፋ ብለው በስህተት እንሚጠሩት ጭምር ይናገራል። ማህዲና ጅሃድን ሲያብራራው የማሃዲ ተልዕኮ ፍቅር ነው፤ ጅሃድ ባላመኑቱ ሰላማዊ በጦርነት ሳይሆን በሰላም ሊፈጸም እንደሚገባ ያበክራል። በሁሉም አግባብ ለመንግስት ታዛኝነት ወሳኝ መሆኑን በማስመር፤ መሲሁ (ማህዲ) የሁለቱም ኢየሱስ እና መሐመድ በስጋ መገለጥ (የክሪሽና መምህር) ሊሆን እንዲገባው ያበክራል።

**አል-ባይዳዊ (AL-BAIDAWI)**

ናስር ኤል-ዲን አብደላህ፣ ሙስሊም ተንተኝ ሲሆን፣ በ1286 አርፏል ፤ መጽሐፉ አኑዋር አል -ታኒዚል ዋኣ አስረር አል- ታዊል (የረዥም ጊዜ ማውረድ እና ሚስጢሮች) ማብራሪያ) ይባላል፡፡

**አል -ጃላላን (Al-JALALAN)**

በጃላል ኤል ዲን ሲዩቲ  እና በጃላል  ኤል ዲን አል ማሃሊ የተጻፈ መጽሐፍ ነው፡፡

**አል-ካልቢ (AL- KALBI)**

ኢብን አል-ሳኢብ የሀዲስ እና ባለ ታሪኮች ተንታኝ ፣ በ763 ዓ.ም ሞተ፡፡

**አል-ራዚ (AL-RAZI)**

ፋኪር አል ዲን ሙስሊም ጸሓፊ ነው፤ መጽሐፉ አል-ታፍሲሩ አል ከቢራ (የታላላቆች ትርጓሜ) ይባላል፡፡

**አል ሱዲ (AL —SUDDI)**

ኢስማኤል ኢብኑ ዐብደል ራህማን ፣ ሀዲስን ከአናስ ኢብን ማሊክ የሰማ እንዲሁም ሁሴን ኢብን አሊ አቡ ጣሊብን ያየ፡፡

**አል- ስዩይቲ (AL-SUYUTI)**

ጃላል ኤል ዲን አብደል ራህማን ፣ሙስሊም የነገረ-መለኮት ሰው እና ተንታኝ( 1445-1505 ዓ.ም)፡፡

**ኤል ተበራ (AL-TABARI)**

አቡ ጋፊር ሙሐመድ ኢቢኑ ጃሪር (በ923 ዓ.ም ሞተ)፣ ሙስሊም ተንታኝ፤ መጽሐፉ ጃሚ አል ቤያን ፊ ታፍሲር አል -ቁርአን  (ጃሚ አል- ቢን በአል -ቁርአን ትርጓሜ) ይባላል፡፡

**አል-ዘማክሕሻሪ (ARABIC)**

አቡ አል-ቃሲም ማህሙድ (1075-1144) ፣ ታዋቂ የሙስሊም ተንታኝ፤ መጽሐፉ አል-ካሽፉ ይባላል፡፡

**አረቢክ (Arabic)**

እንደ ዕብራይስጡ እና ሲራይኩ ከሴሜቲክ   ቋንቋ የመጣ ነው፡፡ የቁርአን እና ሙስሊም ጸሎት ቋንም ነው፡፡

**አሹራ (ASHURA)**

በሺአ ሙስሊሞች በወርኀ ሙሃረም የመጀመሪያ አስር ቀናቶች የሁሴን ከርበላን ሞት ለሚዘክሩ የተሰጠ ስም ነው ።

**አያቶላህ (AYATOLLAH)**

የሺአ ከፍተኛ ሊቅ መጠሪያ ነው።

**ባስማላ**

ቢስምላህ አል-ራህማን አል -ራሂም (በሩህሩህ እና አዛኝረ አላህ ስም)

**ካሊፋ**

ከሙሐመድ ሞት በኃላ ለእስልምና ኃይማኖትና ፖለቲካ መሪዎች የተሰጠ መጠሪያ ነው።

**ደኹ**

እስልምናን ለመቀበል የሚደረግ ጥሪ ነው።

**ኢክሬማ**

ከሙሐመድ ጓደኞች ሻባዎች (ቅርብ ጓደኞች መካከል) አንዱ ሲሆን ፣ በ 634 ዓ.ም ህይወቱ አልፋለች።

**ፉቲሃ**

በቁርአን የመጀመሪያው ሱረቱ ነው።

**ሀዲስ**

ሙሐመድ የተናገራቸው፣ ያደረጋቸው፣ የፈቀዳቸውና ያዘዛቸው ታሪኮች ጥቅል ነው። የተወሰኑት የሀዲስ ክፍሎች ብቻ ስልጣን አላቸው፤ ሆኖም ስልጣኑን አስመልክቶ በሺአ እና ሱኒ ሙስሊሞች መካካል ልዩነት አለ። ሀዲስ ከቁርአን ቀጥሎ ሁለተኛው የእስልምና ህግ፣ ህይወት ፣ የሥነ-ምግባር መመሪያ መጽሐፍ ነው።

**ሂጅራ**

ሙሐመድ እና ተከታዮቹ ከመካ ወደ መዲና የሄዱበት ጉዞ (ፍልሰት) መጠሪያ እና የሙስሊም ዘመን አቆጣጠር አንደኛ ዓመት የጀመረበት ነው (የሙስሊም ዘመን አቆጣጠር የጀመረው በ622 ዓ.ም ነው)።

**ኢብኑ**

ወንድ ሙስሊም "ወንድ ልጅ" ተብሎ የሚጠራበት ነው፡፡ ለምሳሌ፡- ኢብኑ አባሰ "የአባስ ልጅ" ይባላል፡፡

‹

**ኢብኑ አባስ**

የመሐመድን አክስት ልጅ ሲሆን፣ አብዛኛውን የመሐመድን ሀዲስ ተርኳል፡፡ የመጽሐፉ ስም "ታኒዊሩ አል- መኪቢሰን" (ሶኬቱን ያብሩ) ይባላል፡፡

**ኤክዋን አል-ሳፋ**

ቃሉ "የባህሪይ ወንድሞች" የሚል ቀጥተኛ ትርጉም አለው፤ በባስራ ኢራቅ የተቋቋመው ይህ ሚስጢራዊ የአረብ ቡድን የፍልስፍና እና ሀይማኖታዊ አውደ ጥበብ የሆነውን " ራሳ ይል ኢክዋን አል ሳፋ ዋ ካሂላን አል-ዋፋ" (የባህሪይ ወንድሞችና ታማኝ ጓደኞች መልዕክት) በአስረኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ፈጥረዋል፡፡

**ኢማም**

በእስልምና የሀይማኖት መሪ ወይም ቅዱስ ነው፤ በመስጊድ የሚሰጡ አገልግሎቶችን የሚመራ መሪ ጭምር ነው፡፡

**ኢንጅል**

ለ "ወንጌል" የተሰጠ አረብኛ ቃል ነው፡፡ ቁርአን መላውን አዲስ ኪዳን ኢንጅል ብሎ ይጠራዋል፡፡

**እስልምና**

በሙሐመድ የተመሰረተ ኃይማኖት ነው ፤ ቃሉ "መማረክ" ወይም "መሰጠት" ወይም "መገዛት" ከሚለው የመጣ ነው፡፡

**ኢሲያ'ዛ**

ቃሉ " መጠጊያ መፈለግ"ን ያመለክታል ፡- " አወዝ ቢላህ ሚን አልሸይጣን አልረሽም " (ከተረገመ ሰይጣን እግዚአብሔርን እፈልጋለሁ)፡፡ ኢስያ'ዛ አማኙ ከሰይጣን ራሱን የሚጠብቅበት እና የሚቀድስበት የሙስሊም ቀመር ነው፡፡

**ጂን**

መልአክ መሰል ከሰው በላይ የኾኑ ፍጥረታት ናቸው (ነጠላ ቁጥር ፡- ጂንኒ (Jinni) ፣ ኢንግሊዘኛው ጂኒ (genie) ይለዋል፡፡ ከእሳት የተፈጠሩት ጂን የሙሐመድን ስብከት ሰምተዋል፡፡ አንዳንዶች ስብከቱን በመቀበል ሙስሊም ሆኗል፤ ሌሎቹ ግን በማመጻቸው ወደ ገሃነም እንደተጣሉ ይነገራል፡፡ በጂን ማመን በእስልምና የተለመደ ነው፤ ከጥንት ዘመን ጀምሮ በአንዳንድ ቡድኖች ተቀባይነቱ እንደቀጠለ አለ፡፡

**ካእባአ**

ቀጥጠኛ ትርጉሙ " ካሬ " ወይም "ኪዩብ" ማለት ነው፡፡ በመካ የሚገኝ ትንሽ ግንብ ሲሆን "የአላህ ቤት ወይም የፈጣሪ ቤት" የሚል ስም ተሸክሞ በታለቁ መስጊድ ዋና አዳባባይ የሚገኝ ታዋቂ ጥቁር ድንጋይ ነው፡፡ ከአብ የሐጅ ፣ አምልኮ እና ሁሉም ሙስሊማኑ ጸሎት የሚያደርጉበት ማዕከል ነው፡፡

**ሙአዳን**

ሙአዳን አድሃን (ለጸሎት ጥሪ የሚቀርብበት ) ማሰማት ነው፤ ከመስጊድ ማማ በቀን ውስጥ ለአምስት ጊዜ ለጸሎት ጥሪ የሚቀርብበት፡፡

**ቁርአን**

የእስልምና ቅዱስ መጽሐፍ፡፡ ሙሉው ቁርአን የአዲስ ኪዳን ሁለት ሶስተኛውን ያክላል፡፡

**ራእይና**

በአረብኛው "እኛን ስማ" ማለት ነው፤ በአይሁዳውያኑ ለሙሐመድ የተነገረ ነው፡፡ በተለምዶ አነጋገር "ሰማን አልታዘዝንም" የሚለውን ያመላክታል፡፡

**ሻሪያ**

በቁረአን እና ሀዲስ ላይ የተመሰረተ ኃይማኖታዊ ህግ ነው፡፡

**ሺአ**

በአሊ ( አራተኛው ካሊፌት፣ የመሐመድ ልጅ ፋጢማ ባለቤት) ተከታይ የተመሰረተ የእስልምና እምነት ክፍል ነው፡፡

**ሱፊ**

የእስልምና ሚስጥራዊነት የሚወክል ቃል ነው፡፡ ብዙኃኑ የእስልምና ሊቃውንትና ደራሲያን የኃይማኖት ሚስጥራዊ ሥነ-ፍታቴን አበርክተዋል፡፡

**ሱኒ**

የእስልምና ቀትተኛ የእምነት አስተሳሰብ ክፍል ነው፤ በአረብ ፣ ሜድትራያን ሃገራት፣ ህንድ እና ምስራቅ ክፍሎች በአብላጫው ይዟል፡፡

**ሱራ (ሱረቱ)**

የቁርአን ምዕራፎች መጠሪያ ነው፡፡

**ቶራህ**

የመጽሐፍ ቅዱስ የመጀመሪያዎቹ አምስት መጻሕፍት መጠሪያ ነው፤ ቁርአን የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን በሙሉ ቶራህ ብሎ ይጠራዋል፡፡

**ዋሂብ ኢቡን ሙናቢህ**

የጥንታዊያንና ነብያት ጥልቅ እውቀት ያለው የታሪክ ምሁር (በ732 ዓ.ም ሞቷል) ነው፡፡

ሐ

# የእስላማዊ ሐተታ እና ሀዲስ መጻሕፍት


አብዱ ዳውድ፣ ሱለይማን ኢብኑ አል-አሻክቲ፣ ሀዲስ (ካይሮ፣ቀን አልተጠቀሰም)።

አል-ባይዳዊ፣ናስር ኢል-ደን፣ አብደላ፣አኑዋር አል-ታንዚል (ካይሮ፡- ቀ.አ)።

አል-ቡካሪ፣ ሙሐመድ ኢብኑ ኢስማኤል፣ ሳሂህ (ካይሮ፡-ቀ.አ)።

አል-ገዛሊ፣ አቡ ሀሚድ፣ ኢህያ፣ ኡሉም አል-ደን (ካይሮ፡- ቀ.አ))።

አል-ሂኒዲ፣ አላ አል-ደን፣ ሙተቂ፣ ካንዙል ኡማል (ሃይደራባድ፡- 1974)።

አል-ጃላል ("ሁለቱ ጃላስ :- ጃለሉዲን አል- መሀልሊ እና ጃለሉዲን አል-ሱዩቲ") ታፍሲር አል ጃላል (ካይሮ፣ቀ.አ)።

አል-ኩርታብ፣ አቡ አብደላ ኢቡን አህመድ አል-አንሷሪ፣ አል- ጄሚ ለካላም አል-ቁርአን (ካይሮ፡- ቀ.አ)።

አል-ራዚ፣ ፋኪር አል-ደን፣ ማፋቲህ፣ አል-ጋሂብ (ካይሮ፡-1932)።

አል- ሰዌይቲ፣ ጃለሉዲን ፣አሻብ አል- ኑዙል (ካይሮ፡- ቀ.አ)።

አል-ተበራ፣ አቡ ጃፋር ሙሐመድ፣ ኢብኑ ጃሪር ፣ ጄሚ አል- ባይን (ካይሮ፡- 1968)።

አል-ታላቢ፣ አቡ አይሻቅ አህመድ፣ የአራይ፣ አል-ማጋሊስ (ካይሮ፡- ቀ.አ)።

አል- ታሪሚድ፣ አቡ፣ አብደላህ፣ ኢቡን ሙሐመድ፣ሱናን (ካይሮ፣-1934)።

አል- ዛማኽሻሪ፣ አቡ አል-ቃሰም፣ማህሙድ፣ አል-ካሽፍ (ካይሮ.ቀ.አ)።

ኢቡኑ አባስ፣ ታንዊር፣ አል-መክቢስ (ካይሮ፣ ቀ.አ)።

ኢቡን ሀኒባል፣ አህመድ፣ ሙስናድ (ካይሮ፣ ቀ.አ)።

ኢብኑ ሂሻም፣ የመሐመድ ህይወት (ቪ.ሊች፡- የህይወት ብርሀን ፣1997)።

ኢብኑ ኻቲር፣ እስማኤል፣ ታፍሲር አል- ቁራኣን አል -አዚም (ካይሮ፡- ቀ.አ)።

ኢብኑ ኻቲር እስማኤል፣ አል-ቢዳያ ዋል-ኒሃያ፣ ዳር አል-ሻብ (ካይሮ፣ ቀ.አ)፡፡

ኢብኑ ሳዲ ተባኻት (ካይሮ፣ ቀ.አ)፡፡

ሙስሊም፣ ኢብኑ አል-ሃጃጅ፣ ሳሂ (ካይሮ፣1956)፡፡

መ

# ዋቢ መጻሕፍት

አቡዱ-አልመሲህ፣አላህ በእስልምና ማነው? (ቪላክ፣ ኦስትሪያ፡- የህይወት ብርሃን፣ ቀን አልተጠቀሰም)።

አቡዱ-አል መሲህ፣ እስልምና በማጉያ መነጽር (ቪላክ፣ ኦስትሪያ፡- የህይወት ብርሃን፣ ቀ.አ)።

አብዱል-ሀቅ፣ አብዲያሽ አክበር፣ እምነትህን ከሙስሊም ጋር መካፈል (ሚናፖሊስ፡- ቤታ ሕብረት፣1980)።

አካድ ፉአድ ኤሊያስ፣ ድልድይን መገንባት፣ ክርስትና እና እስልምና (ኮሎራዶ ስፕሪንግስ፡- ኔቭፕረስ፣1997)።

አል-ጣባራኒ፣ኢብራሂም፣ ነገረ-መለኮታዊ ክርክር (ቪሊች፣ የህይወት ብርሃን፣ቀ.አ)።

አምብሪ፣ሀምራን፣ እግዚአብሔር የዘላላም ህይወት መርጦልኛል (ሪኮን፡- መልካሙ መንገድ ፣ ቀ.አ)።

አትናሲየስ፣ ቅዱስ፣ የእግዚአብሔር ቃል ትስጉት (ካይሮ፡- ማክተኣብ አል- ማሃብ፣ ቀ.አ)።

ኤፍ ኤፍ ብሩስ፣ የአዲስ ኪዳን ሰነድ (ካምብሪጅ፣ ቲንዳል ፣ 1960)።

ካረሊሌ፣ ቶማስ፣ የቶማስ ካርሊሌ ምርጥ ስራዎች (ኒው ዮርክ፡- የአሜሪካ መጽሐፍ ሊግ)።

ቻፕ ማን፣ ኮሊን፣ መስቀል እና ግማደ- ጨረቃ፡- ለእስልምና ተግዳሮቶች ምላሽ (ሌችርሰተር፡- አይ ቪ ፒ፣1993)።

ኩፐር አኒ ፣ እስማኤል ወንድሜ (ማርክ፣ 1993)።

ክራግ፣ ኬነዝ፣ የእስልምና ቤት (ቤልሞንት፡- ዋድስዎርዝ ማተሚያ ካምፓኒ፣ 1975)።

ክራግ፣ ኬነዝ፣ ዓረብ ክርስቲያኑ በመካከለኛ ምስራቅ (ለንደን፡- ሞው ብሬይ፣1991)።

ክራግ፣ኬነዝ፣ የምናሬት ጥሪ (ለንደን ፡- ኮሊንስ ፣1986)።

ክራግ፣ ኬነዝ፣ መሐመድ እና ክርስቲያን (ለንደን፡- ዳርቶን ፣ ሎንግ ማን እና ቶድ፣ 1984)፡፡

ዳገር፣ ሃምዳን፣ ሴቶች በእስልምና (ቪሊንች ፡- የህይወት ብራሃን ፣1995)፡፡

ጌይስለር፣ ኖርማን ሊ. እና አብዱል ሣሌብ፣ ለእስልምና ምላሽ (ግራንድ ራፒድስ ፡- ቤከር መጻሕፍት፣ 1998) ፡፡

ጉሆሮባል፣ መሐመድ፣ አል -ማውሱኣ አል- አረቢያ አለ-ሙያሳራ (ካይሮ፡- 1986)፡፡

ጊብ፣ ኤች .ኤ. አር. እና ክሬመርስ፣ ጄ.ኤች፣ የእስልምና አጭር ኢንሳይክሎፒዲያ (ሌይደን ፡ ኢ.ጄ፣ ብሪል፣1974)፡፡

ግሊክራይሥት፣ ጆን፣ መሐመድ እና የእስልምና ሀይማኖት፣ (ቤኖኒ፣ ኤስ ኤ፣ ኢየሱስ ለእስልምና ፣1986፡፡

ጉልኤም ኤ፣ የእስልምና ልማድ፣ (ኦክስፎርድ ዩኒቨርስቲ ማተሚያ፣ 1924፡፡

ሀይካል መሐመድ ሁሴን፣ ሃያት መሐመድ፣ (ካይሮ፣ ዳር አልማሪፍ)፡፡

ሄበርማስ፣ ጌሪ፣ አር. የእስልምና ፍርድ (ናሽቪሌ፡- ቶማስ ኔልሰን፣1982)፡፡

ኢብኑ ሂሻም፣ የመሐመድ ህይወት፣ (አብዱል አል- ማሽ ያሳደገው ጽሑፍ) (ቪልች፡- የህይወት ብርሃን)፣1997፡፡

ኢክ ዋን አል-ሰፋ፣ ራስል ኢክዋን  አስ -ሰፋ ዋ ኪ ህላን አል-ዋፋ (የንጹሃን እና ታማኝ ወንድሞች መልዕክት) (ካይሮ፣ቀ.አ)፡፡

ኪንዳል፣ አር፣ ቲ፣ ነገረ-መለኮትን መረዳት (ለንደን ፣ክርስቲያነዊ ትኩረት፣1999)፡፡

ሊዊስ ሲ . ኤስ፣ ክርስትና (ግላስጎው፡- ፎነታና መጽሐፍት ፣1975)፡፡

ሞሻይ ፣ ጂ . ጄይ፣ ኦ. አላህ  ማነው ? (ጌራርድስ ክሮስ ባክስ ፡- ዶርቸሀስተር ሃውስ ፣1994)፡፡

ሙየር ዊሊያም፣ ማህሞት እና  እስልምና (ለንደን፡- ሀይማኖታዊ ጽሑፍ ማህበር፣ ቀ.አ)፡፡

መሰክ ፣ ቢል.ኤ፣ ቀናዒ እምነት (ኬንት፣ ሞናርክ ህትመት፣ 1992)፡፡

መስክ ቢል .ኤ. ያልታየው የሙስሊም ገጽ (ማርክ 1994)።

ኑርባካሽ ጃውድ፣ ኢየሱስ በሱፊዎች አይን (ካኒቃህ ንማቱላህ ፣ ህትመት፣ ለንደን፣ 1983)።

ኩይራዋኒ ፋሪስ፣ ክርስቶስ ተሰቅሏልን? (ቪሊች፣ የህይወት ብርሃን፣ 1994)።

ሳማን አዋድ፣ ካዲያቱል ጎርፍራራን፣ ፊል-ማሺያ (ካይሮ፣ የግል-ህትመት፣1951)።

ሱቢህ መሐመድ፣ መሐመድ (ካይሮ፡- ዳር አል-ታክፋ አል-አማ፣ 1957)።

ታብራራ፣ አፊፍ፣ ሩሁ አል- ዲን አል -እስልምና (ደማስከስ፡- 1972)።

ታጎር ራቢንድራነስ፣ የግጥም ስብስብ (ኒው ዮርክ፡ ማክ ሚላን ፣1937)።

ዕውነተኛው መመሪያ ፣ ክፍል 1-5 (ቪልች፣ ኦስትሪያ፡- የህይወት ብርሃን፣1992)።

ቶማስ ሪቻርድ ደብሊው ፣ እስልምና- ገጽታዎቹ እና ተስፋዎቹ (ቪሊች ፡- የህይወት ብርሃን፣ ቅ.አ)።

ቶር፣ አንደሬ፣ መሐመድ፡- ማንነቱ እና ዕምነቱ (ኒው ዮርክ ፡- ሀርበር እና ሮ፣1960)።

ቲስዳል ደብሊው፣ ቅዱስ ክሌ፡- የመሐመዳዊያን ክርስትና ሙግት መመሪያ (ለንደን ፡- ኤስ፣ ፒ፣ ሲ. ኬ፣1904)።

ቲሪተን ኤ. ኤስ፣ ካሊፎች እን ሙስሊም ያልሆኑ ሰዎች ርዕሶች (ለንደን፡- ፍራንክ ካስ እና ኮው፣ 1970)።

የሱፍ፣ ሚካኤል፣ ሙግተ- ዘመናዊነት (ለይደን ፡- ኢ፣ ጂ፣ ብሪል ፣1985)።

የሱፍ፣ ሚካኤል፣ አሜሪካ፣ ኦይል እና እስላማዊ አእምሮ (ግራንድ ራፒድስ፡- ዞንደርቫን፣1991)።